# ከ
# አምባገነንነት
# ወደ
# ምርታማነት

የመዋቅራዊ ሽግግር ፍኖተ-ካርታ



# ከአምባገነንነት ወደ አምራችነት

## የመዋቅራዊ ሽግግር ፍኖተ-ካርታ

---

# FROM POWER TO PRODUCTIVITY

## A THEORY OF TRANSFORMATION


ማቲያስ ገሠሠ



ሚያዚያ 7, 2018

“ኃብት የዕውቀት መዝገብ የእሚጥለው ጥላ ነው።”

"Wealth is merely the shadow cast by the light of accumulated knowledge."

የ2ሺ ዓመት ዕድሜ ባለጸጋ ከሆነው የኢኮኖሚ “አማካሪ” አባባል የተወሰደ

## ማውጫ


1 መነሻ ........ 1

2 አመክንዮው ........ 5

2.1 የግል ንብረት ባለቤትነት ........ 9

2.1.1 አሠራር ........ 9

2.1.2 ታሪካዊ ማሳያዎች ( የስኬት ታሪኮች) ........ 11

2.1.3 ዓይነተኛ የክስረት ታሪክ : አርጀንቲና ........ 14

2.1.4 ድምዳሜ ........ 17

2.2 የንብረት ተንቀሳቃሽነት ........ 17

2.2.1 አሠራር ........ 17

2.2.2 ታሪካዊ ማሳያዎች (የስኬት ታሪክ) ........ 18

2.2.3 ዓይነተኛ የክስረት ታሪኮች : ኢትዮጵያ እና ሕንድ ........ 20

2.2.4 ድምዳሜ ........ 23

2.3 የሕጉ ነጻ እና ገለልተኛነት ........ 23

2.3.1 አሠራራ ........ 23

2.3.2 ታሪካዊ ማሳያዎች (የስኬት ታሪኮች) ........ 25

2.3.3 ዓይነተኛ የክስረት ታሪክ: ፍሊፕንስ ........ 29

2.3.4 መደምደሚያ ........ 30

2.4 ለልውውጥ እና ውድድር አመቺ የሆነ የንግድ ክፍትነት ........ 31

2.4.1 አሠራር ........ 31

2.4.2 ታሪካዊ ማሳያዎች (የስኬት ታሪክ) ........ 34

2.4.3 ዓይነተኛ የክስረት ታሪክ: ሕንድ ........ 45

2.4.4 መደምደሚያ ........ 46

2.5 የበጀት አስተዳዳር ጥበብ (Fiscal Discipline) ........ 47

2.5.1 አሠራር ........ 47

2.5.2 ታሪካዊ ማሳያዎች (የስኬት እና የክስረት ታሪክ) ........ 49

2.5.3 ዓይነተኛ የክስረት ታሪኮች : ቻይና እና ጀርመኒ ........ 49

2.5.4 ድምዳሜ ........ 51
2.6 ዋናው ነገር ........ 52
3 መመርመሪያው ማሽን ........ 55
4 ማሳያ ሙከራዎች - የተመረጡ አስራ አንድ ሐገራት ኢከነሚ ምርመራ ........ 85
4.1 አሜሪካ ........ 85
4.2 ብራዝል ........ 100
4.3 ቺሊ ........ 113
4.4 ፖላንድ ........ 130
4.5 ፈረንሳይ ........ 143
4.6 ኳታር ........ 160
4.7 ሲንጋፖር ........ 171
4.8 ቪየትናም ........ 185
4.9 ናይጄሪያ ........ 199
4.10 ደቡብ አፍሪካ ........ 212
4.11 ቻይና ........ 224
5 ከታሪክ ስንማር ........ 243
6 የግንዛቤ እጥረት እና የጥቅም እሳቤ ለለውጥ የፈጠሩት ፈተና (Cognitive and Incentive Resistance to Reform) ........ 250
7 የተቋማዊ ሽግግር ጎዳና (Pathways of Institutional Transition) ........ 258
8 ዘመነ ሰውሠራሽ ብልኃት እና የዕውቀት ክፍተትን ለመሙላት ያለው ሚና (The Age of AI and its relevance in narrowing the knowledge gap) ........ 265

# 1 መነሻ

በተፈጥሮ ኹኔታ ይኹን በሰው ማሕበረሰብ ውስጥ መኖር እና ስኬት የኃይል ውጤት ተደርጎ ይታያል። ጉዳዩ በጥንቃቄ ሲመረመር ግን ኑሮ እና ስኬት የኃይል ሳይሆን የዕውቀት ጉዳይ ሆኖ ነው የእሚገኘው።

ባለ ኃይሎች ሳይሆኑ አዋቂዎቹ ናቸው የእሚኖሩት እና የእሚሳካላቸው።

ዝሆንን ተመልከቱት። ከውጭ ሲታይ ግንድ የእሚገነድስበት አካላዊ ግዝፈቱ እና ጉልበቱ ይመስላል በዱር ውስጥ የእሚያኖረው። ተግባራዊው ዕውነታው ግን ከእዚያ የተለየ ነው ፤ ዝሆንን በሕይወት የእሚያቆየው ወደ ስድስት ሺ ኪሎግራም የእሚጠጋው ግዝፉ አካሉ የእሚያላብሰው ኃይል ሳይሆን ፦ ዕውቀት የመሰብሰብ ፣ የማቆየት እና የማስተላለፍ አቅሙ ነው።

የዝሆን መንጋ እጅግ ቀሳፊ እና አስቸጋሪ በሆነ ዱር ውስጥ ከአስርት አመት በፊት ብቻ የእሚያስታውሰውን የውኃ ቦታ ፈልጎ ማግኘት የእሚችልበት የዕውቀት መዝገብ አለው። መንጋው ይኽን ማድረግ የቻለው ፤ የመንጋው መሪ ከሆነች እንስት ዝሆን የእሚተላለፍለትን ፤ የውኃ መገኛ ካርታ በመጠቀም ነው።

አንድ የዝሆን መንጋ አውራ እናት ስትሞት ፤ አንድ የመንጋው አባል እንደ ጎደለ ያኽል ብቻ አይሆንም ጉዳቱ ፤ ይልቁንም በርካታ የውኃ ጉድጓድ ያሉበትን ቦታ የእሚጠቁመው ካርታ እንደ ጠፋም ያኽል ነው።

በእዚኽ ምክንያት ፤ በተለይ ድርቅ በእሚሆንበት እና ውኃ በቅርብ በእማይገኝበት ግዜ ፤ የመንጋው አውራ እናት ካርታውን ሳታስተላልፍ ከሞተች ፤ መንጋው የመጥፋት እድሉ በጣም ይጨምራል ።

በዝሆን መንጋ ውስጥ ፤ ይኽን መሰሉ ለመኖር በመንጋው የዕውቀት መዝገብ ላይ የመደገፉ ነገር በውኃ ብቻ የተወሰነም አይደለም ፦ የምግብ ክምችት ያለበትን ለማወቅ ፣ ረጅም የጉዞ መንገዶችን ለማወቅ ፣ መድህኒት የሆኑ ዕፀዋትን ለማወቅ ፣ የመንጋ ትብብር ለማድረግም ፤ የዝሆን መንጋዎች የእሚጠቀሙበት ነው።

እነ እዚኽም ዕውቀቶች ደመነፍሳዊ (Instinctive) አይደሉም ፤ ነገር ግን በመማር የእሚገኙ ፣ የእሚታወሱ እና ከትውልድ ትውልድ የእሚወራረሱ ናቸው።

ስለ እዚኽ ፦ አንድ የዝሆን “ጥጃ” ረዘም ያለ የልጅነት ግዜ የእሚኖረው ፤ በደንብ እንዲቦርቅ እና እንዲጫወት ሳይሆን ፤ ይኽን ዕውቀት ከመንጋው እንዲማር ነው ፤ ያለ እዚያኽ ዕውቀት አካላዊ ግዝፈቱ እና የተላበሰው ጉልበት ምንም አይፈይደውም።

ከእዚኽ አንጻር ከታየ ፤ አንድ የዝሆን መንጋ አንድ ዓይነት የእንስሳት ቡድን ሳይሆን ፤ አንድ ዓይነት የዕውቀት ስረዓት (Knowledge System) ነው ማለት ይቻላል።

የሰው ማሕበረም ፤ በጥልቀቱ እና በውስብስብነቱ ከዝሆን መንጋ(ማሕበር) ይለይ እንጂ ፤ በእዚኽ ለመኖር በዕውቀት ላይ በመደገፉ ጉዳይ ፤ በተለይ ደግሞ የማሕበረ ኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ ከሌሎች ነገሮች በላይ በዕውቀት ላይ የእሚደገፍ በመሆን ከዝሆን መንጋው አይለይም።

የዘመናዊ አውሮፓ ማንሰራራት ይኽንን ዕውነታ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።

በአውሮፓ 1500 - 1800 ባለው እና ከእዚያ በፊት በነበረው ግዜ መካከል ህዳሴውን የእሚጋብዝ የውጫዊ/የቁሳዊ ኹኔታ ለውጥ አልነበረም። ከ1500 በኋላ በአውሮፓ መሬቱ ድንገት ለም ሆኖ ብዙ ምርት ማምረት አልጀምረም እንዲያውም ከ1300–1850 ከፍተኛ ቅዝቃዜ ኖሮ ፤ የግብርና ግዜን በማሳጠር ርኃብ የፈጠረበት ኹኔታ ነው የነበረው። ወይንም ከ1500 በኋላ በአውሮፓ ተዝቆ የእማያልቅ የወርቅ ወይንም የአልማዝ መዓድን አልተገኘም።

ከሞላ ጎደል ከህዳሴው በፊት እና በኋላ ፤ ከቁሳዊ ወይንም ከውጫዊ ኹኔታ አንጻር አውሮፓ ተመሳሳይ ነበረች።

አንድ የተለወጠ ነገር ቢኖር ፤ ከአውሮፓ ማንሰራራት(ህዳሴ) በፊት ምድራዊ ዕውቀት (Secular Knowledge) በእሚል ተጥለው የነበሩትን የጥንት የግሪክ እና የሮም መጽሐፍትን በሕዳሴው (Renaissance) ዘመን እንደ ገና በማጥናት ፤ የአዕምሮን የማሰብ እና መፍትኼ የማፈላለግ ጉልበት በመጠቀም፦ የግል ፣ የጤና ፣ ማሕበራዊ እና የንግድ ችግሮችን መፍታት ይችላል በእሚል የዕውቀት አብዮት (The Scientific Revolution 1543–1687) መጀመሩ ነበር።

ይኽም የዕውቀት አብዮት (The Scientific Revolution 1543–1687) በባዮሎጂ ፣ በፊዚክስ ፣ በማቲማቲክስ ፣ ወዘተ ብቻ የተወሰነ አልነበረም ፤ ይልቁንም ከፍተኛ ፋይዳ የነበራቸውን የማሕበረ ኢኮኖሚ (Political Economy)ተቋማትን አወቃቀር ዕውቀቶችንም ያካተተ ነበር።

ይኽም የዕውቀት አብዮት ነበር ፤ አውሮፓውን ህዳሴው ውስጥ በማስገባት ፤ የዘመናዊው ስልጣን ፈር ቀዳጅ እና ልዕለ ኃያል ያደረጋት።

ከእዚኽ የዕውቀት አብዮት ፍሬዎች ውስጥ ወሳኙን ድርሻ የተጫወተው ደግሞ ፤ በባዮሎጂ ፣ በፊዚክስ ፣ በማቲማቲክስ ፣ ወዘተ መስክ የተገኘው አዲስ ዕውቀት ሳይሆን የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማትን ከማዋቀር አንጻር የተገኘው እና አሸንፎ የወጣው አዲስ ዕውቀት ነበር። እርሱ ነበርና የባዮሎጂውን ወይንም የፊዚክሱን ርቀት የእሚወስነው።

አሁንም በእኛ ዘመን ፡- ኋላ በቀሩ ፣ በማደግ ላይ ባሉ እና ባደጉ ሐገራት መካከል ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ደረጃ ልዩነት ፤ ባላቸው የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማትን ማወቀሪያ ዕውቀት የዕድገት ደረጃ ልዩነት የእሚገለጽ ነው ።

እነ እዚኽ፡- በሐገራት መካከል የኢኮኖሚ ልማት ደረጃን ልዩነትን ያስከተሉ እና በግዜ ኺደት የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ሊያካትቷቸው የእሚገቡ መርኾች ምንድ ናቸው ካልን ፤ የእሚከተሉት ናቸው፡-

1. **የግል ንብረት ባለቤትነት መብትን ማክበር ፣**
2. **የግል ንብረትን የማንቀሳቀስ መብትን ማክበር ፣**
3. **በሕግ ፊት ኹሉም ዕኩል እንዲሆኑ የማድረግ ፣**
4. **የንግድ ክፍትነት እና**
5. **የበጀት አስተዳደር ጥበብ መያዝ**

ናቸው።

አንድ ሐገር - ከርዕዮት ዓለም ዕሳቤ አንጻር ፡- አምባገነናዊ ፣ ዴሞክራሲያዊ ወይንም ሌላ ስረዓት ሊኖረው ይችላል ፤ ያ ሐገር የያዘውን ርዕዮት ይዞ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማቱ እነ እዚኽን መርኾች እንዲያከብሩ አድርጎ ከገነባቸው ፤ ያን የእሚያደርግበት ዕውቀት ከጨበጠ ፤ ያ ሐገር ፤ ቀጣይነት ያለው መዋቅራዊ ሽግግርን በማድረግ የዜጎቹን የሕይወት ደረጃ የእሚያሻሽል ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ይኖረዋል። በአንጻሩ ችላ ካላቸው ችላ ባለበት ልክ ፤ ከኢኮኖሚያዊ ዕድገት አንጻር ቆሞ ቀር እና የብዝበዛ ሐገር ይሆናል።

የአንድ ሐገር የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት እነ እዚኽን **ኹኔታዎች** ሲያከብሩ ፡- ገበሬው ንብረቱ ድንገት ይወረስብኛል ብሎ ሳይሰጋ ምርቱን ለማሳደግ ኃብቱን ሳይሳሳ በሥራ ላይ ያውላል ፣ ነጋዴው የተዋዋለውን ውል ፍርድ ቤት እንደ እሚያስከብርለት አውቆ ውል እና ሽርክና ውስጥ ይገባል ፣ የሐገሪቱ መንግሥትም ከግብር የእሚሰበስበውን ገንዘብ በአግባቡ አዋጭ የልማት ሥራዎች ላይ በጥንቃቄ በማዋል ሐገሪቱን ከዋጋ ግሽበት ፣ ከከፍተኛ የወለድ መጠን ፣ ወዘተ በመጠበቅ ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት የተመቻቸ የማክሮኢኮኖሚ (Macroeconomy) ድባብ ይፈጥራል ፤ ተወዳጅ ለመሆን ከማደፋፋት ወይንም ያለ አቅሙ የተበደረውን ብድር በመክፈል የሐገርን ኃብት ከማባከን ይልቅ።

ስለ እዚኽ ፡- ዘመናዊ የኢከነሚ ዕድገት በዋናነት ውስብስብ ማሽኖችን የማንጋጋት ፣ ትልቅ የተፈጥሮ ኃብት የማግኘት ወይንም የተጠራቀመ የገንዘብ ኃብት ጉዳይ በፍጹም አይደለም።

ይልቁንም ሐገራት እነ እዚኽን አምስት **ኹኔታዎች** ፋይዳቸውን አውቀው እና ተረድተው በቀጣይነት እና በቋሚነት ከማሕበራዊ ኢኮኖሚያዊ ተቋሞቻቸው ጋር የማስተሳሠራቸው ጉዳይ ነው።

በአንድ ሐገር እነእዚኽን አምስት ኹኔታዎች የእሚያከበር የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋም በእሚኖረት ግዜ ፤ ምርት የማምረት ኺደት ለግዜያዊ ፍጆታ ከመሆን የማምረት ልህቀትን ወደ ማስመዝገብ ፣ ከማምረት ልህቀት ወደ ኢንደስትሪ ግንባታ ፣ ከኢንደስትሪ ግንባታ ወደ ቀጣይነት ያለው የፈጠራ ዑደት ይሸጋገራል።


በአንጻሩ እነ እዚኽን ኹኔታዎች የእማያሟላ ስረዓት በእሚገነባበት ግዜ ፤ ድካም እና ጥረት ከንቱ ይሆናል ፣ ትርፍ ተጠራቅሞ ኃብት ከመሆን ይልቅ ለዕለት ጉርስ ይውላል ፣ እናም መጪው ትውልድ ቀዳሚው ትውልድ በገነባው ላይ ከመቀጠል ይልቅ ፤ ያለፈውን ትውልድ ዕውቀት እና ግኝት ሳይጠቀምበት ፤ እንደ አዲስ ጀማሪ ይሆናል።

የሐገራት ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ደረጃ ፤ እነ እዚኽን አምስት ኹኔታዎች ፡- በግል ንብረት ፣ በንብረት ማንቀሳቀስ ፣ በሕግ እኩልነት ፣ በንግድ ክፍትነት እና በበጀት ተገቢ አስተዳደር ፤ ላይ ካላቸው የግንዛቤ እና ግንዛቤውን በተግባር ከመተርጎም ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ሆኖ ነው የእሚታየው ፤ ሲጨምር እየጨመረ፣ ሲቀንስ እየቀነሰ።

በመሆኑም ፡- ልክ የዝሆን መንጋው ህልውና ግዙፍ አካሉ ካላበሰው ትልቅ ጉልበት ይልቅ ፤ ዕወቀትን በማግኘት ፣ በመጠበቅ እና በማስተላለፍ አቅሙ ላይ እንደ ሆነው ኹሉ ፤ የሐገራትም የኢኮኖሚ ልማት ደረጃቸው ፤ በእዚያች ሐገር የተፈጥሮ ኃብት ፣ በሕዝብ ብዛት ፣ በመንግሥታቸው ወታደራዊ ጥንካሬ ፣ ወዘተ ላይ ሳይሆን እነ እዚኽ አምስት ኹኔታዎች ያላቸውን ፋይዳ አውቀው የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋሟቾቻቸውን ኹኔታዎችን በእሚያስችል መልኩ በማዋቀራቸው ላይ ይወሰናል።

# 2 አመክንዮው

መሠረታዊ በእሚባል ደረጃ እናስቀምጠው ካልን ፤ መዋቅራዊ ለውጥ የእሚያመጣ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ቅብብሎሽ ነው ፦ የምርት ዕድገት ትርፍ ኃብት ያመነጫል ፣ ያ ትርፍ ኃብት የማስፋፊያ ገንዘብ ምንጭ ይሆናል ፣ ያ ገንዘብ በዘመን ኢንቨስት ይደረጋል ፣ ኺደቱ ሲቆይ እና የፋይናንስ ስረዓቱ ሲያድግ በከፍተኛ ደረጃ የምርት ዕድገትን የእሚያስከትል ኢንቨስትመንት ለማድረግ የእሚያግዝ የፋይናንሻል ስረዓት ይመሠረታል ፣ በእዚኽ መልኩ እየተዋለደ እና እየባዛ የእሚኼደው ትርፍ ኃብት ውስብስብ እና ከፍተኛ ምርትን ያስከትላል።




ይኽም የኃብት ቅብብሎሽ እና ማስፋፋት ከትውልድ ትውልድ ሲሸጋገር ፤ ወዋቅራዊ ሽግግር ይከተላል።

ይኽም ቅብብሎሽ እና ማስፋፊያ ቀጣይነት እንዲኖረው ፤ ከእዚኽ በታች ከተዘረዘሩት አምስት ተቋማዊ አሠራሮች የግድ አስፈላጊ ናቸው።

መጀመሪያ ፡- አምራቾች የጥረታቸው ውጤት የሆነን ትርፍ በባለቤትነት መያዝ መቻል አለባቸው። አምራቾች የንብረት ባለቤትነት ስጋት በእሚኖርባቸው ግዜ ፡- ረጅም ምርት የማሳደግ ዕቅድ ከማቀድ ይቆጠባሉ ፣ ኃብት ለማከማቸት መነሳሳት ያጥራቸዋል ፣ ምርት በዋናነት ወቅታዊ ፍጆታን ብቻ ታሳቢ ያደረገ ይሆናል። የንበት መብት በእማይከበርበት ኹኔታ የማምረት ኺደት የውደቱ አስጀማሪ የሆነውን ትርፍ ምርት በበቂ ኹኔታ እሚያመርት አይሆንም።

ኹለተኛ ፡- ምርታማ ንብረቶች ፡- በሽያጭ ከአንድ ባለንብረት ወደ ሌላ በመተላለፍ ፣ ምርታማነትን በእሚያሳድግ መንገድ በአንድ ባለቤትነትን ስር በመሰባሰብ (consolidation) እንዲኹም ለብድር በማስያዣነት መቅረብ በመቻል ፤ የንብረት ተንቀሳቃሽነታቸው (Asset Mobility) ከፍ ብሎ ፤ በኢኮኖሚ ውስጥ በገበያ ዋጋ መሠረት ወደ ከፍተኛው አምራች መተላለፍ መቻል አለባቸው።

የተረጋጋ የንብረት ባለቤትነት ስረዓት መኖር አንድን ዜጋ መሬትን በባለቤትነት መያዝ እንዲችል ሲያስችለው እና ትርፍ ለማምረት መተማመን ሲፈጥርለት ፤ የንብረት ተንቀሳቃሽነት (Asset Mobility) ፡- የመሸጥ ፣ የማከራየት ፣ አስይዞ የመበደር መብት ፤ ያንን ንብረት ከንብረትነት ወደ ካፒታልነት መለወጥ እንዲችል ያስችልዋል።

በአንድ ኢከነሚ ውስጥ ፤ ንብረት በነጻ ገበያ እና በውድድር መንቀሳቀስ በእማችይልበት ወቅት ፤ ንብረቱ "ሙት ካፒታል" ነው የእሚሆነው። ቀለብ መስፈር ይችላል ፤ ለማስፋፊያ እና ለእድገት የእሚሆን የካፒታል ምንጭ መሆን ግን አይችልም።

ባለቤትነት የጥረት ዋጋን እና ትርፍ ምርትን ለማስጠበቅ ዋስትናን ሲሰጥ ፣ የንብረት ተንቀሳቃሽነት (Asset Mobility) ኃብት የመፍጠር ፍጥነትን ይጨምራል።

በአንድ ኢከነሚ ውስጥ ንብረት ፡- በቀላሉ በሽያጭ ፣ በብድር ማስያዣነት ወይንም በልዋጭ መንቀሳቀስ በእማይችልበት ግዜ ፤ ያ ንብረት የቁም እስር ውስጥ ይወድቃል። የንብረት ተንቀሳቃሽነት ነው አንድን መሬት ወይንም ሌላ ንብረት ፤ በካርታ ላይ ካለ አንድ ነጥብነት አውጥቶ ፤ የጥልቅ እና ውስብስብ የገንዘብ ስረዓት (Financial System) አካል የእሚያደርገው።

ንብረት መንቀሳቀስ ሲችል ፤ ሰዎችን ያገናኛል ፡- አንድ ገበሬ የመሬቱን ግማሽ ሊሸጥ ይችላል ምርቱን የእሚያሳድግለትን ማሽን ለመግዛት ፣ አንድ ባለሱቅ ሱቁን ማስያዣ አድርጎ ማስፋፊያ ብድር ሊበደር ይችላል ፣ አንድ ቤተሰብ ቤቱን በልዋጭ ወይንም በሽያጭ ሊቀይር ይችላል የተሻለ ዕድል አለ ብሎ ወደ እሚያስበው ቦታ ለመግባት።

በእዚኽን ግዜ ፤ እያንዳንዱ ልውውጥ አንዱን የመሬት ቁራሽ ከሌላው የመሬት ቁራሽ ጋር ያይዘዋል በጠቅላላው በሐገሪቱ ውስጥ የእሚገኙ ንብረቶችን እርስ በእርሳቸው በማስተሳሰር ፡- የብድር ፣ የኢንቨስትመንት እና የሽያጭ መረብ አድርጎ ትልቅ የገንዘብ ስረዓት (Financial System) አድርጎ ይሸምናቸዋል።

አንድ አንድ ግዜ መንግሥታት የንብረት ተንቀሳቃሽነትን (Asset Mobility) ከፍ ካደረግን እና ዜጎች እንደ አሻቸው ንብረታቸው እንዲሸጡ ፣ በብድር እንድያሲዙ ወይንም እንዲለዋወጡ ከፈቀድንላቸው ፤ ለግዜያዊ ገንዘብ ብለው ንብረታቸውን በመሸጥ ፤ በተለይ መሬት እና ቤትን ፤ መሬት እና ቤት አልባ ተንሳፋፊ ይሆናሉ በተጨማሪም የሐገሪቱ ኃብት በሙሉ ተሰብስቦ በጥቂት ባለኃብቶች እጅ ይገባል ብለው ያስባሉ ፤ የእዚኽ ዓይነቱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ውጤቱ ግን ፤ ዝቅተኛ የሕብረተሰብ ክፍልን ከተጋላጭነት መከላከል ሳይሆን ይልቁንም ዜጎቹን ከቆመ ቀር ኢኮኖሚ ጋር ሰፍቶ ማስቀረት ነው።

ንብረት የመዘዋወር እና የመሸጋገር አቅሙ በሕግ ሲገታ ፤ ያ ንብረት ባለበት ያንቀላፋል ፣ ዕድሎች ይባክናሉ ፤ ከእዚኽም የተነሳ ኢከነሚው በልቶ ከማሳደር መሻገር ይሳነዋል።

እውነተኛ ዕድገት ንብረት በቀላሉ ሲንቀሳቀስ ነው የእሚጀምረው ፤ ምክንያቱም ፦ ያን ግዜ ብቻ ነው ፤ የግል ንብረቶች ፤ ከጠቅላላው ሐገራዊ ንብረት ጋር ተያይዘው የትልቁ ሐገራዊ ኃብት የማመንጨት አካል ሆነው ፤ ሐገራዊ ኃብት የማመንጨት አቅምን ሊያሳድጉ የእምችሉት።

በግለሰብ ወይንም በውስን ደረጃ ተገድበው ሲቀሩ የተናጠል ደካማ ጥረት አካል ነው የእሚሆኑት።

ሰስተኛ ፦ የንግድ ልውውጥ ከአድሎ በጸዳ እና የፍርድ ብያኔዎቹ ተገማች በሆነ የሕግ ስረዓት መዳኘት አለበት። የኢከነሚ ሕግ ስረዓቱ ከአድሎ የጸዳ እና ብያኔዎቹ ተገማች በእማይሆንበት ግዜ ፤ የንግድ ስምምነት እና ትብብር ፤ በጣም ጠባብ በሆኑ የትውውቅ መረቦች ብቻ ይወሰንና ፤ ፈጠራን እና ልህቀትን ይገድባል።

አራተኛ ፦ የማምረት አቅም እና ኺደት ፤ በሐገር ደረጃ ከመወሰን ወጥቶ ፤ ስፋት ላለው ዓለም ዓቀፋዊ ውድድር እና የሞያ ጥራት መጋለጥ አለበት። በእዚኽ መልኩ የንግድ አድማስ በንግድ ክፍትነት በእማይሰፋበት ግዜ ፦ ልምድ በአከባቢ ብቻ ይወሰናል ፣ የቴክኖሎጂ ስርጭት በጣም ይንቀረፈፋል ፣ ምርታማነት ከእነ እዚኽ የተለያዩ የንግድ ክፍትነት ከእሚያገኛቸው ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች ስለ እሚገደብ ፤ ማደግ ባለበት መጠን ማደግ ያቅተዋል።

አምስተኛ፦ የበጀት አጠቃቀም አግባብ (Fiscal Discipline) መኖር።

በእዚኽ አውድ ፤ የበጀት አጠቃቀም አግባብ መኖር ማለት ፦

1) መንግሥት ገቢ በእሚሰበስበት ግዜ ፤ የገቢ አሰባሰቡ ምርታማነትን የእሚጎዳ መሆን የለበትም ፣

2) የመንግሥት የበጀት አጠቃቀምም ፤ ምርታማነትን በእሚያሳድግ አግባብ መሆን አለበት ፣

3) መንግሥት እንደ ብድር ያሉ ከግብር ውጭ ያሉ የበጀት ምንጮችን በእሚጠቀምበት ወቅት ግሽበትን እና የዋጋ ስረዓትን የእማያዛቡ እንዲሆኑ ማድረግ አለበት ፤

ማለት ነው።

ስለ እዚኽ፡- በጀት በአግባብ መጠቀም ሲባል ፤ የመንግሥት የበጀት ጉድለትን ማጥበብ ማለት ሳይሆን ፤ የበጀት አሠራሩ ኢኮነሚያዊ ዕድገትን ደግፎ መዋቅራዊ ለውጥን የእሚያስችል እና የእሚያስቀጥል ነው ወይ የእሚል ነው።

መንግሥት የእሚሰበስበው ገቢ ፤ ሲሰበሰብ እና ሲደለደል ፤ መጻኢ ምርታማነትን በእሚያሳድግ መልኩ መሆን አለበት።

ተገቢ የበጀት አጠቃቀም በእማይኖርበት ግዜ ፤ የመንግሥት ገቢ ዕድገትን በእሚያዳክም መንገድ ሊሰበሰብ እና ለፍጆታ ፣ ታማኝነት ለመግዣ ፣ ወይንም ቀውስ ለማረጋጊያ ሊውል ይችላል ፤ መሠረተ ልማት ለመገንባት ፣ ሕዝብ ለመደጎም እና ለማስተማር እንዲኹም ተቋማዊ አቅምን ለመገንባት ከመዋል ይልቅ።

ይኸ ዓይነቱ አግባብ ያለው የበጀት አስተዳደር ከተለመደው አግባብነት ያለው የበጀት አስተዳደር (Fiscal Discipline) እና አግባብነት ያለውን የበጀት አስተዳደር የመንግሥትን የበጀት ጉድለት እና ዕዳ ዝቅ ማድረግ ጋር በቀዳሚነት ከእሚያይዘው እና የበጀት ገንዘብ እንዴት መነጬ ፣ እንዴት ወጣ ወይንም የበጀት ደጓሚ እንደ ብድር ያሉ የገንዘብ ምንጮች የኢኮነሚውን ምርትማነት በእሚጎዳ መንገድ ተሰበሰቡ ወይንስ አልተሰበሰቡም የእሚለውን ጉዳይ ዝቅ ያለ ትኩረት ከእሚሰጠው የበጀት አስተሳሰብ በትኩረት አቅጣጫው ይለያል።

በመሆኑም ፡- አግባብነት ያለው የበጀት አስተዳደር ያለው መንግሥት ማለት ዝቅተኛ ውጪ ያለው መንግሥት ማለት አይሆንም ፤ ይልቁንም ጠቅላላ ፡- የገቢ አሰባሰቡ ፣ የበጀት አደላደሉ እና ለበጀት ጉደለት ማሟያ የእሚጠቀምባቸው እንደ ብድር ያሉ የገንዘብ ምንጮች አጠቃቀሙ ፤ የኢኮነሚውን የማምረት አድማስ በእሚያሰፋ መልኩ የእሚጠቀም ማለት ነው።

አንድ ሐገር በግዜያዊነት የበጀት ጉድለት ሊኖርበት እና አግባብነት ያለው የበጀት አጠቃቀም አሠራር ያለው ሊሆን ይችላል ፤ የበጀት ጉድለቱን ለሟሟላት የእሚጠቀምባቸው እንደ ብድር ያሉት የገንዘብ ምንጮች ፤ የኢኮነሚውን የማምረት አድማስ በእሚያሰፋ መልኩ እስከ ተጠቀመበት ድረስ ችግሩ ብዙ አይሆንም ምክንያቱም ፤ የኢኮኖሚው ምርታማነት ማደግ በግዜ ኺደት የበጀት ጉድለቱን መሙላት የእሚችል ትርፍ ስለ እሚያመነጬ።

እነ እዚኽ ከላይ የተዘረዘሩት አምስት ኹኔታዎች ፤ አንድ መንግሥት ቢተግብራቸው መልካም ናቸው የእሚባሉ ዓይነት የፖሊሲ አማራጭ ኃሳቦች ሳይሆኑ ፤ ይልቁንም በዘላቂነት ከትውልድ ትውልድ በእሚሻገር መልኩ ፤ መግቢያው ላይ ያስቀመጥነውን፡- ምርት–ትርፍ ምርት–ማስፋፊያ–ይበልጥ ትርፍ ምርት ፤ ዑደት ለማስቻል አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ኹኔታዎች ናቸው።

በእዚኽ ምክንያት ፡- የአንድ የልማት ሞዴል ስኬት - መንግሥት መር ፣ ገበያ መር ፣ የሐገር ውስጥ ኢንደስትሪዎችን ተከላካይ (Protectionist) ፣ የኃብት ስርጭት ፍትኃዊነት ቅድሚያ የእሚሰጥ (distributionism) ፣ ወይንም በተፈጥሮ ኃብት ላይ የተደገፈ (Extractive) - በመሆን እና ባለመሆኑ ላይ

አይመሠረትም ይልቁንም ፤ እነ እዚኽ አምስት መርሆችን በአግባቡ ከማስፈጸም አንጻር ወደ ትክክለኛው አፈጻጸም ምን ያህል ተጠግቷል በእሚለው ላይ ነው የእሚወሰነው።

ይልቁንም ሐገራት በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ የመገኘታቸው ምስጢር ፤ ከእነ እዚኽ ከአምስቱ መርሆች አተገባበር አንጻር ባላቸው ቅርበት እና እርቀት የእሚገለጽ ነው።

ከእዚኽ በመቀጠል ያሉት ክፍሎች ፤ እነ እዚኽኝ አምስት ኹኔታዎች/መርሆች ፦ አሠራራቸውን ፣ በተለያየ ሐገር እንደ አተገባበራቸው እንዴት ስኬት እና ክስረት እንደ አስከትሉ ፤ በዝርዝር ያቀርባሉ።

## 2.1 የግል ንብረት ባለቤትነት

*(የንብረት ባለቤትነት መብት እና የውል አስተማማኝነት)*

### 2.1.1 አሠራር

ኢንቨስትመንት በነገ ላይ መወራረድ ነው። የማምረት ኺደት መዋቅራዊ ለውጥ ማስከተል የእሚችለው ፤ የኢኮኖሚ-ተዋኒያን የእሚያመርቱትን ትርፍ ምርት በባለቤትነት የመያዝ ተስፋ ሲኖራቸው ነው።

ገበሬው ከእለት ቀለቡ ያለፈ ምርት የእሚያመርተው ፤ ትርፍ ምርቱ በአንድም በሌላ ምክንያት ከእጁ የእማይወሰድ ሲሆን ነው።

አንድ ባለኃብት ቋሚ ኃብት የእሚገነባው ፤ ያ ቋሚ ኃብት እና የእሚያመነጨው ገቢ ፤ በአንድም በሌላ ምክንያት በመንግሥት ትዕዛዝ ከእጁ እንደ እማይወሰድ ሲያምን ነው።

አበዳሪ የእሚያበድረው ፤ ያበደረውን ብድር በውሉ መሠረት ማስከፈል እንደ እሚችል ሲያምን ነው።

በአንድ ኢኮኖሚ ውስጥ ፤ እንዲኽ የጥረት ውጤት የሆነ የንብረት ባለቤትነት ዋስትና ደካማ በእሚሆንበት ግዜ ፤ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች አድማሳቸው እየጠበበ ይመጣል። ትርፍ ምርት ኹሉ ለእለት ፍጆታ ፣ ተንቀሳቃሽ ንብረት ለመግዛት ከእዚያም ካለፈ ከሐገር የእሚሸሽበት ኹኔታ ይፈጠራል ፤ ዘላቂነት ያለው እና የምርታማነት አድማስ የእሚያሰፋ ኢንቨስትመንት ላይ ከመዋል ይልቅ።

ስለ እዚኽ ፤ የንብረት ባለቤትነት በአንድ ኢኮኖሚ ውስጥ ዋስትና ሲያገኝ አንድ ግልጽ ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ይሠጣል እርሱም ፦ ሰዎች ነገርን ተስፋ በማድረግ በረጅም ግዜ ክፍያ የእሚከፍሉ ፕሮጀክቶች ላይ ኢንቨስት በማድረግ ፤ ገቢን ወደ ካፒታል ይቀይራል።

ይህም በነገ ትርፍ ላይ ዋስትና ማግኘት ባሕሪን በሦሥት ተያያዥነት ባላቸው መንገዶች ይቀይራል፦

- የዕቅድ አድማስን ያስረዝማል,

- ሰዎች በነገ መወራረድ እንዲችሉ ብርታት ይሰጣል (it increases the willingness to bear risk),
- ሰዎች ትርፍ ኃብታቸውን መልሰው ኢንቨስት ለማድረግ መረጋጋት ይሰጣቸዋል (and it stabilizes the reinvestment of surplus).

ውጤቱም ካፒታል ስር እንዲሰድ እና ኢኮኖሚው ቀስ በቀስ ከእለት ጉርስ እና ተፈጥሯዊ ጥሬ ዕቃዎችን ብዙ እሴት ሳይጨምሩ ከመሸጥ እየተላቀቀ (Rather than being extractive) ፤ መዋቅራዊ ሽግግር ወደ እሚያስከትል በቀጣይነት ምርታማነትን የማሳደግ ዑደት ውስጥ እንዲገባ ያደርጋል።

በተለያየ የታሪክ አጋጣሚ ፤ የተለያዩ የፖለቲካ/የኢኮኖሚ ስረዓቶች ፤ የንብረት ባለቤትነት መብት በማረጋገጥ የእሚፈጠረውን ለኢኮኖሚያዊ ልማት አመቺ የሆነ ኹኔታ ፤ የንብረት ባለቤትነት መብትን ከልክለው ፤ ፖለቲካዊ የማስገደድ አቅምን በመጠቀም ዜጎችን ለማስመረት ፣ በፖለቲካዊ ውሳኔ ንብረትን እየወረሱ ይገባል ወደ እሚሉት ዓላማ በማሠማራት ወዘተ ሊተኩት ሞክረዋል።

እነ እዚኽ ስረዓቶችም ፤ ግለሰቦች እና የንግድ ተቋማት ፤ የጥረታቸውን ውጤት እና የንብረታቸው ባለቤት በማድረግ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ከማበረታታ ይልቅ ፤ በመንግሥታዊ ትዕዛዝ ፣ የፖለቲካ ስረዓታቸው የስረዓቱ ወገንተኛ ብሎ ላለው እና በእየ ተወሰነ ወቅት በእሚደረግ ኃብት የማሸጋሸግ ኺደት ፤ ሐገራዊ ኃብትን ወደ ላቀ የማምረት ደረጃ ለማድረስ ይሠራሉ።

ነገር ግን ፤ የማስገደድ አቅም ግዜያዊ የሆነ ውጤት ሊያስከትል ቢችልም እና የተማከለ አስተዳደራዊ ዕቅድ የማስተባበር ሥራ ሊሠራ ቢችልም ፤ የማስገደድ አቅምም ሆነ የዕዝ ዕቅድ ፤ የግል ንብረት ባለቤትነት የእሚያስገኘውን ጥቅም ሊያስገኙ እና ሚናውን ሊተኩ አይችሉም።

ትርፍ በድንገት ከአትራፊው ተወስዶ ለሌላ እንደ እማይከፋፈል እርግጠኝነት በሌለበት ፤ ኢንቨስትመንት ፣ ፈጠራ እና ካፒታል ማካበት ይዳከማል። ምክንያቱም በእንደ እዚኽ ዓይነት ኢኮኖሚያዊ ድባብ ውስጥ ፤ የኢኮኖሚ ተዋንያን ትኩረታቸው የድካማቸውን ውጤት በድንገት እንደ አይቀሙ እንጂ እንዴት አድርገው ምርታማነታቸውን እንደ እሚያሳድጉ አይሆንም።

የሐገራት ኢኮኖሚያዊ ታሪክም ጥናትም ይኽንን ነው የእሚያሳየው። ሐገራት የንብረት ባለቤትነት ዋስትናን ሲያሳድጉ የዜጎቻቸው ኢኮኖሚያዊ ባሕሪ ይቀያራል። ዜጎች በኢኮኖሚያዊ ጥረታቸው ውጤት ላይ የባለቤትነት መብታቸው ሲረጋገጥ ፤ ኃብትን ለፍጆታ በእሚውል መልኩ ወይንም ድንገታዊ ወረሳን በእሚከላከል መልኩ ከማስቀመጥ ይልቅ ወደ ቋሚ እና ድርጅታዊ ቅርጽ ወደ አለው ካፒታል ሲለውጡ ታይተዋል።

ይኽ ደግሞ ቀጣይነት ላለው የምርታማነት እድገት እና እርሱንም ተከትሎ ለእሚመጣ መዋቅራዊ ለውጥ መሠረት ሆኗል።

ለእዚያም ነው ፤ ለተቋማት ፋይዳ ትኩረት በእሚሰጠው የኢከነሚ ሳይንስ ዘርፍ ፤ ለንብረት ባለቤትነት ዋስትና በመስጠት ተቋማዊ ቁርጠኝነት እና በኢከነሚ ዕድገት መካከል ቀጥተኛ ቁርኝት አለ የእሚለው መላምት (theories) ታዋቂ መላምት የሆነው።

በአጭሩ ፤ የመንግሥት ስልጣን የዜጎችን የንብረት ባለቤትነትን መብት እንደ አይነካ አድርጎ መገደብ ፤ የንብረት ባለቤትነት ዋስትና መሠረት ነው። ይኽም ሲረጋገጥ ዜጎች በማምረት ሥራ ላይ እንዲሠማሩ መተማመን መፍጠር ብቻ ሳይሆን በእዚኽ መተማመን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ሲበረታታ ፤ መንግሥት ራሱ እንኳን ፤ ብድር በርካሽ የእሚያገኝበት ኹኔታ ይፈጠራል።

ምክንያቱም ፡- ዜጎች አትርፈው ትርፋቸውን መያዝ ብቻ ሳይሆን ፤ ትርፋቸውን ራሱ በብድር ቢሰጡ የእሚገጥማቸው የስጋት ዋጋ (risk premium) ስለ እሚቀንስ ፡- በገበያው ውስጥ ብዙ ገንዘብ በርካሽ የወለድ መጠን የእሚገኝበትን ዕድል ይጨምራል።

ሰፊ የብድር ገበያ በርካሽ የወለድ መጠን ለመንግሥት ብቻ አይሆንም ግን የእሚገኘው ፤ ይልቁንም ለግሉ መስክ በመሆኑ ፡- የማምረት ፣ የማትረፍ ፣ ኢንቨስት የማድረግ እና እንደገና አስፋፍቶ የማምረት ኺደቱን ያጠናክረዋል።

በእዚኽ መልኩም ፡- የአንድ ሐገር መንግሥት የንብረት ባለቤትነት መብትን ዋስትና ሲያረጋግጥ ፤ ከፖለቲካዊ ታማኝነት ይልቅ አምራችነትን በመሸለም ፤ ካፒታል ከዋስትና ማጣት የተነሳ ወደ ጉሮኖ ውስጥ መሸሸ ሳይሆን እድገትን ለማምጣት ኢንቨስት እንዲደረግ ያደርጋል - በእዚያውም በገንዘብ ገበያው ውስጥ ለብር የእሚሆን ብዙ ጥሬ ገንዘብ እንዲኖር እና ጠቅላላው ኢከነሚው ወደ ኢንደስትራላይዝድ የሆነ የማምረት ዑደት ውስጥ እንዲገባ ያደርገዋል።

### 2.1.2 ታሪካዊ ማሳያዎች ( የስኬት ታሪኮች)

#### *2.1.2.1 እንግሊዝ*

በ1688 የክብር አብዮት (The Glorious Revolution) በእንግሊዝ ከመካኼዱ በፊት ፤ የስትዋርት ስርወ መንግሥት (Stuart Dynasty) የእንግሊዝ ነገሥታት ፤ በተደጋጋሚ ፡- እንደ አሻቸው ንብረት ይወርሱ ፣ ብድር ተበድረው ያለምንም ተጠያቂነት ያለመክፈል ልማድ ፣ አስገድደው ብድር የመውሰድ ፣ ታማኝ ለእሚሏቸው ሰዎች የብቸኛ ነጋዴነት (monopolies) መብት በመስጠት ይታወቁ ነበር።

ንጉሡም በእዚኽ መልኩ ሕጉን እንደ አሻው በማንኛውም ሰዓት የእሚቀይር በመሆኑ ፤ በእንግሊዝ የወለድ መጠን በጣም ከፍተኛ[1] እና የኢንቨስትመንት መጠን በጣም ዝቅተኛ ነበር።

---

[1] የኢትዮጵያ የወለድ መጠን በጣም ከፍተኛ ነው። ብሔራዊ ባንክ የፖሊሲ ሬት (Policy Rate) የእሚለው እና ባንኮች እንደ መነሻ የእሚጠቀሙበት የወለድ መጠን 15% ሲሆን ፤ በአብዛኛው ባንኮች የእሚያበድሩበት መጠን ከ16% እስከ 22% ነው። አደጉ በእሚባሉት እንደ አሜሪካ እና እንግሊዝ በአሉት ሐገራት የወለድ መጠን ከ4% እስከ 7% በመቶ ነው። በጎረቤት ሐገር ኬንያ ከ8% እስከ 13% ነው።

የክብር አብዮት ከእሚባለው በኋላ የመጣው ስምምነት (settlement) የጨዋታውን ሕግ ፤ ከሥልጣን ወደ ፓርላማ በማዞር ለወጠው።

በእዚኽ ስምምነት ፓርላማው በግብር አጣጣል እና አሰባሰብ ላይ ብቸኛ ባለስልጣን እንዲሆን ስለ ተደረገ ፤ ንጉሡ የበጀት ጉድለቱን ለመሙላት እንደ አሻው የዜጎችን ንብረት የእሚወርስበት ነገር አከተመ።

በ1694 የእንግሊዝ ባንክ የእሚባለው የእንግሊዝ ብሔራዊ ባንክ ፤ በፓርላማ እና በግል አበዳሪዎቹ ቁጥጥር ስር እንዲሆን መደረጉም ከፍተኛ ተቋማዊ ለውጥ ነበር ፤ ምክንያቱም ፡- ለውጡ መንግሥት መኖር ከፈለገ የተበደረውን ብድር መክፈል አለበት ወደ እሚል ዕውነታ ውስጥ ስለ አመጣው ፤ በእዚያም ኺደት አበዳሪዎች መንግሥት የተበደራቸውን ብድር እንደ እሚከፍላቸው ምልክት እንዲያገኙ አደረገ።

በኢከነሚ ውስጥ ምልክት መሥጠት በኢኮኖሚያዊ በባሕሪ ቀረጻ እና በልምድ ግንባታ ውስጥ መተኪያ የሌለው ሚና ነው ያለው። መንግሥታት የእሚያደርጉት ነገር በሙሉ ፤ ለኃብት ምልክት ሰጪ ነው። ኃብት ፈሪ ነው ፤ አደጋ ካየ ይደበቃል ወይንም ይሸሻል። ለእዚያም ነው ፤ የንብረት ስጋት ኮሽታ እማያሰማ መንግሥት ፤ ለኢከነሚያዊ ዕድገት በር ከፋች የእሚሆነው።

በእዚኽ መልኩ የግል ንብረት ዋስትና እንዲኖረው በማድርግ የነበረውን ተገማችነት (predictability) ከፍ ማድረግ የነበረው ኢከነሚያዊ ፋይዳ እጅግ ከፍተኛ ነበር ፤ ምክንያቱም ፡- ማሻሻያው በእዚኽ መልኩ ለንብረት ዋስትና ሲሰጥ ፤ መንግሥት እዳውን መክፈል ያለመቻል (default) እድሉ በጣም ስለ ቀነሰ ፤ በርካታ አበዳሪዎች በመተማመን ለመንግሥት ለማበደር እንዲነሳሱ አደረገ ፤ ይኽም የብድር አቅርቦትን በመጨመር መንግሥት በእሚበደርበት ግዜ የእሚከፍለውን የወለድ መጠን በአንድ ግዜ እንዲያሽቆለቁል አደረገው። ይኽም መንግሥት ከፍተኛ የሆነ ብድር ማግኘት የእሚችልበት ሰፊ የገንዘብ አቅርቦት ያለበት የገንዘብ ገበያ ((massive, liquid market)) እንዲያገኝ አስቻለው።

ይኽ ሰፊ የገንዘብ አቅርቦት ያለበት የገንዘብ ገበያ (massive, liquid market) ግን አገልግሎቱ ለመንግሥት ብቻ አልነበረም ፤ የግሉ መስክም በቀላሉ ብድር ማግኘት እና ንግዱን ማሳደግ እንዲችልም ነበር።

ይኽም የንብረት ባለቤት ዋስትና እና እርሱም የፈጠረው አስተማማኝ ሰፊ የገንዘብ አቅርቦት ያለበት የገንዘብ ገበያ (massive, liquid market) ነበር በእንግሊዝ የኢንደስትሪው አብዮት እንዲጀምር አመቺ ኹኔታን የፈጠረለት።

### *2.1.2.2 ደቡብ ኮሪያ*

ደቡብ ኮሪያ ፈጣን ዕድገት ባስመዘገበችበት (ከ1960-1980) በነበረው ግዜ ውስጥ ፤ ምንም እንኳን እንደ እንግሊዝ ሊበራል ዴሞክራት የሆነ የፖለቲካ ድባብ ባይኖራትም እና ከእዚኽ አንጻር ከእንግሊዝ

ብትለይም ፤ በእራሷ መንገድ ግን በውጤቱ ከእንግሊዝ የሕግ ስረዓት ጋር ተመሳሳይ የሆነ የመንግሥትን የማን አለብኝነት የዘፈቀደ ስልጣን የእሚገደብ አሠራር በማስተዋወቅ ፤ የመንግሥትን ቀማኛነት (Extractive) ባሕሪ ማረቅ ችላ ነበር።

የደቡብ ኮሪያው መንግሥት የእራሱን የዘፈቀደ ስልጣን አደብ ያስገዛው ፤ በሐገር ደረጃ የላኪነት ብቃት (Export Discipline) በእሚባል ፤ መንግሥት ለላኪዎች (Exporters) የእሚሠጠውን ድጎማ እና ዝቅተኛ የወለድ መጠን ያለው ብድር ፤ ከጠንካራ የላኪዎች ውጤታማነት መመዘኛ (Rigorous Performance Metrics) ጋር በማያያዝ ነው።

በእዚኽም መሠረት ካፒታል (ድጎማ እና ብድር) ፤ ከፖለቲካ ስልጣኑ ጋር ቅርርብ ላላቸው ላኪዎች ከማቅረብ ይልቅ ፤ ለኹሉም ቼቦልስ[2] (Chaebols) ለተባሉት ትልልቅ የቤተሰብ የንግድ ቡድኖች (Family Business Groups) የእሚቀርበው ካፒታል ፤ በላኪነት (Exporter) ስኬታቸው ላይ እንዲመሠረት አደረገ። በእዚኽም መሠረት ድጎማ እና ብድር የእሚያገኘው የንግድ ቡድን በላኪነት (Exporter) ውድድሩ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገበው ሆነ።

በእዚኽም መልኩ በመላክ ውድድሩ ወደ ኋላ ለቀሩት ላኪዎች የእሚሰጠውን ድጎማ እና ብድር በማስቀረት ፤ የደቡብ ኮሪያው መንግሥት የሐገሪቱ ኃብት የእሚከፋፈልበት መርኽ በምርታማነት ላይ እንጂ በፖለቲካ ቅርርብ እና ትውውቅ (Cronyism) እንደ አልሆነ አረጋገጠ።

ከእዚያም ጋር አብሮ ፤ ሕግ ድንገት ዱብ ብሎ የንግዱ ማሕበረሰብ ያልጠበቀው ኹኔታ ውስጥ እራሱን እንደ አያገኝ ፤ የንግድ ሕግ የእሚወጣበት አግባብ ዱብ እዳ ሳይሆን ተገማች (Predictable) እንዲሆንም አደረገ።

የምክክር ጉባኤ (Deliberation Councils) በእሚባለው ተቋም አማካኝነት ፤ ለነጋዴው ሕግ ድንገተኛ እና ዘፈቀደ እንደ እማይሆን መተማመኛ ፈጠረላቸው።

ይኽም ለንግዱ ማሕበረሰብ መንግሥት የንብረት ባለቤትነትን ለማክበር ቁርጠኝነት እንደ አለው ምልክት ሰጣቸው።

ምንም እንኳን ፤ በእዚያ ዘመን ኹሉ ፤ የደቡብ ኮሪያው መንግሥት ጣልቃ ገቢ (Interventionist) መንግሥት ቢሆንም ፤ የኢንደስትሪ የንብረት ባለቤትነት ጉዳይ በቀናዒነት የእሚያከበረው ነገር ነው የነበረው። አንድ ነጋዴ የብረት ማቅለጫ ወይንም የመርከብ መገንቢያ ከመሠረተ ፤ የብረት ማቅለጫ ወይንም የመርከብ መገንቢያ ተወዳዳሪ አምራች ሆኖ እስከ ቆየ ድረስ መንግሥት የንብረት ባለቤትነት መብቱን እንደ እሚያከብር በእማያወላዳ መልኩ አረጋገጠ።

---

[2] እነ እዚኽ ቼቦልስ የእሚባሉት የቢዝነስ ግሩፖች ፤ የቤተሰብ ንብረቶች ሲሆኑ ከባንክ እስከ ሎጀስቲክ እና ፋብሪካዎችን በአንድ ላይ በባለቤትነት የእሚይዙ ሲሆኑ ፤ Samsung, Hyundai, and LG ተጠቃሽ ናቸው።

መንግሥታዊ መረጋጋት በሌላቸው ሐገራት ውስጥ እንደ እሚስተዋለው ፤ የኢኮኖሚ እንስቃሴዎች በቶሎ ትርፍ የእሚያመጡ እንደ ማዕድን አውጥቶ መሸጥ እና ያለ ውድድር በመንግሥት ችሮታ የእሚመጣ ፕሮጀክት ላይ በመሳተፍ የግዜያዊ ጥቅም አሳዳጅ እንደ አይሆኑ ፤ በተወዳዳሪነት የማምረት አቅማቸውን ገንብተው ለእሚሠሩ ድርጅቶች ፤ በፖሊሲ ደረጃ ዝቅተኛ የወለድ መጠን ያላቸውን ብድሮች የማመቻቸት ሥራም ይሠራ ነበር።

እንደ ዕሚታየው ፤ በኹለቱም ግዜ ፤ ነጋዴዎች የኢንቨስትመንት አድማሳቸውን ለማስፋት የእሚችሉበት ኹኔታ ተፈጥሯል ፤ ምክንያቱም ፡- መንግሥት ኃብት የእሚገኝበት እና የእሚከፋፈልበት መንገድ ፖለቲካዊ በሆነ ዘፈቀደ ( Political Arbitrariness ) ሳይሆን በምርታማነት ላይ የተደገፈ ነው የእሚለውን ማሳየት ስለ በመቻሉ ።

በዓለም ሕዝብ ኢኮነሚያዊ ታሪክ ፤ በፓርላማ ይኹን እራሱን በእሚገታ ቢሮክራሲ (Disciplined Bureaucracy) አሠራር ባለው አምባገነናዊ መንግሥት ፤ መንግሥት በአንድም ይኹን በሌላ ምክንያት ንብረትን በግብታዊነት (Arbitrarily) ሊነጥቅ ወይንም ሊያከፋፍል የእማይችል መሆኑ በሕብረተሰቡ ውስጥ ተዓማኒነት እያገኘ በመጣ መጠን ፤ ያ ማሕበረሰብ በልቶ ከማደር ዝንባሌ ወደ ኢንቨስትመንት ዝንባሌ (From "survival mode" to "investment mode")ተቀይሯል።

### 2.1.3 ዓይነተኛ የክስረት ታሪክ : አርጀንቲና

እንግሊዝ እና ደቡብ ኮሪያ ፤ መንግሥት የንብረት ባለቤትነት ለማክበር ያለውን ቁርጠኝነት በአሳማኝ መልኩ ያሳየባቸው "የስኬት ተምሳሌት" ሆነው ከቀረቡ ፤ አርጅንቲና ደግሞ መንግሥት ያንን ቁርጠኝነት ሳያሳይ ሲቀር የእሚከተለውን የኢከነሚ ቀውስ የእምታሳይ ፤ የማስጠንቀቂያ ምሳሌ ሆና ትቀርባለች።

በኃያኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ አርጀንቲና የዓለማችን አንዷ ኃብታም ሐገር ነበረች። ከእዚያ በኋላ ግን መንግሥት በተለዋወጠ ቁጥር ፤ መንግሥታዊ ተቋሞቿ በንብረት ባለቤትነት ጉዳይ ተለዋዋጭ አቋም በማሳየታቸው ፤ በሐገሪቱ ለዘመናዊ ኢንደስትሪያላይዝድ ኢከነሚ ያስፈልግ የነበረው "ረዥም የኢንቨስትመንት አድማስ" (Long-term Horizon) ሙልጭ ብሎ ጠፋ።

የአርጀንቲና ውድቀት መሠረቱ ፤ ከተረጋጋ እና በላኪነት ላይ ከተመሠረተ የሕግ የበላይነት ከሰፈነበት ስረዓት(Stable, export-oriented rule based system) በወቅታዊ ፖለቲካዊ ውሳኔ የእሚዘወር (Characterized by discretionary power) ስረዓት መቀየር ነበር።

ከ1900-1930 በአሉት በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያዎች ፤ አርጀንቲና በጣም ጠንካራ የእሚባል የኢከነሚ ባለቤት ነበረች ፤ በተለይ በግብርናው ላይ።

በእዚኽ ወቅት ፤ አርጀንቲና ምንም እንኳን እንደ ደቡብ ኮሪያ ላኪነትን ከአፈጻጸም ብቃት ጋር ያያዘች ሐገር የነበረች ባይሆንም ፤ የመንግሥት ተቋማት በአንጻራዊነት የተረጋጉ እና ግብታዊነት የእማይታይባቸው ፤ የንብረት ባለቤትነት መብት የተከበረበት እና ትልቅ ከኤክስፖርት የእሚመነጭ ትርፍ የእሚገኝባት ሐገር ነበረች ።

ከ1940 በኋላ ግን ሶሻሊስታዊ ሕዝበኝነት ተጸናወታቸው እና እንደ ደቡብ ኮሪያ ፤ በብቃት ላይ የተመሠረተ (Export Discipline) የኤክስፖርት ኢኮኖሚ ከመገንባት ይልቅ ፤ ከኤክስፖርት የእሚያገኙትን ትርፍ ፦ ለደሞዝ ጭማሪ ፣ ለድጎማ እና ተመራጭ የእሚሏቸውን የኢንደስትሪ መስኮችን ለማበረታታት የግብር ማበረታቻ እና የታሪፍ ከለላ ለመስጠት ይጠቀሙበት ጀመር።

ኢምፖርትን መተካት መሠረት ያደረገ የኢንደስትሪ እድገት (Import Substitution Industrialization (ISI) ) የእሚባለው አባዜ ፤ በተወዳዳሪ አምራችነታቸው ሳይሆን መንግሥት ከእሚሰጣቸው (Protected) ድጎማ እና የታሪፍ ከለላ የተነሳ የእሚኖሩ እና የኪሳራ ማዕከል የሆኑ ድርጅቶችን ፈጠረ። ድጎማ እና ብድር ፤ ተወዳዳሪ አምራችነታቸውን ላሳዩት ሳይሆን ፖለቲካዊ ትሥሥር ወደ አላቸው (Politically connected groups) ይፈሱ ጀመር።

የንብረት ባለቤትነት ግብታዊ (Arbitrary) ሆነ - ንብረትም ፦ ለመንግሥታዊ ውርስ (Expropriation) ፣ በከፍተኛ የዋጋ ግሽበት ለመሸርሸር ፣ እና የባለስልጣን ፊት አይቶ ለማደር (Political discretion) ተጋለጠ።

የመጫወቻው ሕግ በእዚኽ መልኩ በግብታዊነት (Arbitrariness) ሲተካ ፤ ረጅም አድማስ ያለው ኢንቨስትመንት ማድረግ ፤ ከስሌት ይልቅ ቁማር መቆመር ሆነ።

በ20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ፤ የባቡር ድርጅቶችን እና እንደ መብራት እና ስልክ ዓይነት አገልግሎት ሰጪ የሆኑ ድርጅቶችን በመውረስ ጀምሮ ፤ በቅርቡ እንደ YPF የተባለውን የነዳጅ እና የተፈጥሮ ጋዝ አምራች ድርጅትን እና የጡረታ ገንዘቦችን በመውረስ ፤ መንግሥት በአርጀንቲና ውስጥ የንብረት ባለቤትነት ዋስትና ኹኔታዊ እንጂ ቅዱስ እና እማይነካ ነገር እንደ አልሆነ በተደጋጋሚ አመላከተ።

ይኽም የመንግሥት ግብታዊነት ፤ በኢኮኖሚክስ ሆልድ አፕ (Hold up) የእሚባለውን እና አንድ ቡድን ወይንም ግለሰብ ከፍተኛ መጠን ያለው እና ሊያንቀሳቅሰው የእማይችለውን ኢንቨስትመንት ካደረገ በኋላ ፤ ይኽን ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ለመከላከል ሲል ፤ በሌላ አካል በአርጀንቲና ልዩ ኹኔታ በመንግሥት አሉታዊ ተጽኖ ሥር የእሚወድቅበትን ኹኔታ አበራከተ።

ይኽም ማለት ፤ አንድ ነጋዴ ፤ በአርጀንቲና ነጻ እና ሕጋዊ የንግድ ኹኔታ አለ ብሎ ፤ በብዙ ሚልዮን የእሚቆጠር ኢንቨስትመንት ያደረገ ነጋዴ ፦ የግብር መጠኑ እጅግ ሊቀየርበት ፣ የማሕበራዊ መዋጮ በሚል ገንዘብ እንዲያዋጣ የእሚገደድበት ፣ ዶላር ከሐገር እንደ አያስወጣ የእሚከለከልበት ፣ ወዘተ ኹኔታ ይፈጠርና ፤ ያፈሰሰውን በሚልዮን የእሚቆጠር ዶላር ለማትረፍ ሲል ይኽን ፤ ስውር ብዝበዛ ይታገሳል ማለት ነው።

ይኽ ዓይነቱ ኹኔታ በእሚበራከትበት ወቅት ፤ አንድ ባለኃብት ሊያንቀሳቅሰው የእማይችለውን ብዙ ወጭ የወጣበትን ትልቅ እና ተወዳዳሪ ፋብሪካ ለምን ይገነባል ? መንግሥት ኃብቱን ለመቀራመት ሲል የታክስ ወይንም ሌላ ሕጎችን እንደ አሻው እሚቀየር ከሆነ።

ይኽም ሆልድ አፕ (Hold up) የእሚባለው ጉዳይ በአርጅንቲና ዋነኛ የስጋት ምንጭ በመሆኑ ፤ ባለኃብቶች ኢንደስትሪን እንደ አያሳድጉ ዋነኛ ዕንቅፋት ሆነ።

የዋጋ ግሽበትም ድምጽ አልባ የኃብት ቀማኛ (Silent expropriator) የሆነበት ኹኔታ ተፈጥሮ ነበር።

እንግሊዝ ብሔራዊ ባንኳን ገንዘቧን ለማረጋጋት ስትጠቀምበት ፤ የአርጀንቲናው ብሔራዊው ባንክ መንግሥት የበጀት ጉድለቱን ለሟሟላት የእሚጠቀምበት የአስፈጻሚው ቀኝ እጅ ነው የሆነው።

የመንግሥት አስፈጻሚው ክፍል በእዚኽ መልኩ ብሔራዊ ባንኩን የበጀት ጉድለት መሸፈኘያ የእሚያደርገው ፤ ብሔራዊ ባንኩ ገንዝብ እንዲያትም እና እንዲሰጠው በማድረግ ስለ ሆነ ፤ ይኽ አካኼድ በኢኮኖሚው ውስጥ ከኢኮኖሚው የምርት አቅም በላይ የሆነ ግንዘብ በመርጨት ፤ የዋጋ ግሽበት ማስከተሉ የእማይቀር ነው።

በእዚኽ መልኩ የዋጋ ግሽበት ሲፈጠር ደግሞ ረጅም አድማስ( Long-term) ያለው የማበደር እና የመበደር ነገር በፍጹም የእማይቻል ይሆናል። አንድ ሰው የ30 ዓመት የቤት መግዣ ወይንም የ10 ዓመት የኢንደስትሪ ማስፋፊያ ብድር ሊወስድ አይችልም የዛሬ ስድስት ወር የገንዘቡ ኹኔታ ምን እንደ እሚሆን ለመገመት የእሚቸገር ከሆነ።

ይኽም የንግድ ተቋማት ለእሚቀጥለው አስር አመት ከማቀድ ይልቅ ለእሚቀጥለው አንድ ሳምንት እንዲያቅዱ አድርጓቸዋል። ይኽም በተራው ኢኮኖሚው ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የማምረት ኺደት ውስጥ ከመግባት ይልቅ ፤ የስጋት መጠናቸው በጣም ዝቅተኛ ወደሆኑ ቶሎ ቶሎ ወደ እሚገላበጡ ወይንም ኪራይ ሰብሳቢ (በመንግሥት ችሮታ እና በፖለቲካ ትውውቅ ላይ ወደ ተመሠረቱ) የንግድ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲገቡ አደረጋቸው (It encouraged rent seeking behavior – where business seek economic favor from governments.)።

በረጅም ግዜ የእሚከፈል ከፍ ያለ ብድር ማግኘት በእማይችልበት ኢኮነሚ ውስጥ ኢንደስትሪዎች ሊዘምኑ አይችሉም። ከእዚኽም የተነሳ የአርጀንቲን ኢንደስትሪዎች ፤ የተረጋጋ የብድር ገበያ ካላቸው ገበያዎች አንጻር ፤ ደካማ ተወዳዳሪ እየሆኑ ፤ አርጀንቲናን ከግዜ ወደ ግዜ እየከፋ የእሚኼድ የኢንደስትሪ መመናመን (Deindustrialization ) ውስጥ አስገባት ።

ይኽም ኹኔታ ሲቀጥል ፤ የሐገሪቱ ገንዘብ እና የሐገሪቱ ባንኮች እማያስተማምኑ ሆነው የመታየታቸውን ነገር እንዲ ጨምር ስለ አደረገ ፤ በተለይ ደግሞ በ2001 ከታየው ኮራሊቶ (Corralito) ከተባለው እና ሰዎች በባንክ ካላቸው ገንዘብ ማውጣት የእሚችሉትን መጠን ከገደበበት ክስተት በኋላ ፤ የአርጀንቲና ዜጎች ገንዘባቸውን ወደ ዶላር ቀይሮ መያዝ ወይንም ከሐገር ማሸሸቱን ተያያዙት።

ይኽም ፤ የአርጀንቲና ዜጎች በመቶ ቢልዮኖች የእሚቆጠሩ ዶላሮች ከሐገራቸው ውጭ እንዲያስቀምጡ አድርጓቸዋል። ይኽ በመቶዎች ቢልዮኖች ዶላሮች የእሚገመት የአርጀንቲና ገንዘብ ፤ በሐገር ውስጥ የኢንደስትሪ ልማትን ለማቀጣጠል መዋል ይችል ነበር ፤ መንሥታዊ ወረሳን ወይንም የገንዘብ መዳከም (Seizure or devaluation) ፍራቻ በውጭ ሐገራት ባንኮች ተቀምጦ የሌሎች ሐገራትን ብድር ከእሚያረክስ እና ኢኮኖሚ ፋይናንስ ከእሚያደርግ ይልቅ።

ይኸም ማለት የአርጀንቲና ገንዘብ የንብረት ባለቤትነት ዋስትና በማጣቱ ምክንያት በተፈጠረ ወጥመድ ተይዟል ማለት ነው።

### 2.1.4 ድምዳሜ

እንግሊዝ በመንግሥት ስልጣን ላይ ሕገመንግሥታዊ የሆነ ገደብ አስቀመጠች ፤ ደቡብ ኮሪያ በተወዳዳሪነት ላይ የተመሠረተ የመንግሥት ስልጣን ገደብ በማስቀመጥ የኢንደስትሪ ንብረቶችን ለማክበር ያላትን ቁርጠኝነት አሳየች ፤ አርጀንቲና በአንጻሩ የመጣው አዲስ የፖለቲካ ስልጣን በሙሉ እንደ አሻው አዲስ ሕግ እያወጣ የንብረት ባለቤትነት ዋስትናን ስጋት ውስጥ እሚከትበት ሐገር ሆነች። ውጤቱም፡- እንግሊዝ እና ደቡብ ኮርያ መዋቅራዊ ለውጥ አምጥቶ የዜጎቻቸውን የኑሮ ደረጃ የእሚያሻሽል ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ሲያድጉ አርጀንቲና ደግሞ ተምሳሌታዊ የነበረውን የ20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ኢኮኖሚያዋን ለውደቀት የዳረገች በመሆን ፤ የተለያየ የኢኮኖሚያዊ ዕድገት አቅጣጫ እንዲኖራቸው አደረገ (Resulted in a diverging economic growth)።

ይኸ የኢከነሚ ዕድገት መለያየት ግን ፡- ከባሕል ፣ ከመልከዓምድር ፣ ወይንም ከተፈጥሮ ኃብት ክምችት ልዩነት አልመጣም ፤ ይልቁንም እያንዳንዱ ስረዓት የኢከነሚውን አድማስ (Economic time horizon) በማስፋት ረዘም ያሉ የኢከነሚ ፕሮጀክቶችን ለመጀመር በማስቻሉ እና ባለማስቻሉ የመጣው ነው።

ከእዚኽ አንጻር ወሳኙ ነገር ፤ ዴሞክራሲያዊ ወይንም አምባገነናዊ መንግሥት የመኖሩ ጉዳይ አይደለም ፤ ይልቁንም መንግሥት ድንገት ተነስቶ ፤ የምርት ጥረት (productive effort) ውጤት የሆነውን ፥ ኃብት ፤ መውረስ እና ማከፋፈል እንደ አይችል ተደርጓል ወይንስ አልተደረገም የእሚለው ነው።

## 2.2 የንብረት ተንቀሳቃሽነት

*(የንብረት ባለቤትነት መብት እና የውል አስተማማኝነት)*

### 2.2.1 አሠራር

በአንድ ሐገር ኢኮኖሚ ውስጥ ንብረትን በባለቤትነት የሚያዝ ዋስትናን ማረጋገጥ ብቻ መዋቅራዊ ለውጥን ለማምጣት በቂ አይደለም። ማምረቻ ንብረቶች ከባለቤታቸ መነጠል መቻልም አለባቸው (Must also be alienable) - ማለትም ፡- መሸጥ ፣ ለብድር ማስያዣነት መቅረብ ፣ ኢከነሚ ኦፍ ስኬል ለማስቻል (To allow economics of scale) በአንድ ባለቤትነት ሥር መጠራቀም እና የተሻለ አምራች ወደ ሆነው ሰው መተላለፍ መቻል አለባቸው።

ንብረት መገላበጥ (Fungible) መሆን በእሚችልበት ኢከነሚ ውስጥ ፤ ያ ንብረት መተዳደሪያ ብቻ ሳይሆን የካፒታል አካልም ይሆናል።

በእዚኽም የብድር ምንጭ ሊሆን ይችላል ፣ የቴክኖሎጂ ማሻሻያን ለማምጣት የገንዘብ ምንጭ ሊሆን ይችላል ፣ ወይንም ከዝቅተኛ አምራች ወደ ከፍተኛ አምራች ሊሽጋገር ይችላል።

በእዚኽ መልኩ ንብረት ሲንቀሳቀስ ነው ፤ ኃብት በቀጣይነት ከፍተኛ አምራች ወደ ሆነው ባለቤት የእሚተላለፈው።

የንብረት ተንቀሳቃሽነት ሲገደብ (Where alienability is restricted) ይኼ አሠራር ይቋረጣል። ንብረቶች እንደ አይሸጡ ወይንም እንደ አይተላለፉ በእሚገደቡበት ግዜ ፤ በደካማ አምራቾች እጅ ተቆልፈው ይቀራሉ።

የንብረት ባለቤትነት መብት ብቻ በተከበረበት እና ንብረት በሽያጭ እና በማስያዣነት በኢኮኖሚው ውስጥ በቀላሉ በእማይንቀሳቀስበት ወቅት ፤ ኢኮኖሚው ያን ንብረት የበለጠ አምራች ሊያደርገው ለእሚችል ባለንብረት ሊያስተላልፈው ቢችልም ፤ ንብረቱ ተንቀሳቃሽነቱ ዝቅተኛ በመሆኑ ኢኮኖሚው የተረጋጋ ነገር ግን ቆሞ የቀረ (Stagnant) ኢከነሚ ሆኖ ይቀራል።

ኢከነሚው በጠቅላላ የተረጋጋ ነገር ግን ፤ የተቆለፈባቸው ኃብቶች ያሉበት ኢከነሚ ይሆናል።

### 2.2.2 ታሪካዊ ማሳያዎች (የስኬት ታሪክ)

#### *2.2.2.1 ጃፓን*

ጃፓኖች በ1873ቱ የመሬት ግብር ማሻሻያ ቻይሶ ኬይዚ (Chiso Kaisei) ፤ ፊውዳሊዝምን ሽረው በግል የመሬት ንብረት ባለቤትነት ላይ የተመሠረተ ዘመናዊ የግብር ስረዓት መዘርጋት ችለው ነበር።

ይኸም ማሻሻያ ጃፓንን በዋናነት በኹለት ምክንያት ለማዘመን ችሏል፡-

የመጀመሪያው ፡- ባላባቱ በመንግሥት እና በባለ መሬት አራሹ መካከል ያለ የመሬት ግብር ሰብሳቢ እንደ አይሆን በማንሳት ፤ በመሬት አራሹ እና በመንግሥት መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት እንዲኖር እና መንግሥት ፤ ምርታማነትን ታሳቢ ያደረገ ፤ አንድ ወጥ ብሔራዊ ወይንም ሐገር ዓቀፍ ግብር እንዲሰበስብ በማድረግ ፊውዳሊዝምን በመሻሩ ነው።

በእዚኽ ምርታማነትን ታሳቢ ባደረገ የግብር ስረዓት መሠረት ፤ እያንዳንዱ መሬት የማምረት አቅም ደረጃ ይወጣለት እና ወጥነት ያለው በማምረት አቅሙ ላይ የተመሠረተ የግብር መጠን ይጣልበታል። መሬቱ በወጣለት የማምረት አቅም ልክ ግብር መክፈል ያልቻሉ ገበሬዎች መሬቱን በእዚያ ልክ ማምረት ለእሚችለው ገበሬ ለመሸጥ ይገደዳሉ።

ምክንያቱም ፡- መሬቱ ተጠቅመው በወጣለት የማምረት ደረጃ ልክ ማምረት ካልቻሉ ፤ የእሚጠበቅባቸውን ግብር መክፈል ስለ እሚያዳግታቸው።

መንግሥትም ከመሬቱ ግብር የእሚያገኘውን ግብር በመውሰድ ፤ በእዚኽ ኺደት እየተፈጠረ የመጣውን አዲስ ኢንደስትሪያላይዝድ ገበሬ እና ማቆጥቆጥ የጀመረውን የፋብሪካ ባለኃብት ለማገዝ ፤ መሠረተ ልማት (በወቅቱ ባቡር እና መንገድ) ላይ በማዋል ሽግግሩን አገዘ።

ይኸም በጃፓን ኢንደስትሪሊያዝድ በመሆነ መንገድ የእሚያርሱ ገበሬዎችን እና እንደስትሪላይዝድ በሆነ መልኩ የእሚያመርቱ ባለኃብቶችን ፈጠረ።

እነ እዚኽ አዳዲሶቹ ኢንደስትሪያላይዝድ ገበሬ እና አቆጥቋጭ የጃፓን ኢንደስትሪያሊስቶች መፈጠር ያቻሉት ፤ ሕጉ ንብረት እንዲገላበጥ እና እጅ እንዲቀይር (Asset Mobility) በመፍቀዱ እና መሬት ወደ ተሻለው አምራች እንዲተላለፍ በማስቻሉ ነበር።

ከእዚኽ በታች ያለው ኃሳብ በእንግሊዘኛው ውስጥ ባይኖርም ፤ ነገሩን ከሐገራችን ኹኔታ ጋር ለማጣጣም ተጭምሯል።

በጃፓን የመሬት ማሻሻያ አዋጅ በተተገበረ በ30 እና በ40 ዓመት ውስጥ በ20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ ጃፓንን ከፊውዳሊዝም አውጥቶ ካፒታሊስት ሲያደርግ በእኛ የመሬት አዋጅ ከ52 ዓመታት በኋላ በ21ኛው ክፍለ ዘመን እንኳን ትርጉም ባለው መልኩ ካፒታሊዝምን መፍጠር የተሳነው ፤ በእኛ ሐገር ለውጥ የገዢ መደብ ለውጥ ላይ ያተኮረ እና የካፒታሊዝም ገንቢ ተቋማት ግንባታን መርህ የእማያውቅ ወይንም የእማይፈልግ ስለነበር ነው።

ምንም እንኳን አንድን ማሕበረሰብ ከፊውዳሊዝም ወደ ካፒታሊዝም ለማሸጋገር የእሚያስፈልገውን የተቋማት ሕግ ለመቀየር ደም አፋሳሽ አብዮት ሊያስፈልግ ቢችልም ፤ ከፊውዳሊዝም ወደ ካፒታሊዝም የእሚደረገው ሽግግር ፤ ደም አፋሳሽ አብዮት ተደረገም አልተደረግም ፤ ከተቋማት ሕግ ቅያሪ ውጭ ሊሳካ አይችልም።

በሌላ አነጋገር ፤ ደም አፋሳሽ አብዮት የእሚያስፈልገው የተቋማትን ሕግ ለመቀየር በመሆኑ ፤ አብዮቱ በራሱ ግብ አይደለም።

ለእዚያም ነው በጃፓን ያለ ምንም "ደም መፋሰስ" የመሬት ሕግን ብቻ በመቀየር ፤ ከ30 እስከ 40 ባለ ዓመት ውስጥ ከፊውዳሊዝም ወደ ካፒታሊዝም የተሸጋገሩት።

ይኸም ካርል ማርክስም ፤ ዳስ ካፒታል በእሚለው መጽሐፍ ውስጥ አንድ ማሕበረሰብ እንዴት ከፊውዳሊዝም ወደ ካፒታሊዝም እንደ እሚሸጋገር በእሚያብራራብት ግዜ ፤ ጉዳዩ የተቋማት ለውጥ ጉዳይ እንደ ሆነ ከአስቀመጠው ጋር ይስማማል፡-

> *"የካፒታሊስታዊው ስረዓት የኢኮነሚ መዋቅር ከፊውዳሉ ስረዓት የኢኮነሚ መዋቅር ውስጥ ነው የበቀለው። የመጀመሪያው መፍረስ የኋላኛው እንዲመጣ ይልቀዋል።*
>
> *አምራቹ (ገበሬው) ፣ ሠራተኛው ፤ በነጻ ገበያ ወጥቶ ጉልበቱን መሸጥ የእሚችለው በባርነት ፣ በገባርነት ፣ በጭሰኝነት ከመሬት ጋር ያለው ትሥሥር ሲበጠስ ነው። እንደገናም የሥራ ጉልበቱን ፤ በአሻው እና ገበያ ባገኘበት ቦታ ኹሉ በነጻ እንዲሸጥ ፤ የሞያ ማሕበራት እና የሠራተኛ ማሕበራት ከእሚያወጡበት ሕግ እና ውስንነት መላቀቅ አለበት።"*

*"The economic structure of capitalist society has grown out of the economic structure of feudal society. The dissolution of the latter set free the elements of the former.*

*The immediate producer, the labourer, could only dispose of his own person after he had ceased to be attached to the soil and ceased to be the slave, serf, or bondsman of another. To become a free seller of labour power, who carries his commodity wherever he finds a market, he must further have escaped from the regime of the guilds, their rules for apprentices and journeymen, and the impediments of their labour regulations."*

በጃፓንም ያደረጉት ይኸንን ነው። ገበሬው መጀመሪያ ጭሰኛ ነበር ፤ በ1873ቱ የመሬት ግብር ማሻሻያ ፤ ገበሬውን ከጭሰኝነት አውጥተው የመሬት ባለቤት አደረጉት። በእዚያ ግን አላበቁም ፤ በእኛ ሐገር እንደ ሆነው መሬትህን መሸጥ አትችልም ከማለት ይልቅ ፤ መሬትህን መሸጥ ትችላለህ ብለው በመፍቀድ ፤ ገበሬው በምርት ተወዳድሮ ግብር መክፈል ሲያቅተው መሬቱን በመሸጥ የፋብሪካ ሠራተኛ እንዲሆን ፈቀዱለት።

ያም ብቻ አይደለም በጃፓን የሠራተኛ ማሕበር የእሚባል የአመጽ እና የስንፍና ጉሮኖ አልፈጠሩም ፤ ይልቁንም ፡- የሠራተኛ ማሕበራት ከአንድ መሥሪያ ቤት አጥር እንደ አይሠፉ አድርገው ፤ ሠራተኛው ከሙብት ጠያቂነት ወደ ሞብነት እንደ አይቀየርም አደርገዋል።

በአጭሩ ጃፓኖች የመሬት ላራሹ አካኼዳቸው ከኢትዮጵያ ይልቅ የሠራው ፤ የንብረት ተንቀሳቃሽነትን ስለ አልከለከለ ነው።

በእኛ እና ድህነት መታወቂያቸው በሆኑት በሌሎቹ የዓለም ሐገራት ግን ፤ ከፊውዳሊዝም ወደ ካፒታሊዝም መግባት አይበቃንም ካፒታሊዝምን ዘለን ሶሻሊስት እንሆናለን ያሉ ቀቢጠ ተስፈኛ አብዮተኞች ፤ የንብረት ልውውጥን ገድበው ፤ ከ52 ዓመታት በሁላ እንኳን ከ75% በላይ የሆነው ኢትዮጵያዊ ከእጅ ወደ አፍ በሆነ ግብርና እንዲኖር አድርገውታል።

### 2.2.3 ዓይነተኛ የክስረት ታሪኮች : ኢትዮጵያ እና ሕንድ

በኢትዮጵያ መንግሥት (የኢትዮጵያ ሕዝብ በጋራ) ብቸኛ የመሬት ባለቤት መሆኑ ፤ ዘመናዊውን "ሙት ካፒታል" ፈጥሯል።

ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ገበሬዎች ፤ የሕይወት ዘመን መሬት የመጠቀም ባቤትነት መብት ቢኖራቸውም ፤ ከመፈናቀል እና የከተማ ለማኝ ከመሆን ለመከላከል በእሚል ፤ መሬት መሸጥ በሕግ ስለ ተከለከሉ ፤ ኢትዮጵያዊያን ቁሞ ቀር ኢከነሚ እንዲኖራቸው አድርጓል።

በቅርቡ በፈረንጆቹ 2020 እስከተደረገው ማሻሻያ ፤ ገበሬዎች መሬታቸውን መሸጥ ብቻ ሳይሆን አስይዘውም መበደር አይችሉም ነበር ፤ ከእዚኽ የተነሳ ገበሬዎች የማስፋፊያ ገንዘብ ለማግኘት መሬታቸውን ማስያዣ ማድረግ እማይችሉ በመሆኑ ፤ ከብድር ገበያው ተገለው ነበር።

በቅርቡ ገበሬዎች መሬታቸውን አስይዘው እንዲበደሩ የእሚፈቅድ አሠራር ቢመጣም ፤ ባንኮች ብድሩ ሲበላሽ ፤ መሬቱን በሐራጅ ማገድ ወይንም በሽያጭ ለሌላ በማስተላለፍ ያበደሩትን ገንዘብ እሚመልሱበት አግባብ ከሌለ ፤ በሌላ አገላለጽ የገጠር መሬት እማይሸጥ ከሆነ ፤ ገበሬው አሁንም ቢሆን ከብድር ገበያው እሚገለል ነው እሚሆነው።

በአግባቡ በእሚሠራ ገበያ ውስጥ ደካማው ገበሬ ይበልጥ አማራች ለሆነው ገበሬ መሬቱን በመሸጥ ከግብርናው ይወጣል። ኢትዮጵያ ይኽንን ከግብርና የመውጫ እና የመግቢያ በር በመዝጋት ፤ ከእጅ ወደ አፍ በሆነ የምርታማነት መጠኑ ደካማ በሆነ ኢከነሚ ውስጥ ተቆልፋለች።

ህንድ ከእዚኽ የተለየ አባዜ ነው የተጠናወታት ፤ ምክንያቱም ፦ በሕንድ መሸጥ መለወጥ የእሚያስችል የመሬት ንብረት ባለቤትነት መብት ከቀኝ ግዛት ዘመን ጀምሮ ነበራት ፤ ነገር ግን ይኽ መብት በቀኝ ግዛቱም ሆነ በነጻነቱ ዘመን ግድፈቶች ምክንያት ተግባራዊ ፋይዳ የሌለው የወረቀት ላይ ብቻ መብት ሆኖ ቀርቷል።

ከጃፓኑ የሜይጃይ ማሻሻያ (The Meiji Reform in Japan) በተቃራኒ ፤ የእንግሊዙ ቀኝ ግዛት በሕንድ ዋና ትኩረቱ ፤ ከመሬት የእሚሰበስበውን ግብር ከፍ ማድረግ ላይ ብቻ ያተኮረ ነበር።

እንግሊዞቹ የግብሩን መጠን ከጥቅላላው ምርት ከ45%-55% ነበር ያደረጉት - ይኽ ደግሞ በአብዛኛው አንድ ገበሬ ከወጪ ቀሪው በላይ ይሆን ስለ ነበር - ገበሬው ግብሩን ለመክፈል ሲል የብድር አዘቅት ውስጥ እንዲገባ ነበር ያደረገው።

በተለይ በድርቅ ወራት ፤ ገበሬው የመንግሥትን ግብር መክፈል ሲያቅተው በእሚቀጥለው ምርት ሲሻሻል እከፍላለኹ በእሚል ከአራጣ አበዳሪዎች የመበደር ነገር ውስጥ ያስገባው እና ብዙ ግዜ ብድሩ እየተከመረ ገበሬው ብድሩን መክፈል እማይችልበት ኹኔታ ይፈጥር ነበር።

በእዚኽ ኹኔታ ገበሬው የተበደረውን ብድር መክፈል ሳይችል ሲቀር ፤ መሬቱ ለተሻለው አምራጭ ከመተላለፍ ይልቅ የአራጣው አበዳሪ ንብረት ይሆናል።

አራጣ አበደሪዎቹ (The Baniya) የመሬቱን ምርታማነት የማሳደግ ምንም ፍላጎት ስለ ሌላቸው ገበሬው እዳውን መክፈል ሲያቅተው ፤ የመሬት ባለቤትነቱን ወደ ራሳቸው ያዞሩ እና ገበሬዎቹን መሬቱ ላይ እንደ ጭሰኛ ጎልተው ፤ ገበሬዎቹ በልተው ከእሚያድሩት ውጭ ሌላውን በመውሰድ ፤ መሬቱ ላይ ምንም ዓይነት ኢንቨስትመንት እንዳይቻል ነው እሚያደርጉት።

በእዚኽ ላይ እንደ ገና እንግሊዞቹ ዘሚንዳርስ (Zamindars) ለእሚባሉ እና በእሩቅ ተቀምጠው (Absentee landlord) የመሬት ግብር ለእሚሰበስቡ ሰዎች የመሬት ባለቤትነት በመስጠት ሌላ ችግር

ፈጥረዋል። ምክንያቱም ፡- እነ እዚኽ የሩቅ ባላባቶች በጣም በርካታ መሬት ስለ እሚኖራቸው ፤ ካልካታ (Calcutta) እንደ እሚባሉት የህንድ ትልልቅ ከተሞች በቅንጦት እየኖሩ ፤ ከመሬታቸው ላይ ግብር የመሰብሰቡን ሥራ ለወኪል ይሠጣሉ ፣ ወኪሉ ለሌላ ወኪል ይሰጣል ፤ እናም በእዚኽ ኺደት ሰብ ኢንፊውዴሽን (sub-infeudation) እሚባል የግብር ሰብሳቢ ሰንሰለት ፈጥረዋል።

ይኽም የሩቅ ባላባቶች እና የግብር ሰብሳቢ ወኪሎች ሠንሠለት ፤ ምርታማነትን ማሳደግ ሳይሆን ጥቅምን መቆራመት ላይ ያተኮረ የጥገኛ ሰንሰለት ነው የሆነው። ምክንያቱም ኹሉም ድርሻውን ማስፋት ላይ ነው ትኩረቱ።

ከግብርና ምርት የእሚገኘው ትርፍም ፤ ግብርናውን ለማሳደግ መልሶ ኢንቨስት ከመደረግ ይልቅ ፤ እየተጨለፈ የከተማ ቅምጥል ህይወትን ለማስቻል ይውላል ፤ በእዚኽም ግብርናውን አቁሞ በማስቀረት መንደሮቹን ያደኸያል።

በእዚኽ ላይ ፤ እንግሊዞች መሬቱን ሲያከፋፍሉ ፤ መሬቱ በባሕላዊ መንገድ ፤ ለአንዱ የማረስ መብት ፣ እርሱ መከር ሲያነሳ ሌላው ከብት እንዲያስግጥበት ፣ ሌላው ደግሞ ጡብ እንዲሠራበት ፣ ወዘተ በማድረግ አንዱን መሬት በጋራ የእሚጠቀሙበት የባሕል አሠራር በነበረበት ኹኔታ ላይ ስለ ሆነ ፤ መሬቱን ቆራርጠው ያከፋፈሉት ፤ አብዛኛው የባለቤትነት መብት ከፍተኛ የሕግ ክርክር የነበረበት ነበር።

የሕግ ክርክሩም በፍርድ ቤት እስከ አስርት ዓመታት ሊቆይ ስለ እሚችል ፤ መሬቱን ባንኮች በዋስትና ለመያዝ እና ብድር ለመስጠት አይፈልጉም ነበር።

በእሚያሳዝን ኹኔታ ግን ሕንዶች ከእንግሊዝ ነጻ ከወጡም በኋላ ቢሆን ፤ የመሬት ሕጋቸው ትርጉም ያለው ማሻሻል ስለ አላደረገ ፤ የሕንድ መሬት ዛሬም ምርታማነትን መሠረት ባደረገ መልኩ ከባለቤት ባለቤት የመቀያየር አቅሙ የተዳከመ ነው።

ከነጻነት በኋላ ምክንያቱ ተቀየረ እንጂ መሬት በህንድ በጣም ዝቅተኛ ተንቀሳቃሽነት ያለው መሆኑ አልተቀየረም።

ከነጻነት በኋላ ፤ ሕንድ ገበሬዎችን ከብዝበዛ እና ከመሬት ንጥቂያ እከላከላለሁ በእሚል ፤ ሳታስበው የቀኝ ዘመኑን አቁሞ አስቀሪ ፖሊሲ ደግማዋለች ፤ በእሚከተሉት ኹለት ምክንያቶች ፡

- **<u>የመሬት ጣሪያ ሕግ</u>** ፡- በሕንድ ፥ አንድ ሰው ሊይዝ የእሚችለው የመሬት ስፋት ላይ ገደብ ስለ አለ ፤ በተግባር ኢንደስትሪያላይዝድ የሆነ ግብርና ለመሥራት የእሚያስፈልገው የመሬት ስፋት ሕገ ወጥ ተደርጓል።
- **<u>የገበሬ ድጎማ</u>** ፡- በጥቃቅን መሬት ላይ የእሚያርሱ የሕንድ ገበሬዎች በጣም ከፍተኛ መጠን ያለው የውኃ እና የኃይል ድጎማ ይደረግላቸዋል ፤ ከእዚኽም የተነሳ እነ እዚኽ ገበሬዎች ፤ ተወዳዳሪ አምራች ገበሬ ባይሆኑም በድጎማ በግብርና ላይ ይቆያሉ ይኽም የሕንድ ግብርና አድጎ ለኢንደስትሪ የእሚያስፈልገውን ካፒታል እና የሰው ጉልበት እንደ አይለቅ ስለ አደረገ ፤ ሕንድ የኢንደስትራላይዜሽን እድሏን እያባከነች ነው።

ሕንድ ፡- ገበሬዎችን በውድድር ከሚመጣ ሽንፈት በመከለል (Promoting farmer protection) እና ንብረት በምርታማነት መሠረት እንደ አይንሸራሸር በመከልከል ፤ ግብርናዋና ቆሞ ቀር በማድረግ የእራሷ መዋቅራዊ ሽግግር እንቅፋት ሆናለች።

### 2.2.4 ድምዳሜ

ቀጣይነት ያለው መዋቅራዊ ሽግግርን የእሚያስከትል የኢኮነሚ ዕድገት ከርዕዮት ጋር ያለው ቁርኝት ውስን ነው ፤ የራሳችን መንገድ በእሚል ግን በአሻን መንገድ ኼደን ልናሳካው የእምንችለው ነገር ግን አይደለም።

የንብረት ባለቤትነት መብት የግድ የሆነ ቅድመ ኹኔታ ነው ፡- ንብረትን በባለቤትነት የመያዝ እና በገበያ ውስጥ የመግዛት እና የመሸጥም መብት አብረው መኖርም አለባቸው።

ንብረት ፤ በፖለቲካ ትስስር ወይንም ውሳኔ (Political connections or decision ) ወይንም ከቤተሰብ ወደ ልጆች በውርስ ከመተላለፍ ይልቅ በምርታማነት መሠረት ሲተላለፍ ነው በአንድ ሐገር ዕውነተኛ መዋቅራዊ ሽግግር የእሚሳካው።

## 2.3 የሕጉ ነጻ እና ገለልተኛነት

(ነጻ እና ገለልተኛ ፍርድ ቤት ፣ የሕግ የበላይነት)

### 2.3.1 አሠራራ

በክህሎት ፣ በቅልጥፍና እና በፈጠራ ችሎታ ላይ የተመሠረተ የምርት ስረዓት ውጤታማ እንዲሆን ፤ የኢኮነሚ ስኬት በብቃት እንጂ በፖለቲካ ቅርበት (Proximity to power) ላይ እንደ አይመሠረት ይፈልጋል።

ይኽ ቅድመ ኹኔታ ደግሞ የንብረት ባለቤትነት መብት ሲረጋገጥ እና ንብረት እጅ የእሚቀይርበት አግባብ በምርታማነት መመዘኛ ላይ ሲሆን ብቻ አይደለም የእሚሟላው ነገር ግን የንግድ ልውውጥን የእሚዳኙት የሕግ ማዕቀፎች ለኹሉም የኢከነሚ ተዋንያን ያለ መድሎ ሲሠሩ ነው።

የንግድ ስምምነቶች በተጻፉበት አግባብ ተፈጻሚ ሲሆኑ ፣ የሕግ አወጣጦች ተገማች (predictable) ሲሆኑ ፣ የፍርድ ቤት ውሳኔዎች በፖለቲካ ስልጣን እና ትውውቅ አንጻር የእሚይለዋወጡ ሳይሆኑ ነው።

ገለልተኛ የፍትሕ ስረዓት ፤ በአንድ ኢኮኖሚ ውስጥ ፤ ኢኮኖሚያዊ ስኬት በተወዳዳሪ አምራችነት እንጂ በፖለቲካዊ ጥገኝነት ላይ እንደ አይመሠረት በማድረግ ፤ ኢኮኖሚያዊ አምራችነት አበረታቶች ኪራይ ሰብሳቢነት በመከላከል ፤ አንድ ትልቅ ሚና ይጫወታል።

ፍርድቤቶች ውሎችን (ኮንትራቶችን) በወጥነት በእሚያስከብሩበት ግዜ ፡-

- ሽያጩ ለማከናወን የእሚወጡ ወጭዎች ይቀንሳሉ (Transaction costs will decline) ፣

- ረዘም ያሉ ውሎች ለመዋዋል አስተማማኝ ኹኔታ ይፈጥራል ፣
- የንግድ ተቋማት ከቤተሰብ እና ከትውውቅ አጥር ወጥተው መተባበር ይችላሉ ፣
- አዲስ የእሚያድጉ ድርጅቶች ፤ ነባር እና ትልቅ አቅም ያላቸውን ድርጅቶች ፤ በተሻለ ምርት እና አሠራር ለመወዳደር ይችላሉ

እንደ እዚኽ ባሉ የኢከነሚ ስረዓቶች ውስጥ ፤ የፈጠራ ችሎታ ይሆናል አንድ የንግድ ተቋም በገበያ ውስጥ ያለውን የገበያ ድርሻ የእሚወስነው።

የተሻለ እና አሸናፊ ቴክኖሎጂ ይዞ የመጣ አንድ ትንሽ የንግድ ድርጅት ለማስፋፊያ የእሚሆን ካፒታል ለማግኘት እና ደካማ ተወዳዳሪዎችን አሸንፎ ከገበያ ለማስወጣት ይችላል ፤ ምክንያቱም ፦ ለምሳሌ ፦ ተወዳዳሪዎቹ ያላቸውን የትውውቅ መረብ በመጠቀም ብድር እንደ አያገኝ ሊያደርጉ የእሚችሉበት እድል ጠባብ ስለ እሚሆን።

ይኽም በኢኮኖሚው ውስጥ ተገማችነትን (Predictability) ይጨምራል ፤ አንድ ኢኮኖሚ ደግሞ ተገማችነቱ ከፍ ሲል ፤ ኢንቨስተሮች ረጅም ግዜ የእሚፈልጉ ትልልቅ ኢንቨስትመንት ወደ እሚፈልጉ መስኮች ለመግባት ያስችላቸዋል።

ቋሚ ካፒታል (Fixed Capital) ፣ ጥናት እና ምርምር ፣ እንዲሁም የአቅርቦት ሠንሠለት አዋጭ እሚሆኑት ፤ የእሚተዳደሩበት የሕግ መዋቅር በዘላቂነት አስተማማኝ ሲሆኑ ነው።

ይኸው አሠራር ብሔራዊ ኃብት በአግባቡ በሥራ ላይ እንዲውል የእሚያደርግ የባሕሪ ግዳጅ ያስከትላል። ብድር ፣ የንግድ ፈቃድ ፣ የመንግሥት ኮንትራቶች እና አስተዳደራዊ ፈቃዶች የእሚገኙበት አግባብ ግልጽ እና የእሚተዳደሩበት ሕግ የእሚወጣበት አግባብ አስማሚ በሆነ መንገድ ስለ እሚሆን ፤ ካፒታል ከፍተኛ አምራች ወደ ሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ይኼዳል።

እነ እዚኽ ውሳኔዎች ኹኔታዊ (Discretionary) ሲሆኑ ግን ፤ ካፒታል ፖለቲካዊ ትሥሥር እና ጥበቃ (Politically protected) ወደ አላቸው ብቻ ይኼዳል ፤ ተወዳዳሪ አምራች ሆኑ አልሆኑ።

የእዚኽ ዓይነቱ ልማድ ኢከነሚያዊ ውጤቱ በግዜ ኺደት እየዳጎለ (Cumulative) የእሚኼድ ነው።

የሕግ ሥረዓቱ ለኹሉም በእኩልነት የእሚሠራ እና ከመድሎ የጸዳ ሲሆን ፤ ደካማ አምራች የንግድ ድርጅቶች በውድድር ተሸንፈው ከገበያ እየወጡ ተወዳዳሪ አምራች የሆኑት እየተስፋፉ ይኼዳሉ ፤ በእዚኽም ኺደት በሐገር ደረጃ ፤ የመማረት ዕውቀት ጥራቱ ከእለት እለት እየላቀ ብቁ አፈጻጸም ማስመዝገብ ወደ እሚችልበት ደረጃ ይደረሳል።

የሕግ ሥረዓቱ ግን መድሎ ሲኖርበት ፤ ከፖለቲካው ጋር ትሥሥር ያላቸው (Politically connected) ድርጅቶች ውድድር እንደ አይነካቸው ይከለላሉ(They will be insulated)። በእዚኽም ግዜ ፣ ካፒታል እና ሠራተኛ በደካማ የማምረት ኺደት ውስጥ ታስሮ ይቀመጣል ፤ ይኽም መዋቅራዊ ሽግግርን ያዘገያል ወይንም ይከለክላል።

አሁንም በድጋሚ አንድ ልብ ሊባል የእሚገባው ነገር ፤ ወሳኙ ነገር ፤ በአንድ ሐገር ያለው የፖለቲካ ስረዓት ዓይነት አይደለም ይልቁንም ስረዓቱ ምንም ዓይነት ይኹን ምን ፤ በሥረዓቱ ውስጥ ሕግ ምርታመነትን በእሚያከብር አግባብ ያለ መድሎ ለኹሉም ይተገበራል የእሚል መተማመን የመፈጠሩ ጉዳይ ነው።

አንድ ሐገር በዴሞክራሲያዊ ወይንም በአምባገነናዊ ስረዓት ስር ሊሆን ይችላል ፤ በእዚያ ሐገር ያሉ የኢከነሚ ተዋንያን በምርታማነት መመዘኛ ሕጉ ለኹሉም በእኩል የእሚሠራ ከሆነ እና የመንግሥት የልማት ድርጅት ፣ ልማታዊ ባለኃብት ፣ ወዘተ በእሚል አንዱ ነጋዴ ከሌላው ነጋዴ የእሚለይ የሙብት እና የግዴታ ሳይኖር ሲቀር ፤ በእዚያ ኢኮኖሚ ውስጥ ውጤታማነትን የእሚወስነው ፤ የፖለቲካ ፖሊሲ (Political discretion) ሳይሆን ለኹሉም በእኩልነት በእሚሠራ የሕግ አግባብ ሲሆን ፤ ሰዎች ለረጅም ግዜ አቅደው ኢንቨስት ለማድረግ እና በሰፊው ለመተባበሩ በመነሳት ፤ ሐገራዊ ምርታማነትን ያሳድጋሉ።

**እንግዲኽ ከእዚኽ አንጻር ከአየነው ፤ የፍትሕ ስረዓቱ ነጻ እና ገለልተኛ መሆኑ ፤ በዋናነት የኃብት ዘብ ሳይሆን ይልቁንም የኢከነሚ ስኬት የሚወሰነው በምርታማነት ላይ የእሚሆንበትን ኺደት ወይም አሠራር ዘብ ነው የእሚሆነው።**

### 2.3.2 ታሪካዊ ማሳያዎች (የስኬት ታሪኮች)

#### *2.3.2.1 ታላቋ ብሪታንያ*

በእዚኽ ረገድ አንድ ትልቅ ምሳሌ ሊሆን የእሚችለው በታላቋ ብሪታኒያ( United Kingdom) በ18ኛው እና በ19ኛው ክፍለ ዘመን የተከናወነው የልማዳዊ ሕግ[3] ፍርድ ቤቶች (Common Law courts) ገለልተኛ መደረግ እና የንብረት ባለቤትነት ሙብት መከበር ናቸው።

---

[3] የልማዳዊ ሕግ (Common Law) የእሚባለው አሠራር ሕግ የማውጣትን ስልጣን ፤ ከሕግ አውጭ አካላት በተጨማሪ ለዳኞችም የእሚሰጥ እና ሕግ ወቅታዊ ቃና የእሚያላብስ አሠራር ነው። በእኛ ሐገር በአለው ሲቪል ሎው (Civil Law) በእሚባለው ስረዓት ዳኞች በዋናነት ሕግን የመተርጎም ድርሻ ያላቸው እና ሕጉ በአንድ ወቅታዊ ጉዳይ ላይ የእሚለው ነገር ከሌለ የተለያዩ የሐገር ውስጥ እና የውጭ አሠራር ልምዶችን መሠረት አድርገው ብያኔ ሊሰጡ ቢችሉም ፤ ይኽ ብያኔ ግን ከእዚያ በኋላ ለእሚፈጠሩ ተመሳሳይ ክሶች ወይንም ክርክሮች ገዢ ሕግ ሆኖ አይቀርብም። በልማዳዊ ሕግ (Common Law) በእሚባለው አሠራር ግን ዳኛው ፤ የተጻፈው ሕግ በአንድ ወቅታዊ ጉዳይ ላይ የእሚለው ነገር ከሌለ እና እነርሱ የተለያዩ የሐገር ውስጥ እና የውጭ አሠራር ልምዶችን መሠረት አድርገው ውሳኔ ካሳለፉ ፤ ያ ውሳኔ ፤ በሌላ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እስከ አልተሻረ ድረስ ፤ እንደ ሕግ ሆኖ ተመሳሳይ ጉዳዮችን ኹሉ ለመዳኘት እንደ ሕግ (Precedent) ሆኖ ያገለግላል። በዓለም ላይ በአለው ልምድ የንግድ ተቋማት እንደ እኛ ሐገር ካለው የሲቭል ሎው (Civil Law) ይልቅ የኮመን ሎውን (Common Law) አሠራር ይመርጡታል ፤ ምክንያቱም ፦ የሕግ ስረዓቱን እንደ ደረቅ የሕግ ማዕቀፍ ሳይሆን ከወቅቱ ኹኔታ ጋር እራሱን እያጣጠመ የእሚኼድ ተገማች (Predictable) እና አገናዛቢ (Adaptable) የሕግ ስረዓት አድርገው ስለ እሚያዩት። የኮመን ሎው (Common Law) አሠራር በሕዝብ ያልተመረጡ ዳኞችን ሕግ አውጭም ተርጓሚም በማድረግ አጓጉል ያጎላቸውል ሊባል ቢችልም ፤ በኮመን ሎው (Common Law) የእሚወጣው ሕግ ከፍ ባለው ፍርድቤት ሊሻር የእሚችል በእዚያ ካልተሻረም

ብዙ ግዜ የእንግሊዙ የኢንደስትሪ አብዮት የቴክኖሎጂ ልህቀት ውጤት ተደርጎ ቢቀርብም ፤ የኢንደስትሪው አብዮት በቀዳሚነት በቀዳሚነት የሕግ እና የፍርድ ስረዓት ለውጥ ውጤት ነበር። የንብረት ባለቤትነት ፣ የንብረት ተንቀሳቃሽነት ፣ የሕግ የበላይነት በሌለበት እና አምራችነት በእማይበረታታበት ምህዳር ውስጥ የቴክኖሎጂ መሻሻል በሐገር በቀልነት ሊኖር አይችልም ፤ ቢጀምርም እንኳን በስረዓቱ ተሸንፎ ይወድቃል።

ከ1688 በፊት በነበረው ግዜ ፤ የእንግሊዙ ንጉሥ የግል ንብረትን በአሻው ግዜ የመወረስ ፣ የተበደረውን ብድር ያለመክፈል ፣ ወይንም ለወዳጆቹ የብቸኛ ነጋዴነት (Exclusive monopolies) ፈቃድ የመስጠት ልማድ ነበረው።

የክብር አብዮቱ ከተደረገ (After the glorious revolution) እና የስምምነት ሕግ 1701 (Settlement 1701) የእሚለው ከተደነገገ በኋላ ፤ ዳኞች በሕይወት እስከ አሉ ድረስ በዳኝነት የእሚቆዩ መሆኑ እና ንጉሡ በውሳኔያቸው ስለ አልተደሰተ ብቻ ከስልጣን ሊያነሳቸው የእማይችል መሆኑ ተወሰነ። ይኽ በዕውነትም በትክክል ገለለኛ የሆነ የፍርድ ቤት ስረዓት ፈጠረ።

ይኽም ነጻ እና ገለልተኛ ፍርድ ቤት ፤ ከከወናቸው በርካታ ነገሮች አንዱ ወደ ንግድ ውስጥ ለመግባት ያለን የውሸት ገደብ (ለምሳሌ ፦ ተፈጥሯዊ ሳይሆን (Unnatural monopolies) በፖለቲካ ውሳኔ የተሰጠን ሞኖፖሊን (Monopoly)) ማንሳት ነበር።

በዳኞች ስያሜ ሕግ ለውጥ ምክንያት ፦ ንጉሡ በዳኞች ውሳኔ ስለ አልተደሰተ ብቻ ከስልጣን ሊያነሳቸው የእማይችል በመሆኑ ፤ ዳኞች የንጉሡን የስልጣን በትር ሳይፈሩ ፤ በንጉሡ የተሠጡ ፤ ከተፈቀዳላቸው በስተቀር በተወሰኑ የንግድ መስክ ላይ እንደ አይሠማሩ የእሚከለክሉ ንጉሣዊ ፈቃዶችን (Royal Patents) እና የብቸኛ ነጋዴነት ፈቃዶችን (Monopolies) ሕገወጥ አድርገው ማንሳት ቻሉ።

በእዚኽም ወደ መረጡት የንግድ መስክ የመግባት ጉዳይ የዜግነት መብት እንጂ ንጉሣዊ ችሮታ (Royal favor) እንደ አልሆነ በማሳየት ፤ አዲስ ድርጅቶች ወደ አሻቸው የንግድ መስክ መግባት እንዲችሉ መንገድ ጠረጉላቸው።

የፍርድ ቤቶች ነጻነት ፤ መንግሥት በአሻው ግዜ ሕጉን እንደ ፈለገ አድርጎ እንደ አይተረጉም ወይንም ብድር ተበድሮ አልከፍልም ማለት እንደ አይችል ስለ አደረገው ፤ የብድር ወለድ መጠን ዝቅም እንዲል አድርጓል ።

ብድር በቀላል ማግኘት ሲቻል ፤ ድርጅቶችን መግዛት እና ማሻሻል አብሮ ስለ ቀለለ ፤ በቀላሉ ወደ ንግድ መግባት እና መውጣት አብሮ ተመቻቸ። አንዱ ሙሰኛ ባለስልጣን ተነስቶ ንብረታቸው ላይ እንደ

---

*እንደ ፓርላማ ያለው ሕግ አውጭ አካል የመጨረሻው ሕግ አውጭ በመሆኑ ፤ በጉዳዩ ላይ ካስፈለገ ሕግ ማውጣት ስለ እሚችል አደጋው እሚያሰጋ አይመስልም።*

አሻው ማድረግ የእማይችል በመሆ ፤ ነጋዴዎች ብድር ወስደው ፋብሪካዎችን ለመገንባት መተማመናቸው ጨመረ።

### *2.3.2.2 አሜሪካ*

በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በአሜሪካ የተዋወቀው የጸረ ሞኖፖሊ ሕግ (Anti-Trust Law) ፤ ምን አልባት በዓለም ላይ ሊበራል ዴሞክራሲ (Liberal democracy) ሕግ የማውጣት እና የፍርድ ቤት ነጻነት ስልጣኑን በመጠቀም ፤ ኢኮኖሚውን በጉልበት ፤ ከጥቂት የባለኃብቶች መንጋጋ (Oligarchic Control) ውስጥ ፈልቅቆ በማውጣት ለኹሉም (Impersonal) ክፍት የሆነ የውድድር ሜዳ የፈጠረበት ፤ ዕውቁ ታሪክ ነው።

ከሞላ ጎደል ከ 1870s–1900 በነበረው ግዜ ፤ በአሜሪካ በጣም ከፍተኛ ኢንደስትሪያላይዜሽን የተስፋፋበት እና ብዙ ኃብት የተፈጠረበት ዘመን ቢሆንም ፤ በርካታ የሐገሪቱ ነዋሪ ግን ስር በሰደደ የኑሮ ደረጃ መበላለጥ ፣ የሙስና እና የብዝበዛ መጠን የእሚሰቃይ ስለነበር ፤ የወርቅ ልብጡ ዘመን (the Gilded Age) በመባል ይታወቃል።

በእዚኽ ዘመን ፤ አሜሪካ የጥቂት ባለኃብቶች ሐገር (oligarchic model) መስላ ነበር።

ሮበር ባረንስ[4] (Robber Barons) የእሚባሉ ጥቂት ባለኃብቶች ትልልቅ የነዳጅ ፣ የብረት እና የባቡር ካምፓኒዎችን ተቆጣጥረው ነበር። እነ እዚኽም ሌባ ባላባቶች ወይንም  ሮበር ባረንስ (Robber Barons) አዲስ እነርሱ ወደ ተሰማሩበት ንግድ ውስጥ ገብቶ ሊወዳደራቸው ያለን ነጋዴ አክስረው ከንግድ እሚያስወጡበት አሠራር ነበራቸው።

ለምሳሌ ፡- ስታንዳርድ ዖይል (Standard Oil) የእሚባለው የነዳጅ አምራች ድርጅት ፤ በጣም ከፍተኛ መጠን ያለው ነዳጅ ስለ እሚያጓጉዝ ፤ የባቡር ድርጅቶቹ ይፈልጉታል። ይኽንንም ተፈላጊነት በመጠቀም ለባቡር ድርጅቶቹ መደበኛ የማጓጓዣ ዋጋውን በመክፍል ነዳጁን ካጓጓዘ በኋላ ፤ የተወሰነውን እንዲመልሱለት (Rebate) ያስገድዳል በእዚኽም የማጓጓዣ ዋጋውን እንዲቀንስ ያደርጋል።

የባቡር ድርጅቶቹ የሌላ ነዳጅ አምራች ምርት ሲያጓጓዙም ፤ ከክፍያው ላይ አጋሩኝ ይላል። በእዚኽም በጠቅላላ ከፍተኛ የመጓጓዣ ዋጋ ቅናሽ በማግኘት ሌሎች ተወዳዳሪዎችን አክስሮ ከንግድ ያስወጣል።

እነ እዚኽን መሰል ድርጅቶች ፤ ከፍተኛ ኃብት ስለ አላቸው ፤ ሌሎች ተወዳዳሪዎች እስኪ ከስሩ ድረስ የዋጋ ቅናሽ የማድረግ እና ተወዳዳሪው ከስሮ ሲወጣ ፤ መልሰው ዋጋ የማናር ልማድም ነበራቸው።

[4] Robber Barons (ሮበር ባሮንስ) ማለት - Robber (ሌባ) Barons (ባላባት ዓይነት ማዕረግ) ሆኖ ፤ በቀጥታ ትርጉሙ ሌባ ባላባት ወይንም ሌባ ባለኃብቶች ማለት ነው።

ይኸንንም አሉታዊ የንግድ አሠራር ለማስቀረት የአሜሪካው የሕግ ማውጫ ምክርቤት ፤ የሸርማን ጸረ ሞኖፖሊ ሕግን (the Sherman Anti-Trust Act) አወጣ ፤ ሕጉ ግን ተፈጻሚነት እና ጉልበት ሊኖረው የቻለው ፍርድ ቤቶቹ ነጻ እና ገለልተኛ በመሆናቸው ነበር።

ነጻ እና ገለልተኛ የሆኑት ዳኞች ፡- አንድ ካምፓኒ ፤ በጣም ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ ውድድርን መግደል አለበት ወይስ የለበትም ብለው መበየን ነበረባቸው።

በእዚኽ ረገድ በጣም ታዋቂ የነበረው ክስ በ1911 ዓም የአሜሪካው መንግሥት (በአቃቢ ሕጉ በኩል) በኒው ጀርሲው የስታንዳርድ ኦይል ኮርፖሬሽን ላይ ያቀረበው ክስ (Standard Oil Co. of New Jersey v. United States (1911)) ነበር።

በውቅቱ ጆን ዲ. ሮክፌለር( John D. Rockefeller) የአሜሪካን የነዳጅ ማጣራት ንግድ 90% ተቆጣጥሮ ነበር። በእዚኽ መልኩ ሮክፌለር የገበያውን 90% መቆጣጠር የቻለው ግን በነጻ ገበያ ተወዳድሮ ሌሎቹን ስለ አሸነፈ ሳይሆን ፤ ይኸን የበላይነቱን ተጠቅሞ ወደ ነዳጅ ማጣራቱ ንግድ ሌላ ተወዳዳሪ እንዳይገባ ያደርግ ስለ ነበር ነው።

የመንግሥት አቃቢ ሕግም ይኸ ዓይነቱ ጸረ ውድድር ባሕሪ ሕገወጥ ነው በእሚል ክስ መሠረተ ፤ ክሱን የተመለከተው የአሜሪካው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፤ ምክንያተ ቢስ (“Unreasonable”) የንግድ ሞኖፖሊዎች (Monopolies) ሕገወጥ ናቸው ብሎ በየነ። ያንም ተከትሎ ስታንዳርድ ኦይል ( Standard Oil) የተባለው ካምፓኒ ወደ 34 የተለያዩ እና ነጻ የንግድ ካምፓኒዎች እንዲከፋፈል በፍርድ ቤት ታዘዙ። በኋላ ፡- ኤክሶን ፣ ሞቢል ፣ ቼቭሮን ፣ ወዘተ (Exxon, Mobil, Chevron) የሆኑት እነርሱ ናቸው።

ፍርድቤቱ በእዚኽ መልኩ ሞኖፖሊውን (Monopoly) በማፍረስ ፤ ሞኖፖሊዎቹ ፈጥረውት የነበረውን የንግድ ገደብ በማንሳት ተወዳዳሪዎች ወደ መስኩ እንዲገቡ አስቻለ። ከእዚኽም የተነሳ ፤ በድንገት አዳዲስ የንግድ ተቋማት ፤ በፖለቲካ ትውውቅ ወይንም በግዝፈት በማስፈራራት (Political or size-based bullying) ሳይሆን በቴክኖሎጂ እና በዋጋ መወዳደር የእሚችሉበት ምህዳር ተፈጠረ።

ይኸም የነዳጅ አምራች ኢንደስትሪዎች ፤ ነዳጅ ቆፍሮ ከማውጣት ባሻገር ወደ ኬሚካል ኢንጂነርንግ እና የነዳጅ ስርጭቱን በማሻሻል ላይ እንዲወዳደሩ አደረጋቸው። በእዚኽም ፡- በኬሚካል ኢንጂነሪንግ ወደ ፔትሮኬሚካሉ በመግባት ዘይት ቆፍሮ ከማውጣት ባሻገር ፡- ከነዳጅ ዘይት ፕላስቲክ ፣ የሌሎች ኢንደስትሪዎች ግብዓት ሊሆኑ የእሚችሉ ኬሚካሎች እና ሲንተቲክ ጎማ ወደ ማምረት ገቡ።

የፍትሕ ስረዓቱ በእዚኽ መልኩ ፤ የኢኮነሚ ስኬት የብቃት ውጤት (ኢመድሏዊ) እንጂ የትኛውን ባለስልጣን ታውቃለኽ ወይንም ሌላ ተወዳዳሪን የእሚገፋ የነባር ባለኃብቶች የጥቅም ትስስር ቡድን (Oligarchy) እንደ አይሆን በእሚያደርግበት ግዜ ፤ መላ ኢኮነሚው “ወጣት” ሆኖ ይቆያል።

#### *2.3.2.3 ደቡብ ኮሪያ*

በጣም በፍጥነት በእሚያድጉበት ወቅት ፤ እንደ ደቡብ ኮሪያ እና ታይዋን በአሉት ሐገራት ፤ መንግሥታቸው የኢከነሚ ሕጎች ነጻ እና ገለልተኛ መሆን እንዲችሉ አድርገው ነበር።

ይክም ማለት ፡- መንግሥታቱ ሰውየው ማነው የእሚለው ነገር ሳይገዳቸው ፤ የኢከነሚ ሽልማታቸውን በሰውየው የምርታማነት ልቀት ላይ እንዲደገፍ ማድረግ ችለው ነበር።

በእነ እዚኽ ሐገራት ፡- ብድር ፣ ድጎማ ፣ እና የላኪነት ፈቃድ ማግኛው መንገድ ግልጽ እና የእሚታወቁ ነበሩ። ነጋዴው የእሚጠበቅበትን የላኪነት ግቦችን (export targets) ካሳካ ይሸለማል ፤ ከተደነቃቀፈ እና ግቡን ሳያሞላ ከቀረ ፤ ድጋፍ ይቋረጥበታል።

እነ እዚኽ መንግሥታት ዘመድ አዝማድ እና ጓደኛቸውን ከማገዝ ይልቅ ፤ የንግድ ድርጅቶች በምርታማነት እንዲወዳደሩ ማድረግ ችለው ነበር። ይኽም እምቢአልሞትም (zombie companies) የእሚባሉ እና በሥራ ላይ የእሚቆዩት በድጎማ እንጂ በአትራፊነት ያልሆኑ የንግድ ድርጅቶች የሐገራቸውን ኃብት እንደ አይሰለቅጡ ማድረግ አስችሏቸዋል።

ፓርክ ቹንግሂ (Park Chung-hee) የእሚባለው የደቡብ ኮሪያ ፕሬዝዳንት አስተዳደር ፤ እንደ ሳምሰንግ እና ሃይንዳይ (Samsung or Hyundai)ያሉ ድርጅቶችን ሲደጉም ፤ ለካማፓኒዎቹ የተለየ ፍቅር ስለ ነበረው አልነበረም። አንድ የደቡብ ኮሪያ የንግድ ድርጅት ዝቅተኛ የወለድ መጠን ያለው ብድር ማግኘት የእሚችለው ጥሩ የኤክስፖርት አፈጻጸም ሲኖረውን እና ሲኖረው ብቻ ነበር።

አንድ የደቡብ ኮሪያ ድርጅት በዓለም ዓቀፍ ደረጃ መወዳደር ካልቻለ ፤ ከሌላ ከእርሱ የተሻለ ተወዳዳሪ ከሆነ ድርጅት ጋር እንዲዋኃድ (forced to merge) ወይንም ከስሮ እንዲወጣ ይገደዳል።

ይኽ ገለልተኛ የሆነ ጫና እነ እዚኽ ድርጅቶች ተወዳዳሪ ሆነው ለመቆየት አዳዲስ አሠራሮችን እና ፈጠራዎችን በብርኃን ፍጥነት ይዘው እንዲመጡ አደረጋቸው።

### 2.3.3 ዓይነተኛ የክስረት ታሪክ: ፍሊፐንስ

በአንጻራዊነት ፤ ፍሊፐንስ በሐገሪቱ ውስጥ ተመራጭ ወደ እሚባሉት የንግድ ዘርፎች ለመግባት የትልቅ ቤተሰብ አባል ወይንም የኃብታሞች መረብ ውስጥ መኖር ግድ በእሚያደርግ ፤ “የዘመድ (crony)” እና “የኃብታም ቡድንተኝነት (oligarchic)” ልማድ ኢኮነሚውን የእሚያንገላታበት ታሪክ ነው ያላት።

የፍሊፐንሱ መንግሥት ፤ የፍትሕ እና የአስተዳደር (ቢሮክራቲክ) ነጻ እና ገለልተኝነት ከማረጋገጥ ይልቅ ፤ ለተወሰኑ የሐገር ውስጥ ድርጅቶች ጥቅም ሲባል እነርሱ በሐገር ውስጥ የእሚያመርቷቸው ዕቃዎች ከውጭ በእሚገባ ዕቃ ውድድር እንደ አይገጥመው ከውጭ የእሚገባው ዕቃ ከፍተኛ ቀረጥ እንዲጣልበት ማድረግ እንደ እዚኽም በተወሰኑ መስኮች ላይ የብቸኛ ነጋዴነትን ፈቃድ(High tariffs on imports or exclusive licenses) ለተወሰኑ እና በኢልት (elites) ለተያዙ የሐገር ውስጥ ድርጅቶች መስጠት ውስጥ ገባ።

ይኽም እነእዚኽ ድርጅቶች ምንም ዓይነት የመወዳደር ግዴታ እንደ አይኖርባቸው ስለ አደረገ ፤ ማሽኖቻቸውን ወይንም አሠራራቸውን ለማዘመን ምንም መነሳሳት አልነበራቸውም። ትርፋማ ይሆኑ

የነበረው ብቃታቸውን በማሳደግ ሳይሆን ፤ የብቸኛ ነጋዴነት (Monopoly) ፈቃድ በመያዝ ስለ ነበር ፤ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ካምፓኒ (World-class companies) ከመሆን ይልቅ እምቢአልሞትም (Zombie) ካምፓኒ ሆኑ።

በ1970ዎቹ እና በ1980ዎቹ የነበሩት የኮኮናት እና የስኳር ፤ ኮሁዋንኮው (Cojuangco) እና ቤኔዲክቶ (Benedicto) ሞኖፖሊዎች ለእዚኽ ተጠቃሽ ምሳሌዎች ናቸው።

ለምሳሌ ፦ የኮከናት ኢንደስትሪውን ለማዘመን በእሚል ፤ የኮከናት ገበሬዎች ላይ በኪሎ የጥናት እና የምርምር ግብር ይጣልባቸው እና ይኽ ግብር ኢንደስትሪውን ለማዘመን ጥናት ይሠራሉ ፣ ዘመናዊ ማሽን በማስገባት የቴክኖሎጂ ሽግግር ያመጣሉ ፣ ወዘተ ለእሚባሉ ድርጅቶች ይሰጥ ነበር። ይኽ ልዩ ግብር እና የኮኮናት ንግድ ሞኖፖሊ ግን ፤ ዘመናዊ ግብርና እና ማሽን በማምጣት መስኩን ከማዘመን ይልቅ ፤ ኃብቱን ከገበሬዎች እየመጠጠ ፤ እነ እዚኽ የኮኮናት ንግድ ሞኖፖሊ በተሰጣቸው የንግድ ድርጅቶች ውስጥ ተሰግስገው ያሉ የመንግሥት ሰዎች ኪስ ነበር የእሚገባው።

ይኽ ዓይነቱ አሠራር መሥኩ ከዓለም ዓቀፍ ውድድር የእሚደርስበትን ጫና ማስቀረት ቢችልም መስኩን አቁሞ በማስቅረት እራሱን ማዘመን እንደ አይችል ነው ያደረገው።

### 2.3.4 መደምደሚያ

ዜጎች ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማግኘት ከፖለቲካው ጋር ጥገኛ ለመሆን ከመወዳደር ወጥተው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማግኘት በምርታማነት ላይ የተመሠረተ ውድድር ወደ ማድረግ የመሸጋገራቸው ጉዳይ የኢከነሚ ሕጎች በገለልተኛነት በመተግበራቸው ላይ ይደገፋል።

ኢኮነሚው የእሚገኝበት የሕግ ስረዓት ፤ እንደ ታላቋ ብሪታንያ ሊበራል ዴሞክራሲ ይኹን ወይንም እንደ ደቡብ ኮሪያ አምባገነናዊ ልማታዊ መንግሥት ይኹን ፤ ወሳኙ ነገር ፤ ገለልተኛ በሆነ መንገድ የኢከነሚ ሕግ እንደ እሚሠራ መተማመን በንግዱ ማሕበረሰብ ዘንድ መፈጠሩ ነው።

ውሎች በተጻፉበት አግባብ እንደ እሚፈጸሙ እና ሕግ እንዲሁም ደንቦች ዘላቂ በመሆናቸው ተገማችነት (Predictability) ሲኖራቸው ፤ ዜጎች ኢንቨስት ባደርግ የኢንቨስትመንት ወሮታዬን አገኛለኹ በእሚል መተማመናቸው ስለ እሚጨምር ኢንቨስት ለማድረግ ይበረታታሉ እንደ እዚኹም ለጉቦ እና ሙስና ለመሳሰሉ ነገሮች ወጪ ብዙ ስለማይኖር የመገበያየት ኺደት ውስጥ የተደበቁ በግልጽ የእማይነገሩ ወጪዎች አለመኖራቸውም ንግድን ያቀላጥፋል። (The "risk premium" on investment drops, transaction costs will also fall)።

ይኽም የንግድ ድርጅቶች ከቤተዘመድ እና ከትውውቅ መረብ ወጥተው ትርፍ ለማምጣት ረጅም ዘመን የእሚፈልጉ ኢንቨስትመንቶችን ለማድረግ እና ውስብስብ የአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ ለመግባት ምቹ ኹኔታን ይፈጥራላቸዋል።

የሕግ ስረዓቱ ፤ የንብረት ባለቤትነት እና ገቢያ የማግኘት ጉዳይ ከንጉሥ ወይንም ከሆነው የፖለቲካ ባለስልጣን የእሚሰጥ ችሮታ (favors) ከመሆን ይልቅ የኹሉም ዜጋ እኩል መብት መሆኑን በማረጋገጥ ፤ መንግሥት በእዚያ ሐገር ውስጥ የኢከነሚ ስኬት ማስመዝገቢያው መንገድ የፈጠራ እና የአፈጻጸም ብቃት እንጂ ወደ ፖለቲካ ስልጣን መጠጋጋት (proximity to power) አይደለም የእሚል አምራችነት (Meritocracy) የነገሠበት ማሕበረሰብ ይፈጥራል።

የፍትሕ ስረዓት ነጻ እና ገለልተኛነት ኢከነሚያዊ ፋይዳው ጎልቶ የእሚወጣው ፤ የኃብት አደላደል (Allocation of resources) ላይ በእሚያሳየው ጥንቃቄ ነው። ነጻ እና ገለልተኛ ስረዓቶች ፦ በአሜሪካው የጸረ ሞኖፖሊ ሕግ እንደ ሆነው በነጻ እና ገለልተኛ ፍርድ ቤት ይፈጸሙ ወይንም "ነብሮቹ" እንደ እሚባሉት ደቡብ ኮሪያ እና ታይዋን በአስተዳደር (ቢሮክራሲ) ይፈጸም ፤ ደካማ ምርታማነት ያላቸው ድርጅቶች ተሸንፈው እንዲወጡ እና ጠንካራ አምራቾቹ እንዲስፋፉ ያደርጋሉ።

በተቃራኒው ፤ በፊሊፕንስ ልምድ እንደ ታየው ገለልተኛ ያልሆኑ ስረዓቶች ፤ የፖለቲካ ትሥሥር ያላቸውን ጥቂት ምርጥ ድርጅቶች ከውድድር በመከለል ፤ እራሳቸውን ለማዘመን ምንም መነሳሳት የሌላቸው ሞኖፖሊዎችን ይፈጥራል።

በስተመጨረሻ ፤ ነጻ እና ገለልተኛ ስረዓት ፤ የኢኮኖሚ ሕጎች ለኹሉም ዜጎች በእኩልነት እንዲተገበሩ በማድረግ ዜጎችን በማምረት አቅማቸው እንዲወዳደሩ እና በእዚኽም የውድድር ምህዳር ውስጥ የማፍረስ እና አዲስ የመፍጠር (Creative destruction) ኺደት በመፍቀድ ፤ አንድ ኢኮነሚ "ወጣት" እና በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆን ያደርጋል ፤ በኺደቱም ኃብት የምርታማነት እንጂ የፖለቲካ ጥገኝነት (Political loyalty) ውጤት እንደ አይሆን ያደርጋል።

## 2.4 ለልውውጥ እና ውድድር አመቺ የሆነ የንግድ ክፍትነት

(የገቢ/ወጪ ንግድ & የገበያ ውድድር)

### 2.4.1 አሠራር

ታዳጊ የሐገር ውስጥ ኢንደስትሪዎችን ከውጭ ውድድር መከላከል ወይንም ሐገር የሌሎች ሐገራት ሸቀጥ ማራገፊያ እንደ አትሆን ማድረግ ፤ ጥሩ የእሚባል ብሔርተኛ የኢንደስትሪ ፖሊሲ ሊመስል ይችላል። ሆኖም አንዲት ሐገር የንግድ ክፍትነት (Trade openness) በማረጋገጥ የውጭ ምርቶች ወደ ሐገር ውስጥ ገብተው በሐገር ውስጥ ከእሚመረቱ ምርቶች እና የውጭ ሐገር ኩባንያዎች ሐገር ውስጥ ገብተው ከሐገር ውስጥ ኩባንያዎች ጋር እንዲወዳደሩ በእሚደረግበት ግዜ ፤ ጉዳዩ ርካሽ የውጭ ሐገር ሸቀጦችችን የመፍቀድ ወይንም በሐገር ድርጅት ላይ ተወዳዳሪ የውጭ ድርጅት ማስገባት ብቻ ሳይሆን ፤ የሐገር ውስጥ ምርቶች እና ኩባንያዎች ከውጭ ሐገር ምርቶች እና ኩባንያዎች ጋር ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የማስገደድ እና በእዚኽም ኺደት በሐገር ደረጃ ጥራትን እና ተወዳዳሪነትን ዓለም ዓቀፋዊ የማድረግ ግዴታ የእሚፈጥር በመሆኑ ፤ የንግድ ክፍትነት (Trade openness) በዘላቂ ፋይዳው ፤ ከንግድ መዘጋት ይሻላል።

የተከላካዮቹ (The protectionist) ሙግት አዳጊ የእሚመስለው ፤ ከውጭ ሐገር ምርቶች እና ኩባንያዎች ውድድር ከለላ ማግኘት የሐገር ውስጥ ኩባንያዎች አቅም ገንብተው ተወዳዳሪ መሆን እንዲችሉ ግዜ ይሰጣቸዋል ፤ በሌላ አገላለጽ ፦ የንግድ በር እምነዘጋው ፤ ሐገራዊ ድርጅቶች ጎልበተው ተወዳዳሪ እስኪሆኑ ፤ ውድድርን ለማስቀረት ሳይሆን ለማዘግየት ነው በማለት የፖሊሲ አማራጩን መልካም ጎን ብቻ ስለ እሚያሳይ እና ፖሊሲው የእሚስከትላቸውን ከእዚኽ በታች የተዘረዘሩትን ዘርፈ ብዙ ጉዳቶች ፦

- የአንጻራዊ ጥቅሞች መሸርሸር ፣
- ዓለም ዓቀፍ ውድድርን ተቋቁሞ ለመኖር የእሚያስፈልገውን ፈጠራ ለማምጣት ግዴታ ማስቀረት ፣
- የዓለም ዓቀፍ ገበያን ለማስፋፊያነት እና ለዓይነት ብዛት የመጠቀምን እድል ማጥፋት ፣
- ተሸጋጋሪ የግብዓት ዋጋ ግሽበት የእሚያስከትለውን የዋጋ ንረት በሌሎች እነ እዚያን ግብዓቶች በእሚጠቀሙ ምርቶች ላይ ያለውን የዋጋ መናር፣

ችግር ስለ እሚሰውር ነው።

ከእዚኽ በታች ፤ የንግድ ክፍትነት (Trade openness) የተሻለው አማራጭ ነው የእሚለውን ለማሳየት እና ተከላካይነት (Protectionism) የእሚያስከትላቸውን ጉዳቶች ለማብራራት ፤ ተከላካይነት (Protectionism) የእሚያስከትላቸውን አራቱን ችግሮች በዝርዝር ዕንመልከት ፦

## 1. የአንጻራዊ ጥቅም ኃይል

የንግድ ክፍትነት አስፈላጊነትን የእሚያጎላው ቀዳሚው ነገር አንጻራዊ ጥቅም ነው። ምንም እንኳን አንድ ሐገር የማምረት ልዕለ ኃያል ሆና ኹሉንም ነገር ከጎረቤት ሐገሮቿ በተሻለ ኹኔታ ማምረት ብትችልም ፤ ኹለቱም ሐገራት ይበልጥ ተጠቃሚ የእሚሆኑት ፤ ኹለቱም ሐገራት በአንጻራዊነት በተሻለ በእሚያመርቱት ምርት ላይ ሲያተኩሩ ነው።

ምንም እንኳን የማምረት ልዕለ ኃያል የሆነችው ሐገር ፤ ማይክሮቺፑንም ካኔቴራውንም ከየትኛውም ሐገር በላይ በርካሽ እና በጥራት ማምረት ብትችልም ፤ ያላትን ግዜ የትኛውን ምርት ለማምረት እንደ እምታውል መምረጥ አለባት።

እያንዳንዷ ካናቴራ ለመስፋት የእምታጠፋው ሰዓት ማይክሮ ቺፕ እማታመርትበት ሰዓት ነው።

ጎረቤቷ ሐገር ካኔተራ ስታመርት ጥራቱ እና ዋጋው እንደ ነገሩ ቢሆን እና ማይክሮቺፕ ስታመርት ደግሞ ውዳቂ የሆነ ማይክሮቺፕ የእምታመርት ከሆነ ፤ ጎረቤት ሐገሯ ማይክሮ ቺፑን ትታ ካኔተራው ላይ ብታተኩር ይሻላታል። ይኽም የማምረት ልዕለ ኃያል (Super-Country) የሆነችውን ሐገር ሙሉ ትኩረቷን ማይክሮቺፕ ላይ እንደታደርግ ያደርጋታል።

እንዲኽ በማድረጋቸው ፤ የማምረት ልዕለ ኃያሏ ሐገር ብዙ ካኔተራ ታገኛለች ምክንያቱም ውዱን ሰዓቷን ካኔተራ ከመስፋት ይልቅ ማይክሮቺፕ ማምረት ላይ ስለ አዋለች ፤ በተመሳሳይ ጎረቤት ሐገሯም ማክሮቺፕ የማምረት አቅሟ ውዳቂ ቢሆንም ብዙ ማክሮቺፕ ማግኘት ያስችላታል።

በእዚኽ መልኩ ኹለቱም ሐገራት በአንጻራዊ ጥንካሪያቸው ላይ ብቻ በማተኮር ፤ በተናጠል ማምረት ከእሚችሉት በላይ በርካታ ምርት ማግኘት ይችላሉ።

በእዚኽ መልኩ ሐገራት በአንጻራዊነት የተሻለ ምርታማ የእሚሆኑበት ምርት ላይ በማተኮር ፤ ውድ ግዜያቸውን ደካማ የሆኑበትን ነገር ላይ ከማባከን ይድናሉ (lowered opportunity cost)።

ይኽም ዓለም ዓቀፍ ብቃትን ያሳድጋል ፤ ያም ዓለም ዓቀፍ ምርታመነትን ይጨምራል ፤ ያም በጽንሰ ኃሳብ ደረጃ ፤ የኹሉንም ኃብት ይጨምራል።

## 2. ውድድርን ተከትሎ የእሚመጣ የፈጠራ ዕድገት

ተከላካይነት (Protectionism) ብዙ ግዜ ዕድገትን አፍኖ የእሚይዝ የደህንነት ሽፋን ("Security blanket") ይሆናል።

አንድ የሐገር ውስጥ ድርጅት ከውጭ ውድድር ከለላ ሲያገኝ ፤ አዲስ ፈጠራ የመፍጠር ተነሳሽነቱ ይቀንሳል።

በአንድ ሐገር የንግድ ክፍትነት ሲኖር ፤ የሐገር ውስጥ የንግድ ድርጅቶች ፤ ወድድሩን ተቋቁመው ለመቀጠል ፤ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን እና የአስተዳደር ልምዶችን የመጠቀም ግዴታ ስለ እሚጋረጥባቸው ፤ ተጎትተውም ቢሆን በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የአስተዳደር ልምድን መከተል እና ዘመናዊ ቴክኖሎጂን መጠቀም ይጀምራሉ ።

ንግድ ማለት ሸቀጥን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ማዘዋወር ማለት ብቻ አይደለም ፤ ከሸቀጡ ጋር አብሮ ኃሳቦችም ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ይዘዋወራሉ።

ክፍት የሆኑ ገበያዎች የአዕምሮ ፈጠራዎች (Intellectual property) እና ቴክኒካዊ ዕውቀቶች ከድንበር ድንበር በፍጥነት እንዲዛመቱ በማድረግ ፤ የቴክኖሎጂ ስርጸትን ያስችላሉ።

## 3. ግዝፈት እና ዓይነት (Scale and Variety)

ለብዙ ኢንደስትሪዎች ፤ ከግዝፈት የእሚገኘውን እንደ ዋጋ ማርከስ መቻል (to achieve Economies of Scale) ያሉ ግቦችን እንዲያሳኩ የሐገር ውስጥ ገበያ ብቻ በቂ አይሆንም።

በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ንግድን ማግዘፍ የምርትን ዋጋ በአሀድ ደረጃ ለመቀነስ ያስችላል ፡ ትልልቅ ካምፓኒዎች ለመላው ዓለም በመሸጥ ፤ አዲስ አውሮፕላን ወይንም መድሀኒት ለማምረት የእሚያደርጉትን ወጪ ፤ በብዙ ሚልዮን በእሚቆጠረው የዓለም ዓቀፍ ደንበኞቻቸው ላይ በማከፋፈል ፤ የአሀድ የመሸጫ ዋጋቸውን ለመቀነስ ያስችላቸዋል።

የንግድ ክፍትነት ሸማቾች የምርት ምርጫ እንዲኖራቸው ያስችላል ፤ በመሆኑም ለንግድ ክፍት መሆን ከዋጋ ባሻገርም ፤ ምርጫን የማስፋት እድል ይሰጣል።

ዜጎች ምንም በእማያወላዳ መልኩ የሐገራቸው ድርጅቶች ብቻ ከእሚያመርቱት ውጭ ፤ ሌሎች የውጭ ሐገር ድርጅቶች የእሚያመርቷቸውን ምግብ ፣ የኪነ ጥበብ ሥራዎች ፣ እና ቴክኖሎጂ ማግኘት ሲችሉ ፤ ሕይወታቸው የተሻለ ምቾት ይኖረዋል።

### 4. የግብዓት ሙግት ( ስውሩ የተከላካይነት ክፍያ - Hidden cost of protectionism)

የሐገር ውስጥ ኢንደስትሪዎችን ከውጭ ተወዳዳሪዎች እንከላከል የእሚለው ፖሊሲ አንዱ ትልቁ ስህተቱ ፤ የአንዱ ኢንደስትሪ ምርት የሌላው ኢንደስትሪ ግብዓት የመሆኑን ነገር መዘንጋቱ ነው።

ለምሳሌ ፦ አንድ መንግሥት የሐገር ውስጥ ብረት አቅላጭ ድርጅት ለማገዝ በእሚል ከውጭ ሐገር የእሚገባ የብረት ምርት ላይ ታሪፍ ከጣለ ፤ በእዚያኸ ሐገር የመኪና አምራቾች እና የኮንስትራክሽን ካምፓኒዎች ላይ የብረትን ዋጋ በጣም ውድ አደረገባቸው ማለት ነው።

ታሪፍን በማንሳት የንግድ ስረዓቱን ክፍት ካደረገው ግን የግብዓቶች ዋጋ የዓለም ዓቀፍ ዋጋ ስለ እሚሆን ፤ ግብዓቶችን የእሚጠቀሙ የሐገር ውስጥ ካምፓኒዎች በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ይሆናሉ።

ስለ እዚኽ ፦ የንግድ ክፍትነት ሸቀጥ የማስገባት እና የማስወጣት ጉዳይ ብቻ ስለ አልሆነ ነገር ግን በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የምርት ብቃት እና የፈጠራ ሞተሩን የማሳደግ ጉዳይ ስለሆነ ፤ ከንብረት ማዘዋወር መብት ጋር ተያይዞ አንዲት ሐገር የመካከለኛው ገቢ ወጥመድ የእሚባለውን ወጥመድ ሰብራ ፤ ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ሐገራት ተርታ መመደብ የመቻሏን እና ያለመቻሏን ነገር ይወስናል።

### 2.4.2 ታሪካዊ ማሳያዎች (የስኬት ታሪክ)

በመቀጠል ጃፓን ፣ ቻይና እና ህንድን ምሳሌ አድርገን ፤ በንግድ ክፍትነት ላይ ያላቸው አቋም የኢኮነሚያቸውን መዋቅራዊ ደረጃ እንዴት እንደወሰነው ዕንይ።

### *2.4.2.1 ጃፓን*

ጃፓን በተመረጠ የፖሊሲ አተገባበር የኢከነሚ ኃያል ሆና የተነሳችበት አግባብ ትልቅ ትምሕርት ነው (A masterclass in strategic adaptation) ።

ሌሎች ሐገራችንን እናዘመን በእሚል ደም አፋሳሽ አብዮት ውስጥ ሲዘፈቁ ፤ ሌሎቹ ደግሞ በትላልቅ መጽሐፍ ተቀብረው መውጫው ሲጠፋቸው ፤ ጃፓን ለየት ያለ መንገድ በመከተል ፤ በታቀደ ኩረጃ (Planned window shopping) ከፍተኛ ብሔራዊ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ማሳካት ችላለች።

ይኽንንም ለማድረግ ፤ የተመረጠ የጥናት እና የኩረጃ ቡድን አዘጋጅታ ወደ ሰለጠነው ዓለም በመላክ ፤ በዓለም ላይ አለ የእሚባለውን ምርጥ ልምድ ለመቅሰም ሠራች – ከእዚያም የፕራሺያን የአገዛዝ ስልት እና የእንግሊዝን የኢንደስትሪ ልምድ ለሐገሬ እሚበጀው እሱ ነው በእሚል የራሷ አደረገችው።

ይኽን ለማድረግ ትልልቅ ዩኒቨርስቲ እስኪነገቡ ወይንም ጎዳናዎቻቸው በአብዮት ደም ቀይ እስኪሆኑ መጠበቅ አልነበረባቸውም ወይንም አላስፈለጋቸውም። ይልቁንም ፦ የምዕራቡን ዓለም ኤክስፐርቶች አስመጡና ፤ ኒኮል ማክያቬሊ ንጉሥ ምክር ሰምቶ ከተቀበለው ምክሩ የእራሱ ይሆናል ያለውን ተከትለው ፤ እነ እዚኽ ምዕራባዊያን አማካሪዎቻቸው የእሚሰጧቸውን ምክሮች ከእራሳቸው ጋር በማዋኃድ የእራሳቸው አደረጉት።

ውጤቱም ጃፓን እንደ እንቁራሪት በመዝለል ፤ ምዕራባዊያን 300 ዓመት የፈጀባቸውን ጃፓኖቹ በ50 ዓመት በማጠናቀቅ ፤ከፊውዳሊዝም ወደ ካፒታሊዝም ከሞላ ጎደል ያለ ምንም ደም ተሸጋገሩ ፤ ።

የጃፓን ለውጥ እንድ ተራ ለውጥ አልነበረም ፤ ይልቁንም በመዋቅራዊ ሽግግር ከአንድ ኋላ ቀር ዘመን ወደ አዲስ ዘመን በመሻገር መዋቅራዊ ነበር ። ያለምንም ደም !

የጃፓኖቹ የኩረጃ ጉዞ (Window shopping) ምሁራንን እና የእንፋሎት ሞተር በማምጣት ብቻ የተወሰነ አልነበረም ፤ አብረውም ተግባራዊ ፖሊሲዎችን/መመሪያዎችንም አምጥተው ነበር።

በእዚኽ መልኩ ይዘው ከመጡት ተግባራዊ መመሪያዎች ዋናው (Hallmark) የ1873 የመሬት ግብር ማሻሻያ ነው። ጃፓኖች የምዕራቡ ዓለም የመንግሥትን ገቢ የእሚፈጥርበትን መንገድ ካዩ በኋላ ፤ የመንግሥትን ገቢ እንደ ሰለጠነውም ዓለም ለማድረግ ፤ ፊውዳላዊ የግብር አሰባሰቡን በካፒታሊስታዊ የግብር አሰባሰብ መተካት እንደ አለባቸው በመወሰን ካፒትሊስታዊ የግብር አሰባሰብ ውስጥ ገቡ ፤ ያም ፊውዳሊዝምን ሽሮ ካፒታሊዝምን ማቆም ሆነ።

በእዚኽም መሬትን የግል ንብረት በማድረግ ፤ እንደ ፊውዳሉ ዘመን ግብር በሩዝ ከእሚከፈል ይልቅ ከእያንዳንዱ ገበሬ በገንዘብ እንዲከፈል በማድረግ ፤ ጠንካራ የመንግሥት ገቢ ፈጠሩ። ይኽ አንድ የፖሊሲ ለውጥ አልነበረው ፤ ስረ ነቀል የሆነ የስረዓት ለውጥ ነበር።

ገበሬዎች ድሮ በጭሰኝነት ያርሱ የነበረውን መሬት አሁን በባለቤትነት ይዘው ማረስ መቻላቸው እያስደሰታቸው መስኖ እና ማዳበሪያ ላይ ኢንቨስት በማድረግ ምርታቸውን በከፍተኛ ደረጃ አሳደጉት። በእዚኽ ኹኔታ ግብርናው የፈጠረው ትርፍ ፤ በገበያው ውስጥ የካፒታል መጠንን በማሳዳግ ፡- ባቡር ፣ ፋብሪካዎች እና ዘመናዊ ጦር ለመገንበት ትልቅ የገንዘብ አቅም ፈጠረ።

ያ እንግዲኽ የ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ የጃፓን ታሪክ ነው ፤ ወደ 20ኛው ክፍለ ዘመን ከ2ኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ስንመጣ ፤ በሐገሪቱ ቅድሚያ የእሚሰጠው ተስተካካይ ዕድገት(Catch Up Growth) ማድረግ ሳይሆን ፖለቲካዊ ህልውና ሆነ። ከኹለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቃት በኋላ ጃፓን በአሜሪካ ወታደራዊ አስተዳደር ስር በቆየችበት ወቅት ፤ የኮሚንስት እንቅስቃሴን መፍራት ፤ መሬትን የምርት መሣርያ ከመሆን ይልቅ ማሕበራዊ መረጋጋትን ማምጫ ተደርጎ ተወሰደ።

ታማኝ የሆነ ፤ ለኮምኒስቶች ማባበያ የእማይታለል ሰፊ የምርጫ ድምጽ እሚሰጥ የሕበረተሰብ ክፍል ለማግኘት መንግሥት መሬት ከትልልቅ ባለ መሬቶች በግድ እየተወሰደ (በግዢ) መሬት ለእሚፈልጉ እንዲከፋፈል በማድረግ ፤ አዲስ ትናናሽ መሬት የእሚያርሱ በርካታ ገበሬዎች ፈጠረ።

በእዚኽም የጃፓኑ ሊበራል ዴሞክራቲክ ፓርቲ (Liberal Democratic Party - LDP) ፤ ታማኝ የሆኑ የምርጫ ድምጽ የእሚሰጡት የሕበረተሰብ ክፍል በማግኘት ስልጣኑን አደላደለ ፤ በእዚኽ አካኼድ ኢኮኖሚያዊ ውጤታማነትን በፖለቲካዊ መረጋጋት ለወጠ ማለት ነው።

ጃፓን ከግብርና በውድድር ተሸንፈው የእሚወጡ ገበሬዎችን ፤ የኢንደስትሪ እና የአገልግሎት መስኩን በማሳደግ እዚያ ውስጥ እንዲቀጠሩ ከማድረግ ይልቅ ፤ ትልልቅ ድጎማ እና ከፍተኛ የታሪፍ ከለላ በመስጠት ፤ ደካማ ምርት የእሚያመርቱ ገበሬዎች በእርሻቸው ላይ እንዲቆዩ አደረጉ።

ይኽ የተከላካይነት ጉንፋን (Protectionist fever) በአጭር ግዜ ሌላውን የኢኮኖሚ ክፍልም ይነካ ጀመር። ማሕበራዊ መረጋጋትን የእሚያስችል ታማኝ ደጋፊ ለማግኘት ፤ የጃፓኑ መንግሥት የአግልግሎት እና የባንክ ዘርፉን ተመሳሳይ ከለላ (Extended its shield) አደረገለት፡

- **የችርቻሮ ንግድ እና ትራንስፖርት:** የሞያ ማሕበራት በእሚመስል አግባብ አደርጅቶ ፤ የትናንሽ ሱቆችን ባለቤቶች ካለም ዓቀፍ ውድድር ከለላ ሰጣቸው ፤ በእዚያ ኺደት ግን ሸማቾች ላይ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት አመጣ።

- **ባንኮች:** ከኹለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የመጣው የጃፓኑ መንግሥት ባንኮችን እንደ ትርፍ አትራፊ የንግድ ተቋማት አድርጎ አልወሰዳቸውም ይልቁንም አንድ የመንግሥትን የኢንደስትሪ ፖሊሲ ማስፈጸሚያ ተቋማት እንደ ሆኑ አድርጎ ነው ያያቸው። ባንኮቹን በፖሊሲ ለተመረጡ እና ከሌሎች ተወዳዳሪዎች በተለየ አሠራር ለተከለሉ የንግድ ድርጅቶች ርካሽ ብድር አቅራቢ ነው ያደረጋቸው።

ለእዚኽ ፖለቲካዊ ታማኝነት ለመግዣ የዋለው ጉቦም እያደር ብዙ ጣጣ ይዞ መጣ።

በእዚኽ መልኩ ባንኮቹ ውድድር አልባ በሆነ ኢከነሚ ውስጥ በፖሊሲ ለተመረጡ እና ፖለቲካዊ ትሥሥር ላላቸው ፤ በምርታማነት እና በተወዳዳሪነት ግን በጣም ደካማ ለሆኑ የንግድ ድርጅቶች ፤ ከፍተኛ መጠን ያለው ብድር ስለ አበደሩ ፤ በ1980 በጃፓን የተፈጠረውን ከፍተኛ የሆነ የንብረት ዋጋ ንረት አስከተሉ።

ምክንያቱም ፡- መንግሥት የተመረጡ መስኮች እያለ ርካሽ ብድር ይሰጣል ፤ ብድሩ የተሰጣቸው ግን ገንዘቡን ለማስፋፊያነት ከመጠቀም ይልቅ ፤ ይበልጥ አትራፊ ለእሚያደርጋቸው የሪል ስቴት እና የስቶክ ግዢ ውስጥ ይገባሉ ፤ ይኽም የንብረቶች የተጋነነ ዋጋ (Asset Bubble) እና ግሽበትን አስከተለ።

አላግባብ ዋጋቸው የጋሸበው እንደ ቤት ፣ ህንጻ ፣ ሼር ፣ ወዘተ ያሉት ንብረቶች ግዢ አጥተው ዋጋቸው ሲወድቅ እና ገበያው ሲተራመስ ፤ ኢኮኖሚው በገበያ ሕግ መሠረት ኪሳራን ቆርጦ መጣል ስለ እማይችል ምክንያቱም በፖሊሲ ማበደሩንም ማቆም ስለ እማይችል እና ላቁም ቢሉም የክስረቱ መጠን ከፍተኛ በመሆኑ ፤ የማገገም ኺደቱ በጣም ቀርፋፋ እና እስከ አሁንም በአግባቡ አገግሟል እማይባል አደረገው።

የ1873 የጃፓን ጥበብ በሐገራቸው አብዮታዊ (ስር ነቀል) የሆነ ለውጥ ለማድረግ ፤ የኩረጃ ሉዑክ መላክ እና የምዕራቡን ዓለም ኤክስፐርቶች መጠቀም ነበር። የ20ኛው ክፍለ ዘመን ስህተታቸው ደግሞ ይኼንኑ ስልት ፤ በሐገራቸው ስር ነቀል ለውጥ እንደአያመጣ መግታታቸው ነው።

ዛሬ የጃፓን የግብርና እና የአገልግሎት መስክ ከእሚደረግለት ከለላ (Protection) የተነሳ በጣም ውድ ፣ ወጥነት የሌለው እና ስብርብር የሆነ ደካማ መስክ ሆኗል - በአጭሩ ጃፓኖች ፖለቲካዊ ታማኝነት ለማግኘት የእሚከፍሉት የኢከነሚ ዋጋ ሆኗል።

ይኽ ሲባል ግን የጃፓን ተከላካይነት (Protectionism) በኹሉም መስክ የስንፍና ቀላቢ ሆኗል ማለት ግን አይደለም ፤ ምክንያቱም ፡- ይኽ ተከላካይነቱ ለሐገር ውስጡ ገበያ የማሕበራዊ ዋስትና አጥር ሲሆነው ፤ ለሐገሪቱ የኤክስፖርት መስክ ግን በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የክህሎት (High-stakes meritocracy) ማረጋገጫ ነው የሆነው።

ጃፓኖቹ የሐገር ውስጡን ኢንደስትሪ በእዚኽ መልኩ ከውድድር ሲከላከሉ ፤ የኢክስፖርት መስኩን ግን ፤ በጣም ጠንካራ የሆነ የዓለም ዓቀፍ ተወዳዳሪነት ግዴታ ነው የጫኑበት።

አንድ በመንግሥት የእሚደጎም ኤክስፖርት የእሚያደርግ ካምፓኒ በዓለም ዓቀፍ ገበያ ውስጥ ድርሻ አግኝቶ ማሸነፍ ካልቻለ ፤ መንግሥት የእሚሰጠውን ድጎማ ያነሳበታል።

ይኽም እንደ ቶዮታ እና ሶኒ ያሉ ካምፓኒዎች ፤ የሐገራቸውን ገበያ እንደ መለማመጃ በመጠቀም ፤ እራሳቸውን በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለማድረግ እንዲጠቀሙበት እድል ሰጥቷቸዋል።

ይኽም ስልታዊ ከፊል የንግድ ክፍትነት ፤ ጃፓንን በዓለም ዓቀፍ ደርጃ ተወዳዳሪ የሆነች የኤክስፖርት ንግድ ማዕከል አደረጋት።

ሆኖም ይኽ ባለሁለት መልክ ኢኮኖሚ (Dual Economy) ፈጠረ። በአንድ በኩል እጅግ በቁ እና በዓለም ዓቀፍ ደረጃ አሸናፊ የሆነ ኤክስፖርተሮች። በሌላ በኩል ደግሞ ፤ እጅግ የተከለለ እና ቆሞ የቀረ የሐገር ውስጥ ሴክተር ፦ ግብርና ፣ አገልግሎት ፣ እና ኮንስትራክሽን ፤ ምክንያቱም እነ እዚኽ የኋለኞቹ ለውድድር ተጋልጠው እራሳቸውን እንዲዘምኑ ስለ አልተገደዱ።

እናም የጃፓን የኢኮነሚ ታሪክ ፤ እነ እዚኽ እጅግ ምርትማ የሆኑ ኮከብ የኤክስፖርት መስኮች እነ ሞትእንቢ (Zombies) የሆኑትን ደካማ ምርታማነት ያላቸውን ግብርና ፣ አግልግሎት እና ግብርና መስኮች የእሚጎትቱበት ነው የሆነ።

ጃፓን የውስጥ ኢንቨስትመንት እና የውጭ ተወዳዳሪ እጥረት ስለ አለበት እንደ ግብርና ፣ አገልግሎት እና ኮንስትራክሽን ባሉ የሐገር ውስጥ መስኮች ፤ ይኽን የደካማ ምርታማነት ልምድ ሰብሮ በአዲስ ተወዳዳሪ እና አምራች ድርጅቶች መተካት የእሚቻልበት እድል የለም።

ውጤቱም ወደ 20 ዓመታት የእሚጠጋ በጣም ዝቅተኛ የሆነ የኢኮነሚ ዕድገት ነው።

የጃፓን ጉዞ የእሚያሳያን ነገር ቢኖር ፤ ስልታዊ ከለላ (Strategic protection) በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ድርጅቶችን ሊገነባ ቢችልም ፤ በከፊል መከፈት ግማሽ የኢኮነሚ አቅም እንደ እሚፈጥር ነው።

መጨረሻውም ደካማው የሐገር ውስጥ ገበያ ፤ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ እንኳን ፈጣን ሊባል የእሚችለው የሐገሪቱ የዕድገት ሞተር የሆነውን የኤክስፖርት መስክን ጎትቶ ሊያዘገየው ይችላል።

#### *2.4.2.2 ቻይና*

ቻይና እንደ በራሪ ኮከብ እንደ እዚኽ አምዘግዝጎ ይኽን ዓይነት ፈጣን የኢኮነሚ ዕድገት እንድታስመዘግብ ያስቻላት ፤ የቁጥጥር ውቅያኖስ በሆነችው ትልቋ ቻይና ውስጥ የንግድ ክፍትነት ደሴት የሆኑ እንደ ሼንዠን (Shenzhen) ያሉ ፤ ልዩ የኢኮነሚ ዞኖችን መፍቀዷ ነበር።

ይኽም ቻይና ፤ መላው ሐገሯን የንግድ ክፍትነት ከእሚያስከትለው ንዝረት ከልላ ፤ በእነ እዚኽ የንግድ ክፍትነት ደሴት በሆኑት ልዩ የኢኮነሚ ዞኖች ውስጥ ከገቡ የውጭ የንግድ ድርጅቶች ፤ "የምዕራቡን ቴክኖሎጂ" እና የንግድ አስተዳደር ጥበብ መቅሰም እንድትችል እድል ፈጠረላት ። ይኽም ቻይና የተከተለችው ስልታዊ (Surgical) የንግድ ክፍትነት ቻይናን እንደ ሐገር ወደ "ዓለም ፋብሪካነት" ቀየራት።

ይኽ ቻይናን "የዓለም ፋብሪካ" ያደረጋት ስልታዊ (Surgical) የንግድ ክፍትነት ግን ውጤታማነቱ እያበቃ ነው። ከእዚኽም የተነሳ ፤ አሁን ቻይና ከፍተኛ ገቢ ያለው ሐገር ለመሆን የእምታደርገው ጉዞ ፤ የተስፋ መደብዘዝ ገጥሞታል።

ቻይና የአዕምሮ ፈጠራ ውጤቶችን (Intellectual Property) የንብረት ባለቤትነት ጥበቃ በመንፈግ እና ቀጣይነት ባለው እና የገበያን የዋጋ ስረዓት በእሚያናጋ መልኩ በከፍተኛ ደረጃ የመንግሥት የልማት

ድርጅቶችን የመደጎም ልማዷን በማስቀጠል ፤ ዓለም ዓቀፉ ካፒታል በቻይና ላይ የነበረው ዕምነት እንዲሸረሸር አድርጋለች።

ቻይና አሁን በደረሰችበት የእድገት ደረጃ የሠራተኛ ደሞዝ በመጨመሩ ፤ ከእዚኽ በፊት እንደ ነበራት ዓይነት በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ርካሽ የእሚባል ጉልበት ማቅረብ ስለ እማትችል ፤ ከውጭ ውድድር በታሪፍ ፣ በድጎማ እና በሌሎች አሠራሮች ከልላ ያቆየቻው የአምራች መስኮች ትርፋማ ሆኖ የመቆየታቸው እድል እየከሰመ ነው።

ቻይና ለዘመናዊ የሸማቾች ኢኮኖሚ[5] (Modern consumer economy) የእሚያስፈልገው ግልጸኝነት እና ስር የሰደደ ተቋማዊ የንግድ ክፍትነት ማምጣት ካልቻለች ፤ የመካከለኛ ሐገራት ወጥመድ (Middle-Income Trap) የእሚባለው ውስጥ ተይዛ የመቆም አደጋ ተጋርጦባታል።

"በውስን ክፍትነት" የመጣው የአሁኑ የቻይና ዕድገት ፤ በቀረው "የመዘጋት ባሕር" ታንቆ ተይዟል። (The growth that was once fueled by "measured openness" is now being choked by the remaining "sea of control.")።

ከእዚኽ በፊት የቻይና ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ውስጥ በመግባት ለመሥራት ከፍተኛ ጉጉት የነበራቸው የዓለም ዓቀፍ የንግድ ድርጅቶች አሁን የቻይና ገበያ ከተደላደለ የመጫወቻ ሜዳነት ይልቅ ኢተገማች የሆነ ጨለማ (black box) ስለ ሆነባቸው ማፈግፈግ ላይ ናቸው።

የቻይና ኢኮኖሚያው ምጥቀት የእሚያረጋግጠልን ነገር ቢኖር ፤ የንግድ ክፍትነት ለአንድ ሐገር ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ፤ ኦክስጂን መሆኑን ነው።

ቻይና የውጭ የንግድ ድርጅቶች ወደ ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖቿ ውስጥ እንዲገቡ በመፍቀድ ፤ የውጭ ሐገር ካፒታል ብቻ አልነበረም የሳበችው ፤ ይልቁንም የሐገሯ የንግድ ድርጅቶች ለዓለም ዓቀፍ የውድድር ጫና እንዲጋለጡ እና የዓለም ዓቀፍ የአሠራር ልምድን ቀስመው እራሳቸውን እንዲለውጡ ማድረግም ነበር የቻለችው።

ቻይና በተወሰነ መልኩ ኢኮኖሚዋን መክፈቷ (Measured openness) ፤ ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖቿ ፤ በዓለም ላይ የእሚገኙ በጣም የበሰሉ የአቅራቦት ሰንሰሎቶችን (Most advanced supply chains) ጎትቶ የእሚያመጣ የስበት ማዕከል ነበር ያደረጋቸው ፤ ይኽም ቻይና በመቶ ሚልዮን የእሚቆጠሩ ቻይኖችን ከድህነት ማውጣት እንድትችል አድርጓታል።

[5] እንደ ኢትዮጵያ እና መሰል ደኃ ሐገሮች ተደጋግሞ ከእሚዘነጉት ነገር ፤ አንድ ሐገር ፤ የሐገር ውስጥ ሸማቾችን አቅም ሳታሳድግ ፤ ትልልቅ ኢንደስትሪዎች በመገንባት ማደግ እንደ እማትችል እና አንድ ሐገር ዘመናዊ ኢኮኖሚ መገንባት ካለባት የሸማች አቅም ማሳደግ እንደ ያለባት መሆኑን ነው። ኹሉም አምራች ሆኖ ገዢ ከሌለ ኢኮኖሚ ቆሞ ይቀራል እንጂ ወደ ፊት አይራመድም።

ሆኖም ግን አሁን ላይ ቻይና ፤ መንግሥት መራሽ የሆነ በኹሉም ምርት ራስን መቻል (Self-reliance) እና የሐገር ውስጥ የንግድ ድርጅቶችን ተከላካይ የሆነ የድጎማ (Protectionist subsidies) ፖሊሲ ውስጥ ስለ ገባች ፤ ያ የዕድገት ኦክስጂን እየተሟጠጠ ነው።

አሁን ለደረሰችበት ዕድገት ያበቃት የንግድ ክፍትነት (Openness) ላይ ፊቷን በማዞር ፤ ቻይና ለግዜያዊ የፖለቲካ ቁጥጥር ስትል ዘላቂ የሆነውን የምርታማነት ዕድገት እየሰዋች ነው - በእዚኽም ኺደት የሐገሯን የንግድ ተቋማት ብቃት እያዳከመች እና ለዓለም ዓቀፉ ማሕበረሰብ ፦ በአንድ ወቅት ወለል ብሎ ተከፍቶ የነበረው የንግድ በሯን በመዘጋት ላይ መሆኑን የዕሚያሳይ ምልክት እየሰጠች ነው።

### *2.4.2.3 ቻይና የገበያን ሕግ የሻረች መምሰሏ የፈጠረው መምታታት*

ቻይና የኢኮኖሚ ሳይንስ የእሚያወድሰውን የንግድ ክፍትነት ሕግ ሽሬ ጠንካራ ኢኮኖሚ ገንብቼ አሳያችኋለው የእምትል ትመስላለች።

ቻይና ፦ አሁን በእምትከተለው እራስን የመቻል (Self-Reliance) የንግድ ፖሊሲ ፤ በሌሎች ሐገራት ቴክኖሎጂዎች ላይ ተደጋፊነትን ለመቀነስ እና የሐገር ውስጥ የንግድ ድርጅቶቿን ከውጪ ውድድር መከላከል አለብኝ በእሚል ሽፋን ፤ ውስን የሆነ የንግድ መከፈት (Selective openness) በማድረግ ፥ አምራች ኩባንያዎቿን በድጎማ ፣ በታሪፍ እና በአሠራር ከውጭ ውድድር ከልላ - የዓለምን ገበያ ደግሞ እነ እዚኽ የምትከልላቸው ኩባንያዎቿ የእሚያመርቱትን ምርት መሸጫ የማድረግ አካኼድ እየተከተለች ነው።

በእዚኽም አካኼድ ፤ ከንግድ ክፍትነት የእሚገኙትን ፦ አንጻራዊ ጥቅም ፣ ፈጠራ ፣ ከግዝፈት የእሚገኝ የዋጋ ማርከስ አቅም ፣ እና ርካሽ የግብዓት ዋጋ (comparative advantage, innovation, economies of scale, and access to global inputs) ጥቅሞች አስጠብቄ ፤ የንግድ ክፍትነት የእሚያመጣው የተወዳዳሪነት ጫና የእሚስከትለውን የብቃት እና የጥራት ዕድገት ፤ በመንግሥት የኢንደስትሪ እና የንግድ ፖሊሲ እንዲሁም በድጎማ አቅም እተካለሁ እያለች ነው።

በሌላ አማርኛ ፤ ሐገሬን ሙሉ በሙሉ ለንግድ ሳልከፍት የልማት ፖሊሲዎችን በመጠቀም ፤ የንግድ ክፍትነት የእሚያስገኘውን ጥቅም እያገኘኹ ግዴታውን ማስቀረት እችላለሁ የእምትል ይመስላል ቻይና።

ይኼ ዕሳቤ በቻይና ፍሬ እንዲያፈራ ግን ፤ ኹለት ቅድመ ኹኔታዎች መሟላት አለባቸው ፦

1. ቻይና - ልዕለ ኃያል አምራች ሆና ፤ አንድ ምርት በማምረት የእሚባክነውን ሌላን ምርት የማምረት ዕድል ወይንም በኢኮኖሚክስ የዕድል ዋጋ (opportunity cost) የእሚባለውን ዋጋ ትርጉም ባለው መልኩ በእሚቀንስ አኳኋን ፤ ዝቅተኛ ከእሚባለው እንደ ካኔተራ ካለው ከፍተኛ እስከ እሚባለው እንደ ማይክሮቺፕ ድረስ ያሉትን ኹሉንም ምርቶች በበላይነት (በርካሽ ዋጋ እና በጥራት) ማምረት አለባት።

2. የዘመናዊ የኢንደስትሪ ፖሊሲ አባት ሊባል በእሚችለው የኮልበርት ልምድ መሠረት ፤ በውድድር ጫና የእሚመጣን የፈጠራን አቅም ፦ በድጎማ ፣ በኢንደስትሪ ፖሊሲ እና በቴክኖሎጂ ግዢ መተካት አለባት።

በጽንሰ ኃሳብ ደረጃ ፤ እነ እዚኽ ኹለት ኹኔታዎች ከተሟሉ ፤ ቻይና የንግድ ክፍትነትን ሳታረጋግጥ ፤ የንግድ ክፍትነትት የእሚያስገኘውን ጥቅም አግኝታ የእሚያስከትለውን ተጋላጭነት ማስቀረት ትችላለች ፤ በኢከነሚ ውስጥ ብቃትን ለማሳደግ የሥራ ክፍፍል እና ግልጽ ውድድር (Specialization and open competition) ያስፈልጋል የእሚለውን ፤ በዴቪድ ሪካርዶ (David Ricardo) የተቀመጠውን የኢከነሚ መርኽ ሽራ አዲስ መርኽም ታስተዋውቃለች።

አሁን ያለው ፤ የቻይና ኢከነሚም ይኽን እያደረግኹ ነው የእሚለው።

ሆኖም ፤ ይኽ የተመሠረተውን የኢከነሚ ሕግ የእሚሽር የእሚመስለው የቻይና ኢከነሚ ኹናቴ ፤ ጠጋ ተብሎ ሲመረመር ፤ በእርግጥም የእሚፈለገውን ውጤት እያስመዘገበ ነው ማለት ያዳግታል።

የቻይናው አካኼድ የጻናውን የኢከነሚ ሕግ(Classical trade theory) ከመቀየር ይልቅ ፤ በእዚኽ አካኼዱ የኢኮኖሚው ሕግ የእሚለውን ተከትሎ ኹለት መዋቅራዊ ዕንቅፋቶች እንደ ገጠሙት ነው የእሚታየው።

**1. አንጻራዊ ተወዳዳሪነትን በበጀት ለመተካት መሞከር**

ቻይና በኹሉም ምርት ፤ በርካሽ ዋጋ እና በጥራት ፤ አሸናፊ ተወዳዳሪ መስላ የእምትታይበት ምስጢር ፤ በኹሉም መስክ አንጻራዊ ብልጫ ይዛ በመገኘቷ ሳይሆን ፋይናንሻል ኢንጂነሪንግ (Financial engineering) የእምትጠቀም በመሆኑ ነው።

በርካታ የመንግሥት ንብረት የሆኑ የቻይና አምራች ድርጅቶች አትራፊ ሆነው የቆሙት በተወዳዳሪነት አሸንፈው ሳይሆን ፦ ከፍተኛ የመንግሥት የበጀት ድጎማ ፣ ከፍተኛ የሆነ ከመንግሥት ባንኮች የእሚገኝ በርካሽ የወለድ መጠን የእሚገኝ ብድር ስለ እሚያገኙ ፣ እና ዕዳ መክፈል ሲያቅታቸው የክፍያ መጠነኑን እየቀነሰ እና የክፍያ ዘመኑን የእሚያረዝም የብድር ሽግሽግ ስለ እሚደረግላቸው ነው።

የእሚከስሩ የመንግሥት የንግድ ድርጅቶች ፤ አንድ አንድ ግዜ ካልሆነ በስተቀር ከስረው እንዲወጡ አይደረግም ፤ ይልቁንም ከስረው እዳ ሲበዛባቸው መንግሥት እዳቸውን ከሕዝብ ገንዘብ ላይ ውስዶ እስከ መክፈል የእሚደርሱ የማዳን ሥራዎችን እየሠራ ፤ ድርጅቶቹ በራቸው እንደ አይዘጋ ያደርጋል።

ይኽ አካኼድ ፤ የዕድልን ዋጋ (Opportunity costs) ይሠውራል። በገበያ ውድድር ሕግ ቢሆን መጥበብ ወይንም ስለ ከሰሩ ከገበያ መውጣት የነበረባቸው የንግድ ድርጅቶች ፤ መንግሥት ከሕዝብ ገንዘብ ላይ ወስዶ በእሚያድርግላቸው ድጎማ ከእነ ሙሉ ይዘታቸው ይቀጥላሉ - በእዚኽም በኢከነሚ ውስጥ እምቢአልሞትም (Zombie) የእሚባሉት እና በአትራፊነት ሳይሆን እየከሰሩም በእሚደረግላቸው ድጎማ ብቻ ገበያ ውስጥ የእሚቆዩ ኩባንያዎችን ያበራክታል።

ቻይና በኹሉም መስክ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በጥራት እና በዋጋ ተወዳዳሪ አምራች መሥላ መቅረብ የቻለችው ፤ ብቃቷን በፈጠራ አሳድጋ ሳይሆን በከፍተኛ ደረጃ ሐገራዊ የዕዳ መጠኗን የእሚያሳድግ ብድር እየወሰደች እና ዜጎቿ በእየባንኩ የቆጠቡትን ገንዘብ ለእነ እዚኽ እምቢአልሞትም (Zombie) ኩባንያዎች ማስቀጣየነት በማበደር ነው።

በቻይና ከፍተኛ የእሚባለው እና ከገጠር መጥቶ ከተማ ሥራ የእሚሠራው ሠራተኛ የማሕበራዊ ዋስትና ወይንም የጡረታ ተጠቃሚ ስለ አልሆነ ፤ ከደሞዙ ላይ እራሱ ውስዶ በመቆጠብ ነው ለእራሱ ጡረታ የእሚዘጋጀው ፤ ችግሩ ግን ባንኮቹ በፖሊሲ ፤ ገንዘባቸውን በቅድሚያ ፤ ለደንበኛው ቤት ፣ መኪና ፣ የቤት ዕቃ ፣ ወዘተ መግዢያነት ሳይሆን ለእምቢአልሞትም (Zombie) ካምፓኒዎቹ እንዲያበድሩ ስለ እሚደረጉ ፤ የኢንደስትሪ ፖሊሲው ፤ የሸማቾችን አቅም እየገደለ ነው እነ እዚኽን እምቢአልሞትም (Zombie) በሕይወት የእሚያስቀጥላቸው።

ስለ እዚኽ ፦ ቻይና በኹሉም መስክ ዓለም ዓቀፍ ፤ የዋጋ እና የጥራት ተወዳዳሪ መስላ የእምትታየው ፤ ሐገራዊ የዕዳ መጠኗን በማሳደግ እና የዜጎችን ቁጠባ በትንሽ ወለድ እና የባንኮች እስረኛ በማድረግ ከዜጎች “እየዘረፈች” የእምታገኘውን ገንዘብ ለእምቢአልሞትም (Zombie) ለሆኑ ኩባንያዎች በርካሽ በማበደር እና በእዚኽም እነ እዚኽን እምቢአልሞትም (Zombie) ኩባንያዎች ተወዳዳሪ በመስመሰል እንጂ በእርግጥም ኩባንያዎቹ ተወዳዳሪ ስለ ሆኑ አይደለም።

በአጭሩ ፤ በአንድም በሌላ መንገድ በሕዝብ ላይ እዳ እየከመሩ ፤ ከሳሪ ከመሆናቸው የተነሳ መዘጋት የነበረባቸውን እምቢአልሞትም (Zombie) ኩባንያዎች ገንዘብ በመስጠት ነው ፤ በዋጋም በጥራትም ተወዳዳሪ ያስመሰሏቸው።

ስለ እዚኽ ፦ ቻይና የዕድልን ዋጋ (Opportunity cost) አላስቀረችውም - የሕዝቡን ኪስ በመጠቀም እና ብሔራዊ የብድር ጫናዋን በማብዛት ለግዜው አዘግይታዋለች (Thus, China does not eliminate opportunity cost—it merely defers and socializes it.)

### 2. ያለ ገበያ ውድድር ፈጠራን ለማምጣት መሞከር

ቻይና የዕድልን ዋጋ (Opportunity Cost) በፖሊሲ መቀነስ እችላለኹ ከማለት በተጨማሪም ብቃትን እና ፈጠራን በገበያ ሳይሆን ፦ **በኢንደስትሪ ፖሊሲ ፣ በቴክኖሎጂ ግዢ እና በመንግሥት አስተዳደራዊ አመራር** ፤ አመጣዋለሁ የእሚል ሙከራ ላይ ነች።

ይኽ አካኼድ በተወሰኑ መስኮች አስደማሚ የእሚባሉ እመረታ ቢያስመዘግብም ፤ መዋቅራዊ ውስንነት መፍጠሩ ግን አልቀረም።

ምክንያቱም ፦ መቼም ቢሆን ደካማ እና ተወዳዳሪ የሆኑ ኩባንያዎች ፤ ከስረው እንደ አይዘጉ በእሚደረጉበት ግዜ ፤ የካፒታል ወደ ተወዳዳሪ አምራቹ እንደ አይሄድ የእሚደረግ በመሆኑ የካፒታል ድልድሉ ይዛባል የቴክኖሎጂ ዕድገትም ይንቀራፈፋል።

ይኽም ብቻ ሳይሆን ፤ በቻያና ተደጋጋሚ የአዕምሮ ንብረት ባለቤትነት ክርክር (Intellectual-property disputes) መኖሩ እና በዓለም ዓቀፍ ገበያ እወዳደራለሁ የእሚሉ ነገር ግን ከፍተኛ የመንግሥት ድግማ ያላቸው የቻይና ኩባንያዎች በመኖራቸው ፤ ሌሎች ኢከነሚዎች ከቻይና ጋር አብረው ለመሠራት ያላቸውን ፍላጎት በመቀነስ ፤ የቴክኖሎጂ ልውውጡን አቀዝቅዞታል።

ከእዚኽም የተነሳ ካደጉ ሐገራት ጋር ያላት የቴክኖሎጂ ልውውጥ እና ትስስር ከእለት ወደ እለት እየቀዘቀዘ ነው።

ከእዚኽ በላይ የተገለጸው ዓይነት ፤ የቻይናው የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን የመከላከል የኢንደስትሪ ፖሊሲ ፤ የአንድ ኢኮኖሚን የፈጠራ ዕምቅ አቅም እንደ አይለቀቅ የእሚከለክል ነው ፤ የቻይና ኩባንያዎች በነጻ ተወዳድረው ከፍተኛ የፈጠራ ችሎታ ያለው ኋላ ቀሩን አሸንፎ (competitive destruction) እንዲያጠፋ ስለ እማይፈቅድ።

### 3. ከእሚፈለገው በላይ የማምረት ችግር

ምንም እንኳን ቻይና በግዜያዊነትም ቢሆንም የዕድልን ዋጋ (Opportunity cost) ተጭና መቀነስ እና ፈጠራን በመንግሥት አመራር ለማምጣት የቻለች ቢመስልም ፤ ሶስተኛ ተግዳሮት ገጥሟታል ፦ ለእምታመርተው ምርት ገበያ የማግኘት ችግር።

ቻይና የእምትከተለው የዕድገት ሞዴል የፈጠረው ከፍተኛ የአምራች ኢንደስትሪ አቅም ፤ በሐገሪቱ ውስጥ የጅዲፒን (GDP Growth) እና የመቅጠር አቅሙን በእየ ዓመቱ እያሳደገ እንዲቀጥል ፤ ምርት ወደ ውጭ መላክ አለበት ።

በ2025 ቻይና ኤክስፓርት ያደረገችው ኢምፖርት ካደረገችው በ 1.2 ትርሊዮን ዶላር ይበልጣል ፤ የቻይና ኢከነሚ ምን ያኽል በኤክስፖርት ላይ ተደጋፊ መሆኑን በእሚያሳይ መልኩ።

ይኽ ከፍተኛ መጠን ያለው የንግድ ሚዛን ወደ ቻይና ማጋደል ከሌላው የዓለም ክፍል ኢከነሚ ጋር የቻይና ኢከነሚ ውጥረት ውስጥ እንዲገባ አድርጓል። ምንም እንኳን ብዙ ሐገራት የቻይናን ርካሽ ዕቃዎች ወደ ሐገራቸው በማስገባት ቢጠቀሙም ፤ ቻይና በድጎማ እና በብድር ያፈረጠመቻቸው ኩባንያዎቿ የሐገራቸውን ኢንደስትሪ ከገበያ እያስወጣ በመሆኑ ፖለቲካዊ ጫና ውስጥ አስገብቷቸዋል።

ይኽንም ተከትሎ ፤ የቻይናንን ተፅዕኖ ለመከላከል በዓለም ላይ ታሪፍ ፣ ድጎማ እና የኢንደስትሪ ፖሊስዎች በእየ ሐገሩ እየተበራከቱ ነው ፤ የቻይናን ከአቅም በላይ የማምረት አካኼድ ለመቋቋም።

### 4. ታሪክ እራሱን ሲደግም ፤ የዖፕየም ጦርነት (Opium War) በሌላ መልኩ

በ1830ዎቹ ፤ ብሪታኒያ ከቻይና አንጻር ከፍተኛ የንግድ ጉድለት ገጠማት ፦ ምክንያቱም ፦ አውሮፓውያኖች እንደ ሻይ ፣ ሲልክ ጨርቅ እና የሸክላ ዕቃዎች ያሉ የቻይናን ምርቶች ይፈልጋሉ ፤ በአንጻሩ ቻይና ከአውሮፓ እምትፈትልጋቸው ምርቶች እምብዛም አልነበሩም።

ስለ እዚኽ ፡- ብሪታንያ ለቻይና ሸጣ የእምታገኘው የብር ረብጣ (Silver) ስለ አልነበረ እና በአንጻሩ ግን የብር ረብጣ ( Silver) እየከፈለች የቻይናን ሻይ ፣ ሲልክ ጨርቅ እና የሸክላ ዕቃዎች ትገዛ ስለ ነበር ፤ በግዜ ኺደት የእምትከፈለውን ብር ረብጣ (Silver) ጨርሳ ፤ ከቻይና የእምትገዛበት የብር ረብጣ (Silver) አጣች።

ያን ግዜ ነበር ፤ በህንድ ታበቅል የነበረውን ኦፐየም (Opium) ወደ ቻይና በኮንትሮባንድ እያስገባች ፤ ከቻይና ገበያ ውስጥ የብር ረብጣ (Silver) ማውጣት ውስጥ የገባችው።

ቻይናዎች ይኽን የኦፐየም ኮንትሮባንድ እየያዙ ሲያቃጥሉ ፤ ብርታኒያ ንብረቴን አቃጠሉ በእሚል ፤ የኦፐየም ጦርነት የእሚባለውን ጦርነት ከፈተች እና በጦርነቱ በማሸነፏ ፤ ቻይናዎቹ ኦፐየሙን እንዲገዙ ተገደዱ ፤ ብሪታኒያም ከኦፐየሙ ሽያጭ የቻይናን ሻይ እና ሲልክ የእምትገዛበት የብር ረብጣ (Silver) ማግኘት ቻለች።

በእዚኽ የኦፐየም ጦርነት ባስከተለ ታሪክ እንደ እሚታየው ፤ የንግድ ፍላጎት መኖሩ እና የንግድ ፍላጎቱ ግን ፤ በንግድ ሚዛን አለመመጣጠን መነሾነት ወደ ጦርነት እንደ አመራ ነው።

ዛሬ ነገሩ የተገላቢጦሽ ነው ፤ በዛሬው ስሌት ቻይና ከፍተኛ የአምራች ኢንደስትሪ ባለቤት ስትሆን ፤ ለሌላው ዓለም ደግሞ ይኽ ከፈተኛ የቻይና አምራች ኢንደስትሪ ያመረተውን ምርት በሙሉ መግዛት ያቃተበት ኹኔታ ነው ያለው።

በእዚያን ግዜ የንግድ ሚዛን መዛባቱ በመሳሪያ ኃይል ቻይናን አስገድዶ አሺሽ እንድትገዛ በማድረግ ተፈታ።

ዛሬ ይኽ ጦርነት በታሪፍ ፣ በማዕቀብ እና በኢንደስትሪያ ፖሊሲ እየተካኼደ ነው።

በኹለቱም ግዜ ፤ መሠረታዊ ችግሩ አንድ ዓይነት ነው ፡- ዓለም ዓቀፉ የንግድ ስረዓት ውስጥ ፤ ሌላው ሊገዛው ከእሚችለው ብላይ አንዱ የእሚያመርትበት መሆኑ ነው።

ስነ አጠቃልለው ፤ ቻይና የንግድ ክፍትነት (Trade openness) ሐገራትን ከኋላ ቀርነት ስቦ የእሚያወጣ ኃይል ነው የእሚለውን የኢከነሚ መርኽ ማዋደቅ አልቻለችም። ይልቁንም ፡- የገበያ ሕጎችን ችላ በማለት መንግሥታዊ ጣልቃ ገብነት ላይ ተመርኵዞ ፤ የንግድ ክፍትነት የእሚሠራውን ሥራ ለመሥራት መሞከር ፤ ውስንነት ያለበት እና የተፈለገውን ውጤት ለማስመዝገብ እሚያዳግተው መሆኑን ነው ያረጋገጠችው።

ቻይና በአብዛኛው ዝግ ሆና የንግድ ክፍትነትት የእሚያስገኘውን ጥቅም ማግኘት የቻለቸው ፤ የሕዝብን ገንዘብ በመጠቀም ፣ የሐገር ውስጥ ሸማቾችን አቅም በማዳከም እና በእዚኽ መልኩ የእምታመርተውን ርካሽ ምርት በጉግት የእሚገዛት የዓለም ክፍል ላይ ተመርኵዛ ነው።

ከእዚኽ አንጻር ፤ ቻይና የንግድ ክፍትነት ጠቀሜታ እንደ ሌለው አይደለም ያሳየችው ፤ ይልቁንም የንግድ ክፍትነትን የእሚተካ የእሚመስል ነገር ግን መተካት ያልቻለ እና ስውር ዋጋ ያለው አካኼድ ነው

የተከተለችው (In this sense, China has not overturned the logic of open trade. It has merely created the temporary mirage of having done so)

### 2.4.3 ዓይነተኛ የክስረት ታሪክ: ሕንድ

*ሕንድ : የፈቃድ ባላባቱ ("License Raj") እና መዋቅራዊ ልሽቀት*

ጃፓን እና ቻይና ስልታዊ ከለላ (*Strategic* protection) ጥቅም ሊኖረው እንደ እሚችል ካሳዩ ፤ ከ1991 በፊት የነበረችው ሕንድ ከለላ እንዴት ወጥመድ (Protectionism as a Trap) ሊሆን እንደ እሚችል ማስጠንቀቂያ ነች።

ለበርካታ አስርት ዓመታት ሕንድ ፤ ራስን መቻል (Self-reliance) እና የውጭ ምርቶችን በመከልከል ሐገራዊ አምራችነት ማሳደግ በእሚል እሳቤ ከውጭ የእሚገቡ ዕቃዎችን በሐገር ውስጥ ምርት መተካት (Import Substitution Industrialization) የእሚል ፖሊሲ ስትከተል ነበር።

ይኽም ሞገደኛ የእሚባለውን "የፈቃድ ራጅ (ባላባት)" አሠራርን ወለደ። በእዚኽም የፈቃድ አሠራር ፦ ለማምረት ፣ ኩባንያ ለማስፋፋት ፣ የምርት ዓይነትን ለማብዛት ፤ የመንግሥት ፈቃድ ማግኘት ግዴታ ነው።

ይኽ "የፈቃድ ራጅ" መደበኛ የንግድ ድርጅቶች የንግድ ፈቃድ የእሚያገኙበት ዓይነት ፈቃድ አይደለም ፤ ይልቁንም ፦ የመንግሥት የፖሊሲ ተቀጥያ ሆኖ ፤ መንግሥት የንግድ ድርጅቶችን በእሚፈልገው በታ እና መስክ የእሚደለድልበት ዓይነት ፈቃድ ነው።

ለምሳሌ፦ አንድ ነጋዴ ፤ የፈለገውን ንግድ ለመጀመር የእሚያስፈልገው የሞያ ብቃት ፣ የካፒታል መጠን እና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች ቢያሟላም እንኳን ፤ መንግሥት ፈቃድ ሊከለክለው ይችላል ፤ ነጋዴው ሊሠማራበት የፈለገው የንግድ መስክ ከእንደስትሪያል ፖሊሲው እና በእቅዱ መሠረት ቅድሚያ ከእሚሰጣቸው መስኮች ውጭ ከሆነ።

የንግድ ፈቃዶች የእሚሰጡት ፦ ከአምስት ዓመት ዕቅዱ ጋር የእሚስማሙ ከሆኑ ፣ የክልል ስርጭት ሚዛንን እሚጠብቁ ከሆነ እና ቅድሚያ ከተሰጣቸው ሴክተሮች ውስጥ እሚካተቱ (ለምሳሌ ፦ ለሸማች የእሚሆን ሸቀጥ ከማምረት ይልቅ ከፍተኛ ኢንደስትሪዎች) ከሆኑ ነው።

የንግድ ተቋማት እንደ አሻቸው የማምረት አቅማቸውን ማስፋትም አይፈቀድላቸውም። እያንዳንዱ የማስፋፊያ ፕሮጀክት የመንግሥት ፈቃድ ይፈልጋል ፤ ፈቃድ የማግኘቱም ነገር መስኩ የምርት መስፋፋት የእሚያስፈልገው ነው ብሎ መንግሥት ከማመኑ ጋር ይገናኛል።

ከእዚኽ የተነሳ ፦ አዲስ ወደ ገበያ ለመግባት የእሚፈልጉ ነጋዴዎች ፤ በገበያ ውስጥ እየሠሩ ያሉት ነባሮቹ የንግድ ተቋማት በአብዛኛው ከመንግሥት ጋር ግንኙነት ያላቸው እና የፈቃድ አሠጣጡ ኺደት ላይ ተፅዕኖ ማሳደር የእሚችሉ በመሆናቸው ፤ብዙ ፈተና ይገጥማቸዋል ።

የፈቃድ አሠጣጡም ኺደት ቀጥተኛ ስለ አልሆነ ፤ የመንግሥት ፈቃድ ሰጪ ኃላፊዎች ከፍተኛ የመወሰን አቅም አላቸው። ይኽም መድሏዊ አሠራርን ፣ መዳተትን እና ሙስናን አበራክቷል።

በእዚኽ መልኩ ለንግድ ተቋማት የእሚሰጠው ከለላ (Protectionism) እጅግ ከፍተኛ ስለ ነበር የሐገር ውስጥ ተቋማቱ ራሳቸውን ለማሻሻል ምንም ተነሳሽነት አልነበራቸውም ፤ በጥቂት ጥረት በመንግሥት ከለላ መኖር ስለ እሚችሉ።

ይኽም የንግድ ዝግነት ነበር በ1970ዎች እና በ1980ዎች እንደ ቻይና ያሉ ሐገራት የአምራች ሐገራት ማዕበልን ሲቀላቀሉ ሕንድ እድሉ እንዲያመልጣት ያደረገው።

በ1991 ሕንድ እድሉ እንደ አመለጣት አውቃ የዘጋችውን የንግድ በር ስትከፍት ፤ ገበሬውን ከግብርና አውጥቶ ወደ ፋብሪካ የእሚስገባው መዋቅራዊ ሽግግር በአስርት ዓመታት ወደ ኋላ ነበር።

ዛሬም ቢሆን ፦ በሕንድ ውስጥ ባለው ውስብስብ የአሠሪ እና የሠራተኛ ሕግ እንዲኹም ባሕላዊ ቅርጽ በያዘው የንግድ ክፍትነትን የመፍራት የተከላካይነት ቅሪት (The legacy of that protectionism) ፤ በሕንድ ብዙ ሚልዮኖችን ከድህነት ለማውጣት የእሚያስችለውን ግዙፍ የኢንደስትሪ አቅም መገንባት አስቸጋሪ እንደ ሆነ ነው።

### 2.4.4 መደምደሚያ

የንግድ ክፍትነት (Trade openness) በአንጻራዊ ብልጫ እና የምርጫ አድማስን በማስፋት (Comparative advantage and the "utility of variety.") ፤ ቀዳሚ ከእሚባሉት የሐገር ዕድገት ዘዋሪ ሞተር ውስጥ የእሚመደብ ነው።

ሐገራት አንጻራዊ የማምረት ብልጫ ባላቸው መስክ ላይ በማተኮር ፤ የጋራ የማምረት አቅማቸውን ማሳደግ እና የዕድል ዋጋቸውን (Opportunity cost) ዝቅ ማድረግ ይችላሉ ፤ በእዚኽም መላውን የዓለም ሕዝብ የኃብት መጠን ይጨምራሉ።

የንግድ ክፍትነት ፤ ከሸቀጥ ልውውጥ በላይ የቴክኖሎጂ ሽግግር የእሚደረግበት መንገድም ነው ፤ የሐገር ውስጥ የንግድ ድርጅቶችን ተከላካይነት (Protectionism) ከእሚሰጣቸው የደህንነት ጥላ (Security blanket) ሥር አውጥቶ ተወዳዳሪ ለመሆን ዓለም ዓቀፍ ቴክኖሎጂዮችን እና አሠራሮችን እንዲላመዱ ስለ እሚያስገደድ።

በእዚኽም ላይ ፤ የንግድ ክፍትነት ፤ በግብዓት ሰንሰለት (Supply chain) ውስጥ የሌሎችን ምርት ግብዓት አድርገው የእሚጠቀሙ የንግድ ድርጅቶች በግብዓት ዋጋ ውድነት እንደ አይመቱ ይጠብቃቸዋል ፤ ለምሳሌ ፦ የሐገር ውስጥ ብረት አቅላጮን ከውጭ ውድድር ለመጠበቅ የእሚደረግ ታሪፍን በማንሳት ፤ የሐገር ውስጥ መኪና አምራቾች ርካሽ ብረት በማግኘት ፤ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ የሆነ መኪና እንዲያመርቱ ያስችላቸዋል።

ታሪካዊ መዝገቦች የተከላካይነት አባዜ (Protectionist fever) በመንግሥታት ዴሞክራሲያዊነት እና አምባገነናዊነት ላይ የእማይደገፍ መዋቅራዊ መጥመድ እንደ ሆነ ያሳያሉ። አንድ መንግሥት ከ2ኛው ዓለም ጦርነት በኋላ እንደ ነበረችው የጃፓን መንግሥት ሊበራል ዴሞክራሲ ይኹን ወይንም እንደ ቻይና መንግሥት አምባገነን ፤ የሐገር ውስጥ ኢንደስትሪዎችን ከዓለም ዓቀፍ ውድድር ለማዳን ሲሉ ጋሻ በማንሳት የንግድ በርን መዝጋት ፤ ወደ ኢኮኖሚያዊ ድርቀት እና ቆሞ ቀርነት ነው የእሚያመራው።

በጃፓን ፤ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ፖለቲካዊ ታማኝነት ለመግዛት ሲል የንግድ ብቃትን በመሰዋት የሐገር ውስጥ ግብርናን እና አገልግሎት መስክ በማዳከም ባለኹለት መልክ ኢኮኖሚ ፍጥሯል ፤ በጣም ብቁ እና ተወዳዳሪ የሆነው የሐገሪቱ የኤክስፖርት ሴክተር ፤ እምቢአልሞትም (Zombie) በሆኑት በሐገር ውስጥ የግብርና እና የአግልግሎት መስኮች ሸክም የጎበጠበት ኢከነሚ በመፍጠር።

በተመሳሳይ ከ1991 በፊት የነበረው የሕንዱ የፈቃድ ባላባት (License Raj) ስረዓት ፤ አንድ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት እንዴት አድርጎ ፤ ዕድገትን ለአስርት ዓመታት አንቆ የእሚይዝ የቤሮክራሲ ትብታብ ሊፈጥር እንደ እሚችል ማሳያ ነው።

በስተመጨረሻ ፤ የንግድ ክፍትነት ፤ አንድ ሐገር የመካከለኛ ገቢ ወጥመድን (Middle Income Trap) ሰብሮ ለመውጣት የእሚያስፈልገው አንድ ቅድመ ኹኔታ ነው ፤ መንግሥቱ ዴሞክራሲያዊ ሆነ አምባገነናዊ።

አንድ ሐገር ፤ በነጻ እና ፍትኃዊ ንግድ ላይ የተመሠረተ የንግድ ክፍትነትን በመቀበል ከዓለም ዓቀፉ ኢከነሚ ጋር ካልተሳሰረ ፤ ዘላቂነት ባለው መልኩ የሐገሩን ምርታማነት የማሳደግ እድሉን ለግዜያዊ የንግድ ቁጥጥር ሲል እያባከነ ነው እሚሆነው።

## 2.5 የበጀት አስተዳዳር ጥበብ (Fiscal Discipline)

(የበጀት አቅምን ግብር ለማብላት ሳይሆን ወዋቅራዊ ሽግግር ለማምጣት መጠቀም)

### 2.5.1 አሠራር

የአንዲት ሐገር የበጀት ጤናማነት ፤ ሐገሪቱ መሰብሰብ በእምትችለው ግብር መጠን ብቻ ላይ ሳይሆን ያን የሰበሰበችውን ገቢ ፤ሐገራዊ ምርታማነትን ለማሳደግ መጠቀም የእምትችል በመሆን እና ባለመሆኗ ላይ ይወሰናል።

አንድ መንግሥት ለግብር አመንጭው የሕበረተሰብ ክፍል የኢኮኖሚ ጤና ሳይጠነቀቅ ፤ ገቢውን በማሳደግ ላይ ብቻ አተኩሮ ፤ በቻለው መጠን ከፍተኛ የግብር ገቢ ለመሰብሰብ ሲሠራ ፤ በእዚክ አካኼዱ ኢከነሚ እየገነባ ሳይሆን ፤ የዛሬ የበጀት ፍላጎቱን ለሟሟላት የሐገሪቱን መጻዒ/ነገ እየሰዋ ነው የእሚሆነው ፤ ያም የእዳ ጫና የእሚያመጣውን ቆሞ የቀረን ኢከነሚ ያስከትላል።

በተመሳሳይ ፤ አንድ መንግሥት ተገቢ ይሁን ተገቢ ባልሆነ መልኩ የሰበሰበውን ገቢ ፤ ከአቅም ግንባታ ይልቅ ፤ ቀልብ ሳቢ (Prestige projects) እና የፍጆታ ፕሮጀክቶች (Consumption Projects) ላይ

ብቻ ሲያተኩር ፤ የበጀት አቅሙ ከእለት እለት እየተዳከመ በመኼድ ፤ ይኽን አካኼዱን ማስቀጠል የእሚሳነው ኹኔታ ነው የእሚፈጠረው።

እንደገናም ፤ በኢኮነሚ ውስጥ የግሉ መስክ ፤ ለማስፋፊያ እና ለእድገት የእሚፈልገውን ገንዘብ የማግኘት እድሉ እንዲጠበቅ (To avoid "crowding out[6]") ፤ መንግሥት በግብር ይኹን በብድር ገቢ ሲፈጥር - የእሚጠቀመው የግብር ሆነ የወለድ መጠን የግሉን መስክ ለንግድ ሥራ የእሚያስፈልግ ገንዘብ በማሳጣት ገፍቶ ወደ ጥግ የእሚያወጣው መሆን የለበትም። በተመሳሳይም ፦ በግብር ወይንም በብድር ያገኘውን ገቢ ፤ አቅም ግንባታን ቅድሚያ በሰጠ መልኩ ለማውጣት መጠንቀቅ አለበት።

የበጀት አጠቃቀም ቅደም ተከተሉ እንደ እሚከተለው መሆን አለበት ፦

1. **መሠረተ ልማት :** የኢኮነሚውን ደም የእሚያዘዋውሩ ፦ መንገዶች ፣ ባቡሮች ፣ የኤንፎርሜሽን ግሪድ ፣ የኃይል ግሪድ ፣ ግንባታ ማስቀደም አለበት ፤ በሐገሪቱ ውስጥ ንግድ ለመንገድ የእሚያስፈልገውን ወጪ እንዲቀንስ።

2. **የሰው ኃብት ልማት:** ከእዚያም ዜጋው በኢከንሚው ውስጥ ከፍተኛ አምራች ሆኖ የመሳተፍ አቅሙ እንዲጨምር ፤ የሕብረተሰቡ ጤና እና ትምሕርት ላይ ኢንቨስት ማድረግ ።

3. **የተመረጡ የድህነት ቅነሳ እና የማሕበራዊ ዋስትና ሥራ :** በስትመጨረሻም ችግረኛ የሕብረተሰብ ክፍሎች ዜግችን ከተረጅነት ማውጣትን ታሳቢ ያደረገ የድህነት ቅነሳ እና የማሕበራዊ ዋስትና ላይ ኢንቨስት ማድረግ ይገባዋል።


የአንድ ሐገር በጀት በእዚኽ መልኩ ሲሰበሰብ እና ወጪ ሲደረግ ፤ እያንዳንዷ ዶላር የሐገሪቱን የምርታማነት ጡንቻ ለማፈርጠም የእምታገለግል ማባዣ ነው እምትሆነው።

በእዚኽ መልኩ ምርታማነት ሲያድግ ፤ የምርታማነት ዕድገቱ የግብር ከፋዩን ግብር የመክፈል አቅም ያሳድጋል ፤ ያ በተራው መንግሥት ብድር ወስዶ ምርት አሳዳጊ ውጪዎችን የማውጣት አቅሙን ይጨምራል።

ይኽም እርስ በእርሱ ተመጋጋቢ የሆነ ፤ የበጀት አቅም መጨመር የኢከነሚውን መዋቅራዊ ለውጥ መጨመር ፤ የኢከነሚው መዋቅራዊ ለውጥ መጨመር የበጀት አቅም መጨመርን እያስከተለ ፤ በእዚኽ ዑደት ቀጣይነት ያለው ዕድገት ይፈጠራል።

---

[6] Crowding out is an economic theory where increased government spending and borrowing (deficit spending) reduces private sector investment. By demanding more loanable funds, the government drives up interest rates, making it more expensive for businesses and consumers to borrow, invest, or consume.




## 2.5.2 ታሪካዊ ማሳያዎች (የስኬት እና የክስረት ታሪክ)

### *2.5.2.1 አሜሪካ*

የዛሬዋ አሜሪካ በብድር ይኹን በግብር ገቢ የመሰብሰብ ችግር ባይኖርባትም ፤ ያንን ገቢ የእምታደላድልበት (Allocation) አግባብ ፤ ከእንቨስትመንት ወደ ፍጆታ ተሻጋግሯል(From “Investment” to “Consumption.”)።

በአሁኑ ሰዓት የአሜሪካ በጀት ለጥናት እና ምርምር እንዲኹም ለመሠረት ልማት ማዋል የእሚችለውን ገንዘብ በከፍተኛ ደረጃ በመቀነስ ፤ አስገዳጅ በሆኑ የማሕበራዊ ዋስትና እና የብድር ወለድ ክፍያዎች (Mandatory welfare spending and interest payments) ተይዟል ።

አንድ መንግሥት በትሪልዮኖች ተበድሮ የወደፊት አቅም ግንባታ ላይ ሳይሆን የዛሬ ፍጆታ ላይ የሚያውል ከሆነ ፤ በእድገት ላይ ኢንቨስት እያደረገ ሳይሆን ፤ የሐገሪቱን የወደፊት የማደግ አቅም አስይዞ ብድር እየተበደረ ነው እሚሆነው።

ውጤቱም ፡- በአግባቡ ኢንቨስት ስለ አልተደረገ ፤ እያደገ በእሚኼድ ምርታማነት ፤ የተበደረውን ብድር መክፈል የእማይችል እና በእየግዜው እየናረ የእሚኼድ የእዳ ጫና ነው የእሚሆነው ፤ ያደግሞ የሐገሪቱን የወደፊት የበጀት አቅም ያዳክማል።

## 2.5.3 ዓይነተኛ የክስረት ታሪኮች : ቻይና እና ጀርመኒ

### *2.5.3.1 ቻይና*

በቻይና በአሁኑ ሰዓት የእሚስተዋለው የኢኮኖሚ ቀውስ የፋይናንስ ስረዓትን በገበያ ሳይሆን በዘፈቀደ የመምራት ዓይነተኛ ውጤት ነው።

ቻይናዎች ፋይናንስን ፤ የገበያ የዋጋ ስረዓት ነጸብራቅ ወይንም ምልክት ሳይሆን አስተዳደራዊ መሣሪያ አድርገው ነው የእሚያዩት። በፓርቲ ስብሰባ ላይ ያስቀመጡትን የዓመታዊ የዕድገት ግብ ለማሳካት ሲሉ ፤ እድገቱን የእሚመጥን ጥየቃ (Demand) ኖረ አልኖረ ፤ በገበያ ውስጥ ገንዘብ ስለ እሚረጩ ፤ በሐገር ደረጃ ከአቅም በላይ የማምረት ችግር ውስጥ በተደጋጋሚ ይገባሉ።

ሰው የእማይጠቀምበት እና የትም የእማይወስድ ድልድይ በመገንባት የኢኮኖሚ ምርት ቁጥርን ለማሳደግ አንድ መንግሥት ሲጥር ፤ ምርታማነትን ያሳደገ ዕድገት ሳይሆን ኢንቨስትመንት የወለደው ዕድገት ነው እሚኖረው(When you build “bridges to nowhere” or cities that remain empty, you are generating “investment-led growth” that doesn’t actually raise productivity)

ይኸ ዓይነቱ ገንዘብ በማፍሰስ የእሚፈጠር ዕድገት ፤ በአቅርቦት እና በጥየቃ (Supply and demand) ላይ ስለ እማይመረኮዝ ፤ ሞትእንቢ (Zombies) የሆኑ በድጎማ ኃይል ብቻ የቆሙ የንግድ ተቋማትን እና ፕሮጀክቶችን ነው የእሚፈጥረው።

በስተመጨረሻም ፡- የብድር ጫናው አንድ ኢኮኖሚ መቋቋም ከእሚችለው በላይ ይሆን እና የኢኮኖሚ ቆሞ መቅረትን ያስከትላል ፤ ብቁ አምራች ያልሆኑት ኩባንያዎች አንቀው እየያዙት።

#### *2.5.3.2 ጀርመን*

በአንጻሩ ጀርመን ደግሞ ፤ መጠኑን ያለፈ ጠንቃቃ የበጀት አጠቃቀም ፤ የእሚያስከትለው ጉዳት ማሳያ ነች። በሕገ መንግሥታቸው ውስጥ የመንግሥትን የመበደር አቅም የእሚገድብ ድንጋጌ በማስቀመጥ ፤ ብድራቸውን ከጂዲፒያቸው (debt-to-GDP ratio) አንጻር በጣም ዝቅተኛ ማድረግ ችለዋል።

በእዚኸ አካኼድ ግን የእዳ መጠናቸውን ዝቅተኛ ለማድረግ ከመወሰናቸው የተነሳ ፤ አስፈላጊ የሆነ የመሠረተ ልማት እደሳ ዓይነት ወጪዎች እንኳን ስለ አስቀሩ ፤ ሐገራዊ የማምረት አቅማቸው ገደቡ ላይ ደርሷል።

ከፍተኛ የመክፈል አቅም ላላቸው እንደ ባቡር እና የዲጅታል ግሪድ ማሻሻያ ፕሮጀክቶች እንኳን ለመሥራት ፤ በሕገ መንግሥቱ ተገድበው ብድር ስለ እማይወስዱ ፤ መሠረተ ልማታቸው እየበሰበሰ ነው።

ይኸ ዓይነቱ አጉል ወግ አጥባቂነት ፤ ገንዘብ ቁጠባ ሳይሆን ፤ ክፍያን ከነወለዱ ማዘግየት ነው።

ኢኮኖሚያቸው የእሚያመጣውን ትርፍ ፤ ወደ ኢኮኖሚው የደም ስሮች መልሰው ኢንቨስት ባለማድረግ ፤ የኢኮኖሚ ኃያል ያደረጋቸውን የኢንደስትሪ ምርታመነት እያሽመደመዱት ነው።

### 2.5.4 ድምዳሜ

አግባብነት ያለው የበጀት አጠቃቀም ፤ ብዙ ገቢ ከመሰብሰበብ በላይ ፤ የተሰበሰበውን ገቢ ምርታማነት በእሚያሳድግ መንገድ መደልደል/ማውጣት የመቻል ጥበብ ነው።

መንግሥታት ገቢ የማሰባሰብን ነገር ፤ የግብር ከፋይ ማሕበረሰቡን አቅም ሳያገናዝቡ ብዙ ግብር የማስከፈል ጉልበት አድርገው ከተመለከቱት እና ገቢውን ሲያደላድሉ/ሲያወጡ ደግሞ በፍጆታ እና የዝና ፕሮጀክቶች (Financing consumption or prestige projects) ላይ ካተኮሩ ፤ የነገ ዕጣፈንታቸውን ዛሬ ላይ ያባክኑታል።

የበጀት ፖሊሲ ፦ ገቢ የማሰባሰብ ኺደቱ የግሉን መስክ ራስን የማሳደግ አቅም በእማይነካ መልኩ ሲሆን እና በጀቱም በእሚደለደልበት ግዜ በእሚከተለው አግባብ በጥንቃቄ ተዋረዱን ጠብቆ ፦ በቀዳሚነት ፦ የንግድ ድርጅቶችን ወጪ ለመቀነስ በእሚያስችል መልኩ በመሠረተ ልማት ግንባታ ላይ ሲውል ፣ ከእዚያም የዜጎችን ምርታማነት ለማሳደግ በጤና እና በትምሕርት አቅም ግንባታ ላይ ሲውል ፣ በስተመጨረሻም ዝቅተኛ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ከተረጂነት ማውጣት ታሳቢ ባደረገ መልኩ ማሕበራዊ ድጎማ ላይ ሲውል ነው ፤ ቀጣይነት (Sustainable) ያለው የበጀት ፖሊሲ የእሚሆነው።

ከበጀት አስተዳደር አንጻር የዓለም ሐገራትን ታሪክ ስናይ ፤ የተሳካላቸው እና ያልተሳካላቸው ሐገራትን እናገኛለን።

በአሜሪካን ፤ ከፍተኛ መጠን ያለው ከግብር እና ከብድር የእሚገኝ የበጀት ገንዘብ ፤ የምርታማነት መጠንን በማሳደግ መንግሥት የእሚበደረውን ብድር የመክፈል አቅሙን ሊያሳድጉ በእሚችሉ መልኩ ኢንቨስት ከማድረግ ይልቅ ፤ ለማሕበራዊ ዋስትና እና ለብድር ወለድ ክፍያ ስለ እሚውል ፤ የበጀት አቅም መዳከምን እየጨመረ ነው።

በአንጻሩ ቻይና ደግሞ ፤ በፓርቲ ስብሰባ ላይ የእሚያስቀምጡትን የዕድገት ግብ ለማሳካት ሲሉ ፤ ገንዘብ እንደ አፈር እየዘገኑ ለኩባንያዎቻቸው በገበያ መርኽ ፥ ያተርፋል አያተርፍም በእሚል ሳይሆን በአስተዳደራዊ ውሳኔ ስለ እሚያከፋፉሉ ፤ ገዢ የሌለው ምርት አምራች በመሆናቸው በድጎማ እንጂ በትርፋማነት በሥራ ላይ መቆየት የእማይችሉ ሞትእምቢ (zombie) የሆኑ እና ኢኮነሚዋን እያጎበጡ ያሉ ኩባንያዎች ፈጥረው ፤ ከአቅም በላይ እያመረቱ ነው።

ጀርመን ደግሞ የእዚኽ ተቃራኒ ነች ፤ ሕገመንግሥታዊ የሆነ የእዳ ጣራ ገደብ የመበደር አቅማቸውን ገድቦት ፤ ምንም እንኳን የእዳ መጠናቸውን ቢያሳንሰውም ፤ የመሠረተ ልማት ማሻሻያ እና ማስፋፊያ ኢንቨስትመንት እንኳን ማድረግ እንደ አይችሉ አድርጎ ፤ የሐገሪቱ መሠረተ ልማት እየበሰበሰ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ አምራችነታቸውን እየጎዳው ነው።

የእነ እዚኽ ሦስት ሐገራት ልምድ የእሚያሳየን ፤ በበጀት ጉዳይ ጠንካራ የገቢ ምንጭ ቢኖር እንኳን ያንን ገቢ ባግባቡ የኢኮኖሚውን ብድር ከፋይነት ለማሳደግ በእማይችል መንገድ ወይንም የበጀት ጉድለትን ሳይፈሩ ገንዘብን እንደ አፈር እየዘገኑ ለአምራች ድርጅቶች ማከፋፈል ወይንም የበጀት ጉድለትን ፍራቻ

ኢኮኖሚው መክፈል የሚችለውን ብድር እንኳን አለመበደር ልክ እንደ አልሆኑ እና አንድ ሐገር በአንዱ ሳይሆን በኹሉም መስክ ፦ በአሰባሰቡም ፣ በአበዳድሩም ፣ በአከፋፈሉም እንደ እዚኹም በአደላደሉም መስክ ትክክለኛ የበጀት አስተዳደር የሚይስፈልጋት መሆኑን ነው።


አጉል ወግ አጥባቂነት ወይንም በጀትን እንደ አፈር እየዘገኑ ማከፋፈልም የማይበጅ መሆኑን እና በጀት ጥንካሬ እና ዘላቂነት የሚኖረው ምርታማነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ሲሰበሰብ እና ሲደለደል ወይንም ወጪ ሲደረግ መሆኑን ነው።

## 2.6 ዋናው ነገር

የሐገር ውስጥ ይኹን ዓለም ዓቀፋዊ ኢኮኖሚ ፤ እንደ ማንኛውም ሌላ ስረዓት (System) ፤ ሰዎች የሚፈጥሩት ሳይሆን ሰዎች በፍለጋ እና በምርምር የሚደርሱበት ወይንም የሚያገኙት ፤ የራሱ መስተጋብር እና መስተጋብሩን የሚገዛ ሕግ ያለው ነው።

የሰውን የኢኮኖሚ ስረዓት (System) ከተመለከትነው ፤ የሰውን ልጆች የሕይወት ደረጃ የማሻሻል ግብን ለማሳካት የሚሠሩ ሶሥት የኢኮኖሚ ተዋንያኖች ኖረውት እናገኛዋለን ፤ እነርሱም፦

- የሰው ክህሎት
- የሰው ፍላጎት
- እና በሰው ክህሎት የሰውን ፍላጎት የሚያረኩ ምርት እና አገልግሎት ተደርገው የሚቀየሩ የተፈጥሮ ኃብቶች



እነ እዚኽ ሶስት የኢከነሚ ስረዓት ተዋንያን እርስ በእርሳቸው በእሚያደርጉት መስተጋብር የሰውን ልጅ የሕይወት ደረጃ ከፍ የእሚያደርጉበት ፤ የተሻለው አግባብ (The optimal way) የቱ ነው የእሚለው ወይንም የኢከነሚ ሕጉ በሰው የእሚፈጠር ሳይሆን ሰው በፍለጋ ወይንም በጥናት እና ምርምር የእሚደርስበት ነው።

ብዙዎች የተሻለው አግባብ (The optimal way) የቱ ነው በእሚል ብዙ ስለ ተመራመሩ ፣ አንዳንዶች እንዲያውም የተሻለውን አግባብ (The optimal way) ለመፍጠር በመሞከራቸው ፤ ኢከነሚያዊ ልማት እንዴት ሊመጣ ይችላል የእሚሉ ፦ ወሳኙ መልከዓምድር ነው ፣ ባሕል ትልቅ ቦታ አለው ፣ ርዕዮት (ገበያ መር ፣ መንግሥት መር ፣ ቅይጥ) ዋና የእሚያደርጉ ፣ የሐገራትን ታሪክ ዋና የእሚያደርጉ ፣ ወዘተ በርከት ያሉ የኢከነሚ ልማት መንገዶች ነን የእሚሉ መላምቶች አሉ።

የዓለማችንን የኢከነሚ ታሪክ ማስረጃ አድርገን ከወሰድን ግን ፤ እነ እዚኽ ከእላይ የተዘረዘሩት እንደ መልከዓምድር (Geography) ፣ ባሕል፣ ገበያ መር ፣ መንግሥት መር ፣ ወዘተ ያሉት ልዩነቶች ውጫዊ ወይንም የቅርጽ እንጂ የይዘት ልዩነቶች እንደ አልሆኑ እና እነርሱ ምንም ይኹኑ ምን ፤ በእዚኽ አመክንዮው በእሚለው ምዕራፍ ውስጥ ያየናቸውን አምስት ኹኔታዎች (Five Conditions) በጥሩ ኹኔታ የተገበሯቸው ሐገራት ፤ ከአንድ አንድ ሊባል በእሚችል ኹኔታ ፤ የጸና እና ቀጣይነት ያለው (Robust and Sustainable) ዕድገት ሲያስመዘግቡ ፤ በአንጻሩ ከእነ እዚኽ አምስት ኹኔታዎች አንዱን ወይንም ሌሎቹን በጥሩ ኹኔታ ከመተግበር ችላ ያሉ ሐገራት ፤ ሲከፋ በአምራችነት ሳይሆን የተፈጥሮ ኃብት ላይ እሴት ሳይጨምር በመሸጥ ላይ የተመሠረተ ኋላ ቀር ኢከኖሚ (Extractive Underdeveloped Economy) ሲሻል ደግሞ በመካከለኛ ገቢ ወጥመድ (Middle Income Trap) የተያዘ ሐገር የመሆን አደጋ ሲገጥማቸው ነው የዕሚታየው።

ከእዚኽም ትልቁ ጉዳይ ፤ እነ እዚኽን አምስት ኹኔታዎች የማክበር እና የማስፈጸም ጉዳይ (Adherence to these conditions) ፤ አንድ ሐገር በእምትመራበት የፖለቲካ ስረዓት ዓይነት ወይንም በእምትከለው የፖለቲካ ርዕዮት የተወሰነ አለመሆኑ ነው።

የነጻነት ዴሞክራሲ (Liberal democracies)፣ ልማታዊ መንግሥት ፣ አንድ አንዴ እንዲያውም ፍጹም አምባገነናዊ መንግሥታት እነ እዚኽን አምስት ኹኔታዎች ወይንም መርሆች በቻሉት መጠን ተጠጋግተው ተግባር ላይ ሲያዉሉ (When they approximated these principles) ፈጣን ዕድገት አስመዝግበዋል ፤ በአንጻሩ ደግሞ ሐገራት ተመሳሳይ የፖለቲካ ስረዓት ኖሯቸው ለምሳሌ ፦ በተመሳሳይ ዴሞክራሲያዊ ወይንም አምባገነናዊ ሆነው ፤ እነ እዚኽን አምስት ኹኔታቸው ከመቀራረብ (Approximate) አንጻር ሲለያዩ ፤ የኢከነሚ ዕድገታቸው ይለያያል ፤ ጥሩ አድርገው የተቀራረቡት እያደጉ ፤ መቀራረብ ያልቻሉት በቆሞ ቀር ኢከነሚ ውስጥ ለመኖር እየተገደዱ።

ሐገራት እነ እዚኽን አምስት ኹኔታዎች ከማሟላት አንጻር የተሻሉ ሆነው ሲገኙ - የበሰለ ክህሎት የተፈጥሮ ኃብትን ለሰው የእሚጠቅም አገልግሎት እና ምርት አድርጎ እንዲያመጣ የተሻለ ዕድል ይፈጥራሉ። እነ እዚኽ አምስቱ ኹኔታዎች በአግባቡ በእማይተገበሩበት ግዜ ፤ ክህሎት ይባክናል ፤ የተፈጥሮ ኃብትም "ሙት ካፒታል" ሆኖ ተቀብሮ ይቀራል።

*<u>ስለ እዚኽ ፡- ከኢከነሚ ዕድገት አንጻር ወሳኙ ፤ አንዲት ሐገር ፡- ዴሞክራሲያዊ ፣ ሶሻሊስታዊ ፣ ብሔርተኛ ፣ ገበያ መር ፣ ወይንም ከፍተኛ የተፈጥሮ ኃብት ያላት ወይንም የሌላት መሆኑ አይደለም ፤ ይልቁንም ፡- የኢከነሚ ተቋሞቿ ፡- በእዚያች ሐገር ውስጥ የኢከነሚ ስኬት የምርታማነት እንጂ ከፖለቲካ ስልጣን ጋር ያለ ቅርርብ ውጤት እንደ አይሆን በማድረጋቸው ይወሰናል።</u>*

ይኽ ነው እንግዲኽ ፤ የኢከነሚ ዕድገት ጉዳይ ፤ በዋናነት የርዕዮት ሳይሆን የአንድን ሐገር ተቋማት ምርት አሳዳጊ በእሚሆኑበት መንገድ ለማዋቀር የእሚያስፈልገው ዕውቀት የመያዝ ወይንም ያለመያዝ እና ከያዙም በኋላ የእርሱም አፈጻጸም ጉዳይ የእሚያደርገው። በአግባቡ ከአወቁት አፈጻጸሙን እያቀለለው።

ዘላቂነት ያለው የምርታማነት ዕድገት ማምጣት በእሚችሉበት መንገድ ተቋማትን ማዋቀር ያወቁበት ሐገራት ፤ መነሻቸው ምንም ይኹን ምንም የኢከነሚ ዕድገትን ያስመዘግባሉ። በአንጻሩ እነ እዚኽን መርህዎች የእሚዘነጓቸው ወይንም ሆን ብለው የእሚያስቀሯቸው ፤ በሐገራቸው ውስጥ ንግድ ለመንገድ የእሚኖረውን ድባብ እያጨለሙ ፤ ኃብት በዋናነት ፡- ለወቅታዊ ፍጆታ (Consumption) ፣ ታማኝነትን ለመግዛት (Patronage) እና ለቀውስ አስተዳደር (Crisis Management) ብቻ እንዲውል በማድረግ ፤ አምራች ሳይሆን በላተኛ ኢከነሚ በመገንባት ራሳቸውን ያቆረቁዛሉ።

ስለ እዚኽ ፡- አንድ ሰው በዓለም ላይ የተለያዩ ሐገራት ለምን የተለያየ የዕድገት ደረጃ ኖራቸው ብሎ ከጠየቀ ፡- መልሱ ሐገራቱ የተለያየ የመሰልጠን ዕምቅ አቅም ስለ ኖራቸው ነው የእሚል ሳይሆን ይልቁንም እነ እዚኽን አምስት ኹኔታዎች በጥሩ ኹኔታ ለመተግበር የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋሞቻቸው ካላቸው ዝግጅት ጋር የተያያዘ ነው ፤ የእሚል ነው።

ልክ የፊዝክስ ሕግ በዓለም በሙሉ በአንድ ዓይነት መንገድ እንደ እሚሠራው ፤ እነ እዚኽ አምስት ኹኔታዎች በየትኛውም ሐገር ውስጥ እንደ አተገባበራቸው ተመሳሳይ ውጤት ያመጣሉ። ሐገራት በኢከነሚ ልማት ደረጃቸው ከተለያዩ የእሚለያዩት እነ እዚኽ አምስት ኹኔታዎች በጥሩ ኹኔታ ለማስፈጸም ከደረሱበት (Approximation) አንጻር ነው።

ይኽም የኢኮኖሚ ዕድገትን በዋናነት ተቋማት የማቀራረብ (Approximation) ዕውቀት ጉዳይ ያደርገዋል ፡- አንድ ማሕበረሰብ መዋቅራዊ ለውጥ ሊያመጡ በእሚችሉ መልኩ የኢከነሚ ተቋማትን የማደራጀት ዕውቀት ኖሮት እና በእዚያ መልኩ የማሕበረ ኢከነሚ ተቋማቱን ለማዋቀር በመቻል እና ባለመቻሉ ላይ ፤ ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት የማምጣት ኹኔታው ስለ እሚወሰን።

# 3 መመርመሪያው ማሽን

በእዚኽ ምዕራፍ ፤ ከእዚኽ በፊት በነበረው በምዕራፍ 2 ያቀረብኩትን አምስቱ ተቋማዊ ኹኔታዎች እና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸውን ተመርኩዤ ፤ የሐገራትን ኢኮኖሚ በአኃዝ በተደገፈ መልኩ ከአምስቱ ኹኔታዎች አንጻር ለመመዘን የእሚሞክር እና በምዘናውም መሠረት የሐገራቱን ኢኮኖሚ ጥንካሬ ከድካም መዝኖ ፤ በነፍስ ወከፍ ገቢ ላይ በተመሠረተው የሐገራት የኢኮኖሚ ደረጃ መሠረት ደረጃቸውን ለማግኘት እና ከአምስቱ ኹኔታዎች አንጻር ከወቅታዊ አፈጻጸማቸው ተነስቶ ኢኮኖሚያዊያቸው ፤ ምንዓይነት ዕድል እና አደጋ ሊገጥመው እንደ እሚችል ለመተንበይ የእሚሞክር መመርመሪያ ማሽን (Diagnostic Engine) አስተዋውቃለኹ።

የምርመራው ማሽን ከአስምቱ ኹኔታዎች አንጻር ምርመራውን በእንዴት ያለ መንገድ እንደ እሚያካኺድ ዕንመልከት።

የምርመራ መሣሪያው ከእዚኽ በታች ያሉትን አምስቱን ኹኔታዎች ፡-

1. የግል ንብረት
2. የንብረት ተንቀሳቃሽነት

3. የሕግ ሥረዓቱ ነጻ እና ገለልተኛነት

4. የንግድ ክፍትነት እና

5. የበጀት አስተዳደር ጥበብ

በኹለት ዋና ዋና እና በአንድ ንዑስ ፤ በጠቅላላው በሦሥት በቅደም ተከተል ፡- አንኳር ( Core or Stabilizer) ፣ አጥዳፊ (Accelerator or Mobilizer) እና የፈጠራ ማጥለያ (Innovative Sieve) በእሚባሉ ጎራዎች በመከፋፈል ይጀምራል:-

አንኳር (መሠረታዊ) የእሚባሉት ኹኔታዎች:

- የግል ንብረት ባለቤትነት
- የሕግ የበላይነት
- የበጀት አስተዳደር ጥበብ

አጥዳፊ (አንቀሳቃሽ) የእሚባሉት ኹኔታዎች:

- የንብረት ተንቀሳቃሽነት (Asset Mobility)
- የንግድ ክፍትነት (Trade Openness)

የፈጠራ ማጥለያ:

- በግል ንብረት ውስጥ እንደ አመላካች የእሚቀመጠው የውድድርያገደብ (Contestability) አንድ ሐገር የመካከለኛ ገቢ ወጥመድን በፈጠራ ኃይል ሰብራ መውጣት ትችል አትችል እንደ ሆን የእሚወስን ነው

በአንድ ሐገር ውስጥ አንኳር የእሚባሉት ኹኔታዎች ጠንከር ብለው ሲገኙ ፤ በእዚያ ሐገር የተረጋጋ እና በእዚያ ሐገር የእሚገኙ ቤተሰቦች ፣ የንግድ እና የመንግሥት ተቋማት ፤ ዘላቂ የሆኑ ሥራዎችን ለመሥራት ረዘም ያሉ ብድር ለመውሰድ ፣ ኢንቨስት ለማድረግ ፣ በነገ ለመወራረድ (Risk taking) እንዲችሉ እና በእዚኽም ሐገራቸውን ከዝቅተኛ የኢከነሚ ደረጃ ወደ ከፍተኛ የኢከነሚ ደረጃ ወውሰድ የእሚችሉበት የማደግ ምሕዳር ይፈጥራሉ።

ሆኖም ፤ አንኳር ኹኔታዎቹ ፤ ምንም እንኳን ለኢከነሚያዊ ዕድገት አስፈላጊ ኹኔታዎች ቢሆኑም ከአንድ የእድገት መደብ ወደ ቀጣይ የእድገት መደብ ለማሸጋገር በቂ አይደሉም።

እነ እዚኽ መደቦች ዓለም ባንክ ሐገራትን በዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ መሠረት የእሚከፋፍልበት መደቦች ናቸው፡-

- ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ኢኮነሚዎች
- ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ያላቸው ኢኮነሚዎች
- ከፍተኛ መካከለኛ ገቢ ያላቸው ኢኮነሚዎች
- ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ኢኮነሚዎች

እናም አንኳር ኹኔታዎቹ ለምሳሌ ፡- የልኬት ደረጃቸው 2 ከሆነ እና የአጥዳፊ ኹኔታዎቹ ግን 1 ከሆነ ፤ ያ ሐገር ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ውስጥ ከመገኘት ይልቅ ፤ ዝቅተኛ ገቢ ውስጥ የመገኘት እድሉ ይበልጣል።

ስለእዚኽ፡- በአንኳር ኹኔታዎች ላይ ሐገራት ጥሩ አፈጻጸም ሲኖራቸው ፤ በእዚያ በእሚገኙበት የኢኮነሚ መደብ ፤ የእሚገኘውን የማደግ ዕድል አሟጠው መጠቀም ችለዋል ወይንም ይችላሉ ሆኖም ፤ ከአሉበት መደብ ወደ እሚቀጥለው የመሸጋገራቸው ጉዳይ ፤ አጥዳፊ የእሚባሉትን ፤ የንብረት ማንቀሳቀስ እና የንግድ ክፍትነትን ፤ ባጠነከሩበት ልክ የእሚወሰን ይሆናል።

በመሆኑም ፡- አንኳር የእሚባሉት ኹኔታዎች ዋና ጠቀሜታ ፤ ሐገራት በእሚገኙበት የኢኮነሚ መደብ ውስጥ ያላቸውን የማደግ ዕድል አሟጠው እንዲጠቀሙ ነው ፤ በሌላ መልኩ ደግሞ ሐገራት በአሉበት የኢኮነሚ መደብ ውስጥ ሆነው አንኳር ኹኔታቸውን ከመደቡ በላይ ካላጠነከሩ ባሉበት ለመረገጥ የእሚገደዱ ይሆንና ፤ የአጥዳፊ ኹኔታዎቹን ፋይዳ እምባዛም ያደርገዋል ፤ አንድ ሐገር ባለበት ኹኔታ ያሉትን የማደግ ዕድሎች አሟጦ ካልተጠቀመ ፤ አጥዳፊ ኹኔታው ወደ እሚቀጥለው የኢኮነሚ ደረጃ ሊያሻግረው ስለ እማይችል።

ከእዚኽም መረዳት እንደ እምንችለው ፤ አጥዳፊ የእሚባሉት ኹኔታዎች በእራሳቸው መዋቅራዊ ለውጥ ወይንም ከአንዱ መደብ ወደ ሌላው መደብ የማሸጋገር ሥራ መሥራት አይችሉም ፤ ሆኖም ካፒታል የእሚከማችበትን እና ቴክኖሎጂ የእሚሰርጽበትን ፍጥነት እንደ እዚኹም ማክሮኢኮኖሚው ርጋታ እና ጽናት የመኖሩን ኹኔታ በማገዝ ፤ ኢኮነሚው ከነበረበት ወደ እሚቀጥለው ደረጃ መሻገር እንዲችል አመቺ ኹኔታን ይፈጥራሉ።

ስለእዚኽ፡- ሐገራት በአጥዳፊ የኢኮነሚ ኹኔታዎች ካሉበት የተሻለ አፈጻጸም ሲኖራቸው ፤ ከእሚገኙበት የኢኮነሚ መደብ በመውጣት ፡-

- ከዝቅተኛ ገቢ ኢኮነሚ ወደ ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ኢኮነሚ
- ከዝተኛ መካከለኛ ገቢ ኢኮነሚ ወደ ከፍተኛ መካከለኛ ገቢ ኢኮነሚ
- ከከፍተኛ መካከለኛ ገቢ ኢኮነሚ ወደ ከፍተኛ ገቢ ኢኮነሚ

ለመሸጋገር የተሻለ ዕድል ይኖራቸውል።

የግል ንብረት አመላካች የሆነው የውድድርገደብ (Contestability) ፤ በአንድ ሐገር ውስጥ የእሚገኘው ኃብት እና ንብረት ፤ ኦሊጋሪክክ (Oligarchic) በመሆን እራሱን ከአዲስ በፈጠራ ብቃት በመወዳደር የገበያ ድርሻ ለመጋራት ከእሚመመጡ ተወዳዳሪዎች ለመከላከል ሕጉን እና ሌላ ክልከላዎችን ይጠቀም ወይንስ አይጠቀም እንደ ሆነ የእሚወስን ነው። በእዚያም ሐገር ፤ የውድድርገደብ (Contestability) ከኖረ ፤ ፈጠራ እና ውድድር ሕጋዊ እና ሕጋዊ ባልሆኑ መንገዶች ስለ እሚዳከም ፤ ያ ሐገር የመካከለኛ ገቢ (Middle Income) ወጥመድ የእሚባለውን ሰብሮ ወደ ከፍተኛ ገቢ ሐገር ለማደግ ይሳነዋል ፤ ከፍተኛ ገቢ ሐገር ከሆነም የከፍተኛ ሐገር ቁንጮው ላይ ለመድረስ ይሳነዋል።

ከእዚኽ በታች ያለው ፤ እነ እዚኽ አምስት ኹኔታዎች ፤ የአመላካቾችን ልኬት አማካይ በመውሰድ እና ያንን አማካይ ደግሞ በአራት ጎራዎች በመከፈፈል እንደ እሚለኩ ያሳያል።

እያንዳንዱ ኹኔታ (Condition) የተለያየ ቁጥር ያላቸው አመላካቾች (Indicators) ይኖሩት እና እያንዳንዳቸው አመላካቾች (Indicators) 0 ለዝቅተኛ, 1 ለመካከለኛ እና 2 ለከፍትኛ ከተሰጣቸው በኋላ ፤ ለእየኹኔታው (Conditions) የአመላካቾቹ አማካይ ይወሰዳል ፤ ያም አማካይ በእከተለው መልኩ በአራት ይከፈላል: -

1. 0.0 - 0.49 = 1
2. 0.5 - 0.99 = 2
3. 1.0 - 1.49 = 3
4. 1.5 – 2.00 = 4

በእዚኽም መሠረ ፤ የግል ንብረት ኹኔታ በአንድ ሐገር የእሚኖረው ደረጃ ከእዚኽ በታች ባሉት አራት አመላካቾች (Indicators) አማካይ መሠረት ይሆናል፡-

1. **በእዚያ ሐገር ውስጥ** ፡- የኹሉም የጋራ ንብረት ከሆኑት (አየር፣ ባሕር ፣ ዋና ዋና ወንዞች ፣ እና የአየር ንብረት) ፣ የሉዓላዊ መንግሥት ሥልጣን ብቻ ሊሆኑ ከእሚገባቸው (ገንዘብ ማተም ፣ ብሔራዊ ባንክ ፣ ወታደር ፣ ፍርድ ቤት ፣ ሕግ ማውጣት እና መንግሥታዊ አገልግሎቶች) ፣ እንዲኹም በተፈጥሯዊ ሞኖፖሊ ሥር ሊሆን የእሚገባቸው መሠረተ ልማቶች (ሐገር አቋራጭ ትልልቅ ጎዳናዎች ፣ ዋና ዋና ወደቦች ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ እና ማከፋፈያ **<u>መሠረተ ልማት</u>** ፣ ውኃ የማጣራት እና የማከፋፈል **<u>መሠረት ልማት</u>** ) ፤ ውጭ ያሉት ንብረቶች በሙሉ የግል ንብረት እንዲሆኑ ይፈቀዳል ?
2. **መውስረስ ፡** - በእዚያኽ ሐገር በወቅቱ የገበያ ዋጋ መሠረት የካሳ ክፍያ ሳይደረግ ንብረት መውረስ አደጋ ተወግዷል ?
3. **የውድድርገደብ(Contestability)** - በእዚያ ሐገር ለኢከነሚ ጥቅም የእሚደረገው ውድድር በዜጎች መካከል (በእኩዮች) እንጂ በመደበኛ ዜጎች እና አንዳች ዓይነት ሕጋዊ እና የአሠራር ከለላ ካላቸው ስለ እዚኽም መንግሥታዊ እና የአሠራር ከለላ ባላቸው ዜጎች መካከል (በዜጋ እና ከለላ ባለው ባለኃብት) መካከል እንደ አይሆን የእሚያደርግ ሕግ እና አሠራር አለ ወይ?

ይኸም ማለት ፡- ወደ ገበያ ውስጥ አዲስ ነጋዴዎች ፤ በትንሽ ካፒታል በፈጠራ ፣ በጥራት እና በዋጋ ነባር ባለኃብቶችን ተወዳድረው አሸንፈው የገበያ ድርሻ መያዝ እንዲችሉ የእሚያደርግ ፡- ጠንካራ የሆነ የጸረ ሞኖፖሊ (Robust anti-monopoly) ሕግ ፣ የመክሰር አደጋ ላጋጠማቸው ነጋዴዎች የተቀላጠፈ ክስረት የእሚያውጅቡት አሠራር ፣ የአዕምሮ ንብረት ባለቤትነትን በንቃት የእሚጠብቅ እና የእሚያስከብር የሕግ ስረዓት አለ ወይ ? (ይኽ መኖሩ በአንድ ሐገር ፈጠራ እንዲኖር ትልቅ ምክንያት ነው: አንድ ሐገር የከፈተኛ ገቢ ሐገራት መደብ ውስጥ ለመግባት ፤ የንብረት ባለቤትነት ከመፍቀድ እና ከማክበር አልፎ ፤ ንብረቱ ለተሻለው አምራች እንዲተላለፍ ወደ ማስቻል መምጣት አለበት። የግል ንብረት ባለቤትነት መብት ኦሊጋርኪክ (Oligarchic) ሆኖ ብቻ ከቀረ ፤ አዲስ ባለኃብቶች እንዳይፈጠሩ የእሚገታ እና ኢከነሚው አሮጌውን እያስረጀ አዲስ እየፈጠረ ታዳሽ ኢከነሚ እንደ አይሆን የእሚገታ ፤ አዲሱን የእሚከላከል የአሮጌው ግን ኃብት ዘበኛ ሆኖ ነው እሚቀረው። በአንጻሩ ኃብት ዴሞክራሲያዊ እና ለሕጋዊ ሽሚያ ክፍት ከሆነ (If Democratic and Contestable) ምርታማ የሆነውን ምርታማ ካልሆነው አጥልሎ የእሚለይ ወንፊት ነው የእሚሆነው። የግል ንብረት ባለቤትነት መብት በእዚኽ መልኩ ዴሞክራሲያዊ ሲሆን ፤ ኃብት/ንብረት በአምራችነት እንጂ በቀደመ ወይንም በፖለቲካ ጣልቃ ገብነት እንደ አይተላለፍ በማድረግ የማሕበረሰቡን ኢከነሚያዊ አምራችነት እና ታዳሽነት ያረጋግጣል።)

4. **የሠራተኛው ነጻነት (Labor Freedom)** - ይኽ አመላካች በአንድ ሐገር ውስጥ ሠራተኛው የማምረት ጉልበቱን በምን ያኽል ነጻነት በገበያ ውስጥ ሸጦ ያድራል የእሚለውን የእሚመልስ ነው።

እነ እዚኽ የግል ንብረት አመላካቾች በአንድ ሐገር ዝቅተኛ/መካከለኛ/ከፍተኛ ተብለው የእሚለኩበት ከእዚኽ በታች በሰንጠረዡ ውስጥ በተቀመጠው አግባብ ይሆናል:

| **አመላካቾ** | **ዝቅተኛ (0)** | **መካከለኛ (1)** | **ከፍተኛ (2)** |
|---|---|---|---|
| ባለቤትነት | አብዛኛው የኢከነሚው ክፍል ለግሉ ዘርፍ ዝግ ነው። ቁልፍ ቁልፍ የእሚባሉት እንደ መሬት ፣ ባንክ ፣ ቴሌኮም ፣ ኃይል የማመንጨት ወይንም ትላልቅ ኢንደስትሪዎች | አብዛኛው ዘርፍ ለግሉ ዘርፍ የተፈቀደ ነው ፤ የግሉ ዘርፍም በተፈቀዱት ዘርፎች ውስጥ በስፋት ይሳተፋል ፤ ሆኖም መንግሥት ከፍተኛ ፋይዳ አላቸው የእሚባሉትን እንደ መሬት ፣ ባንክ ፣ | በኹሉም ዘርፍ ሊባል በእሚችል ደረጃ የግል ባለቤትነት ይፈቀዳል። ተፈጥሯዊ ሞኖፖሊ (natural monopolies) ፣ የሉዓላዊ መንግሥት ኃላፊነት ሊሆኑ የእሚገባቸው መንግሥታዊ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | በመንግሥት የተያዙ ወይንም ለግሉ ዘርፍ ዝግ የሆኑ ናቸው። የግሉ መስክ በትንንሽ ንግዶች ፣ ጅምላ እና ችርቻሮ ወይንም በግብርናው የተወሰነ ነው። | ቴሌኮም፣ ኃይል የማመንጨት እና የትራንስፖርት መስኮች በባለቤትነት ይይዛል ወይንም በጥብቅ ይቆጣጠራል። | አገልግሎቶች ፣ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የኹሉም የጋራ ንብረት የሆኑት (ትላልቅ ወንዞች ፣ አየር ንብረት ፣ ወዘተ) በስተቀር ኹሉም ነገር የግል ንብረት መሆን ይችላል። የግሉም መስክ አብዛኛውን የኢኮኖሚ መስክ ይቆጣጠራል። |
| መንግሥታዊ መውረስ | ሕጋዊ ሆነ ተግባራዊ መንግሥታዊ ንብረት የመውረስ አደጋ ከፍተኛ ነው። ንብረት በእሚወረስበት ግዜ የካሳ ክፍያው መጠን ከንብረቱ የገበያ ዋጋ በጣም ያነሰ ነው ወይንም ክፍያው የእሚፈጸመው በጣም በተንዛዛ እና ረጅም ግዜ በእሚወስድ አግባብ ነው። | ሕጋዊ የሆነ የንብረት መብት ዋስትና አለ ሆኖም የሕጉ ክፍተት ፣ የፖለቲካ ተፅዕኖ እና የፍርድ ቤቶች ደካማነት ከፍተኛ የሆነ ከገበያ ዋጋ በታች የሆነ የውርስ ካሳ ክፍያ ወይንም የተንዛዛ የውርስ ዋጋ ክፍያ አደጋ ይደቅናሉ። | መንግሥት ንብረት የእሚውረሰው ግልጽ የሆነ የሕዝብ ጥቅም ለማስከበር ነው ፤ በእሚወርስበትም ግዜ ፈጣን እና በገበያ ዋጋ ላይ የተመሠረተ የካሳ ክፍያ ይፈጽማል። በድንጋጌ እና በተግባር (De jure and de facto) የንብረት ወረሳ አደጋ ዝቅተኛ ነው። |
| የውድድርገደብ (Contestability) | ንብረቶች በጥቂት እና መንግሥታዊ ከለላ ባላቸው (oligarchic) ባለኃብቶች የተያዙ ናቸው። አዲስ ገቢ ነጋዴ ብዙ በሕጋዊ መንገድ እማያሸንፋቸው | ሕጉ በእየመስኩ አዲስ ገቢዎችን እና ውድድር ይፈቅዳል ሆኖም ቢሮክራሲው ፣ የፈቃድ አሰጣጡ ፣ ብድር የማግኘት ፈተናው ፣ ፖለቲካዊ ከለላ ያላቸው ነባር ባለኃብቶች | በሕግም በተግባርም በአምራችነት ተወዳድሮ ገበያ ማግኘት እና የነባር ባለኃብቶችን የገበያ ድርሻ መሻማት ይቻላል። በሐገሪቱ የጸረ ሞኖፖሊ ሕጉ በአግባቡ ይሠራል |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ክልከላዎች አሉበት ። ፖለቲካዊ ክለላ ያለው ሞኖፖሊ እና የጥቂት ባለፆብቶች ቡድን በርካታ ናቸው። ከሥሮ እንደገና ለመጀመር በጣም ከባድ ነው(Bankruptcy ineffective.) | የእሚፈጥሩት ተግዳሮት የሕጉን ተፈጻሚነት አዳጋች ያደርጉታል። | (Anti-trust enforcement exists) ፣ የክስረት ሕጉ በአግባቡ ይሠራል (bankruptcy works)፣ አዳዲስ ነጋዴዎች ነባሮቹን በጥራት እና በዋጋ ተወዳድረው አሸንፈው መተካት ይችላሉ። |
| የሠራተኛው ነጻነት (Labor Freedom) | ሠራተኞች የእሚቀጠሩበትን መስክ የመምረጥም ሆነ ሥራ በፈቃዳቸው የመልቀቅ መብት የላቸውም። ሕጋዊ ወይንም የአሠራር ክልከላ አለባቸው ፦ ለምሳሌ ፦ ሥራ የእሚያገኙት በደላላ ነው ፣ የግዳጅ ሥራ ሊሠሩ ይችላሉ ፣ ሥራ ለመልቀቅ ብዙ ቁጥጥር አለባቸው) ከእዚኽ የተነሳ ሠራተኞቹ ከቀጣሪያቸው ወይንም ከመንግሥት ጋር በነጻ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ግንኙነት የላቸውም። | ሠራተኞች ሥራ መምረት ይችላሉ ነገር ግን በብዙ ትግል ነው ያን ማድረግ የእሚችሉት። የአሠሪ እና ሠራተኛ ሕጉ ድርቅ ያለ ነው ፤ ሠራተኛ ማባረር ከፍተኛ ዋጋ ያስከፍላል ፣ በኢኮኖሚው ውስጥ የኢመደበኛው የሥራ መስክ ሰፊ ነው። ሠራተኛ በቀላሉ ለመቅጠር እና ለማባረር ያለው ክልከላ ብዙ ነው። ከእዚኽ የተነሳ ሠራተኛው ወደ አሻው ለመንቀሳቀስ ብዙ ችግር አለብት። | ሠራተኞች እንደ አሻቸው ሥራ መምረጥ፣ መቀየር እና መልቀቅ ይችላሉ። ሠራተኛ መቅጠር እና ማባረር በአንጻራዊነት ቀላል ነው። ከእዚኽም የተነሳ ሠራተኛው ከዘርፍ ወደ ዘርፍ ወይንም ከድርጅት ወደ ድርጅት በቀላሉ ይንቀሳቀሳል። |

በእዚኽ መሠረት የንብረት ባለቤትነት ኹኔታን በአመላካቾቹ አማካኝነት በኢትዮጵያ ከመዘነን ፤ የእሚኖረው ውጤት ከሞላ ጎደል ከእዚኽ በታች የተመለከተውን ይሆናል፡-

| **አመላካች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **1. ባለቤትነት** | በ1995 በወጣው ሕገመንግሥት መሠረት ፤ መሬት የመንግሥት እና “የሕዝብ” ነው። ከ2020 አከባቢ ጀምሮ የባንኩን እና የቴሌኮም መስኩን ክፍት የማድረግ ሙከራ ቢኖርም ፤ መሬትን በሊዝ ካልሆነ በንብረትነት መያዝ የእማይቻል በመሆኑ እና ስትራቴጂክ በእሚባሉት መስኮች የመንግሥት ባለቤትነት ስለ እሚበዛ ፤ የግል ንብረት ባለቤትነት ውስንነት አለበት። | **1 (መካከለኛ)** | ተንቀሳቃሽ ነገሮችን እና የንግድ ድርጅቶችን በአብዛኛው በንብረትነት መያዝ ይችላል ፤ ሆኖም መሬት ላይ ገደብ መኖሩ እና ስትራቴጂክ የእሚባሉትን መስኮች ወደ ግል የማዛሩ ነገር አሁንም ዝግ ያለ በመሆኑ ከፍተኛ ገደብ ይፈጥራል። |
| **2. ውርስ** | በሕገ መንግሥቱ መሠረት መንግሥት መሬትን ለሕዝባዊ አገልግሎት ብሎ መውረስ ይችላል። ይኽም ከተማ ለማስፋፋት እና ለኢንደስትሪያል ፓርክ ግንባታ በስፋት መሬት ለመውሰድ በሥራ ላይ ውሏል። የካሳ ክፍያውም በመሬቱ ላይ ያለውን ግንባታ ወጪን ብቻ ታሳቢ ያደረገ ነው ፤ መሬቱ በግዜ ኺደት የፈጠረውን የዋጋ ጭማሪ ከግምት አያስገባም። | **0 (ዝቅተኛ)** | በተግባር ያለው አደጋ ከፍተኛ ነው። የካሳ ክፍያ በአብዛኛው ከገበያ ዋጋ በታች ነው ፤ ዜጎች በመፈናቀላቸው ቅሬታ ኖሯቸው ወደ ፍርድ ቤት ቢኼዱ ውጤታማ አይሆኑም ወይንም ፖለቲካዊ ተፅዕኖው ከፍተኛ ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **3. የውድድርገደብ** (**Contestability**) | በሐገሪቱ ለረጅም ግዜ የንብረት ባለቤትነት ከመንግሥት ወደ ጥቂት ሰዎች (State-to-Elite) ነው። ከቅርብ ግዜ ወዲኽ ፤ የንብረት ውድድሩን ቀጥታ በዜጎች መካከል የሚያደርግ ማሻሻይ ቢኖርም ፤ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች እና እንደ ኢፈረት (e.g., EFFORT) ያሉ ኮንግሎመሬትስ በርካታ በመሆናቸው ነጻ የንግድ ውድድር ከባድ ነው። | **0 (ዝቅተኛ)** | **የፈጠራው ወንፊት ምዘና (Innovative Sieve Analysis)**<br>ንብረት ለአብዛኛው ነባር ባለፃብት እንደ ምሽግ ("Wealth Vault") ነው። ተወዳድሮ ገብቶ የገበያ ድርሻ ለማግኘት አስቸጋሪ መሆኑ ፣ ደካማ የሆነ የክስረት እና የጸረ ሞኖፖሊ ሕግ መኖሩ ፤ በሐገሪቱ አዲሱ አሠራር አሮጌውን አስረጅቶ የእሚያጠፋበት (Creative Destruction) አግባብ ደካማ ስለ ሆነ ፤ ሐገሪቱ ያላትን የእምታከፋፍል እንጂ አዲስ ፃብት በአግባቡ መፍጠር የእምትችል ሐገር መሆን አቅቷታል። |
| **4. የሠራተኛ ነጻነት (Labor Freedom)** | በጠቅላላው ሠራተኞች የአሻቸውን ሥራ መምረጥ ይችላሉ ፤ በ2019 የወጣው የአሠሪ እና የሠራተኛ ሕግ መዳኛው ሕግ ጥሩ መሻሻል ነው። ሆኖም በኢኮኖሚው ውስጥ ከፍተኛ የኢመደበኛ የሥራ ገበያ በመኖሩ እና የሠራተኛ ማሕበሩ ጥንካሬ የሠራተኛውን 14% ብቻ የእሚወክል መሆኑ ፤ ከአንድ ክልል ወደ ሌላ በሥራ ለመዘዋወር ያለው የሕግ ፣ አስተዳደራዊ እና የአሠራር | **1 (መካከለኛ)** | በሐገሪቱ የግዳጅ ሥራ በሕግ ክልክል መሆኑ እና ሠራተኞች እንደ አሻቸው ሥራ መምረጥ መቻላቸው ጥሩ ጎን ሲሆን ፤ ጥሩ ቀጣሪ የሆነ የግል መስክ ባለመኖሩ ፤ ሠራተኛ በእየ ኢኮኖሚው ዘርፍ በቀላሉ መንቀሳቀስ እንደ አይችል ገደብ ሆኖታል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ችግር ፤ ሠራተኛው በመላ ሐገሪቱ በቀላሉ ተንቀሳቅሶ እንደ አይሠራ ገድቦታል። | | |

ይኽንም ተከትሎ ፤ የአመላካቾቹ አማካይ (2/4) ውጤት 0.5 ስለ እሚሆን ፤ ከእላይ ባስቀመጥነው መከፋፈያ መሠረት ፤ በኢትዮጵያ የንብረት ባለቤትነት መብት ዝቅተኛው ውጤት 2 ይኖረዋል።

የንብረት ተንቀሳቃሽነት (Asset mobility) ኹኔታ አመላካቾች (indicators) ተንሽ በርከት ብለው የእሚከተሉት ናቸው፡-

1. የውጭ ዜጎች የንግድ ድርጅት ባለቤት መሆን ይችላሉ?
2. መሬት በቀላሉ መሸጥ ይቻላል?
3. የካፒታል ኮንትሮል (Capital controls) ወይንም ኃብት ከሐገር እንደ አይወጣ ቁጥጥር ይደረግበታል?
4. የስቶክ ገበያው (Stock market) ከኢከነሚው አመታዊ ምርት አንጻር ስንት እጅ ነው (size % of GDP) ።
5. የንግድ ድርጅት ለመጀመር እና ድርጅቱን ለመሸጥ ቀላል ነው?
6. በቀላሉ የባንክ ብድር ለንግድ ሥራ ማግኘት ይቻላል?

እነ እዚኽም አመላካቾች ዝቅተኛ/መካከለኛ/ከፍተኛ በእሚል ከእዚኽ በታች ባለው ማብራሪያ መሠረት ይመዘናሉ:

| **አመላካች** | **ዝቅተኛ (0)** | **መካከለኛ (1)** | **ከፍተኛ (2)** |
|---|---|---|---|
| የውጭ ዜጎች ባለቤትነት | የውጭ ዜጎች የንግድ ድርጅት ባለቤት መሆን አይችሉም ወይንም 51% ባለቤትነት ካለው የሐገር ውስጥ ባለኃብት ጋር መጣመር አለባቸው። አብዛኛው ዘርፍ ለውጭ ሐገር ባለኃብቶች ዝግ ነው። | በተወሰኑ ዘርፎች ውስጥ የውጭ ዜጎች ባለቤት እንዲሆኑ ይፈቀዳል ሆኖም ቁልፍ በእሚባሉት ኢንደስትሪዎች ውስጥ የውጭ ባለቤትነት አይፈቀደም ወይንም ከ49% በላይ ባለቤትነት እንዲኖራቸው አይፈቀደም። | ከተወሰኑ ጥቂት መስኮች በስተቀር የውጭ ባለኃብቶች ሙሉ ባለኃብቶች እንዲሆኑ ይፈቀዳል። |
| የመሬት ገበያ | መሬት በቀላሉ መተላለፍ ወይንም መሸጥ አይቻልም። | መሬት በሊዝ ሊያዝ ወይንም ሊተላለፍ ይችላል ሆኖም ኺደቱ | ግልፅ የሆነ የንብረት ባለቤትነት ሰርተፍኬት አሰጣጥ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የመሬት ባለቤትነት ውስንነት አለበት ወይንም የሊዝ ስረዓቱ ይጎላል ፤ በመስኩ የመንግሥት ቁጥጥርም በጣም ከፍተኛ ነው። | ገደብ አለበት ፣ የመንግሥት ፈቃድ ያስፈልገዋል ወይንም የባለቤትነት ማረጋገጫው ግልጽነት ይጎለዋል (Land can be leased or transferred but with restrictions, approval requirements, or unclear titles.) | ያለበት እና መሬት በቀላሉ መገዛት ፣ መሸጥ እና ለብድር እንደ ማስያዣ መዋል የእሚችልበት ነው። |
| የኃብት ቁጥጥር (Capital Controls) | ጥብቅ የኃብት ቁጥጥር አለ። ገንዘብ ወደ ሐገሪቱ በቀላሉ መግባት እና መውጣት አይችልም። የውጭ ምንዛሪ ላይ ጥብቅ ቁጥጥር አለ። | የተወሰነ የካፒታል ቁጥጥር አለ። ዳጎስ ያለ መጠን ያለውን ገንዘብ ከሐገር ለማስወጣት እና ለማስገባት የተከለከለ ነው ወይንም መንግሥታዊ ፈቃድ ይፈልጋል። | በቀላሉ ካፒታል ከሐገር ማስወጣት እና ማስገባት ይቻላል ፤ ከተወሰኑ ጥቂት ክልከላዎች በስተቀር የካፒታል እንቅስቃሴ አይወሰንም። |
| ከኢክነሚው አመታዊ ምርት አንጻር የስቶክ ገበያው (Stock Market Size (% of GDP)) | በሐገሪቱ የእሚገኘው የስቶክ ገበያ መጠኑ በጣም ትንሽ ወይንም የሌለ ነው (በአብዛኛው የኢከነሚው አመታዊ ምርት20% ወይንም ከእዚያ በታች ነው የእሚሆነው)። የንግድ ድርጅቶች በአብዛኛው ለባንክ አገልግሎት የመንግሥት ባንክ ላይ ይደገፋሉ። | መካከለኛ ደረጃ ፤ የኢከነሚው አመታዊ ምርት20–60% (20–60% of GDP) የሆነ የስቶክ ገበያ ሲኖር። አንድ አንድ የንግድ ድርጅቶች ለማስፋፊያ የእሚያስፈልጋቸውን ገንዘብ በስቶክ ገበያ አክሲዮኖቻቸውን በመሸጥ ነው የእሚያገኙት። | ከፍተኛ በመጠን እና እንቅስቃሴ ያለበት ከኢከነሚው አመታዊ ምርት አንጻር ከ60% በመቶ በላይ የሆነ (>60% of GDP) የስቶክ ገበያ አለ። የንግድ ድርጅቶች የማስፋፊያ ገንዝበ አክሲዮኖቻቸውን በገበያ በመሸጥ የማግኘት አሠራር በስፋት ይስተዋላል። |
| በቀላሉ ንግድ መጀመር እና መሸጥ | ንግድ መጀመር እና መዝጋት ከባድ ፣ | ንግድ መጀመር በአንጻራዊነት ቀላል ነው | ንግድ መጀመር ፣ መዝጋት ፣ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ኹኔታ(Ease of Starting / Selling Business)። | የተንጓተተ እና ብዙ ቢሮክራሲ የእሚበዛበት ነው። የክስረት ሕጉ (The Bankruptcy Law) አተገባበር የተንዛዛ እና ደካማ ነው። | ምንም እንኳን ቢሮክራሲው ውስብስብ ቢሆንም። ንግድ መጀመር እና መሸጥ ኺደቱ ውስብስብ ነው ፣ ግዜ ይወስዳል። | መሸጥ በአንጻራዊነት በግልጽ በእሚታወቅ የሕግ አሠራር በትክክል በእሚሠራ የክስረት ሕግ (Functioning bankruptcy system) መሠረት በአንጻራዊነት በቀላሉ ይከናወናል። |
| ብድር ማግኘት | አብዛኛው ነጋዴ ብድር ከባንክ ማግኘት አይችልም።ብድር በዋናነት ከፖለቲካው ጋር ንክኪ (Government or politically connected firms) ላላቸው የንግድ ተቋማት ነው የእሚሰጠው። | ብድር አለ ሆኖም ወለዱ በጣም ከፍተኛ ነው ወይንም ለትላልቅ የንግድ ተቋማት ብቻ ነው እሚቀርበው። ትንንሽ እና መካከለኛ የንግድ ድርጅቶች ብድር ለማግኘት ይቸገራሉ። | ለግል እና ለንግድ ሰፊ ብድር የማግኘት እድል አለ። በውድድር የተሞላ እና በአግባቡ የእሚሠራ የብድር ገበያ አለ። |

በእዚኽ መሠረት የኢትዮጵያን የንብረት ማንቀሳቀስ ደረጃ ለመመዘን ከሞከርን ፤ አመላካቾቹ ከእዚኽ በታች ያለውን ውጤት ከሞላ ጎደል ይኖራቸዋል ፡-

| **አመላካች** | **ገለጻ ያለፈውን 40 ዓመት ታሳቢ ሲደረግ (40-Year Horizon)** | **መጠን (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የውጭ ዜጋ ባለንብረትነት** | ባለፈው አርባ ዓመት ፤ 51% ድርሻ ካለው የሐገር ውስጥ ባለኃብት ጋር ጥምረት ግዴታ በማድረግ ፤ የውጭ ዜጋ ባለኃብትነት ይገደባል። ከ2024 እስከ | **1** | ባለፈው አርባ ዓመት ለአባዛኛው ግዜ ብዙ ገደቦች ኖረውበት ነው የቆየው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 2026 የችርቻሮ/ጅምላ መስኩን ለመክፈት የማሻሻያ ሙከራ አለ። | | |
| **የመሬት ገበያ** | መሬት መሸጥ አይቻልም ሊዝ ብቻ ነው ማስተላለፍ የእሚቻለው ፤ እርሱም የተንዛዛ ቢሮክራሲ እና የመንግሥት ፈቃድ የእሚያስፈልገው ነው። | **0** | በሐገሪቱ ያለው የሊዝ ሕግ (በተለይ በገጠር) መሬትን በማስያዣነት የመጠቀሙን ነገር ያከብደዋል። |
| **የኃብት ቁጥጥር(Capital Controls)** | ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እጥረት አለ ፤ ገንዘብ ከሐገሪቱ የማስወጣት ኺደቱ ከፍተኛ ቁጥጥር ያለበት ነው። | **0** | ባለፈው አርባ ዓመት የውጭ ምንዛሪ በጣም አሰልቺ የሆነ የወረፋ አሠራር በቋሚነት የታየበት ነው። |
| **የስቶክ ገበያው መጠን (Stock Market Size)** | ለባለፈው 39 ዓመታት የስቶክ ገበያ የእሚባል አልነበረም። የኢትዮጵያ ስቶክ ገበያ ከተጀመረ ዓመት ገደማ ቢሆነው ነው (The ESX (Ethiopian Securities Exchange) only launched in 2025/26)። | **0** | በአለፈው አርባ ዓመት የስቶክ ገበያ ከኢኮነሚው አመታዊ ምርት (of GDP) አንጻር ከ20% በታች ሆኖ ነው የኖረው (of GDP)። |
| **በቀላሉ ወደ ንግድ መግባት/መውጣት** | በጣም ቢሮክራሲያዊ መንዛዛት የበዛበት ነው። ፈቃድ የማውጣት እና በሐገሪቱ የንግድ ዕቃ ማዳዳዝ ("Logistics") በጣም ይዘገያል።(Highly bureaucratic; licensing and "Logistics" are historically slow.) | **0** | ንግድ መጀመር እና መዝጋት በጣም አስቸጋሪ እና የተንዛዛ መሆኑ እንደ ቀጠለ ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **ብድር የማግኘት ኹኔታ** | የባንኩ ገበያ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ((CBE)) ከፍተኛ ተፅዕኖ ሥር ነው። ባለፈው አርባ አመት ብድር በዋነኛነት ወደ መንግሥት የልማት ድርጅቶች ነው ሲኼድ የነበረው። | **0** | ትናንሽ እና መካከለኛ የንግድ ተቋማት ብድር ለማግኘት ይቸገራሉ ፤ ብድር ከገበያ ይልቅ በፖለቲካ ትሥሥር ይሰጣል(lending is politically connected.)። |

ይኸም የስድስቱን አማክኝ (1/6) ውጤት 0.17 እንዲሆን በማድረግ ፤ ኢትዮጵያ በንብረት ማንቀሳቀስም 1 እንድታገኝ ያደርጋታል።

የፍትሕ ስረዐቱን ነጻ እና ገለልተኛነት ደረጃ ለመመዘን የእምንጠቀምባቸው አመላካቾች (indicators) ከእዚክ በታች የተዘረዘሩት ስድስቱ ናቸው: -

1. የዳኝነት ነጻነት
2. የሙስና ድባብ (Corruption perception)
3. ኮንትራት የማስፈጸም ቅልጥፍና (Contract enforcement time)
4. በሕግ ፊት እኩል የመታየት ኹኔታ
5. በፍርድ ቤቶች ላይ የፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት ደረጃ
6. የፖሊስ አስተማማኝነት

እነ እዚኽም አመላካቾች (indicators) ዝቅተኛ/መካከለኛ/ከፍተኛ በእሚል በእሚከተለው ሠንጠረዥ አግባብ ይመዘናሉ፡-

| **አመላካች** | **ዝቅተኛ (0)** | **መካከለኛ (1)** | **ከፍተኛ (2)** |
|---|---|---|---|
| የዳኝነት ነጻነት | ፍርድ ቤቶች በመንግሥት ወይንም በፖለቲከኞች ቁጥጥር ሥር ናቸው። የዳኞች ዋና ዋና የእሚባሉ ፖለቲካዊ ወይንም ኢከነሚያዊ ውሳኔዎች በተፅዕኖ ሥር ናቸው። | ፍርድቤቶች የተወሰነ ነጻነት አላቸው ሆኖም ፖለቲካዊ ይዘት ወይንም ጠንከር ያለ ፋይዳ (high-profile cases) ያላቸው ጉዳዮች ተፅዕኖ ይደረግባቸውል። | ፍርድ ቤቶች በአብዛኛው ነጻ ናቸው። ዳኞች ውሳኔያቸው የመንግሥትን ወይንም ከፍተኛ ተፅዕኖ ያላቸውን ዜጎች ጥቅም የእሚጎዳ ቢሆንም እንኳን በሕጉ መሠረት ይበይናሉ። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሙስና | ሙስና በጣም የተንሠራፋ እና በፍርድ ቤቶች ፣ በፖሊስ ፣ በፍቃድ አወሳሰድ ፣ እና የመንግሥት አገልግሎት ለማግኘት በተለመደ ኹኔታ የእሚጠበቅ ነው። | ሙስና ይኖራል ሆኖም ኹሉም ነገር በሙስና አይደለም የእሚሠራው ፤ የሕጉ ተፈጻሚነት ወጥነት ይጎድለዋል። | ዝቅተኛ ሙስና። ጉዳይ ለማስፈጸም ጉቦ ብዙ ግዜ አይሠጥም ፤ የሙስና ጉዳይ ለፍርድ ይቀርባል። |
| ኮንትራት ማስፈጸም | ኮንትራት (ውል) ለማስፈጸም ከባድ ነው። የፍርድ ቤት ክርክሮች ረጅም ግዜ ይወስዳሉ ፤ ውሳኔውም በሕጉ አግባብ ተጠባቂ አይሆንም። | ውሎች ተፈጻሜነት አላቸው ኺደቱ ግን በጣም የዘገየ እና ብዙ ዋጋ እሚያስከፍል ይሆናል። የሕግ ስረዓቱ የተንዛዛ ነው። | ውሎች በአስተማማኝ መልኩ ተቀባይነት ባለው የግዜ መስኮት ውስጥ ይፈጸማሉ። የሕግ ስረዓቱ ውሳኔ ተገማች ነው።(Legal system predictable.) |
| በሕግ ፊት እኩል መታየት | ሕጉ የእሚፈጸመው በዜጎቹ ፖለቲካዊ ግንኙነት (political connections) ፣ የኃብት መጠን ፣ ብሔር እና ዝና መሠረት ነው። | ሕጉ ለአብዛኛው ዜጋ በእኩልነት ይተገበራል ሆኖም ጥቂት በተለይ ከፖለቲካ ስረዓቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ለየት ያለ መስተንግዶ ሊያገኙ ይችላሉ። | ሕጉ ለዜጎች ፣ ለንግድ ተቋማት እና ለመንግሥት በእኩልነት ይተገበራል። ብዙ ግዜ ኹሉም በሕግ ፊት እኩል ናቸው። |
| በፍርድ ቤቶች ውስጥ የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት | መንግሥት በፍርድ ቤቶች ፣በፍርድ ኺደት እና በፍርድ አሰጣጥ ውስጥ በተደጋጋሚ ጣልቃ ይገባል። | በአንድ አንድ ወሳኝ ጉዳዮች ላይ መንግሥታዊ ጣልቃገብነት ይኖራል ሆኖም ለመደበኛው የንግድ ሥራ ነጻ እና ገለልተኛ ነው። | ፍርድ ቤቶች ከጥቂት ፖለቲካዊ ተፅዕኖ በስተቀር ነጻ እና ገለልተኛ ናቸው። |
| የፖሊስ አስተማማኝነት | ፖሊስ እማያስተማምን ፣ ሙሰኛ እና የፖለቲካው መጠቀሚያ መሣሪያ | ፖሊሥ ይሠራል ሆኖም ሙስና እና የብቃት ማነስ ብቃቱን ይፈታተኑታል። | ፖሊስ አስተማማኝ ነው ፤ ሕጉን በወጥነት ያስፈጽማል ፣ ንብረት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ነው። ንብረት እና ውልን ለማስከበር አይሠራም። | | ለመከላከል እና ውሎችን ለማስፈጸም ይሠራል። |

ይኸንንም መመሪያ አድርገን የኢትዮጵያን የፍትሕ ስረዓት ነጻ እና ገለልተኛነት ከመዘንን ፤ ውጤቱ የሚከተለውን የሚመስል ይሆናል ፦

| **አመላካች** | **ገለጻ ያለፈውን 40 ዓመት ታሳቢ ሲደረግ (40-Year Horizon)** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **ነጻነት** | በአብዛኛው የዳኝነት ስረዓቱ ከፍተኛ ተፅዕኖ ባለቸው እና ወሳኝ በሆኑ (high-profile or sensitive cases) ጉዳዮች ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት አለበት ተብሎ ይታሰባል። | **1** | ፍርድ ቤቶች ከሞላ ጎደል ዝቅተኛ እንደምታ ባላቸው የንግድ ክርክሮች ነጻ ናቸው ፤ በፖለቲካ ጉዳዮች ግን ተፅዕኖ አለባቸው። |
| **ሙስና** | ሙስና ፦ በፈቃድ አሰጣጥ ፣ በመሬት አሰጣጥ እና በመንግሥት ግዢ ወቅት ስረዓታዊ እና በተደራጀ መልኩ የሚሠራ ነው። | **0** | በቢሮክራሲው ሰንሰለት ውስጥ ፋይል የሚንቀሳቀሱት ጉቦ እና ፖለቲካዊ ኔትዎርክ ናቸው ተብሎ ይታመናል። |
| **የውል ተፈጻሚነት** | በጣም ይዘገያል ፤ በፍርድ ቤት የሚደረግ የንግድ ክርክር ከ 2 እስከ 5 ዓመት ሊፈጅ ይችላል። | **0** | የፍትሕ ኺደቱ እጅግ የተንዛዛ እና ውጤቱም ኢተገማች ነው። |
| **በሕግ ፊት እኩል መታየት** | የመንግሥት የልማት ድርጅቶች እና አንድ የግል ንግድ በሕግ ፊት እኩል ዓይታዩም። | **0** | ጥቂት ባለኃብቶች እና ፖለቲካዊ ግንኙነት ያላቸው የንግድ ተቋማት ለየት ያለ መስተንግዶ ይደረግላቸዋል (are treated differently.) |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት** | ወሳኝነት ባላቸው (sensitive) የኢኮነሚ ጉዳዮች ላይ ጣልቃ ገብነት አለ። | **0** | በፍርድ ስረዓቱ ውስጥ የመንግሥት ጣልቃገብነት የተለመደ ነው። |
| **የፖሊስ አስተማማኝነት** | የፖሊስ ትኩረቱ በስልጣን ላይ ያለውን መንግሥት ህልውና ማረጋገጥ ላይ ነው ፤ የግል ንብረት ማስከበር ላይ ሲመጣ ወጥነት ይጎድለዋል። | **1** | ፖሊስ ሥራውን ይሠራል ሆኖም ያለባቸው ክፍተት ውልን በአስተማማኝ ኹኔታ በእሚስከብርበት ደረጃ ነው አይባልም። |

የእዚኽም አማካይ (2/6) የእሚሰጠን ውጤት 0.33 በመሆኑ ፤ ኢትዮጵያ ከነጻ እና ገለልተኛ የፍርድ ስረዓት አንጻር የእሚኖራትን ውጤት 1 በማድረግ ፤ ዝቅተኛ መደብ ውስጥ ያስቀምጣታል።

በአንድ ሐገር ውስጥ የንግድ (Trade openness) ክፍትነት ለመመዘን የእምንጠቀምባቸው አመላካቾች ከእዚኽ በታች የተዘረዘሩት ናቸው ፡-

1. የቀረጥ መጠን
2. ከቀረጥ ውጭ ያሉ ገደቦች
3. የገቢ/የወጪ (Import/export) ንግድ ከኢከነሚው አመታዊ ምርት አንጻር (% of GDP)
4. በገቢ እና በወጪ ንግድ ላይ ያሉ ክልከላዎች(Import/export restrictions )
5. የጉሙሩክ ፕሮሰስ ለመጨረስ የእሚፈጀው ግዜ (Customs time )
6. የዓለም የንግድ ድርጅት (WTO) አባል መሆን እና ሕጉን ማክብር (WTO membership compliance)

እነእዚኽ ስድስት አመላካቾች (indicators) በእሚከተለው መመሪያ መሠረት ዝቅተኛ/መካከለኛ/ከፍተኛ በእሚል በመመዘን ፤ የአንድን ሐገር የንግድ ክፍትነት ለመመዘን ይውላሉ ፡-

| **አመላካች** | **ዝቅተኛ (0)** | **መካከለኛ (1)** | **ከፍተኛ (2)** |
|---|---|---|---|
| የቀረጥ መጠን | አብዛኛው ከውጭ የእሚገባ ዕቃ ከፍትኛ መጠን ያለው ከ15–20% በላይ የሆነ ቀረጥ ይጣልበታል። | መለስ ያለ ከ5–15% የእሚሆን ቀረጥ ይጣላል። መለስ ያለ ቀረጥ ነው የሐገር ውስጥ ኢንደስትሪዎችን | በጥቅላላው ከ5% በታች የሆነ ቀረጥ ነው ያለው። ኢከነሚው ለአብዛኛ ከውጭ ለእሚገቡ ዕቃዎች ክፍት ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የሐገር ውስጥ ኢንደስትሪዎችን ለመከላከል በእሚል ከውጭ የእሚገቡ ዕቃዎች ከፍተኛ ቀረጥ ይጣልባቸዋል። | ለመከላከል ከውጭ የእሚገቡ ዕቃዎች ላይ የእሚጫነው ቀረጥ። | |
| ከቀረጥ ውጭ ያሉ ገደቦች | በርካታ የኮታ ፣ የፈቃድ አሰጣጥ ፣ የዕቃ ዓይነት ወይንም አስተዳደራዊ ክልከላዎች ይኖራሉ። በእነ እዚኽም ምክንያት ታሪፍ ባይኖር እንኳን እቃ ማስገባት ከባድ ነው። | የተወሰኑ :- የጥራት ደረጃ ምዘና ፣ የፈቃድ አሰጣጥ ፣ የኮታ ክልከላዎች ይኖራሉ ሆኖም ዕቃ ማስገባት ይቻላል። | በጣም ጥቂት ከታሪፍ ውጭ ያሉ ገደቦች ናቸው ያሉት። ዕቃ የማስገባት ኺደቱ ግልጽ እና የእሚታወቅ/ተገማች ነው። |
| የገቢ ወጪ ንግዱ ከኢከነሚው አመታዊ ምርት አንጻር(% of GDP) | በአብዛኛው የገቢ ወጪ ንግዱ ከኢከነሚው አመታዊ ምርት አንጻር ከ30% በታች በመሆን በጣም ዝቅተኛ ነው። ኢከነሚውን በአንጻራዊነት ዝግ ነው ማለት ይቻላል። | የገቢ ወጪ ንግዱ ከኢከነሚው አንጻር ከ30% –60% (30–60% of GDP) ይሆናል። ኢከነሚው በተወሰነ ደረጃ ከዓለም ዓቀፍ የንግድ ስረዓት ጋር የተሣሠረ ነው። | ከኢኮኖሚው አንጻር ከ60% በላይ (>60% of GDP) የሆነ የገቢ ወጪ ንግድ ይኖራል። ከዓለም ዓቀፉ የንግድ ስረዓት ጋር በጣም የተሣሠረ ነው። |
| በገቢ/ወጪ ንግድ ላይ ያለ ገደብ (Import/Export Restrictions) | አብዛኛው ዕቃ ገደብ ያለበት ነው ወይንም መንግሥት ነው በዋናነት በማስመጣት እና በመላክ ላይ የተሠማራው። ዕቃ ለመላክ የላኪነት ፈቃድ ያስፈልጋል። | የተወሰኑ እቃዎች እንደ አይላኩ ወይም እንደ አይገቡ ሊታገዱ ወይንም ቁጥጥር ሊኖርባቸው ይችላል ፤ አብዛኛውን ዕቃ ግን መላክም ማስገባትም ይቻላል። | በጣም ጥቂት የመላክ/የማስገባት ገደቦች ናቸው ያሉት። ነጋዴዎች አብዛኛውን ዕቃ ማስገባትም መላክም ይችላሉ። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| የጉምሩክ ቆይታ ግዜ | የጉምሩክን ጉዳይ ጨረሶ ወረቀት የማግኘት ኺደት ይንጓተታል ፣ ኢተገማች ነው ፣ ከቢሮ ቢሮ ያመላልሳል ወይንም ቢሮክራቲክ ነው። መዘግየት የተለመደ ነው። | ከጉምሩክ አጣርቶ የማውጣቱን ኺደት ለማፍጠን ይሠራል ሆኖም የተንዛዛ የፋይል ብዛት እና ግዜ የመውሰዱ ነገር ይኖራል። (Customs process exists but paperwork and delays still common.) | የግሙሩክ ጉዳይ ማስፈጸም ኺደት ቀልጣፋ ፣ የእሚታወቅ/የእሚገመት ኺደት ያለው ፣ እና በአንጻሩ ፈጣን ኺደት ነው። |
| የዓለም የንግድ ድርጅት (WTO) አባልነት እና የሕጉ አክባሪነት (WTO / Trade Agreement Compliance) | ወይ የ WTO አባል አይደለም ከሆነም ሕጉን በተደጋጋሚ አያከብርም። | የዓለም ንግድ ድርጅት (WTO) አባል ሐገር ይሆናል ሆኖም ሕጉን በወጥነት አያከብርም። | የዓለም የንግድ ድርጅት (WTO ) አባል እና ሕጉንም አክባሪ ነው። |

በእዚኽ አግባብ ኢትዮጵያን እንደ ማሳያ አድርገን ፤ ከንግድ ክፍትነት (trade openness) አንጻር ኢትዮጵያ በአመላካቾቹ እንዴት ትመዘናለች ብለን ካየን ፤ የእሚከተለውን ዓይነት ውጤት እናገኛለን ፡-

| **አመላካች** | **ገለጻ ያለፈውን 40 ዓመት ታሳቢ ሲደረግ (40-Year Horizon)** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የቀረጥ መጠን** | የሐገር ውስጥ ኢንደስትሪ ለመከላከል እና የመንግሥትን ገቢ ለማሳደግ በእሚል ፤ ከፍተኛ የእሚባለው ፤ ከ20% በላይ የሆነውን | **0** | በባለፈው 40 ዓመት ለእሚበዛው ግዜ ከፍተኛ የእሚባለው የቀረጥ መጠን ሲጣል ነው የነበረው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ቀረጥ ነው በአብዛኛው የእሚጣለው። | | |
| **ከታሪፍ ውጭ ያሉ ገደቦች** | የውጭ ምንዛሪ በወረፋ መሆኑ ፤ ትልቁ ከታሪፍ ውጭ ያለ ገደብ ሆኗል ፤ የብዙዎችን ዕቃ ከውጭ የማስገባት አቅም እየገደበ። | **0** | ከበድ ያሉ አስተዳደራዊ ክልከላዎች እና ገደቦች በፈቃድ አሰጣጥ እና በውጭ ምንዛሪ አደላደል አለ። |
| **የማስመጣት እና የመላክ መጠን ከኢኮኖሚው አንጻር (Trade (% of GDP))** | ኢትዮጵያ በታሪክ ከዓለም ዓቀፉ የንግድ ስረዓት ጋር ዝቅተኛ መጠን ያለው ትሥሥር ነው ያላት ፤ የውጭ ንግድ የሐገሪት ትልቁ ዘርፍ ከሆነው ግብርና በብዙ እጥፍ ያንሳል። | **0** | የውጭ ንግድ ከሐገሪቱ ኢኮኖሚ አንጻር ከ30% በታች ነው ፤ ላለፉት 40 ዓመታት። |
| **በገቢ/ወጭ ንግድ ላይ ያለ ክልከላ (Import/Export Rest.)** | ወደ ውጪ የእሚላኩ እንደ ቡና እና ወርቅ ያሉ ዕቃዎች የመንግሥት ቁጥጥር አለባቸው ፤ ወደ ሐገር ውስጥ የእሚገቡ ዕቃዎችም ገደብ አለባቸው። | **0** | ብዙ ሸቀጦች ክልከላ አለባቸው ወይንም በመንግሥት ቁጥጥር ነው የእሚደረጉት። |
| **የግምሩክ ቆይታ ግዜ** | ከጅቡቲ አዲስ አበባ ባለው የጉዞ ኮሪደር ላይ እና በደረቅ ወደቦች ላይ ንብረት ረዘም ላለ ግዜ ሊቆይ ይችላል። | **0** | በጥቅላላው ከጉሙሩኩ የማጣራት ኺደቱን አጠናቆ የመውጣቱ ነገር ዝግተኛ እና ከቢሮ ቢሮ የእሚያመላልስ ወይንም ቢሮክራቲክ ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **የዓለም ንግድ ድርጅት ሕግ አክባሪነት (WTO Compliance)** | ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት አባል ለመሆን ካመለከተች ወደ 23 ዓመት ቢሆናትም መስፈርቱን አሟልታ አባል መሆን አልቻለችም። | **0** | የዓለም የንግድ ድርጅት አባል አይደለችም። |

በእዚኽም መሠረት በኹሉም አመላካቾች ዜሮ ስለ አገኘች አማካዩ (0/6) የሚሆነው 0.00 ስለ ሆነ ፤ ከንግድ ክፍትነት አንጻር ኢትዮጵያ 1 በማግኘት ዝቅተኛው መደብ ውስጥ ነው የእምትገባው።

የሐገራትን የበጀት አስተዳደር ጥበብ ደረጃ ለመለካት የእምንጠቀምባቸው አመላካቾች (Indicators) የእሚከተሉት ናቸው: -

1. የግብር ስረዓት ቀንበር ክብደት እና ተገማችነት
2. የመንግሥትን የበጀት ጉድለት ለመሙላት ገንዘብ ማተም(Monetary financing of deficit)
3. ብድርን ከፍጆታ ይልቅ ለምርታማነት የመጠቀም ኹኔታ (Productive use of debt)
4. የግሽበት መጠን (Inflation rate)
5. የብሔራዊ ባንኩ ገለልተኛነት
6. የመገበያያ ገንዘቡ ርጋታ
7. መንግሥት በዕዳ የመያዙ ኹኔታ
8. የበጀት አደላደል ቅደም ተከተል

እነ እዚክ ስምንት የበጀት አስተዳደር ጥበብ ዝቅተኛ/መካከለኛ/ከፍተኛ በእሚል የእሚመዘኑበት አግባብ በእሚከተለው መሠረት ነው፡-

| **አመላካች** | **ዝቅተኛ (0)** | **መካከለኛ (1)** | **ከፍተኛ (2)** |
|---|---|---|---|
| የግብር ጫና እና የግብር ስረዓቱ ተገማችነት(Tax System Burden & Predictability) | የታክስ ስረዓቱ ኢተገማች ፣ ግብታዊ ፣ ወይንም በጣም ጫና የእሚያሳድር ነው። ተደጋጋሚ ለውጥ | የግብር ጫናው መለስ ያለ ሆኖ ስረዓቱ ግን ውስብስብ እና ኢተገማች ነው። | የግብር ስረዓቱ ተገማች ነው ፣ በአንጻራዊነት ውጤታማ አሠራር አለው ፣ ገደፉን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የእሚስተዋልበት እና ወጥነት ያለው ሳይሆን ኹኔታዊ አፈጻጸም (discretionary enforcement) ያለው ነው። | | ያልፈ ጫናም አያሳድርም። |
| የበጀት ጉድለት ለመሙላት ገንዘብ ማተም(Monetary Financing of Deficit) | መንግሥት የበጀት ጉድለቱን ለመሙላት ገንዘብ ማተም ያዘወትራል። ከእዚኽም የተነሳ ከፍተኛ መጠን ያላቸው የዋጋ ግሽበቶች የተለመዱ ናቸው። | የበጀት ክፍተት ለመሙላት ገንዘብ የማተሙ ነገር ባይዘወተርም በተደጋጋሚ ይደረጋል ፤ በብሔራዊ ባንኩም ላይ ፖለቲካዊ ጫና ይኖራል። | መንግሥት በጣም ውስን በሆነ አጋጣሚ ካልሆነ በፍጹም የበጀት ጉድለት ለመሙላት ገንዘብ አያትምም። |
| ምርታማ የብድር አጠቃቀም(Productive Use of Debt) | መንግሥት ብድር በመበደር የእሚያመጣውን ገንዘብ በአብዛኛው ለፍጆታ ፣ ለድጎማ እና ለደሞዝ ክፍያ ነው የእሚያውለው ፤ ምርታማነትን የእሚያሳድግ መሠረተ ልማት ላይ ኢንቨስት ከማድረግ ይልቅ። | መንግሥት በብድር የእሚያገኘውን ገንዘብ ለፍጆታም ለመሠረተ ልማት ኢንቨስትመንትም በእኩልነት ይጠቀማል።(Debt mixed between consumption and infrastructure/investment.) | መንግሥት በብድር የእሚያገኘው ገንዘብ በአብዛኛው ምርታማነትን በእሚያሳድግ መልኩ እንደ መንገድ ፣ ኃይል ፣ ትምሕርት ፣ ወዘተ ባሉ ጉዳዮች ላይ ይውላል። |
| የዋጋ ግሽበት መጠን | ከፍተኛ መጠን እና ተለዋዋጭነት ያለው | መካከለኛ ደረጃ ያለ ከ5 እስከ 15 በመቶ የእሚደርስ የዋጋ ግሽበት ይኖራል። | ከ5% በታች የሆነ ዝቅተኛ እና ብዙ መዋዥቅ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | በአብዛኛው ከ15% በላይ የሆነ የዋጋ ግሽበት ይኖራል። | | የሌለው የዋጋ ግሽበት ይኖራል። |
| የብሔራዊ ባንክ ገለልተኝነት/ነጻነት | ብሔራዊ ባንኩ በመንግሥት እና በፖለቲካ አመራሩ ቁጥጥር ስር ይሆናል። | ብሔራዊ ባንኩ የተወሰነ ነጻነት ይኖረዋል ሆኖም የመንግሥት ቀጥተኛ ተፅዕኖ ይኖራል። | ብሔራዊ ባንኩ ከመንግሥት ፖለቲካዊ ተፅዕኖ ነጻ ሆኖ ዋነኛ ትኩረቱን ዋጋ ማረጋጋት ላይ አድርጎ ይሠራል። |
| የመገበያያ ገንዘቡ ርጋታ | ገንዘቡ ከፍተኛ የዋጋ አለመረጋጋት የሚታይበት እና በየግዜው ዲቫልዩ (Devalue) የሚደረግ ነው። | ገንዘቡ የተወሰነ አለመረጋጋት አለው ግን ከቁጥጥር ውጭ አይደለም። | ገንዘቡ በአንጻሩ የረጋ እና ለመገመትም ቀላል ነው። |
| በእዳ የመያዝ ልምድ | ሐገሩ ተደጋግሞ በእዳ ይያዛል ወይንም የብድር ሽግሽግ ይጠይቃል። | መንግሥቱ አንድ አንድ ግዜ በእዳ የመያዝ ወይንም የብድር ሽግሽግ የመጠየቅ ባሕል አለው። | ምንም በእዳ የመያዝ ታሪክ አይኖረውም ወይንም ብድሩን በግዜው የመክፈል ጥሩ ልማድ ይኖረዋል። |
| የበጀት አደላደል ትኩረት ፦ምርታማ ኢንቨስትመንት ወይንስ ፍጆታ ላይ<br><br>Budget Allocation | አብዛኛው በጀት በደሞዝ ፣ በድጎማ እና በፍጆታ ላይ ይውላል ፤ ትርፍራፊው ነው ምርታማነት በሚያሳድጉ | በጀቱ እኩል በእኩል በኢንቨስትመንት እና ፍጆታ ላይ ይውላል ። | ከፍተኛ መጠን ያለው የበጀቱ ክፍል ምርታማነትን የሚያሳድጉ እና ዘላቂነት ባላቸው መሠረተ ልማቶች ላይ ይውላል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| (Investment vs Consumption) | መልኩ እንደ ትምሕርት እና መንገድ ባሉ ፕሮጀክቶች ላይ የእሚውለው። | | |

እነ እዚኽን የበጀት አስተዳደር ጥበብ አመላክቾች መመዘኛ የኢትዮጵያን የበጀት አስተዳደር ጥበብ ደረጃ ለመመዘን ብንጠቀምበት የእሚከተለውን ዓይነት ውጤት እናገኛለን ፦

| **አመላካች** | **ገለጻ ያለፈውን 40 ዓመት ታሳቢ ሲደረግ (40-Year Horizon)** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የግብር ተገማችነት** | የግብር ስረዓቱ ግብታዊ ነው የእሚል ግንዛቤ ነው የንግዱ ማሕበረሰብ ያለው ፤ የግል ንግድ ተቋማት ገቢያቸውን ቀንሰው ነው ያስታወቁት በእሚልለተደጋጋሚ ኦዲት ይጋለጣሉ ። | **0** | ኢተገማች እና ኹኔታዊ ብያኔ (discretionary enforcement) እና አፈጻጸም እሚበዛበት ነው። |
| **ብር ማተም( Monetary Financing)** | ከፍተኛ የሆነ ብር በማተም የበጀት ጉድለትን የመሙላት ልምድ አለ (Historically high reliance on "Direct Advances" (printing money) to fund the budget.) | **0** | ብሔራዊ ባንኩ በተደጋጋሚ ብር በማተም የመንግሥትን የበጀት ጉድለት ስለ እሚሞላ ፤ ይኽ ልማድ ዋነኛ የዋጋ ግሽበት ምንጭ ሆኗል። |
| **ብድርን ለምርታማ ወጪ መጠቀም (Productive Debt)** | ትልልቅ በብድር የተሠሩ እንደ ህዳሴ ግድብ እና ባቡር የማዘመን ሥራዎች አሉ ፤ ሆኖም እነ እዚኽ መሠረት ልማቶች አትራፊ ስለ አልሆኑ ብድር የመክፈል አቅማቸው ዝቅተኛ | **1** | ቅይጥ አፈጻጸም ነው ያለው ፤ ትልልቅ መሠረተ ልማቶች ተገንብተዋል ሆኖም እነርሱን ለመገንባት የተወሰደው ብድር ባግባቡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ነው (Large debt-funded infrastructure (GERD, Rails), but much is commercially non-viable.) | | መክፈል ስለ አልተቻለ ፤ ከፍተኛ የዕዳ ጫና አለ። |
| **የዋጋ ግሽበት** | በጣም ተለዋዋጭ እና ከቅርብ አመታት ወዲኽ ከ20 እስከ 30 በመቶ ነው። | **0** | በአለፉት አርባ አመታት በጣም የእሚዋዥቅ የዋጋ ግሽበት ዋነኛ የሐገሪቱ የኢኮነሚ ራስ ምታት ሆኗል። |
| **የብሔራዊ ባንክ ገለልተኝነት** | ብሔራዊ ባንኩ የገንዘብ ምኒስትሩ የቀኝ እጅ ሆኖ ነው እሚሠራው ስለ እዚኽ በመንግሥት ቀጥታ ተፅኖ ስር ነው። | **0** | ብሔራዊ ባንኩ ከመንግሥት ተፅዕኖ ነጻ አይደለም። |
| **የገንዘብ ርጋታ** | ተደጋጋሚ የሆነ የብር አቅም ማዳከም (Devaluations) ለምሳሌ ፡- 2017 ፣ 2024/25 የእምደረግበት እና ሰፊ የጥቁር ገበያ ያለበት ነው። | **0** | ገንዘቡ በጣም የእሚዋዥቅ እና በተደጋጋሚ እንዲዳከም (Devalue) የእሚደረግ ነው። |
| **በዕዳ መያዝ** | በቅርቡ በ2023 ዓም የዩሮቦንድ ብድሩን በአግባቡ መክፈል መንግሥት አቅትቶ የብድር ማሸጋሸጊያ ይደረግልኝ ብሎ ድርድር አድርጓል። | **0** | በቅርቡ የብድር ማሸጋሸጊያ አድርጓል ፤ ተደጋጋሚ የሆነ የእዳ ጫና ታሪክም አለ። |
| **የበጀት አደላደል** | ከፍተኛ የመሠረተ ልማት ግንባታ የነበረ ቢሆንም ፤ ከቅርብ ግዜ ወዲኽ ግን እንደ ደሞዝ ክፍያ ያሉ የፍጆታ ወጪዎች ትልቁ የበጀቱ ክፍል ሆነዋል። | **1** | በመሠረተ ልማት እና በፍጆታ መካከል እኩል በእኩል ለማመጣጠን የመሞከር ዝንባሌ ነው ያለው። |

በበጀት አስተዳደሩም ጉዳይ የአመላካቾቹ አማካይ (2/8) በመሆን የእሚያስገኘው ውጤት 0.25 በመሆኑ ፤ ኢትዮጵያ በበጀት አስተዳደር ጥበብ የእሚኖራት ልኬት መጠን 1 ይሆናል።

ከአምስቱ ኹኔታዎች አንጻር ጠቅልለን ስናስቀምጠው የኢትዮጵያ ልኬት ከእዚኽ በታች ያለውን ሠንጠረዥ ይመስላል: -

| ሐገር | ኹኔታ | ልኬት |
|---|---|---|
| Ethiopia | የግል ንብረት | 2 |
| | የንብረ ተንቀሳቃሽነት | 1 |
| | የሕግ ገለልተኝነት እና ነጻነት | 1 |
| | የንግድ ክፍትነት | 1 |
| | የበጀት አስተዳደር ጥበብ | 1 |

የመመርመሪያው ማሽን ኃሳብም ፤ ሐገራት ከእላይ ለመግለጽ በተሞከረው መልኩ በአምስቱ ኹኔታዎች ከተመዘኑ በኋላ ፤ በአምስቱ ኹኔታዎች ተያያዥ ውጤት (Cumulative and Interactive result) መሠረት ፤ ከእሚከተሉት አራቱ የዓለም ባንክ (World Bank) የገቢ መጠን መደቦች በየትኛው ሊካተቱ እንደ እሚችሉ ለማመልከት ወይንም ለመተንበይ መሞከር ነው፡-

1. ዝቅተኛ የነፍስ ወከፍ ገቢ ያለው ሐገር (Low Income Country)
2. ዝቅተኛ መካከለኛ የነፍስ ወከፍ ገቢ ያለው ሐገር (Lower Middle-Income Country)
3. ከፍተኛ መካከለኛ የነፍስ ወከፍ ገቢ ያለው ሐገር (Higher Middle-Income Country)
4. ከፍተኛ የነፍስ ወከፍ ገቢ ያለው ሐገር (High Income Country)

ምንም እንኳን እነ እዚኽ አራቱ የገቢ መደቦች በዋናነት በሐገራቱ አማካይ የነፍስ ወከፍ ገቢ ላይ የተመሠረቱ ቢሆንም ፤ በተመሳሳይ የገቢ መደብ ውስጥ ያሉ ሐገራት ተመሳሳይ የሆነ የኢኮነሚ ባሕሪ ይጋራሉ፡-

### 1. ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ኢኮነሚዎች (Low-Income Economies)

በእዚኽ የገቢ ደረጃ ላይ ያሉ ኢኮነሚዎች መዋቅራዊ ተጋላጭነት ያለባቸው እና በከፍተኛ ደረጃ ከእጅ ወደ አፍ (Subsistence) በሆነ የኢኮነሚ እንቅስቃሴ የእሚታወቁ ናቸው።

- **የኢኮነሚ ውቅራቸው:** ግብርናው በኢኮነሚው ውስጥ የእሚኖረው ድርሻ 30% እና ከእዚያ በላይ ሆኖ የሐገሪቱ ከፍተኛ ቀጣሪ መስክ ይሆናል። የአምራች መስኩ በጣም ውስን እና መሠረታዊ የማምረት ተግባራት ላይ የተሠማራ ይሆናል።

- **ሠራተኛ እና የሕዝብ ስብጥር (Labor & Demographics) :** ማሕበረሰቡ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት የእሚያሳይ እና የተደጋፊዎች ቁጥር ፥ በአንድ በእሚሠራ ሰው የእሚደገፉ ልጆች እና ቤተዘመዶች ፤ ከፍተኛ የእሚሆንበት ነው። ከመደበኛው ይልቅ ኢመደበኛው መስክ ይሆናል አብዛኛውን ሰው የእሚቀጥረው።

- **መሠረተ ልማት እና ጤና :** ከፍተኛ የሆነ የኤሌክትሪክ ኃይል የማግኘት ችግር ያለበት ነው። የጤና ጥበቃው ደካማ በመሆኑ አማካይ የእድሜ ጣራ ዝቅተኛ እና ተላላፊ በሽታዎች እሚበራከቱበት ነው።

- **የውጭ ንግድ:** ወደ ውጭ ሐገር የእሚላኩ ዕቃዎች በዋናነት እሴት ያልተጨመረባቸው እንደ ማዕድን እና የግብርና ምርት የሆኑ ጥሬ ዕቃዎች ናቸው ፤ ከእዚኽም የተነሳ ኢኮኖሚያቸው በጣም ለዓለም ዓቀፉ የጥሬ ዕቃ (Commodity) ገበያ ወዋዥቅ ተጋላጭ ነው።

### 2. ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ያላቸው ኢኮኖሚዎች (Lower-Middle Income Economies)

ይኽኛው መደብ ውስጥ የእሚገኙ ሐገራት በፈጣን ፤ ከግብርና መር ወደ ኢንደስትሪ መር በእሚደረግ ሽግግር ላይ ናቸው።

- **የኢኮኖሚው ውቅር:** የግብርናው መስክ ከነበረበት የመሪነት ሚና እየቀነሰ የኢኮኖሚው ከ15–20% የእሚሆንበት እና የአምራች እና የአገልግሎት መስኩ ከግብርናው አንጻር እየሰፋ የእሚኼድበት ኹኔታ ይኖራል።

- **ከተሜነት:** ሠራተኛው ግብርናውን እየለቀቀ አዲስ ወደ እሚስፋፉት የኢንደስትሪ ማዕከላት ስለ እሚፈልስ ፤ በጣም ፈጣን የከተማ መስፋፋት ይኖራል።

- **የሰው ኃብት ልማት:** የመሠረተ ትምሕረት ደረጃ ዕውቀት እና ከፍተኛ መጠን ያለው የአንደኛ ደረጃ ትምሕርት ማጠናቀቅ ይኖራል ፤ የከፍተኛ ትምሕርት እድል እና ጥራት በጣም ዝቅተኛ ቢሆንም።

- **የተቋማት ዕድገት ደረጃ:** እያደገ የእሚኼድ የባንክ ስረዓት (Growing financial systems) እና የቴክኖሎጂ ተደራሽነትም በቀጣይነት የእሚያድግበት ድባብ ይኖራል ፤ ለምሳሌ ፡- ከፍተኛ የሞባይል ኔትዎርክ ሽፋን ይኖራል ፤ ምንም እንኳን ቴክኖሎጂውን ለመጠቀም የኢኮነሚ እና የዕውቀት አቅሙ ሕብረተሰቡን በእሚችል እና በእማይችል በኹለት ቢከፍለውም (Though the "digital divide" remains)።

### 3. ከፍተኛ መካከለኛ ገቢ ኢኮነሚዎች (Upper-Middle Income Economies)

እዚኽ ውስጥ የእሚካቱት ሐገራት ፤ በአብዛኛው "ታዳጊ ገበያዎች" በመባል የእሚታወቁ እና ጠንካራ የእሚባል የኢንደስትሪ ልማት ብስለት ላይ የደረሱ ሆነው "የመካከለኛ ገቢ ወጥመድ" የእሚባለው ወጥመድ አደጋ የተጋረደባቸው ሐገራት ናቸው።

- **የኢኮኖሚያቸው ውቅር (Economic Structure):** ኢኮኖሚያቸው በተለያዩ ዘርፎች ጥሩ የሚባል እድገት ያስመዘገበ እና ጠንካራ የአምራች መስክ ኖሮት እንደ ባንክ ፣ የጅምላ እና ችርቻሮ ፣ የቱሪዝም ፣ ወዘተ መስኩ በፍጥነት እየተስፋፉ ያሉበት ነው። ግብርናው ድርሻው ወርዶ ፤ በአብዛኛው በኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ድርሻ ከ10% በታች የወረደበት ነው።

- **ማሕበራዊ ገጽታው:** የሕዝብ ቁጥር ዕድገቱ በጣም የቀነሰ እና እያደገ የሚኼድ መካከለኛ ገቢ ያለው የሕብረተሰብ ክፍል ያለበት ነው (a growing middle class.)። አብዛኛው ዜጋ የኹለተኛ ደረጃ ትምሕርት እና መሠረታዊ የጤና አገልግሎት የሚያገኝ ነው።

- **መሠረተ ልማት:** በአግባቡ የተገነቡ እንደ መንገድ ፣ ወደብ ፣ የኃይል ማመንጫ እና ማከፋፈያ ያሉ መሠረተ ልማቶች ያሉበት እና ከ60% በላይ የሆነ ከፍተኛ የሚባል ከተሜነት ያለበት ነው።

- **ፈታኝ ኹኔታዎች:** ከኢኮኖሚ ዕድገታቸው ጋር ተያይዞ የተፈጠረው የደሞዝ እድገት በርካሽ የማምረት ሥራ ላይ ተወዳዳሪ ሆኖ መቆየትን ፈተና ያደርግባቸዋል ፤ ከእዚኽም የተነሳ ከፍተኛ ገቢ ካላቸው ሐገራት ጋር ፤ በፈጠራ እና ከፍተኛ ዋጋ ባላቸው አገልግሎቶች መወዳደር እስኪችሉ ፤ በመካከለኛ ገቢ ወጥመድ ውስጥ ለመቆየት ይገደዳሉ።

**4. ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ኢኮኖሚዎች (High-Income Economies)**

እዚኽ መደብ ውስጥ እሚካተት ኢኮኖሚ ያላቸው ሐገራት ፤ ከትላልቅ ኢንደስትሪዎች እና ማምረቻ ፋብሪካ በማለፍ ድህረ-ኢንደስትሪ (Post-industrial) የሚባለው እና የኢኮኖሚው ዋነኛ የእድገት ምንጭ ፦ ቴክኖሎጂ ፣ ዕውቀት እና አገልግሎት የሆነበት እንዲኹም ተቋሞቻቸው መርጋት የሚታይባቸው ናቸው።

- **ኢኮኖመያዊ ውቅር (Economic Structure):** የኢኮኖሚው ከፍተኛ ባለድርሻ መስክ ሶሥተኛው መስክ የሚባለው አገልግሎት እና አራተኛው መስክ የሚባለው እውቀት እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የሆነበት ነው (Dominated by the tertiary sector (services) and quaternary sector (knowledge/information).) ግብርና በእዚኽ ዓይነቱ ኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖረው ድርሻ ፤ ከኢኮኖሚው 2% በታች ነው(less than 2% of GDP)።

- **ሠራተኛ እና የሕዝብ ስብጥር:** ከፍተኛ ደረጃ ያለው በልዩ ሞያ የሠለጠነ (Specialized human capital) እስከ ዩኒቨርስቲ ደረጃ የተማረ የሰው ኃይል እና ከፍተኛ መጠን ያለው የነፍስ ወከፍ ምርታማነት ያለበት ነው። እዚኽ መደብ ውስጥ ያሉ ሐገራት ፤ የእድሜ ጣራቸው ከፍተኛ እና የውልደት ፍጥነታቸው ዝቅተኛ ስለ እሚሆን ፤ ሽማግሌ እየበዛ ልጆች እየቀነሱ ይኼዳሉ።

- **ቴክኖሎጂ እና ፈጠራ:** በጥናት እና ምርምር (Research and Development (R&D)) ላይ ከፈተኛ በጀት መደበው ይሠራሉ። በእነ እዚኽ ኢኮኖሚዎች ውስጥ የዕድገት ምንጭ ፦

አዳዲስ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች ናቸው ፤ ከተጠራቀመ ኃብት እና የሠራተኛ መጠን ከመጨምር ወይንም ርካሽ ደሞዝ ከመሆን ይልቅ።

- **መንግሥት:** ከሌሎቹ ሶስቱ መደቦች ሲነጻጸር ፡- ሕግ በበላይነት የእሚገዛበት እና ኹሉም ዜጋ በሕግ ፊት እኩል የሆነበት ፣ ሕጉም ቀጥተኛ እና ግልጽ እንዲኹም የሙስናው መጠን ዝቅተኛ ይሆናል ፤ ከሌሎቹ ከሶስቱ መደቦች አንጻር ። ዓለም ዓቀፉ የገንዘብ እና የንግድ ስረዓት ሞተርም እዚኽ መደብ ውስጥ ያሉት ሐገራት ናቸው።

ከእላይ ለማለት እንደ ሞከርነው መመርመሪያው ማሽን የሐገራቱን ኢከነሚ በአምስቱ ኹኔታዎች ለክቶ ፤ ከአራቱ በአንዱ የገቢ ቡድን ሲያስቀምጥ ፤ በተዘዋዋሪ ሐገራቱ የእሚገኙበትን የኢከነሚ ገጽታ በመግለጽ ፤ ከእላይ የተቀመጠው የእየ መደቡ የኢከነሚ ገጽታ ከእነ ምክንያቱ ለማብራራት የተሻለ ዕድል ይሰጣል።

አመላካቾቹ እና ኹኔታዎቹ የሐገራትን የኢከነሚ ቅርጽ ለመወሰን ግዜ ስለ እሚያስፈልጋቸው ፤ ባለፈው 40 ዓመት በነበራቸው አፈጻጸም ላይ ነው ምዘናው የተደረገው ፤ የግዜያዊ እና ወቅታዊ ለውጦችን ተፅዕኖ በመቀነስ ፤ በባለፈው 40 ዓመት የአምስቱ **ኹኔታዎች** አፈጻጸም የሐገራቱን የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የነበረውን አዎንታዊ ወይንም አሉታዊ ተፅዕኖ ለማየት።

የአምስቱ ኹኔታዎች በሐገራቱ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ውስጥ የነበራቸው አፈጻጸም የነበራቸው ተፅዕኖ በስተመጨረሻ በምርመራ ውጤት (Diagnostic Report) ለማካተት ይሞከራል።

ይኽ መጽሐፍ በእሚጻፍበት ወቅት ፤ የዓለም ባንክ የኢትዮጵያን መደብ ፤ እንደ ቬንዝዌላ ካሉ ሐገራት ጋር አብሮ ፤ የእማይታወቅ ቢለውም ፤ የምርመራ ማሽኑ ፤ ኢትዮጵያ ከአምስቱ ኹኔታዎች አንጻር ባለፈው 40 ዓመት ከነበራት አፈጻጸም አንጻር ልትካተት የእምትችለው ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ኢከነሚ ውስጥ እንደሆነ ያመለክታል ፤ ምክንያቱም አይደለም በአጥዳፊዎቹ እና በፈጠራ ወንፊቱ ይቅርና አንኳር በእሚባሉት ፡- የግል ንብረት ባለቤትነት ፣ የሕግ የበላይነት እና በበጀት አስተዳደር ጉዳይ ዝቅተኛውን ውጤት ነው ያገኘችው። ምንም እንኳን በግል ንብረት ጉዳይ ተንፏቃ 2 ብትገባም።

በዝቅተኛው ገቢ ላይ ያለው የኢከነሚ ባሕሪ ገለጻም ከኢትዮጵያ የኢከነሚ ባሕሪ እና ውቅር ጋር ተመሳሳይ ነው ፤ ለምሳሌ ፡- ግብርና ከ30% በላይ ነው በኢከነሚው ውስጥ ያለው ተዋጽዖ።

ሌሎች እንደ ኢትዮጵያ በአብዛኛዎቹ ኹኔታዎች ልኬት 1 ከማስመዝገብ ይልቅ ፤ ቅልቅል ውጤት ላላቸው ሐገራት ፤ የመመርመሪያው ማሽን የፖሊሲ ምክር ፤ አንድ ሐገር በእሚገኝበት የከነሚ መደብ ውስጥ ፤ የእሚኖረውን የኢከነሚ ዕድገት ዕድል በመጠቀም እራሱን ወደ እሚቀጥለው ደረጃ ለማንደርደር ፤ አንኳር የእሚባሉትን ኹኔታዎች ያ ሐገር ከእሚገኝበት መደብ በላይ ከፍ ማድረግ አለባት የእሚል ይሆናል።

ሆኖም አንኳር ኹኔታዎቹ ከእምትገኝበት መደብ በላይ ሆነው ፤ አጥዳፊ ያልናቸው የንብረት ተንቀሳቃሽነት እና የንግድ ክፍትነት ዝቅተኛ ከሆኑ ፤ ያ ሐገር ወደ እሚቅጥለው ደረጃ ለመሻገር ይቸገራል።

እንዲያውም አንድ አንድ ግዜ ፤ ከፍተኛ መጠን ያላቸው የንግድ ክፍትነት እና የንብረት ተንቀሳቃሽነት ፤ ደካማ አንኳር ያላቸውን ሐገራት ስበው ደረጃቸውን ሊያሻሽሉ ይችላሉ።

ሆኖም አንኳሩ ተፈላጊው ደረጃ ላይ መድረስ አለበት።

የውድድርገደብ (Contestability) የእሚባለው በግል ንብረት ባለቤትነት ስር ያለው አመላካች ፤ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረስ እና አለመድረስ ፤ ሐገራት የመካከለኛ ገቢ (Middle Income) ሐገራት ወጥመድ የእሚባለውን ሰብረው ከፍተኛ ገቢ ካላቸው ሐገራት መግባት ይችሉ አይችሉ እንደ ሆን እርሱም ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ገቢ ባላቸው ሐገራትም ውስጥ የነፍስ ወከፍ ገቢያቸው ወደ መደቡ ጣሪያ ይደርስ አያደርስ እንደ ሆን ሲወስን ይታያል።

በስተመጨረሻም ፤ ኢትዮጵያ ዝቅተኛ ገቢ ውስጥ መካተት ብቻ ሳይሆን ፤ ባለፉት አስርት አመታት ከፍተኛ መጠን ያለው ዕድገት ብታስመዘግብም ፤ ዝቅተኛ ገቢ ያለው ሐገር ወጥመድ ሰብራ ቢያንስ ወደ ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ያለው ኢከነሚ መደብ ውስጥ ልትገባ ያልቻለችበት ምክንያት በመመርመሪያው ማሽን ሎጂክ መሠረት በዚኽ መልኩ ተበራርቷል፦

**ምደባ: ዝቅተኛ ገቢ ኢከነሚ (Low-Income Economy)**

- **የአንኳሮቹ ትንተና (Core Analysis):** መሠረታዊ የሆኑት አንኳር ኹኔታዎቿ ከንብረት በስተቀር( ሕግ እና በጀት) ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እርሱም **1** በመሆናቸው ፤ ኢትዮጵያ በዝቅተኛ ገቢ መደብ ውስጥ እንደትገኝ ምክንያት ሆነዋል። ንብረት 2 ቢሆንም ብቻውን መሆኑ እና ኹለት የሆነውም ተንፏቆ በመሆኑ የሐገሪቱን ኢኮኖሚ መደብ ለማሻሻል ተፅዕኖው ዝቅተኛ ነው። የበጀት አስተዳደር ጥበብ ጉድለት (ዋጋ ግሽበት በእሚጨምር መልኩ የበጀት ጉድለት ለመሙላት ገንዘብ ማተም) እና ባላባታዊ ወይንም ኦሊጋሪኪክ (Oligarchic) የሆነ በመንግሥት የንብረት ባለቤትነት(የልማት ድርጅቶች) የሚገልጽ የንብረት ባለቤትነት ድባብ ስለ አለ ፤ ተከታታይ የሆኑት የሐገሪቱ የጂዲፒ (GDP) እድገቶች ሐገሪቱን ከዝቅተኛ ገቢ ሐገር ወደ ከፍተኛ ገቢ ሐገር እንደ አያሸጋጋሩ ፤ ደንቃራ ሆነዋል።
- **የአጥዳፊዎች ትንተና(Accelerator Analysis):** የንብረት ተንቀሳቃሽነት (Asset Mobility) እና የንግድ ክፍትነት (Trade Openness) ኹለቱም በጋራ ልኬታቸው 1 ነው። እነ እዚኽም ሐገሪቱ ወደ መካከለኛ ገቢ ለመግባት የእምታደርገውን ጥረት ጎድተዋል። አንድ አንድ ግዜ አንኳሮቹ በተወሰነ ደረጃ ዕድገትን የእሚፈቅዱ ሆነው ፤ ካፒታል ፣ መሬት እና ሸቀጦች በቀላሉ እጅ የእሚለውጡበት ኹኔታ ስለሌለ ፤ የሐገሪቱ ኢከነሚ ጥሬ ዕቃን ወደ ውጭ በመላክ ላይ የተመሠረተ ደካማ ኢከነሚ እንዲሆን አድርገዋል።
- **የለውጥ ብልጭታዎች (The Reform Signal (Potential)):** ከ2021 እስከ 2026 የለውጥ ሙከራዎች ታይተዋል። የቴሌኮም እና የባንክ መስኩን ለውጭ ውድድር መክፈት እና በኢትዮጵያ የስቶክ ገበያ ESX (Ethiopian Securities Exchange) ማስጀመር ከባለፈው 40

ዓመት የዕዝ ኢኮኖሚ አንጻር ትልቅ ለውጥ ነው። እነ እዚኽ ለውጦች ጸንተው ከቀጠሉ ፤ በተለይ ከመሬት ሕጋ ማሽሚያ እና የምንዛሪ ገበያውን ሊበራላይዝ ከማድረግ አኳያ ፤ በእሚቀጥለው አስር ዓመት ኢትዮጵያ ከዝቅተኛ ገቢ ወደ ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ የመሸጋገር የተሻለ ዕድል ይኖራታል።

- **የፈጠራው ወንፊት (Innovative Sieve Filter):** ኢትዮጵያ አሁን ባለችበት ኹኔታ በኋላ ቀር የኢኮነሚ ቅርዝ ላይ የበቀሉ ኃብቶችን እና ኃብታሞችን በዘብነት የእምትጠብቅ ሐገር ነች። በሐገሪቱ ውስጥ ያለው የንብረት ባለቤትነት መብት ፤ ነባር ባለኃብቶችን በመንግሥት ስልጣን ከውድድር እና መታደስ የእሚከልል( "Vertical" (State-to-Elite), acting as a "Wealth Vault" for SOEs) ነው። ኢትዮጵያ የፈጠራ ምሕዳር (Innovation Pool) ፈጥራ ታዳሽ እና ቀጣይ (Creative Destructive hence sustainable) ኢኮነሚ መገንባት ከፈለገች ፤ የንብረት ባለቤትነት መብትን ዴሞክራታይዝ አድርጋ ፤ የገበያ ድርሻ እና ኃብት በምርታማነት እንጂ በፖለቲካዊ ውሳኔ እንደ አይጠበቅ ማድረግ አለባት። በተለይ ደግሞ መሬት ላይ ያለውን የውድድርገደብ (Contestability ) ማንሳት አለባት።

# 4 ማሳያ ሙከራዎች - የተመረጡ አስራ አንድ ሐገራት ኢኮነሚ ምርመራ

## 4.1 አሜሪካ

አሜሪካ የተቋማት አደረጃጀት ዕውቀትን በመጠቀም እራሷን ከአንድ ለጥሬ ዕቃ (ጥጥ ፣ ትምባሆ ፣ ወዘተ) አቅራቢነት ከተመሠረተ የቀኝ ግዛት ሠፈራነት ወደ ውጤታማ ሕዝባዊ መንግሥት ኢኮነሚ የመቀየር ታሪክ ዓይነተኛ ማሳያ ነች።

ከ1776 በፊት በነበረችው አሜሪካ ፤ የግል ንብረት ባለቤትነት ፣ የንብረት ተንቀሳቃሽነት እና የሕግ የበላይነት ፈጽመው አልነበሩም። በእዚያን ወቅት በአሜሪካ ለነበሩት ሰፋሪዎች (Colonist) ኃብት እና ደህንነት ከፈጠራ ችሎታቸው እና ከታታሪነታቸው ጋር የተገናኘ የዜግነት መብታቸው ጉዳይ አልነበረም ፤

ይልቁንም በአሻቸው ሰዓት የፈለጉትን ንብረት መውረስ ፣ ማስተላለፍ ወይንም የፈለጉትን ዓይነት የግብር ሕግ ማውጣት የእሚችሉት ሳልሳዊው ንጉሥ ጆርጅ (King George III) እና በለንደን የእሚገኘው ፓርላማው ጋር ባለ ቅርበት እና ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ነበር።

ይኽ ከለንደን ሆኖ የአሜሪካን ሰፋሪዎች (Colonist) የኢኮኖሚ ትርፍ ምርት እንደ አሻው የእሚበዘብዝ የፖለቲካ ስልጣን አሜሪካኖችን ከኋላ ቀር የብዝበዛ (Extractive) ኢኮኖሚ ተይዘው እንዲቀሩ ነበር ያደረጋቸው።

ለእዚኽ ነው እንግዲኽ ፤ ትልቁ የአሜሪካ አብዮት ድል የተገኘው ፤ ከእንግሊዝ ቀኝ ግዛት ለመውጣት በተደረገው ጦርነት ሳይሆን ፤ ከጦርነቱ ድል በኋላ የሐገሪቱን የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት በአዲስ መልክ ያዋቀረውን ሕገመንግሥታቸውን በማጽደቅ የእሚሆነው። የአሜሪካ መሥራች አባቶች ፤ በአጸደቁት ሕገመንግሥት ፤ የንጉሡን የማይከሰስ እና የማይገረሰስ ስልጣን ፤ የየትኛውንም ፖለቲካዊ ስልጣን አምባገነንነት እና ዘፈቀደነት በእሚገታ ሕጋዊ መዋቅር ተኩት። ሶስት እኩል ስልጣን ያላቸው የመንግሥት ቅርንጫፎችን (ሕግ አውጭው ፣ ሕግ ተርጓሚው ፣ አስፈጻሚው) በመፍጠር ፤ የመንግሥት ስልጣን በአንድ ግለሰብ ወይንም ስብስብ ፍጹም ቁጥጥር ስር እንደ አይገባ አደረጉ።

በሕገመንግሥታቸው ውስጥ የግል ንብረት ባለቤትነት መብት ፤ ቅዱስ እና ክቡር የኹሉም ዜጎቹ እኩል መብት አድርገው በመደንገግ ፤ የፈጠራ ውጤት ባለቤት የሆነ ሰው ፤ የኢኮኖሚ ስኬቱ የእሚወሰነው ፤ ከፖለቲካው ጋር ባለው ግንኙነት ሳይሆን ይዞት የመጣው ፈጠራ ባለው ጥቅም ላይ እንዲሆን አደረጉ።

አሜሪካ ነበረች ፤ የአዕምሮ ንብረትን እንደ ቁሳዊ ንብረት የባለቤትነት ሰርተፍኬት በመስጠት የአዕምሮ ንብረትን አክብሮ አስከባሪ ሐገር ለመሆን ፤ በዓለም ላይ የመጀመሪያዋ ሐገር። ይኽም የአዕምሮ ንብረት ከለላ ፤ በርካታ የፈጠራ ስራዎችን በትልቁ የአሜሪካ የኢኮኖሚ ሕንጻ ውስጥ ጡብ አድርጎ በማቅረብ ፤ በአሜሪካ ውስጥ ታላቅ የፈጠራ መዝገብ ቤት ፈጠረ። ይኽም የሐገሪቱን የኢኮኖሚ ዕምቅ አቅም ፤ ከፍተኛ የፖለቲካ ስልጣን ያላቸውን ሰዎች ለማስደሰት ከመዋል ይልቅ ፤ ትልቅ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያላቸውን የተለያዩ ቴክኒካዊ ችግሮችን በመፍታት ላይ እዲያተኩር አደረገው።

አሜሪካ ራሷን ከእንግሊዝ ነጻ በማውጣቷ ፤ በኮሎኒያል ዘመን አሜሪካን ኋላቀር የጥሬ ዕቃ አቅራቢ ብቻ አድርጎ እንዲያስቀራት ታስቦ የተቀመጠውን ሕጋዊ እና ተቋማዊ ገደብ አፈራርሳ ጣለች። ለምሳሌ ፦ በቀኝ ገዢዋ እንግሊዝ ተጥሎባት የነበረውን በአሜሪካ ፋብሪካ መክፈት አይቻልም ይል የነበረው ሕግ በመሻሩ ፤ ታፍኖ የነበረው የአሜሪካ የዕውቀት አቁማዳ ፈነዳ ፤ ይኽም ፋብሪካ አበራከተ። ከእዚኽ በፊት አንዱ የአሜሪካ ግዛት (State) ከሌላው ጋር እንደ አይነግድ የነበረው ክልከላ ስለ ተነሳ ፤ ቨርጅንያ ከማሳቹሴትስ ጋር በአጠቃላይም አንዱ ስቴት ከሌላው ስቴት ጋር መነገድ በመቻሉ ፤ አሜሪካን በእዚያን ወቅት በዓለም ላይ ትልቁን ነጻ የንግድ ቀጠና አደረጋት።

ይኽንም ተከትሎ ፖውቶኬት (Pawtucket) በእሚባለውን ቦይ/ካናል የእሚወርደውን የወንዝ የውፍኃ ፍሰት በመጠቀም የጨርቃ ጨርቅ መሸመኛ ትላልቅ ማሽኖችን ማንቀሳቀስ ስለ ተቻለ እንደ ሎወል

(Lowell) ዓይነት የኢንደስትሪ ከተሞችን መገንባት ተቻለ ፤ በእዚኽም አሜሪካኖቹ የወቅቱን የእንፋሎት ሞተር እና የጨርቃጨር ማሽን ቴክኖሎጂ ከመጠቀም አልፈው አዲስ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች ውስጥ ገቡ።

በአሜሪካ ሕገመንግሥት ቀረጻ ውስጥ የአንበሳውን ድርሻ የእሚይዘው እና በኋላ ደግሞ የመጀመሪያ የአሜሪካ ገንዘብ ምንስትር በመሆን የፋይናንስ ስረዓት ግንባታቸው ላይ ትልቅ ሚና የተጫወተው አሌክሳንደር ሐሚልተን (Alexander Hamilton) ፤ በታላቅ ጥበብ የሐገሪቱን በጀት አስተዳደረ (performed a masterclass in Fiscal Discipline)።

የአሌክሳንደር ሐሚልተን የበጀት አስተዳደር ጥበብ ዝርዝር በእንግሊዘኛው እትም ውስጥ ባይኖርም ፤ የተወሰነ ልምድ ካካፈለ በእሚል እና በግሌ የአሌክሳንደር ሐሚልተን የፖለቲካ እና የኢከነሚ ጥበብ አድናቂ በመሆኔም ፤ ትንሽ ዘርዘር አድርጌ ላቅርበው።

አሌክሳንደር ሐሚልተን የመጀመሪያው የአሜርካ የገንዘብ ምኒስትር ሲሆን ፦ አሜሪካ ከእንግሊዝ እራሷን ነጻ ለማውጣት ለአካኼደችው ጦርነት የተበደረችውን ብድር መክፈል አትችልም በእሚል አበዳሪዎቿ ብድሩን በርካሽ ለሌሎች የእሚሸጡበት ፣ አሜርካ የራሷ ባንክ የሌላት ስለ እዚክ በባንክ ውስጥ በግለሰቦች የተቆጠበ ገንዘብ የሌለበት እና መንግሥት ከሕዝቡ ቀጥታ ግብር የእማይሰበስበት ስለ እዚኽ ፦ ከመሬት ሽያጭ ፣ ከቀረጥ ፣ ከኤክሳይዝ እና ከፖስታ ብቻ መንግሥት ገቢ የእሚያገኝበት ነበር።

በአጭሩ ፤ የአሜሪካው መንግሥት ብዙ ዕዳ እና እዚኽ ግባ የእማይባል ገቢ ነበር የነበረው። ስለ እዚኽ ሰዎች ለአሜሪካው መንግሥት ያበደሩት ብድር ሊከፈል እንደ እማይችል ብድር ቆጥረው ገዢ ካገኙ ከዋጋ በታች ይሸጡት ነበር።

ከእዚኽ አንጻር ሐሚልተን መጀመሪያ ያደረገው ነገር ፤ በጦርነቱ ወቅቱ ለጦርነቱ ማስኬጃ ብድር የተበደሩት ስቴቶች በተናጠል ስለ ነበር ፤ የኹሉንም ስቴቶች የተናጠል ብድር ፤ አንድ የአሜሪካ መንግሥት ብድር በማድረግ ፤ አበዳሪዎቹ ክፍያቸውን ከስቴቶቹ ሳይሆን ከፌደራል መንግሥቱ እንዲጠብቁ አደረገ።

አሜሪካ ብድሩን መክፈል አትችልም በእሚል ፤ አበዳሪዎች ከአሜሪካ መንግሥት የገዙትን በንድ ፤ በርካሽ እየሸጡ ቢሆንም ፤ ሐሚልተን መንግሥት በንዱን በውሉ መሠረት ከእነ ወለዱ ይከፍላል በማለት ፤ አበዳሪዎቹ በመንግሥት እንዲተማመኑ አደረገ።

ከእዚያም የመጀመሪያውን የአሜርካ ባንክ ፤ 20% የመንግሥት ድርሻ እና 80% የግሉ ዘርፍ ድርሻ አድርጎ አቋቋመ። የግሉ ዘርፍ 80% የእሚሆነውን ሼሩን የከፈለው ከመንግሥት በገዛው በንድ ነበር። ስለ እዚኽ የባንኩ መነሻ ካፒታል በዋናነት መንግሥት የተበደረውን ብድር እከፍላለኹ የእሚለው ተስፋ ብቻ ነበር ማለት ነው።

የመጀመሪያው የአሜርካ ባንክም ይኽን በንድ መሠረት አድርጎ ገንዘብ አትሞ ገንዘቡን ለነጋዴዎች እና ለአሜርካው መንግሥት እራሱ በማበደር ፤ ገንዘቡ ኢከነሚው ውስጥ በመግባት ኢከነሚውን እንዲያነቀሳቅስ አደረገ።

ይኽ በእንዲኽ እያለ ፤ የፌደራል መንግሥቱ ከመመሥረቱ በፊት ፤ እያንዳንዱ ስቴት እንደ አሻው ወጥነት በጎደለው መልኩ ይወስን እና ይሰበሰብ የነበረውን ቀረጥ እና ኤክሳይዝ ፤ በተማከለ መልኩ በፌደራል መንግሥቱ መጠኑ እንዲወሰን እና አሰባሰቡም በተደራጀ አኳኋን እንዲሆን አደረገ። በተለይ ደግሞ በውስኪ ላይ ወጥነት ያለው ሐገራዊ ኤክሳይስ ታክስ እንዲጣል እና እንዲሰበሰብ አደረገ። ቀረጡም ገና እቃው ሲገባ ወደብ ላይ ስለ እሚሰበሰብ አሰባሰቡ በጣም ጥሩ ነበር።

በእዚኽ መልኩ ፤ በሐገሪቱ ሰፊ የባንክ ስረዓት ብሎም የቁጠባ ገንዘብ ፤ ከዜጎች የእሚሰበሰብ የትርፍ/የገቢ ግብር በሌለበት ኹኔታ ፤ መንግሥት ከመሠረታዊ ውጮዎቹ አልፎ እዳዎቹን በአግባቡ መክፈል እንዲችል አደረገ።

እንዲኽ አድርጎ ፤ ሞቶ ሊበሰብስ የነበረን የአሜሪካን የጦርነት ብድር ወደ ህያው ኢከነሚ አንቀሳቃሽ በማድረግ ፤ የአሜሪካን የኢከነሚ ተዓምር ፤ ፋይናንሻል ሲስተም ፤ ትልቅ ጥበብ በታየበት የበጀት አስተዳደር ዕውነት አደረገ።

ይኽም ለኢንቨስተሮች ረጅም ዘመንን ታሳቢ ያደረገ ኢንቨስትመንት ማድረግ እንዲችሉ የተረጋጋ ማሕበረ ኢከነሚ ድባብ ፈጠረላቸው። በ1795ቷ ማለትም አሜርካ ከእንግሊዝ ነጻነት ካወጀች 20 ዓመት በኋላ በነበረችው አሜርካ ፤ ከነጻነቱ 6 ዓመት በፊት ማለትም በ1770 የእማይቻል የነበረው ፤ አንድ ነጋዴ የዛሬው ዶላር ከጥቂት ግዜ በኋላ ዋጋው ወርዶ ከገንዘብነት ወደ ወረቀትነት ይለወጥ ይሆን ብሎ የእማይሰጋበት ሐገር ሆነች።(By 1795, a merchant could trust the future value of the dollar—a stability that was impossible under the shifting whims of 1770.)

እዚኽ ጋር አንድ ልብ ሊባል ይገባዋል ብዬ የእማስበው ነገር ፤ ሀሚልተን የበጀት አስተዳደር የማስተርስ ዲግሪ ኖሮት እያንዳንዱን ነገር በመጽሐፉ መሠረት ስለ አደረገ ሳይሆን ፤ ከወቅቱ ኹኔታ ጋር የእሚጣጣም ነገር ግን መሠረታዊ የሆኑትን እንደ ንብረት ባለቤትነት ፣ የንብረት ተንቀሳቃሽነት ፣ ወዘተ መርኾች ባከበረ እና ፈጠራ የታየበት መፍትኼ ይዞ መምጣቱ ነው ትልቁ ጉዳይ።

ክርክሩ መንግሥት ይበደር አይበደር ፣ ግብር ይጣል አይጣል ፣ ወዘተ አይደለም ፡- ይልቁንም ከወቅቱ ኹኔታ አንጻር ፤ አምስቱ ኹኔታዎችን ከግምት ባስገባ እና ፈጠራ በታከለበት መንገድ መፍትኼ ማምጣቱ ነው።

አምስቱ ኹኔታዎች የእሚሉት ደግሞ ሌላ ነገር አይደለም ፡- መድሏዊነት እና ሕግ አልባነት የኢከነሚ ጸር ነው ፣ ሰዎች ለራሳቸው እንዲሰሩ እና እንዲያተርፉ ሊፈቅድላቸው ይገባል ፤ እያንዳንዱ ዜጋ ለራሱ ሠርቶ በእማያተርፍበት ኹኔታ ዘላቂነት ያለው የኢከነሚ ዕድገት የለም ፣ መንግሥት ከኢከነሚያዊ ግብታዊነት በመግታት እራሱም የተበደረውን ብድር በመክፈል ፣ የግብር እና መሰል ሕጎችን እንደ አሻው በአለመቀያየር ፣ እራሱን ነጋዴ አድርጎ የንግድ ውድድርን ባለመግደል ፣ ወዘተ አስተማማኝ እና የተረጋጋ የኢከነሚ ምህዳር መፍጠር አለበት ነው። እነ እዚኽ መሠረታዊ የኢከነሚ ምህዳሮች እስከ ተጠበቁ ድረስ ፤ በግብር ይሁን በቀረጥ ፣ ወይንም በሌላ መንገድ ሐገር የእሚገነባ የፖሊሲ አካኼድ ተቀባይነት ይኖረዋል።

በሐሚልተን ዘመን ከነበረው ኹኔታ አንጻር በበጀት አስተዳደር ጉዳይ የዛሬዋ አሜሪካ ትንሽ አሻሚ መልክ ያላት ሆና ተለውጣለች። ምንም እንኳን አሜሪካ ዛሬም በአምስቱም ኹኔታዎች ከፍተኛ ውጤት ያላት እና የከፈተኛ ገቢ ኢኮኖሚ ባለቤት ብትሆንም ፤ በእዚኽ ዘመን የበጀት አስተዳደር ጥበቧ ጥያቄ ውስጥ የገባ ይመስላል። አሜርካ በኢኮኖሚው ላይ አላስፈላጊ ጫና ሳትፈጥር ፤ እንደ ህንድ እና ጃፓን ካሉ ሐገራት ጠቅላላ ሐገራዊ ምርት (The GDP of Japan or India) ጋር የእሚቀራረብ 4 እና 5 ትሪልዮን ዶላር የግብር ገቢ መሰብሰብ ትችላለች ፤ ሆኖም ይኽን ገቢ አምራችነትን በእሚያሳድግ ኢንቨስትመንት እና ሐገራዊ የእዳ ጫናን በእሚቀንስ መልኩ በቅድሚያ ከማዋል ይልቅ ከፍተኛ የእሚባለውን የእዚኽን ገቢ ክፍል ለማሕበራዊ አገልግሎት በማዋል ፤ የአሮጌ መሠረት ልማት እና ከፍተኛ መጠን የአለው የእዳ ጫና ስጋት እየደቀነባት ነው።

የአለፈውን 40 ዓመት አፈጻጸም መሠረት አድርገን አሜሪካን በአመላካቾቿ አማካኝነት ስለ አምስቱ ኹኔታዎቿ በመመርመሪያው ማሽን እሳቤ መሠረት ስንመዝናት የእሚከተለውን ውጤት እናገኛለን፡-

**1. የግል ንብረት (አንኳር ኹኔታ)**

| **አመላካች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **1. ባለቤትነት** | ከሞላ ጎደል ኹሉም የእሚባሉት ንብረቶች - መሬት ፣ የአዕምሮ ንብረት እና ኢንደስትሪያል ካፒታል ፤ በሕጋዊ መንገድ በግል ንብረትነት ለመያዝ ይችላሉ። የሉዓላዊነት መገለጫ የሆኑት እንደ ገንዘብ ማተም እና ወታደራዊ አገልግሎቶች ለግሉ መስክ ዝግ ቢሆኑም ፤ ወሳኝ የእሚባሉት እንደ ባቡር እና ኃይል ማመንጨት ዓይነቶቹ የኢኮነሚ ዘርፎች ራሳቸው በግል ዘርፍ ነው በብዛት የተያዙት። ከ2025/2026 አከባቢ ጀምሮ ግን የብሔራዊ ደህንነት ስጋት በእሚል ከ36 በእሚሆኑ የአሜርካ ግዛቶች የግብርና መሬትን እና | **2 (ከፍተኛ)** | ምንም እንኳን ከቅርብ ግዜ ወዲኽ የውጭ ዜጎች የንብረት ባለቤትነትን የእሚገድብ ሕግ በብዛት እየወጣ ቢሆንም ፤ የአሜርካ የግል ንብረት ሕጋዊ መዋቅር በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በጥሩ ማሳያነት መቅረብ የእሚችል ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ወታደራው ተቋም አከባቢ መሬትን ለውጭ ዜጎች የእሚያግድ ሕግ ወጥቷል። | | |
| **2. ውርስ** | በአሜሪካ ሕገመንግሥት አምስተኛው ማሻሻያ (The Fifth Amendment) ወይንም አምስተኛው መብት ላይ እንደ ተደነገገው ፤ መንግሥት እንደ መንገድ ላሉ የሕዝብ አግልግሎትች ካልሆነ በስተቀር እና ተገቢውን ክፍያ በመክፈል ካልሆን የግል ንብረትን መውረስ አይችልም ተብሎ ተቀምጧል። በአሜሪካ ታሪክ ደግሞ ተገቢው ክፍያ ማለት ፤ የወቅቱ የገበያ ዋጋ ማለት እንጂ አንዳች ዓይነት በፖለቲካ ባለስልጣናት ፍላጎት ወይንም ልዩ ኹኔታ በእሚል ከገበያ ዋጋ በታች የእሚሰጥ ዋጋ አይደለም።<br><br>ምንም እንኳን በ2005 ኬሎ እና ኒው ለንደን (*Kelo v. New London*) በእሚለው የፍርድ ቤት ክርክር ፤ ከነቲከት (*Connecticut*) ውስጥ የእሚገኘው ፍርድ ቤት የሕዝብ አገልግሎት የእሚለውን ፤ ልማቱ የሰፊውን ሕዝብ ጥቅም ፡- የግብር ገቢን በመጨመር ፣ ስራ እድል በመፍጠር እና አከባቢን የማደስ ነገር | **2 (ከፍተኛ)** | ተገቢው ካሳ ሳይከፈል ንብረት የመወረስ አደጋ ዜሮ ነው። ሕጋዊ ማዕቀፉ ፡- ድርብርብ እና ጠንካራ የሆነ ለሕዝብ ግልጋሎት ተብሎ የእሚወረስ ንብረት ዋጋውን በገበያ ዋጋ የእሚተምን አስተማማኝ ስረዓት አለው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የእሚያመጣ እስከ ሆነ ድረስ ፤ በግል እና አትራፊ አልሚም (Private Developer) ቢሠራ ለሕዝብ አገልግሎት ተብሎ ሊወሰድ ይችላል ብሎ ቢልም ፤ ከ50ዎቹ ስቴቶች 47ቱ ይኸንን ውሳኔ የእማይቀበል እና በስቴታቸው የንብረት ባለቤትነትን መብት የእሚያከብር ሕግ አውጥተዋል። | | |
| **3. የውድድርገደብ (Contestability)** | በአሜሪካን የንብረት ባለቤትነት በአብዛኛው ዴሞክራቲክ ነው ፤ ሰው በኃብቱ ወይንም በፖለቲካ ትውውቁ ንብረቱን ከውድድር ለመከላከል የእሚችልበት አግባብ በጣም ዝቅተኛ ነው። ከፍተኛ ፍጥነት ያለው ክስረት (High-velocity bankruptcy (Chapter 11)) የእሚለው አዋጅ ንብረት ከደካማ አምራቹ ወደ ከፍተኛው አምራቹ በፍጥነት እንዲሸጋገር ያደርጋል።<br><br>ሆኖም ኦሊጋሪክ ("Oligarchic") ዝንባሌዎች በዲጅታል ኢከኖሚው ውስጥ እየታዩ ነው።<br><br>ከ2024 እስከ 2026 ባለው ግዜ ውስጥ ትልልቅ እንደ አማዞን ፣ ጉግል ያሉ | **1 (መካከለኛ)** | የአሜሪካው ኢከነሚ በጣም ብዙ ፈጠራ የእሚከናወንበት ኢከነሚ ቢሆንም ፤ እንደ ጉግል ፣ ሜታ ፣ ወዘተ ያሉትን የፕላትፎርም ሞኖፖሊ ("Platform Monopolies") የእሚባሉትን አሸንፎ አዳዲሶቹ ለመግባት የእሚቸገሩ በመሆኑ ፤ ከፍተኛ ገቢ ላላቸው የፈጠራ ስራዎች ውንፊቱ ውጥረት እያጋጠመው መሆኑን ያሳያል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የዲጅታል ቴክኖሎጂ ("Big Tech" (Google, Amazon)) ካምፓኒዎች በጸረ ሞኖፖሊ ሕጉ ተከሰው ፍርድ ቤት የቀረቡ ቢሆንም ፤ ፍርድ ቤቶቹ ግን ብዙ ፍላጎት አላሳዩም እነ እዚኽን ትልልቅ የቴክኖሎጂ ካምፓኒዎሽ ለማፍረስ እና ለማከፋፈል። | | |
| **የሠራተኛ ነጻነት (Labor Freedom)** | ሠራተኞች በነጻነት ሥራ ፈልገው መቀጠር እና መልቀቅ ይችላሉ።የጉልበት ገበያው ይኽ ነው የእሚባሉ የመቅጠር እና የማባረር ገደብ የለበትም። | **2** | ከፍተኛ የሠራተኛ እንቅስቃሴ ያለበት ነው። የመቅጠር እና የማባረሩ ኹኔታም በጣም ዝቅተኛ የሆነ ገደብ ያለበት ነው። |

**የአመላካቾቹ አማካይ: 2.00 → የንብረት ባለቤትነት ደረጃ: 4**

**2. የንብረት ተንቀሳቃሽነት (አጥዳፊ)**

| **አመላካች** | **ያለፈ 40 አመት ጠቅላላ ኹኔታ** | **ልኬት(0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የውጭ ዜጋ የንብረት ባለቤትነት** | ለባለፉት 40 ዓመታት አሜሪካ ለውጭ ባለ ኃብት በሯ ክፍት ነበር ፤ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በመቀበልም በዓለም ዓቀፍ ደረጃ 1ኛ ነች። | **2** | ባለፈው 5 ዓመት በደህንነት ስም መፈጠር ከጀመሩ ክልከላዎች በስተቀር ፤ አብዛኛው መስክ ክፍት ነው። |
| **የመሬት ገበያ** | መሬት ቀዳሚው ለብድር ማስያዣነት የእሚቀርብ ኃብት ነው ፤ በአሜርካ ከክርክር የጸዳ | **2** | ባለፈው 40 ዓመት ጥልቀት ያለው ፤ ብዙ ገንዘብ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የባለቤትነት ካርታ መኖር እና ያንንም ለብድር ማስያዣነት መጠቀም የተለመደ ነው። | | የእሚንቀሳቀስበት የመሬት ገበያ አለ። |
| **የካፒታል ቁጥጥር (Capital Controls)** | በአሜርካ የካፒታል ቁጥጥር ብሎ ነገር የለም ፤ የአሜሪካን ዶላር በዓለም ላይ ንብረት የእሚገዛበት እና የእሚሸጥበት ቀዳሚ የንብረት አጓጓዥ ነው። | **2** | የብሪተን ውድስ (Bretton Woods) የእሚባለው እና ከታላቁ ዲፕሬሽን እና ከኹለተኛው የዓለም ጦርነት ቀውስ በኋላ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የተረጋጋ የገንዘብ ስረዓት ለመፍጠር በእሚል በወርቅ እና በአሜሪካ ዶላር የተመሠረተ ዓለም ዓቀፍ የገንዘብ ስረዐት አሠራር ካበቃ ወዲኽ በካፒታል እንቅስቃሴ ላይ ምንም ዓየነት ገደብ የለም። |
| **የስቶክ ገበያ መጠን (Stock Market Size)** | በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በመሪነቱ ቀዳሚ የሆነ የአክስዮን ገበያ (equity markets) እና ለብዙ ግዜ የቆየ ከኢከነሚው (GDP) 100% በላይ የሆነ ካፒታላይዜሽን ወይንም ራሳቸውን ለአክስዮን ሽያጭ ያቀረቡ የንግድ ድርጅቶች ያሉበት ነው። | **2** | የዓለም ሐገራት እራሳቸውን የእሚለኩበት እና ለበርካታ አሜርካዊ እና አሜርካዊ ላልሆኑ ኩባንያዎች የገንዘብ ምንጭ የሆነ የአክስዮን ገበያ አለ። |
| **ንግድ ለመጀመር እና ለማቆም ያለ** | እንደ ደለዌር (Delaware model) ዓይነት ፈጣን ንግድ ማቋቋሚያ እና ከስሮ | **2** | በቋሚነት በቀላሉ ንግድ ለመጀመር ከእሚቻልባቸው ሐገራት ተርታ የእሚመደብ ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **አመቺነት (Ease of Start/Exit)** | መዝጊያ የሕግ አሠራር አለ። | | |
| **በቀላሉ ብድር ማግኘት** | በጣም ምጡቅ የባንክ ስረዓት ያለበት ነው፤ አነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች ብድር በቀላሉ ማግኘት ይችላሉ። | **2** | ላለፈው 40 ዓመት የበሰለ እና ውድድር ያለበት የብድር ገበያ አለ። |

**የአመላካቾች አማካይ: 2.00 → የንብረት ተንቀሳቃሽነት ልኬት: 4**

### 3. የሕጉ ነጻ እና ገለልተኛነት (አንኳር)

| **አመላካች** | **ባለፈው 40 ዓመታት የነበረው አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **ነጻነት** | በአሜርካን ሐገር ሕግ ተርጓሚው እራሱን የቻለ እና ከአስፈጻሚው ጋር በፈርጁ እኩል ስልጣን ያለው ከሰሥቱ አንዱ የሆነ የመንግሥት ቅርንጫፍ ነው ፤ በዙ ግዜ የአስፈጻሚውን ፍላጎት የእሚቃረን ውሳኔ ሲወን ይታያል። | **2** | ምንም እንኳን ከቅርብ ግዜ ወዲኽ ፍርድ ቤት ወደ አንድ ፅንፍ ተወስዷል የእሚል ክስ ቢበዛም ፤ ለበርካታ አስርት ዓመታት የቆየ የነጻነት ልምድ ያለው ነው። |
| **ሙስና** | በትንንሽ ጉዳዮች ላይ ፔቲ (petty) ሙስና ቢኖርም ፤ በጠቅላላው የመንግሥት አፈጻጸም ላይ ከፍተኛ ደረጃ ያለው ግልጸኝነት አለ። | **2** | በዙዎቹን ከንግድ ጋር የተያያዙም ያልተያያዙም ጉዳዮችን ያለ ጉቦ ማስፈጸም ይቻላል። |
| **ውል ማስፈጸም** | ውል እንደ ቅዱስ ነገር ነው እሚከበረው ፤ የሕጉ ሥረዓት በጣም ተገማች ነው። | **2** | የሕግ ስረዐቱ በጣም አስተማማኝ ከመሆኑ የተነሳ ፤ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ እንደ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ተመራጭ የቱሪዝም መዳረሻ ፤ የአሜሪካ የፍትሕ ስረዓትም ብዙዎች ለመዳኘት ተመራጭ የእሚያደርጉት የዳኝነት ስረዓት ነው። |
| **በሕግ ፊት እኩል መታየት** | ጠንካራ የሆነ የዜጎችን መብት የእሚከላከል መዋቅር እና ቋሚ የሆነ የነጋዴውን መብት የእሚያስጠብቅ መዋቅር አለ። | **2** | የባለፈው 40 ዓመት ልምድ በሕግ ፊት ኹሉም እኩል ነው የእሚለው በተግባር ታይቷል ፤ ምንም እንኳን በእዚኽ አምስት አመት የተወሰኑ መሸርሸሮች ቢታዩም። |
| **ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት** | መንግሥት በንግድ እና በንብረት ክርክር በጣም ዝቅተኛ ጣልቃ ገብነት ነው የእሚኖረው። | **2** | ፍርድ ቤቶች በአብዛኛው ከማንኛውም ዓይነት ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት ነጻ ሆነው ነው እሚሠሩት። |
| **የፖሊስ አስተማማኝነት** | ፖሊስ በቋሚነት የዜጎችን ንብረት እና የሕዝብ ሠላም ያስከብራል። | **2** | ፖሊስ መሠረታዊ ሕጎችን እና ማሕበራዊ ሠላምን የማስከበር ሥራ ይሠራል። |

**የአመለካቾቹ አማካይ: 2.00 → የሕጉ ነጻ እና ገለልተኛነት ልኬት: 4**

**4. የንግድ ክፍትነት (Trade Openness - Accelerator)**

| **አመላካች** | **ያለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የቀረጥ መጠን** | ለባለፈው 40 ዓመት ቀረጥ በአብዛኛው ከ3 በመቶ በታች ነው በናፍታ ፣ በዓለም የንግድ ድርጅት (NAFTA/WTO era) አባልነት ፣ ወዘተ ምክንያት። | **1** | ይኽ የባለፈ 40 ዓመት አመርቂ አፈጻጸም ግን ፤ በ2025/2026 ከፍተኛ አሉታዊ ለውጥ አሳይቷል ፤ አሜሪካን ወደ ተከላካይነት በመለወጥ። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **ከታሪፍ ውጭ ያሉ ክልከላዎች** | ከቅርብ ግዜ ወዲኽ ወታደራዊ እና ሕዝባዊ ደህንነት መከላከል በእሚል በአለፈው 10 ዓመት ፤ የደህንነት ማረጋገጫ እንደ ክልከላ ሆኖ ቀርቧል። | **1** | ግልጽ ከሆኑ ሕጎች ወደ አስተዳደራዊ ውሳኔ መሸጋገር ይታያል። |
| **የገቢ/ወጪ ንግድ ከኢከነሚው አንጻር (Trade (% of GDP))** | የአሜሪካ ሐገራዊ ገበያ እራሱ በጣም ትልቅ በመሆኑ ኢከነሚው ከዓለም ዓቀፉ ገበያ ጋር ያለው ትስስር ውስን ነው። የገቢ ወጪ ንግድ ከኢከነሚው አንጻር አነስተኛ ነው። | **1** | ከኢከነሚው አንጻር የገቢ ወጪ ንግዱ በ25% እና 30% መካከል ነው። |
| **በገቢ/ወጭ ንግድ ላይ ገደብ** | በአብዛኛው ምንም ዓይነት ክልከላ የለውም ፤ ከቅርብ ግዜ ወዲኽ ግን በስሪታቸው ሲቭል ሆነው ግን ወታደራዊ ግልጋሎት ሊሰጡ የእሚችሉ ቴክኖሎጂዎች ላይ ቁጥጥር ተጠናክሯል። | **1** | በንግድ ፍሰቱ ላይ ስትራቴጂክ የሆነ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት ተጠናክሯል። |
| **የግሙሩክ ቆይታ ግዜ** | በቋሚነት ፈጣን እና ኮምፒውተራይዝድ የሆነ ነው። | **2** | የግሙሩክ ስረዓቱ ብቁ እና በፍጥነት አጣርቶ መልቀቅ መለያው ነው። |
| **የዓለም የንግድ ድርጅት ሕግ አክባሪነት(WTO Compliance)** | አሜሪካ የዓለም ንግድ ድርጅት ፈጣሪ መኃንዲስ ነች ሆኖም ከቅርብ ግዜ ወዲኽ ፤ ባለፊት 10 ዓመታት ሕጉን ማክበር እየተቀዛቀዘ ነው። | **1** | በማዕቀፍ ሆኖ በማዕቀፍ ውስጥ ካሉት ሐገራት ኹሉ ጋር በመርኽ መሠረት ከመተባበር ይልቅ ፤ ከእያንዳንዱ ሐገር ጋር የኹለትዮሽ የንግድ ስምምነት ለመፈራረም መፈለግ ተበራክቷል። |

**የአመለካቾች አማካይ: 1.16 → የንግድ ክፍትነት ልኬት: 3**

**5. የበጀት አስተዳደር ጥበብ (Fiscal Discipline - Stabilizer)**

| አመላካች | የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም | ልኬት (0–2) | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| **የግብር ስረዓቱ ተገማችነት** | በአንጻራዊነት የተረጋጋ የግብር ስረዓት አለ ፤ በእየ ወቅቱ ትልልቅ ማሻሻያዎች የእሚደረግበት። | **2** | በጥቅላላው የረጅም ዘመን የንግድ ዕቅድ አውጥቶ ለመነገድ የእሚያስችል ድባብ የእሚፈጥር ነው። |
| **የበጀት ጉድለት ለመሙላት ገንዘብ ማተም (Monetary Financing)** | የአሜርካው ብሔራዊ ባንክ ወይንም ፌደራል ሪዘርፍ (The Federal Reserve) ለገንዘብ ምኒስትሩ ገንዘብ አትሞ እንደ አይሰጥ በሕግ የተከለከለ ነው (is prohibited from direct monetary financing of the treasury.) | **2** | ባለፈው 40 ዓመት ገንዘብ ማተምን የእሚከለክል ፤ጠንካራ የሆነ ፤ ተቋማዊ አሠራር ነበር ። |
| **ብድርን ምርታማነትን ለማሳደግ መጠቀም (Productive Debt)** | የባለፈው 40 ቅይጥ አፈጻጸም ነው ያለው ፤ በቅርቡ ከመሰረት ልማት/ትምሕርት ወደ ድጎማ ትኩረት የመቀየር ነገር ይስተዋላል። | **1** | የባለፈውን 40 ዓመት መልካም ልምድ በእሚያጠፋ መንገድ ፤ ከቅርብ ግዜ ወዲኽ መንግሥት በቀጣይነት ብድር ወስዶ እንደ ማሕበራዊ ድጎማ ያሉ የፍጆታ ፕሮጀክቶች ላይ በማዋል ላይ ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **የግሽበት መጠን** | ባለፈው አርባ ዓመት በጠቅላላው ዝቅተኛ እና የተረጋጋ ነው ፤ ከ2.5% እስከ 3% በመሆን። | **2** | የዋጋ ግሽበት ለባለፈው አርባ ዓመት ዝቅተኛ ሆኖ እንዲቆይ ማድረግ ተችሏል። |
| **የብሔራዊ ባንክ ነጻነት** | የአሜሪካው ፌደራል ሪዘርቭ ፤ የዋጋ መረጋጋትን እና ሥራ አጥነትን መቀነስ ግቦቹ አድርጎ እንዲሠራ ተደርጎ ከመንግሥት ፖለቲካዊ ተፅዕኖ ነጻ ሆኖ ነው እሚሠራው። | **2** | የአሜሪካው ፌደራል ሪዘርቭ የብሔራዊ ባንክ ነጻነት ተምሳሌት ሆኖ ነው ያለው። |
| **የመገበያያ ገንዘብ እርጋታ (Currency Stability)** | የአሜሪካው ዶላር የዓለም ኃብት ማስቀመጫ ነው (The US Dollar is the world's primary reserve currency.) | **2** | የአሜሪካው ዶላር ፤ ለረጅም ዓመታት ለማቀድ የእሚያስችል መረጋጋት እና ተገማችነት አለው ። |
| **መንግሥቱ በእዳ የመያዙ ታሪክ** | ኹሉንም ዓይነት እዳዎቹን ሳይዛነፍ የመክፈል ልምድ ነው ያለው። | **2** | የአሜርካ መንግሥት ከ40 ዓመት በላይ ጠንካራ እዳን የመክፈል ታሪክ ነው ያለው። |
| **የበጀት አደላደል** | የበጀት አደላደሉ ማሕበራዊ ዋስትናን ወደ ማረጋገጡ ያዘነብላል ፤ ከኢከነሚው አመታዊ ምርት ( GDP) አንጻር ለመሠረተ ልማት የእሚያወጣው ጥቂት ሊባል የእሚችል ነው። | **1** | የባለፈውን 40 ዓመታት መልካም የበጀት አፈጻጸም ታሪክ በእሚሸረሽር መልኩ ፤ የአሜሪካ መንግሥት ፍጆታን የበጀቱ ከፍተኛ ድርሻ እየሰጠው ነው። |

**የአመለካቾች አማካይ: 1.75 → የበጀት አስተዳደር ጥበብ ልኬት: 4**

**ከአምስቱ ኹኔታዎች ምዘና አንጻር የአሜሪካን የውጤት ካርድ ስናወጣ ይኽን እናገኛለን ፡**

| **ሐገር** | **ኹኔታዎች** | **ልኬት** |
|---|---|---|

| | | |
|---|---|---|
| **አሜሪካ** | **የግል ንብረት (አንኳር)** | **4** |
| | **ንብረት ማንቀሳቀስ (አጥዳፊ)** | **4** |
| | **ነጻ እና ገለልተኛ ሕግ (አንኳር)** | **4** |
| | **የንግድ ክፍትነት (አጥዳፊ)** | **3** |
| | **የበጀት አስተዳደር ጥበብ (አንኳር)** | **4** |

**የምርመራ ውጤት: አሜሪካ**

**ፍረጃ: ከፍተኛ ገቢ ያለው ኢኮነሚ**

- **የአንኳር ኹኔታዎቹ ትንተና:** በአርባ ዓመቱ ልምድ ስናየው ፤ አሜሪካ የከፍተኛ ገቢ ያላቸው ኢከነሚዎች ቁንጮ ሆና ነው የእምናገኛት። ሶስቱም አንኳር ኹኔታዎች ፡- የግል ንብረት ፣ የሕግ የበላይነት ፣ እና የበጀት አስተዳደር ጥበብ ፤ ከፍተኛውን 4 በማግኘታቸው ፤ አሜሪካ በእምትገኝበት የኢከነሚ መደብ ውስጥ የማደግ እድሎቿን በሙሉ አሟጣ የተጠቀመች ሐገር መሆኗን እያሳየን።

- **የአጥዳፊ ኹኔታዎቹ ትንተና:** የምርመራው ውጤት ከንግድ ክፍትነት አንጻር በአሜሪካ ትንሽ መቀዛቀዝ እንደ አለ ያሳያል ፤ ውጤቱ ከነበረበት 4 ወደ 3 በመቀነሱ። በንግድ ክፍትነት 3 ማግኘት እራሱ ትልቅ ውጤት ሆኖ ፤ የአካኼዱ ለውጥ መኖሩ ግን ፤ አሜሪካ ከዓለም አገናኝነት ወደ ከባቢያዊ ወይንም ስትራቴጂካዊ ተከላካይነት እየዞረች እንደ ሆነ ያሳያል(suggests the US is moving from "Global Integrator" to "Regional/Strategic Hedger.")

- **የወደፊት ትንበያ:** ምንም እንኳን ጠቅላላው የአሜሪካ የውጤት ካርድ ጥንካሬን ቢያሳይም ፤ የባለፈው አምስት ዓመት ልምድ ግን ስለ መጪው ግዜ ጥሩ ነገር አያመለክትም። በቅርቡ ከ2021 እስከ 2026 በተደረጉ ለውጦች ፤ ከባለቤትነት አንጻር የውጭ ዜጎች ላይ እና ቴክኖሎጂዎች ላይ የተደረገው ክልከላ እንደ እዚኽም የቅርቡ ከፍተኛ መጠን ያለው ታሪፍ/ቀረጥ ፤ የባለፈውን 40 መልካም ልምድ የእሚቀይር ነው። ይኽ ዓይነት አካኼድ አሜሪካን እራሷን ፈጠራን አጥልላ በማውጣት አዲስ የኃብት ድንበር ፈጣሪ ሐገር ከመሆን ይልቅ ፤ ነባሩን ኃብት ተከላካይ ወደ መሆን እየተሸጋገረች መሆኑን ያሳያል። ይኽ አሁን እየታየ የመጣው ፤ ነዋሪውን ኃብት ከውድድር የመከላከል (Trend of "Oligarchic" contestability) አባዜ እና የንግድ ተከላካይነት (Trade protectionism) ከቀጠለ ፤ አሜርካ በረጅም ዘመን የገንባችውን ተቋማዊ ኃብት በመሸርሸር ፤ ቆሞ የቀረ ከፍተኛ ገቢ ያለው ሐገር የመሆን አደጋ ይገጥማታል።

- **የፈጠራ አጥላይ ወንፊቱ (Innovative Sieve Filter):** አሁን በአለበት ኹኔታ የውድድርገደቡ Contestability) የልኬት መጠኑ 4 ነው, ሆኖም ባለፈው አምስት ዓመት ያለው

ለውጥ ፤ መንግሥታዊ የሆኑ የጥቂት ባለኃብቶችን ነባር ኃብት የመከላከል ( "Vertical" (State-to-Elite) protectionism) ልምድ እያደገ መሆኑን ያሳያል። ይኽ በእዚኽ ከቀጠለ ፤ አሜሪካ ፤ የፈጠራ መፍለቂያ (Innovation Pool) ሐገር ከመሆን ይልቅ ፤ ያረጁ እና ዘመን ያለፈባቸው የኢከነሚ ኃብት ማመንጫ መንገዶችን የእምትከላከል (a Vanguard of Anachronistic Ivory Towers.) ቆሞ ቀር ሐገር የመሆን አደጋ ይጋረጥባታል።

## 4.2 ብራዝል

ዘመናዊ የእሚባለውን የብራዚልን ታሪክ ካየነው ፤ ከአጀማመሩ አንጻር ፤ ለቀኝ ገዢው የጥሬ ዕቃ ምንጭ እንዲሆን ታስቦ የተቋቋመ ሠፈራ (Colonial outpost) በመሆኑ ፤ ከአሜሪካ ጋር ይመሳሰላል።

ሆኖም ግን ፤ ከቀኝ ገዢያቸው ነጻ ከወጡ በኋላ ኹለቱ ሐገራት የተለያየ አቅጣጫ በመከተል ተለያይተዋል።

አሜርካ ሕገመንግሥቷን በመጠቀም እራሷን ግለሰባዊ ወይንም የጥቂት ቡድኖች አምባገነንነት ከናኘበት ሐገርነት ወደ ሕግ የበላይነት የእሚከበረበት እና ዜጎች በምርታማነታቸው የእሚወዳደሩበት ሐገር አድርጋ እራሷን ስትቀይር ፤ ብራዚል የሩቁን የሊዝበን አምባገነን በቅርብ በብራዚሊያ አምባገነን በመተካት እና በተሰነካከሉ የለውጥ ፕሮግራሞች እራሷን በመካከለኛ ገቢ ሐገር ወጥመድ ውስጥ የተያዘች ሐገር አድርጋለች።

ጅማሮው ላይ የብራዚሉ ፤ የቀኝ ግዛት ሠፈራ ግልጽ ያለ የብዝበዛ መሣሪያ ነበር። ሕጉ የእሚደነገግበት ዋነኛ ምክንያት 20% የወርቅ እና የዳይመንግድ ግብር ለመሰብሰብ ሲሆን በብራዚል ውስጥ የኢከነሚ ስኬት የእሚወሰነው ፤ ከፖርቹጋሉ ቤተመንግሥት ጋር ባለ ቅርበት እንጂ በታታሪነት እና በአምራችነት አልነበረም።

የብራዚል ኃብት በሙሉ ወደ ፖርቹጋል ብቻ እንዲገባ ስለ እሚፈለግ ፤ ኤክስክሉሲቮ ኮሜርሻል (*Exclusivo Comercial)* በእሚባለው ሕግ መሠረት ብራዚል ከፖርቹጋል በስተቀር ከሌላ ከማንም ሐገር ጋር እንድትነግድ አይፈቀድላትም ነበር ። በጣም ሰፊ መጠን ያላቸው መሬቶች ፤ በንጉሡ ድርጎ ንጉሡ ለፈለገው ሰዎች ይሰጥ ነበር ፤ በተመሳሳይም የሰጠውን መሬት በፈለገው ሰዓት መውሰድ ይችል ነበር ፤ ከእዚኽም ጋር አብሮ በብራዚል ፋብሪካ ማቋቋም ክልክል ነበር። ይኽም የብራዚልን መሬት የልማት እና የፈጠራ ማዕከል ሳይሆን ፤ ኋላ ቀር የሆነ ነገር ግን የፖርቹጋል ንጉሥ ዋነኛ ኃብት ሆኖ እንዲቆይ አደረገው።

በ1822 ብራዚል ነጻነት ስታውጅ ፤ ነጻነቷ እንደ አሜሪካው ሕዝባዊ መንግሥት ወደ መመሥረት አልመራትም ፤ ይልቁንም በአባቱ ላይ ያመጸው የፖርቹጋሉ ንጉሥ ልጅ ፤ ቀዳማዊ ዶም ፔድሮ የእሚገዛት ሌላ ንጉሣዊት ኢምፓየር ሆና ነው የቀጠለችው።

ይኼ ዓይነቱ ከቀኝ ግዛት ነጻነት ማግኘት ፤ ምንም እንኳን ብራዚል ከሊዝበን ጋር ያላትን ግንኙነት ቢያቋርጥም ፤ ያንኑ የድሮውን መርኽ አልባ የመንግሥት ስልጣን የእሚናኝበትን ልማድ ነው ያስቀጠለው። ነጻነቱን ተከትሎ የመጣው የ1824 ሕገመንግሥት የንብረት ባለቤትነት መብትን እና ኃሳብን የመግለጸ መብትን እንደ እሚያከበር ተስፋ ቢሰጥም ፤ ወደ ተግባር ሲመጣ ፤ ሕገመንግሥታዊ ተስፋው ወጥነት ባለው መልኩ ስለ እማይተገበር ፤ ኢከነሚው መብት የእሚከበርላቸው እና የእማይከበርላቸው ሰዎች የእሚኖሩበት ጉራማይሌ ነበር። ከእዚኽም የተነሳ የብራዚል ኢምፓየር የፖለቲካዊ ጡት አባት ስረዓት ሆኖ ነው የቀጠለው ፤ በመጀመሪያ ንጉሡ  በኋላ ላይ "የቡና እና የወተት" ባለኃብቶች ፤ ኢኮኖሚውን በመንግሥት ባንኮች እና በግላቸው በልዩ ኹኔታ በእሚሰጣቸው ብድር አማካኝነት ይቆጣጠሩት ስለ ነበር።

ቡና አብቃይ በሆኑት አከባቢዎች ፤ የንብረት ባለቤትነት መብት ይከበር እና መሬቱም ምርታማ ነበር ፤ ሆኖም የቡና ምርት በባሪያ ጉልበት ላይ የተመሠረተ ነበር።

በ1888 ባርነትን በመሻር በሰሜን እና ደቡብ ካሉ ሐገራት በሙሉ ባርነትን ለመሻር የመጨረሻዋ ሐገር በመሆን ፤ ብራዚል እራሷን የኢከነሚ እና የህሊና ግራ መጋባት ውስጥ ያስገባች ሐገር ነበረች ፦ በአንድ በኩል የንብረት ባለቤትነትን መብት እምታከበር በሌላ በኩል ደግሞ ሰውን እንደ ንብረት የመያዝ መብትን የእምታከብር ሐገር በመሆን።

በእዚኹ ዘመን ነው ፤ የጦርነትን ወጪ እና ሌሎች የመንግሥት ወጪዎችን ለመሸፈን ፤ በግብር በእሚሰበሰብ ገንዘብ ላይ ከመደገፍ ይልቅ ገንዘብ በማተም ላይ በመደገፏ ምክንያት  ከእዚያን ግዜ አንስቶ እስከ ዛሬ ለተከታታይ 200 ዓመታት የእምትታገለው የዋጋ ግሽበት አባዜ የያዛት።

ከእዚያም በ1889 ንጉሣዊ ስረዓቱ ሲወድቅ ፤ አሁንም ብራዚል እንደ አሜሪካ የግለሰቦች እና የቡድኖች የበላይነት ሳይሆን የሕግ የበላይነት የሰፈነበት ስረዓት ወደ መሆን ከመለወጥ ይልቅ ፤ በአንድ አምባገነን ንጉሥ ከእምትዘወርበት ፤ በተለያዩ የኢከነሚ ጥቅም ቡድኖች (Oligarchic) የእምትዘወር ሐገርነት ነው የተቀየረችው።

የብራዚል ለውጦች ችግራቸው ፤ እንደ አሜርካ ፤ ሕገመንግሥታዊ በሆነ መልኩ ፤ ግብታዊ የፖለቲካ ስልጣንን የእሚገቱበት ወደ መሆን አለመለወጡ ነው። ከ1889 እስከ 1930 በአለው ግዜ ውስጥ የግል ንብረት መብት የጥቂት ባለኃብቶች መብት ብቻ እንደ ሆነ ቀረ ፤ መንግሥትም እንደስትረን አስፋፋለሁ በእሚል እራሱን የብድር ጫና ውስጥ ማስገባት እና ከኢከነሚው የማምረት አቅም በላይ በሆነ መልኩ ገንዘብ የማተም ልማድ ውስጥ አስገባው። ይኽም ሐገሪቱ የሕግን ነጻ እና ገለልተኛነት እንዲኹም የበጀት አስተዳደር ጥበብ (Fiscal discipline) እንድ ታሻሽል ስለ አላደረጋት ፤ ሐገሪቱን ተቋማዊ ብልሽት አሣስሮ አስቀመጣት።

ከ1930 በኋላ ደግሞ ፤ ብራዚል በልማታዊ መንግሥት ("State Development") አቋራጭ እራሷን ልታዘመን ፈለገች። ሆኖም የእዚኽ የልማታዊ መንግሥት ዋነኛ እሳቤ ፤ ኢምፖርት ሰብስቲቲውሽን (Import

Substitution) ስለ ነበር ፤ ውጤቱ የብራዚል መዘመን ሳይሆን ፤ ከዓለም ዓቀፍ ውድድር ታሪፍ የተከለሉ ፤ ሞትእንቢ ("zombie companies") የብራዚል ካምፓኒዎች ነበሩ።

ይኽ ዓይነቱ የሐገር ኢንደስትሪዎችን ተከላካይነት (Protectionism) ከፍተኛ መጠን ካለው የመሠረተ ልማት ለማስፋፋት ከእሚወሰድ ብድር ጋር ተዳምሮ ፤ ብራዚል በመካከለኛ ገቢ ወጥመድ ውስጥ (Middle Income Trap) ተይዛ ያለች ሐገር አድርጓታል።

የዛሬዋ ብራዚል ነገን ተስፋ እምታደርግ እንጂ ተስፋዋን እምትኖር ሐገር መሆን አልቻለችም ፤ ምክንያቱም ፡- ዘመናዊ እና የተራቀቀው የግል ዘርፏ ፤ መንግሥት ስትራቴጂክ በእሚል በገበያ እንዲወዳደሩ ከማድረግ ይልቅ በድጎማ ጉልኮስ ሊያቆያቸው ከእሚፈልጋቸው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ጋር ተፋጦ።

የምርመራው ማሽን ከአምስቱ ኹኔታዎች አንጻር በባለፈው 40 ዓመት (1986–2026) በነበራት አፈጻጸም ብራዚልን ሲመዝን ፤ ብራዚል “የባከነው አስር አመት” በእሚባለው ዘመን ካናወጣት አውሎግሽበት (hyperinflationary) ዘመን ወጥታ የፕላኖ ሪል (*Plano Real*) ማሻሻያ ሐገሪቱን ያረጋጋበት እና አሁን ደግሞ በመጨረሻዎቹ 5 ዓመታት የበጀት እና የሕግ የበላይነት እየተሸረሸረ ከመምጣቱ የተነሳ አስጊ ኹኔታ ያጠላበትን ኹኔታ ያሳያል።

### 1. የንብረት ባለቤትነት (አንኳር)

| አመላካች | ያለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም | ልኬት (0–2) | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| **1. ባለቤትነት** | ብራዚል መቶ በመቶ ሊባል በእሚችል ደረጃ የከተማ ንብረቶችን ፣ ኢንደስትሪዎችን እና የንግድ ድርጅቶችን በግል ባለቤትነት እንዲያዙ ትፈቅዳለች።<br><br>ሆኖም ፤ አሁንም አንድ አንድ መዋቅራዊ ክልከላዎች አሉ ፤ በ5709/1971ሕግ መሠረት የውጭ ባለኃብቶች የገጠር መሬት በባለቤትነት እንዲይዙ አይፈቀድላቸውም ፤ የባሕር ዳሮች (Terrenos de marinha) የፌደራል መንግሥት ንብረት ሆነው ፤ በታውን የመጠቀም | **1 (መካከለኛ)** | አምራች በእሚባለው የከተማው ክፍል የንብረት ባለቤትነት በአብዛኛው የተረጋገጠ ነው ፤ የገጠሩ መሬት ግን በግድግዳ የተከፋፈለ በእሚመስል መልኩ ወጥነት የእሚጎድለው እና ክልከላ የበዛበት በመሆኑ ፤ ንብረት በአግባቡ በኢኮኖሚው ውስጥ እንደ አይንሸራሸር ከልክሏል ( has prevented full asset fluidity)። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | መብት ብቻ ነው እንደ ሊዝ በግል ንብረት መያዝ የእሚቻለው። ስትራቴጂክ ናቸው የእሚባሉ የኒውክለር ኃይል ማመንጫ እና የፖስታ አገልግሎት አሁንም የመንግሥት ሞኖፖሊ ናቸው። | | |
| **2. ውርስ** | ሕገመንግሥቱ ፤ ንብረት ከመወረሱ በፊት እና ተመጣጣኝ የሆነ የካሳ ክፍያ እንዲደረግ ያዛል። ሆኖም በእዚያው ሕገመንግሥት ውስጥ የንብረት ማሕበራዊ ግልጋሎት ("Social Function of Property") በእሚለው አንቀጽ መሠረት አንድ መሬት ፤ የገጠር ሆነ የከተማ ፤ መንግሥት ባስቀመጠለት የምርታማነት[7] ልክ በሥራ ላይ ካልዋለ ፣ ለአከባቢ ጥበቃ ተብሎ ካልተተወ ፣ ለሥራ በእሚውልበት ግዜ የሠራተኛ ጥቅም እሚጎዳ ከሆነ መንግሥት ካሳ ከፍሎ ሊወርሰው ይችላል ፤ ሲወርሰው ደግሞ የመንግሥት ቦንድ እንጂ በጥሬ ገንዘብ በመክፈል አይደለም። ፕሪካቶርየስ (Precatórios system) በተባለው እና መንግሥት በፍርድ ቤት የተወሰነበትን ገንዘብ ለመክፈል የእሚገደድበት መንገድ "ተገቢ የገበያ ዋጋው" ስንት ነው | **0 (ዝቅተኛ)** | ምንም እንኳን ሕጉ ንብረት ያለ ተገቢ ካሳ ክፍያ እንደ አይወረስ ብሎ ቢልም ፤ የንብረት ማሕበራዊ ግልጋሎት ("Social Function of Property") በእሚለው አንቀጽ እና ፕሪካቶርየስ (Precatórios system) ምክንያት ብዙ ውጣ ውረድ እና መጓተት ስለ አለ ፤ የመወረስ አደጋ ከፍተኛ ነው። |

[7] ይኸ የንብረት ማሕበራዊ ግልጋሎት የእሚለው አንቀፅ ንብረት ወደ አምራች ግልጋሎት እንዲገባ ማድረጊያ መንገድ ይመስላል ፤ የብራዚል ሰዎች ያ ዕውነተኛ ፍላጎታቸው ቢሆን ኖሮ ፤ መሬቱ ባለው የምርታማነት አቅም መሠረት የግብር መጠን ተምነው ግብር እንዲከፍል ቢያደርጉት ኖሮ ፤ ማንም ከፍ ያለ ግብር እየከፈለ ንብረት ስለ እማያባክን ፤ ንብረቱን በተለይ መሬቱን ለምርታማ አገልግሎት እንዲውል ማድረግ ይችሉ ነበር ፤ ሆኖም የዓለማችንን ግሎባል ሳውዝ (Global South) ያደኸየው አባዜ ስለ አለባቸው ፤ መሬቱ/ንብረቱ ማሕበራዊ ግልጋሎቱን ሰጥቷል ወይ ብሎ የእሚወስነው ግብሩ ሳይሆን የመንግሥት ሹመኛው እንዲሆን ስለ አደረጉት ፤ የሐገራቸውን ንብረት ባለቤትነት ደረጃ ደካማ እንዲሆን ነው ያደረጉት።

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የእሚለው ፤ አንድ አንድ ግዜ ለአስር ዓመት የእሚቆይ አሠልቺ እና ብዙ ግዜ የካሳያ ክፍያን በጣም የእሚያዘገይ ነው። | | |
| **3. ሕጋዊሽሚያ** | በብራዚል የንብረት ባለቤትነት መብት ከግዜ ወደ ግዜ ለኹሉም ዜጎች በእኩልነት የእሚከበር እየሆነ ነው። በብራዚል በጣም ፕሮፌሽናል የሆነ ፤ (CADE) የእሚባል ተወዳዳሪነትን የእሚያረጋግጥ ባለስልጣን መሥሪያ ቤት እና ዘመናዊ የሆነ የክስረት ሕግ በቅርቡ ወጥቷል (Bankruptcy law 2021/2024) የብራዚን አሮጌውን አፍርሶ አዲሱን የመገንባት ("Creative Destruction.") ኺደቱን በማጠናከር ኢከነሚውን ታዳሽ ለማድረግ። ሆኖም የ"ድሮው ኢከነሚ" በእሚባሉት እንደ ኮንስትራክሽን ፣ ባንኪንግ እና አግሮቢዝነስ ባሉት መስኮች ኦሊጋሪኪክ (Oligarchic) መሆኑ እና ፖለቲካዊ ግንኙነት ያላቸው የመስኩ ባለኃብቶች አዲስ ተወዳዳሪን የእሚከለክሉበት አካኼድ እንደ አለ ነው። | **1 (መካከለኛ)** | ሐገሪቱ እራሷን ፈጠራ የእሚበረታታበት ለማድረግ ብዙ ማሻሻያ እያደረገች ነው ፤ ሆኖም የፈጠራ ወንፊቱ (Productivity Sieve) በነባር የፖለቲካ-ኢከነሚ የጥቅም ትሥሥሩ ምክንያት ፤ አዲስ ለእሚመጡ እና የጥቅም ትሥሥሩ አባል ላልሆኑ ሰዎች በር እሚዘጋብት ኹኔታ ከፍተኛ ነው። |
| **የሠራተኛ ነጻነት (Labor Freedom)** | ሠራተኞች ስራ ማማረጥ ይችላሉ ፣ ሆኖም ጥብቅ (Rigid) የሠራተኛ ሕግ ፣ ለመቅጠር እና ለማባረር ያለው ፈተና ፣ እንደ እዚኹም የኢመደበኛ መስኩ ግዝፈት የሠራተኛን ተንቀሳቃሽነት(Mobility) ገድቧል። | 1 | የሠራተኛ መብት/ነጻነት አለ ፤ ሆኖም ያሉ መዋቅራዊ ችግሮች የሠራተኛ ምደባን ( Labor reallocation) ይገድባል |

**የአመለካቾቹ አማካይ: 0.75 → በብራዚል የንብረት ባለቤትነት ልኬት: 2**

**2. የንብረት ተንቀሳቃሽነት (አጥዳፊ)**

| **አመላካች** | **የባለፈው አርባ ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የውጭ ዜጎች የንብረት ባለቤትነት** | በጥቅላላው ለውጭ ዜጎች የብራዚል ኢኮነሚ ክፍት ነው ፤ ምንም እንኳን በገጠር መሬት እና መንግሥት "ስትራቴጂክ" በእሚላቸው የመሠረተ ልማት ዘርፎች ገደቦች ቢኖሩም። | **1** | ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት (FDI) ቢኖርም ፤ የእዚኽን የኢንቨስትመንት ፍሰት አቅም ቢሮክራሲው የእሚደቅነው መሰናክል ብዛት እና በአንድ አንድ መስኮች ላይ ያለው የውጭ ተሳትፎ ገደብ ፤ ውጤታማነቱን ይቀንሱታል። |
| **የመሬት ገበያ** | ውስብስብ የሆኑ የመሬት ባለቤትነት ማረጋገጫ አሰጣጥ ኺደቶች በተለይ በገጠራማው አማዞን (Amazon/Rural areas) አከባቢ መሬት በቀላሉ የእሚንሸራሸር ንብረት እንደ አይሆን አድርገውታል። | **1** | ጥሩ የመሬት ምዝገባ ስረዓት ስለ ሌለ ፤ የመሬት ገበያው ትራንዛክሽን ኮስቱ (high transaction costs) ከፍተኛ ነው። |
| **የካፒታል ቁጥጥር (Capital Controls)** | የብራዚል የካፒታል ቁጥጥር በጣም ተለዋዋጭ ነው። በተለይ ደግሞ ነጋዴዎች የወለድ መጠን ርካሽ ከሆነባቸው እንደ ጃፓን ካሉ ገበያዎች ገንዘብ ተበድረው አምጥተው የወለድ መጠኑ በጣም ውድ በሆነበት | **1** | ቁጥጥር ከግዜ ወደ ግዜ እየላላ ነው ሆኖም ፤ አሁንም ቢሆን ማክሮ ኢኮነሚውን ለማረጋጋት በእሚል ተደጋጋሚ ቁጥጥር አለ። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የብራዚል ገበያ የእሚያበድሩብትን ("Carry trade") እና ይኽም የብራዚልን ገንዘብ በማጠናከር ኤክስፖርት እንደ አይጎዳ እና የገንዘቡን መረጋጋት እንደ አይረብሽ በእዚኽ የገንዘብ ንግድ ላይ በተደጋጋሚ ቀረጥ ስለ እሚጣል የካፒታል ቁጥጥር አለ። | | |
| **የስቶክ ገበያው መጠን (Stock Market Size)** | B3 የእሚባለው የብራዚል የስቶክ ገበያ ወሰብሰብ ያለ ዘመናዊ ገበያ ነው ምንም እንኳን በተወሰኑ መስኮች ላይ ብቻ ያተኮረ ቢሆንም ፤ ስፋቱም የኢኮነሚው (Market cap/GDP) ከ40 እስከ 60 በመቶ ይደርሳል። | **1** | ለሐገሪቱ ትልልቅ 50 ኩባንያዎች ጥሩ የገንዘብ ምንጭ (Deep liquidity) ነው ፤ ከእዚያ ውጭ ላሉት ግን ውስን ነው። |
| **በቀላሉ ንግድ መጀመር እና መዝጋት ይቻላል** | በጣም መዘግየት አለበት። በብራዚል የግብር እዳ ማጣራት በእሚል አንድ ንግድ ለመዝጋት አመታት ሊወስድ ይችላል። | **0** | በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ንግድ ለመጀመር እና ለመዝጋት ዝቅተኛ አመቺነት ካላቸው ሐገራት ነው ብራዚል እምትመደበው። |
| **በቀላሉ ብድር ማግኘት ይችላል** | አብዛኛው ብድር ለመንግሥት ስለ እሚሰጥ ሌላው ሰው ብድር የማግኘት እድሉ ጠባብ ነው (Crowded out by high public debt.) በሐገሪቱ ያለው ከፍተኛ የወለድ መጠን አነስተኛ እና መካከለኛ የሆኑ የንግድ ድርጅቶች ብድር ማግኘት እንደ አይችሉ አድርጓል። | **0** | የብራዚሉ ልማት ባንክ (BNDES) ፤ በብድር ድልድል ውስጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። |

**የአመላካቾች አማካይ: 0.66 → የብራዚል የንብረት ተንቀሳቃሽነት ልኬት: 2**

**3. ነጻ እና ገለልተኛ ሕግ (አንኳር)**

| አመላካች | የባለፈው 40 አመት አፈጻጸም | ልኬት (0–2) | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| **የዳኝነት ነጻነት** | ምንም እንኳን ለውትወታ (Activism) የተጋለጠ ቢሆንም ከፍተኛ የዳኝነት ነጻነት አለ ፤ ለምሳሌ ፦ በአንድ የመኪና ማጠቢያ ድርጅት ላይ የተጀመረ ምርመራ ብዙ ፖለቲከኞችን እና ነጋዴዎችን ያጋለጠበት *Lava Jato* (Car Wash) በተባለው የክስ ኺደት ለእዚኽ ማሳያ ምሳሌ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል። | **2** | የባለፈው 40 ዓመት ልምድ ፤ የዳኝነት ስረዓት አስፈጻሚውን ሲያጠፋ መጠየቅ እንደ እሚችል እና እንደ እሚጠይቅም አሳይቷል። |
| **ሙስና** | በመንግሥት ግዢ እና በመንግሥት ፋይናንስ እሚደረጉ ፕሮጀክቶች ላይ እንደ ታየው ፤ ስረዓታዊ የሆነ ሙስና አለ። | **0** | ሙስና የብራዚል የመንግሥት ተቋማት ለኹሉም ዜጋ በእኩልነት እንደ አያገለግሉ ትልቅ ወደ ኋላ ሳቢ ልጓም ሆኗል። |
| **የውል ተፈጻሚነት (Contract Enforcement)** | የአፈጻጸም ኺደቱ በጣም የዘገየ ነው ፤ የፍታብሔር ጉዳዮች አስር ዓመታት እና ከእዚያ በላይ ሊፈጁ ይችላሉ። | **0** | ብራዚል ከፍርድ ቤት አሠራር ፍጥነት እና ቅልጥፍና አንጻር በዓለም ላይ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ካላቸው ሐገራት ተርታ የእምትመደብ ነች። |
| **በሕግ ፊት እኩል መታየት** | ፖለቲካዊ ከለላ ባላቸው ጥቂት ሰዎች እና በመደበኛ ዜጋ መካከል ፤ በሕጉ ፊት ከፍተኛ ልዩነት አለ። | **0** | ያሻቸውን ቢያደርጉ የሕግ ተጠያቂነት የሌለባቸው ተብለው በሕበረተሰቡ ዘንድ የእሚታዩ ከፖለቲካው ጋር ግንኙነት ያላቸው በርካታ ሰዎች አሉ። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት** | ከአምስት አመት ወዲኽ ዳኞች በሞያ ክህሎት ሳይሆን በፖለቲካ ተፅዕኖ ሲሾሙ እና ከእዚኽ በፊት የተወሰኑ ውሳኔዎች ሲሻሩ ይታያል። | **1** | ባለፈው 40 ዓመት ከፖለቲካ ተፅዕኖ ነጻ ሆኖ የቆየ ነው ፤ ሆኖም ከባለፈው አምስት ዓመት ወዲኽ ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት ጨምሯል። |
| **የፖሊስ አስተማማኝነት** | ከክልል ክልል ይለያያል ፤ የንግድ ማዕከል በሆኑ በታዎች አስተማማኝ የፖሊስ አገልግሎት አለ ፤ ወጣ ሲባል ግን አስተማማኝነቱ ይቀንሳል። | **1** | በአንድ አንድ በታዎች ሞያዊ ስነምግባሩን የጠበቀ የፖሊስ አገልግሎት አለ ፤ በሌሎቹ በብቃት ማነስ እና ያልተመጣጠነ ኃይል(Violence) በመጠቀም የተሞላ ነው። |

**የአመላካቾቹ አማካይ: 0.66 → በብራዚል የሕግ የበላይነት ልኬት : 2**

**4. የንግድ ክፍትነት (አጥዳፊ)**

| **አመላካች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የታሪፍ መጠን** | በብራዚል ፤ ሞስት ፌቨርድ ኔሽን( MFN) የእሚባለው እና የዓለም ንግድ ድርጅት (WTO) አባል ለሆኑ ሐገራት በሙሉ እኩል ታሪፍ እንዲያስጥል በእሚያስገድደው ሕግ መሠረት ብራዚል በአማካይ የእምትጠለው የታሪፍ/የቀረጥ መጠን ከ12 እስከ 14 ስለ ሆነ ከፍተኛ የእሚባል ነው እንደ ገና መርኮሰር (Mercosur) | **0** | ከአቻዎቿ አንጻር ብራዚል ዝግ የእሚባል ዓይነት ኢኮነሚ ነው ያላት። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | በእሚባለው እና ብራዚል፣ አርጀንቲና ፣ ኡራጋይ እና ፓራጓይ አባል በሆኑበት ነጻ የንግድ ቀጠና ሕግ መሠረት በሌሎች ላይ የእሚጥሉት ቀረጥም ከፍተኛ ነው። | | |
| **ከታሪፍ ውጭ የሆኑ ክልከላዎች** | እንደ ደረጃ መዳቢዎች ዓይነት ሥራ የእሚሠራው የብራዚሉ ኢንሜትሮ ("Inmetro") በጣም ሰፊ የምዘና ቁጥጥር የእሚያደርግ እና ጸረ ሸቀጥ ማራገፍ (Anti-Dumping) አሠራራቸው እራሱን የቻለ ክልከላ ነው። | **0** | ውስብስብ የሆነ የቁጥጥር ስረዓት ፤ ከግልጽ ክልከላ በላይ በገቢ ንግድ ላይ የተቀመጠ ክልከላ ነው። |
| **ከኢኮነሚው አንጻር የገቢ/ወጪ ንግድ (Trade % of GDP)** | ብራዚል በአብዛኛው የውጭ ንግድ መጠኗ የኢኮነሚው ከ~25-35% የእሚደርስ እና ዝቅተኛ ነው ፤ ከእዚኽም የተነሳ ትልቅ ከእሚባሉት ኢኮኖሚዎች ውስጥ በጣም ዝግ የሆነው ነው የብራዚል ኢኮኖሚ። | **0** | ሰፊ ሐገራዊ ገበያ መኖሩ እና የብራዚልም መንግሥት ተከላካይ (Protectionist) መሆኑ የብራዚልን የውጭ ንግድ መጠን ወስነውታል። |
| **በገቢ ወጭ ንግድ ላይ ያሉ ክልከላዎች** | ውስብስብ የሆነ ቢሮክራሲ እና የሐገር ውስጥ ምርት ማካተት የእሚል አስገዳጅ ሕግ የተለመደ ነው። | **0** | የገንዘብ እና የግዜ ጫና የእሚያበዛ (Burdensome) እቃ የመላክ እና የማስገባት ኹኔታ ነው ያለው። |
| **የግምሩክ ቆይታ** | በብራዚል ጉሙርክ ዕቃ በእሚመመረመርበት ወቅት ፤ ማጭበርበር የተለመደ ስለሆነ ፤ ቀዩ በይ (Red Channel) ውስጥ የእሚካተተው እና ዶክመንት | **1** | ኮምፒውተራይዝ ለማድረግ እና ለማሻሻል እየተሞከረ ቢሆንም እስካሁን ማነቆ እንደ ሆነ ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ብቻ ሳይሆን ዕቃው ራሱ የእሚመረመርበት ኮንቴነር በጣም ብዙ ነው ፤ በአጠቃላይ ኺደቱ የተንዛዛ ነው። | | |
| **የዓለም የንግድ ድርጅት አክባሪነት (WTO Compliance)** | ብራዚል ንቁ የዓለም ዓቀፍ ንግድ ድርጅት ተሳታፊ ነች ሆኖም የሐገር ውስጥ ኢንደስትሪ መከላከል በእሚል በእምታደርገው ድጎማ ሕግ አክባሪነቷ ይቀንሳል። | **1** | በጥቅላላው የሕጉ አክባሪ ነች ሆኖም የንግድ ሚዛን መዛባትን ለማስተካከል ብላ የእምትወስዳቸው እርምጃዎች መጠኑን ያልፏሉ።." |

**የአመላካቾቹ አማካይ: 0.33 → የብራዚል የንግድ ክፍትነት ልኬት: 1**

## 5. የበጀት አስተዳደር ጥበብ (Fiscal Discipline - Stabilizer)

| **አመላካቾች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የግብር ስረዓት ተገማችነት** | ትልቅ ውስብስብነት ያለው ነው ፤ ነጋዴዎች በሙቶ የእሚቆጠሩ የንግድ ሕጎች ነው የእሚገጥሟቸው ፤ በፌደራል፣ በክልል እና በአከባቢ መንግሥታት። | **0** | በ2026 የVAT ሕጉ ማሻሻያ ጥሩ ምልክት ሰጥቷል ሆኖም ብራዚል ባለፈው 40 ዓመት በታክስ ሕግ ቀውስ ነው እምትታወቀው። |
| **የበጀት ጉድለት ለመሙላት ገንዝበ ማተም (Monetary Financing)** | ከ1994 በፊት መንግሥት ገንዘብ ማተምን በከፍተኛ ደረጃ የበጀትን ጉድለት ለመሙላት ይጠቀም ነበር ፤ ፕላኖ ሪል (Plano Real) ወይንም ሪል የእሚባል አዲስ መገበያያ ካስተዋወቁበት1994 በኋላ | **2** | በብራዚሉ የገንዘብ ምኒስተር እና በብራዚል ብሔራዊ ባንክ መካከል የመለያያ ግድብ ሆኖ ሕግ 2021 ወጥቷል ፤ ሰለ እዚኽ ገንዘብን ለመንግሥት በጀት ማሟያ የማተሙ ነገር ተቋማዊ ገደብ አለበት። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ግን ከእዚኽ ልማድ ተቆጥበዋል። | | |
| **ብድርን በምርታመንት መጠቀም (Productive Debt)** | ብድር ከኢከነሚው አንጻር ከ85-90% በላይ (debt/GDP >85-90%) ከፍተኛ የእሚባል ነው ፤ ያም ብድር ግን በአብዛኛው ለማሕበራዊ ድጎማ እና የብድር ወለድ ለመክፈል ነው እሚውለው። | **0** | መንግሥት ለመሠረት ልማት እና ለጥናት እና ምርምር (Infrastructure/R&D) የእሚያወለው ገንዘብ አሁን በ40 ዓመቱ ዝቅተኛ የእሚባለው ደረጃ ላይ ደርሷል። |
| **የግሽበት መጠን** | ብራዚል ወራዊ የግሽበቱ መጠን ከ50% በላይ ከሆነበት እና አውሎግሽበት( Hyperinflation) ከነበረበት ከ1980ዎቹ የግሽበት ዘመን ታሪክ በመውጣት አሁን የተረጋጋ ከ 2.5-6% የሆነ ግሽበት ውስጥ ገብታለች. | **1** | በ1980ዎቹ የነበረው አውሎግሽበት የ40 ዓመቱን አፈጻጸም ዝቅ አድርጎታል ፤ በባለፈው 5 ዓመት ደግሞ በፕላኖ ሪል የመጣው ውጤት እየተሸረሸረ ነው። |
| **የብሔራዊ ባንክ ነጻነት** | በ2021 ብሔራዊ ባንኩ በሕግ ነጻ ተደርጓል ፤ ከእዚያ በፊት በሕግ ነጻ በአይደረግም በተግባር ግን ነጻ ነበር። | **2** | የብራዚል ብሔራዊ ባንክ አስተማማኝ እና ነጻ የሆነ አንዱ የሐገሪቱ የኢከነሚ መልህቅ ነው። |
| **የመገበያያ ገንዘብ ርጋታ (Currency Stability)** | የብራዚሉ ሪያል ፤ በኮሞዲቲ ("Commodity currency") ላይ የተመሠረተ በጣም የእሚዋዠቅ መገበያያ ነው። | **1** | በዓለም ላይ ነጋዴዎች ወደ ወርቅ ፣ ዶላር እና የአሜርካ መንግሥት ቦንድ በእሚሸሹባቸው የስጋት ("Risk-off") ወቅቶች የብራዚሉ ገንዘብ በጣም ይዳከማል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **መንግሥት በእዳ የመያዝ ልምዱ** | ከ1980 ወዲኽ በውጭ አበዳሪ በእዳ ተይዘው አያውቁም ፤ የሐገር ውስጥ እዳ በቋሚነት ይከፍላሉ። | **2** | ባለፈው 40 ዓመት የመንግሥትን ዕዳ በቋሚነት ሲከፍሉ ነው የነበሩት። |
| **የበጀት አደላደል** | በብራዚል የግዴታ ውጪ የሚባሉ እንደ ጡረታ እና የደሞዝ ክፍያ ያሉት ወጪዎች የፌደራል በጀቱን ከ90 በመቶ በላይ ሆነዋል። | **0** | የግዴታ ወጭዎች በሕገመንግሥት ደረጃ ተደንግገው መቀመጣቸው ፤ የበጀት አደላደሉን ከወቅታዊ ኹኔታ ጋር ለማጣጣም አዳጋች አድርገውታል። |

**የአመላካች ኹኔታዎች አማካይ: 1.00 → በብራዚል የበጀት አስተዳደር ጥበብ ልኬት: 3**

**ከአምስቱ ኹኔታዎች ምዘና አንጻር የብራዚል የውጤት ካርድ ስናወጣ ይኽን እናገኛለን ፡**

| **ሐገር** | **ኹኔታዎች** | **ልኬት** |
|---|---|---|
| **ብራዚል** | **የግል ንብረት (አንኳር)** | **3** |
| | **የንብረት ተንቀሳቃሽነት (አጥዳፊ)** | **2** |
| | **ነጻ እና ገለልተኛ ሕግ (አንኳር)** | **2** |
| | **የንግድ ክፍትነት (አጥዳፊ)** | **1** |
| | **የበጀት አስተዳደር ጥበብ (አጥዳፊ)** | **3** |

**የምርመራ ውጤት: ብራዚል**

**ፍረጃ: ከፍተኛ መካከለኛ ገቢ ያለው ኢከነሚ**

- **የአንኳር ኹኔታዎች ትንተና (Core Analysis):** ብራዚል ዓይነተኛ የመካከለኛ ገቢ ሐገር ምሳሌ ነች። የግል ንብረት መብት እና የበጀት አስተዳደር ጥበብ ልኬት 3 በመሆናቸው ጠንካራ ሊባሉ የእሚችሉ ናቸው ሆኖም ጥንካሬያቸው ግን ብራዚልን ከመካከለኛ ገቢ ሐገርነት አውጥተው ከፍተኛ ገቢ ያላት ሐገር ማድረስ በእሚችሉበት ጥንካሬ ላይ አይደሉም ያሉት። ከበጀት አስተዳደር አንጻር ብራዚል ልኬቷ 3 ሆኖ ከፍተኛ መሆን የቻለበት ዋነኛ ምክንያት ዎርልድ ክላስ

(World-class) የሆነ ብሔራዊ ባንክ ስላላት ነው እንጂ ፤ በበጀት አስተዳደር ውስጥ ያለው እና የበጀቱን ከ90 በሞቶ በላይ ለፍጆታ ማዋል የእሚያስገድደው አሠራር የፈጠረው ቀውስ ሐገሪቱን በገደብ አልባ የዋጋ ግሽበት አሽቀንጥሮ ዝቅተኛ ገቢ ያለው ሐገር መደብ ውስጥ ነበር የእሚያስገባት።

- **የአጥዳፊ ትንተና (Accelerator Analysis):** የንግድ ክፍትነቷ (1) እና የንብረት ተንቀሳቃሽነት (2) በመሆናቸው የብራዚል ኢኮነሚ ፍሬን ሆነዋል። ከእዚኽም የተነሳ ብራዚ ፤ በውድድር እየታደሰች ፤ ያፈጃ እና ያረጃ የኢኮነሚ መስኮችን በአዲስ እየተካቸ መኼድ ተስኗት ፤ የድሮው ኢኮነሚ ዘብ ሆናለች ፤ የሐገር ውስጥ ኢንደስትሪዎችን ከውጭ ውድድር በታሪፍ ከለላ እጠባበቃለኹ በእሚል። በሐገሪቱ የእሚገኘው አብዛኛው ካፒታል ገበያ ውስጥ ገብቶ አዳዲስ የፈጠራ (Innovative ) ንግዶችን ፋይናንስ ከማድረግ ይልቅ በከፍተኛ ወለድ ለመንግሥት እየተሰጠ ቀለብ የእሚሰፍር ብድር ሆኗል።

- **የመሻሻል ተስፋ:** በ2026 የወጣው የቫት ማሻሻያ ሕግ በአግባቡ በተግባር ላይ ከዋለ ጥሩ ጅማሮ ነው። ሕጉ እንደ ተጻፈው ከተተገበረ የብራዚልን የታክስ ተገማችነት አሁን ከእሚገኝበት 0 አንስቶ 2 በማድረስ ፤ ከስቶ ብራዚል("Custo Brasil") እና ብራዚል ውስጥ ለመነገድ ያለውን አስቸጋሪነት የእሚገለጽበትን ኹኔታ መቀነስ ፤ ምን አልባትም የብራዚልን የንብረት ተንቀሳቃሽነት ሊጨምር ይችላል።

- **የማስጠንቀቂያ ትንበያዎች:** የምርመራው ማሽን ውጤት ብራዚል የሕግ የበላይነት ላይ ትኩረት ሰጥታ ካልሰራች ፤ በቅርቡ መታየት የጀመሩት ፤ የቀድሞ ብያኔዎችን የመሻር እና የፍርድ ውሳኔዎች በሕግ መሠረት ከእሚሆኑ ይልቅ በፖለቲካ ውትወታ (Activism) የእሚሆኑበት አግባብ ከቀጠለ ፤ የብራዚሉ የፈጠራ ወንፊት (Innovative Sieve) ሥራውን በአግባቡ መሥራት እየተሳነው ሐገሪቱ የኦሊጋሪኮች ወይንም የጥቂት ባለኃብት ጥበቃ (Oligarchic Protectionism) ውስጥ ያለች ሐገር ልትሆን ትችላለች።

## 4.3 ቺሊ

ቺሊ አብዮታዊ ሊባል የእሚችል እና በፖለቲካውም በኢኮነሚውም ከፍተኛ ንዝረት የእሚፈጥር ለውጥ በማካኼድ ፤ በዋናነት የጥሬ ዕቃ አቅራቢ ከነበረች የቀኝ ግዛት ሠፈራነት በላቲን አሜሪካ የእሚገኝ በማሕበረ ኢኮነሚ ተቋማቱ ጥራት ተወዳዳሪ ኢኮነሚ ለመሆን የቻለች ዓይነተኛ ሐገር ነች።

**የቀኝ ዘመኑ የትልቅ እርሻ ትውስታ**

ቺሊ እንደ ጎረቤት ሐገሮቿ በጥሬ ዕቃ አቅራቢነት ላይ የተወሰነች ኋላ ቀር ኢኮነሚ ነበረች። ሆኖም ቺሊ ብዙ ወርቅ ከእሚገኝባት ብራዚል ወይንም የትንባሆ ከፍተኛ አምራች ከሆነችው አሜሪካ አንጻር ደከም ያለች ነበረች ።

በቺሊ ከተማከለ ስልጣን ይልቅ ፤ ሕግ አውጭም ፣ አስፈጻሚም ፣ ፖሊስም እራሳቸው በሆኑ ኃስየንዳ (Hacienda) በእሚባሉ በትላልቅ እርሻ ባለቤቶች ዘንድ ነበር ኃብቱ ተከማችቶ የእሚገኘው።

የሀሲየንዳ (Hacienda) ባለቤት የሆኑት ኃብታም ገበሬዎች እራሳቸው ሕጉ ፣ ባንኩም ፣ መንግሥቱም የሆኑበት ነው የነበረው። ይኽም ልማድ በኋላ ቺሊ እንደ ሐገር ተዋቅራ ወደ ሕዝባዊነት ልታደርግ የነበረውን ሽግግር ብዙ ተፈታትኖታል።

### የ 20ኛው ክፍለ ዘመን: "ራስን የመቻል" እሳቤ ወጥመድ (1930–1970)

ቺሊ ከ1880 እስከ 1910 በነበረው ግዜ ውስጥ ለማዳበሪያ እና ለቦንብ መሥሪያነት በጣም አስፈላጊ የነበረው (nitrate) የእሚባለው ንጥረ ነገር ፤ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ብቸኛ አቅራቢ (Monopoly) ነበረች ፤ አንድ ግዜ ግን ይኽን ጥሬ ዕቃ በሰው ሰራሽ መንገድ ማምረት ሲቻል እና ቺሊ ያላትን የብቸኛ ላኪነት ክብር ሲያሳጣት ፤ ቺሊ ብራዚልን እና መሰል ሐገራትን አፍዝዞ ወደ አስቀረው ኢምፖርት ሰብስቲቲውሽን አዙሪት/ወጥመድ (Import Substitution (ISI) trap) ውስጥ ገባች።

ከእዚያም የቺሊ መንግሥት ኮርፎ (CORFO) የእሚባለውን እና ፦ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን የእሚፈጥረውን ፣ ለልማት ድርጅቶቹ ብድር የእሚያቀርበውን ፣ እንደ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ዓይነት መሠረተ ልማቶችን የእሚገነባውን ፣ ወዘተ ተቋማ በመፍጠር ፤ የመንግሥት የስለት ልጅ ስለሆኑ ከገበያው ውድድር የእሚከለል መስኮችን አበራከተ።

ውጤቱም ስረዓታዊ ጭለማ ነበር ፦ የዋጋ ግሽበት 500% ደረሰ ፣ በመንግሥት የንብረት ወረሳ ምክንያት የግል ንብረት ባለቤትነት እስከ እነ አካቴው ጠፋ በእዚኽም ሐገሪቱ የለየላት መርኽ አልባ የመንግሥት ስልጣን (Arbitrary Power) የአሻውን የእሚያደርግባት ሐገር ሆነች ።

### "ዓብዮታዊ ለውጥ": የቺካጎዎቹ ልጆች (1973–1989)

በ1973 የተደረገው የመንግሥት ግልበጣ የሐገሪቱን መሪ ብቻ አልነበረም የቀየረው ፤ የሐገሪትን ተቋማዊ አዕምሮ ሪፎርማት ("reformatted" the national brain) ያደረገው ወይንም በአዲስ መርኽ ያዋቀረው።

ቺሊ ፦ የቺካጎ ቦይስ (Chicago Boys) በተባሉት እና በቺካጎ ዩኒቨርስቲ የነጻ ገበያ ሰባኪ የነበረው የሚልተን ፍሪድማን (Milton Friedman) ተማሪ የነበሩ የቺሊ ዜጎች መሀንዲስነት ፤ የነጻ ገበያን ስረዓት በአምባገነናዊ መንግሥት ትዕዛዝ የሐገሪቱ የኢኮነሚ መመሪያ አደረገች።

ብዙ ግዜ ሐገራት መጀመሪያ ዴሞክራሲያዊ ሆነው ነው ወደ ነጻ ገበያ የእሚገቡት በቺሊ ግን የለየለት እና ጨካኝ የተባለው የፒኖሼ አምበገነናዊ መንግሥት ፤ አምባገነንነቱን የፖለቲካ ስልጣኑን ለመከላከል ብቻ ሳይሆን የነጻ ገበያ ስረዓትንም በግዴታ በቺሊ ለማስፈን ተጠቀመበት።

ተቃርኖው እሚገርም ነው!

ይኽንም ተከትሎ በቺሊ የግል ንብረት ቅዱስ እና ክቡር ሆነ ፤ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ለግለሰብ ተሸጡ ፣ በሳልቫዶር አሌንዴ (Salvadore Allende) ዘመን ከትላልቅ የእርሻ ባለቤቶች ተወርሰው ለገበሬ የተከፋፈሉ መሬቶች ተመልሰው ለቀድሞ ባለቤታቸው ተመለሱ ወይንም በመንግሥት ቁጥጥር ሥር

የነበሩ እርሻዎች ተመልሰው ለግለሰብ ተሸጡ ፤ በአጠቃላይ አምባገነናዊው የቺሊ መንግሥት የንብረትን መብት ለማስከበር ያለውን ቁርጠኝነት አሳየ።

በመላው ላቲን አሜሪካ ባልተለመደ መልኩ ፤ የበጀት ጉድለትን ለመሙላት ብሔራዊ ባንኩን ገንዘብ እንዲያትም የማድረግን አካኼድ በሕግ በማገድ ፤ ቺሊ በበጀት አስተዳደር ጉዳይ ላይም ቁርጠኛ ለውጥ አመጣች ።

በጡረታ አስተዳደርም ላይ ከፍተኛ ለውጥ አመጣች ፦ ቺሊ በአብዛኛው የዓለም ክፍል እንደ እሚደረገው እና የዛሬው ሠራተኛ የትናንቱን ሠራተኛ ጡረታ እንዲከፍል (Pay as You Go) ከእሚደረግበት እና በጡረታ የእሚሰበሰበው ገንዘብ በመንግሥት እጅ ተቀምጦ መንግሥት ከእሚያስተዳድርበት አሠራር በመውጣት ፤ የጡረታ ገንዘብ በግል እንዲተዳደር አደረገች።

በእዚኽም መሠረት እያንዳንዱ ሠራተኛ ከደሞዙ ላይ በግዳጅ የጡረታ በእሚል 10% እንዲቆረጥበት ይደርግና ይኽ ገንዘብ ግን በስሙ በባንክ እንዲጠራቀም ይደረጋ ፤ ያ የተጠራቀመ ገንዘብ ባለሒሳቡ ለፈለገው የፈንድ ማናጀር ተሰጥቶ ኢንቨስት እንዲደረግ እና በስተመጨረሻ ቁጣባውን እና የኢንቨስትመንቱን ትርፍ የእሚወስድበትን ስረዓት አቋቋመች። ይኽም በካፒታል ገበያ ውስጥ ጥሩ የተቀማጬ ገንዘብ ብዛት እንዲኖር በማድረግ ፤ የግሉን ዘርፍ ፋይናንስ በማድረግ ኢከነሚው ውስጥ ትልቅ ሚና ተጫወተ።

ጡረታን ካየነው እንደ ሌላው እንደ ማንኛውም ኢኮነሚያው ክስተት ፤ በአቅርቦት እና በጥየቃ መሰሳብ የእሚሠራ ነው። ጥቂቱ ሠራተኛ ብቻ ነው ጡረታ እስኪወጣ ድረስ ሥራ ላይ ቆይቶ ፤ ሙሉውን የጡረታ ቁጠባ የእሚያደርገው ፤ በአንጻሩ ደግሞ ኹሉም ሠራተኛ ፤ ከጅማሮ እስከ ጡረታ መውጫ የቆጠበውም ያልቆጠበውም ፤ የጡረታ ዘመኑ ላይ ሲደርስ የጡረታ ክፍያ ማግኘት ይፈልጋል። በመሆኑም በጡረታ ቁጠባ እና በጡረታ ክፍያ መካከል ብዙ ግዜ አለመጣጣም አለ ፤ ትንሽ ቁጠባ እና ብዙ ክፍያ እየኖረ።

ብዙ ግዜ በጡረታ ቁጠባ እና በጡረታ ክፍያ መካከል ልዩነት ስለ እሚኖር መንግሥታት የእሚያደርጉት ፤ ፔይ አዝ ዩ ጎ (Pay as You Go) የእሚባለውን እና የአሁኑ ሠራተኛ የትናንቱን ሠራተኛ ጡረታ እንዲከፍል ማድረግ እና ይኽም ተደርጎ የአሁኑ ጡረታ አስተዋፆ የተናንቱን ጡረተኛ በሙሉ መክፈል ስለ እማይቻል ጉድለቱን መንግሥት ይሞላል።

ቺሊ ግን ከእዚኽ ፍጹም የተለየ እና ከእላይ ለመግለጽ የተሞከረው እያንዳንዱ ሠራተኛ እስከ ጡረታ መውጫው ግዜ ድረስ ወጪ አድርጎ ሊጠቀምበት የእማይችለው ነገር ግን የእራሱ የሆነ ጡረታ ቁጠባ ሒሳብ ባለቤት የእሚሆንበት እና ያንንም ቁጠባ ማውጣት ባይችል ኢንቨስት ማድረግ የእሚችልበት ፤ የጡረታ ስረዓት ውስጥ ገባች።

በእርግጥ ኹሉም አሟልቶ ጡረታ ስለ እማያጠራቅም ፥ ቢያጠራቅምም ያ የቆጠበው ገንዘብ ፤ አንድ አንድ ግዜ በጡረታው ወቅት ለማኖር በቂ ስለ እማይሆን ጡረተኛው ተወደደም ተጠላም የመንግሥትን ድጎማ መፈለጉ ላይቀር ይችላል።

ሆኖም ይኽ ዓይነቱ ጉድለት ፤ የጡረታ ቁጠባው በግል ተያዘ ወይንም በመንግሥት ተያዘ ፤ ስለ እሚኖር እና የመንግሥትን ድጎማ ግድ ማለቱ ስለ እማይቀር ልዩነቱ እምብዛም ነው።

ሆኖም የቺሊው አካኼድ ግን አንድ ተጨማሪ ትልቅ የማክሮ ኢከነሚ ጥቅም ነበረው። እርሱም በቺሊ ገንዘብ ባንኮች ውስጥ ተቀምጦ ባንኮቹ ወይንም ሌሎች ኢንቨስተሮች ሊያበድሩት ወይንም ኢንቨስት ሊያደርጉ ይችሉት የነበረ በመሆኑ ፤ በቺሊ ውስጥ ትልቅ የኢንቨስትመንት ምንጭ ሆነ (Generate a large pool of long-term domestic capital)።

ያ ገንዘብ ግን በመንግሥት ቁጥጥር ውስጥ ቢሆን ፤ በተለይ ደካማ የበጀት አስተዳደር በተንሠራፋባቸው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሐገራት ፤ የታይታ ፕሮጀክት ፋይናንስ እያደረገ ፤ ኢከነሚዊ ምርታማነት አሳዳጊ ሳይሆን የዋጋ እና የብድር ወለድ ግሽበት በመፍጠር ኢከነሚ አዛቢ ሊሆን ይችላል።

በቺሊ ግን ገብያ ውስጥ ገብቶ በውድድር በገበያ መርኽ ስለ እሚከፋፈል ፤ ፋይዳው ብዙ ሆኗል።

ሆኖም ፤ በቺሊ የግል ጡረታ ቁጠባው በመንግሥት ድጎማ ስለ አልተደገፈ ፤ ብዙ ሰው ጡረታ መውጫው ላይ ሲደርስ በቂ የጡረታ ቁጠባ አልነበረውም። ይኽም ፤ ወርልድ ክላስ (World-class) የእሚባል የካፒታል ገበያ ያስቻለ የጡረታ ቁጠባ ጡረተኞችን ማኖር ስለ አልቻለ ነበር በ2019 የባቡር ትኬት ጨመረ ከሚሉ ዓይነት ክስተቶች ጋር ተዳምሮ የ2019ን አመጽ የቀሰቀሰው።

ተቋማዊ ማሻሻያው በተሳካ ኹኔታ ኃብት እና ኢንቨስትመንት መፍጠር ሲችል ፤ ማሕበራዊ ድጎማ ላይ ግን ደካማ ነበር።

ሆኖም ፤ የቺሊ ኢኮኖሚ ከብራዚል ኢኮኖሚ ይልቅ ተወዳዳሪነት እና አምራችነት ስለ እሚታይበት ፤ ከ90 በመቶ በላይ የእሚሆነውን በጀቷን በድህነት ቅነሳ እና በሰው ኃብት ልማት ላይ ከእምታጠፋው ብራዚል ይልቅ የቺሊ ኢከነሚ ለዜጎቹ ከብራዚል የታሻለ የኑሮ ደረጃ ይሰጣል ፦ በሰው ኃብት ልማት ፣ በእድሜ ጣራ ፣ በጤና ሽፋን ፣ በሕጻናት ሞት ፣ በመሳሰሉ መመዘኛዎች ቺሊ ከብራዚል ትበልጣለች ምንም እንኳን ብራዚል የእምትሻልባቸው የተወሰኑ ለምሳሌ አነስተኛ የስራ አጥነት ቁጥር ዓይነት ነገሮች ቢኖሩም።

**ወርቃማዊ ዴሞክራሲያዊ ዕድሳት (1990–2014)**

በ1973ቱ አብዮት ወደ ስልጣን የመጣው የቺሊው አምባገነን ፤ ጀነራል አውግስቶ ፒኖሼ (General Augusto Pinoche) የጀመረውን የኢከነሚ ማሻሻያ ፦ ሕዝባዊ ድጋፍ ኖሮት እንዲቀጥል ስለ ፈለገ ፣ የአሜሪካ መንግሥት ጫና ስለ በረታበት እና ከሐገርም ውስጥ ተቃውሞ ስለ ጠነከረ ፤ በ1980 የጸደቀው የሐገሪቱ ሕገመንግሥት በ1988 ሬፍረንደም እንደ እሚያካኺድ አንድ አንቀጽ አስቀመጠ።

በእዚኽም መሠረት በ1988 የፒኖሼ መንግሥት ይቀጥል ወይንስ አይቀጥል የእሚል ሪፈረንደም ተደረገና ፤ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ፤ አምባገነኑ ፒኖሼ በድምጽ ብልጫ ተሸንፎ ፤ ዴሞክራሲያዊ መብቶችን የእሚያከበር ፣ የሕግ የበላይነትን የእሚያረጋግጥ እና በእየግዜው ምርጫ የእሚያደርግ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ተመሠረተ።

ሆኖም ቺሊ በእዚኽ መልኩ ወደ ዴሞክራሲ ስትመለስ ፤ በአብዛኛዎቹ የላቲን አሜሪካ ሐገራት እንደ ሆነው ፤ በፒኖሺ በግድ የተጫነው የነጻ ገበያ ስረዓት አልተሻረም። አዲሶቹ የቺሊ መሪዎች ፤ በአምባገነኑ ፒኖሼ የተጀመረውን የበጀት ጥንቃቄ (Fiscal Discipline) እና የንግድ ክፍትነት አስቀጠሉት እንጂ አላቋረጡትም ፤ ያደረጉት አዲስ ነገር ቢኖር ፤ ሕዝቡን የመስማት አቅማቸውን በምርጫ እና ኃሳብን የመግለጽ መብትን በማክበር መጨመር ነበር።

ይኽም በአምባገነኑ መንግሥት የተጀመረው የኢከነሚ ማሻሻያ በዴሞክራሲያዊ መንገድ እንዲቀጥል አደረገ።

***የመዳብ ገቢ ፈንድ:***

ብዙ ግዜ እንደ መዳብ ፣ ወርቅ ፣ ወዘተ ያሉ ጥሬ ዕቃዎችን በመላክ ላይ ተደጋፊ የሆነ ኢከነሚ ያላቸው ሐገራት የእሚቸገሩበትን የዋጋ መለዋወጥ ችግር ለመፍታት ፤ ቺሊ ፡- የመዳብ ምርት በእሚወደድበት ግዜ የእሚገኘውን የዋጋ ጭማሪ አንስቶ በመቆጠብ የመዳብ ዋጋ በእሚርክስበት ግዜ የመጠቀም አሠራር በመፍጠር ፤ የመንግሥትን በጀት የመዳብ ዋጋ መዋዠቅ ከእሚፈጥረው የበጀት መዛባት ተከላከሉት።

በእየ አመቱ ፤ ገለልተኛ የሆኑ እና የመዳብ ዋጋ ትመና ላይ ኤክስፐርት የሆኑ ሰዎች ፤ መዳብ በመጪዎቹ ግዜያት አማካይ ዋጋው ስንት ሊሆን እንደ እሚችል ይትመናሉ። ለምሳሌ ፡- መዳብ በኪሎ 3 ዶላር ይሆናል ብለው ከተመኑ እና ዋጋው በኪሎ 4 ዶላር ቢገባ ፤ መንግሥት ትርፉን አንድ ዶላር እንደ አይጠቀምበት ይልቁንም እንዲቆጥብ በሕግ ይታዘዛል።

ያም ገንዘብ ኢኤስኤስኤፍ (ESSF - Economic and Social Stabilization Fund) የእሚባለው የኢከነሚ እና የማሕበራዊ መዛባት ማረጋጊያ ሒሳብ ውስጥ ይቀመጣል።

በአጠቃላይ መንግሥት ከመዳብ ሽያጭ መጠቀመ የእሚችለው ፤ የአስር አመቱን አማካኝ የመዳብ ዋጋ ብቻ ነው ፤ ይኽም ተለዋዋጭ የሆነውን የመዳብ ገቢ ወደ ተረጋጋ እና ተገማች የገቢ ምንጭ ቀየረው።

የመዳብ ዋጋ ሲወድቅ ፤ ኢኤስኤስኤፍ (ESSF - Economic and Social Stabilization Fund) ፤ የበጀት ጉድለቱን ለመሙላት ያገለግላል። ስለእዚኽ፡- የመዳብ ዋጋ በእሚቀንስበት ወቅት ፤ መንግሥት ለጤና ፣ ለትምሕርት ወይንም የመሠረተ ልማት የእሚመድበውን ገንዘብ ከመቀነስ እና ማሕበራዊ አለመረጋጋት ከመፍጠር ይልቅ ፤ ከአደጋ ግዜ ኪሱ እያወጣ ይከፍላል። ይኽም ሕዝቡ ፤ ገበያው ቢወጣም ቢወርድም የመንግሥት እገዛ አብሮት እንደ አለ እንዲያስብ እና መተማመን እንዲኖረው በማድረግ ማሕበራዊ መረጋጋት ይፈጥራል።

ይኽን መልክ ያለው የቺሊ የማሕበረኢከነሚ አገነባብ የቺሊን ኢኮኖሚ ቀስ በቀስ በመገንባት በ2010 ቺሊን ኦኢሲዲ (OECD) የእሚባለው እና የዓለማችን 38 ትልልቅ ኢከነሚዎች ከእሚካተቱበት ቡድን ውስጥ አምጥቶ አስገባት ፤ ይኽም ቺሊ ከመካከለኛ ገቢ ወጥመድ (Middle-Income Trap.) ሰብራ መውጧትን በትክክል አሳይቷል።

**የቺሊ የቅርቡ እንቆቅልሽ (The 2026 Paradox: The "Social Amnesia")**

የቺሊ የኢኮኖሚ ታሪክ ፤ አምስቱ ኹኔታዎች በሐገራት ኢኮኖሚያዊ አፈጻጸም ላይ ያላቸውን ተዘማጅ (Direct relation) ግንኙነት የእሚያሳይ ነው።

ወረድ ብለን እንደ እምናየው ፤ በምርመራው ማሽን ምርመራ መሠረት ፤ ቺሊ ከሞላ ጎደል በአምስቱም ኹኔታዎች ከፍተኛውን ውጤት 4 የእምታገኝ ሐገር ናት። በእዚያም መሠረት ውጤቱ ከፍተኛ ገቢ ያለው ሐገር ደረጃ ላይ ቢያስቀምጣትም ፤ ቺሊ ግን የሲንጋፖርን ወይንም የአሜሪካን ዓይነት ፤ የከፍተኛ ገቢ ያላቸው ሐገራት ቁንጮ አይደለችም ፤ እንደ ሲንጋፖር እና አሜርካ ካሉት የመደቡ ቁንጮዎች በነፍስ ወከፍ ገቢ ምን አልባት በ5 ዕጥፍ ታንሳለች።

ምክንያቱም ፦ በአንድ ሐገር አምስቱ ኹኔታዎች በደረሱበት የዕድገት ደረጃ ነው የሐገራት የኢኮኖሚ ደረጃ የእሚወሰነው ስንል ፤ ጉዳዩ የሆነ የቁጥር ጉዳይ ሆኖ ፤ እንዴትም ተብሎ ቁጥሩ ከፍ ከተደረገ ውጤት የእሚመጣ ወይንም አምስቱን ኹኔታዎች ማሸሻል በእራሱ ገቢ ስለ ሆነ አይደለም።

ከ1970 እስከ 80ዎቹ ባሉት የአብዮታዊ ለውጥ ዘመን ፤ የቺሊው መንግሥት ከፍተኛ ንብረትን ወደ ግል የማዘዋወር አብዮት ውስጥ ገብቶ ነበር። ሆኖም ንብረት በእዚኽ መልኩ በስፋት ወደ ግል ሲዞር ፤ በወቅቱ ከመንግሥት ወደ ግል ሲዞሩ የነበረቱን ንብረቶች ለመግዛት ኃብት ወይንም የመበደር አቅም የነበራቸው ጥቂት የወቅቱ ባለኃብቶች ብቻ ነበሩ። ስለ እዚኽ ፦ አብዮቱ ንብረት ሲያዞር ፤ ምንም እንኳን ንብረት የማዞር ኺደቱ ከመድሎ በጸዳ መልኩ ለኹሉም ነው እሚደረገው ቢባልም ፤ በወቅቱ ግን ገንዘብ ኖሯቸው መጠቀም የእሚችሉት ጥቂቶች ስለነበሩ ፤ ሕጉ ለኹሉም በእኩልነት ነው የሠራው ማለት አይቻልም።

ሕጉ ኹሉም ሰው ባንክ መመሥረት ይችላል አለ ፤ ነገር ግን ገንዘቡ ኖሯቸው ባንክ መመሥረት የቻሉት በጣት የእሚቆጠሩ ጥቂት ቤተሰቦች ነበሩ። ይኽ በየትኛውም ግዜ የእሚኖር ተጨባጭ ኹኔታ ነው እንደ አይባል ፤ እነ እዚኽ ባለኃብቶች በወቅቱ የነበራቸውን ብልጫ ተጠቅመው የኢኮኖሚ ከፍታውን ከተቆጣጠሩ በኋላ ፤ ያላቸውን ኃብት እና የተለያዩ አሠራሮች በመጠቀም ሌሎች ዜጎች እንደ አይወዳደሯቸው አደረጉ። በአጭሩ የንብረት ባለቤትነት መብቱ ሕጋዊውድድርን (Contestability) በአግባቡ ያካተተ አልነበረም።

በእዚኽ ዓየነቱ ድባብ ውስጥ የንብረት ተንቀሳቃሽነት ("Asset Mobility") ንብረተን በሐራጅ እንደ ማገድ ሌላው እንደ አይጠቀምበት የማድረግ እንጂ ንብረት በውድድር ለተሻለው አምራች እንዲተላለፍ ማድረጊያ መንገድ አይሆንም። አንድ አዲስ ነጋዴ አዲስ የእርጎ ዓይነት ይዞ መጥቶ የእርጎውን ገበያ መቀላቀል ቢፈልግ ፤ ነባራዊ ባለኃብቱ ፤ ያላቸውን ኃብት እና የሱፐርማርኬት ሰንሰለት ተጠቅመው ፤ አዲሱ ነጋዴ ከስሮ እስኪወጣ ዋጋ በማርከስ ሊጎዱት ወይንም እሚቀበለው ሱፐር ማርኬት እንደ አይኖር ማድረግ የእሚችሉበት አሠራር አለ።

ይኸም አልሠራ ካለ በባንኩ ዘርፍ ያላቸውን ተፅዕኖ ተጠቅመው ፤ ይኸ አዲስ ገቢ ሰው ብድር እንደ አያገኝ ወይንም ካምፓኒውን ገዝተው ሊዘጉት ይችላሉ ፤ ተወዳዳሪው ከማደጉ በፊት።

ከእዚኸ አንጻር የቺሊ ትልቁ ስህተት የግል ንብረት መፍቀዷ ወይንም ማክበሯ አልነበረም ፤ ይልቁንም የጸረ ሞኖፖሊ (Anti-Trust Laws) ሕግ እና የውድድር መኖርን የእሚያረጋግጥ ሕግ ሳይኖር የንብረት መብትን ወደ ልዩ ጥቅም (Privileges) መለወጧ ነው።

ቺሊ ፍትኃዊ የኃብት ክፍፍል ሳታደርግ በፊት ነጻ ገበያን በማስተዋወቅ ፤ ቺሊ የነጻ ገበያ እና የውድድርን ስረዓት የጥቂቶች የበላይነት ወደ እሚረጋገጥበት ስረዓት ቀየረችው።

በግል ንብረት መብት የተፈጠረው ይኸ "የብቃት ደሴት" እራሱን ወደ ኃብት ምሽግነት ስለ ቀየረ ፤ በቺሊ የኢኮነሚ እድገት የአንድ ሰው ታታሪነት እና ምርታማነት ውጤት ሳይሆን ከባለኃብቶች ጋር ባለ ግንኙነት የእሚወሰንበት ዓይነት ኢኮኖሚያዊ ኹኔት ፈጥሯል።

የቺሊ ለውጥ ፤ እድሉ ለሌላቸው ሰዎች ድጎማ እና የተደላደለ የውድድር ምህዳር ሳይፈቅድ ፤ የንብረት ባለቤትነትን ማክበር በእሚል ኃብትን በጥቂቶች እጅ ተሰብስቦ እንዲቀመጥ እና የሌሎችን እድል እንዲያጠብ ስለ አደረገ ፤ በኺደቱ ተጋላጭ እና ተጠቂ ዜጎች ፈጠረ።

ለእዚያም ነበር በ2019 በባቡር ቲኬት ላይ 30 ፔሶ ሲጨመር እና ሕዝቡ አመጽ ሲወጣ ይዞት የወጣው መፈክር 30 ፔሶው አይደለም 30ው ዓመት ነው የእሚል ሆኖ የነበረው። ሕዝቡ ስረዓቱ የእሚጎድለው ነገር እንደ አለ አውቀዋል ፤ ጉድለቱ ግን ምን እንደ ሆነ አላወቁም።

ከአመጹ በኋላ ችግሩን ለመፍታት ሲነሱ ፤ የለየላቸው የአከባቢ ጥበቃ ፅንፈኛ ነው የሆኑት።

ሰው ብቻ አይደለም ተፈጥሮም መብት አለው አሉ። ለምሳሌ ፡- በሕገ መንግሥት ውስጥ ውኃ ንጹ የመሆን መብት አለው ብለው በማስቀመጥ ፤ ባለኃብት ውኃውን እንደ አይበክለው ለመከልከል እና ባለ ኃብቱ ውኃውን መበከል ሲከለከል ከስሮ ውኃው እንዲለቀቅ ነው እሳቤው።

ይኸ ዓይነቱ ከፖለቲካዊ መፍትኼ ይልቅ ወደ ተፈጥሮ አምልኮ የእሚቀርብ ማሻሻያ ግን ፤ ባለኃብቱ ውኃን በእማይበክል መልኩ ትርፋማ ሊያደርገው በእሚችል መንገድ ሊጠቀምበት ስለ እሚችል ማሻሻያው ተቀባይነት ሊያገኝ አልቻለም።

መፍትኼው የጸረ ሞኖፖሊ ሕግ እና ማሕበራዊ ዋስትና (The Lack of Anti-Trust and Social Insurance) ነበር እንጂ ለተፈጥሮ መብት መስጠት አልነበረም።

የቺሊው ማሻሻያ ቅደም ተከተል ያለውን ትልቅ ዋጋ ያሳያል። የንብረት መብት ባለቤትነት ፤ የውድድር አቅም ባላደገበት እና ጸረ ሞኖፖሊ (Lack of Anti-Trust) ሕግ በሌለበት ኹኔታ ፤ የጥቂቶችን ባለኃብትነት ነው እሚፈጥረው። በተመሳሳይም የበጀት አስተዳደር ከመሠረት ልማት ግንባታ ጋር አብሮ ፤ የድህነት ቅነሳ እና ማሕበራዊ ድጎማ አብሮት ከሌለ ፤ የጥቂቶች ሐገር ነው እሚገነባው።

ስለ እዚኽ ፦ በተመረጠ መንገድ አምስቱን ኹኔታዎች በማሻሻል ፤ የበለጸገ ሐገር መፍጠር ይቻላል ፤ ሆኖም በእዚኽ ዕድገት ሰፊ የሕዝብ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ካልተቻለ ፤ በኋላ ላይ የተፈጠረውን ኃብት መሠረት እሚያሳጣ ማሕበራዊ አለመረጋጋት ይሆናል ውጤቱ።

እንዲኽ ዓይነት ኢከነሚያዊ ታሪክ ያላትን ቺሊን ፤ ያለፈው 40 (1986–2026) ዓመት አፈጻጸሟን መሠረት አድርገን ፤ በምርመራ ማሽን ውስጥ ስናሳልፋት ፤ በወታደራዊ አምባገነን ከእሚመራ የገበያ ኢከነሚነት እራሷን የዋሽንግተን ኮንሰንሰስ (Washington Consensus) ሰርቶ ማሳያ የሆነ ዴሞክራሲያዊ ሐገርነት የቀየረች እና አሁን ደግሞ ከ2020–2026 አካኼዷ ብዙ ጥያቄ ውስጥ የገባ ሐገር ሆናለች።

**1. የግል ንብረት (አንኳር)**

| **አመላካች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **1. ባለቤትነት** | ኹሉም ሊባል በእሚችል ደረጃ ፤ ኢከነሚያዊ ፋይዳ ያላቸው ንብረቶች በሙሉ መቶ በመቶ በግል ንብረትነት መያዝ ይችላሉ። የውጭ ዜጎች እንደ ሐገሩ ዜጎች በከተማም ሆነ በገጠር መሬትን ጨምሮ በግል የንብረት ባለቤት መሆን ይችላሉ። በእዚክ የማይካተቱት የሐገሪቱ የመሬት ውስጥ እንደ መዓድን እና ነዳጅ ያሉ ንብረቶች ናቸው ፤ ይኽ በሕገ መንግሥት የመንግሥት ነው ተብሎ ተቀምጧል ሆኖም የግሉ መስክ ፤ የሐገር ውስጥም ሆነ የውጭ ዜጋ ፤ ከመንግሥት ጋር በሽርክና (Private Public Partnership) እንዲሠራ የተፈቀደ ነው። ሆኖም ከድንበር ደህንነት ጋር በተያያዘ ፤ የሽርክና ፈቃድ በድንበር አከባቢ የተወሰነ ክልከላ አለበት። | **2 (ከፍተኛ)** | ከማዕድኑ መስክ በስተቀር የግሉ ዘርፍ ከ90 በመቶ በላይ የእሚሆነውን የኢከነሚውን መስክ ተቋጥሯል ፤ አስተማማኝ ሕጋዊ ከለላም አለው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **2. ውርስ** | ሕገመንግሥቱ እና የውርስ ሕጉ (DL 2186) የግድ ንብረቱ ከመወረሱ በፊት በገበያ ዋጋ የሆነ የካሳ ክፍያ ድንጋጌ አለው። በልምድም እንደ ታየው መንግሥት ንብረት የመውረሱ ጉዳይ ዜሮ ነው።<br><br>ከቅርብ ግዜ ወዲኽ **(2025-2026):** በሐገሪቱ ውስጥ ካለው የቤት ችግር የተነሳ ፤ የግል ንብረት ላይ ጨምሮ ፤ በተደራጀ መልኩ የእሚደረጉ የጨረቃ ቤት ሠፈራዎች እየተበራከቱ በመምጣታቸው እና መንግሥትም ከኹኔታው አንጻር ፤ የጨረቃ ቤቶችን ከማፍረስ ስለ እሚዘገይ ፤ የንብረት ባለቤትነት ትንሽ ጥያቄ ውስጥ ገብቷል። | **2 (ከፍተኛ)** | በቺሊ ባለፈው አርባ ዓመት የግል ንብረት ቅዱስ እና ክቡር ነው ሆኖም ከቅርብ ግዜ ወዲኽ ምንም እንኳን ሕጉ ግልጽ ቢሆንም እና መንግሥትም ሕጉን ለማስከበር ፈቃደኛ ቢሆንም ፤ በመሬት ጉዳይ የቤት ችግር እና የፈጠረው ማሕብራዊ ጫና በመሬት ጉዳይ የግል ንብረትን አደጋ ውስጥ ከቶታል። |
| **3. ሕጋዊውድድር (Contestability)** | ቺል የጸረ ሞኖፖሊ ችሎት እና ጉዳዮች አቃቢ ሕግ አላት ። ሆኖም ዳኞቹ ሕጉን ውድድርን ለማበረታት ከመጠቀም ይልቅ እንደ ተጻፈ እንበይንበት የእሚል ዝንባሌ ስለ አሳዩ ፤ ለምሳሌ አንድ ሰው በተለያየ ንግድ ድርጅት ውስጥ የቦርድ አባል ለመሆን የእሚከለከለው ፤ ድርጅቶቹ የተለያዩ ሲሆኑ ብቻ እንጂ በአንድ ቢዝነስ ግሩፕ ስር ከሆነ አደለም ብለው በመበየን (Interlocking directorates,) ኦሊጎፖሊን ይከላከላሉ። በቺሊ በአንድ አንድ | **1 (መካከለኛ)** | የንብረት ውድድሩን ወይንም ሽሚያውን ዴሞክራሲያዊ የማድረግ ሕጋዊ ውቅር አለ ፤በተግባር ግን ኢከነሚው ኦሊጋሪክ (Oligarchic) ነው። በባንክ እና የጅምላ/ችርቻሮ ንግድ ለመግባት ያለው አዳጋችነት (Barriers) ከፍተኛ ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | መስኮች ለመሠመራት ከ90 በላይ የፈቃድ ዓይነቶች ያስፈልጋሉ ይኸም አዲስ ነጋዴዎች ሊቋቋሙት ይከብዳቸዋል ፣ ወዘተ በአጠቃላይ ተግባር ላይ ችግር አለ። | | |
| **የሠራተኛ ነጻነት (Labor Freedom)** | በአፕሪል 2026 የወጣው “40 የሥራ ሰዓት” የእሚለው (Law 21.561) ሕግ ሣምንታዊ የሥራ ሰዓትን ቀንሷል። ይኸ ለሠራተኛው የእረፍት ሰዓት ቢጨምርለትም ፤ የሥራ ማስኬጃ ወጪን ይጨምራል። ሆኖም በ2026 መንግሥት የሠራተኛ ማሕበራት ከአንድ ድርጅት ጋር ሳይሆን ከበርካታ ድርጅቶች ጋር መደራደር የእሚችሉበትን ሕግ ማንሳቱ ፤ የቅጥር ገበያውን ነጻነት አላብሶታል። | **1 (መካከለኛ)** | ቺሊ የቅጥር ኹኔታን በስምምነት የእሚያደርግ ሕግ አላት ፤ ሆኖም የሥራ ሰዓት ቅነሳ ፣ ሠራተኛ ለማባረር በቀጣሪዎች ላይ ያለው ገደብ ከ1990ዎች አንጻር ሲታይ ፤ የቅጥር ገበያው ብቁ የሆነ የሠራተኛ ድልድል የማድረግ አቅሙን ገድቧል። |

**የአመላክቾች አማካይ: 1.66 → በቺሊ ፥ የንብረት ባለቤትነት መብት ልኬት: 4**

**2. የንብረት ተንቀሳቃሽነት (አጥዳፊ)**

| **አመላካች** | **የባለፈው 40 ዓመታት አፈጻጸም** | **ልኬት(0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የውጭ ዜጎች የንብረት ባለቤትነት** | የቺሊ የንብረት ገበያ ለኹሉም በጣም ክፍት ነው። DL 600 የእሚባለው ሕግ የውጭ ካፒታል በቺሊ ንብረት እንዲገዛ የብረት መዝጊያ ነው። | **2** | የውጭ ዜጎች በኹሉም ሊባል በእሚችል ደረጃ የግል ንብረት ያለ ምንም ክልከላ ይይዛሉ። |
| **የመሬት ገበያ** | የመሬት ገበያ ከፍተኛ ገንዘብ የእሚንቀሳቀስበት እና ግልጽ የሆነ የባለቤትነት | **2** | መሬትን በብድር ማስያዣነት መጠቀም እንዲኹም መግዛት እና |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ሰርተፍኬት በኮምፒውተራይዝድ መንገድ ያለበት ነው። | | መሸጥ በጣም ቀላል ነው። |
| **የካፒታል ቁጥጥር (Capital Controls)** | ለባለፈው 25 ዓመት ምንም ዓይነት የካፒታል ቁጥጥር የለም ፤ ምንም እንኳን በ1990ዎቹ አከባቢ ፤ ወደ ሐገር ውስጥ ለአጭር ግዜ ለኢንቨስትመንት ገንዘብ የእሚያስገቡ ሰዎች ከ20 እስከ 30 በመቶ የእሚሆነውን የገንዘቡን መጠን ወለድ በእማይከፈልበት ሂሳብ ለአንድ ዓመት እንዲያስቀምጡ ይጠየቁ የነበር ቢሆንም። | **2** | በቺሊ የካፒታል ፍሰት ምንም ቁጥጥር የለበትም። |
| **የስቶክ ገበያ መጠን (Stock Market Size)** | የገበያ ጥጉ (Market cap) የእሚባለው እና በአንድ ሐገር ለሽያጭ የቀረቡ የአክስዮን መጠን የእሚገልጸው ቁጥር ፤ ከኢኮነሚው ዓመታዊ የማምረት አቅም (GDP) አንጻር 70% ነው ፤ ይኸንንም ገበያ የጡረታ ቁጠባው የገንዘብ አቅርቦት በማስፋት (By Providing Liquidity) ትልቅ ሚና ይጫወታል። | **2** | የስቶክ ገበያው እንደ ቺሊ ላለ መካከለኛ መጠን ላለው ኢኮነሚ በጣም እንቅስቃሴ የበዛበት የእሚባል ነው። |
| **በቀላሉ ንግድ መጀመር እና መዝጋት ይቻላል?(Ease of Start/Exit)** | የንግድ ፈቃድ በአንድ ቀን ("Empresa en un día" (Business in a day)) በእሚል አሠራር በኦንላይን ምዝገባ በአንድ ቀን ፡- የግብር ከፋይ መለያ ማግኘት ፣ የንግድ ፈቃድ ማውጣት እና የባንክ አካውንት | **1** | በጠቅላላው ንግድ ለመጀመር እና ለመዝጋት ፤ በጣም ዝቅተኛ ቢሮክራሲያዊ ጣጣ ነው ያለው ማለት ይችላል ፤ አንድ አንድ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | መክፈት እንዲቻል በማድረግ ፤ የንግድ ፈቃድ አወጣጥን በጣም ቢያቀሉትም እና ዋጋውን ቢያረክስቱም ፤ እንደ ማዕድን ፣ ኃይል ማመንጨት ፣ ምግብ ፣ ጤና ፣ ትራንስፖርት እና ኮንስትራክሽን ባሉት መስኮች ነጋዴዎች ከ90 እስከ 400 የእሚደርሱ የተለያዩ ዓይነት ፈቃዶች ስለ እሚያስፈልጋቸው ፤ አፈጻጸማቸው ቅይጥ ነው። | | መስኮች ላይ ግን ዓመታት ሊፈጅ ይችላል። |
| **በቀላሉ ብድር ማግኘት** | በጣም ዘመናዊ የሆነ የባንክ ዘርፍ አለ ፤ ሆኖም ብድር በቀላሉ የእሚያገኙት ባሕላዊ የእሚባሉት እንደ ማዕድን እና ትራንስፖርት ያሉት ዘርፎች ብቻ ናቸው። | **1** | በንግድ ላይ ለቆዩ እና ትላልቅ ለሆኑ ድርጅቶች ብድር ማግኘት በጣም ቀላል ነው ፤ ሆኖም አነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች ግን ብድር የማግኘት ፈተና አለባቸው። |

**የአመላካቾቹ አማካይ: 1.67 → በቺሊ የንብረት ተንቀሳቃሽነት ልኬት: 4**

**3. የሕግ የበላይነት (አንኳር)**

| **አመላካች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የፍርድ ቤት ነጻነት** | የዳኝነት ስረዓት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ ሞያዊ ስነምግባር ያለው እና ከአስፈጻሚው ተፅዕኖ የሌለበት ነው። | **2** | ፍርድ ቤቶች ብዙ ግዜ በሠራተኛ መብት እና በአከባቢ ጥበቃ ጉዳዮች መንግሥት የእሚሸነፍበት ውሳኔ ይወስናሉ። |
| **ሙስና** | ለባለፉት ተከታታይ አስርት አመታት በመላው ላቲን አሜሪካ | **2** | የሙስና ወንጀል በፍርድ ቤት ተከሶ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ዝቅተኛ የሚባል የሙስና መጠን ነው በቺሊ ያለው ፤ ከንግድ ሥራ ጋር በተለያየ ለመንግሥት ሠራተኞች ጉዳይ ለማስፈጸም በእሚል ጉቦ መክፈል እሚባል ነገር የለም ማለት ይቻላል። | | ይቀጣል ፤ ግልጸኝነት በሕጉ ስረዓት ከመደንገጉ በላይ በሕበረተሰቡም ውስጥ እንደ ባሕል ተመሥርቷል። |
| **የውል ተፈጻሚነት (Contract Enforcement)** | አስተማማኝ ደረጃ ላይ ይገኛል ፤ ምንም እንኳን ከ2020-2026 ባለው ግዜ ውስጥ መዳተት ታይቶ ፤ የከረሙ ፋይሎች መፈጠር ቢጀምሩም። | **1** | አስተማማኝ እና ተገማች ነው ምንም እንኳን ተካሳሽ በሙብዛቱ ( Increased litigation volume) መዘግየት እየተስተዋለ ቢሆንም። |
| **በሕግ ፊት እኩል መታየት** | ጠንካራ ሕጋዊ መዋቅር አለ ሆኖም ፤ የሱፐር ማርኬት ሰንሰለት ባለቤቶች እና አንድ አንድ የወረቀት ፋብሪካ ባለቤቶች ፤ በአቃቢ ሕግ እስኪጋለጡ ድረስ ፤ በአሠራር ሳይያዙ በመቅረታቸው የሕዝቡን መተማመን ሸርሽሯል ፤ ምንም እንኳን ከተጋለጡ በኋላ ፍርድ ቤት ጥፈተኛ ብሏቸው ካሳ እንዲከፍሉ ቢደረጉም። | **1** | ጥቂት ትልልቅ ባለኃብቶች ሕጋዊ ሳይሆን አስተዳደራዊ ከለላ ያገኛሉ የእሚል ዕምነት አለ። |
| **ፖለቲካዊ ጣልቃገብነት** | በመደበኛ የንግድ እና የንብረት ጉዳይ ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት በጣም ዝቅተኛ ነው። | **2** | የሕግ ስረዓቱ የዜጎችን እኩልነት ማረጋገጫ ሆኖ ይሠራል። |
| **የፖሊስ አስተማማኝነት** | የቺሊ ፖሊሶች (Carabineros) ከፍተኛ ሞያዊ ስነምጋብር ያላቸው ናቸው ፤ ምንም እንኳን ከ2019 እስከ 2021 የቆየውን አመጽ የያዙበት መንገድ ትንሽ ቢያጠለሻቸውም። | **2** | በጠቅላላ ንብረትን ለመከላከል እና ማሕበራዊ መረጋጋትን ለማቀጠል አስተማማኝ ነው። |

**የአመላካቾቹ አማካይ: 1.66 → በቺሊ የሕጉ ነጻ እና ገለልተኛነት ደረጅ ልኬት : 4**

**4. የንግድ ክፍትነት (አጥዳፊ)**

| **አመላካች** | **የባለፈው 40 ዓመታት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የታሪፍ መጠን** | በቀጥታ ለኹሉም የገቢ ዕቃዎች 6% ቀረጥ ይጣላል ፤ በተግባር ግን ፤ ቺሊ ከ30 በላይ ሐገራት ጋር የንግድ ስምምነት ስለ አላት ፤ የገቢ ዕቃ ቀረጥ ዜሮ ነው ማለት ይቻላል። | **2** | ቺሊ በዓለም ላይ ከፍተኛ መጠን ያለው የንግድ ክፍትነት ካላቸው ሐገራት የእምትመደብ ነች ። |
| **ከታሪፍ ውጭ ያሉ ገደቦች** | የገቢ/ወጭ ንግዱ በጣም ጥራት ያለው ሳኒተሪ (Sanitary) የእንስሳት እና የሰው ጤና እንዲሁም ፋይቶሳኒተሪ (Phytosanitary) የእጽዋት ጤና መቆጣጠሪያ መርኽ ያለው ነው ። | **2** | በጣም ጥቂት አስተዳደራዊ ገደብ ነው ያለው። |
| **የገቢ/ወጪ ንግድ ከኢኮኖሚው አንጻር (Trade (% of GDP))** | ከዓለም ዓቀፍ ገበያ በጣም የተሳሰረ ፤ የገቢ ወጪ ንግዱ የኢኮኖሚው ከ60–70% በመሆን (60–70% of GDP)። | **2** | ከዓለም ዓቀፍ ገበያ በእሚገባ የተሳሰረ። |
| **በገቢ/ውጪ ንግድ ላይ ያለ ክልከላ** | በጣም ጥቂት ክልከላ ነው ያለው ፤ የመዳብ ኤክስፖርት በመንግሥት ክትትል ይደረግበታል ህኖም ክልከላ የለበትም። | **2** | ነጋዴዎች ከሞላ ጎደል ኹሉንም ነገር መላክ እና ማስመጣት ይችላሉ። |
| **የጉምሩክ ቆይታ** | ብቁ እና በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የጉሙሩክ አሰራር አለ። | **2** | ፈጣን እና ከእንግልት የጸዳ አሠራሩ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | የእሚታወቅ የግሙሩክ አሠራር አለ። |
| **የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት እና ሕግ አክባሪነት (WTO Compliance)** | በቋሚነት የድርጅቱ አባል የሆነች እና በተለያዩ ደረጃዎች ከሌሎች የድርጅቱ አባላት ጋር በስምምነት የእምትሠራ ነች። | **2** | ባለፈው 40 ዓመት ጠንካራ የእሚባል የድርጅቱ ሕግ አክባሪነት ታሪክ ነው ያለው። |

**የአመላካቾቹ አማካይ ውጤት : 2.00 → በቺሊ የንግድግ ክፍትነት ደረጃ ልኬት: 4**

## 5. የበጀት አስተዳደር ጥበብ (Fiscal Discipline - Stabilizer))

| **አመላካች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የግብር ተገማችነት** | የአርባ ዓመቱ ልምድ የተረጋጋ እና ተገማች የእሚባል ሆኖ ፤ በ10 ዓመት (2014-2024) ሶሥት ትልልቅ ማሻሻያ መደረጉ ፤ ጥርጣሬ እንዲጨምር አድርጓል። | **1** | በቅርቡ የተፈጠረው ውስብስብነት እና ተደጋጋሚ ለውጥ ጥርጣሬ ፈጥሯል። |
| **የበጀት ጉድለት ለመሙላት ገንዘብ ማተም (Monetary Financing)** | በሕገመንግሥት ደረጃ የተከለከለ ነው ፤ ብሔራዊ ባንክ የመንግሥትን ብድር እንደ አይገዛ ተከልክሏል። | **2** | የበጀት ጉድለትን ለመሙላት ገንዘብ ማተም ጠንካራ ክልከላ ነው ያለበት። |
| **ብድርን ለምርታማ ኢንቨስትመንት ማዋል (Productive Debt)** | ከኢኮነሚው አንጻር ብድሩ 38% በመሆን በጣም ዝቅተኛ ነው ፤ አጠቃቀሙም ለማሕበራዊ ዋስትና እና ለመሠረተ ልማት በአግባቡ ነው። | **2** | ብድር በጥሩ ኹኔታ ረጅም ግዜን ታሳቢ ባደረገ መልኩ በጥንቃቄ እራሱን ሊከፍል በእሚችልበት መንገድ በሥራ ላይ ይውላል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **የዋጋ ግሽበት መጠን** | ለተከታታይ አስር ዓመታት የዋጋ ግሽበት ከ5% በታች ነበር ፤ በ2022/2023 ድንገተኛ ማሻቀብ ቢፈጠርም ብሔራዊ ባንኩ ጥሩ የመቆጣጠር ሥራ ሠርቶ ወደ ልማዳዊ በታው መልሶታል። | **2** | በሐገሪቱ የእማይለዋወጥ እና ዝቅተኛ መጠን ያለው የዋጋ ግሽበት እንደ አለ ሕዝቡ ራሱ ይስማማል። |
| **የብሔራዊ ባንኩ ገለልተኝነት** | የቺሊ የብሔራዊ ባንክ ያለው ነጻነት በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የእሚታወቅ እና ወርቃማ ምሳሌ ነው። | **2** | ብሔራዊ ባንኩ የዋጋ መረጋጋትን እና የገንዘብ ስረዓቱን መረጋጋት ማረጋገጥ ዓላማው አድርጎ ይሠራል። |
| **የመገበያያ ገንዘብ ርጋታ (Currency Stability)** | የቺሊው ፔሶ ምንዛሪ በነጻ ገበያ እንዲወሰን የተንሳፈፈ (Float) ፣ በቂ የገንዘብ እንቅስቃሴ ያለው እና የተረጋጋ ነው። | **2** | ተገማች የሆነ የምንዛሪ ገበያ ነው ያለው። |
| **መንግሥት ብድር መክፈል አቅቶት በእዳ የተያዘበ ኹኔታ(Default History)** | በአለፈው 40 ዓመት መንግሥት በእዳ የተያዘበት ግዜ የለም። | **2** | በአለፈው አርባ ዓመት መንግሥት እዳውን በመክፈል ነው እሚታወቀው። |
| **የበጀት አደላደል** | በአለፈው 40 ዓመት በተገቢው መንገድ በጀቱ ሥራ ላይ ውሏል ፤ ምንም እንኳን ከ2020-2026 ትኩረትን ወደ ጤና/ጡረታ ማድረግ ቢታይም። | **1** | ማሕበራዊ መረጋጋት ለመፍጠር እንደ ጡረታ/ጤና ያሉ ማሕበራዊ ፍጆታዎች ላይ መንግሥት የድጎማ መጠኑን ስለ ጨመረ ፤ ለመሠረተ ልማት የእሚያወጣውን ወጪ ቀንሶበታል። |

**የአመላካቾቹ አማካይ: 1.75 → በቺሊ የበጀት አስተዳደር ጥበብ ልኬት: 4**

**ከአምስቱ ኹኔታዎች ምዘና አንጻር የቺሊ የውጤት ካርድ ስናወጣ ይኽን እናገኛለን ፡**

| ሐገር | ኹኔታዎች | ልኬት |
|---|---|---|
| ቺሊ | የግል ንብረት (አንኳር) | 4 |
| | የንብረት ተንቀሳቃሽነት (አጥዳፊ) | 4 |
| | የሕጉ ነጻ እና ገለልተኛነት (አንኳር) | 4 |
| | የንግድ ክፍትነት (አጥዳፊ) | 4 |
| | የበጀት አስተዳደር ጥበብ (አንኳር) | 4 |

**የምርመራ ውጤት : ቺሊ**

**ፍረጃ: ከፍተኛ ገቢ ያለው ኢከነሚ**

- **የአንኳር ኹኔታዎች ትንተና (Core Analysis):** ቺሊ በሶስቱም አንኳር ኹኔታዎች ከፍተኛውን 4 ልኬት በማግኘት ፤ የዋሽንግተን ስምምነት ("Washington Consensus") አስሩን መርሆች በመጠቀም እራሷን ከፍተኛ ገቢ (High-Income) ካላቸው ሐገራት ተርታ ማሰለፍ ችላለች። በባለፈው 40 ዓመት በአምስቱም ኹኔታዎች ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገብ እና ያንንም በማስቀጠል በመላው ላቲን አሜርካ ተወዳዳሪ የላትም።

- **የአጥዳፊ ትንተና (Accelerator Analysis):** የቺል የንግድ ክፍትነት እና የንብረት ተንቀሳቃሽነት ልኬት ደረጃዋ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ ነው። የጡረታ አስተዳደሩን ወደ ግለሰብ በማዞሯ ፤ ቺሊ ፖለቲካዊ ውጥረት በእሚኖርበት እና ኢከነሚያዊ ጫና በእሚኖርበት ወቅት እንኳን ፤ በገበያ ውስጥ በቂ የኢከነሚ ማንቀሳቀሻ ገንዘብ እንዲኖር ማድረግ ችላለች።

- **የፈጠራ ወንፊቱ ያለበት ፈተና (Innovative Sieve Filter - The Warning):** ምንም እንኳን አምስቱም ኹኔታዎች ከፍተኛውን ውጤት 4 ቢያስመዘግቡም ፤ የግል ንብረት ኹኔታ አመላካች የሆነው የውድድርገደብ( Contestability) በሐገሪቱ ያለው በውድድር ላይ የተመሠረተ የኃብት ክፍፍል ሳይሆን ኦሊጋሪክ የሆነ ገደብ ("Oligarchic Ceiling") ወይንም ጥቂት ነባር ባለኃብቶች እና የአሠራር ክፍተቶች ስትራቴጂክ በሆኑ መስኮች ውድድርን የእሚከለክሉ መሆኑን ያሳያል። በቺሊ መንግሥት የጸረ ሞኖፖሊውን (Anti-trust) ሕግ ጨከን ብሎ ከማስፈጸም ይልቅ ትሕትና ስለ እሚያበዛ ፤ ኢከነሚው የተወዳዳሪነት ማጥለያ ወንፊት ከመሆን ይልቅ የአሮጌ ኃብት ክቡር ዘበኛ የመሆን ባሕሪ አለው።(Because anti-trust enforcement has historically

been "polite" rather than "robust," the economy risks moving from a Productivity Sieve to a Wealth Vault)። ከሕጉ በአሻገር በተጨባጭ በቺሊ ያለው ኹኔታ ፤ የግል ንብረት ባለቤትነት መብት ፤ የኹሉም ዜጋ እኩል መብት ሳይሆን የጥቂት ትልልቅ ባለፃብቶች ልዩ ጥቅም (Privileges in Disguise) ፤ የሆነበትን ኹኔታ ፈጥሯል።

- **የማስጠንቀቂያ ትንበያ (The Predictive "Premonition"):** የባለፈው አምስት ዓመት አካኼድ ሲታይ በቺሊ የበጀት አስተዳደር ጥንቃቄ (Fiscal Discipline) በማሕበራዊ አለመረጋጋት ጫና ምክንያት የነበረውን ልማድ በመቀየር እየተዳከመ ነው። ለማሕበራዊ ዋስትና በግዴት የእሚመደቡት የበጀት ወጪዎች ፤ በኃይል እና በማዕድኑ መስክ ቺሊን ትልቅ ቦታ እንድትደርስ ያደረጉት የመሠረተ ልማት ወጪዎች እየቀነሱ ነው። በተጨማሪም ቺሊ ለትንንሽ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ብድር ለመስጠት ያለባትን የአሠራር ግግርነት (Administrative Sclerosis) እና በውድድርገደብ (Contestability) ጉዳይ ላይ የእሚታየውን ኦሊጋሪኪክ (Oligarchic) የሆነ ውድድርን የመከላከል ነገር ካላሻሻለች ፤ ቺሊ ከፍተኛ ገቢ ሐገር ደርጃ ውስጥ የገባች ነገር ግን ፤ ፈጠራ እና ዕድገት የሌለበት ፤ በአለችበት የገቢ ደረጃ ተቅርቅራ የቀረች ሐገር የመሆን አደጋ ተጋርጦባታል።

## 4.4 ፖላንድ

ቺሊ የላቲን አሜሪካ ወርቃማ የተቋማት አደረጃጀት ምሳሌ ከሆነች ፤ ፖላንድ ደግሞ የአውሮፓ የፈጣን ኢከነሚያዊ ዕድገት ሻምፒዮን ነች። ፖላንድ ከ1989 ጀምሮ ፦ በተከታታይ ለ30 ዓመታት በማደግ እና ኋላ ቀር የሆነ የሶቭየት ሳተላይት ከሆነ ኢከነሚ ከመሆን ወደ ከፍተኛ ገቢ (High-income) ያለው የአንድ ትሪልዮን ዶላር (Trillion-dollar economy) ኢከነሚ በመቀየር ፤ ብዙ ሐገራት የእሚመኙትን እና ማሳካት ያልቻሉትን ዓይነት ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አሳክታለች።

ከ2ኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ፤ በፖላንድ የግል ንብረት ባለቤትነት ትዝታውን እንኳን ማጥፋት ችሎ ነበር። የወቅቱ የኮምኒስት መንግሥት የግል ኢንደስትሪዎችን በመውረስ የመንግሥት ንብረት በማድረግ እና የእርሻ መሬት ደግሞ የገበሬ ማሕበር (Collectivize) በማድረግ የግል ንብረትን አጥፍቶ ነበር።

ፖላንድ የሶቭየት ሕብረት ሳተላይት ሐገር (Satellite state) ስለ ነበረች ፤ ምንም እንኳን በወረቀት ላይ ነጻ እና ሉዓላዊ ሐገር ብትሆንም ፤ የእራሷ ተቋማት እና መንግሥት ኖሯት ፤ በተግባር ግን ፦ ኢከነሚያዊ እና ወታደራዊ ውሳኔዎቿ በሞስኮ ጥብቅ ቁጥጥር ይደረግባቸው ነበር። ስለ እዚኽ ፖላንድ በሶቭየቱ ዘመን በእምትገኝበት የፖለቲካ ኹኔታ ፤ የሶቭየት ሪፐብሊክ (Soviet republic) ከእሚባሉት እና እንደ ዩክሬን እና ካዛክስታን (Such as Ukraine or Kazakhstan) ካሉት እና በሕገመንግሥት ደረጃ የሶቭየት ሕብረት አባል ከሆኑ ሐገራት በተለየ ፤ ፖላንድ በሕግ ከሶቭየት ዩንየኑ ውጭ የሆነች እራሷን የቻለች ሐገር ነበረች።

ሆኖም ፤ ፖላንድን የእሚገዛው የኮምኒስት ፓርቲ ፤ ለሶቭየቱ መመሪያ ተገዢ የነበረ እና የውጭ ፖሊሲው ከሞስኮ ፖሊሲ ጋር አብሮ የእሚዘወር እና ኢከነሚውም የጋራ የኮምኒዝም ኢከነሚ ከእሚባለው

ኮምኮን (Comecon) ስረዓት ጋር የተዋኸደ ነበር። ይኽም የሰቭየት ሕብረቱ (The Soviet Union) ፤ ፖላንድን በቀጥታ ሳይጠቀልል በተዘዋዋሪ በተፅዕኖው ስር እንድትሆን ማድረግ አስችሎታል።

ስለ እዚኽ ፦ በሶቭየት ዘመን ከላይ ስትታይ ፖላንድ ሉዓላዊት ሐገር ትመስላለች ፤ ሆኖም ሉዓላዊነቷ በጣም የተወሰነ በመሆኑ ፤ እንደ ሌሎቹ የምስራቁ ጎራ (Eastern Bloc) የእሚባሉት ሐገራት ዓይነት የይስሙላ ሉዓላዊነት ነው የነበራት።

ሆኖም ከሌላው የሶቭየት ብሎክ (Soviet Bloc) ለየት ባለ መልኩ ፤ ፖላንድ የሞስኮውን ተፅኖ የመቃወም ዝንባሌ ነበራት። ከእዚኽም የተነሳ ፤ ከእላይ በተገለጸው መልኩ በሶቭየት ተፅዕኖ ሥር ብትሆንም ፤ 70% የእሚሆነው የሐገሪቱ የግብርና መሬት የግል እንደ ሆነ ቀጥሎ ነበር። ይኽም የንብረት ባለቤትነት በተወሰነ ደረጃ በፖላንድ እንደ ተከበረ እንዲቀጥል አድርጎ ነበር።

በእዚኽ መልክ የተዋቀረችው ፖላንድ ፤ የጌሪክ (the Gierek era) ዘመን በእሚባለው ከ1970 እስከ 1980 በቆየው ግዜ ፤ ዕድገትን በብድር ለመግዛት አስባ ነበር። ሆኖም ፤ የብድርን ወለድ መጠን እና የኢንቨስትመንት አዋጭነት የእሚመዝን ገበያ ስለ አልነበረ ፤ መንግሥት የተበደረውን ብድር አክሳሪ የሆኑ ትላልቅ ኢንደስትሪዎች ላይ አውሎ አባከነው። በ1970ዎቹ ውስጥ የጀመረው ፤ ይኼ ዕድገትን በብድር የመግዛት አካኼድ ፤ 1980 ላይ ፤ የግሽበት መጠኑን 344% በማድረስ ወደ አውሎግሽበት (hyperinflation) በመለወጥ የሐገሪቱን ሱቆች ባዶ አድርጎ ብዙ ችግር ፈጠረ።

ፖላንዶቹ በእዚኽ ዓይነት አውሎግሽበት (Hyperinflation) መላ ኢንደስትሪያቸው በክስረት ሊያፈራርስ የመሆኑን አደጋ ሲመለከቱ ፤ ሌሲክ ባልሴሮዊች (Leszek Balcerowicz) የተባለው የገንዘብ ሚንስትራቸው ባስተዋወቀው የባልሴሮዊች ዕቅድ  (Balcerowicz Plan) ፤ አውሎግሽበቱን (hyperinflation) እና የገንዘቡን መዋዠቅ በማረጋጋት ኢኮኖሚውን ሊበራላይዝ ለማድረግ ተነሱ በእዚኽም ፦ ኢኮኖሚው በነጻ ገበያ እንዲመራ ፣ የመንግሥት ድጎማ እንዲቀንስ እና የንግድ ክፍትነት እንዲጨምር አደረጉ። ገበያው ሳይሆን መንግሥት እንደ አሻው ከእሚሆንበት አካኼድ ለመውጣት እና በገበያ ለመመራት ፤ ፖላንድ ከጎረቤቶቿ በጣም የተለየ እና ፈጣን የሆነ እርምጃ ነበር የወሰደችው።

የአውሮፓን ሕብረት በአባልነት መቀላቀሏ ደግሞ ፤ የፖላንድን የሕግ እኩልነት እና የባላይነት በአንድ ግዜ ከፍተኛው ደረጃ ላይ አደረሰው። እንዲያውም ፖላንድ ፤ ሐገር በቀል ማሻሻያ በእሚል አጉል መንደፋደፍ ሳይሆን ፤  የአውሮፓ ሕብረት አባል ለመሆን የእሚያስፈልጋትን ተቋማዊ ማሻሻያ በማድረግ ነው ፤ ኋላ ቀር የሆነ ፤ የዕዝ ኢኮኖሚ ተቋም ሐገርነት ፤ በአንድ ግዜ የዘመናዊ እና የነጻ ገበያ ተቋማዊ ቅርፅ ያለው ኢኮኖሚ መሆን ያቻለችው ማለት ይችላል።

የአውሮፓን የኢኮኖሚ ተቋም ሕግ ቀጥታ በመገልበጥ (Copy-paste) ነው የኢኮኖሚ ተቋም ደረጃዋን በአንድ ግዜ ያሻሻለችው።

ይኸም ፖላንድን በአውሮፓ ውስጥ ፡- የአውሮፓ ደረጃ ያለው የንብረት ዋስትና እና የሕግ ስረዓት ያለው ነገር ግን በጣም ርካሽ ዋጋ ያለው ጉልበት ማቅረብ የእሚችል ፤ ልዩ ጥቅም የእምትሰጥ ኢከነሚ አድርጎ ፤ ልዩ የተወዳዳሪነት ጥቅም ሰጣት።

ይኸም ፖላንድን የአውሮፓ ፋብሪካ (Factory of Europe) አደረጋት ፤ ኢከነሚያዋን በከፍተኛ ደረጃ ከጀርመን እና ከፈረንሳይ ኢኮኖሚ ጋር እንድታስተሳስር እና ብቸኛዋ የ2008ቱን ሪሴሽን (Recession) ወይንም የኢከነሚ መቀዛቀዝ ያለምንም ችግር ያለፈች የአውሮፓ ሕብረት እንድትሆን አደረጋት።

ምንም እንኳን የሩቅ ምስራቅ ነብሮች የእሚባሉት እንደ ደቡብ ኮርያ እና ታይዋን ያሉት ሐገራት ዕድገት ቢሆንም በባለፈው 30 ዓመት ባስመዘገበው ዕድገት ብዙ እሚነገርለት ፤ በ30 ዓመት ከፍተኛ መጠን ያለው እና የዕድገቱም ጥራት ከፍተኛ በመሆን የፖላንዱ ኢከነሚ ዕድገት ይበልጣል።

በ30 ዓመት ብቻ ፖላንድ ፤ እንደ ቻይና የሕዝብ ቁጥር በመቀነስ ኢከነሚዬን አሳድጋለው በእሚል ዴሞግራፊክ ዴቭደንዷን (demographic "Dividend") ሳትሰዋ እና አምባገነናዊ በሆነ መልኩ ገበያ ውስጥ ጣልቃ በመግባት ገበያዋን ሳታዛባ ፤ የከሰረ ኋላቀር ሳተላይት (Satellite) ሐገር ከመሆን ከፍተኛ ገቢ (High-income) ያለው ሐገር መሆን ችላለች። በነፍስ ወከፍ ገበያ ደርጃ ብናነጻጽራቸው ዛሬ ላይ የፖላንድ የነፍስ ወከፍ አማካይ ገቢ 30 ሺ ዶላር በላይ ሲሆን የቻይና ደግሞ 14 ሺ ዶላር ነው።

ፖላንድ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት ግንባታን አስቀጥላ ፤ የከፍተኛ ገቢ ሐገራት ተርታ መመደብ ችላለች ፤ ቻይና ዕድገት ብታስመዘግብም ሐገሯን ዴሞክራሲያዊነት እና ተጠያቂነት ያለበት ለማድረግ ወደ ፊት ካልሆነ አሁን አምባገነን እንደ ሆነች ነው።

በእርግጥ በቅርቡ ፤ ፖላንድ ሉዓላዊነትን ማስከበር በእሚል ከአውሮፓ ሕብረት ጋር በሕግ ጉዳይ የተወሰኑ ቅራኔዎች እያስተናገደች ነው። እንደገናም የጂዖግራፊ እርግማን (The Curse of Geography) በእሚባለው ምክንያት ፤ ከራሺያ ሊቃጣባት የእሚችለውን ወታደራዊ ጥቃት ለመከላከል በእሚል ከበጀት አስተዳደር አንጻር ከፍተኛ መጠን (የአመታዊ ኢከነሚያዊ ምርቷን 5% ገደማ) ለመከላከያ እና ለኒውክለር ኃይል ማመንጫ ግንባታ እያዋለች መሆኗ ፤ በበጀቷ ላይ ጫና በመፍጠር የበጀት አስተዳደር (Fiscal Discipline) ላይ ጫና እየፈጠረ ነው።

ይኸን መልክ ያለው የኢከነሚ ታሪክ ያላትን ፖላንድን በመመርመሪያው ማሽን ውስጥ ስናስገባት ፤ የእሚከተለውን ዓይነት ውጤት ነው የእምናገኘው ፡-

**1. የግል ንብረት (አንኳር)**

| **አመላካች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **1. ባለቤትነት** | አፓርታማ እና የንግድ ድርጅቶችን በግል ንብረትነት | **1 (መካከለኛ)** | ከፍተኛ ደረጃ ያለው የከተማ/የንግድ ንብረት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ማግኘት በስፋት አለ። ሆኖም ስትራቴጂክ ከልካይ ግድግዳዎች ግን አሉ። በ2026 የመንግሥት እርሻዎች እስከ 2036 ድረስ ለግል ባለኃብት በሽያጭ እንደ አይተላለፉ አግዳለች። ምንም እንኳን የአውሮፓ ሕብረት አባል ለሆኑ ሐገራት እንደ ፖላንዳዊ ቤት መግዛት እንዲችሉ ቢፈቀድም ፤ መሬት ያለው ቤት ለመግዛት ከአውሮፓ ሕብረት ውጭ የሆኑ የውጭ ዜጎች ከ3 እስከ 6 ወር የእሚወስድ የፈቃድ አሰጣጥ ኺደት መኖሩ ልክ እንደ አስተዳደራዊ ኢንቨስትመንት ክልከላ ሊታይ ይችላል። | | ባለቤትነት መብት የእሚያስመዘግበውን ድል ፤ ብዙ አስርት አመታት በሆነው የገጠር መሬት ላይ ያለ ገደብ እና የአውሮፓ አባላት ላልሆኑ ያለው አስተዳደራዊ ክልከላ ያጠፋዋል። |
| **2. ውርስ** | ሕገመንግሥቱ እና ፍትሓብሔሩ ንብረት ሲወረስ ተገቢ ክፍያ ይከፈል ይላል። ከ2015 እስከ 2024 በአፈጻጸም ላይ ብዙ ውጥረት ቢታይም ፤ በ2026 የአውሮፓው ሕግ የበላይነት ነገሩን አረጋግቶታል። ለምሳሌ ፦ ከብራዚል ጋር ሲነጻጸር፤ በፖላንድ ንብረት ሲወረስ የእሚከፈለው ክፍያ ፈጣን እና ተመጣጣኝ ነው። | **2 (ከፍተኛ)** | መንግሥት ድንገት ንብረቴን ይወርሰኛል የእሚል ስጋት በጣም ዝቅተኛ ነው ፤ ንብረት ለሕዝብ አገልግሎት ተብሎ ሲወረስም በፍርድ ቤት ለመከራከር አመቺ ነው ፤ ፍርድቤቶችም በነጻነት ነው የእሚወስኑት። |
| **3. የውድድርገደብ (Contestability)** | ፖላንድ በጣም ጠንካራ የሆነ የጸረ ሞኖፖሊ (Antitrust) ተቆጣጣሪ አላት። በ2026 ዓለም ዓቀፋዊ በሆኑት | **1 (መካከለኛ)** | እንደ ዲጅታል እና ችርቻሮው መስክ የተረጋገጠው ተወዳዳሪነት አሮጌው በእሚባለው |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | እንደ ዜለንዶ ፣ ተሙ (Zalando, Temu) ላይ ዋጋ ላይ ጣልቃ ገባችሁ በእሚል ትልቅ ቅጣት በይኗል። ሆኖም ኢኮነሚው ባለ ኹለት መልክ ነው ፤ የጅምላ/ችርቻሮው እንዲኹም የዲጅታል መስኩ በጣም ውድድር ያለበት እና የፈጠራ ወንፊቱ የእሚሠራበት ሲሆን ፤ ስትራቴጂክ የሆኑት ማዕድን እና የኃይል መስኮች ግን ከውድድር መንግስታዊ ከለላ የእሚደረግላቸው ደካማ መስኮች እና ፈጠራን የእማያበረታቱ ናቸው። | | የኢከነሚ መስክ ባለው ክልከላ ይጣፋል። |
| **የሠራተኛ ነጻነት (Labor Freedom)** | በ2026 በተደረገው ማሻሻያ ፤ ዝቅተኛውን የደሞዝ ክፍያ 4,806 የፖላንድ ገንዘብ አደርጉት አብረውም የአውሮፓ ሕብረት የደሞዝ ግልጸኝነት የእሚለውን ሕግ ተገበሩ። ሆኖም በፖላንድ የሠራተኛ እጥረት እና ቅጥር ለማቋረጥ ጥብቅ የሆነ የቅድመ ማስጠንቀቂያ የመሰጠት ግዴታ መኖሩ ችግር ፈጥሯል ። ከእዚኽም የተነሳ ከፍተኛ መጠን ያለው ሠራተኛ በኮንትራት እንጂ በቋሚ አይቀጠረም ፤ ለማባረር እንዲቀል። | **1 (መካከለኛ)** | በፖላንድ የቅጥር ገበያው በአንጻራዊነት ነጻ ቢሆንም እና ሠራተኛም ብዙ እንቅስቃሴ ቢኖረውም ፤ ለሠራተኛ ከደሞዝ ውጪ መቅረብ ያለባቸው ጥቅማጥቅሞች እና የሥራ/ሕይወት ሚዛን የእሚለውን የአውሮፓ ሕብረት ሕግ ለመተግበር መነሳታቸው ፤ የቅጥር ገበያው ተገቢውን ሰው ተገቢው ቦታ እንደ አያደርግ አሎኬትቭ ኢንኢፊሽንሲ (Allocative Inefficiency) ፈጥሯል። |

**የአመላካቾቹ አማካይ : 1.25 → በፖላንድ የግል ንብረት ባለቤትነት ልኬት : 3**

## 2. የንብረት ተንቀሳቃሽነት (አጥዳፊ)

| አመላካች | የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም | ልኬት (0–2) | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| **የውጭ ዜጎች ባለቤትነት** | በመካከለኛው እና ምስራቃዊው አውሮፓ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በመሳብ ቀዳሚዋ ሐገር ነች ፖላንድ። የፖላንድ ኢኮኖሚ ከጀርመን/አውሮፓ የምርት ሰንሰለት (Supply chains) ጋር በከፍተኛ ደረጃ የተሳሰረ ኢከነሚ ነው። | 2 | አብዛኛው ዘርፍ ላይ ፤ ሙሉ ለሙሉ ሊባል የእሚችል የውጭ ካፒታል ኢንቨስት ማድረግ እንዲችል ክፍት ነው። |
| **የመሬት ገበያ** | በጠቅላላው ጥሩ መጠን ያለው ገንዘብ የእሚንቀሳቀስበት (Generally liquid) የመሬት ገበያ ነው ያለው። ሆኖም በቅርቡ አዲስ የግብርና መሬት ገዢዎች በግብርና ትምሕርት ያላቸው ፣ ቢያንስ ለ5 ዓመት ያረሱ ፣ መሬቱን ቢያንስ ለተከታዩ 10 ዓመት ለማረስ ቃል የገቡ መሆን አለባቸው የእሚል መመሪያ ወጥቷል ፣ የውጭ ዜጎች ከሆኑ ደግሞ ቅድመ ኹኔታው ትንሽ ከፍ ይላል። | 1 | የግብርና መሬትን ለማንኛውም ሰው መሸጥ አይቻልም ፤ ገዢው እንዲያሟላቸው እሚፈለጉ መሥፈርቶች አሉ። |
| **የካፒታል ቁጥጥር (Capital Controls)** | በፖላንድ ዘውቲ (Zloty (PLN)) የእሚባለው ገንዘባቸው የምንዛሪ መጠኑ ምንም ቁጥጥር ሳይደረገብት በገበያ የእሚወሰን ነው ፤ ገንዘብ ለማስገባት ለማስወጣትም ምንም ዓይነት ቁጥጥር የለም። | 2 | ወደ ባለ አንድ ትሪሊዮኑ የፖላንድ ኢከነሚ ካፒታል ያለመንም ችግር መግባትም መውጣትም ይችላል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **የስቶክ ገበያው መጠን (Stock Market Size)** | የዋርሶው ስቶክ ኤክስቼንጅ (Warsaw Stock Exchange - WSE) ፤ የፖለንድ ብቻ ሳይሆን የአከባቢው ሐገር ዜጎችም ኢንቨስት እሚያደርጉበት ነው ሆኖም ከኢከነሚው አመታዊ ምርት አንጻር 20% በመሆን መጠኑ ትንሽ ነው(but market cap/GDP is low ~20%). | **1** | የሐገሪቱ ኢኮኖሚ የእሚፈልገውን ገንዘብ ለማቅረብ በቂ ፤ ከሌሎች የአውሮፓ ሐገራት አንጻር ግን ትንሽ ነው። |
| **በቀላሉ ንግድ መጀመር እና መዝጋት ይቻላል** | በጣም ቀልጣፋ የሆነ በኮምፒውተር የታገዘ እና የንግድ ፈቃድ በአንድ ቀን (Business in One Day) ዓይነት አሠራር አለ። | **2** | አዲስ ነጋዴዎች ወደ ንግድ ለመግባት ይኽ ነው የእሚባል ችግር የለባቸውም። |
| **በቀላሉ ብድር ማግኘት** | ዘመናዊ ሊባሉ የእሚችሉ ጥሩ የገንዘብ አቅም ያላቸው ባንኮች አሉ ሆኖም ባንኮች የመንግሥት የግምጃ ቤት ሰነድ ወደ መግዛት ያመዝናሉ ለአነስተኛ እና መለስተኛ የንግድ ድርጅቶች ብድር ከመስጠት ይልቅ። | **1** | ያለው ገንዘብ በአብዛኛው ለመንግሥት በብድር ስለ እሚሰጥ ፤ አነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች ብድር ለማግኘት ይቸገራሉ። ይኽ ግን መንግሥት አስገደዶ ቦንድ ስለ እሚያስገዛ አይደለም ይልቁንም ባንኮቹ የመንግሥትን በንድ መግዛት ስለ እሚመርጡ ነው። |

**የአመለካቾቹ አማካይ: 1.50 → በፖላንድ የንብረት ተንቀሳቃሽነት ልኬት: 4**

### 3. የሕጉ ገለልተኛ እና ነጻነት (አንኳር)

| አመላካቾቹ | የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም | ልኬት (0–2) | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|

| | | | |
|---|---|---|---|
| **የዳኝነት ነጻነት** | **አሳሳቢ የሆነ ከ** 2015–2024 ባለው ግዜ ውስጥ የታየ የዳኝነት ነጻነትን ጥያቄ ውስጥ የማስገባት ነገር ቢኖርም ፤ ባለፈው 40 ዓመት የዳኝነት ነጻነት ከፍተኛ ነበር። የኮምኒዝም ዘመኑ ትዝታ ያገረሸ ይመስላል። | **1** | የዳኝነት ማሻሻያው በብዙዎች ዘንድ በዳኝነት ነጻነት ላይ ያላቸውን ዕምነት እንዲቀንስ አደርጓል። አንድ አንድ ጥናቶች እንደ እሚያሳዩት ~24% ነጋዴዎች ብቻ በፍርድ ቤት ይተማመናሉ። |
| **ሙስና** | በትንንሽ ጉዳዮች በጣም ዝቅተኛ ነው ሆኖም በመንግሥት ግዢ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ውስጥ በእሚሰጡ ሹመቶች ላይ ግን ጥርጣሬ አለ። | **1** | ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል (Transparency International) ከ2012 በኋላ ዓየተውት በእማያውቁት መልኩ የፖላንድን ሙስና ደረጃ ከፍ አድርጎታል። |
| **የውል ተፈጻሚነት** | አስተማማኝ ነው ግን በጣም ቀርፋፋ ነው። የንግድ ክርክሮች ዓመታት ሊወስዱ ይችላሉ። | **1** | የተንዛዙ የፍርድ ቤት ጉዳይ አፈጻጸሞች የግዜ ግብር ያስከፍላሉ። |
| **በሕግ ፊት እኩልነት** | ሕጉ በጥቅላላው እኩልነትን ያከብራል ሆኖም ባለፈው አምስት አመት ግን አንድ አንድ ፖለቲከኞች ካለተጠያቂነት ሕጉን መሻር እሚችሉ እየመሰለ ነው። | **1** | ከፍተኛ ፋይዳ (High-level) ጉዳዮች አንድ አንድ ግዜ ፖለቲካዊ ከለላ ሊያገኙ ይችላሉ። |
| **የፖለቲካ ጣልቃገብነት** | የዳኝነት ስረዓቱ ብሔራዊ መማክርት የእሚባለው መመማክርት ውስጥ ባለፈው 5 ዓመት ፖለቲካው ጣልቃ ሲገባ ይታያል። | **0** | በሐገሪቱ ፕሬዝደንት እና ፓርላማ መካከል ማን ዳኛ ሆኖ ይሾም በእሚል ጠንካራ ክርክር ሲደረግ ይታያል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **የፖሊስ አስተማማኝነት** | የንብረት መብት ለመከላከል እና መሠረታዊ ማሕበራዊ መረጋጋትን ለማረጋገጥ አስተማማኝ ነው። | **2** | በዜጋ ደረጃ መሠረታዊው የሕግ የበላይነት ጠንካራ አፈጻጸም አለው። |

**የአመላካቾቹ አማካይ : 1.00 → በፖላንድ የሕግ የበላይነት ያለው ልኬት: 3**

**4. የንግድ ክፍትነት (አጥዳፊ)**

| **አመላካች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የታሪፍ/ቀረጥ መጠን** | የአውሮፓው ሕብረት ከሕብረቱ ውጭ ላሉ ሐገራት የሚጥለው ቀረጥ ነው ያለው። በአውሮፓ ሕብረት ውስጥ ላሉ ሐገራት ቀረጡ 0% ነው። | **2** | ፖላንድ አብዛኛውን ንግድ በምታደርግበት በአውሮፓ ውስጥ ፍጹም የንግድ ነጻነት ነው ያለው ፤ ምንም ቀረጥ የሌለበት። |
| **ከታሪፍ ውጭ የሆኑ ክልከላዎች** | የአውሮፓ ሕግ አክባሪ በመሆኑ ፤ በጣም የተደራጀ እና ተገማች የሆነ ነው። | **2** | የቁጥጥር ክልከላዎች ተገማች እና ከዓለም ዓቀፍ ልማዱ ጋር የሚስማሙ ናቸው። |
| **የገቢ/ወጪ ንግድ ከኢኮኖሚው አንጻር (Trade % of GDP)** | ከዓለም ዓቀፍ ገበያ ጋር በጣም የተሳሰረ ነው ፤ የገቢ/ወጪ ንግዱ ከኢኮኖሚው አመታዊ ምርት በመቶ እጅ በላይ ይበልጣል(exceed 100% of GDP) | **2** | በአውሮፓ ውስጥ ካሉ በከፍተኛ ደረጃ በገቢ እና በወጪ ንግድ ላይ ከሚደገፉ ኢኮኖሚዎች ይመደባል። |
| **የገቢ/ወጪ ንግድ ክልከላዎች** | በጣም ጥቂት ናቸው። ክልከላዎቹ ወታደራዊ እና ሠላማዊ አግልግሎት | **2** | ሸቀጦች በውስን አስተዳደራዊ ገደብ ብቻ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | (dual-use) እና ከዩክሬን የእሚመጡ በጣም ርካሽ የግብርና ምርቶች ላይ እና መሰል ገደቦች ላይ የተወሰነ ነው። | | በነጻ በገበያ ውስጥ ይንሸራሸራሉ። |
| **የጉምሩክ ቆይታ** | ዓለም ዓቀፍ ደረጃውን የጠበቀ (World-class) በኮምፒውተር የታገዘ የጉምሩክ አሠራር እና ከአውሮፓ ሕብረት የውስጥ ድንበር አውቶማቲክ ቁጥጥር ጋር አለ። | **2** | ፈጣን እና ተገማች ነው። |
| **የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት እና ሕግ አክባሪነት (WTO Compliance)** | የድርጅቱ አባል እና በአውሮፓ ሕብረት አማካኝነት የሕጉ አክባሪ | **2** | ጠንካራ የሆነ ከተለያዩ ሐገራት ጋር በነጻ ንግድ ስምምነት መሠረት የእሚደረግ የወጪ እና የገቢ ንግድ አለ። |

**የአመለካቾች አማካይ : 2.00 → በፖላንድ የንግድ ክፍትነት ልኬት: 4**

## 5. የበጀት አስተዳደር ጥበብ (Fiscal Discipline - Stabilizer)

| አመላካች | የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም | ልኬት (0–2) | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| **የታክስ ሕጉ ተገማችነት** | ውስብስብ እና በእየ ምርጫው ድምጽ ለማግኘት እንዲኽ አድርጌ ቀይረዋለኹ የእሚል አጉል ተስፋ የበዛበት ነው። | **1** | የማሕበራዊ ታክስ ፖሊሲው ተደጋጋሚ ለውጥ የእሚታይበት እና ለንግድ ድርጅቶች ለመገመት አስቸጋሪ ነው። |
| **የበጀት ጉድለት ለመሙላት ገንዘብ ማተም** | የበጀት ጉድለት ለመሙላት ገንዘብ ማተም በሕግ ክልክል ነው ሆኖም | **1** | የፖላንድ ልማት ባንክ እና የፖላንድ የልማት ፈንድ የእሚባሉ ኹለት ባንኮችን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **(Monetary Financing)** | የተወሰነው የመንግሥት ገቢ ግዴታ ሊውልባቸው ይገባል የሚባሉ እና ከገቢው ተቀንሶ የሚፈጠሩ ፈንዶች አሉ (Extra-budgetary funds)። | | በመጠቀም ፤ መንግሥት የበጀት ጉድለቱን ይደብቃል። እነ እዚኽ ኹለቱ ከበጀት ጋር ስለ እማይከተቱ ፤ መንግሥት ገንዘብ እያተመ ፦ የኮቪድ ድጎማ ዓይነት ድጎማ ፣ የመብራት ድጎማ እና የመሠረተ ልማት ማስፋፊያ ያደርጋል ፤ ብር በማተም። |
| **ብድርን አትራፊ መስክ ላይ ማዋል (Productive Debt)** | የመንግሥት ዕዳ ከኢኮነሚው አመታዊ ምርት አንጻር ከፍተኛ ዕድገት እየ ዐሳየ በ2027 የአመታዊ ምርቱ ~69% ይደረሳል ተብሎ ይገመታል ፤ ዕዳውም በአብዛኛው የጦር አቅምን ለመገንበት እና ለማሕብራዊ ዋስትና ወይንም በጠቅላላ ከምርታመነት ይልቅ ለፍጆታ ይውላል። | **1** | የመንግሥት የበጀት ትኩረት ፤ የመሠረተ ልማት ከማስፋፋት ይልቅ የፍጆታ እና መከላከያ ግንባታ ላይ ወደ ማተኮር ተቀይሯል። |
| **የዋጋ ግሽበት** | ፖላንድ የእሚዋዥቅ የግሽበት ታሪክ ነው ያላት ፦ ከ1989 በኋላ አውሎግሽበት (Hyperinflation) ነበር ፤ በ2000ዎቹ መረጋጋት ነበር ፤ በ2022/2023 እንደ ገና ተነስቶ 16% አከባቢ ደርሶ ነበር ፤ አሁን ተመልሶ 3% ቢሆንም። | **1** | በጥቅላላው የዋጋ ግሽበቱ የተረጋጋ ነው ፤ ሆኖም ከኢኮነሚ ዕድገቱ ጋር አብሮ የደመዝ እድገት እንዲደረግ በሠራተኛው ግፊት ስለ አለ እና ያ ደግሞ ከምርታመነቱ ጋር አብሮ እሚኼድ ስለ አልሆነ ፤ የዋጋ ግሽበት አደጋ ይከስታል። |
| **የብሔራዊ ባንክ ገለልተኛነት** | የፖላንድ ብሔራዊ ባንክ ነጻ እና ገለልተኛ ነው | **1** | ፖለቲከኞች የብሔራዊ ባንኩ ገዢ ገለልተኛ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ሆኖም አሰልቺ የመንግሥት ቁጥጥር አለበት። | | ነው ወይንስ አይደለም በእሚል ብዙ ይከራከራሉ፣ |
| **የመገበያያ ገንዘቡ ርጋታ (Currency Stability** | ዞውቲ (Zloty (PLN)) ምንዛሪው በገበያ ስለ እሚወሰን ፤ ለምሳሌ ፦ የነዳጅ ዋጋ ሲወደድ ብሩ ይዳከማል በእዚያም ኤክስፖርት ያበረታታል ፤ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ሲበዛ ብሩ ይጠነክርና ከውጭ እሚገባው ካፒታል ገበያ እንደ አያዛባ ያደርጋል ፤ በእዚኽም ኺደት ገንዘቡ ፤ እንደ መኪና አሞርዛተር (Shock absorber) መናጋትን የማርገብ ሥራ ይሠራል። | **2** | አስተማማኝ የሆነ የገንዘብ ርጋታ ነው ያለው። |
| **መንግሥት በዕዳ የመያዝ ታሪኩ** | ከሶቭየት ከተለዩ በኋላ በእዳ ተይዘው አያውቁም። ጠንካራ ብድር የመክፈል ታሪክ አላቸው። | **2** | ቋሚነት ያለው የመንግሥትን ዕዳ የመክፈል ልምድ አለ። |
| **የበጀት አደላደል** | ፖላንድ ፦ በልጅ ከ800 የሐገራቸውን ብር በላይ መደጎም ፤ ለጡረተኞች 13ኛ/14ኛ ደሞዝ በእሚል በ12ቱ የዓመቱ ወር ከእሚከፈላቸው ውጭ የተለያዩ ድጎማዎች በማድረግ ብዙ ወጪ ስለ እሚያወጡ ፤ በጀታቸው ላይ ከፍተኛ ጫና አለ። ይኽን የእሚያደርጉት ፦ ሰው ገንዘብ እንዲያጠፋ እና ዲማንድ እንዲፈጥር እንዲሁም | **0** | ይኼ አስገዳጅ የሆነ ድጎማ ፤ በአውሮፓ ውስጥ ትልቁ የእሚባለውን የበጀት ጉድለት ፤ የሐገሪቱን አመታዊ ምርት 7 በመቶ (~7% of GDP) እንዲሆን አድርጓል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | መውለድ እንዲበረታታ እና የሕዝብ ቁጥር እንዲጨምር ነው። | | |

**የአመለካቾቹ አማካይ: 1.12 → በፖላንድ የበጀት አስተዳደር ጥራት ደረጃ : 3**

**በአለፈው 40 አፈጻጸሙ ሲመዘን ፖላንድ ከ5 ኹኔታዎች አንጻር የእሚኖራት የውጤት ሪፖርት ከእዚኽ በታች ያለውን ይመስላል፦**

| **ሐገር** | **ኹኔታዎች** | **ልኬት** |
|---|---|---|
| **ፖላንድ** | **የግልን ንብረት ባለቤትነት (አንኳር)** | **3** |
| | **የንብረት ተንቀሳቃሽነት (አጥዳፊ)** | **4** |
| | **የሕግ ነጻ እና ገለለተኛነት (አንኳር)** | **3** |
| | **የንግድ ክፍትነት (አጥዳፊ)** | **4** |
| | **የበጀት አስተዳደር ጥበብ (አንኳር)** | **3** |

**የምርመራ ውጤት: ፖላንድ**

**ፍረጃ: ከፍተኛ ገቢ ያለው ኢኮኖሚ**

- **የአንኳር ኹኔታዎች ትንተና (Core Analysis):** ምንም እንኳን የኢከነሚ ተቋሞቿ ቅይጥ (ዘመናዊ እና ኋላቀር) ይዘት ቢኖራቸውም ፤ ፖላንድ ከፍተኛ ገቢ ያለው ሐገር ደረጃ ውስጥ መግባት ችላለች። አጥዳፊ የሆኑት የንግድ ክፍትነት እና የንብረት ተንቀሳቃሽነት ኹኔታዎቿ የአውሮፓን ሕብረት በመቀላቀሏ ምክንያት ከፍተኛው 4 ደረጃ ላይ ደርሰዋል። ሆኖም አንኳር የሆኑት ፦ የንብረት ባለቤትነት ፣ የሕግ የበላይነት እና የበጀት አስተዳደር 3 ሆነዋል ፤ ይኽም ባብዛኛው ከ2015 በኋላ በፖላንድ እየተስተዋለ የመጣውን የተቋማት ደረጃ መሸርሸር ውጤት ነው።

- **በጣም እያደገ የመጣ ለፍጆታ የእሚውል ድጎማ የኢኮኖሚው ዕድገት ልጓም እየሆነ ነው:** ፖላንድ እንደ ብራዚል አቻዋ ፤ ፍጆታ ላይ ትኩረት በማብዛት ፤ የሐገሪቱ በእድገት እንደ አይነጉድ የእሚይዝ የፍጆታ መልህቅ ( "Consumption Anchor") እየፈጠረች ነው። መንግሥት በእየ ዓመቱ የእሚፈጥረውን የሐገሪቱ አመታዊ ምርት 7% የእሚሆነው የበጀት ጉድለት ፤ ልጅ መውለድን ለማበረታታ በእሚል ለወላጅ እናቶች በልጅ 800 የፖላንድ ገንዘብ የእሚሰጥበት እና መሰል ድጎማዎች ይበልጣሉ ፤ ለጥናት እና ምርምር ወይንም ለመሠረተ ልማት ከእሚጠቀምበት ይልቅ። ይኽም ዓይነቱ ፍጆታ ላይ ያተኮረ የበጅት አጠቃቀም ፤ በእሚቀጥለው 5 ዓመት በፖላንድ የምርታመነት መዳከም ይክሰታል ለእሚለው ግምት መነሻ ሆኗል።

- **የፈጠራ ማጥለያው ውንፊት (Innovative Sieve Filter):** ፖላንድ ቀስ በቀስ ወደ አረጀ ኃብት ግምጃቤትነት (Wealth Vault) እየተቀየረ ያለ የፈጠራ መራቢያ( Innovation Pool ) የሆነች ሐገር ነች። መንግሥት የኮምኒዝም ዘመን አባዜው ተነስቶበት መልሶ በባንኩ እና በኃይል ማመንጫት ዘርፉ በባለቤትነት መሳተፍ ስለ ጀመረ ፤ የግል የፈጠራ ባለቤቶች (Private innovators) እንዲያንሠራሩ ያደርግ የነበረው ምህዳር እየተቀየረ ነው።

- **የማስጠንቀቂያው ምልክት (The "Ominous" Signal):** የምርመራ ማሽኑ ፤ በፖላንድ የሕጉ ነጻ እና ገለልተኛነት እያሳየ ያለው መዳከም ትልቁ ስጋት ነው ብሎ ያመለክታል። ፖላንድ ከአውሮፓ ሕብረት የዳኝነት ነጻነት ጋር በእሚቃረን መልኩ የዳኞችን ሹመት በፖለቲካ ለመቆጣጠር የእሚፈልግ ዓይነት አካኼድ በመከተል ፤ ከአውሮፓ ሕብረት ልምድ የመገንጠል ዝንባሌ እያሳየች ነው ፤ በእዚኽም የብዙ ሚልየን ዶላር ቅጣት ደርሶባታል ፤ ድምጽ የእማትሰጥ አባል ከመደረግ ያዳናትም የሐንጋሪ አለመስማማት ነው። በእዚኽም አካኼድ የውጭ ሐገር ኢንቨስተሮች በፖላንድ የሕግ ስረዓቱ ለኹሉም በእኩልነት ከእሚሠራ ይልቅ በፖለቲካው የእሚዘወር ነው ብለው ካመኑ ፤ የንግድ ክፍትነት ደረጃዋ ሊይሽቆለቁል ይችላል።

## 4.5 ፈረንሳይ

አንድ ከውጭ ላለ ተመልካች ፤ ከ(1600–1900) የነበሩት የእንግሊዝ እና የፈረንሳይ ማሕበረ ኢከነሚ ፦ በዘውዳዊ ስረዓት የእሚመሩ የቀኝ ገዢዎች ሞኖፖሊስቲክ እና ተከላካይ (monopolistic, protectionist, and colonial) ፖለቲካዊ ስረዓቶች ይመስላሉ።

ከእዚኽ ውጫዊ መመሳሰል ባሻገር ግን ወደ ውስጥ ሲገባ እነ እዚኽ ኹለት ሐገራት መሠረታዊ ልዩነት አላቸው። ፈረንሳይ ኢከነሚዋን በዋናነት የመንግሥትን ስልጣን በማጠናከር እና ብሔራዊ ክብርን በመገንባት ላይ እንዲያተኩር ስታደርግ ፤ እንግሊዝ ደግሞ ቀስ በቀስ የተናጠል የግለሰቦች ጥረት የእሚገነባው ኢከነሚ ወደ መፍጠር አድልታ ነበር። ይኽ የማሕበረ ኢከነሚ የተለያየ አካኼድ ከኹለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ እነ እዚኽ ኹለት ሐገራት ወደ ተመሳሳይ መንገድ እስኪመጡ አብሮ ቆይቷል።

በልዊስ 14ኛ (Louis XIV) የስልጣን ዘመን እና በገንዘብ ምኒስትሩ ዣን ባፒቲስታ ኮልበርት (Jean-Baptiste Colbert) ዘመን የፈረንሳይ ኢኮኖሚ በግልጽ የሐገሪቱን ታላቅነት እና ዝና ለማሳየት በእሚል ነበር የተደራጀው።

የገንዘብ ምኒስትሩ ዣን ባፒቲስታ ኮልበርት (Jean-Baptiste Colbert) የዘውዱ ፋብሪካዎች (Manufactures Royales (Royal Manufactories)) የእሚባሉትን ከዛሬው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ጋር የሚመሳሰሉትን ፋብሪካዎች አቋቋመ።

በእዚኽም መንግሥት ፡- የግሉ ሙሥክ በሕግ አግባብ የእሚቆጣጠር እና ግብር የእሚሰበስብ ኃይል ከማድረግ ይልቅ ፤ የንግድ ድርጅቶችን :- የእሚያቅድ ፣ የእሚቀርጽ እና የእሚገነባ ነጋዴ መንግሥት አደረገ። የጎብሊን ፋብሪካ (Manufacture des Gobelins) የእሚባለው ጨርቃጨርቅ እና የቤት ዕቃ የእሚያመርተው በፓሪስ የእሚገኘው ፋብሪካ ለእዚኽ ጥሩ ምሳሌ ነው።

ይኽን ፋብሪካ መንግሥት ከግለሰብ ከገዛው በኋላ ፡- መስታወት ፣ በተለያዩ መልክ ያሸበረቁ ጨርቆች እና ማስዋቢያ የዲኮሬሽን እቃዎችን የፈረንሳይን ታላቅነት በእሚያሳዩ መልኩ እንዲያመርት እና ወርቅ እነ እዚኽን ዓይነት ምርቶች ለመግዛት ከፈረንሳይ እንደ አይወጣ (Mercantilism) የእሚከላከል የመንግሥት የንግድ ፖሊሲ ማስፈጸሚያ ፋብሪካ ሆኖ ነበር።

ይኽ መንግሥታዊ አሠራር ውጤታማ እንዲሆን መንግሥት በሺ የእሚቆጠር ገጽ ያላቸው የኢንደስትሪውን ጥራት የእሚያረጋግጡ የኢንደስትሪ ሕጎች ያወጣ ነበር። በሕጉ መሠረት ፤ በፋብሪካው የእሚመረቱት ጨርቆች ምን ያህል ርዝመት እና ቁመት እንደ እሚኖራቸው ፣ በስክዌር ሴንትሚትር ምን ያኽል ክር መጠቀም እንደ እሚቻል ፣ ጨርቆቹን ለማቅለም የእሚፈቀዱ ቀለሞች ወዘተ ይደነገጉ ነበር።

እንደ ገንዘብ ምኒስትሩ ዣን ባፕቲስታ ኮልበርት (Jean-Baptiste Colbert) ጥራት የአንድ ነጋዴ ጉዳይ ሳይሆን ብሔራዊ ኃብት ሆኖ ነበር የእሚታየው።

ስለ እዚኽ ፤ አንድ የፈረንሳይ አምራች ጥራት ሲያጓድል ፤ የአንድ ነጋዴ ኪሳራ እንደ ሆነ ሳይሆን እሚታየው ፤ የታላቋን የፈረንሳይን ክብር እንደ ጎዳ ነበር።

ተቆጣጣሪዎች በቋሚነት ማምረቻ በታዎችን ይቆጣጠራሉ። አንድ ምርት መንግሥት ያወጣውን የጥራት ደረጃ ካላሟላ ፤ አምራቹ ከፍተኛ ቅጣት ሊጣልበት እና ምርቱ ባደባባይ ሊቃጠል ይችላል። ማንም ሰው ዘውዳዊ መንግሥቱ ካወጣው የጥራት ሕግ የተለየ የእራሱ አዲስ ስልት ይዞ መምጣት አይችልም።

በመንግሥት የሞኖፖሊ ፈቃድ የእሚሰጣቸው (Chartered companies) የፈረንሳይ ድርጅቶችም ተመሳሳይ ፍልስፍና ይታይባቸው ነበር። የእንግሊዙ ኢስት ኢንድያ ኩባንያ (East India Company) ዓይነት የብቸኛ ነጋዴነት ፈቃድ (Monopoly License) ነጋዴዎች መንግሥትን የብቸኛ ነጋዴነት ወይንም የሞኖፖሊ ፈቃድ እንዲሰጣቸው ወትውተው የእሚያገኙት ሲሆን ፤ የፈረንሳይ ሞኖፖሊዎች ግን መንግሥት እራሱ ከባዶ ተነስቶ የእሚመሠርታቸው ነበሩ (ex nihilo by the state)።

መንግሥት ነበር መነሻ ካፒታሉን ፣ ሠራተኞችን ፥ አንድ አንድ ግዜ መልምሎ ፣ ወይንም ጉቦ ሰጥቶ ፣ ወይንም እንደ ቬነስ እና ፍላንደርስ ከእሚባለው የቤልጅየም አከባቢ በኮንትሮባንድ በማስገባት ጨምሮ ሌሎች ግብዓቶችን የእሚያቀርበው።

የዘውዱ የፊት ማያ መስታወት ማምረቻ (Manufacture Royale de Glaces) ተብሎ የተቋቋመው እና ቬነስ በመስታወት ምርት ላይ የነበራትን ምርት ለመቀማት የተቋቋመው ድርጅት ይኽን ያሳያል። የፈረንሳዩ መንግሥት የፈረንሳይ ነጋዴ አድጎ የቬንሱን የመስታወት ንግድ መወዳደር እስኪችል አልጠበቀም ይልቁንም እራሱ ፋብሪካውን ከሥር መሠረቱ ጀመረው።

ይኽ ኮልበርት የእሚባለው ሰው መንግሥት መር የኢንደስትሪ ፖሊሲ (state-led industrial policy) የእሚባለውን እና አብዛኛው ደኃ ሐገር እሚሰቃይበትን የኢንደስትሪ ፖሊሲ መሥራች እና አስጀማሪ ነው ማለት ይችላል ።

ከእዚኽ በታች ያሉት በእዚኽ የኢንደስትሪያል ፖሊሲ ውስጥ እርሱ ያስጀመራቸው ልማዶች ናቸ፡-

**1. የመስክ መረጣ**

በእዚኽ ፖሊሲ መሠረት ኹሉም መሥክ እኩል ትኩረት አይሰጠውም ፤ ትልቅ ፋይዳ ያላቸው የእሚባሉ መስኮች ይመረጣሉ። ለምሳሌ ፡- በእዚያን ወቅት ትልቅ ወታደራዊ ፋይዳ ያላቸው ወይንም በጣም ትርፍ የእሚያመጡ ተብለው የእሚታሰቡ ፤ ለምሳሌ ፡- እንደ መርከብ ግንባታ ያሉ መስኮች ፤ ከፍተኛ የመንግሥት ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

**2. ኢምፖት የእሚደረጉ ዕቃዎችን መተካት (Import Substitution)**

ኮልበርት በወቅቱ ተፎካካሪ ቀኝ ገዢ የነበሩ እንደ የደች እና የእንግሊዝ ያሉ መንግሥታት እጅ የፈረንሳይ ወርቅ እንደ አይገባ ይፈልግ ስለ ነበር ፤ ከውጭ ተገዝተው የእሚገቡ ዕቃዎችን በሐገር ውስጥ ለማምረት ይሠራ ነበር። እንዲያውም አንድ ግዜ ፤ ዓለም ዓቀፍ ንግድ እንደ ጦርነት የዜሮ ድምር ጨወታ ነው ፤ ማለትም ፡- አንዱ ለማሸነፍ ሌላው መሸነፍ አለበት ፤ ብሎ ተናግሯል። አመክንዮው በእሚለው ምዕራፍ 2 ውስጥ ግን ዓለም ዓቀፍ ንግድ የዜሮ ድምር ጨወታ እንደ አልሆነ እና ይኽም በበርካታ ታሪካዊ የንግድ ማስረጃዎች እንደ ተረጋገጠ ዓይተናል።

**3. መንግሥት የእሚመራው የጥራት ቁጥጥር (State-Controlled Quality)**

ጥራት በገበያ ውስጥ በነጋዴዎች መካከል ከእሚደረግ ውድድር እንዲመጣ ከማድረግ ይልቅ ፤ መንግሥት እራሱ በቀጥታ መጠነ ሰፊ የጥራት ሕግ በማውጣት እና የእዚያን ሕግ ተፈጻሚነት በመቆጣጠር ያመጣዋል የእሚል እምነት።

እነ እዚኽ ሶሥት ዋነኛ የኮልበርት የኢንደስትሪ ፖሊሲዎች ፤ ጃፓን ፣ ደቡብ ኮሪያን እና ቻይናን ጨምሮ ፤ በዘመናዊ የልማታዊ መንግሥት (Modern developmental states) የኢንደስትሪ የልማት ፖሊሲዎች ውስጥ በስፋት ይስተዋላሉ።

ለምሳሌ ፡- ሜድ ኢን ቻይና 2025 (Made in China 2025) የእሚባለው የቻይና የኢንደስትሪያሌዜሽን ፖሊሲ ከእዚኽ ጋር ተመሳሳይ አስተሳሰብ ያራምዳል። ይኽ የቻይና ፖሊሲ ፡- ስትራቴጂክ የእሚላቸው እና ቅድሚያ የእሚሰጣቸው መስኮች አሉት ፣ በቻይና የእሚመረቱ ዋና ዋና ቴክኖሎጂዎች

በከፍተኛ ደረጃ ሐገር ውስጥ የእሚመረቱ ግብዓቶችን እንዲጠቀሙ አቅጣጫ ያስቀምጣል ፣ የሐገሪቱ ገበያ አንድ ዓይነት የጥራት ደረጃ እንዲከተል ከእላይ ወደ ታች ትዕዛዛ እና ቁጥጥር ያወርዳል።

ሆኖም ፤ አንድ ስረዓት ከዕላይ ወደ ታች በዝርዝር ተሠርቶ ሲወርድ ፤ ለለውጥ የእማይመች ድርቅ ያለ ይሆናል። ለምሳሌ ፦ በፍረንሳይ አዲስ ቴክኖሎጂ ወይንም ፋሽን ሲመጣ ፤ ያን ቴክኖሎጂ መጠቀም ወይንም አዲሱን ፋሽን ልብስ ማምረት ይቸገሩ ነበር። ምክንያቱም ፦ የእሚጠቀሙበት መሣሪያ ወይንም ማሽን ፣ የእሚያመርቱበት መንገድ እና የእሚያመርቱት ምርት ዓይነት በመንግሥት በዝርዝር ተወስኖ የእሚሰጣቸው ስለ ነበር። ይኽ ዓይነቱ የፈረንሳይ ስረዓት ፤ ዝርዝር የአደራረግ እና የአሠራር መመሪያ ስለነበረው እና ቁጥጥሩም ከባድ ስለነበር የሰዎችን ብቃት አሳድጓል ሆኖም ካፒታል እና ክህሎት እንደ አሻው እንደ አይንቀሳቀስ አድርጎ አስሮ ነበር (Limited the mobility of capital and experimentation )።

ፈረንሳይ በእዚኽ መልኩ የንጉሡ ቤተመንግሥት እና ከተማ ባለበት በቨርሳይ (Versailles) የኢኮኖሚ ስልጣን ስታከማች ፤ እንግሊዝ ቀስ በቀስ ያልተማከለ እና በዜጎች መካከል በነጻ ገበያ መርኽ መሠረት በእሚደረግ ውድድር እና ትብብር የእሚሠራ (distributed market coordination) የኢከነሚ ስረዓት እየገነባች ነበር ።

ከእዚኽም ጋር አብራ በአክስዮን ማሕበሮች የእሚመሩ ኩባንያዎች (Joint-stock companies) እና የመርከብ ኢንሽራንስ ድርጅቶችን እንደ ሎይድ ኦፍ ለንደን (Lloyd's of London) ባሉ ኩባንያዎች አማካኝነት ስትገነባ ነበር።

የእንግሊዙ ነጋዴ ከፈረንሳዩ ነጋዴ በተለየ ፤ በወቅቱ ገበያ መሠረት ያዋጣል ብሎ ወደ አሰበው ፤ ከበግ ጠጉር ወደ ሻይ ፣ ወደ የድንጋይ ከሰል ወይንም የመርከብ ማጓጓዣ ካፒታሉን በቀላሉ ማዞር ይችላል።

በ18ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ አከባቢ የእንግሊዝ የፍትሕ ስረዓት በጣም ተሻሽሎ እና አድጎ ፤ የንግድ ውሎች መንግሥትን እንኳን ሊያስገድድ እና ሊከበሩ የእሚችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል። ይኽም በዓለም ዓቀፉ የነጋዴ ማሕበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ መተማመን ስለ ፈጠረ ፤ ለንደን (London) የመጀመሪያዋ ትክክለኛ የዓለም የካፒታል ገበያ (A true global capital market) እንድትሆን አስችሏታል።

የእንግሊዝ የሞኖፖሊ (Monopoly charters) ድርጅቶችም ከፈረንሳይ የተለዩ ናቸው። ለእንግሊዝ ነጋዴ ማሕበረሰብ ፓርላማው ፦ ይኽን ለንግዳችን የእሚጠቅም ሕግ አውጣልን ፣ ውሳኔ ስጥልን ፣ ወዘተ በእሚል ፦ የሚለምኑት ፣ ጉቦ የእሚሰጡት ፣ የእሚወተውቱት ነበር። ምንም እንኳን ትልቁ እና ታዋቂው የኢስት ኢንዲስ ካምፓኒ (East India Company) ሞኖፖሊውን እንደ ያዘ ቢቆይም ፤ ሞኖፖሊውን የእሚቃረን ውሳኔ ስለ እሚወሰንበት ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ብዙ ግዜ እሚጋጭ ነበር።

በፈረንሳይ ፤ ዘውዱ ያቋቋመውን ሞኖፖሊ መቃወም ወይንም ከእርሱ ጋር መወዳደር ፤ እንድ የንግድ ጉዳይ ሳይሆን ፤ በመንግሥት ላይ እንደ ማመጽ ተደርጎ ነው እሚወሰደው። በእንግሊዝ ግን ምንም እንኳን ዘውዱ ለኢስት ኢንዲስ ወይንም ለሮያል አፍሪካ ካምፓኒ (East India Company, Royal African Company) የሞኖፖሊ ፈቃድ ቢሰጥም ሌሎች ትንንሽ ነጋዴዎች ፤ የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እና

የመነገድ ነጻነት መብትን መሠረት አድርገው ፍርድ ቤት ኼደው መወዳደር መብቴ ነው በእሚል ይከሥሱ እና አንድ አንድ ግዜ ፍርድ ቤት ከእነርሱ ጋር ወግኖ ፤ ዘውዱ የሰጠውን የሞኖፖሊ ፍቃድ ተቃውሞ ፤ ውሳኔ ያሳልፍ ነበር ፤ ምንም እንኳን ሞኖፖሊዎን ባይሽረውም ወይንም ባያፈረሰውም።

ይኽ ዓይነቱ በፈረንሳይ እና በእንግሊዝ የማሕበረ ኢከነሚ ተቋማት አደረጃጀት መካከል የነበረ ልዩነት ፤ የኢንደስትሪ አብዮት (Industrial Revolution) ሲመጣ ፤ የፈረንሳይ እና የእንግሊዝ ኢኮኖሚዎች በተለያየ መንገድ እንዲያስተናግዱት አደረገ።

ምክንያቱም ፦ እንግሊዝ ተቋሞቿን ያደራጀችበት መንገድ ፦ እጅ በቀላሉ የእሚቀይር ካፒታል ፣ የገበያ የምልክት ስረዓት (market signals) እና የውል ተፈጻሚነትን ያረጋገጠ ስለ ነበር ፤ በቀላሉ የቴክኖሎጂ ለውጦችን ተቀብሎ እራሱን ማሻሻል የእሚችል ነበር። በአንጻሩ ፈረንሳይ በቀላሉ ለውጥን ማስተናገድ የእምትችልበት ስረዓት ስለ አልነበራት ፤ ከመቶ ዓመታት በላይ የፈጀ የፖለቲካ ነውጦች ማስተናገድ ነበረባት ፤ ጠንካራውን የመንግሥት ቁጥጥር ለማማላላት።

ከ1789 እስከ 1799 የቆየው የፈረንሳይ አብዮት እንኳን የፈረንሳይን የኢከነሚ ስረዓት ረድዛይን (Redesign) ወይንም እንደገና በአዲስ መልክ ለመቅረጽ ሞክሮ ፤ የመንግሥትን መዓከላዊ ቁጥጥር ሊይላላው አልቻለም።

መጀመሪያ ላይ ፤ የፈረንሳይን ኢከኖሚ ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ በማሰብ ፤ በጣም ሰፊ በቤተክርስቲያን የተያዙ ቦታዎችን በሙሉ እየወረሱ ለዜጋው ሸጡ ፦ አንድ የመሬትን ክፍፍል ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ ፣ ሲቀጥል በወቅቱ የነበረባቸውን ጦርነት ወጪ ለመሸፈን እና አዲስ ያተሙትን ገንዘብ ለማጠናከር። ሆኖም በእዚኽ መልኩ የሸጡት አብዛኛው መሬት የተገዛው በደኻው የሕበረተሰብ ክፍል ሳይሆን ፤ "በኻብታም" ጭሰኞች እና በከተማ ከበርቴ ነበር። ውጤቱም አዲስ ብዙ መሬት የያዘ የመሬት ከበርቴ መፍጠር ነው የሆነው ፤ የመሬት ስረጭትን ከማደላደል ይልቅ።

በእዚያ ላይ አሲያት (Assignat) የተባለው እና አዲስ ያተሙት ገንዘብ በመርኽ ስላልተመራ እና ከኢከነሚው ምርት በላይ ስለ ታተመ ፤ ዋጋው በእየግዜው እየተዳከመ ኼዶ ፤ የዋጋ ግሽበት እና የገንዘብ ስረዓት አለመረጋጋት ፈጠረ። በእዚኽ ላይ አብዮታዊ መንግሥቱ ፤ የፈረንሳይ አብዮት በአጭሩ ካልተገታ የእኛንም ቤት ያንኳኳል ብለው የፈሩ ፤ የአውሮፓ ነገሥታት ከአብዮተኛው የፈረንሳይ መንግሥት ጋር ጦረነት ስለገቡ ፤ አብዮታዊው መንግሥት ጦርነቱ የፈጠረውን ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ለመከላከል ፦ የተማከለ እና የዋጋ ቁጥጥር እንዲኹም የንብረት ወረሳን የእሚጨምር የኢኮኖሚ አስተዳደር ውስጥ ገባ።

የናፖሊዮን መምጣትም ይኽን የተማከለ የኢከነሚ አስተዳደር ይበልጥ አጠናክሮ አስቀጠለው። ኮንትነንታል ስረዓት (Continental System) ብሎ ያመጣው እና ከእንግሊዝ ጋር የእሚደረግ ንግድን ለማስቀረት ብሎ ያቋቋመው አውሮፓዊ ስረዓት ፤ ፈረንሳይ ከውጭ የእምታስገባቸውን ዕቃዎች እራሷ በእምታመርታቸው ዕቃዎች እንድትተካ አስተገደዳት። የኮሎንያል ስረዓቱ የስኳር አቅርቦት ሲቋረጥ ፤ የፈረንሳይ መንግሥት ስኳርን ከስኳር ድንች በሐገር ውስጥ ወደ ማምረት ገባ።

ናፖሊዮን አብሮም የፖሊቴክኒክ ትምሕርት ቤት ወይንም ኢኮል ፖሊቴክኒክ (École Polytechnique – Polytechnic School) የእሚባል ትምሕርት ቤት አቋቁሞ ፤ መንግሥት ያቋቋማቸው እነ እዚኽ ድርጅቶች ውስጥ የእሚሠሩ ኢንጂነሮች እና አስተዳዳሪዎች ማሰልጠን ውስጥ ገብቶ ነበር።

ይኽም ከፍተኛ ብቃት ያላቸው ሞያተኛ የመንግሥት ሠራተኞች ፈጠረ (Technocratic bureaucracy)። ስለ እዚኽ ፦ መንግሥት መሆን ማለት የፖለቲካ ስልጣን መያዝ ብቻ ሳይሆን አስተዳዳራዊ እና ሞያዊ ብቃትም ሆነ ፤ ይኽም ለመንግሥት ሌላ ጥንካሬ ሰጠው (መልካም ያልሆነ)።

ይኽም፦ መንግሥት እራሱ በእዚኽ መልኩ የንግድ ድርጅቶችን ጥሩ አድርጎ እሚያስተዳድራቸው ከሆነ ለምን ወደ ግል ይዞራሉ? የእሚለውን መንግሥት ፖለቲከኛም ነጋዴም መሆን ይችላል የእሚለውን እሳቤ የእሚያጠናክር ነበር።

እንደገናም ከኹለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ፤ ፈረንሳይ ድርጂዝም (dirigisme) የእሚባል እና በመንግሥት የእሚመራ ጦርነት ካደረሰው ውድመት የማገገሙን (Reconstruction) ሥራ የእሚመራ የኢኮኖሚ ፕሮጀክት አመጣች።

እንደ ብሔራዊ የአስተዳደር ትምሕርት ቤት (École Nationale d'Administration) ያሉት ተቋማት የኢኮኖሚ ዕቅዱን የእሚመሩ ሞያተኞችን አሰልጥኖ ማውጣት ጀመረ። መንግሥትም እንደ ኤርበስ (Airbus) ፣ ሬኖልት (Renault) እና የፈጣን ባቡሩን ድርጅት (TGV) ዓይነት ትላልቅ ድርጅቶችን በተለያየ መልኩ ማገዝ ውስጥ ገባ።

ይኽም አካኼድ ለ30 ዓመታት በተከታታይ ፤ በፈረንሳይ ፈጣን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እና ዘመናዊነትን አመጣ።

የእንግሊዘኛው መጽሐፍ ውስጥ ይኽ ባይኖርም ፤ ከሐገራችን አኳያ ለማነጻጸር ፤ የፈረንሳዩ ድርጂዝም (Dirigisme) የሠራው ፤ የመንግሥት ባለቤትነቱ የገበያውን ሕግ የሻረ ስለ አልነበረ ነበር። ከሞላ ጎደል መንግሥት ከአንድ ሌላ ግለሰብ የተለየ አልነበረም በባለቤትነቱ። የመንግሥት የሆኑት ድርጅቶች ከግል መስኩ ድርጅቶች ጋር በእኩልነት የእሚወዳደሩ እና ከእላይ የተዘረዘሩትን አምስት ኹኔታዎች የእሚጥሱ አልነበሩም። ያም ብቻ ሳይሆን ማንግሥት እራሱን በጣም ስትራቴጂ በእሚላቸው በተወሰኑ ትልልቅ መስኮች የወሰነ ነበር።

ለምሳሌ ፦ የግል የሆነው ፔጆት (Peugeot) የመንግሥት ድርሻ ካለበት ሬኖልት (Renault) ወይንም የመንግሥት አየር መንገድ ከግል አየር መንገድ ጋር በእኩል የመወዳደሪያ ሜዳ ይወዳደራሉ።

ይኽ ቢሆንም ፤ ዛሬ ላይ የፈረንሳዩ ሞዴል ችግር ገጥሞታል። በፈረንሳይ በጣም ጠንካራ የማሕበራዊ ድጎማ እና የሠራተኛ መብት ከለላ በመኖሩ ፤ ምንም እንኳን ይኽ ዓይነቱ "የሕዝብ" ወገንተኝነት ማሕበራዊ መረጋጋትን ቢፈጥርም ፤ ስረዓቱ ግን ታዳሽ እንደ አይሆን አድርጎታል።

በአሁኑ ሰዓት የፈንሳይ መንግሥት ከፍተኛ ግብር[8] የመሰብሰብ አቅም እና የመበደር አቅም ስለ አለው ፤ ከአመታዊ ምርቱ (GDP) ግማሹን በላይ ለድህነት ቅነሳ ፣ ለትምሕርት ፣ ለጤና ፣ ወዘተ ፍጆታ ስለ እሚያውል እና በጣም የተንዛዛ የሕግ ስረዓት ስለ አለው ፤ አካኼዱ ለነጋዴ የእሚሞች አይደለም።

በእርግጥ ዛሬም ቢሆን ፈረንሳይ እንደ ኤሮስፔስ (Aerospace) እና የቅንጦት (Luxury) እቃዎች ምርት በዓለም ላይ መሪ ናት። ሆኖም የማማከል ልምዷ ፤ በአልተማከለ መልኩ አዳዲስ ፈጠራዎች እንዲፈጠሩ እድል አይሰጥም።

ጠቅለል ብሎ ሲቀመጥ ፤ ፈረንሳይ ከፍ ባሉ እና በመንግሥት ትኩረት በእሚሰጣቸው (Elite, state-guided innovation) መስኮች የፈጠራ ልቀት ስታሳይ እንግሊዝ ደግሞ ሰፊ እና ማሕበረሰባዊ በሆኑ በመላ ገበያው (Broad, distributed experimentation across the market economy) ውስጥ በእሚሠሩ የፈጠራ ስራዎች የተሻለ ስኬት ታስመዘግባለች።

ፈረንሳይ የተቋማዊ አብሿምነት ("Institutional Bipolarity") ጥሩ ምሳሌ ነች። በአንድ በኩል በዓለም ዓቀፍ ደረጃ (World-class) ተወዳዳሪ የሆነ የሕግ እና የንግድ ተቋማት ሲኖራት ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከበጀት አስተዳደር አንጻር ከታናሿ ብራዚል ጋር የእሚነጻጸር ኢከነሚዋን የእሚያዘገይ የኢንቨስትመንት ሳይሆን የፍጆታ ልጓም (Consumption Gravity) አለባት ፤ እዚኽ ላይ እንደገና በመንግሥት የእሚመራ በዓይነቱ ልዩ የሆነ የኢኮኖሚ ውድድርን የእሚያረጋግጥ (State-Directed Contestability) አላት።

### 1. የግል ንብረት (አንኳር)

| አመላካች | የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም | ልኬት (0–2) | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| **1. ባለቤትነት** | ለመኖር ይሁን ለንግድ ኹሉም ዓይነት ንብረቶች ለኹሉም ሐገር ዜጎች መቶ በመቶ ነጻ ናቸው ፤ በግል ንብረትነት ለመያዝ። ሆኖም የግብራና መሬት ሴፈር (SAFER) በእሚባለው ተቋም ለግብርና ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ ቁጥጥር ይደረግበታል። ከ2025/2026 በኋላ ደግሞ በአርተፊሻል | **2 (ከፍተኛ)** | ምንም እንኳን በግብርናው መስክ የማጣራት እና የመቆጣጠር ነገር ቢኖርም ፤ ለሐገሩ ዜጋ ሆነ ለውጭ ሐገር ዜጋ ፤ የንብረት ባለቤትነት በእኩልነት የእሚከበር መሆኑ ፤ የፈረንሳይ ኢከነሚ አንድ ምሰሶ ሆኗል። |

[8] የአመታዊ ምርቱን (GDP) 45% በመቶ ገደማ ይሰበስባል ፤ ኢትዮጵያ 8 በመቶ ገደማ እምትሰበስበው።

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ኢንተለጀንስ እና ወሳኝ በእሚባሉ ማዕድኖች ላይ የውጭ ዜጎች የእሚያደርጉትን ኢንቨስትመንት መቆጣጠር ጀምረዋል ፤ ካስፈለገ መከልከል እንዲችሉ። | | |
| **2. ውርስ** | የፈረንሳዩ የውርስ ሕግ (*Code de l'expropriation pour cause d'utilité publique*) በእዚኽም ሕግ መሠረት ንብረቱ ከመወረሱ በፊት ተወጣጣኝ ዋጋ ይከፈላል። የፈረንሳይ ፍርድቤቶች ደግሞ ንብረታቸው ለእሚወረስባቸው ሰዎች ያደላሉ ፤ የንብረት ካሳ ብቻ ሳይሆን በመፈናቀል ለእሚፈጠር እንግልትም ነው ካሳ እሚወስኑት።<br><br>እንደ ብራዚል ወይንም በቅርቡ ከፍተኛ ተለዋዋጭነት እንደ አሳየው የፖላንዱ ሕግ ሳይሆን ፤ የፈረንሳይ ሕግ በጣም የጸና እና ተገማች ነው። | **2 (ከፍተኛ)** | በፈረንሳይ ካሳ ሳይከፈል ንብረት ይወረሳል የእሚባል ነገር የለም። በዓለም ላይ አሉ ከእሚባሉ ጠንካራ ሕጎች አንዱ ነው የፈረንሳይ ሕግ። |
| **3. የንብረትውድድር (Contestability)** | ፈረንሳይ በ2025 ብቻ በጣም ሶስት መቶ ሰባ አምስት ሚልየን ዩሮ (379M ) ቅጣት የበየነ ፤ ጠንካራ ጸረ ሞኖፖሊን የእሚመራ ተቋም አላት (*Autorité de la concurrence*) ።<br><br>በተመሳሳይም በአዘቅትነቱ (Permit Quagmire) ከቺሊ ጋር | **1 (መካከለኛ)** | ምንም እንኳን የጸረ ሞኖፖሊ ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ከኹኔታዎች ጋር እራሱን እሚያጣጥም ቢሆንም እና ሕጉንም ለማስከበር ቆራጥነቱ ቢኖረው ፤ በአፕል እና መሰል ኩባንያዎች ላይ የወሰናቸው ውሳኔዎች ማሳያ ናቸው (like Apple/Doctolib) ፤ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የእሚወዳደር እጅግ የተንዛዛ የፈቃድ አወጣጥ ስረዓት አላት። <br><br> በፈረንሳይ በጣም ጠንካራ የሆነ የአከባቢ ጥበቃ እና ለምሳሌ ፦ የንብረት ባለቤት የሆነ ሰው ጥብቅ የሆኑትን የአከባቢም የሠራተኛም ሕግ (ለምሳሌ፡- በእዚያ ቦታ የእሚሠሩ ሠራተኞች ደህንነታቸው እንዲጠበቅ) እንዲያከብሩ ይገደዳሉ ፤ ይኸ ዓይነት ጠንካራ ሕግ ፤ ለአዲስ ገቢዎች ችግር ይፈጥራል። <br><br> በ2026 የወጣ አዲስ ሕግ ከ5 ሚልዮን ዩሮ (€5M) በላይ ኃብት ያላቸው ሰዎች ላይ ፓትሪሞንያል (Patrimonial Holding Tax) የእሚባል ግብር በመጣል በግል በጣም ኃብታም መሆንን ሊቀጣ ይፈልጋል። ይኸ ግን አዲስ ካፒታል ፈጠራን ሊጎዳ ይችላል። | | በፈረንሳይ ውስጥ ያለው አስተዳደራዊ ውትፍትፍ ግን የምርታማነት ማጥለያው እንደ አይሠራ እያደረገው ነው። |
| **የሠራተኛ ነጻነት (Labor Freedom)** | የ2017 የማክሮን ማሻሻያ እንኳን በቅጥር ገበያው ውስጥ ያለውን አጉል ጥብቅ ኹኔታ ሊያረግበው አልቻለም። በ2026 ሠራተኞች ከባሕሪ ችግር ውጭ ከሥራ ሲባረሩ የእሚከፈላቸው ክፍያ በ40% እንዲጨምር ተደረገ ፣ አብሮም 55 ዓመት ያለፉቸውን ሰዎች ላለመቅጠር ወይንም ከሥራ ለመቀነስ የእሚሞክሩ ድርጅቶች የእሚቀጡት ቅጣት ከፍ እንዲል | **1 (መካከለኛ)** | ሠራተኛው የሞያው የግል ባለቤት ነው ፤ ሆኖም ቀጣሪዎች በቀላሉ ሠራተኛ መቅጠር እና መልቀቅ ስለ እማይችሉ ፤ ኢኮኖሚው በብቁ ኹኔታ ሠራተኛ እንደ አይደለድል አድርጎታል። የቅጥር ገበያው በአንጻራዊነት ነጻ ነው ፤ ሆኖም ማሕበራዊ ኃላፊነቱ ብዙ በመሆኑ ብዙ ውጥረት አለበት። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ተደረገ። ሠራተኞች ሥራ እንደ አሻቸው ፈልገው መቀጠር የእሚችሉ ሲሆን ፤ ሠራተኛ ማባረር ግን በጣም ብዙ ዋጋ የእሚያስከፍል ነው። | | |

**የአመላካቾቹ አማካይ : 1.66 → በፈረንሳይ የግል ንብረት ባለቤትነት መብት ደረጃ ልኬት: 4**

**2. የንብረት ተንቀሳቃሽነት (አጥዳፊ)**

| **አመላካች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የውጭ ዜጎች የንብረት ባለቤትነት** | በጠቅላላው ለኹሉም ሐገር ዜጋ ንብረት ክፍት ነው ፤ ሆኖም 2019-2026 ባለው ግዜ እንደ ቴክኖሎጂ እና ምግብ መስኩ ላይ የሚሰማሩ ሰዎች የተለየ ማጣራት ይደረግባቸዋል። | **1** | የተለመደው ከፍተኛ የንግድ ክፍትነት ፤ የኢኮነሚ ሉዓላዊነት ("Economic Sovereignty") በእሚል የተወሰነ ክልከላ እየተደረገበት ነው። |
| **የመሬት ገበያ** | ብዙ ገንዘብ እሚንቀሳቀስበት (Highly liquid) ግልጽ የሆነ አሠራር ያለበት ነው። | **2** | ውጤታማ የመሬት ምዝገባ አለ ፤ መሬት በኢኮነሚው ውስጥ ዋነኛ እና አስተማማኝ የብድር ማስያዣ ነው። |
| **የካፒታል ቁጥጥር (Capital Controls)** | ምንም ዓይነት የካፒታል ቁጥጥር የለም ፤ ካፒታል በአውሮፓም ሆነ በዓለም ላይ እንደ ፈለገው መንቀሳቀስ ይችላል። | **2** | ባለፈው 40 ዓመት ነጻ የካፒታል እንቅስቃሴ ነው የነበረው። |
| **የስቶክ ገበያው መጠን** | ዩሮኔክስት (Euronext) የእሚባለው በፓሪስ ያለው | **2** | ከፍተኛ ገንዘብ እሚገላበጥበት (Deep) |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **(Stock Market Size)** | አክስዮን ገበያ ፤ ብሪትን ከአውሮፓ ሕብረታ ከወጣች በኋላ ፤ በአውሮፓ ትልቁ የስቶክ ገበያ ነው። ከዩሮ አከባቢ አመታዊ ምርቱ አንጻር ለሽያጭ የቀረቡት ኩባንያዎች ወይንም ማርኬት ካፑ (Market cap/GDP) 59% በመሆን ከፍተኛ ነው። | | በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የአክሲዮን ገበያ አለ (World-class equity markets.) |
| **በቀላሉ ንግድ መጀመር እና መዝጋት** | የግል/ለራስ ነጋዴ ("Auto-entrepreneur") የሚባለው አዲሱ አሠራር ንግድ መጀመርን ቀላል አድርጎታል ፤ ከ2017–2026 ባለው ግዜ በጠቅላላው ብዙ ለውጥ ተደርጓል። | **2** | ከዛሬ 20 ዓመት ጋር ሲነጻጸር በጣም በቀላሉ ንግድ መጀመር ይቻላል። |
| **ብድር ማግኘት** | ዘመናዊ ባንኮች አሉ ፤ ነገር ግን ፤ የቁጥጥሩ ሕግ በጣም ይበዛል በዛ ላይ ባንኮች ከቴክኖሎጂ ጋር ላልተያያዙ ለአነስተኛ እና መለስተኛ(SMEs) ንግዶች ብድር ለመስጠት ይፈራሉ። | **1** | የበሰለ የብድር ገበያ አለ ፤ ሆኖም አስተዳደራዊ ግግርቱ ("Administrative Sclerosis") ለትንንሽ ተበዳሪዎች አይመችም። |

**የአመላካቾቹ አማካይ: 1.66 → የፈረንሳይ የንብረት ተንቀሳቃሽነት ደረጃ ልኬት : 4**

### 3. የሕጉ ነጻ እና ገለልተኛነት (አንኳር)

| **አመላካች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የዳኝነት ነጻነት** | ዳኞች ከፍተኛ ነጻነት ነው ያላቸው ፤ በስልጣን ላይ ያሉ ፕሬዝደንድቶችን እና | **2** | ባለፈው 40 ዓመት የፈረንሳይ ፍርድ ስረዓት ነጻ እና ገለልተኙነቱን እንደ ጠበቀ ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ሚንስትሮችን ኹሉ በመርመር። | | |
| **ሙስና** | ጥቃቅን ("petty") የእሚባሉ ሙስናዎች ትንሽ አሉ። ሴፐን በእሚባል ሰው ስም የተሰየመ (Sapin II - 2016) እንደ አሜሪካ ዓይነት የጸረ ሙስና ሕግ አጽድቀዋል። | **2** | ከፍተኛ ግልጽነት ያለበት እና የባለ ነጭ ኮሌታሞች (white-collar) ወንጀል የእሚባሉ እንደ ሙስና ዓይነት ወንጀሎችን በጣም እሚዋጉ አቃቢ ሕጎች አሉ። |
| **የውል ተፈጻሚነት** | ሕጉ አስተማማኝ እና ተገማች ነው ሆኖም በጣም ቀርፋፋ ነው ፤ የእሚያስከፍለው የግዜ ግብር (Time Tax) ብዛት ከፍተኛ ድከመቱ ነው። | **1** | ሕጉ በጣም አስተማማኝ እና ተገማች ነው ሆኖም አፈጻጸሙ በጣም የተንዛዛ ነው። |
| **በሕግ ፊት እኩል መታየት** | የሕጉ መዋቅር ጠንካራ ነው ፤ ምንም እንኳን የታላላቆች ቡድን (*Grandes Écoles*) በእሚባሉት ምክንያት መጠነኛ ልዩነት ቢኖርም። | **1** | ሕጉ እኩልነትን ያከብራል (de jure) ሆኖም የመንግሥት ባለስልጣን የነበሩ ሰዎች ወጥተው የንግድ ድርጅቶች የቦርድ አባል ስለ እሚሆኑ እና እንደገናም ከቦርድ አባልነት ወደ መንግሥት ባለስልጣንነት ስለ እሚመለሱ ፤ ማን ሕግ አውጭ ማን ሕግ አክባሪ መሆን ሳይለይ ይቀርና ፤ ስውር የሆነ ሕጉን ለራሱ ጥቅም የእሚጠቀም የሊህቅ ቡድን ይፈጥራል። |
| **ፖለቲካዊ ጣልቃገብነት** | በንግድ ክርክር ላይ በጣም ዝቅተኛ ነው ፤ ነገር ግን ከፍተኛ ኢንደስትሪ በእሚባሉት | **1** | ትላልቆቹ ሐገራዊ ኩባንያዎች ላይ ፖለቲካው በፍርድ ቤቶቹ ላይ ተፅዕኖ ያደርጋል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ውስጥ ጣልቃ ገብነቱም ከፍተኛ ነው። | | |
| **የፖሊስ አስተማማኝነት** | ከፍተኛ ደረጃ ያለው የንብረት ጥበቃ እና ማሕበራዊ መረጋጋትን የእሚያረጋግጥ ፖሊስ አለ። | **2** | ሕጉን በአስተማማኝ መልኩ ያስከብራል። |

**የአመለካቾቹ አማካይ: 1.50 → በፈረንሳይ የሕጉ ነጻ እና ገለልተኛነት ደረጃ ልኬት: 4**

**4. የንግድ ክፍትነት (አጥዳፊ)**

| **አመላካች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የታሪፍ/የቀረጥ መጠን** | በጠቅላላው የአውሮፓ ሕብረት ከሕብረቱ ውጭ ባሉ ሐገራት ላይ የእሚጥለው ቀረጥ አለ ፤ ከእዚያ በተረፈ የሕብረቱ ሐገራት ላይ የተጣለ ምንም ቀረጥ የለም። | **2** | በሰፊው ከነጋዴው የዓለም ክፍል ጋር የተሳሰረ ጠንካራ የንግድ ክፍትነት አለ። |
| **ከታሪፍ ውጭ ያሉ ክልከላዎች** | ለጥንቃቄ በእሚል ሰፊ መርሆች እና ቁጥጥር ስለ አለ ፤ እንደ ክልከላ ያክል ይቆጠራሉ። | **1** | ለአከባቢ ጥበቃ እና ለጤና በእሚል የእሚደረጉ ከፍተኛ ቁጥጥሮች ፤ መልካቸውን ወደ ክልከላ ቀይረዋል። |
| **የገቢ/ወጪ ንግድ ከአመታዊ ምርቱ አንጻር (Trade - % of GDP)** | ከፍተኛ የእሚባል የንግድ ትስስር አለ ፤ የአመታዊ ምርቱ 70% ይሆናል (approx. 65-70% of GDP). | **2** | ፈረንሳይ በዓለም ላይ ከፍተኛ ከእሚባሉት ዕቃ ላኪ እና ተቀባይ ሐገራት መካከል ነች። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **በወጪ ገቢ ንግድ ላይ ያለ ክልከላ** | በጣም ጥቂት ክልከላ ነው ያለው ፤ ምንም እንኳን ስትራቴጂክ አውቶኖሚ ("Strategic Autonomy") የሚለው አዲስ አካኼድ በኤክስፖርት ላይ ብዙ ቁጥጥር ቢያበዛም። | **2** | ለአብዛኛው ሸቀጥ ትንሽ ቁጥጥር ነው ያለው። |
| **የጉምሩክ ቆይታ** | በዓለም ደረጃ ተወዳዳሪ (World-class) የሆነ እና በኮምፒውተር የታገዘ የጉምሩክ ሲስተም አለ። | **2** | የፈረንሳይ የሎጀስቲክ ፍጥነት እንደ መወዳደሪያ የሚያገለግል ቅልጥፍና አለው (Benchmark for logistical speed.) |
| **የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት እና ሕግ አክባሪነት (WTO Compliance)** | ንቁ እና ሕግ አክባሪ ተሳታፊ ነች ፈረንሳይ። | **2** | ባለፈው 40 ዓመት ጠንካራ አፈጻጸም ነው ያለው። |

**የአመላካቾቹ አማካይ: 1.83 → በፈረንሳይ የንግድ ክፍትነት ደረጃ ልኬት: 4**

### 5. የበጀት አስተዳደር ጥበብ (አንኳር)

| አመላካች | የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም | ልኬት (0–2) | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| **የግብር ተገማችነት** | የሚሰበሰበው ግብር በጣም ብዙ ነው ፤ የአመታዊ ምርቱ ከ45 በመቶ በላይ ነው ሆኖም ሕጉ ግልጽ በቋሚነት የሚተገበር በመሆኑ ተገማች ነው። | **2** | ከፍተኛ ተገማችነት አለው ፤ የመንግሥት ትኩረቱ ኮርፖሬሽኖች የሚከፍሉት ግብር ላይ ሳይሆን ሰዎች የሚያከማቹት ኃብት ላይ ነው ፤ ስለ እዚኽ የኮርፖሬሽኖቹ ሳይሆን ኃብት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ላይ እሚጣለው ግብር ነው እሚለዋወጠው። |
| **የበጀት ጉድለት ለመሙላት ገንዘብ ማተም (Monetary Financing)** | የበጀት ጉድለትን ለመሙላት ገንዘብ ማተም በአውሮፓ ሕብረት ማዕከላዊ/ብሔራዊ ባንክ የተከለከለ ነው (Banned by the ECB - Maastricht Treaty). | **2** | ጠንካራ የሆነ ከአውሮፓ ሕብረት ጋር የተደረገ ትሥሥር መኖሩ የበጀት ጉድለት ገንዘብ በማተም እንደ አይሞላ አድርጓል። |
| **ብድርን ወስዶ ለአምራች ዓላማ መጠቀም (Productive Debt** | ፈረንሳይ ከፍተኛ የብድር መጠን ነው ያላት ፤ በ2024 ከኢኮነሚው አመታዊ ምርት ~113% ገደማ ሆኗል (Debt-to-GDP hit ~113% in 2024) የመንግሥት ብድር ፤ በ2027 ወደ 120% ይደርሳል ተብሎ ተገምቷል. | **0** | ብድር መሠረተ ልማት ከመገንባት ይልቅ ፤ በተደጋጋሚ ማሕበራዊ ድጎማ ለማድረግ እያዋለ ነው ። |
| **የዋጋ ግሽበት** | ዝቅተኛ ነው ፤ በ2026 ወደ 1.3% ገደማ ነው። | **2** | የአውሮፓ ሕብረት ባንክ(ECB) ረጅም ዘመን የእሚቆይ የዋጋ መረጋጋት እንዲኖር አድርጓል። |
| የብሔራዊ ባንክ ነጻነት | የፈረንሳዩ ብሔራዊ ባንክ የአውሮፓው ብሔራዊ ባንክ አካል ነው (Banque de France is part of the Eurosystem (ECB)) ስለ እዚኽ ሙሉ ነጻነት አለው። | **2** | ዓለም ዓቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እና ነጻ ብሔራዊ ባንክ(World-class central bank autonomy.) |
| **የመገበያያ ገንዘብ ርጋታ (Currency Stability)** | ዩሮ የዓለም ሪዘርቭ (Global Reserve) ወይንም ዓለም ኃብቱን | **2** | በጣም የተረጋጋ እና ተገማች ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | እሚያስቀምጥበት ገንዘብ ነው። | | |
| **በብድር እዳ የመያዝ ታሪክ** | ምንም ዓይነት በእዳ የመያዝ ታሪክ የለም። | **2** | ብድራቸውን በቋሚነት በመክፈል ይታወቃሉ። |
| **የበጀት አደላደል** | መንግሥት የአመታዊ ምርቱን ~57% (~57% of GDP) በድጎማ ላይ በማጥፋት በኦኢሲዲ(OECD) ሐገራት ትልቁ ሆኗል። | **0** | መንግሥት በእዚኽ መልኩ ከፍተኛ ገንዘብ በማሕበራዊ ድጎማ ላይ ስለ እሚያወጣ ፤ ፈረንሳይ በ2030 ("France 2030") ያወጣውን የኢንቨስትመንት ግብ ለማሳካት የገንዘብ እጥረት ፈጥሮበታል። |

**የአመላካቾቹ አማካይ : 1.50 → በፈረንሳይ የበጀት አስተዳደር ጥበብ ደረጃ ልኬት: 4**

**በባለፈው 40 ዓመት ከአምስቱ ኹኔታ አንጻር የፈረንሳይ ውጤት ፦**

| **ሐገር** | **ኹኔታዎች** | **ልኬት** |
|---|---|---|
| **ፈረንሳይ** | **የግል ንብረት (አንኳር)** | **4** |
| | **የንብረት ተንቀሳቃሽነት (አጥዳፊ)** | **4** |
| | **የሕጉ ነጻ እና ገለልተኛነት (አንኳር)** | **4** |
| | **የንግድ ክፍትነት (አጥዳፊ)** | **4** |
| | **የበጀት አስተዳደር ጥበብ (አንኳር)** | **4** |

**የምርመራ ውጤት: ፈረንሳይ**

**ፍረጃ: ከፍተኛ ገቢ ያለው ኢከነሚ**

- **የአንኳር ኹኔታዎች ትንተና (Core Analysis):** በወረቅት ላይ ፈረንሳይ በ3ቱም አንኳር ኹኔታዎች ከፈተኛውን 4 ውጤት ነው ያላት። በዓለም ላይ ጠንካራ ሊባል የእሚል የኢከነሚ

ተቋማት ገንብታለች። ሆኖም የምርመራው ውጤቱ ፦ በሰለጠነው ዓለም ከተለመደው በተለየ በጣም በተጋነነ የማሕበራዊ ድጎማ አባዜው ፤ የበጀት አስተዳደሩ ድክመት ሆኖ ሐገሪቱን በስውር እስራትነት ("Hidden Stagnation") ቆሞ የመቅረት አደጋ ውስጥ አስገብቷታል።

- **የድጎማው ልጓም (The Consumption Drag):** ፈረንሳይ ከብራዚሉ እና ከፈረንሳዩ ጋር ተመሳሳይ የሆነ በጀትን በከፍተኛ ደረጃ ድጎማ ላይ በማዋል የእሚፈጠር የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ( "Consumption Anchor") ችግር አለባት። በጀቱ የአመታዊ ሐገራዊ ምርቱ ~57% (~57% of GDP) ሆኖ መንግሥት የሐገሪቱ ኢኮኖሚው የበላይ ጠባቂ ("Umpire") ሳይሆን የኢኮኖሚው ጥገኛ (Customer) ሆኖ ነው ያለው። ይኽም የፈጠራ ማጥለያው ወንፊት (Innovation Sieve) በአግባቡ እንደ አይሠራ ያደርገዋል ምክንያቱም ፦ ከፍተኛ መጠን ያለው ካፒታል በማሕበራዊ ድጎማ በመያዝ ፈረንሳይ 2030 ("France 2030") ወደ እሚለው የኢንደስትሪ ፖሊሲ እንደ አይፈስ ስለ እሚያደርግ። (From working correctly because too much capital is "locked" into the welfare state rather than flowing toward the "France 2030" industrial policy.)

- **የፈጠራ ማጥለያ ወንፊቱ (Innovative Sieve Filter):** ምንም እንኳን በመንግሥት የእሚመራ ቢሆንም ( Though it is "State-Directed") በፈረንሳይ የንብረት ተንቀሳቃሽነት ደረጃ ልኬት ከፍተኛው ደረጃ 4 ላይ ነው። የፈንሳይ የፈጠራ ወንፊት (Innovation Pool) የሆነች ሐገር ናት መንግሥት ግን እንደ አሮጌ ኃብት ምሽግ (Wealth Vault) ሊያስተዳድራት ነው የእሚፈልገው። መንግሥት እንደ ኃይል ማመንጨት ፣ መከላከያ ፣ እና AI ያሉትን መስኮች ስትራቴጂክ (Strategic) በእሚል ፈርጆ ለየተ ያለ ብድር የማግኘት ፣ የሕግ ከላለ ፣ ገበያ ፣ ወዘተ ስለ እሚሰጥ ፤ ስትራቴጂክ አይደሉም (Non-strategic) ለተባሉት መስኮች ተወዳዳሪነት እና ሥራ ፈጣርነትን አዳክሟል።

- **የማስጠንቀቂያ ትንበያ (The Predictive "Premonition"):** ፈረንሳይ በአለፈው 5 አመት በበጀት አስተዳደር አኳያ ያሳየችው ደካማ አፈጻጸም በእዚኹ መልኩ ከቀጠለ ሐገሪቱን ጥሩ ወደ አልሆነ አቅጣጫ ሊያመራት ይችላል (Ominous Fiscal Signal)። በፈረንሳይ የመንግሥት እዳ ከኢከነሚው አመታዊ ምርት አንጻር በ2027 ዓመት 120% ይደርሳል ፤ በእዚኽ ላይ ኢከነሚው በእሚያድግበት ይኹን በእሚቀዛቀዝበት ግዜ ፤ መንግሥት ለተበደረው ብድር ከእሚከፍለው ወለድ ውጭ ፤ ከእሚያደርገው ከፍተኛ ማሕበራዊ ድጎማ የተነሳ ፤ ኹል ግዜ የበጀት ጉድለት እንደ አጋጠመው ነው (It has primary deficit) ፤ ስለ እዚኽ ፦ የፈረንሳይ መንግሥት የበጀት አጠቃቀም ችግሩ ጫፍ ላይ ደርሷል ፤ ሐገሪቱን ከፍተኛ መቃወስ ውስጥ ሊያስገባት በእሚችልበት መልኩ። (Public debt rising toward 120% of GDP in 2027, combined with "Primary Deficits" independent of the economic cycle, suggests that France is nearing its Fiscal Frontier)። የፈረንሳይ መንግሥት በግዜ የማሕበራዊ ድጎማውን ካልቀነሰ ፤ አሁን 4 የሆነው የበጀት አስተዳደር ጥበብ ደረጃ ልኬት ወደ 3 ብሎም ወደ 2 ሊወርድ እና እንግሊዝ

በ2020 እንደ አጋጠማት ዓይነት የእድገት መቀዛቀዝ ውስጥ ሊያስገባት ይችላል።በእንግሊዝ በ2020 በኮቪድ ምክንያት የኢኮኖሚው አመታዊ ምርት ለ300 ዓመታት ታይቶ በእማይታወቅ መልኩ በ10% ቀነሰ ፤ አብሮ የመንግሥት ገቢ ቀነስ ፤ ነገር ግን መንግሥት ፤ ለበርካታ ዜጎች ድጎማ ማድረግ ነበረበት ይኽም የመንግሥትን ፕራይመሪ ደፍሲት (Primary Deficit) የእሚባለውን እና ወለድን ሳይጨምር መንግሥት ለማሕበራዊ ድጎማ የእሚያወጣው ወጪ ከገቢ የእሚያንስበትን አስከተለ ፤ መንግሥትም ጉድለቱን ለመሸፈን ብድር ውስጥ ገባ ፤ በእዚኽም የመንግሥት የብድር መጠን ለብዙ አስርት አመታት ታይቶ በእማይታወቅ መልኩ የአመታዊ ምርቱን 100% በላይ ሆነ ፤ ይኽንም ተከትሎ ፦ በእንግሊዝ በ300 ዓመት ታይቶ የእማይታወቅ የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ (Recession) ፣ ከፍተኛ መጠን ያለው ስረዓጥነት እና ከፍተኛ ጠቅላላ ምርታማነት መዳከም (Productivity Scarring) አስከተለ ፤ ይኽም የእንግሊዝ ኢኮኖሚ በውስጡ የነበረውን የተሰወረ ደካማነት ያጋለጠ ነበር ።

## 4.6 ኳታር

በቀኝ ግዛቱ ዘመን ኳታር በፐርዥያ ገልፍ (Persian Gulf) ላይ ለመከላከል አመቺ የሆነ ቦታ ላይ መሆኗ ፣ ከእስልምናው ዓለም ጋር ባላት ታሪካዊ ቁርኝት ምክንያት ፣ እና ለንግድ ያላት ጠቀሜታ ፤ እንደ ኦቶማን እና እንግሊዝ ላሉ ቀኝ ገዢዎች ጠቀሜታዋን ከፍ ስለ አደረገ ፤ ለቀኝ ገዢዎች ተፈላጊ ቦታ ነበረች።

የተፈጥሮ ጋዝ እና ነዳጅ (Hydrocarbons) ሳይገኝባት በፊት የኳታር ዋነኛ የኢኮኖሚ አውታር የተፈጥሮ ዕንቁ (natural pearl trade) ንግድ ነበር። ዕንቁውን ከባሕር ውስጥ እየሰረጎዱ (diving) በማውጣት እና እርሱን ለሽያጭ ማዋል ፤ ለኳታር ብቻ ሳይሆን የፐርዢያ ገልፍ የእሚባለውን አከባቢ ከሕንድ ጋር የእሚያገናኝ እና ለአከባቢው ነዋሪዎች የገቢ ምንጭ ነበር።

በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ሚክሞቶ ካኪቺ (Mikimoto Kōkichi) በእሚባል ተመራማሪነት ጃፓኖች ዕንቁውን በፋብሪካ ማምረት ሲጀምሩ ፤ የተፈጥሮ ዕንቁውን ካባሕር ውስጥ አውጥቶ በመሸጥ ላይ የተመሰረተው የኳታር ኢኮኖሚ ፈረሰ። በ1920 እና 1930 ሰው ሠራሽ ዕንቁዎች የዓለምን ገበያ አጥለቀለቁት ፤ ይኽም በዕንቁ ንግድ ላይ የተመሠረተውን የኳታርን ንግድ በከፍተኛ ደረጃ ጎዳው። ኳታር ንግዷ በመጎዳቱ ፤ ሐገሪቱን የከፋ ድህነት ውስጥ አስገባት ፤ ኢኮኖሚዋም በዋናነት ፦ ከእጅ ወደ አፍ የሆነ አሳ ማጥመድ ፣ ትናንሽ የችርቻሮ እና በጀልባ የእሚደረግ ንግድ ሆነ።

ይኽ የኳታር የኢኮኖሚ ገጽታ መለወጥ የጀመረው በ1939 አንግሎ ፐርዥያን (Anglo-Persian Oil Company) የእሚባለው የእንግሊዙ ኩባንያ በኳታር ነዳጅ ሲያገኝ ነው። ምንም እንኳን ነዳጅ የማምረቱ ነገር ከፍተኛው ደረጃው ላይ እስከ ኹለተኛው የዓለም ጦርነት መጠናቀቅ (1945) ድረስ ቢዘገየም ፤ ትንንሽ የነዳጅ ምርት ኤክስፖርት ማድረግ ግን ወዲያው ጀምሮ ነበር። የነዳጁም ገቢ ፦ የመንገድ ፣ የትምሕርት ቤት እና ሆስፒታል ግንባታዎችን በመሰረተ ልማት በኩል አስቻለ።

የተፈጥሮ ኃብቱን አውጥቶ የመሸጡ ነገር የኳታርን ኢኮኖሚ አሳደገው ሆኖም ፤ የኢኮኖሚው ተቋማዊ አቅም ግን በድሮው ደካማ ደረጃ ላይ ነው የነበረው። ከነዳጅ ሽያጭ የሚገኘው ገቢ ፤ የታኒ ቤተሰብ (House of Thani) በሚባለው በገዢው ስረወ መንግሥት ነበር የሚተዳደረው ፤ እንደ ሐገር በተቋም ከሚተዳደር ይልቅ። ይኽም ማለት ኢኮኖሚውን የማዘመን ነገር ፤ በዋናነት የሚመነጨው አምባገነናዊ ከሆነው ዘውዳዊ ስረዓት እንጂ በሐገሪቱ ኢኮኖሚ የሚያንቀሳቅሱ ሰፊ ቢሮክራሲያዊ አሠራሮች ስለ ነበሩ አይደለም።

ኹለተኛው እና ትልቁ የኳታር ኢኮኖሚ ለውጥ የመጣው በሐገሪቱ ሰሜናዊ ክፍል በዓለም ላይ ትልቁ ክምችት ያለው የተፈጥሮ ጋዝ ክምችት ሲገኝ ነው። የእዚኽ የተፈጥሮ ጋዝ ልማትም ኳታር ከእንግሊዝ ነጻነቷን በ1971 ስታገኝ ፤ እንደ፡- ኤክሰንሞቢል ፣ ሼል እና ቶታል (ExxonMobil, Shell, and TotalEnergies) ካሉ ዓለም ዓቀፍ የነዳጅ ኩባንያዎች ጋር በመሥራት በመጠናከር ፤ ኳታር ከፍተኛ ፈሳሽ የተፈጥሮ ጋዝ (Liquefied natural gas - LNG)) መሠረተ ልማት መገንባት አስቻላት።

ይኽም አካኼድ ኳታርን በዓለም ላይ ትልቁ ፈሳሽ የተፈጥሮ ጋዝ ኢክስፖርት አድራጊ ሐገር አደረጋት። በተለይ ደግሞ ከአውሮፓ እና ከኤስያ ሐገራት ጋር ለረጅም ዓመታት የሚቆይ ፈሳሽ የተፈጥሮ ጋዝ አቅራቢነት ስምምነት መፈራረሟ ፤ ኢኮኖሚዋን ከሌላ የዓለም ኢኮኖሚ ጋር በማስተሳሰር ፤ ኢኮኖሚውን ከነዳጅ ወደ ፈሳሽ ተፈጥሮ ጋዝ ተደጋፊነት አሸጋገረው።

ከእዚኽ የሚገኘው ገቢ ከፍተኛ የሆነ የሐገር ልማት አስከተለ። ኳታር ዘመናዊ ፡- አየር መንግዶች ፣ ወደቦች ፣ አውራጎዳናዎች (Highways) እና አሁን በኳታር ዋና ከተማ ዶሐ (Doha) የሚታዩትን ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ገነቡ። በተለይ የትምሕርት ከተማ (Education City) ባሉት ቦታ ፤ የትምሕርት እና የዕውቀት ማዕከላት ገነቡ ፤ የአሜሪካዎቹ እንደ ጆርጅታወን እና ካርኒጊ (Georgetown University and Carnegie Mellon University) ዩኒቨርስቲዎች በእዚያ ቅርንጫፍ ከፍተዋል።

ከእዚኽም ጋር አብረው ፤ የኳታር የኢንቨስትመንት ፈንድ (Qatar Investment Authority) የሚባል እና ከነዳጅ የሚገኘውን ገቢ ፤ የተወሰነውን ወስዶ በዓለም ላይ በተለያየ ቦታ የባንኮችን ሼር የሚገዛ ፣ ሪል እስቴት የሚገዛ ፣ በመሠረተ ልማት እና በስፖርት ላይ ኢንቨስት የሚያደርግ ፤ ፈንድ ፈጠሩ።

ለምሳሌ ፡- በ2022 የዓለም ዋንጫ ላይ ኢንቨስት ያደረገው ይኼ ፈንድ ነበር ፤ ምንም እንኳን ይኽ ኢንቨስትመንት ከቀጥታ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ ይልቅ የኳታርን ገጽታ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ከፍ በማድረግ የሚያገኘው ተዘዋዋሪ ጥቅም ቢበልጥም።

በእዚኽ መልኩ ከፍተኛ የመሠረተ ልማታ ግንባታ ፣ የሰው ኃይል ልማት ፣ እና በአንድ ዘርፍ ብቻ ሳይሆን በሌሎች በርካታ ዘርፎች ኢኮኖሚዋን በማስፋፋቷ (Because they have attempted to diversify their economy) ፤ ኳታር የተቋማዊ አቅሟን በጣም ከፍ አድርጋለች።

ምንም እንኳን አሁን በኳታር ውስጥ በጠቅላላ የሚኖረው ሕዝብ 3.2 ሚልዮን ቢሆንም ፤ ከእዚያ ውስጥ የኳታር ዜጋ የሆነው 330, 000 ነው። አብዛኛው የኳታር ነዋሪ ፤ ኤክስፓትርየት (Expatriate) የሚባል እና ከውጭ ሐገር ለሥራ ወደ ኳታር የመጣ ነው።

የኳታር ዜጎች ከፍተኛ የነፍስ ወከፍ ገቢ አላቸው ፣ በጣም ሰፊ የማሕበራዊ ድጋፍም በመንግሥት ይደረግላቸዋል ፤ ይኽም የድጎማ አካኼድ ሕብረተሰቡ ከሐገራዊ ኃብቱ እንዲ ቋደስ ሲያደርግ ፤ መንግሥትም የሕዝቡን ታማኝነት ለመግዛት ይጠቀምበታል።

ስለ እዚኽ ፦ የኳታር ስረዓት ፤ ከነዳጅ እና ከተፈጥሮ ጋዝ ኃብት ሽያጭ የሚገኝ ገቢን ወስዶ ለሕዝቡ በማከፋፈል ፤ ዴሞክራሲያዊ መሆን ሳያፈልገው ፤ ማሕበራዊ መረጋጋትን መፍጠር አስችሎታል።

በኢኮኖሚያዊ ቋንቋ እንግለጸው ካልን ፤ ኳታር ከፍተኛ መጠን ያለው ከተፈጥሮ ኃብት ፤ በተለይ ከፈሳሽ የተፈጥሮ ጋዝ ሽያጭ የሚገኝ ገንዘብን በመውሰድ በጣም ፈጣን ብሔራዊ ዕድገት ያስመዘገበች ሐገር ሆና እናገኛታለን።

በተለይ የኳታር ልቀት የሚታየው ፤ ከእዚኽ የተፈጥሮ ኃብት የሚገኘውን ከፍተኛ ገቢ ፦ መሠረተ ልማት ላይ በማዋል ፣ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ኢንቨስት በማድረግ እና የሐገሯን ገጽታ ግንባታ ላይ በመሥራት ፤ በአብዛኛው በተፈጥሮ ኃብት ሽያጭ ላይ ኢኮኖሚያቸውን የሚገነቡ ሐገራት የሚያጋጥማቸውን እና የተፈጥሮ ኃብት ርግማን (Resource curse) እና የተቋማት መበስበስ መሻገር በመቻሏ ነው።

እንግዲኽ ኳታር እንዴት አድርጋ ከፍተኛ ገቢ ወዳለው ሐገር ደረጃነት ገባች ካልን ፤ ማሕበረሰቡን የኢኮኖሚ ተሳታፊ እና ተጠቃሚ በማድረግ የፈጠራ አቅምን በመገንባት ሳይሆን (Broad-based Innovation Sieve) ፤ በዋነኝነት በአንድ የተፈጥሮ ኃብት ፦ ፈሳሽ የተፈጥሮ ጋዝ ላይ በመመሥረት በመሆኑ ፤ የምርመራው ማሽን የምርመራ ውጤት ፤ የኳታርን ኢኮኖሚ ተቋማት ፤ የዘመናዊ እና የኋላ ቀር ኢኮኖሚ መልክ ያለው ፤ ባለ ኹለት መልክ ("Dual-Track") አድርጎ እና በፈጠራ ሳይሆን በጣም ከፍተኛ መጠን ያለው በተወሰነ ቦታ የተከማቸው ኃብት ያለበት የኃብት ምሽግ (Hyper-Concentrated Wealth Vault) ሆኖ አግኝቶታል።

### 1. የግል ንብረት (አንኳር)

| **አመላካች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **ባለቤትነት** | ነዳጁም የተፈጥሮ ኃብቱም 100% የመንግሥት ንብረት ነው። የሪል ስቴት(Real | **1** | በጣም ስትራቴጂክ (Most strategic ) የሆኑት የሐገሪቱ ኃብቶች በመንግሥት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | estate) ለውጭ ዜጎች በተለያየ መልክ እና ደረጃ የእሚፈቅድ ሕግ አንድ 2004 ሌላ ደግሞ በ2020 አውጥተዋል። | | ንብረትነት የተያዙ ናቸው ፤ የግል ንብረት የእሚፈቅድባቸው ልዩ ዞኖች አሉ። |
| **ውርስ** | ለጊዢው መደብ እና ለትላልቅ የመንግሥቱ አጋር ለሆኑ የውጭ ባለኃብቶች የውርስ ስጋት የለም ፤ ሆኖም ለአንስተኛ እና መካከለኛ ንግዶች አስተዳደራዊ ስጋት አለ። | **1** | የንብረት ጥበቃ ጠንካራ ነው ሆኖም “ዋስታ” ("Wasta") በእሚሉት እና ማንን ታውቃለህ በእሚል ላይ የተመሠረተ ነው ።  በተቋማዊ መንገድ  ነጻ እና ገለልተኛ ሕግ ላይ ከመመሥረት ይልቅ በትውውቅ ላይ ይመሠረታል። |
| **ሕጋውድድር(Contestability)** | የሐገሪቱ ዋነኛ የእሚባሉት መስኮች ገዢው ቤተሰብ እና በመንግሥት ንብረትነት የተያዙ እና የኃብት ውድድሩ ለኹሉም እኩል ያልሆነ ነው። | **0** | መንግሥት ስትራቴጂክ ሞኖፖሊ (State’s strategic monopolies) በእሚላቸው መስክ ፤ አዲስ ተወዳዳሪ መሳተፍ አይችልም። |
| **የሠራተኛ ነጻነት ( Labor Freedom)** | ኳታር ከፈላ (*Kafala)* የእሚባለውን የስፖንሰርሺፕ | **1 (መካከለኛ)** | የሠራተኛ ነጻነት ዝቅተኛ ከእሚባልበት ደረጃ ከፍተኛ መሻሻል |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | (sponsorship) ቅጥር አግዳለች። ሠራተኞች ተቃዋሚ የለም የእሚል ሰርተፍኬት ሳያቀርቡ ሥራ መቀየር ይችላሉ። ሆኖም አሁንም 2026 ቢሆን ፤ አስተዳደራዊ የሆኑ እና ጥሎ መኮበልል በእሚል የእሚቀርቡ ክሶች በቤት ሠራተኞች አከባቢ ብዙ ነው።. | | አሳይቶ መካከለኛ ደረጃ ላይ ገብቷል። አሁንም ቢሆን ግን ሠራተኞች እንደ አሻቸው ሥራ መቀየር ይችላሉ የእሚል ሕግ ቢኖሩም ፤ በተግባር ግን የተለያዩ ችግሮች አሉ። |

**የአመላካቾቹ አማካይ: 0.75 → በኳታር የግል ንብረት የእሚከበረበት አግባብ ልኬት: 2**

**2. የንብረት ተንቀሳቃሽነት (አጥዳፊ)**

| **አመላካች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የውጭ ዜጋ ባለቤትነት** | ለረጅም ግዜ ከኳታር ዜጋ ጋር በሽርክና ሆኖ የኳታሩ ዜጋ 51% ድርሻ እንዲኖረው ግድ ነበር ፤ ከ2019 ወዲኽ ግን በአብዛኛው መስክ የውጭ ዜጋ 100% ባለቤት መሆን ይችላል። | **1** | ባለፈው 5 አመት ለውጭ ዜጋ ኢኮኖሚውን በመክፈት ረገድ ከፍተኛ ለውጥ አለ ፤ ሆኖም ለአብዛኛው የባለፈው 40 ዓመት ለውጭ ዜጋ አመቺ አልነበረም። |
| **የመሬት ገበያ** | ዘ ፐርል ፣ ሊዩሴል (The Pearl, Lusail) በእሚባሉት “ነጻ ዞኖች” ብዙ ገንዘብ የእሚንቀሳቀስበት የመሬት ገበያ አለ ፤ “ከነጻ | **1** | ኹለት መልክ ያለው (Dual-track) አሠራር በመኖሩ ፤ መሬት በመላ ሐገሪቱ የብድር ማስያዣ በመሆን ካፒታል መፍጠር እንደ አይችል አድርጎታል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ዞኖቹ" ውጭ ግን ክልከላ አለ። | | |
| **የካፒታል ቁጥጥር (Capital Controls)** | ምንም ዓይነት የካፒታል ቁጥጥር የለም ፤ የካታሪ ሪያል በሐገሪቱ የዶላር ክምችት ላይ እንዲመሠረት ተደርጓል ፤ ያለ ምንም ክልከላ ወደ ማንኛውም የሌላ ሐገር ገንዘብ መለወጥ ይችላል። | **2** | ለበርካታ አስር አመታት ያለ ምንም ክልከላ ካፒታል ሲንቀሳቀስ ነበር። |
| **የስቶክ ገበያው ከኢኮነሚው አመታዊ ምርት (Stock Market Size) አንጻር** | የኳታር የስቶክ ገበያ በጣም እንቅስቃሴ ያለው ነው ሆኖም ባንኮች እና ከመንግሥት ጋር የተያያዙ ኩባንያዎች ይበዙበታል። | **1** | ከፍተኛ ገንዘብ የእሚያወጡ ኩባንያዎች የተወከሉበት ነው ሆኖም ብዙ የግል እና ከመንግሥት ጋር ንክኪ የሌላቸው ኩባንያዎች አይገኙበትም። |
| **በቀላሉ ንግድ መጀመር እና ማቆም ይቻላል** | የኳታር ፋይናንሺያል ማዕከል (Qatar Financial Centre" (QFC)) ውስጥ ላሉ በጣም የተቀላጠፈ አገልግሎት አለ ፤ ከእዚያ ውጭ ለሆኑት ግን መጓተት አለ። | **1** | ኹለት ዓይነት አስተዳደር ስለ አለ ፤ ለተወሰኑ ዞኖች እና ለሌላው የሐገሪቱ ክፍል ፤ አንዱ ፈጣን ሌላው ጎታታ ነው። |
| **በቀላሉ ብድር ማግኘት** | በሐገሪቱ ውስጥ የአመታዊ ምርቱ 110% (credit-to-GDP ratio >110%) ቢኖሮም የ2026 መረጃ እንደ እሚያሳየው ብድሩ በአብዛኛው የተሰጠው ለሪል እስቴት እና ከመንግሥት ጋር ግንኙነት ላላቸው ኩባንያዎች ነው። | **1** | የብድር አቅርቦት አለ ሆኖም በኮላተራል/ማስያዣ ምክንያት ለነባራዊ ትልልቅ ባለኃብቶች እንጂ አዲስ ለእሚመጡ ነጋዴዎች አስቸጋሪ ነው። |

**Condition Average: 1.16 → Condition Value: 3**

**3. የሕጉ ነጻ እና ገለልተኛነት (አንኳር)**

| **አመላካች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የዳኝነት ነጻነት** | ዳኝነቱ የሞያ ስነ ምግባር ያለው ነው ሆኖ ከፍተኛ ፋይዳ ባላቸው ጉዳዮች ላይ የኢምሩ/ንጉሡ ውሳኔ ገዢ ነው። | **1** | ነጋዴ ሀ እና ነጋዴ ለ ለክርክር ከቀረቡ ዳኝነቱ ነጻ እና ገለልተኛ ነው ሆኖም መንግሥት እና ነጋድ ሀ ከሆነ እሚካሰሱት ፍርዱ ለመንግሥት ሊያደላ ይችላል። |
| **ሙስና** | በጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ሙስና አለ ("petty") ፤ ከፍ ባሉ መንግሥታዊ አገልግሎቶች ግን በጣም ግልጸኝነት አለ። | **2** | በሰሜናዊ አፍሪካ እና በመካከለኛው ምስራቅ ፤ ግልጸኝነት ኣላቸው ከእሚባሉ መንግሥታት መካከል ይመደባል። |
| **የውል ተፈጻሚነት** | በኳታር ነጻ የፋይናንሻል ማዕከል የእንግሊዝ ሕግ ስለ ሆነ እሚሠራው ጥሩ አፈጻጸም አለ ፤ በመደበኛ የፍትሀብሔር ፍርድ ቤት ግን መዳተት አለው። | **1** | ኹለት መልክ (Dual-track) ያለው የሕግ ስረዓት በመኖሩ ፤ ፈጣን አገልግሎት የእሚያገኙት የውጭ ካፒታሎች ብቻ ናቸው። |
| **በሕግ ፊት እኩል መታየት** | ግልጽ የሆነ ልዩነት አለ ፦ ዜጋው ፣ ቋሚ ዜጋው እና ቱታ ለባሽ ስደተኛ ሠራተኛው (Blue-collar Migrants) በሕግ ፊት እኩል አይታዩም። | **0** | ሕጉ በግልጽ በሰዎች የኑሮ ደረጃ መሠረት የተለያየ ተደርጎ የተቀረጸ እንጂ ለኹሉም እኩል የሆነ ስረዓት አይደለም። |
| **በፍርድ ስረዓት ውስጥ ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት** | በመደበኛ የንግድ ክርክር በጣም ዝቅተኛ ነው ፤ የዘውዱን ወይንም ብሔራዊ ጥቅም በሚነኩ ጉዳዮች | **1** | ተቋማዊ እርጋታ ከፍተኛ ነው ሆኖም የመንግሥት እጅ ኹል ግዜ ከኋላ አለ። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ፍጹም የሆነ ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት አለ። | | |
| **የፖሊስ አስተማማኝነት** | በጣም አስተማማኝ ነው ፤ ኳታር በተደጋጋሚ በዓለም ላይ ለመኖር አስተማማኝ ከሆኑ ቦታዎች ነው እምትመደበው። | **2** | ንብረት እና ማሕበራዊ ሠላም በአስተማማኝ ኹኔታ ነው በፖሊስ የእሚጠበቀው። |

**የአመላካቾች አማካይ: 1.16 → በኳታር ሕጉ ነጻ እና ገለልተኛ ከመሆን አንጻር ያለው ልኬት: 3**

**4. የንግድ ክፍትነት (አጥዳፊ)**

| **አመላካች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የታሪፍ/ቀረጥ መጠን** | የገልፍ ሐገራት ካውንስል (GCC) በጋራ የእሚጥለው ~5% ቀረጥ ነው ያለው። | **2** | ለቁሳዊ ሸቀጦች በጣም ዝቅተኛ የሆነ ሸቀጥ ነው ያለው። |
| **ከታሪፍ ውጭ ያሉ ክልከላዎች** | በጣም ጥቂት ናቸው። ኳታር የእቃ መተለለፊያ (Logistics hub ) ነች እንደ ሀማድ ወደብ እና በአየረ መንገዷ(Hamad Port/Qatar Airways) አማካኝነት። | **2** | በጣም ቀልጣፋ እና ለንግድ አመቺ የሆነ ኹኔታ ነው ያለው። |
| **የገቢ/ወጪ ንግድ ከአመታዊ ምርት አንጻር (Trade – as % of GDP)** | በጣም ከፍተኛ ነው ፤ ፈሳሽ የተፈጥሮ ነዳጅ መላክ እና ሌሎች ዕቃዎችን ኢምፖርት ማድረግ ነው በጠቅላላው የኳታር ኢኮኖሚ። | **2** | ከዓለም የኢነርጂ እና የፋይናንስ ገበያ ጋር በእጅጉ የተሳሰረ ኢከነሚ ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **በገቢ ወጪ ንግድ ላይ ገደብ ያለ ገደብ** | 2017–2021 ከፈጠረው እና አሁን ከተፈታው እገታ በስተቀር በጣም ውስን ገደብ ነው ያለው። | **2** | በታሪክ ብዙ ግዜ የንግድ ክፍት ሆኖ ነው የቆየው። |
| **የጉምሩክ ቆይታ ግዜ** | በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ (World-class) ነው ሀማድ(Hamad) ወደብ በዓለም ላይ አሉ ከአሚባሉ ቀልጣፋ የወደብ አገልግሎት ከእሚሰጥባቸው መካከል ነው። | **2** | የኳታር አንዱ ዋነኛ መወዳደሪያው ፤ ቀልጣፋ የሎጅስቲክ አገልግሎት ነው። |
| **የዓለም የንግድ ድርጅት አባልነት እና ሕግ አክባሪነት (WTO Compliance)** | ንቁ የድርጅቱ ተሳታፊ እና ሕግ አክባሪ ። | **2** | ከበርካታ ሐገራት ጋር በጥሩ ኹኔታ ለመነገድ ታጥቀው የተነሱ ናቸው። |

**የአመላካቾች አማካይ: 2.00 → በኳታር የንግድ ክፍትነት ደረጃ ልኬት: 4**

**5. የበጀት አስተዳደር (አንኳር)**

| **አመላካች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የግብር ተገማችነት** | ምንም ዓይነት የግል ገቢ/ትርፍ ግብር የለም ፤ ኹሉም የውጭ ኮርፖሬሽኖች 10% ግብር ይከፍላሉ። | **2** | በዓለም ላይ ካሉ በጣም የተረጋጋ እና ሳቢ የግብር ስረዓት ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **የበጀት ጉድለት ለመሙላት ገንዘብ ማተም (Monetary Financing)** | ገንዘብ ማተም አያስፈልግም ፤ ከፈሳሽ የተፈጥሮ ጋዝ በጣም ብዙ ትርፍ ይገኛል። | **2** | የኳታር ብሔራዊ ባንክ ለመንግሥት ገንዘብ እንዲያትም አያስፈልገውም። |
| **ብድርን ለትርፋማ አገልግሎት ማዋል (Productive Debt)** | ብድር በጥሩ ኹኔታ ለመሠረተ ልማት ነው እሚውለው ፤ ለምሳሌ፦ የዓለም ዋንጫ ማዘጋጀት ፣ በሰሜን የእሚገኘው የተፈጥሮ ጋዝ ማምረቻ ማስፋፋት ፣ ወዘተ። | **2** | የኳታር የኢንቨስትመንት አሴት QIA) ከፍተኛ መጠን ያለውን የሐገሪቱ ብድር ማስያዣ ሆኗል። |
| **የዋጋ ግሽበት** | ገንዘባቸው በዶላር ክምችታቸው ጋር ስለ ተያያዘ በጣም ዝቅተኛ ግሽበት ነው ያለው ፤ ከዶላር ዋጋ ጋር ተያይዞ። | **2** | የተረጋጋ እና ለመገመት ቀላል የሆነ ነው። |
| **የብሔራዊ ባንክ ነጻነት** | ከፍተኛ የሞያ ስነምግባር የእሚታይበት ነው ፤ ምንም እንኳን በሐገሪቱ ስትራቴጅክ ዕቅድ ድባብ ውስጥ የእሚደረግ ቢሆንም። | **1** | ብሔራዊ ባንኩ ከፍተኛ ሞያዊ ብቃት አለው ነገር ግን በምዕራቡ ዓለም እንደ ተለመደው ዓይነት ነጻነት የለውም። |
| **የመገበያያ ገንዘብ መረጋጋት** | የኳታሪ ሪያል ከ2001 ጀምሮ ከዶላር ጋር 3.64 ተተምኖ ተቀምጧል። ስለ እዚኽ፦ በኢኮነሚው ውስጥ ዶላር በዝቶ ሪያሉ ሲጠነክር የኳታር ባንክ ዶላር ይገዛል ፤ የዶላር እጥረት ሲፈጠር ዶላር ያቀርባል ምንዛሪው ኹሌ 3.64 እንዲሆን። | **2** | ለንግድ እና ኢንቨስትመንት ከፍተኛ ተገማችነት አለው። |
| **በእዳ የመያዝ ታሪክ (Default History)** | እንከን የሌለበት የመክፈል ልምድ አላቸው። | **2** | AA ደረጃ የእሚቀመጥ ለማበደር ከፍተኛ ተመረጫነት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ካላቸው ባንኮች መደዳ የእሚመደብ ነው። |
| **የበጀት አደላደል** | ከፍተኛ የሆነ ቁሳዊ ካፒታል ፈጠራ እና ሶቨሪን ፈንድ ላይ የእሚደረግ ኢንቨስትመንት መገለጫው ነው።(Heavy investment in Physical Capital and Sovereign Wealth) | **2** | ኳታር እንደ ብራዚል እና ፈረንሳይ ካሉ ሐገራት በተለየ ከፍጆታ ይልቅ ኢንቨስትመንትን ታስቀድማለች። |

**የአመለካቾች አማካይ: 1.87 → በኳታር የበጀት አስተዳደር ጥበብ ያለበት ደረጃ ልኬት: 4**

**በባለፈው 40 ዓመት ከአምስቱ ኹኔታዎች አንጻር የኳታር ውጤት**

| ሐገር | ኹኔታዎች | ልኬት |
|---|---|---|
| ኳታር | **የግል ንብረት (አንኳር)** | **2** |
| | **የንብረት ተንቀሳቃሽነት (አጥዳፊ)** | **3** |
| | **የሕጉ ነጻ እና ገለልተኛነት (አንኳር)** | **3** |
| | **የንግድ ክፍትነት (አጥዳፊ)** | **4** |
| | **የበጀት አጠቃቀም ጥበብ (አንኳር)** | **4** |

**የምርመራ ውጤት: ኳታር**

**ፍረጃ: ከፍተኛ ገቢ ያለው ኢኮኖሚ** (የኪራይ ሰብሳቢዎች ውጤታማ ምሳሌ)

- **የአንኳር ኹኔታዎች ትንተና (Core Analysis):** ኳታር ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ የኃብት ምሽግ ነች (Qatar is a "Wealth Vault" of the highest order)። ይኽንን የከፍተኛ ገቢ ሐገርነት ደረጃ እንድትጠብቅ ያስቻላት ፤ በንግድ ክፍትነት እና በበጀት አስተዳደር ጥራት ከፍተኛውን ልኬት 4 ያላት በመሆኑ ነው። ብዙ የተራቀቀ የፈጠራ ወንፊት አያስፈልጋትም ምክንያቱም

የእንግሊዝን ኮመን ሎው በነጻ የፋይናንሻል ማዕከሏ (English Common Law in its Qatar Financial Center) በመጠቀም ከፍተኛ የውጭ ካፒታል መሳብ ስለ እምትችል።

- **የኹለት መልክ ኢኮኖሚ መጥመድ (The "Dual-Track" Trap):** በኳታር የሕጉ ነጻ እና ገለልተኝነት ከንብረት ተንቀሳቃሽነት ጋር አብሮው **(3)** ቢያገኙም ይኸ የተጠቅላላ ኹኔታ ነው እንጂ ወደ ውስጥ ሲገባ አንድ አንዴ 1 ሌላ ግዜ ደግሞ 4 የእሚሆኑ ናቸው። የውጭ ሐገር ዜጋ ለሆነ ቢልየነር ወይንም የፈሳሽ የተፈጥሮ ጋዝ ኩባንያ ውጤቱ **4።** ለስደተኛ ሠራተኛ ወይንም ለሐገሬው አነስተኛ እና መካከለኛ ነጋዴ ውጤቱ **1** ነው። ይኸም የተቋማት ባለ ኹለት መልክነት ፤ በሐገሪቱ ውስጥ ከነዳጅ እና ከተፈጥሮ ጋዝ በተለየ በሌላ መስክ ላይ የተሠማራ የፈጠራ ሥራ (It is discouraging innovation) እንደ አይሆን ግርዶሽ ሆኗል።

- **የፈጠራ ማጥለያ ወንፊት (Innovative Sieve Filter):** ኳታር የፈጠራ (*Innovation*) ሐገር አይደለችም። የእምትታወቅበት መለያዋ የኢንቨስትመንት መዓከልነት ነው (Investment Pool)። ሕጋዊ የሆነ የንብረት ውድድር Contestability (0) እንዲኖር ከማድረግ ይልቅ ፤ ጠንካራ የበጀት አስተዳደር ጥበቧን (Fiscal Discipline (4)) በመጠቀም ፈጠራን(innovation) ከውጭ ሐገር ትገዛለች ፦ የትምሕርት ከተማ ፣ የቴክኖሎጂ ማዕከል ፣ ወዘተ(Education City, Tech Hubs) በመገንባት።

- **የማስጠንቀቂያ ደውል (The Predictive "Premonition"):** የባለፍው አምስት ዓመት አፈጻጸም (2021–2026) አዎንታዊ ነው። ከፈላ (Kafala) የእሚባለውን የሠራተኛ መቅጠሪያ ስረዓት በወረቀት መሻሩ እና ነጻ የግል ንብረት ባለቤትነት መፈቀዱ ፤ ኳታር ከኃብት ምሽግ ከሆነ ኢኮነሚነት (Wealth Vault) ወደ ተንቀሳቃሽ የፈጠራ ኢኮነሚ ለመሆን ሽግግር እያደረገች እንደ ሆነ ያሳያል። ሆኖም የንብረት ባለቤትነት ደረጃው እንዲህ ዝቅ እንደ አለ በቀጠለበት እና ከግለሰባዊ ክብር ጋር በተያያዘበት ኹኔታ ፤ በሐገሪቱ ውስጥ በእሚገኙ ጥቂት ባለኃብት ከፍተኛ ተፅዕኖ ("Oligarchic Ceiling") ሌሎች አዲስ እሚፈጠሩ ባለኃብቶችን እንደ አያድጉ አድርጎ እንደ ከለከለ ነው እሚቆየው።

## 4.7 ሲንጋፖር

የሲንጋፖር ዘመናዊ ጉዞ ከጂኦግራፊያዊ አቀማመጧ ጋር ይያያዛል። ጥልቅ እና ለመርከብ ማቆሚያነት የእሚመቸው የባሕር በሯ ለወቅቱ የእንግሊዝ ኢምፓየር አስፈላጊ ሲያደርጋት ፤ በ1965 ደግሞ ከማሌዥያ ተገፍታ መውጣቷ የህልውና አደጋ ጋርጦባት ነበር ፤ ምክንያቱም ፦ ከአመቺ ወደቧ ውጭ ፤ ምንም የተፈጥሮ ኃብት የሌላት ረግረጋማ ቦታ እና ከጉልበት ሥራ ውጭ ብዙም ሞያ የሌላቸው ነዋሪዎች የሞሉባት ደሴት ነው የነበረችው።

ስለ እዚኽ ፡- የመርከብ መግቢያ እና መውጫ በመሆን የእምታገለግል ፤ ከጎማ እና ከቲን ንግድ በስተቀር ሌላ የኢኮኖሚ አቅም የሌላት በመሆኗ ፤ ባለ ሁለት አሀዝ የሥራ አጥነት መጠን እና በጣም ስር የሰደደ ድህነት ነበረባት።

### የድሆችን ብሔራዊ መዝሙር መተው : ከተከላካይነት በብዙ ሐገራት ለእሚነገዱ ዓለም ዓቀፍ ኩባንያዎች በር ወደ መክፈት

ሲንጋፖር እራሷን መለወጥ የቻለችው ፤ ግሎባል ሳውዝ (Global South) የእሚባለውን እና የዓለማችን ድሆች ሐገራት የእሚካተቱበትን ቡድን ያቆረቆዘውን እና በፍቅር እንደ ብሔራዊ መዝሙር የእሚዘምሩትን ፤ ከውጭ እምናስገባቸውን ዕቃዎች እዚኽ በእሚመረቱ ምርቶች እንተካ ("Import-substitution") የእሚለውን መርኽ በመተው ነው።

የሲንጋፖር ጎረቤቶች ፤ በኢኮኖሚያዊ ብሔርተኝነት እና በፖሊሲ ነጻነት ስም በራቸውን ለዓለም ዓቀፉ ካፒታል ሲዘጉ ፤ የሲንጋፖር አመራሮች በተለይ ደግሞ ሊ ኳን የው እና ዶ/ር ጎህ ኬንግ ስዊ (Lee Kuan Yew and Dr. Goh Keng Swee) - ከሶስተኛ ዓለምነት ጎራ ለመውጣት ከአንደኛው ዓለም ሐገር ጋር መቆራኘት እንደ እሚያስፈልግ ገባቸው።

በእጃቸው ላይ የእሚገኘው ብሔራዊ መረጋጋት ከዝቅተኛ ግብር ጋር አያይዘው በዓለም ላይ ላሉ በቴክኖሎጂ ምርት ከፍተኛ ደረጃ ላይ (High-tech manufacturing) ለደረሱ ፋብሪካዎች በመክፈት ፤ በአንድ ግዜ ጎረቤቶቻቸውን ተሻግረው ከአደገው የዓለም ክፍል ጋር መነገድ ጀመሩ። መጀመርያ ቴክሳስ ኢንስትሩመንትስ (Texas Instruments) የእሚባለው ታዋቂውን የአሜሪካውን የኤልክትሮኒክስ አምራች በመሳብ ጀመሩ እና ቀስ በቀስ ሌሎች በርካታ ዓለም ዓቀፍ ኮርፖሬሽኖችን (Multinational Corporations (MNCs) )መሳብ ቻሉ።

ይኽም አካኼድ የቢንቢ (Mosquito-ridden) ልዩ መራቢያ ዞን የነበረችውን ረግረጋማዋን ሲንጋፖር የዓለም ኤሌክትሮኒክስ አምራች ኩባንያዎች መራቢያ አድርጎ ቀየራት።

### ኹለተኛው ለውጥ ፡- ከፋብሪካ እና የገንዘብ መተላለፊያ ማዕከልነት (The Pivot: From Factory to Financial Synapse)

ሲንጋፖር ዝቅተኛ የሕዝብ ቁጥር ያላት በመሆኑ እና በፋብሪካ መስፋፋት ምክንያት ሐገራዊ ኢኮኖሚያዋ አድጎ የደሞዝ ክፍያዋ ስለ ጨመረ ፤ በርካሽ እና በርካታ ቁጥር ባለው የጉልበት መጠን ፤ የዓለምን ትላልቅ አምራቾች ስባ እራሷን አምራች ማድረግ ብዙም ርቀት ሊወስዳት አልቻለም ። ነገር ግን ይኽ ገደብ አላቆማትም ፤ ይልቁንም ልክ የዓለምን ትልልቅ አምራቾች እንደ ሳበችው ፤ የዓለምን ትልልቅ ባንኮች እና ፈንድ ማንጀሮች (Fund Managers) ወደ መሳብ ገባች።

ከሲንጋፖር የዕድገት ስልት በስተጀርባ ያለው አስተሳሰብ አንድ እና ተመሳሳይ ነው ፡- በኢኮኖሚያዊ ብሔርተኝነት ስም በርን ለዓለም ካፒታል ዝግ ከማድረግ ይልቅ ፤ ለዓለም ካፒታል አመቺ ምህዳር በመፍጠር የዓለምን ካፒታል ወደ ሐገር ውስጥ በመሳብ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን አረጋገጥ የእሚል ነው ።

ምክንያቱም ፦ አንድ ሐገር ፤ በሩን ለዓለም ዓቀፍ ፍይናንሻል ካፒታል ሲከፍት የእሚከተሉትን ዓይነት ብዙ ጥቅሞች ያገኛል፦

1. **የአገልግሎት ክፍያ:** በሲንጋፖር ባንክ በኩል የትኛውም ዓይነት የገንዘብ እንቅስቃሴ (Transaction) ሲደረግ — የውጭ ምንዛሬ ፣ ከአንድ ባንክ ወደ አንድ ባንክ ዝውውር ወይንም ክፍያ ሲፈጸም ፤ የሲንጋፖር ባንኮች የአገልግሎት ክፍያ ያገኛሉ።

2. **ከፍተኛ የገንዘብ መጠን (Liquidity Pools):** አንድ ሐገር እራሱን ለዓለም ዓቀፉ የባንክ ስረዓት አመቺ እና ክፍት አድርጎ እራሱን የገንዘብ ማዕከል በማድረግ ብዙ ነጋዴዎች በእርሱ በኩል ገንዘብ እንዲለዋወጡ ሲያደርግ ተፅዕኖውን በማጉላት ሌሎችን ስቦ ያመጣል።

3. **የእውቀት ሽግግር (Expertise Transfer):** የዓለም ዓቀፍ ባንኮች በአንድ ሐገር በነጻነት ሲንቀሳቀሱ ለሐገር ውስጥ ባንክ ሞያተኞች ዓለም ዓቀፉን የባንክ አሠራር ያስተምራሉ።

4. ***ገጽታ ግንባታ* (Systemic Credibility):** አስተማማኝ ፣ በአግባቡ የእሚመራ እና መልካም ስም ያለው የገንዘብ ስረዓት ሌሎች በርካታ ዓለም ዓቀፍ ነጋዴዎችን ይስባል።

5. **ተጓዳኝ መስኮችን ያሳድጋል (Ancillary Growth):** አብሮ የሕግ ፣ የሒሳብ ሥራ እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መስኮች ባንኮቹን ለማገልገል እንዲያድጉ ያደርጋል።(Creating a demand for legal, accounting, and IT services.)

**የኤስያን ዶላር መሳብ እና የሲንጋፖር የኢኮኖሚ ባትሪ ማድረግ (The "Asian Dollar" and the Sovereign Battery)**

የዓለምን ባንኮች በመሳብ ያገኘችውን ደረጃ ለመጠበቅ ሲንጋፖር የኢስያን ዶላር ገበያ (Asian Dollar Market) ፈጠረች። ይኽንንም ለማድረግ ፤ የሲንጋፖር ባንኮች ከውጭ ሐገር የእሚመጣ ዶላር ተቀብለው ሲይዙ ምንም ዓይነት የሪዘርቭ ሪኳየርመንት (reserve requirements) እንደ አይኖር እና በእሚያስከፍሉት ወለድ ላይ ግብር እንደ አይከፍሉ በማድረግ ሲንጋፖር እራሷን ፤ ኤስያ የዓለምን ካፒታል የእሚገዛበት መስኮት አደረገች። በእዚኽ ረገድ ያስቀመጠችው አንድ ገደብ ብቻ ነበር እርሱም ፤ ባንኮቹ ኹሉንም ዓይነት ገንዘብ መግዛት እና መሸጥ ይችላሉ ፤ ከሲንጋፖር ዶላር በስተቀር ፤ ምክንያቱም ፦ የዓለም ዓቀፉ የገንዘብ ገበያ መረባበሽ የሐገሪቱን የገንዘብ ስረዓት እንደ አይረብሽ።

በእዚኽ ኺደት በሐገሪቱ የእሚፈጠረውን ትርፍ በአግባቡ የእሚጠቀም “ብሔራዊ ባትሪ” ("Sovereign Battery") ፈጠረች። ኹላችንም እንደ እምናውቀው ባሪ ትርፍ ኃይል ወስዶ እራሱን ይሞላል ፤ የሞላውን አጠራቅሞ ይይዛል በኋላም ኃይል ሲፈለገ ከአጠራቀመው ይሰጣል።

ሲንጋፖርም ቴማሴክ ሆልዲንግ (Temasek Holdings 1974) የሚባል እና የሲንጋፖር መንግሥት የኢንቨስትመንት ኮርፖሬሽን (GIC[9] 1981)) የሚባሉ ተቋምን አቋቋመች እና ከእዚኽ የኢስያ ዶላር ስርዓት የምታገኘውን ትርፍ በተለያየ ቦታ ኢንቨስት ማድረግ ጀመረች።

ይኽ እያንዳንዱ ዜጋ በግድ እንዲቆጥብ ከሚገደድበት የሐገሪቱ ፕሮቪደንት ፈንድ ( Central Provident Fund (CPF)) ጋር ተዳምሮ ፤ እያንዳንዱን የሲንጋፖር ዜጋ የሐገሪቱ የካፒታል ዕድገት ባለድርሻ አደረገው።

**<u>እንደ እዚኽ በማድረግ ፤ ሲንጋፖር የተፈጥሮ ኃብት ማጣት ፤ ደመ ነፍሳዊ ነፍስ አድን መንገድ ሆኖ ፤ አንድን ሐገር አምስቱን ኹኔታዎች እንደ ታሻሽል ካደረጋት ፤ የልዕለ ኃይልነት ልዩ ምስጢር እንደ ሆነ ማሳየት ቻለች።</u>**

የቀረው የሶስተኛው ዓለም ሐገር ፤ ዓለም ዓቀፍ ካፒታል አድኖ ሊገነጣጥለኝ (Predator) ነው ብሎ ሲፈራ ፤ ሲንጋፖር እንደ እድገት ነዳጅ አየችው።

ሲንጋፖር የውጭውን ዓለም ኃብት እና ችሎታ ስቦ ወደ ሲንጋፖር የሚያስገባ ቀጫጭን መምጠጫ (Capillary Engine) በመገንባት እና ወደ ሐገሯ የዓለምን ካፒታል እና ችሎታ በመሳብ ፤ የሶስተኛው ዓለም ሐገራት የሚሰቃዩበትን ፤ የተፈጥሮ ኃብት እርግማን (Resource Curse) እና ተቋማዊ ውትፍትፍነትን (Institutional Clog) የሚፈጥረውን ተከላካይነት አለፈችው ፤ ለትንሽነት ብቸኛው መፍትሔ ክፍትነት መሆኑን በማሳየት።

የምርመራ ማሽኑ ሲንጋፖርን በተቋም ጥራት አንደኛ ደረጃ የወርቅ ተሸላሚ አድርጎ ነው የሚያገኛት።

ሲንጋፖር ብዙም ባልተለመደ መልኩ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያለው መንግሥት ፤ ስልጣኑን ተጥቅሞ የፈጠራት ፤ በአምስቱም ኹኔታዎች ከፍተኛ የሚባለውን ውጤት 4 ለተከታታይ በርካታ አመታት ያስመዘገበች ነጻ ገበያ ነች "State-Directed Liberalism"።

ሲንጋፖር ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ የፈጠራ ማጥለያ (Innovation Sieve) ኢኮነሚ የገነባች ናት ፤ ምንም እንኳን ይኽ የፈጠራ ማጥለያ ስርዓት በሐገሪቱ ሊህቃን የተገነባ ቢሆንም።

### 1. የግል ንብረት (አንኳር)

| **አመላካች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| | | | |

[9] GIC – Government of Singapore Investment Corporation

| | | | |
|---|---|---|---|
| **ማብራሪያ** | የግሉ መስክ ዋነኛ የኢኮኖሚው ሞተር ቢሆንም መንግሥት በቴሜሰክ እና ጂኤልሲ( via Temasek/GLCs) በእሚባሉት የኢንቨስትመንት ፈንዶቹ አማካኝነት በባንኪንግ፣ በቴሌኮም እና በኃል ማመንጨት መስክ ከፍተኛ ድርሻ አለው። ከ90 በመቶ በላይ የእሚሆነው የሐገሪቱ መሬት ፤ በግል ባለቤትነት ከእሚያዝ ይልቅ በ99 ዓመት ሊዝ ነው የተያዘው። | **1 (መካከለኛ)** | አብዛኛው መስክ ውስጥ በግል ባለ ኃብትነት መሰተፍ ይቻላል ፤ ሆኖም ዋነኛ የእሚባለው ኃብት (መሬት) እና ስትራቴጂክ ሴክተሮች (strategic sectors) መንግሥት በከፍተኛ ደረጃ ድርሻ አለው ወይንም ሙሉ በሙል በባለቤትነት ይይዛል። |
| **ውርስ** | መሬት የመረከብ ሕግ (The Land Acquisition Act (LAA)) ለመንግሥት ለሕዝባዊ አገልግሎት በእሚል መሬት የመውረስ ከፍተኛ ስልጣን | **1 (መካከለኛ)** | በወረቀት ላይ በሠፈረ ሕግ ንብረት ከለላ አለው (De jure protections) ሆኖም ከባለፈው 40 ዓመት ተግባራዊ አፈጻጸም አንጻር ስናየው ፤ ከሕጉ በተቃራኒ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ይሰጠዋል። እስከ 2007 ድረስ የካሳ ክፍያው ከገበያ ዋጋ በታች ነበር ፤ ከእዚያን በኋላ ግን በገበያ ዋጋ እንዲሆን ተሻሽሏል። ሆኖም የሕዝብ አገልግሎት የእሚለው በሰፊው የእሚተርጎም እና ለብዙ ምክንያት ንብረት እንዲወረስ የእሚፈቅድ ነው። | | መንግሥት በትጋት መሬት እሚሰበስበበት አካኼድ ነበር የእሚታየው። |
| **ሕጋዊውድድር(Contestability)** | ሲንጋፖር በጣም የተራቀቀ ሕጋዊ መዋቅር (Competition Act) እና ጠንካራ የአዕምሮ ንብረት ጥበቃ አላት። ሆኖም ከመንግሥት ጋር የተያያዙ እንደ ጂኤልሲ (GLCs) ዓይነት ኩባንያዎች ሌሎቹን ገፍተው የማስወጣት ኹኔታ ("crowding out") ሊፈጥሩ ይችላሉ። በ2018 የወጣው የክስረት | **2 (ከፍተኛ)** | ጂኤልሲ (GLC) ቢኖርም እና እርሱን መወዳደር ከባድ ቢሆንም ፤ ጠንካራ የአዕምሮ ንብረት ጥበቃ መኖሩ እና ገለልተኛ የሆነ የዳኝነት አሠራር በመኖሩ ፤ ከዓለም ዓቀፉ ኢኮኖሚ ጋር እራሱን ባስተሳሰረው የሲንጋፖር ኢኮኖሚ ፤ ነባራዊውን ባለኃብት በውድድር አሸንፎ ለመተካት እዱሉ አለ። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ሕጉም (Bankruptcy laws) የተዋጣለት ነው ፤ በውድድር አሸንፎ ነባሩን ለመተካት (creative destruction) መመከር ይበረታታል ፤ ምንም እንኳን የመንግሥት ከሆኑት ጋር መወዳደር ትንሽ ቢያስቸግርም። | | |
| **የሠራተኛ ነጻነት** | ሲንጋፖር ለጉልበት ገበያው ከፍተኛ አመቺነት ያለው በእሚል በተደጋጋሚ ከፍተኛ ምዘና የእምታገኝ ነች። ሠራተኛ በቀላሉ መቅጠር እና ማባረር ይቻላል ፤ የሐገሪቱ መዓከላዊ የፕሮቪደንት ፈንድ (Central Provident Fund - CPF) ሠራተኞች ማሕበራዊ ዋስትናቸውን ሳያጡ በቀላሉ | **2 (ከፍተኛ)** | በጣም ውጤታማ የሆነ ፤ ሠራተኞች ጉልበታቸውን በሙሉ ባለቤትነት ይዘው ፤ ያዋጣኛል ብለው ባሰቡት መልኩ ያለ ብዙ ችግር እንዲሸጡ የእሚያደርግ ፤ የጉልበት/የሌበር ገበያ (labor market) አለ ። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ሥራ መቀየር እንዲችሉ ያስችላቸዋል። በሥራ ፈቃድ ወደ ሲንጋፖር ለመጡ ሰዎች ፤ ሥራ ሲቀይሩ የተወሰነ ቁጥጥር አለ። | | |

**የአመላካቾች አማካይ : 1.5 → በሲንጋፖር የንብረት ባለቤትነት ደረጃ ልኬት ፡ 4**

**2. የንብረት ተንቀሳቃሽነት (አጥዳፊ)**

| **አመላካቾች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የውጭ ዜጋ ባለቤትነት** | በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ታሪክ በከፍተኛ ደረጃ ለውጭ ባለኃብት ክፍት የሆነ ኢኮኖሚ። | **2** | በአብዛኛው መስክ የውጭ ዜጋ ባለቤትነት ላይ ምንም ዓይነት ክልከላ የለም ። |
| **የመሬት ገበያ** | ከፍተኛ ገንዘብ የሚንቀሳቀስበት (Highly liquid) የሊዝ ገበያ አለ (መሬቱ ባይሸጥ ሊዙ በጣም በሽያጭ ይዘዋወራል) ፤ ኮምፒወተራይዝድ የሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ እና በጣም በቀላሉ ስም ማዞር የእሚቻልበት አሠራር አለ። | **2** | የሪል ስቴት ንብረት በገበያው ውስጥ በጣም በፍጥነት እጅ የእሚቀይር በመሆኑ ብዙ ገንዘብ ይንቀሳቀስበታል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **የካፒታል ቁጥጥር (Capital Controls)** | ምንም የካፒታል ቁጥጥር የለም ፤ ሲንጋፖር በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የኃብት አስተማማኝ ማስቀመጫ ነች። | **2** | ፍጹም የሆነ ኃብት የማንቀሳቀስ ነጻነት አለ ፤ የሲንጋፖር ዶላር የእሚባለው የሲንጋፖር የመገበያያ ገንዘብ ፤ እንደ ዶላር እና ዩሮ ባይሆንም እንኳን ፤ በብዙ ብሔራዊ ባንኮች በሪዘርቭ ከረንሲነት ይያዛል። |
| **የስቶክ ገበያ መጠን (Stock Market Size)** | ኤስጂኤክስ (SGX) የእሚባለው የሲንጋፖር የስቶክ ገበያ በርካታ የዓለም ኢንቨስተሮችን የእሚያሳትፍ ነው ፤ ምንም እንኳን ከፍተኛ መጠን ያላቸው ስቶኮች የሪልስቴት ትረስት (Real Estate Investment Trusts) እና የብድር ሽያጭ ቢሆንም። | **2** | ከሐገሪቱ ዓመታዊ ምርት አንጻር ከፍተኛ መጠን ያላቸው አክስዮኖች በሽያጭ ይቀርቡበታል ፤ አብሮትም በጣም ዘመናዊ የፋይናንሻል ስረዓትም አለ እሚያግዘው። |
| **በቀላሉ ንግድ መጀመር እና ማቆም ይቻላል** | ንግድ ለማቋቋም 15 ደቂቃ ነው እሚፈጀው ፤ ሲንጋፖር ንግድ ለመጀመር ባላት ቅለት ፤ በተደጋጋሚ በዓለም ላይ አንደኛ ወይንም ኹለተኛ ነው እምትሆነው። | **2** | ንግድ ለመጀመር ያለው አስተዳደራዊ ችግር ዜሮ ነው። |
| **በቀላሉ ብድር ማግኘት ይቻላል** | ሶሥት (DBS, OCBC, UOB) የእሚባሉ ትልልቅ የሐገር ውስጥ ባንኮች የእሚወዳደሩበት የባንክ ኢንደስትሪ አለ። መንግሥት እገዛ የእሚያደርግበት ለአነስተኛ እና መካከለኛ የንግድ ድርጅቶች እስከ 90% የእሚደርስ የመንግሥት ዋስትና | **2** | ከፍተኛ የገንዘብ መጠን እና ለነባሮችም ሆነ ለአዲስ መጪ ነጋዴዎች ሰፊ ተደራሽነት ያለው የብድር ገበያ አለ። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የእሚሰጥበት (ተበዳሪዎቹ ከከሰሩ መንግሥት አብዛኛውን እዳ እርሱ ይከፍላል) እና በኤአይ(AI) ታግዞ በ48 ሰዓት ውስጥ የተበዳሪ ምዘና የእሚያልቀበት እና ብድር የእሚሰጥበት አሠራር አለ። | | |

**የአመለካቾች አማካይ: 2.00 → በሲንጋፖት የንብረት ተንቀሳቃሽነት ደረጃ ልኬት: 4**

### 3. የሕጉ ነጻነት እና ገለልተኛነት (አንኳር)

| አመለካቾች | የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም | ልኬት (0–2) | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| **የዳኝነት ነጻነት** | ዳኞቹ ከፍተኛ የሞያ ደረጃ ያላቸው እና በተለይ በንግድ ሕግ ላይ የኤክስፐርት ዕውቀት ያላቸው ናቸው። | **2** | ዓለም ዓቀፍ የንግድ ተቋማት የሲንጋፖርን ፍርድ ቤት በኤስያ እንደ እሚገኝ የገለልተኝነት ግዛት ወይንም ደሴት ነው የእሚያዩት። |
| **ሙስና** | ሙሰና ዜሮ ነው ማለት ይቻላል። የመንግሥት ሠራተኞች ጉቦ እንደ አይበሉ የገበያው ተወዳዳሪ ደሞዝ ይከፈላቸዋል። | **2** | ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል በእሚያወጣው ደረጃ (Transparency International Index) በተደጋጋሚ ዝቅተኛ ሙስና አለባቸው ከእሚባሉት ከአንድ እስከ አምት ያሉት ሐገራት ውስጥ የእሚካተት ነው። |
| **የውል ተፈጻሚነት** | ዓለም ዓቀፍ ደረጃውን የጠበቀ (World-class) ፍጥነት እና አስተማማኝነት አለው። | **2** | የሲንጋፖሩ ዓለም ዓቀፍ የግልግል ማዕከል (Singapore International Arbitration Centre (SIAC)) በዓለም ዓቀፍ ደረጃ መሪ ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **በሕግ ፊት እኩል መታየት** | በሲንጋፖር ሕጉ ፤ እንደ ማሽን በእማይሳሳት እና ወጥነት ባለው መልኩ ፤ ለሐገሩም ለውጭ ሐገርም ዜጋ በእኩልነት ይተገበራል። | **2** | በንግድ ሆነ በወንጀል ልዩ ከለላ የእሚደርግለት ምርጥ ዜጋ የለም ፤ ሕጉ ለኹሉም በእኩልነት ይተገበራል። |
| **ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት** | በኢከነሚያዊ ጉዳይ ምንም ዓይነት ጣልቃ ገብነት የለም። | **2** | ሲንጋፖር በሐገራዊ ምርትነት የእምታቀርበው ትልቁ መወዳደሪያዋ ፤ የተረጋጋ ሐገርነት እና ተገማችነት ነው። |
| **የፖሊስ አስተማማኝነት** | በጣም ከፍተኛ ነው ፤ በሲንጋፖር ወንጀል በዓለም ላይ በጣም ዝቅተኛ ከሆነባቸው አንዱ ነች። | **2** | የንብረት መብት ባለቤትነት ይከበራል። |

**የአመላካቾቹ አማካይ : 2.00 → በሲንጋፖር የሕግ የበላይነት ደረጃ ልኬት: 4**

**4. የንግድ ክፍትነት (አጥዳፊ)**

| **አመላካች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የታሪፍ መጠን** | ዜሮ ነው። ሲንጋፖር ነጻ ወደብ ነች። | **2** | ለአልኮል ፣ ትንባሆ እና መኪና ካልሆነ ምንም ቀረጥ የለም። |
| **ከታሪፍ ውጭ ያሉ ክልከላዎች** | ዝቅተኛ ነው ፤ በጤና አና በደህንነት ቁጥጥር ላይ ብቻ ያተኮሩ ክልከላዎች ናቸው ያሉት። | **2** | ምንም ዓይነት የሐገር ውስጥ ኢንደስትሪን መከላከል የእሚል ዓይነት አሰተዳደራዊ ክልከላ እንኳን የለም። |
| **የገቢ/ወጪ ንግድ ከአመታዊ** | ሲንጋፖር ዓለም ዓቀፍ አንትርፖት (**Entrepot**) | **2** | ከዓለም ዓቀፉ ንግድ ጋር የተሳሰረ ብቻ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **ምርቱ አንጻር (Trade % of GDP)** | ማለትም ፦ ዕቃ ያለምንም ቀረጥ የእሚገባበት እና የእሚወጣበት ነች። የገቢ ወጪ ንግዱ የአመታዊ ምርቱ ~300-400% (Trade-to-GDP is ~300-400%) ድረስ ይደርሳል። | | ሳይሆን በዓለም ዓቀፍ ንግዱ ላይ የተደገፈ ነው የሲንጋፖር ኢኮኖሚ። |
| **በገቢ እና ወጪ ንግድ ላይ ያለ ክልከላ** | ዓለም ዓቀፍ ማዕቀቦችን ለማስፈጸም ካልሆነ ምንም ዓይነት ክልከላ የለም። | **2** | ከፍተኛ የእሚባል ሽቀጥ የማንቀሳቀስ መብት ነው ያለው። |
| **በግሙሩክ የእሚባክን ግዜ** | **ትሬድኔት (TradeNet)** የእሚባል የጉምሩክ ሶፍትዌር በመጠቀም ፤ አብዛኛውን ዕቃ ከ10 ደቂቃ ባልበለጠ ቆይታ አጠናቆ ክሊራንስ ማግኘት ይቻላል። | **2** | ዕቃ በማስተላለፍ ቅልጥፍና ( logistical velocity) ዓለም ዓቀፍ የልቀት ምልክት (Global benchmark) ናቸው። |
| **የዓለም ዓቀፍ የንግድ ድርጅት አባልነት እና ሕግ አክባሪነት (WTO Compliance)** | አስፈላጊ አባል እና ከሕጉ አክባሪነት አልፈው ሌሎች እንዲሳተፉ ጎትጓች ናቸው። | **2** | የጸና የሕጉ አክባሪ ናቸው። |

**የአመላካቾቹ አማካይ : 2.00 → በሲንጋፖር የንግድ ክፍትነት ደረጃ ልኬት: 4**

### 5. የበጀት አስተዳደር ጥበብ (አንኳር)

| **አመላካች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የግብር ተገማችነት** | ኮርፖሬሽኖችን ዝቅተኛ የሚባል 17% ግብር ነው እሚያስከፍሉት ፤ የግብር | **2** | ለረጅም ግዜ አቅዶ ለመነገድ በጣም ሳቢ እና ተገማች ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ሕጋቸውም በጣም የተረጋጋ እና ተገማች ነው። | | |
| **የበጀት ጉድለት ለመሙላት ገንዘብ ማተም (Monetary Financing)** | በሕገመንግሥት ደረጃ የተከለከለ ነው። ሲንጋፖር ከፍተኛ መጠን ያለው ኢምፖርት እና ኤክስፖርት የእሚደረግበት ስለ ሆነ እና ያም በሐገሪቱ ገንዘብ ምንዛሪ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ስለ አለው ፤ የሲንጋፖር ብሔራዊ ባንክ ስለ በጀት ጉደልት ከእሚጨነቅ ይልቅ ስለ ምንዛሪ ማረጋጋት ነው እሚጨነቀው። | **2** | የሲንጋፖር የገንዘብ ባለስልጣን (MAS Monetary Authority) በበጀት አስተዳደር ጥበብ ልቀት በዓለም ዓቀፍ ደረጃ መሪ ነው። |
| **ብድርን ለምርታማ ተግባር ማዋል (Productive Debt)** | **የሲንጋፖር መንግሥት ምንም ዕዳ የለበትም.** የሲንጋፖር ንብረት ከተከፋይ ይበልጣል (Assets exceed liabilities). | **2** | ብድር የእሚበደሩት የካፒታል ገበያውን ለማሳደግ እንጂ ወጪ ለመሸፈን አይደለም። |
| **የግሽበት መጠን** | ባለፈው 40 ዓመት በጣም ዝቅተኛ እና የተረጋጋ ነው። | **2** | የሲንጋፖር የገንዘብ ባለስልጣን (MAS) ዋጋን የሲንጋፖር ዶላር ምንዛሪን በመቆጣጠር በተሳካ ኹኔታ ማረጋጋት ችሎበታል። (successfully anchors price expectations via the exchange rate.) |
| **የብሔራዊ ባንክ ገለልተኛነት** | የሲንጋፖር የገንዘብ ባለስልጣን (MAS) የእሚባለው ነው የብሔራዊ ባንክን ሥራ የእሚሠራው። ባለስልጣኑም ገለልተኛ እና ትኩረቱን ከፖለቲካ | **2** | ዓለም ዓቀፍ ደረጃውን የጠበቀ (World-class) ብሔራዊ ባንክ ነው ያላቸው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ተፅዕኖ በጸዳ መልኩ ኢኮኖሚ ማረጋጋት ላይ ያደረገ ነው። | | |
| **የመገበያያ ገንዘብ ርጋታ (Currency Stability)** | የሲንጋፖር ዶላር (The SGD) በዓለም ላይ አሉ ከእሚባሉ ርጋታ ካላቸው ገንዘቦች መካከል የእሚመደብ ነው። | **2** | አስተማማኝ የኃብት ማስቀመጫ እና መለኪያ ነው። |
| **መንግሥት በእዳ የተያዘበት ግዜ (Default History)** | የሲንጋፖር መንግሥት በእዳ ተይዞ አያውቅም በኤስያ በብቸኝነት ከፍተኛ የእሚባለው አስተማማኝ ተበዳሪ ሆኖ ትሪፕል ኤ (AAA credit rating) ደረጃ ያለው ነው። | **2** | እንከን አልባ የበጀት አስተዳደር ነው ያላቸው። |
| **የበጀት አደላደል** | **የሲንጋፖር በጀት፡** በተገቢ ኹኔታ ቅደም ተከተሉን አክብሮ ፡- ጥናት እና ምርምር **(**R&D) ፣ ትምሕርት እና የጤና መሠረተ ልማቶች ላይ የእሚያወጣ ነው። | **2** | በክፍተኛ ደረጃ በጀታቸውን ምርታማነትን ለማሳደግ ነው የእሚጠቀሙበት ፤ ማሕበራዊ ድጎማቸው ከተረጂነት ማላቀቅን ታሳቢ ያደረገ ነው። |

**የአመላካቾቹ አማካይ : 2.00 → በሲንጋፖር የበጀት አስተዳደር ደረጃ ልኬት: 4**

**ባለፉት 40 በነበረ አፈጻጸም መሠረት ከ5ቱ ኹኔታዎች አንጻር የነበረ አፈጻጸም**

| ሐገር | ኹኔታዎች | ልኬት |
|---|---|---|
| **ሲንጋፖር** | **የንብረት ባለቤትነት (አንኳር)** | **4** |
| | **የንብረት ተንቀሳቃሽነት (አጥዳፊ)** | **4** |
| | **የሕጉ ነጻነት እና ገለልተኛነት (አንኳር)** | **4** |
| | **የንግድ ክፍትነት (አጥዳፊ)** | **4** |
| | **የበጀት አስተዳደር ጥበብ (አንኳር)** | **4** |

**የምርመራ ውጤት: ሲንጋፖር**

**ፍረጃ: ከፍተኛ ገቢ ኢኮኖሚ** (የተቋማዊ ልቀት ጉልላት)

- **የአንኳር ኹኔታዎች ትንታኔ (Core Analysis):** ሲንጋፖር በ5ቱም ኹኔታዎች ከፍተኛውን ውጤት 4 ነው ያስመዘገበችው። ውጤታማ ተቋማትን ገንብቶ ዓለም ዓቀፍ ተወዳዳሪ መሆን ፤ ወደ መላው ዓለም ኤክስፖርት የእምታደርገው የሐገሯ ትልቁ የተፈጥሮ ኃብት አድርጋ ነው የወሰደችው። ሲንጋፖር አለ እሚባለው የፈጠራ ማጥለያ ወንፊት ነች ፤ ድህነትን እና ስንፍናን ወደ ውጭ አስቀርታ ፤ ከዓለም ላይ ምርጥ ምርጡን ካፒታል እና ክህሎት ስባ የእምታስገባ። ከእዚኽም የተነሳ ሲንጋፖር በምርታማነታቸው በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ ኩባንያዎች ዋና መሥሪያቤታቸውን ሲንጋፖር አድርገው ወደ ሌላው ዓለም የእሚስፋፉበት ሆናለች።

- **መንግሥት የእሚንከባከበው ወንፊት (The "Managed" Sieve):** የሲንጋፖሩ የልህቀት ወንፊት እንደ አሜርካው ትርምስምስ የሞላበት ሳይሆን በመንግሥት በጥንቃቄ የእሚመራ ነው ("Sovereign-Guided")። የሲንጋፖሩ መንግስት የበጀት አቅሙን ተጠቅሞ ከፍተኛ ፋይዳ ያላቸው እንደ ባዮቴክ፣ ፊንቴክ እና ኤአይ (Biotech, Fintech, AI) ኢንቨስት በማድረግ ይንከባከባል ፤ ይኽን ሲያደርግ ግን የንብረት ሕጋውተወዳዳሪነትን Contestability) በከፍተኛ ደረጃ እንዲኖር በማድረግ የእራሱ የልማት ድርጅቶች ከዓለም ዓቀፍ ኩባንያዎች ጋር ተወዳድረው ፤ በተወዳዳሪነት ብቻ እንዲኖሩ በማድረግ እንጂ የሐገሬ ድርጅቶች ብሎ ከውድድር መከለል ውስጥ አይገባም።

- **የፈጠራ ማጥለያ ወንፊት (Innovative Sieve Filter):** ሲንጋፖር ለቀረው ኢስያ እንደ ፈጠራ ማዕከል (Innovation Pool) የእምታገለግል ከፍተኛ የፈጠራ ማዕከል ነች። ችግርን “ኢምፖርት” በማድረግ መፍትኼ “ኤክስፖርት” ታደርጋለች (It "imports" problems and "exports" institutional solutions.)

- **የማስጠንቀቂያ ደውል (The Predictive "Premonition"):** በባለፈው አምስት ዓመት ሲንጋፖር አስተማማኝነቷ ላይ ስጋት እሚደቅን ነገር አልታየም ፤ ሆኖም የሕዝብ ቁጥር ማነስ ችግር ሊሆን ይችላል። በመጪው ግዜ ሲንጋፖር ከውጭ ለሥራ በእሚመጡ ሰዎች ላይ ልትደገፍ ትችላለች። በአንዳች የደህንነት ምክንያት የውጭ ሐገር ሠራተኞች ማስገባት ካቆሙ ፤ የከፍተኛ ገቢ ሐገርነት ታሪካቸው ሊቀየር ይችላል።

## 4.8 ቪየትናም

ቪየትናም ዛሬ በእምትገኝበት ኹኔታ ፤ የሐገር ውስጥ ኢንደስትሪን መከላከል እና ኢምፖርትን መተካት (import substitution) በእሚል ተይዞ ከነበረበት “የሶስተኛው ዓለም ወጥመድ” ውስጥ በመውጣት ፤ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ አምራች ለመሆን ተቋማዊ ለውጥ በማድረግ ጥሩ ውጤት ያስመዘገበች ተምሳሌታዊ ሐገር ሆና ነው።

በእዚኽም ፤ የዓለም የምርት ማዕከልነት ማዕረግ ከቻይና ተፎካክራ ለመውሰድ ያለችበት ኹኔታ ነው ያለው።

ቬትናም እንደ አብዛኛው ፤ የቀኝ ግዛት ሰለባ እንደ ሆኑ ሐገራት ፤ ነጻ ገበያን እና የንግድ ክፍትነትን ፤ የቀኝ ገዢዎች የጭቆና እና የብዝበዛ ሌላ እጅ አድርጋ የእምታይ እና ይኽም ደግሞ በማርክሲስታዊው የኢምፔሪያልዝም ትችት የተጠናከረባት ሐገር ነበረች።

በፈረንሳይ ቀኝ ግዛት ሥር በነበረችበት ከ1887–1954 በነበረው ግዜ ፤ የቬትናም ኢኮኖሚ በከተማ የእሚኖሩ የፈረንሳይ ቀኝ ገዢዎችን ለማገልገል ተብሎ የተዋቀረ ነው የነበረው። ዋነኛ የሐገሪቱ ምርት ሩዝ እና ጎማ ሆኖ ፤ ኢንደስትሪ ሆን ተብሎ የተዳከመበት ነበር። ባቡር ቢገባ እና ወደብ ቢገነባ ፤ ዋነኛ ዓላማው ከገጠሩ የጥሬ ዕቃ ምርትን ለማውጣት ብቻ ነበር። የቀኝ ግዛቱ መንግሥት የሐገሬው ሰው በኢከነሚው ውስጥ በንብረት ባለቤትነት እና በሥራ ፈጣሪነት (entrepreneurship) እንዲሳተፍ አይፈለግም ነበር ፤ ይልቁንም ኢኮነሚውን በተማከለ መልኩ ተቆጣጥሮ እራሱን ብቻ መጥቀም ነበር የእሚፈልገው።

በኹለተኛው የዓለም ጦርነት ፤ ጃፓን ቪየትናምን ከፈረንሳይ በኃይል ስትረከብ ፤ የቬይትናምን ሩዝ በኃይል እየቀማች ለጦርነት ዓላማው መሳካት ታውለው ስለ ነበር ፤ በሐገሪቱ ከፍተኛ ረኃብ አስከትላ ነበር።

እንደ እዚኽ ዓይነቶቹ ፤ ካፒታሊስታዊ ቃና ያላቸው ሐገራት ፤ በቬትናም ሕዝብ ላይ ያደረሱት ስቃይ እና ብዝበዛ ፤ በኋላ ላይ ቬትናየም የሐገር ውስጥ ኢንደስትሪ መገንባት በእሚል ተከላካይ የሆነ እና የልማታዊ መንግሥት እሳቤ እንድትከተል (protectionism and state-led development) በር ከፍተዋል።

ከነጻነት በኋላ ሆቺ ሚን (Ho Chi Minh) ይዞ የመጣው አካኼድ ፤ በጣም የተማከለ ሶሻሊስታዊ አስተዳደርን ይበልጥ የእሚያጠናክር ነበር ፤ ለምሳሌ ፦ የመሬት ማሻሻያ ፕሮግራማቸው ፤ በከፍተኛ መንግሥታዊ አምባገነናዊነት መሬት በኃይል እየቀሙ ሸንሽኖ የማከፋፈል አካኼድ ነበረው። ከእዚያም የግብርና ምርታማነትን ለማሳደግ በእሚል ፤ ገበሬዎችን በገበሬ ማሕበር በማደራጀት ፦ የማምረት ኺደቱን በማዕከል ደረጃ የእሚቀመጥ ኮታን ማሟላትን ታሳቢ ያደረገ እንዲሆን የማድረግ ፣ በጋራ ያመረቱት ምርትም ወደ ማዕከል ከገባ በኋላ መንግሥት ድርሻውን ከወሰደ በኋላ ለእነርሱ መልሶ እሚያከፋፍልበት ነበር ፤ በነጻ ውድድር መርኽ መሠረት ዜጋው በተናጠል ተወዳድሮ አምርቶ ፤ ግብሩንም ምርቱንም እንደ ተወዳዳሪነቱ መጠን እንዲከፍል እና እንዲወስድ ከማድረግ ይልቅ።

አብሮም በሶቭየት እርዳታ ኢምፖርትን የመተካት (Import substitution) ሙከራ ተደረጎ ነበር ፤ አፈጻጸሙ ግንዛቤ እና ከሐገር ኹኔታ ጋር ማጣጣም ይጎድለው ስለ ነበር ውጤቱ እሚፈለገውን ያኽል አልነበረም።

የቬትናም የኢኮኖሚ ቴክኖክራቲክ ካድሬዎች (Vietnam’s technocratic cadres) የናፖልዮንን ፈረንሳይ ጋር ተመሳስለው ነበር ፦ ያለችውን አብቃቅቶ በመጠቀም በጣም ብቁ ፤ ሐገራዊ የፈጠራ እና የማምረት ዕምቅ ችሎታን ከታሰረበት ፈትቶ ለቅቆ ፤ ኃብት መፍጠር ግን የእማይችል በመሆን።

ቬትናም ይኽን መልክ ካለው የተሳሳተ የኢከነሚ አካኼድ ወውጣት የጀመረችው በ1986 ዶይሞይ (Đổi Mới) ወይንም ዕድሳት (Renovation) የእሚል እንቅስቃሴ ከጀመረች በኋላ ነው። በእዚኽም ፦ በግል መነገድ ተፈቀደ ፣ የውጭ ኢንቨስትሮች ተበረታቱ እና የገበሬ ማሕበሮች ፈረሱ።

ይኽም በቬትናም የካፒታል እንቅስቃሴ እንዲ ጨምር አደረገ ፣ ነጋዴው በፓርቲ ትዕዛዝ ሳይሆን በገበያ የእሚፈለገውን ዕቃ ፤ የዕቃዎችን ዋጋ በማየት ማምረት እንዲጀምር አደረገው ፤ በ2007 ደግሞ ቬትናም የዓለም ንግድ ድርጅት (WTO) አባል ስትሆን ቬትናም ከድሮው የመነጠል ዝንባሌ ወጥታ የዓለም የንግድ ሰንሰለት አካል መሆኗን ዓሰየ።

ዶይሞይ ባለችው እራስን የማደስ አካኼድ ቬትናም ከተከላካይነት (Protectionism) ወደ የዓለም የአቅርቦት ሰንሰለት አባል ሐገርነት ተቀየረች።

ተከላካይነት (Protectionism) የቬትናም መመሪያ በነበረት ግዜ ፤ የእሚመረቱት ምርቶች በጣም ሰፊ የጥራት ችግር እና የዋጋ ውድነት ቢኖራቸው እንኳን ፤ ትኩረቱ የሐገር ውስጥ አምራቾችን ከውጭ ውድድር መከላከል እና ኹሉንም ነገር በሐገር ውስጥ ማምረት ላይ ነበር ። በአንጻሩ ከዓለም ዓቀፉ የአቅርቦት ሠንሠለት ጋር መያያዝ (Supply chain integration) ቬትናምን ከዓለም ዓቀፉ የምርት ሠንሠለት ወይንም መረብ ውስጥ አስገባት።

ከእዚኽም የተነሳ አሁን ቬትናም ፤ ወደ ሐገሯ የውጭ ሐገር ዕቃ እንደ አይገባ ከመከላከል ይልቅ ፤ በሌላ ሐገር የተመረቱ እና የምርት ኺደታቸውን ያልጨረሱ ፦ የኤሌክትሮንኪስ ፣ የጨርቃጨርቅ እና የመርከብ ግንባታ ዕቃዎችን በማስገባት ፤ ያላትን ተወዳዳሪ የእሚያደርጋትን የማምረት አቅም (comparative advantage) በመጠቀም ፤ ለምሳሌ ፦ኤሌክትሮኒሱን በመገጣጠም እና ያለቀ ዕቃ በማድረግ ኤክስፖርት የእምታደርግ ኢኮኖሚ ሆናለች።

ይኽም የኢኮኖሚውን የልማት አቅጣጫውን ለወጠው፦

- **ከመነሖል ወደ መተሳሰር :** ይኽ ቬትናምን እራስን መቻል እምትፈልግ ሳይሆን በዓለም ዓቀፍ የእሴት ሰንሰለት ውስጥ ተሳታፊነትን እምትፈልግ ሐገር አደረጋት (strategic participation in global value chains.)

- **የውጭ ምርትን በሐገር ውስጥ ምርት እተካለኹ ከእሚል ተከላካይነት ወደ የራስን ጠንካራ ጎን ተጠቅሞ ተወዳዳሪ ወደ መሆን አዛወራት (From defensive substitution to offensive specialization):** የዓለም ኢንደስትሪዎችን በሙሉ በሐገሬ ውስጥ እገነባለኹ ከማለት ይልቅ ፤ በዓለም ኢንደስትሪ ውስጥ የእራሴን ቦታ እይዛለሁ የእምትል ሆነች። (Rather than duplicating entire industries, Vietnam focuses on niches where it can add value)

- **ከደረቅ ዕቅድ ወደ የካፒታል ፍሰት ጋር የተጣጣመ እንቅስቃሴ (From rigid planning to flexible capital flows):** የውጭ ሐገር የንግድ ድርጅቶች እንደ አሻቸው ካፒታል

ወደ ፈለጉት መስክ ማቀያየር እንዲችሉ ሲሆኑ ፤ የሐገር ውስጥ ነጋዴዎች በሶፍትዌር ፣ በአግሪቢዝነስ እና በቀላል አምራችነት (light manufacturing) ይሳተፋሉ።

ከእዚኽ የተነሳ ዛሬ ቬትናም በዓለም ዓቀፍ አምራችነት ቻይናን የእምትቀናቀን ሐገር ሆናለች። በእርግጥ የተመረጡ መስኮችን ፦ ኤሌክትሮኒክስ ፣ ጨርቃጨርቅ ፣ እና ሰሚኮንዳክተርስ (semiconductors) ቅድሚያ ይሰጣቸዋል። እንደ እዚያውም መንግሥታዊ የጥራት ቁጥጥር አለ ሆኖም አሁን ቁጥጥሩ መንግሥት የእሚያስቀምጠውን የጥራት ደረጃ ለማሟላት ሳይሆን ዓለም ዓቀፍ የጥራት ደረጃን ለማሟላት ነው።

እንደ እዚያውም ከፍተኛ የማሕበራዊ ድጎማ እና ከፍተኛ የመንግሥት ቁጥጥር አለ ፤ የፈረንሳዩን ድርጅዝም (dirigisme) በእሚያስታውስ መልኩ ፤ ሆኖም ወጣት ሠራተኛ ስለ አለ እና ዓለም ዓቀፍ ካፒታል ስለ እሚገባ ፤ ኢኮኖሚውን ከመንግሥታዊ ዕቅድ ከእሚመጣ ድርቀት (Rigidity) ይታደጉታል።

ቬትናም አንድ ሐገር እንዴት የኢኮኖሚ ውሳኔዎች በፖለቲካ መሪዎች ከእሚወሰኑበት (Arbitrary power) ፤ የኢከነሚ ውሳኔዎች በምርታማነት መመዘኛ ወደ እሚወሰኑበት ስረዓት እንደ እሚለውጥ ዓይነተኛ ማሳያ ነች ፦ ከቀኝ ግዛት የብዝበዛ ኢኮኖሚ (Extractive Economy) ወደ በደረቅ (Rigidity) ሶሻሊስታዊ ስረዓት የእሚመራ ኢኮኖሚነት ከእዚያም ወደ ገበያ መር ኢከነሚ ሙከራ በመሸጋገር።

የቬትናም መጪው ፈተና አሁን እያረጋገጠች ያለችውን እራሱን ከወቅቱ የገበያ ኹኔታ ጋር አዋዶ የእሚኼደው ኢኮኖሚያዊ አካኼዷ የሕበረተሰቡን ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ማሕበራዊ እርጋታውን ሳይናጋ እንዲቀጥል ማድረግ ነው - ያን ስታደርግ ነው ፤ በመጭው ግዜ ፤ ግብታዊ የፖለቲካ ውሳኔ ሳይሆን ምርታማነቷ መጪው ዘመኗን እንዲወስን ማድረግ የእምትችለው።

በገበያ ወደ እሚመራ የውድድር ኢከነሚ በመሸጋገር ላይ ያለችው ቬትናም አሁን የተጋረጠባት ፈተና ፤ ይኽን የገበያ ስረዓት እንዴት አድርጋ ከማሕበራዊ መረጋጋት (Social stability) ጋር ልታስቀጥል የእምትችል ይሆናል የእሚለው ጉዳይ ነው ፤ መጪው ዘመኗን ተወዳዳሪ አምራችነቷ ሳይሆን መንግሥት ማሕበራዊ ፍትሕን ላረጋግጥ በእሚል ኃብት እንደ አሻው (arbitrary authority) ወስዶ እንደ አሻው የእሚያከፋፍልበት አካኼድ እንደ አይወስነው።

የቬትናምን ኢከነሚ ከባለፈው 40 ዓመት አንጻር በመመርመሪያው ማሽን ውስጥ ስናሳልፋት ፤ ከቻይናው ወደ ውስጥ መመልከት (Inward Looking) ስኬት ጋር በእሚመሳሰለው በዶይ ሞይ (Doi Moi) ወይንም የመታደስ ፕሮግራም ስኬት ነው ፤ ሆኖም በ2024–2026 በጀመረችው የንብረት ባለቤትነትን የማጠናከር አካኼድ ከቻይና ትለያለች።

ቬትናም አስተዳደራዊ ድንዛዜ (Administrative Sclerosis) የፈጠረባትን ደንቃራ አልፋ የጀመረችውን የፈጠራ ማዕከልነት (Innovation Pool) ለማረጋገጥ የእምትጣጣር ሐገር ነች።

**1. የግል ንብረት (አንኳር)**

| አመላካቾች | የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም | ልኬት (0–2) | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| **1. ባለቤትነት** | ሕገመንግሥቱ መሬት መንግሥት የሚያስተዳድረው “የመላው ሕዝብ” ንብረት ነው ይላል። በመሬቱ ላይ ያሉ የግል ንብረቶች መሬቱን የመጠቀም መብት ብቻ ነው ያላቸው። ያም ብቻ ሳይሆን የመጠቀም መብቱን መሸጥ እና መለወጥ ቢቻልም በዙ የመንግሥት ቁጥጥር እና ውሳኔ የሚፈልግ ነው። በጠቅላላው በቬትናም እንድ አሜሪካ ባሉት ሐገራት ዓይነት ያለው መሬትን ሙሉ በሙሉ ባለቤትነት ይዞ (fee-simple) እንደ አሻ መግዛት እና መሸጥ አለመቻል አንድ ትልቅ መዋቅራዊ ችግር ሆኗል። | **1** | የግል ንግድ ባለቤት መሆን በአብዛኛው መስክ ይቻላል ፤ ከግል ንብረቶች ቀዳሚ የሆነው መሬት ግን በመንግሥት ቁጥጥር ስር ነው። |
| **2. ውርስ** | ለብሔራዊ ወይንም ሕዝባዊ አገልግሎት በሚል መሬትን መውረስ የተለመደ ነው። በ2024/2025 የመሬት ሕግ ማሻሻያ የተደረገ እና የካሳ ክፍያዎች የገበያ ዋጋ ይኹኑ ቢባልም ፤ አሁንም ቢሆን መንግሥት ያሻውን የማድረግ ከፍተኛ አቅም ያለው በመሆኑ እና የካሳ ክፍያ ክርክር ዋነኛ የሕዝብ ቅሬኔ ምንጬ በመሆኑ ፤ ኹኔታው ለንግድ እሚመች አይደለም። | **0** | የሕጉ ተፈጻሚነት ደካማ በመሆኑ ፤ የካሳ ክፍያው ብዙ ግዜ ከገበያው ዋጋ በታች ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **3. ሕጋዊውድድር (Contestability)** | ኢኮኖሚው ባለኹለት መልክ ነው። የቴክኖሎጂ እና የአምራቹ መስክ በጣም ተወዳዳሪ ሲሆኑ ፤ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች (State-Owned Enterprises (SOEs)) ስትራቴጂክ በእሚባሉት እንድ ባንክ ፣ ቴሌኮምንኬሽን እና ኃይል ማመንጨት ስለ እሚሰተፉ እና አስፈላጊ ግብዓቶችን ለማግኘት ቅድሚያ ስለ እሚሰጣቸው ፤ ከግሉ መስክ ጋር በመሻማት የግሉን መስክ ወደ ጥግ የእሚገፉበት ግዜ አለ። | **1** | ሕጉ አዲስ ተወዳዳሪዎችን ይፈቅዳል ፤ ሆኖም በመንግሥት እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች መካከል ያለው ግንኙነት ከፍተኛ ገደብ ይፈጥራል። |
| **4. የሠራተኛ ነጻነት (Labor Freedom)** | ቬትናም ከፍተኛ ቁጥር ያለው በመሥራትም ሥራ በመፈለግም የእሚሰተፍ ሠራተኛ አላት። በ2021 የወጣው የሠራተኛ ሕግ ፤ ሠራተኛ ከሐገራዊ የሠራተኞች ማሕበር የተለየ የራሳቸውን ማሕበር እንዲያቋቁሙ ይፈቅዳል ፤ ሆኖም በተግባር ግን ፤ ሠራተኛ በጣም ተንቀሳቃሽ ነው ፤ ያም ማሕበሩ ተጠናክሮ የሠራተኛውን መብት ማስጠበቅ እንዲሳነው ያደርጋል ፤ በመሆኑም አብዛኛው የሠራተኛ መብት የእሚከበረው በመንግሥት ነው። ሥራ ለመቀጠር ወይንም ለመልቀቅ ምንም ዓይነት አገናኝ ደላላ አያስፈልግም። | **2** | ሠራተኛ በአሻው ግዜ ስራ መቀየር ይችላል ፤ የሥራ ገበያው ከዓለም ዓቀፉ ኢከነሚ ጋር የተያያዘ እና በእዚያ የእሚወሰን ነው። |

**የአመለካቾች አማካይ: 1 → በቬትናም የንብረት ባለቤትነት ደረጃ ልኬት: 3**

**2. የንብረት ተንቀሳቃሽነት (አጥዳፊ)**

| አመላካቾች | የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም | ልኬት (0–2) | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| **1. የውጭ ዜጋ የንብረት ባለቤትነት** | አብዛኛው መስክ ለውጭ ዜጋ ክፍት ነው ፤ ሆኖም የውጭ ባለኃብት ድርሻው ከ49% መብለጥ አይችልም ፤ በአክስዮን ገበያ ለእሚሸጡ ኩባንያዎች እና ለባንኮች ደግሞ ከ30% መብለጥ አይችልም ፤ በ2026 ደካማ ባንኮች ላይ 49% ተደርጓል። ስትራቴጂክ በእሚባሉ እንደ ቴሌኮም እና ኃይል ያሉትም ተቀራራቢ ገደብ አለባቸው። | **1** | ለውጭ ዜጎች አሳታፊ ነው ሊባል ይችላል ገበያው ሆኖም ሕጋዊ ወሰኖቹ ኃብት( equity) በወድድር በቀላሉ እጅ እንደ አይቀይር ያደርጋል። |
| **2. የመሬት ገበያ** | በቬትናም መሬት በመንግሥት የእሚተዳደር የወል የሕዝብ ንብረት ነው። የውጭ ዜጎች እና የንግድ ድርጅቶች መሬትን ከ50–70 በእሚቆይ ሊዝ ነው የእሚያገኙት። የመጠቀሙ መብቱ ሊሸጥ ፣ ሊከራይ ወይንም የብድር ማስያዣ መሆን የእሚችል ሲሆን ፤ የውጭ ዜጎች በአንድ ኮንደሚንየም ላይ ከ30% በላይ በባለቤትነት መያዝ አይችሉም። | **1** | እንቅስቃሴ ያለበት የሊዝ ገበያ አለ ሆኖም መሬትን በንብረትነት መያዝ አለመቻሉ እና በውጭ ዜጎች ላይ ያለው የባለቤትነት መጠን ገደብ የገበያውን ዕድገት ወስኖታል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **3. የካፒታል ቁጥጥር (Capital Controls)** | ጥብቅ የሆነ የውጭ ምንዛሪ ቁጥጥር አለ። ትርፍ ከሐገር ውስጥ ለማስወጣት ኦዲት የተደረገ የሒሳብ መዝገብ እና ግብር የከፈሉ መሁንን የእሚያሳይ ማረጋገጫ ይፈልጋል። የቬትናም ዶንግ (Vietnamese Dong -VND )) የእሚባለው መገበያያ ገንዘብ በቀላሉ ወደ ፈለጉት ሌላ ገንዘብ እሚመነዘር አይደለም። | **0** | ጥብቅ የካፒታል ቁጥጥር መኖሩ ፤ ድንበር ተሻጋሪ ንግድን በተሳካ መልኩ ለማድረግ አዳጋች አድርጎታል። |
| **4. የስቶክ ገበያው ከኢኮኖሚው አመታዊ ምርቱ አንጻር (Stock Market Size - % of GDP)** | እስከ 2026 ድረስ ፤ በአክሲዮን ገበያ የእሚሸጠው አክስዮን የኢኮኖሚው አመታዊ ምርት ከ 86 እስከ 90 በሞቶ ደርሷል (Market capitalization is approximately 86–90% of GDP)። ኤፍቲኤስኢ ረስል (FTSE Russell) የእሚባለው ደረጃ መዳቢ ድርጅት ቬትናምን "ኹለተኛ ደረጃ እያቆጠቆጠ ያለ ገበያ ("Secondary Emerging Market") የእሚል ደረጃ ሰጥቷል ፤ ይኽም ብዙ ኢንቨስተሮችን ስቧል ። | **2** | 60% በላይ በመሆኑ ከፍተኛ የእሚባለው ደረጃ ውስጥ ገብቷል ፤ ብዙ ገንዘብ የእሚንቀሳቀስበት ነው ፤ ከሌላው የዓለም ክፍል ጋር የተሳሰረ መሆኑን በእሚያሳይ መልኩ። |
| **5. በቀላሉ ንግድ መጀመር እና ማቆም/መሸጥ** | ኩባንያ በአንድ ሳምንት ማስመዝገብ ይቻላል ፤ የ2026 ማሻሻያ የውጭ ዜጎች ፈቃድ ለማውጣት የእሚፈጅባቸውን ግዜ በግማሽ ቀንሶታል። ሆኖም ንግድ ዘግቶ ወይንም ሽጦ መውጣት ፤ ከግብር እዳ ነጻ | **1** | ንግድ ፈቃድ ለማውጣት ቀላል ነው ሆኖም ዘግቶ ወይንም ሽጦ ለመውጣት ብዙ መንዛዛት አለው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | መሆንን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ እና በእግድ መብቶች ("pre-emptive rights") ምክንያት በጣም የተንዛዛ ነው። | | |
| **6. በቀላሉ ብድር ማግኘት** | የብድር ገበያው ከፍተኛ ዕድገት እያስመዘገበ ነው ሆኖም የመደበኛ ባንክ ብድር ተድራሽ የሆኑ አነስተኛ እና መካከለኛ ንግዶች 10–15% የሚሆኑት ናቸው። ትላልቅ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች (Large state-owned enterprises (SOEs) ) እና የሪል እስቴት ድርጅቶች የብድር ገበያውን ተቆጣጥረውታል ፤ ሆኖም ከ2026 ጀምሮ ኮላተራል ሳይዙ የሚያበድሩበት የዲጅታል የብድር አሠጣጥ ተጀምሯል። | **1** | ብድር አለ ሆኖም በአብዛኛው ትልልቅ ለሆኑት ነው ፤ አነስተኛ እና መካከለኛ የሆኑ ድርጅቶች በኮላተራል ምክንያት እና በሌሎች አስተዳደራዊ ገደቦች ምክንያት ይቸገራሉ። |

**የኩኔታዎች አማካይ : 1.00 → በቬትናም የንብረት ተንቀሳቃሽነት ደረጃ ልኬት: 3**

**3. የሕጉ ነጻ እና ገለልተኛነት (አንኳር)**

| **አመለካቾች** | **የባለፈው 40 ዓመታት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የዳኝነት ነጻነት** | ዳኞች የፓርቲ/መንግሥት አንድ ተቀጥያ ናቸው ፤ ስለ እዚኽ የዳኝነት ነጻነት በጣም ዝቅተኛ ነው። | **0** | ፍርድ ቤቶች ሶሻሊስት ሌጋሊት ("Socialist Legality") እና የፓርቲ መመሪያ ይከተላሉ። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **ሙስና** | ከ2021–2026 ከፍተኛ ባለስልጣናትን የነካ ጸረ ሙስና እርምጃ ተወስዷል። | **1** | መንግሥት ሙስናን በንቃት እታገላለሁ ይላል/ይታገላል ሆኖም ኺደቱ በነጻ እና ገለልተኛ ፍርድቤት በሕግ አግባብ ከእሚደረግ ይልቅ ፖለቲካዊ ነው። |
| **የውል ተፈጻሚነት** | ለኢንተርናሽናል ንግድ (International trade) አስተማማኝ ነው ፤ ለግለሰቦች እና ለፍታብሔር ጉዳዮች ግን በጣም ይዳተታል። | **1** | ከውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ጋር ሲያያዝ በጣም ቀልጣፋ ነው ፤ ካልሆነ ግን መዳተት ይገጥመዋል። |
| **በሕግ ፊት እኩልነት** | እኩልነት የለም ፡- የመንግሥት የልማት ድርጅቶች(SOEs) አንደኛ ደረጃ ናቸው ፤ ከፍተኛ መጠን ያለው ኃብት ያላቸው የውጭ ኢንቨስተሮች ኹለተኛ ናቸው ፤ ከእዚያ ሐገራዊ የንግድ ድርጅቶች ፤ በተስመጨረሻ ዜጋው። | **0** | ፍትሕ በከሳሹ/ተከሳሹ ደረጃ ("status") ይወሰናል። |
| **ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት** | ስትራቴጂክ ወይንም ከፍተኛ በእሚባሉ ጉዳዮች ቀጥታ የሆነ ጣልቃ ገብነት ነው ያለው። | **0** | የሕግ የበላይነት ሳይሆን በሕግ መግዛት (Rule *by* law) ነው ያለው። |
| **የፖሊስ አስተማማኝነት** | ሠላም ለማስከበር እና መሠረታዊ የንብረት ጥበቃ ለማድረግ ከፍተኛ ነው። | **2** | ንብረት እና የንግድ እንቅስቃሴ አስተማማኝ ጥበቃ ነው ያላቸው። |

**የአመለካቾች አማካይ: 0.66 → በቬትናም የሕጉ ነጻ እና ገለልተኛነት ደረጃ ልኬት : 2**

**4. የንግድ ክፍትነት (አጥዳፊ)**

| አመላካቾች | የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም | ልኬት (0–2) | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| **የታሪፍ መጠን** | የበርካታ ነጻ የንግድ ቀጠናዎች አባል (CPTPP, EVFTA, and RCEP) ነች ፤ ቀረጥ ወደ ዜሮ እየወረደ ነው። | **2** | በዓለም ላይ ካሉ ከነጻ የንግድ ቀጠናዎች ጋር የተሳሰረ ኢኮኖሚ ከእሚባሉት አንዱ ነው። |
| **ከታሪፍ ውጪ የሆኑ ገደቦች** | አንድ አንድ የፈቃድ እና የሐገር ውስጥ ግብዓት መጠቀም የእሚሉ መሳንተያዎች አሉ። | **1** | ውስብስብ የአሠራር ችግሮች እንደ ክልከላ ይሆናሉ። |
| **የገቢ/ወጪ ንግድ ከአመታዊ ምርት አንጻር (Trade - % of GDP)** | ከዓለም ገበያ ጋር በጣም ከፍተኛ ትሥሥር ያለው ነው ያለው ፤ የገቢ/ወጪ ንግድ የአመታዊ ምርቱ ~160-180% ገደማ ነው። | **2** | ቬትናም በዓለም ዓቀፉ ጀስት ኢን ኬዝ ("Just-in-Case")[10] የአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ ትልቅ ቦታ አላት። |
| **በገቢ/ወጪ ንግድ ላይ ክልከላ** | በጣም ውስን እና በዋናነት ወሳኝ ቴክኖሎጂዎች (high-tech) ላይ ያተኮረ ነው። | **2** | ክፍተኛ የሸቀጥ ፍሰት ነው ያለው ። ገደብ በጣም ትንሽ ነው። |
| **የግሙሩክ ቆይታ** | ከ 2024-2026 ባለው ግዜ ከፍተኛ መጠን ያለው የግሙርክ አሰራርን የማዘመን ኢንቨስትመንት አለ። | **2** | የቬትናም ወደቦች ለአከባቢው ሐገሮች ተምሳሌት የእሚሆኑ ናቸው። |
| **የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት እና ሕግ አክባሪነት(WTO Compliance)** | ከ2007 ጀምሮ ጥሩ አባል እና አለመግባባትን | **2** | ለዓለም ዓቀፋዊ የንግድ ስምምነት ከፍተኛ ተገዢነት አለ። |

[10] "Just-in-Case" የእሚባለው ተመርቶ ትዕዛዝ የእሚጠብቅ ሲሆን "Just-in-Time" ደግሞ ልክ ሲታዘዝ የእሚመረት ነው።

| | | | |
|---|---|---|---|
| | በሕጉ ለመፍታት የእምትሠራ ነች። | | |

**የአመለካቾች አማካይ: 1.83 → በቬትናም የንግድ ክፍትነት ደረጃ ልኬት: 4**

**5. የበጀት አስተዳደር ጥበብ (አንኳር)**

| **አመላካቾች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የግብር ተገማችነት** | ለውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የግብር እፎይታን መጠቀም የተለመደ ነው ነገር ግን ለኹሉም ስለ እማይሠጥ የውድድር መሥኩን ያዛባል። | **1** | ትንሽ የእሚባለው ("Global Minimum Tax" (OECD)) የግብር ደረጃ ላይ ለመድረስ በተደጋጋሚ ይሻሻላል። |
| **የበጀት ጉድለት ለመሙላት ገንዘብ ማተም (Monetary Financing)** | ውስን ነው የቬትናም ብሔራዊ ባንክ ትኩረቱ ገንዘቡ እንዲረጋጋ ነው። | **1** | የቬትናም ብሔራዊ ባንክ ገለልተኛ አይደለም ፤ የዕድገት ግብን ለማሳካት የገንዘብ ፖሊሲን ይጠቀማሉ። |
| **ብድርን ምርትማነትን ለማሳደግ መጠቀም (Productive Debt)** | የመንግሥት ብድር ከኢኮኖሚው አመታዊ ምርት አንጻር በጣም ትንሽ ነው 33% በመሆን እና እንደ አደጋ ከእሚታየው 60% በታች በመሆን። | **2** | ብድር በአብዛኛው የእሚወሰደው የኃይል ማመንጫ እና ወደብ ለማልማት ነው። |
| **የግሽበት መጠን** | በ1980ዎቹ ከነበረበት 400% አሁን ወደ ~3-4% (2026) ወርዶ እንዲረጋ ማድረግ ተችሏል። | **2** | ለተከታታይ አስርት አመታት የተረጋጋ ነው። |
| **የብሔራዊ ባንክ ነጻነት** | ምንም ነጻነት የለውም ቀጥታ በጠቅላይ | **0** | የቬትናም ብሔራዊ ባንክ ፖሊሲ ማስፈጸሚያ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ምኒስትሩ ነው የእሚታዘዘው ። | | እና የኢኮኖሚ መረጋጋት መፍጠሪያ ተድርጎ ዓይታይም። |
| **የመገበያያ ገንዘብ ርጋታ (Currency Stability)** | ከዶላር አንጻር የእሚድኽ ነው (Managed crawl against the USD) | **1** | የተረጋጋ ነው ፤ ነገር ግን ርጋታው የተፈጠረው በአስተዳደራዊ ጣልቃ ገብነት እና የካፒታል ቁጥጥር በማድረግ ነው። |
| **በእዳ የመያዝ ታሪክ (Default History)** | ጥሩ የብድር አከፋፈል ነው ያለው። | **2** | ጠንካራ የመንግሥት የእዳ አያያዝ ነው ያለው። |
| **የበጀት አደላደል** | ቬትናም እንደ ብራዚል አይደለችም ፤ ብዙ ትኩረቷ በመሠረተ ልማት ላይ ነው። | **2** | አብዛኛው የበጀት ገንዘብ ካፔክስ(Capex (Capital Expenditure) ) ወይንም የካፒታል ወጪ ነው ከፍጆታ (consumption) ይልቅ። |

**Condition Average: 1.37 → Condition Value: 4**

**ከአምስቱ ኹኔታዎች አንጻር በባለፈው 40 ዓመት የቬትናም አፈጻጸም**

| **ሐገር** | **ኹኔታዎች** | **ልኬት** |
|---|---|---|
| **ቬየትናም** | **የግል ንብረት (አንኳር)** | **3** |
| | **የንብረት ተንቀሳቃሽነት (አጥዳፊ)** | **3** |
| | **የሕጉ ነጻ እና ገለልተኛነት (አንኳር)** | **2** |
| | **የንግድ ክፍትነት (አጥዳፊ)** | **4** |
| | **የበጀት አስተዳደር ጥበብ (አንኳር)** | **4** |

**የምርመራ ውጤት : ቬየትናም**

**ፍረጃ: ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ** (በመንደርደር ላይ ያለች ሐገር)

- **የአንኳር ኹኔታዎች ትንተና (Core Analysis):** ቬትናም አምስቱን ኹኔታዎች ለራሷ በእሚመቻት መልኩ በመጠቀም ዓይነተኛ ሐገር ነች ፤ በንግድ ክፍትነት እና በበጀት አስተዳደር ጥበብ ያላትን ከፍተኛ 4 ውጤት ደካማ የሆነችባቸውን የንብረት ባለቤት እና የሕግ ገለልተኝነት ችግር ለመሻገር ችላለች። ገቢዋን ጡረታ በመክፈል ከማጥፋት ይልቅ ወደቦቿን በማልማት ላይ አውላ ፤ ምርታማነቷን እያሳደገች ነው።

- **የመታወቂያ ስረዓት ማሻሻያው (The Ho Khau Breakthrough):** በጣም ኋላ ቀር የሆነውን እና እንደ ሽያጭ/ግዢ ላሉ ለብዙ አገልግሎት አስፈላጊ የሆነውን የመታወቂያ ስረዓት በመቀየር (2023–2026) የንብረት ተንቀሳቃሽነታቸውን ወደ 3 አሳድገው በጣም እድገት እያገኙ ነው። ይኸም በሚልዮን የእሚቆጠሩ እንደ ግብርና ያለ በዝቅተኛ ምርታማነት (low-productivity) ባላቸው መስክ የተሰማሩ ሰዎችን ወደ እንደ ኤሌክትሮኒክስ ያሉ ከፍተኛ ምርታማነት ( high-productivity) ወዳላቸው መስኮች እያሸጋገረ ነው።

- **የፈጠራ ማጥለያ ወንፊቱ (Innovative Sieve Filter):** ከፈጠራ አንጻር ቬትናም ባለኹለት መልክ ናት ፤ እንደ ሳምሰንግ ፣ አፕል (Samsung, Apple suppliers) ላሉት የፈጠራ ማጥለያ ነች (Productivity Sieve)። የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን የእሚከላከል በመሆኑ ደግሞ ያረጀ ኃብት ምሽግ ነው (Wealth Vault for its SOEs)። የቬትናም ትልቁ ክፍተት የእሚሆነው በዓለም ዓቀፍ ደርጃ ተወዳዳሪ በሆኑት ትላልቅ ኩባንያዎች እና በጥቃቅን የንግድ ድርጅቶች (micro-SMEs) መካከል መፈጠር የነበራባቸው የግል ኩባንያዎች በመንግሥት የልማት ድርጅቶች (SOEs) ተገፍተው ( "Crowded Out") መውጣታቸው ነው።

- **ማሳሰቢያው ደውል (The Predictive "Premonition") :** እንደ ምርመራ ማሽኑ ቬትናም ከአስተዳደራዊ ግግርነት (**"Administrative Sclerosis."**) የተነሳ ተቋማዊ አቅም መዳከም አለባት። እንደ እሚንበገበግ ኦቭን (The "Blazing Furnace") ብዙ ባለ ስልጣናትን ያስደነገጠው የጸረ ሙስና ዘመቻ ፤ ባለስልጣናት ትንንሽ ፕሮጀክቶች ላይ እንኳን መፈረም እንዲፈሩ ስለ አደረጋቸው ፤ የኢንቨስትመንት ማነቆ ፈጥሯል። ቬትናም በግዜ ከፖለቲካዊ አስተዳደር ወደ ተቋማዊ የሆነ ነጻ እና ገለልተኛ የሕግ መዋቅር ካልተሸጋገረች እና የሕግ የበላይነትን አሁን ካለበት **2 ወደ 3** ካላሳደገች ፤ በመካከለኛ ገቢ ሐገር ወጥመድ ውስጥ ("Middle-Income Trap") ተይዛ የቆመች ሐገር የመሆን አደጋ አለባት ፤ ምክንያቱም ፡- ኢኮኖሚያዋ እያደገ የደሞዝ ተወዳዳሪነቷን እየሸረሸረ ነው በአንጻሩ ደግሞ በፈጠራ እንደ አትወዳደር ተቋማዊ ኹኔታዋ ፈጠራን የእሚያበረታታ አይደለም።

## 4.9 ናይጄሪያ

የናይጄሪያ የኢኮኖሚ ታሪክ የአብዛኛውን ከቀኝ ግዛት ነጻ የወጡ ሐገራትን የኢኮኖሚ ታሪክ ይመስላል ፦ በቀኝ ግዛት ዘመን ለቀኝ ገዢዎች ጥሬ ዕቃ አቅራቢ (Extraction) ፣ ከነጻነት በኋላ ሐገራዊ የኢንደስትሪ አቅም መገንባት በእሚል የመከላከል (Protectionism) ሙከራ ፣ እርሱም አልሠራ ሲል ቀስ በቀስ ነገርን ግን ወጥነት በጎደለው መንገድ በርን በመክፈት ከዓለም ዓቀፉ ገበያ ጋር አብሮ ለመሥራት (Global integration) መሞከር።

ናይጄሪያ በዛሬው ኹኔታዋ ፦ የተፈጥሯዊ ኃብቷን ፤ ዘርፈ ብዙ አምራችነት (Diversified productivity) የእሚታይበት ኢኮኖሚ አድርጎ በመገንባት ራሷን የአህጉሩ የምርት እና የአገልግሎት መዓከል ለማድረግ ታልማለች።

**የቀኝ ግዛቱ ኢኮኖሚያዊ ውቅር**

ናይጄሪያ በእንግሊዝ ቀኝ ግዛት ውስጥ በነበረችበት ከ1900–1960 በነበረው ግዜ ፤ የናይጄሪያ ኢኮኖሚ የተዋቀረው ፦  የኮካዋ ፣ የፓልም ዘይት እና ኦቾሎኒ (Groundnuts) ጥሬ ዕቃን የእሚያመርቱን የሐገሪቱን ገጠራማ አከባቢዎች ከናይጄሪያ ወደቦች ጋር በእሚያገናኙት ባቡሮች አማካኝነት ፤ እነ እዚኽ የግብርና ምርቶች ለእንግሊዝ ገበያ እና ፋብሪካ በጥሬ ዕቃነት እንዲያቀርቡ ነበር።

ናይጄሪያ በቀኝ ገዢዎቹ በዋናነት የእምትፈለገው ለቀኝ ገዢዎቹ ፋብሪካ እና ነጋዴዎች የጥሬ ዕቃ አቅራቢ እንድትሆን በመሆኑ ፤ በናይጄሪያ ፋብሪካ እንዲኖር ወይንም ሥራ ፈጣሪ (Entrepreneurial) የሆኑ ነጋዴዎች እንዲኖሩ አይፈለግም ነበር ፤ ከእዚኽም የተነሳ ናይጄራዊ ፋብሪካ እና ሥራ ፈጠራ በጣም የተዳከመ ነበር።

ይኽን መልክ ካለው የቀኝ ገዢዎች የዘፈቀደ (Arbitrary) የፖለቲካ ስልጣን የተነሣ ፤ የቀኝ ዘመኑ የናይጄሪያ ኢኮኖሚ ዘርፈ ብዙ አምራችነት (Diversified production) ሳይሆን ጥሬ ዕቃዎችን ኤክስፖርት (Commodity export) የማድረግ ባሕል ነው የነበረው።

**ድህረ-ቅኝግዛት የመጣው ኢኮኖሚያዊ ብሔርተኝነት (Post-Independence Protectionism)**

ናይጄሪያ በ1960 ከቀኝ ግዛት ነጻነቷን ካገኘች በኋላ ፤ እንደ አብዛኛው የቀኝ ግዛት ሰለባ ሐገር ፤ የኢኮኖሚያዊ ብሔርተኝነትን መስመር (Protectionist policies) ነው አጥብቃ የያዘችው። ከውጭ የእሚገቡ ምርቶችን በሐገር ውስጥ ምርት መተካት (Import substitution) በእሚል ፦ ከውጭ የእሚገቡ ምርቶችን በሐገር ውስጥ የእሚያመርቱ ፋብሪካዎች ተቋቋሙ ፣ እነ እዚኽን ሐገራዊ ፋብሪካዎች ከውጮቹ ውድድር ለመከላከል የውጭ ሐገር ምርቶች ላይ ከፍተኛ መጠን ያለው ታሪፍ/ቀረጥ ተጫነ ፣ ስትራቴጂክ (Strategic) በእሚባሉት መስኮች በርካታ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቋቋሙ።

ሆኖም ፦ የብቃት ማነስ ፣ ሙስና እና የመሠረተ ልማት ችግር እነ እዚኽን ሐገራዊ ፋብሪካዎች እና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች የታሰበውን ውጤት ከማስመዝገብ ገደባቸው። ልክ በቬትናም በመጀመሪያዎቹ የሶሻሊስት ቆራጥነት (Socialist rigidity) ዘመን እንደ ሆነው ፤ የናይጄሪያውም የኢኮኖሚ ብሔርተኝነት (Protectionism) የኢንደስትሪያል ብቃት በኪስ ቦታዎች ላይ ፈጠረ ፤ ነገር ግን ሰፊውን የናይጄሪያን የኢንደስትራሊያዜሽን ዕምቅ አቅም ሊለቅ ግን አልቻለም።

**የነዳጅ መገኘት የፈጠረው መነቃቃት እና የማማካል አባዜ (Oil Boom and Centralization)**

ኒጀር ዴልታ (Niger Delta) በእሚባለው ቦታ በ1970ዎቹ ነዳጅ መገኘቱ ፤ የናይጄሪያን ኢኮኖሚ በከፍተኛ ደረጃ ለወጠው። ከነዳጅ የተገኘው ገቢ ፤ መንግሥት በመሠረተ ልማት እና በድኅማ ላይ ከፍተኛ መጠን ያለው ኢንቨስትመንት ማድረግ እንዲችል አደረገው ፤ ሆኖም አብሮ ኪራይ ሰብሳቢነት እና መማከልን (Rent-seeking and centralized control) ይዞ መጣ።

የናይጄሪያው መንግሥት የፈረንሳዩን ኮልበርት ፍልስፍና በእሚያስታውስ (echoing Colbertist France) መልኩ ፦ የኢንደስትሪዎች አቃጅ ፣ ፋይናንሰር እና አስተዳዳሪ/ተቆጣጣሪ ሆነ። ይኽም የንግድ ተቋማትን ህልውና የእሚወስነው ጥራት እና ተወዳዳሪነት ሳይሆኑ ፖለቲካዊ አባትነትን (political patronage) እንዲሆን አደረገ ፤ አብሮም የደች በሽታ (Dutch Disease) የእሚባለውን አከተለ።

በደች በሽታው (Dutch Disease) ፦ ናይጄሪያ ነዳጅ በመላክ ብዙ ዶላር ማግኘት ስትጀምር ፤ የናይጄሪያው መገበበያ ገንዘብ የመግዛት አቅሙ ጠነከረ ይኽም በሐገር ውስጥ ፋብሪካ እና ግብርና የእሚመረቱ ምርቶች ከውጭ ከእሚገቡት ይልቅ ዋጋቸው በጣም ውድ እንዲሆን በማድረጉ ፤ የሐገር ውስጥ ፋብሪካዎች እና ግብርና ተዳከሙ። በእዚኽ ላይ የመንግሥትም የኢንቨስትመንት ትኩረት ትልቁን ገቢ የእሚያመጣለት የነዳጁ መስክ ላይ ስለ ሆነ ፤ የፋብሪካ እና የግብርናው መስክ ተዳከመ።

**መዋቅራዊ ማስተካከያ እና ገበያ መክፈት (Structural Adjustment and Liberalization)**

በ1980ዎቹ የነዳጅ ዋጋ መውደቅ ፤ ናይጄሪያ ስትከተለው የነበረውን የኢኮኖሚያዊ ብሔርተኝነት ሞደል (protectionist model) ተጋላጭነት ዓሳየ። ከእዚያም አይኤምኤፍ እና የዓለም ባንክ (IMF and World Bank) መዋቅራዊ ማሻሻያ እንዲደረግ ግፊት በማድረጋቸው ፦ በመንግሥት ይሰጡ የነበሩ ድጎማዎች ተቋረጡ ፣ ታሪፍ/ቀረጥ ቀነስ ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ለግል ተሸጡ ። ይኽም የናይጄሪያን ከኢኮኖሚ ብሔረተኝነት (protectionism) ወደ ዓለም ዓቀፋዊ የንግድ ትሥሥር የመቀየር ጉዞ አስጀመረ።

ሆኖም ማሻሻያው ወጥነት ይጎድለው ነበር ፤ በተለይ በኢኮኖሚ ብሔርተኛ ስረዓት ውስጥ ተሰግስገው የነበሩ በርካታ ሊህቃን በጣም ተቃውመውት ስለ ነበር ፤ ማሻሻያው ያስከተለው ማሕበራዊ ዋጋ ከፍተኛ ነበር።

### ከኢኮኖሚያዊ ብሔርተኝነት ወደ ዓለም ዓቀፍ ንግድ ተሳታፊነት (From Protectionism to Supply Chain Integration)

የናይጄሪያው አካኼድ ከቬትናሙ ጋር አንድ የእሚያመሳስለው ነገር አለው ፤ እርሱም በቬትናም እንደ ሆነው በናይጄሪያም ኢኮኖሚያዊ ብሔርተኝነት ከዓለም ዓቀፉ የአቅርቦት ሠንሠለት ጋር በመተሳሰር (supply chain integration) መተካቱ ነው። ናይጄሪያዎች ራስን በመቻል ስም ኹሉን ነገር በሐገራችን እናምርት ከእሚል ወጥተው ፤ በዓለም ዓቀፉ የማምረት ሠንሰልት ውስጥ በመግባት ፦ ነዳጅ ማጣራት ፣ ሲሚንቶ ማምረት ፣ የፊንቴክ ስራዎች እና የአግሪቢዝነስን መሳተፊያ መስካቸው አደረጉ። እንደ ዳንጎቴ ቡድን (Dangote Group) ያሉት እና በተለያየ ሐገር ኢንቨስት (Multinationals) የእሚያደርጉት እና በቴክኖሎጂው ዘርፍ በሌጎስ በማደግ ላይ ያሉት የንግድ ድርጅቶች የእዚኽ ማሳያ ናቸው።

በእዚኽም አካኼድ የናይጄሪያ የኢኮኖሚ ፍልስፍና በመሠረታዊነት ተቀይሯል ፦

- **አጥር ሰርቶ እራሴን ልቻል ከማለት ወደ ዓለም ዓቀፍ ትስስር (From shielding to linking):** ናይጄራ ራስን መቻል (autarky) የእሚል የኢኮኖሚ ብሔርተኝነትን ኢኮኖሚያዊ ግብን በዓለም ዐቀፉ የእሴት ሰንሰለት ውስጥ (global value chains) የእራሷን ቦታ በማግኘት ተክታዋለች።

- **ሌሎችን ከመድገም እራስን ወደ መሆን (From duplication to specialization):** ከውጭ የእሚመረቱ ምርቶችን በራስ ምርት በመተካት በእሚል የተወዳዳሪነት ችግር ያለባቸው ምርቶችን በሐገር ውስጥ ከማምረት(ከመድገም) ይልቅ ፤ ናይጄሪያ እሴት ልትጨምርባቸው በእምትችላቸው ፦ በኃይል ፣ በፊንቴክ እና በፈጠራ ኢንደስትሪዎች ላይ መሠመራት።

- **ከእማያፈናፍን መንግሥታዊ ቁጥጥር ወደ የመንግሥት እና የግል ተሳትፎ ወደ አለበት የመንግሥት አስተዳደር (From rigid state control to hybrid governance):** ምንም እንኳን አሁንም የመንግሥት ቁጥጥር (Regulation) ጠንካራ ቢሆንም ፤ የግል ካፒታል እና የውጭ ኢንቨስትመንት የሐገሪቱን ምርታማነት በከፍተኛ ደረጃ እያሳደጉ ነው።

**የቅርብ እድሳት (Contemporary Refurbishment)**

ዛሬ ፣ ናይጄርያ ኹለት ፈተና ተደቅኖባታል ፦ ኢኮኖሚያዋን በነዳጅ ኤክስፖርት ላይ ከመደገፍ አላቃ ሌሎች ዘርፎችንም እሚያካትት (diversify) የማድረግ እና የማሕበረ ኢኮነሚ ተቋሞቿን በማዘመን አስተማማኝነታቸውን ማሳደግ።

ዛሬም በናይጄሪያ እንደ ኃይል ፣ ስሚንቶ እና ፊንቴክ ያሉ መስኮች ስትራቴጂክ በእሚል ቅድሚያ ይሰጣቸዋል። እንደ እዚያውም መንግሥት የኢንደስትሪዎች ጥራት ተቆጣጣሪ ነው ፤ ምንም እንኳን አሁን አሁን ፤ ጥራቱን በራሱ ስትንዳርድ መሠረት ሳይሆን ዓለም ዓቀፍ ደረጃዎቹን ከማሳካት አንጻር ቢያደርገውም። ተቋሞችም እንደ ድሮው ከእማያፈናፍን መንግሥታዊ የተዋረድ ትዕዛዝ ወጥተው ፤

እራሳቸውን ከዘመኑ ጋር የማጣጣም ዝንባሌያቸው እያደገ ነው ፤ የናይጄሪያ ነጋዴዎችም ከዓለም ዓቀፉ የአቅርቦት ሰንሰለት (Supply chains) ጋር ፡- በቴክኖሎጂ ፣ በፊልም እና በግብርና እያስተሳሰሩ ነው።

ናይጄሪያ በእዚኽ አካኼዷ አንድ ሐገር ከኢኮኖሚ አንጻር ዘፈቀደ በሆነ መልኩ በፖለቲካ ፍላጎት (arbitrary power) ከእሚዘወር ኢክኖሚ እንዴት በተወዳዳሪ አምራችነት ወደ እሚመራ ኢኮኖሚ እንደ እምትሻገር ሌላ ማሳያ ናት ፡- የቀኝ ገዢዎች የጥሬ ዕቃ አቅራቢ ከመሆን ወደ ሶሻሊስታዊ ድርቅ (Rrigid) የኢኮኖሚ ብሔርተኝነት (Protectionism) ከእዚያም ወደ ዓለም ዓቀፉ ንግድ ትሥሥር ውስጥ በመሸጋገር።

አሁን ናይጄሪያ የተደቀነባት ፈተና የኢኮኖሚ ዘርፎቿን በማስፋት (Diversification) ፣ በነዳጅ ላይ ያላትን ተደጋፊነት ቀንሳ ፤ የናይጄሪያን ኢኮኖሚያዊ መጻኢ የእሚወስነው በገበያ ውድድር የእሚረጋገጥ ምርታማነት እንጂ ከኢኮኖሚ አንጻር ዘፈቀደ የሆነ የፖለቲካ ስልጣን (Arbitrary authority) አለመሆኑን ማረጋገጥ ነው።

ይኽን ዓይነት ኢኮኖሚያዊ መልክ ያላት ናይጄሪያ ወደ መመርመሪያ ማሽኑ ስትገባ ፤ ተቋማዊ ተቃርኖ የእሚንጣት ሆና ነው እምትገኘው ፤ የናይጄሪያ ኢኮኖሚ ፡- አንጸባራቂ የሆነ የፈጠራ አቅም (The Innovation Pool) የእሚታይበት የግሉ መስክ በደረጃ ልኬቱ 1 ያገኘ የሕግ የበላይነትን እና የበጀት አስተዳደር ጥበብ ጉድለትን የእሚታገለበት ነው።

የናይጄሪያ ኢኮኖሚ የፈጠራ/የምርታማነት ወንፊት (Productivity Sieve) በአስተዳደራዊ ግግርታምነት (Administrative Sclerosis) እና የጥቂት ባለኃብቶች ኢተወዳዳሪነት (Oligarchic barriers) ታግቶ የተያዘበት ነው።

**1. የግል ንብረት (አንኳር)**

| **አመላካች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **1. ባለቤትነት** | የ1978 የመሬት አጠቃቀም አዋጅ ፤ ለፌደራል ክልል ገዢዎች (State Governors) ኹሉንም ስልጣን በመስጠት ፤ የናይጄሪያ ኢኮኖሚ ዋንኛ ሕጋዊ ደንቃራ ሆኗል ። የውጭ ባለኃብቶች የንግድ ድርጅቶችን እና ተንቀሳቃሽ ኃብትን በባለቤትነት መያዝ ሲችሉ ፤ መሬት ግን በክልል | **1** | በርካታ ንብረቶች በግል ንብረትነት መያዝ ይችላሉ ፤ መሬት ግን በሊዝ ብቻ ነው የእሚገኘው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ገዢዎች በሊዝ ብቻ ነው የእሚሰጠው። | | |
| **2. ውርስ (Expropriation)** | ለሕዝበዊ አገልግሎት በእሚል ፤ ለምሳሌ ፦ ኹለተኛው የኒጀር ድልድይ ወይንም የሌጎስ የባቡር ፕሮጀክት ፤ በግድ መውረስ የተለመደ ነው። ምንም እንኳን ሕጉ ተገቢ ካሳ ይከፈል ቢልም በ2025/2026 የተደረጉ ጥናቶች እንደ እሚያሳዩት የካሳ ክፍያዎች ከገበያው ዋጋ ከ28%–58% የእሚያንሱ ሲሆን ክፍያቸውም እስከ 40 ወር ሊዘገይ ይችላል። | **0** | ሕጉ ተገቢ ካሳ ይከፈል ቢልም ፤ ከግምት ልዩነት እና ከአስተዳደር ችግር የተነሳ ከገበያ በታች የሆኑ የካሳ ክፍያዎች የተለመዱ ናቸው። |
| **3. ሕጋዊውድድር (Contestability)** | በወረቀት ላይ አዲስ ንግድ ለመጀመር ቀላል ነው ፤ ለምሳሌ ኮምፒውተራይዝድ በመሆኑ መልኩ የፈቃድ አሰጣጡ ስለ ተቀላጠፈ ሆኖም ፖለቲከኞች እና የጥቅም ኔትወርካቸው የውጭ ምንዛሪን ፣ የኢምፖርት ፈቃድ አሰጣጥን እና ከፍተኛ መጠን ያላቸው የመንግሥት ፕሮጀክቶች ለማን እንደ እሚሰጡ ስለ እሚወስኑ ፤ ኢተወዳዳሪነቱ ከፍተኛ ነው። የጸረ ሞኖፖሊ ሕግ እና ባለስልጣን መሥሪያቤት አለ ሆኖም ከፖለቲካ ስልጣኑ ከፍተኛ ተፅዕኖ አለበት። | **1** | ከፍተኛ ኃብት በእሚያስፈልግባቸው (capital-intensive) መስኮች ፤ ፖለቲካው ለነባር ባለኃብቶች (Oligarchic) በማድላት አዲስ ተወዳዳሪዎችን አመቺ የመወዳዳሪያ ሥፍራ ይነሳቸዋል። |
| **4. የሠራተኛ ነጻነት** | ናይጄሪያ በአንጻራዊነት ጥሩ የሠራተኛ ነጻነት አለባት ፤ | **2** | ግለሰቦች የማምረት ጉልበታቸው ነጻ ባለቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **(Labor Freedom)** | ሔርቴጅ (Heritage) በእሚባለው ድርጅት ምዘና መሠረት **73/100** (2025/2026) በማግኘት። ኢመደበኛው የኢኮኖሚ መስክ አሁንም ጉልህ ስፍራ ያለው ቢሆንም ፤ መደበኛው የቅጥር እና የቅጥር ማቋረጥ ኺደት በመንግሥት ተፅዕኖ ሳይሆን በገበያ ኹኔታ በነጻ የእሚደረግ ፤ በአጎራባች ሐገራት ከእሚታየው ይልቅ ነጻነት ያለበት እና ሠራተኞችም እንደ አሻቸው የእሚንቀሳቀሱበት ነው። | | ሆነው ያዋጣኛል ባሉበት መንገድ ከመስክ መስክ ሥራ ይቀይራሉ፤ የኢመደበኛው ቅጥር ከፍተኛ ቢሆንም። |

**የአመላካቾች አማካይ : 1 → በናይጄሪያ የግል ንብረት ባለቤትነት ደረጃ ልኬት : 3**

**2. የንብረት ተንቀሳቃሽነት (አጥዳፊ)**

| **አመላካች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **1. የውጭ ባለቤትነት** | የናይጄሪያ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ኮምሽን (NIPC Act) በእሚባለው አዋጅ መሠረት አብዛኛው መስኮች ለግል ክፍት ናቸው። ሆኖም በነዳጅ እና በተፈጥሮ ጋዝ ኢንደስትሪዎች ላይ የሐገር ባለኃብቶችን ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ በእሚል የወጣው (Oil and Gas Local Content Act) አዋጅ ፤ የሐገሪቱ ኢኮነሚ የጀርባ አጥንት በሆነው በነዳጁ መስክ ፤ በእዚኽ መልክ ሐገራዊ ተሳትፎን ለማሳደግ በእሚል ክገበያ መርሕ ውጭ ጣልቃ ይገባል። | **1** | በጠቅላላው ክፍት ነው ፤ ሆኖም በስትራቴጂኩ የነዳጅ እና የተፈጥሮ ጋዝ መስክ ፤ ሐገራዊ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ማሳደግ የእሚለው አካኼድ ፤ የውጭ ባላኃብቶችን የእሚገድብ ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **2. የመሬት ገበያ** | በ1978 የመሬት ሕግ መሠረት በእየ ፌደራሉ ክልል መሬትን መስጠት እና መንሳት የክልሉ ገዢዎች (Governor) ስልጣን ነው። እያንዳንዱ የመሬት ሽያጭ የፌደራል ክልሉን ገዢ (Governor) ይኹንታ መፈለጉ ፤ አንድ መሬት ለመሸጥ ከ6 ወር እስከ 2 ዓመት እንዲፈጅ በማድረግ እና በሽያጭ ወቅት ለእሚፈጠሩ ለሌሎች ኢመደበኛ ወጪዎች በር እንዲከፈት አድርጓል። | **0** | መሬት በነጻ ገበያ መርሕ መሠረት በቀላሉ በገበያ አይሸጥም ፤ የመሬት ሽያጭ በጣም በተንዛዛ እና በፖለቲከኞች ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ነው። |
| **3. የኃብት ቁጥጥር (Capital Controls)** | በ2024–2025 በተደረገው ማሻሻያ ፤ ናይራ የተባለውን የናይጄሪያን የመገበያያ ገንዘብ ያለውን ምንዛሪ በነጩም በጥቁሩም ገበያ አንድ ለማድረግ ቢሞከረም ሊሳካ አልቻለም። የውጭ ሐገር ኢንቨስተሮች ትርፋቸውን በዶላር ቀይረው ከሐገር ለማውጣት ሰልፍ ይጠብቃሉ ፤ የጥቁሩ ገበያም እንደ ቀጠለ ነው። | **0** | የውጭ ምንዛሪ በገበያ እንዲወሰን የማድረግ ነገር ቢኖርም ፤ በሐገሪቱ የዶላር እጥረት በመኖሩ ፤ ገንዘብ ከናይጄሪያ ማውጣት አሁንም ፈተና እና ኢተገማች ነው። |
| **4. የስቶክ ገበያው ከአመታዊ ምርቱ አንጻር (Stock Market Size -% of GDP)** | የናይጄሪያ የስቶክ ገበያ በቅርቡ እንደ ዳንግቴ እና ቢዩኤ (e.g., Dangote, BUA) ዓይነት ትልልቅ ኩባንያዎች አክስዮናቸውን በመሸጥ ስለ ተቀላቀሉት በ2025/2026 ከፍተኛ ዕድገት በማሳየት የኢከነሚው ዓመታዊ ምርት ከ 18–22% (Market Cap-to-GDP) ገደማ ደርሷል። | **1** | በጠቅላላው ልኬቱ ዝቅተኛ እና መካከለኛ በእሚል መካከል እሚቀመጥ ሆኖ ቀላል የእማይበል መጠን አለው ሆኖም ከኢኮነሚው አንጻር ሲታይ ትንሽ ነው። |
| **5. በቀላሉ ንግድ መጀመር እና መዝጋት (Ease of Starting/ Selling Business)** | ኮርፖርት አፌር የእሚባለው ኮሚሽን (Corporate Affairs Commission) የንግድ ፈቃድ አሰጣጥን ኮምፒውተራይዝድ | **1** | ንግድ ለመጀመር በኮምፒውተር የታገዘ እና ፈጣን ነው ፤ ሆኖም ንግድ መዝጋት ፤ ከግብር ዕዳ ነጻ መሆንን በማረጋገጥ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | በማድረ 24–48 hours ሰዓት እንዲያልቅ አድርጓል። ሆኖም ንግድ ለመዝጋት ፤ ግብር በማጣራት አስቸጋሪነት እና በደካማ የክስረት ሕግ (slow insolvency framework) ምክንያት አስቸጋሪ ነው። | | አስፈላጊነት ምክንያት የተንዛዛ ነው። |
| **6. ብድር ማግኘት (Access to Credit)** | ተወዳዳሪ የባንክ ዘርፍ አለ እንደ ዜኒት ፣ አክሰስ እና ጂቲባንክ (Zenith, Access, GTBank) ዓይነት ባንኮች የሚሳተፉበት ፤ ሆኖም ምንም እንኳን ባንኮች ከሚያበድሩት ብድር 50 በመቶውን ለቁጠባ ደንበኞቻቸው እንዲያበድሩ የሚያስገድድ ( "Lending-to-Deposit Ratio") ቢያውጡም ፖሊሲው ጥቃቅን የንግድ ድርጅቶች (SME) ነጋዴዎች በአነስተኛ ደረጃ የብድር ተጠቃሚ የመሆናቸውን ችግር ሊፈታው አልቻለም። አብዛኛው ብድር ከፍተኛ አስተማማኝነት ላላቸው (blue-chip corporates) ትላልቅ ኮርፖሬሽኖች እና ለመንግሥት በገበያ የቦንድ ግዢ የሚሰጡ ናቸው። | **1** | በገበያው ውስጥ ብድር አለ ሆኖም ለአብዛኛው መካካለኛ እና ከእዚያ በታች ላለ ነጋዴ በጣም ውድ እና አስቸጋሪ ነው። |

**የአመላካቾች አማካይ : 0.66 → በናይጄሪያ የንብረት ተንቀሳቃሽነት ደረጃ ልኬት: 2**

**3. የሕጉ ነጻ እና ገለልተኛነት (አንኳር)**

| **አመላካቾች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|

| | | | |
|---|---|---|---|
| **የዳኝነት ነጻነት** | የዳኝነት ስረዓቱ ተደጋጋሚ ለሆኑ የአስፈጻሚ አካሉ ጫና እና የበጀት መዘግየት የተጋለጠ ነው። | **1** | ፍርድ ቤቶች በገለልተኝነት ለመሥራት ሞያዊ ብቃቱ አላቸው ሆኖም ብዙ ግዜ ፖለቲካው ይጫናቸዋል። |
| **ሙስና** | ሙስና ስረዓታዊ ነው ፡- ጥቃቅን (Petty) በሆኑ ሆነ እንደ ነዳጅ እና የመንግሥት ፕሮጀት ማግኘት ዓይነት ትላልቅ ጉዳዮች ላይ ሙስና አለ። | **0** | በትራንስፓረንሲ ምዘና(transparency indices) መሠረተ በአብዛኛው ከፍተኛ ሙሰና አለባቸው በእሚል ከእሚቀመጡ ጎራ ይመደባሉ። |
| **የውል ተፈጻሚነት (Contract Enforcement)** | በጣም የዘገየ ነው ፡- የንግድ ክርክር በከፍተኛው ፍርድ ቤት ከ5–10 ዓመታት በላይ ሊቆይ ይችላል። | **0** | በናይጄሪያ የፍትሕ ስረዓቱ የእሚያስከፍለው የግዜ ግብር ("Time Tax") የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ኢንዲቀንስ የእሚያደርገው ዋነኛ ምክንያት ነው። |
| **በሕግ ፊት እኩልነት** | **ሕጉ በሰዎች ማሕበራዊ ደረጃ ላይ የተመሠረተ ነው** ፡- የተፅዕኖ ሰዎች እና እንደ ጡትአባት ዓይነት ሰዎች የተጻፈውን ሕግ ፋይዳ ቢስ ሊያደርጉት ይችላል። | **0** | ሕጉ የጉልበትኞች የግል መጠቀሚያ ነው ፤ ለኹሉም ዜጎች በእኩልነት ከእሚሠራ ይልቅ። |
| **ፖለቲካዊ ጣልቃገብነት** | ትልልቅ ንግዶች በፍርድ ቤት ወይንም በተቆጣጣሪ መሥሪያቤት በእሚከራከሩበት ግዜ ጣልቃገብነት ከፍተኛ ነው። | **0** | በተለይ የቁጥጥር ስረዓቱ ለተወሰኑ ትልልቅ ባለኃብቶች ያደላል የእሚል ግንዛቤ ይበዛል። |
| **የፖሊስ አስተማማኝነት** | ወጥነት ይጎድለዋል ፡- የተለዩ ሰዎችን መጠበቅ ( focused on "VIP Protection") ላይ | **1** | ደህንነት እና ጥበቃ ፤ በመንግሥት ለኹሉም ዜጎች |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ያተኩራል ኹሉንም ዜጎች እና ንብረታቸውን በእኩልነት ከመከልከል ይልቅ። | | የእሚቀርብ ከመሆን ይልቅ በገንዘብ እሚገዛ ነው። |

**የአመለካቾች አማካይ: 0.33 → በናይጄሪያ የሕጉ ነጻ እና ገለልተኝነት ደረጃ ልኬት: 1**

**4. የንግድ ክፍትነት (አጥዳፊ)**

| **አመላካቾች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የታሪፍ/ቀረጥ መጠን** | ከፍተኛ እና በጣም ተለዋዋጭ ነው። በተደጋጋሚ ምግብ እና አንድ አንድ የውጭ ሐገር ፋብሪካ ምርቶች ወደ ሐገር ውስጥ እንደ አይገቡ ይከለከላሉ። | **0** | ክልከላ (Protectionism) እንደ ኢንደስትሪያል ፖሊሲ ነው እሚታየው። |
| **ከታሪፍ ውጭ የሆኑ ክልከላዎች** | **በጣም ከፍተኛ ነው።** በሌጎስ ወደብ ያለው መጣበብ እና በእየ ድንበሩ ቀስ እያሉ የእሚከማቹ ጥቃቅን ብዙ ወጭዎቹ አሉ። | **0** | ወደብ ላይ ያለው መጨናነቅ ፤ በዕቃ ላይ ~30-50% ዋጋ ይጨምራል። |
| **የገቢ ወጭ ንግድ ከአመታዊ ምርት አንጻር (Trade - % of GDP)** | ከአመታዊ ምርቱ አንጻር ~30-40% ቢሆንም እና መካከለኛ ሊባል ቢችልም ፤ የነዳጅ ኤክስፖርት ከፍተኛ ድርሻ አለው። | **1** | እንደ ጥሬ አቅራቢነት ("Commodity Supplier") ከዓለም ዓቀፉ ንግድ ጋር ተሳስረዋል ሆኖም እንደ አምራችነት( "Global Manufacturer.") አይደለም። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **የገቢ ወጪ ንግድ ክልከላ** | በ2023 ትንሽ እስኪሻሻል ድረስ ከ43 በላይ ዕቃዎች ኢምፖርት ለማድረግ ዶላር እንደ አያገኙ ተከልክለዋል። | **0** | የገቢ ወጪ ንግድ የብሔራዊ ባንክ በእሚያወጣው ሕግ ብዙ ግዜ ይቆራረጣል። |
| **የጉምሩክ ቆይታ** | በቀርፋፋነቱ ይታወቃል ፤ እስከዛሬ (2026) ድረስ በአካል ("Manual Inspection") የእሚደረግ ምርመራ አለ። | **0** | ዕቃ የማስተላለፍ ፍጥነት (Logistical velocity) በአጎራባች ሐገራት ደረጃ እንኳን ዝቅተኛ ነው። |
| **የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት እና ሕግ አክባሪነት (WTO Compliance)** | አባል ነች ግን በተደጋጋሚ ሕጉን በመጣስ ክልከላ በማድረግ ትታወቃለች። | **1** | ሐገራዊ ጥቅምን ለማስከበር በእሚል ስልታዊ ክልከላ አለ። |

**የአመልካቾች አማካይ: 0.33 → በናይጄሪያ የንግድ ክፍትነት ደረጃ ልኬት: 1**

**5. የበጀት አስተዳደር ጥበብ (አንኳር)**

| **አመላካቾች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የግብር ተገማችነት** | ትንሽ ግብር ከፋይ (Small tax base) ነው ያለው ፤ የግብር ውሳኔ ይታይለኝ ወይንም ይቀነስልኝ የእሚሉ ጥየቃዎች በርካታ ናቸው ፤ ትልልቅ ኩባንዎች ላይ ዘፈቀደ የሆኑ የግብር መጠኖች ይጣላሉ (Arbitrary assessments on large firms.) | **1** | የመንግሥት የግብር አሰባሰብ በጣም ደካማ ነው ፤ በአማካይ የአመታዊ ምርቱን 6 በመቶ ነው (~6% tax-to-GDP ratio)። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **የበጀትን ጉድለት ለመሙላት ገንዘብ ማተም (Monetary Financing)** | የበጀት ጉድለትን ለመሙላት ብር እንዲያትም በብሔራዊ ባንኩ ላይ ከፍተኛ መደገፍ አለ። | **0** | ብሔራዊ ባንኩ እንደ ገንዘብ ምኒስትሩ የምስጢር ኪስ ነው የእሚያገለግለው። |
| **ብድርን ምርታማነትን ለማሳደግ መጠቀም (Productive Debt)** | የናይጄሪያ መንግሥት አንድ አንድ ግዜ ከ80 እስከ 90 በመቶ የእሚሆነውን የግብር ገቢውን ወለድ በመክፈል ብቻ ሊያጠፋው ይችላል። | **0** | መንግሥት በአብዛኛው ብድር የእሚበደረው ከእዚኽ በፊት የተበደረውን ብድር ለመክፈል እና የተወሰኑ ማሕበራዊ ድጎማዎች ለማድረግ ነው አስፈላጊ መሠረተ ልማቶችን ከመገንባት ይልቅ። |
| **የግሽበት መጠን** | በጣም ከፍተኛ ደረጃ ላይ ይደረሳል ፤ ከ25-30% በላይ ሆኖ ነበር 2024-2026። | **0** | የማክሮ ኢኮኖሚ ማረጋጋትን ማረጋገጥ ለባለፈው 40 ዓመታት ያዳገታቸው ነገር ነው። |
| **የብሔራዊ ባንክ ገለልተኛነት** | በጣም ዝቅተኛ ነው ፤ የናይጄሪያ ብሔራዊ ባንክ ገዢ በፖለቲካ አመራሩ ፤ የፖለቲከኛውን የፖሊሲ ግብ እንዲያስፈጽም ነው የእሚሾመው። | **0** | የሐገሪቱ የገንዘብ ፖሊሲ (Monetary policy) ሳይንሳዊ ዓላማውን ሳይሆን የሐገሪቱን ፖለቲካዊ ግብ ለማሳካት በእሚል ፤ በፖለቲካው ነው እሚዘወረው። |
| **የመገበያያ ገንዘብ ርጋታ** | በተደጋጋሚ የመግዛት አቅሙ እንዲዳከም (Frequent large devaluations) ይደረጋል ለምሳሌ፦ 2016, 2023, 2024 ፤ በጥቁር ገበያ ያለው የትርፍ መጠን ከፍተኛ ነው። | **0** | የናይጄርያው ኔያራ ምንዛሪ በጣም ተለዋዋጭ እና ለመገመት አስቸጋሪ ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **መንግሥት በእዳ የመያዝ ታሪኩ (Default History)** | መንግሥት እዳውን መክፈል ያቃተበት ግዜ የለም ሆኖም ከፓሪስ ክለብ ("Paris Club") ጋር ተደጋጋሚ የብድር ማሸጋሸግ ድርድር ይደረጋል። | **1** | የሐገር ውስጥ ብድር ግን ያለ መዛነፍ ይከፈላል ምንም እንኳን ብድሩን ለመክፈል ገንዘብ ስለ እሚያትሙ  የዋጋ ግሽበት ቢያስከትሉም። በእዚያም የሐገር ውስጡን ብድር በዋጋ ግሽበት ነው እሚከፍሉት ይባላል። |
| **የበጀት አደላደል** | **ካፔክስ (**Capex) ወይንም የመሠረተ ልማት ላይ ከማዋል ይልቅ በቢልዮን የእሚቆጠር ዶላር በሐገር ውስጥ የነዳጅ ድጎማ በማድረግ ያጠፋሉ። | **0** | የናይጄሪያ በጀት አስተዳደር የናይጄርያ ኢኮኖሚ ከፍተኛ እንቅፋት ነው። |

**የአመለካቾች አማካይ: 0.25 → በናይጄሪያ የበጀት አስተዳደር ጥበብ ደረጃ ልኬት: 1**

**በባለፈው 40 ዓመት በነበረው ግዜ ውስጥ ከአምስቱ ኹኔታ አንጻር የናይጄሪያ አፈጻጸም**

| ሐገር | ኹኔታዎች | ልኬት |
|---|---|---|
| **ናይጄርያ** | **የግል ንብረት (አንኳር)** | **2** |
| | **የንብረት ተንቀሳቃሽነት (አጥዳፊ)** | **2** |
| | **የሕጉ ነጻ እና ገለልተኛነት (አንኳር)** | **1** |
| | **የንግድ ክፍትነት (አጥዳፊ)** | **1** |
| | **የበጀት አስተዳደር ጥበብ (አንኳር)** | **1** |

**የምርመራ ውጤት: ናይጄርያ**

**ፍረጃ: ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ** (በተቃርኖ ወጥመድ የተያዘ)

- **የአንኳር ኹኔታዎች ትንተና (Core Analysis):** ናይጄሪያ የፈጠራ ልህቀት መዓከል (Sieve) ለመሆን የእምታደርገው ትግል ነባራዊ ኃብት ደንቃራ (Nigeria is a Wealth Vault ) የሆነበት ሐገር ነች። ከፍተኛ ገቢ ያለው ሐገር የመሆን ፍላጎቷ በጣማ ደካማ (Value 1) በሆነው የሕግ ስረዓቷ እና የበጀት አስተዳደሯ ተሸንፏል። ቬትናም በመንግሥት ጣልቃ ገብነት የተመራ ዕድገት ማስመዝገብ ስትችል ፤ የናይጄርያ መንግሥት በጣም ተወዳዳሪ እና አምራች የሆነው የግል መስካቸውን (Hyper-productive private sector) ተለቆ ትልቅ ውጤት እንደ አያመጣ ደንቃራ ሆኖበታል።

- **ገንዘብ የማተሙ አባዜ (The "Ways and Means" Anchor):** መንግሥት የበጀት ጉድለትን ለመሙላት በገንዘብ እትመት ላይ መደገፉ የዋጋ ግሽበትን ስውር ግብር በማድረግ የዜጎችን ቁጠባ የእሚያዳክም እና የንብረት ተንቀሳቃሽነትን በመቀነሱ ሐገሪቱ እራሷን የፈጠራ መዓከል ("Innovation Pool") ለማድረግ የእምታደርገውን ጥረት አክሽፏል።

- **የፈጠራው ማጥለያ ወንፊት (Innovative Sieve Filter):** ናይጄሪያ ኦሊጋርኮች ወድድርን በእሚገቱበት (Oligarchic Vault) ድባብ ውስጥ እንድ ኖሊውድ እና ፊንቴክ (Nollywood, Fintech) ያሉ ግለሰባዊ የሆኑ የፈጠራ (Innovation Pool ) ኢኮኖሚ ያለበት ነው። ሆኖም የፈጠራ ማጥለያው ወንፊት ሰባራ ነው ፤ ምክንያቱም ከፍተኛ ቦታ የእሚደርሱት የንግድ ድርጅቶች ከፍተኛ ምርታማ የሆኑት ሳይሆኑ የክልል መንግሥቱ ፈቃድ ("Governor's Consent") ያላቸው ወይንም የውጭ ምንዛሪ በቀላሉ ( "FX Access" ) የእሚገኙት ናቸው።

- **የማሳሰብያ ደውል (The Predictive "Premonition"):** የባለፈው አምስት ዓመት (2023–2026) ማሻሻያ እየተደረገ ነው የእሚል ምልክት ይሰጣል( "Reform Signal.") ነዳጅ ላይ የእሚደረግ ድጎማን ማንሳት እና የውጭ ምንዛሪ በገበያ እንዲወሰን የማድረግ አካኼድ የመንግሥትን የበጀት አስተዳደር ከ 1 ወደ 2 ከፍ ለማድረግ የመሞከር ነገር ናቸው። ይኽ ማሻሻያ ከተሳካ እና የታሰበለትን ግብ ካሳካ ናይጄርያ 200 ሚልዮን ሕዝብ ያለውን ኢኮኖሚዋን በከፍተኛ መጠን ከፍ ታደረገዋለች። ሆኖም በሕገሪቱ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የእሚገኘውን የሕግ የበላይነት (Impersonality of Law (1)) ወደ 3 ማሳደግ ካልቻለች ሽልማቱም አደጋውም ከፍተኛ የሆነበት ኢኮኖሚ ትሆናለች የተረጋጋ የፈጠራ ማዕከል (A stable innovation hub) ከመሆን ይልቅ።

## 4.10 ደቡብ አፍሪካ

ደቡብ አፍሪካ በተፈጥሮ ኃብት የበለጸገች የቀኝ ግዛት ፣ ከእዚያም አፓርታይዳዊ የኢኮኖሚ ብሔርተኝነት እና መገለል (Protectionism and exclusion) ውስጥ የገባች ፤ ከ1994 በኋላ ደግሞ ገበያዋን ለመክፈት እና ከዓለም ጋር ለመተሳሰር በመፈልግ የእሚገለጽ የኢኮኖሚ ታሪክ ነው ያላት። በአፍሪካ አንደኛ ደረጃ ኢንደስትሪያላይዝድ የሆነች ሐገር ብትሆንም ፦ ከፍተኛ መጠን አለእኩልነት (Inequality)፣ ተቋማዊ ድካም (Institutional fragility)፣ የማማከል ባሕል (Legacy of centralized)፣ እና ዘርን መሠረት ያደረገ ቁጥጥር ያለባት ነች።

**የቀኝ ግዛቱ የማዕድን ዘመን (Colonial and Mining Foundations)**

በ19ኛው ክፍለ ዘመን ፤ በእንግሊዝ ዘውዳዊ መንግሥት ቀኝ ግዛት ሥር ሆና ፤ የወርቅ እና የዳይመንድ መአድን እንድትሆን ነበር። ባቡር እና ወደቦች የእሚገነቡት እነ እዚኽን ማዕድኖች አውጥቶ ኤክስፖርት ለማድረግ ነበር። የሐገሩ ሰው በንግድ ላይ እንዲሠማራ አይፈለግም ነበር ፤ የመሬት ቅሚያው ደግሞ አለእኩልነቱን (Inequality) አባባሰው።

ዘፈቀደ( Arbitrary) የሆነው የቀኝ ገዢዎች ስልጣን ኃብት በጥቂት ሰፋሪዎች እጅ እንዲገባ እና ሰፊው የሐገሪቱ ኢኮኖሚ በጥሬ ዕቃ ንግድ ላይ ተደጋፊ እንዲሆን አደረገው።

**የዘመነ አፓርታይድ የኢኮኖሚ ብሔርተኝነት (Apartheid Protectionism )**

የአፓርታይዱ መንግሥት (1948–1994) ማዕቀብ እና ማግለል ይደረግበት ስለ ነበር ፤ ራስን መቻል በእሚል ፤ ከውጬ የእሚገቡ ዕቃዎችን በሐገር ውስጥ ምርት መተካት (Import substitution) የእሚል እና ይኽንም ለማሳካት የሐገር ውስጥ አምራቾችን ከውጭ ውድድር መከላከል (Protectionism) የእሚል ፖሊሲ ይከተል ነበር። ከእዚኽ እንደ እሚታየው ማዕቀብ እና ማግለሉ ይኽን ዓይነቱን ፖሊሲ እንደ አጠናከረው ነው።

ስትራቴጂክ የተባሉ ፦ የጦር መሣሪያ ማምረት ፣ ብረት ማቅለጥ እና ኃይል ማመንጨት (Sasol, Eskom) ተመራጭ መስኮች ተብለው ትኩረት ተሰጣቸው። ጉዳዩ ተወዳዳሪ የሆኑ ጥሬ ዕቃዎችን ማምረት ሳይሆን ፖለቲካዊ ስልጣንን እና የሆነውን ዘር የበላይነት ማስጠበቅ ሆነ።

በእዚኽ አካኼዱ የአፓርታይድ መንግሥት ኢንደስትሪያዊ አቅም ገንብቷል ፤ ሆኖም ሰፊውን የሕብረተሰብ ክፍል ከምርታማ የኢኮነሚ ክፍል አስወጣው።

**ዴሞክራሲያዊ ለውጥ እና ነጻ ገበያ (Democratic Transition and Liberalization)**

ከ1994 በኋላ ደቡብ አፍሪካ የንግድ ክፍትነት እና ተቋማዊ ለውጥ ውስጥ ገባች። ታሪፍ ተቀነሰ ፣ የካፒታል ገበያው በገበያ ሕግ እንዲመራ ተደረገ ፣ ሐገሪቱም ሰፊውን የዓለም ንግድ ተቀላቀለች። የጆሐንስበርጉ የስቶክ ኤክስቼንጅ (Stock Exchange) የአፍሪካ ትልቁ የአክሲዮን ገበያ ሆነ ፤ ሳውዝ አፍሪካም በማዕድን ፣ በመኪና እና በፋይናንስ የዓለምን የእሴት ሰንሰለት (Global supply chains) ተቀላቀለች። ሆኖም አለእኩልነት (Inequality) በጣም ስር በመስደዱ ፤ የደቡብ አፍሪካ የኢኮኖሚ ተቋማት ሕዝባዊ ተደራሽነት ያለው ኢኮነሚያዊ ዕድገት ማረጋገጥ ተሳናቸው።

**የቅርቡ እድሳት (Contemporary Refurbishment)**

የዛሬዋ ደቡብ አፍሪካ ድርጅዝምን (Dirigiste traditions) ከነጻ ገበያ ለማጣጣም እየሞከረች ነው። ማዕድን ፣ መኪና እና የፋይናንስ መስኩ አሁን ተመርጦ ልዩ ትኩረት ማግኘቱን እንደ ቀጠለ ነው። በውጬ የእሚመረቱ ምርቶችን በሐገር ውስጥ ምርቶች የመተካት (Import substitution) ዝንባሌ በዓለም ዓቀፉ የአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ እራስን በከፊል(Partial supply-chain integration) በማሳተፍ ተተክቷል ፤

በእዚኽም ደቡብ አፍሪካ ለአከባቢው ሐገራት እንደ መኪና መገጣጠሚያ እና የፋይናንሻል አገልግሎት (Financial services) ማዕከል ሆና ታገለግላለች።

ሆኖም ፦ የተቋማት ደካማነት ፦ ሙስና ፣ ደካማ የንብረት ባለቤትነትን የማስከበር ጉዳይ ፣ እና የበጀት ውጥረት ፤ ምርታማነት ማደግ በእሚገባው መጠን ማደግ እንደ አይችል አድርገዋል።

የደቡብ አፍሪካ ፈተና ፤ በወሳኝነት ከፖለቲካዊ ዘፈቀደ ውሳኔ (Arbitrary authority) ወደ ለኹሉም በእኩልነት ወደ እሚሠራ ፖለቲካዊ ታማኝነትን ሳይሆን ምርታማነትን ወደ እሚሸልም ስረዓት መሻገር ነው።

ይኽን መልክ ያለው የደቡብ አፍሪካ ኢኮኖሚ ወደ ምርመራው ማሽን ሲገባ ፤ ተቋማዊ መበስበስ እና መዋቅራዊ ጥንካሬ ("Institutional Decay vs. Structural Resilience.") አብረው የእሚገኙበት ሆኖ ነው የእሚታየው። ከባለፈው አርባ ዓመት የወረሰው ፤ ከፍተኛ ገቢ ካላቸው ሐገራት ጋር የእሚስተካከል የፋይናንስ እና የሕግ ስረዓት አለው ፤ ይኽ ጥንካሬ ግን አሁን በገጠመው አስተዳደራዊ ጋግርታምነት (Administrative Sclerosis) እና ከፍተኛ ድጎማ ( Consumption Anchor) ምክንያት የጥንካሬውን ያኽል ውጤት የማምጣት አቅሙ ሲሸረሸር ይታያል። በእዚኽም ኺደት ሐገሪቱ ታዳሽ የሆነ በፈጠራ ኃይል ( Productivity Sieve ) ከእሚመራ ኢኮኖሚነት ቀስ በቀስ ወደ ቆሞ ቀር አሮጌ ኃብት ጠባቂነት ( Wealth Vault ) በመቀየር ነባር ኃብቶችን እና ፍላጎቶችን ከውድድር እና ከለውጥ እሚጠብቅ ሆኗል።

**1. የግል ንብረት (አንኳር)**

| አመላካቾች | የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም | ልኬት (0–2) | ማብራሪያ |
| --- | --- | --- | --- |
| **1. ባለቤትነት** | በደቡብ አፍሪካ ከአከባቢው በተለየ መልኩ አብዛኛውን ነገር መሬትን ጨምሮ በግል ንብረትነት መያዝ ይችላል። ሆኖም ስትራቴጂክ በእሚባሉት እንደ መአድን እና የነዳጅ ኃብት በመንግሥት ጥበቃ (Custodianship) ሥር ናቸው። እንዲኹም እንደ ኃይል እና ባቡር ያሉ መስኮችም ከፍተኛ የመንግሥት ድርሻ አለባቸው። | **2** | በአብዛኛው የኢኮኖሚ መስክ የግሉ መስክ ነው ትልቁን ድርሻ ያለው ፤ በግል ንብረትነት የእማይያዙ እንደ ወንዝ ፣ አየር ፣ ወዘተ ያሉት የኹሉም የጋራ የሆኑት እና የተወሰኑ ስትራቴጂክ የእሚባሉ መስኮች ናቸው። |
| **2. ውርስ** | የሕገ መንግሥቱ ክፍል 25 የግል ንብረትን ይደነግጋል | **1** | ሕጉ ጠንካራ ጥበቃ ያደርጋል ነገር ግን አስፈጻሚ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ሆኖም የውርስ ሕግ ተብሎ ከ2024-2026 ከፍተኛ ክርክር የተደረገበት ሕግ ፤ አንድ አንድ በታዎች ለምሳሌ የተተወ መሬት (e.g., abandoned land) ያለ ምንም ካሳ ክፍያ ይወረስ ይላል። ፍርድ ቤቶች አስተማማኝ ቢሆኑም ፤ በሕግ አውጭው ፓርላም የእሚታየው ሽርተት ማለት አሳሳቢ ነው። | | እና ሕግ አውጭው ቀዳዳ እየከፈቱ እና መተማመንን እየሸረሸሩ ነው።. |
| **3. ሕጋዊውድድር (Contestability)** | ደቡብ አፍሪካ በዓለም ላይ አሉ ከእሚባሉት አንዱ የሆነ የጸረ ሞኖፖሊ መዋቅር አላት (Competition Commission)።ሆኖም ኢኮኖሚው ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ባንክ ፣ ቸርቸሮ ንግድ እና መዓድን ማውጣት ናቸው። ቢቢኢ( B-BBEE) የእሚባለው እና ብላክ ኢምፓውርመት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ፤ ፖለቲካዊ ግንኙነት ለሌላቸው አዲስ ገቢዎች ፈታኝ ሊሆን ይችላል። | **1** | ሕጉ አዲስ ገቢን ይፈቅዳል ፤ የክስረት ሕጉም ይሠራል (bankruptcy works well) ሆኖም ትልቅ ካፒታል ያላቸው ድርጅቶች መኖራቸው እና ተቆጣጣሪውም አካል ለእነ እርሱ እሚያደላ መሆኑ ፤ ውድድርን ትንሽ አዳጋች ያደርገዋል።. |
| **4. የሠራተኛ ነጻነት (Labor Freedom)** | የሥራ ገበያው በጣም ቁጥጥር አለበት። በጣም የተደራጁ እና የመደራደር አቅማቸው የጎለበተ የሠራተኞች ማሕበሮች በመኖራቸው ፤ ሠራተኛ ማባረር በጣም ዋጋ ያስከፍላል። ሠራተኞች ሥራ እንደ አሻቸው መቀየረ የእሚችሉ ቢሆንም ፤ ሠራተኛን ከደካማ | **1** | ሠራተኞች ነጻነት አላቸው ፤ ሆኖም ለአሠራር አስቸጋሪ የሆነ የሠራተኛ ሕግ በመኖራቸው እና ሠራተኛ እንደ ፈለጉ ማንቀሳቀስ የእማይቻል መሆኑ ውጥረት ይፈጥራል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | መሥክ ወደ አምራች መስክ ለማዘዋወር ከባድ ነው (While workers can choose jobs, the "reallocation" of labor from inefficient to efficient sectors is slow)። | | |

**የአመላካቾቹ አማካይ 1.25 → በደቡብ አፍሪካ የንብረት ባለቤትነ ደረጃ ልኬት: 3**

**2. የንብረት ተንቀሳቃሽነት (አጥዳፊ)**

| **አመላካቾች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **1. የውጭ ዜጋ ባለቤትነት** | ደቡብ አፍሪካ አብዛኛውን መስክ ለውጭ ዜጋ ባለቤትነት መቶ በመቶ ትፈቅዳለች። ሆኖም ሰፊ የጥቁሮችን ኢኮነሚያዊ አቅም መገንባት የእሚል (Broad-Based Black Economic Empowerment (B-BBEE)) ፖሊሲ በመኖሩ ፤ ጥቁሮችን በሽርክና ማሳተፍ ይጠይቃል የመንግሥት ፕሮጀክቶች ላይ ለመሣተፍ ወይንም አንድ አንድ ስትራቴጂክ የእሚባሉ እንደ ማዕድን ማውጣት እና ቴሌኮም ያሉ መስኮች ላይ ፈቃድ ለማግኘት። | **1** | በመርኽ ደረጃ ክፍት ነው ፤ ሆኖም የቁጥጥር መዋቅሩ እና የጥቁሮችን ኢኮኖሚ መገንባት ("empowerment") አሠራር ተሳትፎን ይገድባሉ። |
| **2. የመሬት ገበያ (Land Market)** | በአፍሪካ ውስጥ የውጭ ዜጎች መሬት በስማቸው በባለቤትነት መያዝ ከእሚችሉባቸው ጥቂት ሐገራት አንዷ ነች ደቡብ አፍሪካ። የካርታ ምዝገባው ውስብስብ ነው። ሆኖም | **1** | የሕጉ ከለላ በመኖሩ መሬት በቀላሉ እና በፍጥነት እጅ ይቀይራል ይኽም ትልቅ ገበያ ፈጥሯል ሆኖም ፤ የፖለቲካው ትርክት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | እስካሁን እያከራከረ ያለው ፤ አንድ አንድ በታዎችን ካሳ ሳይከፍሉ መውረስ ይገባል የሚለው ("Expropriation Without Compensation" (EWC)) ለብዙዎች ዘላቂ ስጋት እየፈጠረ ነው። | | እየተለወጠ መሆኑ ስጋት ፈጥሯል። |
| **3. የካፒታል ቁጥጥር (Capital Controls)** | ደቡብ አፍሪካ በብሔራዊ ባንኳ የሚመራ የካፒታል ቁጥጥር ታደርጋለች። ዜጎቿ ለትናንሽ ጉዳዮች በዓመት እስከ 1 ሚልዮን ራንድ (የደቡብ አፍሪካ ገንዘብ) ለኢንቨስትመንት ደግሞ እስከ 10 ሚልየን ራንድ የውጭ ምንዛሪ ማንቀሳቀስ ይችላሉ።በኮርፖሬሽን ደረጃ ካፒታል ለማንቀሳቀስ ግን ውስብስብ ፈቃድ እና አሠራር አለው። | **1** | ዝግ ከሚባሉት ኢኮነሚዎች በተለየ ገንዘብ ይንቀሳቀሳል ሆኖም ገንዘብ ከሐገር ለማስወጣት ቁጥጥር አለው ቁጥጥሩም ገለልተኛ ሳይሆን አስተዳደራዊ ግምት ያለበት ነው። |
| **4. የስቶክ ገበያው ከአመታዊ ምርቱ አንጻር (Stock Market Size - % of GDP)** | የደቡብ አፍሪካው ስቶክ ገበያ በአፍሪካ ትልቁ ነው። በ 2025/2026 ለሽያጭ የቀረቡ አክስዮኖች የሐገሪቱ ዓመታዊ ምርት 250–300% (250–300% of GDP) ነበር እንደ ፕሮሱዩስ እና ሪችሞንት (e.g., Prosus, Richemont) ያሉ ድርጅቶች ኹለት ቦታ አክስዮናቸውን ለሽያጭ ስለ ሚያቀርቡ። | **2** | ከፍተኛ ለመባል የሚያበቃውን 60% ደረጃ በጣም የሚያልፍ ነው ፤ ገበያውም ብዙ ገንዘብ የሚንቀሳቀስበት እና በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ትልቅ ቦታ ያለው ነው። |
| **5. በቀላሉ ንግድ መጀመር እና መዝጋት (Ease of Starting/ Selling Business)** | በኮምፒውተር የታገዘ ፈቃድ የማውጣት ስረዓት ስለ አለ ፈቃድ ማውጣት ቀላል ነው ፤ ሆኖም ጉቦ እና አስተዳደራዊ መንጎታቶች በመኖራቸው መስተጓጎል ይኖራል። ንግድ መሸጥ በጣም ቀላል ነው ፤ ነገር ግን የጥቁርን ኢኮኖሚ አቅም ማሳደግ (B-BBEE) የሚለውን | **1** | ሕጉ ይሠራል ፤ ሆኖም አስተዳደራዊ ችግሮች ፤ አዲስ ንግድ መጀመር እና ሽጦ መውጣትን ያከብዱታል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ሕግ የማክበር አስፈላጊነት ለአዲስ ገቢዎች አስቸጋሪ ያደርገዋል ፤ እንደ እዚኹም በዋጋ ትመና ላይ ችግር ይፈጥራል ፤ ገዢም ያሸሻል። | | |
| **6. ብድር ማግኘት** | ደቡብ አፍሪካ አንደኛ ደረጃ የባንክ አገልግሎት አለ (Standard Bank, FirstRand, Nedbank, Absa)። ለግሉ መስክ የተሰጡ ብድሮች ከአመታዊ ምርቱ አንጻር (Private sector credit-to-GDP) ከ~70%+ በላይ በመሆን ከፍተኛ ነው። ሆኖም ከ2026 ጀምሮ የወለድ መጠን መጨመሩ (~10.25%) እና ባንኮች ለማበደር መስጋት መጀመራቸው ያሳያል። አነስተኛ እና መለስተኛ (SMEs) ነጋዴዎች ማስያዣ የእማይፈልግ ብድር ለማግኘት ይቸገራሉ። | **1** | የብድር ገበያው ብዙ ገንዘብ የእሚንቀሳቀስበት (deep) ፣ ሞያዊ ልቀት የእሚታይበት እና ቋሚ ንብረት ላላቸው ተደራሽ ነው ፤ ምንም እንኳን ለዝቅተኛው የሕብረተሰብ ክፍል ውድ ቢሆንም። |

**የአመለካቾቹ አማካይ: 1.17 → በደቡብ አፍሪካ የንብረት ተንቀሳቃሽነት ደረጃ ልኬት: 3**

**3. የሕጉ ነጻ እና ገለልተኛነት (አንኳር)**

| **አመለካቾች** | **የባለፉት 40 ዓመታት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የዳኝነት ነጻነት** | ሕገመንግሥታዊም ሆነ ሕጋዊ ፍርድቤቶቹ ከፍተኛ የዳኝነት ነጻነት አላቸው። | **2** | ፍርድ ቤቶች በዳኞች የሐገሪቱን ፕሬዝደንት ጨምሮ ወይንም በአስፈጻሚዎች ላይ መበየናቸው የተለመደ ነው። |
| **ሙስና** | እንደ ኤክሶም እና ትራንስኔት(Eskom, Transnet) | **0** | ዞንዶ የተባለው አጣሪ ኮምሽን (The Zondo |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ባሉት የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ስረዓታዊ የሆነ ሙስና እንደ ነበር ታይቷል። | | Commission) በከፍተኛ ደረጃ የእሚገለጽ የተቋማዊ ገለልተኝነት ችግር እንደ አለ አሳይቷል። |
| **የውል ተፈጻሚነት** | አስተማማኝ ነው ሆኖም ወረፋው ብዙ በመሆኑ በእየግዜው አፈጻጸሙ እየዘገየ ነው። | **1** | ውሳኔው ተገማች ቢሆንም ከፍተኛ የሰዓት ግብር ("Time Tax.") ያስከፍላል። |
| **በሕግ ፊት እኩልነት** | የሕግ መዋቅሩ ጠንካራ ነው ሆኖም ፖለቲካዊ ትስስር ላላቸው ሰዎች ተጠያቂነት እምብዛም ነው( High-level "Impunity" )። | **1** | ለነጋዴው ማሕበረሰብ ሕጉ የእኩልነት ሜዳ ነው ፤ ለፖለቲካዊ ሊህቁ ግን የግል ጥቅም ማስከበሪያ ነው። |
| **ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት** | በዳኝነት ስረዓቱ ላይ አናሳ ነው ፤ ለመንግሥት ሥራ እና ፖሊስ ሹመት ግን በፖለቲካ ሹመት ነው። | **1** | የመንግሥታዊ ግልጋሎት አሠጣጥ ጥራት እየተሸረሸረ ነው ፤ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ባብዛኛው እሚሾመው ካድሬ በመሆኑ። |
| **የፖሊስ አስተማማኝነት** | ዝቅተኛ እና እያሽቆለቆለ ነው። ማሕበረሰቡ ከግዜ ወደ ግዜ የግል ጥበቃ ድርጅቶችን ወደ መጠቀም እየዞረ ነው። | **0** | መሠረታዊ ደህንነት አሁን የግል እና እንደ ሸቀጥ ከገበያ የእሚገዛ እንጂ ለኹሉም ዜጎች በእኩልነት የእሚቀርብ መንግሥታዊ አገልግሎት አይደለም። |

**የአመላካቾቹ አማካይ: 0.83 → በደቡብ አፍሪካ የሕጉ ነጻ እና ገለልተኛነት ደረጃ ልኬት: 2**

**4. የንግድ ክፍትነት (አጥዳፊ)**

| **አመላካቾች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|

| | | | |
|---|---|---|---|
| **የቀረጥ መጠን** | መካከለኛ ። እንደ ሴኩ እና ሳድክ ( SACU and SADC) ቀጠናዊ የነጻ ንግድ ቀጣና አባል ናቸው። | **1** | አማካይ የቀረጥ መጠን ከ ~7-8% ነው ሆኖም የሸቀጥ ማራገፍን ለመከላከል የእሚለው ቀረጥ የተለመደ ነው። ("Anti-Dumping" duties are frequent.) |
| **ከቀረጥ ውጭ ያሉ ክልከላዎች** | **ግግር የሆነ ዕቃ የማስተላለፍ ችግር አለ (Logistical Sclerosis.)** ደርባን ወደብ ላይ ከፍተኛ መዘግየት አለ ትራንስኔት (Transnet) የእሚባለው ባቡር ብዙ ይቋረጣል። | **0** | የመሠረተ ልማት መዳከም እንደ ንግድ ገደብ (de facto trade barrier) ሆኗል። |
| **የገቢ ወጪ ንግድ ከአመታዊ ምርት አንጻር (Trade - % of GDP)** | ~60% ገደማ በመሆን ከፍተኛ ነው ፤ ማዕድን ኤክስፖርት ማድረግ የኢኮኖሚው የልብ ትርታ ነው። | **2** | ከዓለም ዓቀፉ የማዕድን አቅርቦት ጋር በጣም የተሳሰረ ነው። |
| **የገቢ ወጪ ንግድ ክልከላ** | አናሳ ነው ፤ ምንም እንኳን የመዓድን ፈቃድ ለማግኘት ከፍተኛ ቁጥጥር ቢኖርም። | **2** | ከፍተኛ የሆነ ሸቀጥ የማስተላለፍ ነገር አለ። |
| **የግሙሩክ ቆይታ** | በአባዛኛው ቀልጣፋ ነው ሆኖም ከ 2024–2026 የመብራት እና የኮምፒውተር መቆራረጥ ችግር ፈጥረውበታል። | **1** | ከጉምሩኩ ይልቅ ወደብ ላይ ያሉ መንጓተቶች ከፍተኛ መዘገየት እና የዋጋ ጭማሪ ያስከትላሉ። |
| **የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት እና ሕግ አክባሪነት (WTO Compliance)** | ንቁ ተሳታፊ እና ሕግ አክባሪ። | **2** | ባለፈው 40 በጥሩ ኹኔታ የዓለም ዓቀፍ ንግድ ውስጥ ተሳትፏል። |

**የአመላካቾቹ አማካይ: 1.33 → በደቡብ አፍሪካ የንግድ ክፍትነት ደረጃ ልኬት: 4**

**5. የበጀት አስተዳደር ጥበብ (አንኳር)**

| **አመላካቾች** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የግብር ተገማችነት** | ከፍተኛ ነው ፤ የደቡብ አፍሪካው የገቢዎች ሚኒስትር SARS (Revenue Service) ብቁ ነው ሆኖም የግብር ከፋዩ ትንሽ ነው( tax base is extremely narrow.) | **2** | በጣም ተገማች ነው ፤ የበጀት ውጥረት ግብር እንዲጨምር ብዙ ጫና እያሳረፈበት ነው። |
| **የበጀት ጉድለት ለመሙላት ገንዘብ ማተም (Monetary Financing)** | በሕገመንግሥት ደረጃ ክልክል ነው ፤ የደቡብ አፍሪካው ብሔራዊ/ሪዘርቭ ባንክ (SARB (Reserve Bank) ) ዓለም ዓቀፋዊ ደረጃውን የጠበቀ ነው (world-class.) | **2** | **የደቡብ አፍሪካው** ብሔራዊ/ሪዘርቭ ባንክ (SARB (Reserve Bank) ) በሐገሪቱ ውስጥ በሞያዊ ስነምግባር እና ልቀት ተወዳዳሪ የለውም። |
| **ብድርን ምርትን ለማሳደግ መጠቀም (Productive Debt)** | አሳሳቢ ደረጃ ላይ ነው ፤ ብድር ከኢኮኖሚው አመታዊ ምርት አንጻር ከ75 በመቶ በላይ እየደረሰ **(**Debt-to-GDP >75%) ነው።ከእዚኽ ብድር ደግሞ አብዛኛ እንደ እስኮም (Eskom) ዓይነት ወዳቂ የመንግሥት የልማት ኩባንያዎችን ከውድቀት ለመታደግ ነው እሚውለው። | **0** | ብድር ቀዳዳ መሸፈኛ እንጂ ምርታማነት ማሳደጊያ አይደረግም። |
| **የግሽበት ደረጃ** | ምንም እንኳን ብዙ ጫናዎች ቢኖሩም ፤ 3-6% ሆኖ የመቆየት ግቡን ያሳካል። | **2** | በደቡብ አፍሪካው ብሔራዊ ባንክ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ብቃት የዋጋ ግሽበትን መቆጣጠር ተችሏል። |
| **የብሔራዊ ባንኩ ገለልተኛነት** | **የደቡብ አፍሪካው** ብሔራዊ/ሪዘርቭ ባንክ (SARB (Reserve Bank) ) ወርቃማ ተምሳሌታዊ ተቋም ነው። | **2** | ፈጽሞ ከፖለቲካ ውጣ ወረድ ነጻ ነው። |
| **የመገበያያ ገንዘብ ርጋታ`** | የራንድ ምንዛሪ (The Rand (ZAR)) በጣም ተለዋዋጭ ነው ሆኖም ለኢኮኖሚው እንደ ማስተንፈሻ ያገለግላል። | **1** | ከፍተኛ መጠን ያለው እና በገበያ የእሚወሰን ምንዛሪ ነው ፤ ሆኖም ምንዛሪው ይለዋወጣል። |
| **በእዳ የመያዝ ታሪክ (Default History)** | እንከን አልባ ብድር የመክፈል ታሪክ ነው ያለው። | **2** | የመንግሥትን እዳ ለመክፈል ከፍተኛ ቁርጠኝነት አለ። |
| **የበጀት አደላደል** | በዓለም ላይ የበጀታቸውን ከፍተኛ ክፍል ለደሞዝ እና ለማሕበራዊ እርዳታ ከእሚጠቀሙ መንግሥታት መካከል ይመደባል። | **0** | አብዛኛው ለፍጆታ ስለ እሚውል የመሠረተ ልማት ግንባታ በቂ በጀት አያገኝም። |

**የአመላካቾች አማካይ: 1.37 → በደቡብ አፍሪካ የበጀት : 3**

**ከአምስቱ ኹኔታዎች አንጻር በባለፈው 40 ዓመት በደቡብ አፍሪካ የነበረው አፈጻጸም**

| **ሐገር** | **ኹኔታዎች** | **ልኬት** |
|---|---|---|
| **ደቡብ አፍሪካ** | **የግል ንብረት (አንኳር)** | **3** |
| | **የንብረት ተንቀሳቃሽነት (አጥዳፊ)** | **3** |
| | **የሕጉ ገልተኛነት እና ነጻነት  (አንኳር)** | **2** |
| | **የንግድ ክፍትነት (አጥዳፊ)** | **4** |
| | **የበጀት አስተዳደር ጥበብ (አንኳር)** | **3** |

**የምርመራ ውጤት: ደቡብ አፍሪካ**

**ፍረጃ: ከፍተኛ መካከለኛ ገቢ ያለው ኢኮኖሚ** (ሠላማዊ መልክ ግን ውስጣዊ ነውጥ የያዘው ኢኮኖሚ)

- **የአንኳር ኹኔታዎች ትንተና (Core Analysis):** ደቡብ አፍሪካ ከፍተኛ ገቢ ያለው ኢኮኖሚ የመሆን የእሚያስችል ተቋማዊ ኹኔታ ያላት እና በአስተዳደራዊ ችግር ምክንያት ከፍተኛ መካከለኛ ገቢ ላይ ያለች ኢኮኖሚ ነች ። በበጀት አስተዳደር ደህና የእሚመስል (3) ቢኖራትም ያ በደቡብ አፍሪካው ብሔራዊ ባንክ ልሀቀት የመጣ እና ደካማ የሆነ በፍጆታ ላይ ያተኮረ የበጀት አደላደሏን የእሚደብቅ ነው።

- **ዕቃ የማስተላለፍ ግግርት (The "Logistical Sclerosis" Brake):** የንግድ ክፍትነት **4** ቢሆንም በወረቀት ላይ በዝቅተኛ መጠን ታሪፍ ምክንያት ፤ ይኽ ከፍተኛ ውጤት ያለው የንግድ ክፍትነት ግን በተዳከመው የሐገሪቱ መሠረተ ልማት ምክንያት ውጤታማ መሆን አልቻለም። በመንግሥት አስተዳደር ሥር ባሉት ወደቦች እና ትራንስኔት (Transnet) የእሚባለው የባቡር መሥመር  እንዲኹም ኤስኮም (Eskom) በእሚባለው ኤልክትሪክ ኩባንያ ምክንያት ኢኮኖሚው ነባራዊ ኃብትን እሚከላከል (Vertical Barrier) ፈጠራ እና ተወዳዳሪነትን ( Innovation Pool) እሚያበረታታ አልሆነም።

- **የፈጠራ ማጥለያ ወንፊቱ (Innovative Sieve Filter):** ደቡብ አፍሪካ በባንክ እና በማዕድን መስክ ለተሰማሩት እና ብሔራዊ ጅግኖቼ ለእምትላቸው ኩባንያዎች የኃብት ምሽግ ( Wealth Vault) ለዜጎቿ ደግሞ የማሕበራዊ ዋስትና ነች (Social Safety Net) በእዚኽ ኺደት ግን የኢኮኖሚያዊ ታዳሽነት እና የፈጠራ አቅም (Productivity Sieve) አድክማ አጥፍታለች። የብራዚል ኢኮኖሚ መለያ እንደ ሆነው እና በብራዚል መነገድ ዋጋ ያስከፍላል የእሚባለው ከስቶ ብራዚል(The "Custo Brasil") ጋር የእሚመሳሰለው የደቡብ አፍሪካ አስተዳደራዊ ችግር እና የጥቁርን አቅም ማሳደግ (BEE ) የእሚለውን ሕግ ማክበር ግዴታ በጣም ከፍተኛ ተወዳዳሪነት ያላቸውን አነስተኛ እና መለስተኛ (SMEs) የንግድ ድርጅቶች ራሳቸው ማሳደግ እንደ አይችሉ አድርጓል።

- **የማስጠንቀቂያ ደውል (The Predictive "Premonition"):** የምርመራው ማሽን 2026 ላይ ሆኖ ሲያየው  ደቡብ አፍሪካ ተቋማዊ መገንጠል ( "Institutional Divergence." ) እያመጣች መሆኑን ያሳያል ። የግሉ መስክ ከመንግሥት ጋር ያለውን ትስስር እየበጠሰ ፦ የእራሱን ኃይል ማመንጫ እየገነባ ፣ የእራሱን ፖሊስ እየቀጠረ ፣ የእራሱን ዕቃ ማስተለለፍ (its own logistics) እየጀመረ እንደ ሆነ ያሳያል። የሕጉ ገለልተኛነት እና ነጻነት በእዚኽ መልኩ ማዘቅዘቁ ከጠለ ( Impersonality of Law (2)) እና የሙስና መረቦች መንግሥትን የማገት ("State Capture") ልማዳቸውን ካስቀጠሉ ፤ ደቡብ አፍሪካ አሁን ከእምትገኝበት ከፍተኛ መካከለኛ ግቢ ( Upper-Middle tier) ደረጃ ልትወርድ ትችላለች.

## 4.11 ቻይና

### 1. የመሐሉን መንግሥት አስተሳሰብ ያናጋው የቀኝ ግዛት ጫና (The Middle Kingdom and the Shock of Extraction 17ኛው እስከ –1949)

ለብዙ መቶ ዓመታት ቻይና እራሷን ፤ የዓለም የስነምግባር እና የፖለቲካ በላይነት መሐል (Middle Kingdom) እንደ ሆነች አድርጎ በአሚረዳ እና በዙሪያዋ ያሉ ሐገራት እና ማሕበረሰቦች ፤ ከእዚክ ከመሐሉ የቻይና ስልጣኔ በራቁ ቁጥር ኋላቀር እና አረመኔ (Barbarian) አድርጎ በእሚያቀርብ ፍልስፍና/አስተሳሰብ ነበር ስትመራ የቆየችው። ለምሳሌ ፦ ቪየትናሞች ከአውሮፓዊያን ለመሐሉ ስለ እሚቀርቡ ፤ ቪየትናሞችን የተሻለ ስልጣኔ አደርገው ያስቡ ነበር።

ከእዚኽም የተነሳ ፤ ቻይና የዓለም ብሌን በመሆኗ እና ሌላው ደግሞ በእርሷ ዘንድ የተሰበሰበ ተድርጎ ስለ እሚታይ ፤ ቻይና ለሌች ሐገሮች ከእርሷ ጋር እንዲነግዱ መፍቀድ ፤ የጋራ ተጠቃሚነት ሳይሆን ፤ ከስልጣኔ ማዕከሏ ጋር እንዲነግዱ የተሰጠ ልዩ ጥቅም ወይንም ችሮታ ተደርጎ ይወሰድ ነው የነበረው።

ይኽ እራስን ከፍ አድርጎ የማየት ብሔራዊ ግንዛቤ ፤ ቻይኖች ከእንግሊዝ ጋር የፆፒየም ጦርነት (Opium Wars) በእሚባለው ጦርነት ተሸንፈው እና የተዛባ ስምምነት ("Unequal Treaties") እንዲፈርሙ ሲገደዱ እና ይኽንንም የተዛባ ስምምነት እንግሊዝ ከቻይና ጋር የነበራትን የንግድ ጉድለት ለመሙላት ስትጠቀምበት ፤ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበት ፤ ቻይኖች በራሳቸው ከመኩራራት በራስ ወደ መጠራጠር ገቡ።

የተዛባ ስምምነት ("Unequal Treaties") በተባለው ስምምነት ፤ ቻይና በወደቦቿ ላይ የፈለገችውን ዓየነት ቀረጥ የመጣልን ጨምሮ ሌሎች በርካታ መብቶቿን ተነፈገች ፤ አብሮም በቻይና ሕግ የእማይተዳደሩ ነገር ግን በቀኝ ገዢዎቹ የእሚተዳደሩ ከተሞችን እና ወደቦችን ለምዕራባዊያን ፤ ከልለው ወይንም "አጥረው" እንዲሰጡ ተገደዱ።

ይኽ የቀኝ ግዛት ዘመን አካኼድ በቻይና ላይ ያደረሰው ብሔራዊ ውርደት እና የኢኮኖሚ ብዝበዛ ፤ በቻይና ውስጥ ከፍተኛ ቁጭት እና ጸረ ኮሎኒያሊዝም ስሜት መፍጠሩ ነበር ፤ በኋላ ጸረ ኮሎኒያሊዝም ዝንባሌ ላለው የማርክሲዝም ጽንፈኝነት ቻይናዎችን ያጋለጣቸው።

### 2. የማዖ ዘመን ከራራ አካኼድ እና የፈጠረው ልማት አልባ ቁጥጥር (Maoist Rigidity: Control Without Development 1949–1978)

የማዖ ዘመኗ ቻይና ፤ ልዩ መታወቂያዋ ማዖ ያስተዋወቀው ፤ ሙላውን ማሕበረሰብ እና መላውን የማሕበረሰብ እንቅስቃሴ ፍጹም የሆነ ማሕበራዊ እና ፖለቲካዊ ቁጥጥር ውስጥ ማስገባቱ ነበር።

- **ተቋማዊ የሆነ የሕዝብ እንቅስቃሴን መግታት ነበር (Institutional Immobilization):** ኹኮ (The *hukou)* የእሚባለው የመኖሪያ ፈቃድ አሰጣጥ ፤ የቻይናን ሕዝብ የከተማ እና የገጠር ነዋሪ በእሚል ከፈለና ፤ የገጠር ነዋሪ ተብለው የተለዩት ዜጎች ፤ የገጠር የግብርና መሬታቸውን በሕብረት በባለቤት እንዲይዙት እና በማሕበር እንዲያርሱት ብሎም ገጠራቸውን

ለቀው ወደ ከተማ እንደ አይመጡ አደረገ። የእዚኽ ዓላማው አንድ ነበር ፦ ገበሬዎቹ በጋራ ከእሚያርሱት ምርት ላይ ፤ በጋራ አርሰው በግል ቢያርሱ ከእሚያገኙት በላይ ከፍተኛ ምርት አገኙ የእሚል የውሸት ትርክት በማድረግ ፤ ገበሬዎቹ ከፍተኛ መጠን ያለው ትርፍ ምርት ወደ መንግሥት ጎተራ እንዲያስገቡ እና መንግሥትም ይኽን ትርፍ የግብርና ምርት ኤክስፖርት እያደረገ በገቢው ትላልቅ ኢንደስትሪ እንዲገነባ ነበር። ሆኖም የጋራ እርሻው ግን እንኳንስ ትርፍ ምርት አብዝቶ ፤ የመንግሥትን ኢንደስትርላይዜሽን ፋይናንስ ሊያደርግ ፤ ገበሬውን በርኃብ ነበር የጨረሰው።

- **ገበያን ማስቀረት (Suppression of Markets):** በማዖ ዘመኗ ቻይና የግል ንግድ ክልክል ነበር ፣ የግል ንብረት ባለቤትነት ክልክል ነበር ፣ እናም ሸማችነት እና ሸቀጥ መግዛት (consumption) እንደ ቡርዣነት የእሚታይ እና የእሚያስኮንን ነገር ሆኖ ነበር።

- **የመሠረተ ልማት ግንባታ ቻይናን ከዓለም ለማስተሳሰር ሳይሆን ራስን በመቻል ስም ለመነጠል ነበር (Isolationist Infrastructure):** በማዖዋ ቻይና መንግሥት የመሠረተ ልማት ላይ ኢንቨስት ያደርግ የነበረው ወታደር እና የፖለቲካ ካድሬ በመላ ሐገሪቱ በቀላሉ ማንቀሳቀስ እንዲችል እንጂ ንግድን ለማቀላጠፍ አልነበረም። ምንም እንኳን ይኽ አካኼድ መንግሥት በመላ የሐገሪቱ ክፍል መድረስ እንዲችል እና ሕዝብን በእሚፈልገው መንገድ ማንቀሳቀስ (Mobilize) የመቻል አቅምን ቢፈጥርም ፤ ከኢኮኖሚ አንጻር ግን ከፍተኛ የእድገት ፍላጎት ያለው ነገር ግን እንደ ተረገጠ ስፐሪንግ ("compressed spring") እምቅ አቅሙ ታፍኖ የተያዘ ማሕበረሰብ ስለ ፈጠረ ፤ የማዖ የስልጣን ዘመን በእሚያበቃበት አከባቢ ፤ የቻይና ሕዝብ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በመሐል መንግሥት አስተሳሰቡ ፤ እንደ አረመኔ (Barbarian) ከእሚያያቸው እንደ ጃፓን ካሉ በዙሪያው ካሉ ሐገራት አንጻር እንኳን ዝቅተኛ ሆኖ ነበር።

## 3. የሕዝብን መፍትኼ የራስ በማስመሰል የተጀመረ ለውጥ (The Pivot: Reform as Tactical Accommodation 1978–Present)

ከ30 ዓመታት ለእሚበዛው ግዜ በማዖ ፖለቲካ ቻይና እራሷን ከንግዱ ዓለም ነጥላ ከቆየች በኋላ ፤ ከ1978 ጀምሮ ግዴታ በወለደው ውዴታ በተመረጠ መልኩ እራሷን ከዓለም ንግድ ጋር አስተሳሰረች።

የቻይናው መንግሥት ድህረ ማዖ ይኽንን ዓይነት ለውጥ እንዲያመጣ ያደረገው የአመራሩ ብስለት አልነበረም ፤ ይልቁንም የማዖ መንገድ የፈጠረው ረኃብ የፈጠረው ጫና ያስከተለው የገበሬ "አመጽ" ነበር። ገበሬዎቹ በማዖ መንገድ ላይ አምጸው ፤ የግል አምራች ራሳቸውን ማድረጋቸው ደግሞ ፤ የጉልበት እና የመሬት አጠቃቀማቸውን ስለ አሳደገው ፤ ግብርናው ምርት ማሳደግ ብቻ ሳይሆን ብዙ ሠራተኛም ከግብርና አላቀቀ ፤ ይኽን ከግብርና ወጥቶ የእሚመጣ ሠራተኛ በከተማው ላይ ያሳደረው ጫና ነበር ቻይናን የለወጡትን የነጻ የኢኮኖሚ ዞኖች የፈጠረው።

- **ከታች ወደ ላይ የመጣው ግፊት (Bottom-Up Impulse):** በቻይና ለውጥ ሲመጣ ከፍተኛው የፖለቲካ አመራር ግንዛቤው አድጎ አዲስ አቅጣጫ በመቅረጹ አልመጣም ይልቁንም ፤ ሺያጋንግ (Xiaogang) በእሚባለው አከባቢ ይኖሩ የነበሩ ገበሬዎች በጋራ ማረስ

ያደረሰባቸውን ድህነት እና ረኃብ ለማምለጥ እስክ ሞት ድረስ ሊያስቀጣ የእሚችል እምቢተኝነት በማሳየት ፤ በሚስጥር የጋራ መሬታቸውን በግል አርሰው ፤ ለመንግሥት ገቢ የእሚደረገውን የኮታ ግዴታቸውን ከግል እርሻቸው ለመክፈል በመወሰናቸው ነው። ይኽም በጋራ ከማረሱ ዘመን በከፍተኛ ደረጃ የእሚበልጥ ምርታማነትን ስለ አስከተለ ፤ በጋራ እረሱ እምቢ ብትሉ ጸረ አብዮተኞች ተብላችሁ ትገደላላችሁ ያለው መንግሥት ፤ የእርሱ መንገድ ሳይሆን የገበሬው መንገድ ከፍተኛ ምርት አምጥቶ ሲያየው እና ይኽንን ጥፋት ብሎ መቅጣት ስለ ከበደው ፤ የእራሱን አሠራር በመለወጥ ፤ አዲሱን የገበሬዎቹን አካኼድ ፤ የቤተሰብ ግዴታ ስረዓት ( Household Responsibility System) የእሚል ስም ፤ ከማሕበር ግዴታ ይልቅ ፤ ሰጥቶት ፤ ሕጋዊ አሠራር በማድረጉ ነው።

- **የልዩ ኢኮኖሚ ዞኖቹ አሠራር (The SEZ Model):** በሺያጋንግ (Xiaogang) የተጀመረው የግብርና ለውጥ በሐገር ደረጃ በትንሽ ጉልበት ከፍተኛ የግብርና ምርት ዕድገት ማስመዝገብ በመቻሉ ፤ ቀላል የእማይባሉ የቻይና ገጠር ነዋሪዎችን ከግብርና ውጭ ሌላ የእሚቀጥራቸው መስክ እንዲፈልጉ አድርጓቸው ነበር ፤ ከእዚኽ የተነሳ ሕጉ ባይፈቅድም በመቶ ሚልዮኖች የእሚቆጠሩ የቻይና የገጠር ሰዎች ፤ ጠንካራ ሠራተኝነታቸውን በርካሽ ለማቅረብ (cheap, disciplined migrant labor) ወደ ቻይና ከተሞች በገፍ መፍለስ ጀመሩ ። ፍጹም አምባገነናዊ ስልጣን ያለውን የቻይናው መንግሥት ይኽን ርካሽ ጉልበት ወደ ልዩ ኢኮኖሚው ዞን አስገብቶ ፤ ልዩ ዞኑ ርካሽ ጉልበቱን በግብዓትነት በመጠቀም የዓለም ፋብሪካ አንቀሳቃሽ አንድ ሞተር እንዲሆን አደረገው። ውጤቱም በ1978 አከባቢ ከሰላሳ ሺ በታች ነዋሪዎች የእሚኖሩበት በጭቃ የተሞላ የድኃ አሳ አጥማጆች ከተማ የነበረው እና አኹን ከ17 ሚልየን በላይ ነዋሪዎች የእሚኖሩበት የሆነው እና አይደለም በቻይና በዓለም ደረጃ በዘመናዊ ከተማነት ከቀዳሚዎች ጎራ የእሚመደበው ሸንዠን(Shenzhen) ዓይነት ልዩ የኢኮኖሚ ዞን (Special Economic Zones) የሆኑ ከተሞች ነበር።

- **የገንዘብ ጭቆና (Financial Repression):** ግብርናው እና ኢንደስትሪው በእዚኽ መንገድ ገንዘብ እና ጉልበት (ሠራተኛ) ሲፈጥሩ ፤ ይኽ አካኼድ ያመጣውን የሕዝብ ቁጠባ (ኃብት) መንግሥት ስትራቴጂክ ወደእሚላቸው መስኮች የሐገሪቱን ገንዘብ ለመንዳት (Direct) የባንክን የቁጠባ ወለድ ከገበያው መጠን በመቀነስ ለትልልቆቹ መስኮች ብድርን እያረከሰ ፣ ዜጎች ከቁጠባ ውጭ ያሉ የግል ኢንቨስትመንት አማራጮችን እየቀነሰ እና ለግል የሚገኙ ብድሮችን በመቀነስ ፤ ዜጎች በግለሰብ ደረጃ ኃብት የመፍጠር አቅማቸውን በማዳከም ፤ የግለሰቦችን የኢኮኖሚ ትርፍ ወስዶ ወደ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አስተላለፈ። በእዚኽ መልኩ ነበር እንግዲኽ የቻይና መንግሥት ከፍተኛ የመሠረተ ልማት ማምጣት የቻለው።

## 4. አኹን የገጠመው ፈተና ፤ አስተዳደራዊ ግግርነት (The Current Challenge: Administrative Sclerosis)

የዛሬዋ ቻይና የኢኮኖሚ እና የማሕበራዊ ተቋሞቻን ከነጻነት እና ከገበያ አንጻር ማደግ በእሚገባቸው መልኩ ሳታሳድግ ፤ ነገር ግን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ያስመዘገበች ("Growth without Conversion") ኢኮኖሚ ተምሳሌት ሐገር ሆና ነው የእምናገኛት ፡

- **የብድሩ ወጥመድ (The Debt Trap):** ቻይና ዓመታዊ የዕድገት ግቦቿን የእምታሳካው ፤ ለማስቀጠል የእሚፈልጉት ወጪ በጣም ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ አክሳሪ ለማለት ነጭ ዝሆን[11] የእሚባሉ ታላላቅ ፕሮጀክቶችን የሐገሪቱ ምርት እስከ 300% (300% of GDP) በደረሰ ከፍተኛ ብድር በመሥራት ነው። ይኸም ቻይናን ከጃፓን ቀጥሎ ትልቁ ብድር ያለባት ሐገር አድርጓ ለከፍተኛ የእዳ ጫና ዳርጓታል።

- **ተቋማዊ መዛል (Institutional Exhaustion):** መንግሥት የቻይናን የደሞዝ ተወዳዳሪነት ለማረጋገጥ የሠራተኛን ደሞዝ ከገበያው በታች በፖሊሲ ውሳኔ ዝቅ እንዲል ስለ አደረገ ፤ በሐገር ውስጥ ሠራተኛው የመግዛት አቅሙ ተዳክሟል ፤ ይኸም በኢኮኖሚው ውስጥ ጥየቃን (demand) እንዲቀንስ አድርጓል ፤ ይኸም የቻይና ኢኮኖሚ ከአቅሙ በላይ የእሚያመርት ነገር ግን የእሚያመርታቸው ምርቶች ገዢ ስለ እሚያጡ ዋጋቸው እንዲወርድ በማድረግ ከአቅም በላይ ማምረት እና ገዢ ማጣት (overcapacity and deflation) የቻይና ኢኮኖሚ ችግር እንዲሆን አድርጓል።

የቻይና መጻኢ ከኢኮኖሚ አንጻር ዘፈቀደ (arbitrary authority) ከሆነው የመንግሥት ስልጣን ፤ ለኹሉም በእኩልነት ተጠያቂነት እና ግልጸኝነት ወደ አለው የተቋማዊ አደረጃጀት ትሻገራለች ወይንስ ሰው የሐገር የኢኮኖሚ ዕድገት መሠረት ነው ከማለት ይልቅ ሰውን እንደ አንድ ቁሳዊ ግብዓት የእድገት መሳሪያ አድርገን እንጠቀምበታለን በእሚል ትቀጥላለች በእሚለው ይወሰናል።

ቻይናን በባለፈው 40 (1986–2026) ዓመት ከአምስቱ ኹኔታዎች አንጻር የነበራትን አፈጻጸም ተመርኩዘን በመመርመሪያው ማሽን ውስጥ ስናሳልፋት የእሚከተሉትን መልክ ያለው ምዘና እናገኛለን፡-

**1. የግልን ንብረት (አንኳር)**

| **አመላካቾች** | **የባለፈው 40 ዓመታ አፈጸጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **ባለቤትነት** | ምንም እንኳን የግል ንግድ በስፋት ቢገኝም ፤ የከተማ መሬት | **1** | ለተንቀሳቃሽ ንብረት ባለቤትነት ይችላል ሆኖም መሬት እና |

[11] ነጭ ዝሆን ቶሎ ቶሎ ስለ እሚቆሽሽ ማጠቡ እና ማጽዳቱ ከባድ ነው ፤ ስለእዚኽ ፦ ነጭ ዝሆን በእሚል የእሚገለጹ ፕሮጀክቶች ከእሚሰጡት ጥቅም ይልቅ የእሚያስወጡት ወጪ የእሚበልጡ ናቸው ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የመንግሥት ንብረት ሲሆን ፤ የገጠር መሬት ግን የመንደሩ ነዋሪዎች የጋራ ንብረት ሆኖ ፤ በግል ሊያዝ አይችልም። ስትራቴጂክ የእሚባሉት ፡- ባንኮች ፣ ኃይል ፣ ቴሌኮም ፤ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ናቸው። | | ስትራቴጂክ የእሚባሉ ንበረቶች አሁንም ክልከላ አለባቸው። |
| **ውርስ** | ንብረትን ከውርስ ከመከላከል አንጻር ጥሩ የሕግ መሻሻሎች አሉ ፤ ሆኖም ፤ በተለይ መንግሥት ዓመታዊ የዕድገት ግቡን ለማሳካት ሲል መሬትን በተደጋጋሚ ይወርሳል ፤ በእዚኽ ግዜ የእሚከፍለው ካሳም ከገበያው ዋጋ በጣም ዝቅ ያለ ነው። | **1** | ከፍተኛ መጠን ያለው የመወረስ አደጋ አለ ፤ በተለይ ደግሞ የገጠር መሬቶች ፍረጃቸው ወደ ከተማ በእሚለወጥበት ግዜ ። |
| **ሕጋዊውድድር(Contestability )** | በቻይና የንብረት ባለቤትነት | **0** | በቻይና ንብረት በጥቂቶች ያለውድድር |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ከፖለቲካዊ ስልጣን በእርሱ ውሳኔ ወደ ጥቂቶች የእሚወርድ ነው(state-to-elite)። የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የወለድ ክፍያው አናሳ የሆነ እና መሠል የብድር ማቅለያዎች ይሰጣቸዋል ፤ በአንጻሩ የግል ነጋዴዎች ብድር ለማግኘት ብዙ ይቸገራሉ ፤ አስተዳደራዊ ድንዛዜውም ("Administrative Sclerosis") ብዙ ዋጋ ያስከፍላቸዋል። | | የመያዝ(oligarchic) ኹኔታ አለበት። መንግሥት የአከባቢ መንግሥታት የእሚያቋቁማቸው እና ሎካል ገቨርመንት ፋይናንሲንግ ቬህክልስ (LGFVs) ለእሚላቸው እና ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች ቅድሚያ ይሰጣል ፤ ወደ ገበያ አዲስ ለመግባት ከእሚፈልጉት ይልቅ። |
| **የሠራተኛ ነጻነት (Labor Freedom)** | የኹኮው ስረዓት (The *hukou* system) የሠራተኛ ነጻ እንቅስቃሴን ይግድባል ፤ ይኽም ከገጠር ወደ ከተማ ሥራ ፍለጋ የእሚሰደዱ ሰዎችን ሕገ ወጥ | **1** | ሠራተኞች እንደ አሻቸው ሥራ መቀየር ይችላሉ ፤ ሆኖም ያሉት ተቋማዊ ገደቦች እና የመንቀሳቀስ ገደቦች ፤ በምርታማነታቸው እንደ አይወዳደሩ ያደርጋቸዋል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ሥራ ፈላጊ ስለ እሚያደርጋቸው ፤ እንደ ሕጋዊ ሰው በሥራ ገበያ የመወዳደር አቅማቸውን ይገድባል። | | |

**የአመላካቾቹ አማካይ :** 0.75 | **በቻይና የንብረት ባለቤትነ ደረጃ ልኬት : 2**

**2. የንብረት ተንቀሳቃሽነት (አጥዳፊ)**

| **አመላካቾቹ** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የውጭ ዜጎች ባለቤትነት** | በሽርክና ወይንም በልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች ውስጥ የውጪ ሐገር ዜጎች ኢንቨስት ማድረግ ይችላሉ ፤ ሆኖም በርካታ መስኮች ፤ የኢንቨስትመንት መጠን ገደብ አለባቸው ወይንም አዕምራዊ ንብረታቸውን በመስዋትነት እንዲያቀርቡ ይገደዳሉ። | **1** | ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ኢንቨስትመንት አለ ሆኖም ቁጥጥሩም በእዚያው መጠን ስለ ሆነ ፤ ቁልፍ በሆኑ ዘርፎች የውጭ ባለቤትነት ሙሉ በሙሉ እንደ አይሆን ገደብ አለ። |
| **የመሬት ገበያ** | መሬት መሸጥ አይቻልም ፤ የመጠቀም መብት ወይንም ሊዙ ብቻ ነው እሚሸጠው። በተለይ የገጠር የአከባቢ መንግሥታት ዋነኛ የገቢ ምንጫቸው ፤ የገጠርን መሬት ወደ ከተማ በመለወጥ እርሱን በማስያዣነት በማቅረብ | **0** | ነጻ የሆነ የመሬት ገበያ የለም ፤ መሬት በገበያ ውስጥ በገበያ ዋጋ መሠረት እጅ የእሚለውጥ ሳይሆን መንግሥት የበጀት ገንዘቡን የእሚያገኝበት ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ከእሚያገኙት ብድር ወይንም እርሱን ብሊዝ በመሸጥ ከሚያገኙት ትልቁን የበጀታቸውን ምንጭ የእሚያገኙት። | | |
| **የካፒታል ቁጥጥር (Capital Controls)** | በቻይና ገንዘብ ከሐገር ውስጥ ማስወጣት ከፍተኛ ቁጥጥር አለበት ፤ የቻይናው ሬንምቢም (The Renminbi) ለምሳሌ ፦ ወደ ዶላር ቀይሮ ዶላሩን ከሐገር ለማስወጣት ከሆነ ፤ እንደ አይመነዘር ክልከላ አለበት። | **0** | በሐገሪቱ ጥብቅ የካፒታል ቁጥጥር ስለ አለ ፤ ሰዎች የተለያዩ ክፍተቶችን ተጠቅመው የቻይናውን ገንዘብ ወደ ውጭ አውጥተው መልሰው በቀጥታ ኢንቨስትመንት መልክ ያስገቡት እና በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ስም እንደ አሻቸው ማስወጣት ማስገባት እሚችሉበትን ኹኔታ ይፈጥራሉ ("round-tripping" )። |
| **የስቶክ ገበያው ከኢኮኖሚው አመታዊ ምርት አንጻር (Stock Market Size** | የሻንጋይ እና የሼንዜን የስቶክ ገበያዎች በጣም ትልልቅ ናቸው ሆኖም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ናቸው ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው። የመንግሥት ጣልቃ ገብነትም የእሚበዛባቸው ናቸው። | **1** | ገበያዎቹ ትልልቅ ናቸው ፤ የኢኮኖሚውን ዓመታዊ ምርት ~20-60% በመድረስ (~20-60% GDP historically) ሆኖም ገለልተኛ የሆኑ እና ኩባንያዎች ማስፋፊያ በገበያ ዋጋ መሠረት የእሚያገኙባቸው ሳይሆኑ መንግሥት ካፒታል እሚደለድልበት አንድ መንገድ ናቸው(state-directed funding vehicles)። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **ንግድ ለመጀመር እና ለመዝጋት ያለ ቅለት (Ease of Starting/Selling)** | በልዩ የኢኮኖሚ ዞኖቹ ንግድ መጀመር ቀላል ነው ፤ ሆኖም የከሰሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚዘጉበት አጋጣሚ ጥቂት ነው እንደ እዚኹም ስትራቴጂክ የሚባሉ ንብረቶችን መሸጥ ከባድ ነው። | **1** | በልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች ውስጥ ሙስና አይኖርም ፤ ሆኖም ክስሮ ለመውጣት መንገዱ ዝግ ነው። |
| **በቀላሉ ብድር ማግኘት ይቻላል (Access to Credit)** | ለብድር የሚሆነው ገንዘብ አለ ፤ ሆኖም መንግሥት ለልማት ድርጅቶች እና ለአከባቢ መንግሥታት (LGFVs) እንዲኼድ ነው እሚያደርገው ፤ አነስተኛ እና መለስተኛ ንግዶች (SMEs) የመበደር አቅማቸውን የሚጎዳ ፋይናንሻል ጫና ("financial repression") ይደርስባቸዋል። | **1** | ከፍተኛ መጠን ያለው ብድር ይንቀሳቀሳል ሆኖም ስርጭቱ የፖለቲካ ውሳኔ ነው በገበያ መሠረት ከመሆን ይልቅ። |

**የአመላካቾች አማካይ:** 0.66 | **በቻይና የንብረት ተንቀሳቃሽነት ደረጃ ልኬት: 2**

### 3. የሕጉ ነጻ እና ገለልተኛነት (አንኳር)

| አመለካቾች | የባለፈው 40 ዓመታት አፈጻጸም | ልኬት (0–2) | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| **የዳኝነት ነጻነት** | ፍርድ ቤቶች በፓርቲው ነው እሚታዘዙት ፤ የዳኝነት ስረዓቱ ትኩረቱ የመንግሥትን ስልጣን ለመገደብ ከመሆን | **0** | ለተለመዱ የንግድ ጉዳዮች ሕጉ ተገማች ነው ፤ ነገር ግን ወሳኝ ለሚባሉ ጉዳዮች( sensitive cases) |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ይልቅ ፖለቲካዊ ቁጥጥርን ማረጋገጥ ነው ። | | በፖለቲካው ነው እሚታዘዘው ። |
| **ሙስና** | ከፍተኛ የጸረ ሙስና ዘመቻ አለ ፤ ሆኖም ሙስና ተቋማዊ እንደ ሆነ ቀጥሏል ምክንያቱም ሙስናን በተቆማዊ አሠራር ሳይሆን በፖለቲካ ውሳኔ መዋጋት ስለ እሚፈልጉ። | **1** | ሙስና እንደ መደበኛ ስራ ማስኬጃ ተደርጎ አይወሰድም ሆኖም አስተዳደራዊ ድንዛዜውን ("Administrative Sclerosis") ለማንቃት ግን አስፈላጊ ነው። |
| **የውል ተፈጻሚነት** | በትልልቅ ከተሞች እና በልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች ውስጥ (SEZs/major cities) ውሎች ተፈጻሚነት አላቸው ሆኖም መንግሥታዊ ይዘት ያላቸው ተቋማትን እና የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን (State actors or SOEs) በውል መሠረት ማስገደድ እማይታሰብ ነው። | **1** | ውሉ በዜጋ(በእኩዮች) መካከል ከሆነ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ፤ ሆኖም ዜጋው ከመንግሥት ወይንም ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች ጋር ከሆነ ፤ ተፈጻሚነቱ ይዳከማል። |
| **በሕጉ ፊት እኩልነት** | ጥቂት ልሂቃን እና የመንግሥት ተቋማት ፤ ሌላው መደብኛው ዜጋ ፤ በገጠርም በከተማም ፤ ከእሚዳኝበት ሕግ ውጭ ይንቀሳቀሳሉ። | **0** | የኹኮው ስረዓት (The *hukou* system) እና ከፓርቲው ጋር ቅርርብ ያላቸው ድርጅቶች በሐገሪቱ ሕጉ የኹሉም እኩል አገልጋይ እንደ አይሆን ያደርጋል። |
| **ፖለቲካዊ ተፅዕኖ** | ማሕበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ግቦቹን ለማሳካት፤ መንግሥት በገበያ እና በሕግ ስረዓት ውስጥ ተደጋጋሚ ጣልቃገብነት ያደርጋል ። | **0** | በቻይና ሕግ ከመንግሥት ስልጣን በላይ ሆኖ ኹሉምንም በእኩልነት የእሚያገለግል ሳይሆን የመንግሥት መጠቀሚያ መሣሪያ ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **የፖሊስ አስተማማኝነት** | ፖሊስ ማሕበራዊ መረጋጋትን ለማምጣት እና መንግሥት ዕውቅና የእሚሰጣቸውን ምርቶች ለመጠበቅ ውጤታማ ነው ፤ ሆኖም የጭቆና መሣሪያም ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። | **1** | ለደህንነት እና ለማሕበራዊ መረጋጋት አስተማማኝ ነው ፤ ሆኖም ከመንግሥት ፖሊሲ ጋር ለተስማሙት ነው አስተማማኝነቱ። |

**የአመላካቾቹ አማካይ :** 0.50 | **በቻይና የሕጉ ነጻነት እና ገለልተኝነት ደረጃ ልኬት: 2**

**4. የንግድ ክፍትነት (አንኳር)**

| **አመላካቾቹ** | **የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም** | **ልኬት (0–2)** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|
| **የታሪፍ መጠን** | የዓለም የንግድ ድርጅት አባል ከሆኑ በኋላ (Post-WTO entry) ታሪፍ በጣም ቀንሰዋል ሆኖም የነጻ ገበያ ካለባቸው ሐገራት አንጻር ከፍተኛ ነው። | **2** | ቻይናዎች በጋራ በኹሉም ላይ የእሚጥሉት ቀረጥ ዝቅተኛ ነው ፤ የቻይናን ዓለም ዓቀፍ የንግድ መዓከልነትም ከፍ አድርጎታል። |
| **ከታሪፍ ውጭ ያሉ ክልከላዎች** | የፈቃድ አሰጣጥ መንዛዛት ፣ ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች (SOEs) የእሚደረጉ ድጎማዎችም ፣ የውጭ ኢንቨስተሮች የቴክኖሎጂ ማስተላለፍ እንዲያደርጉ የእሚያደርጉ ግዴታዎች ፤ ስውር የሆነ የንግድ ክልከላዎች ሆነዋል። | **1** | መደበኛ ታሪፎች ዝቅተኛ ናቸው ፤ አስተዳደራዊ ክልከላዎች እና ምዕራቡ ሐገር በሩን እንዲከፍትላቸው እየጠየቁ ራሳቸውን በታዳጊ ስም እያቀረቡ ምዕራቡ እንዲያከብርላቸው የእሚጠብቁትን ሕግ እነሱ አለማክበር (Asymmetric practices) በጣም የተለመደ ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **የገቢ/ወጪ ንግድ ከኢኮኖሚው አመታዊ ምርት አንጻር (Trade % of GDP)** | የገቢ/ወጪ ንግድ ከፍተኛ የቻይና ኢኮነሚ ሞተር ነው ፤ ሺዢፒንግ (Xi jinping) መጥቶ የወል ብልጽግና ("Common Prosperity") በእሚል ኢኮኖሚያዊ እኩልነት ለማሻሻል ፤ ድጎማ ማብዛት እና የኃብት ቁጥጥር ዓይነት አስተዳደራዊ የኃብት ማከፋፈል አካኼዶችን ማበራከት ፤የገቢ/ወጪ ንግዱን እድገት መገደብ እስኪጀምር ድረስ በከፍተኛ ደረጃ እያደገ ነበር። | **2** | የቻይና ኢኮኖሚ ከዓለም ዓቀፉ ኢኮኖሚ ጋር የተሳሰረ ነው። ቻይና በዓለም ላይ ትልቁ የገቢ ወጪ ንግድ መጠን ነው ያላት ። |
| **የገቢ/ወጪ ንግድ ላይ ያሉ ክልከላዎች** | የነጻ ኢኮኖሚ ዞኖች ውስጥ (SEZs) አብዛኛዎቹ ሸቀጦች ያለ ምንም ክልከላ ይገባሉ ፤ ሆኖም መንግሥት ቁልፍ ጥሬ ዕቃ የሚባሉትን ዕቃዎች ኢምፖርት የማድረጉን እና ስትራቴጂካዊ የእሚላቸውን ምርቶች ኤክስፖርት ይቆጣጠራል። | **1** | የፋብሪካ ግብዓቶች እና ውጤቶች በአብዛኛው ነጻ ናቸው ፤ ስትራቴጂክ የእሚባሉ የተወሰኑ ዕቃዎች ግን ቁጥጥር አለባቸው። |
| **የጉሙርክ ቆይታ** | እንደ ሻንጋይ እና ሼንዞን ያሉት የቻይና ወደቦች በዓለም ላይ ካሉ በቅልጥፍናቸው ከእሚታወቁ ወደቦች መካከል ናቸው። | **2** | በወደብ አገልግሎት ልማት ላይ በጣም ከፍተኛ መጠን ያለው ኢንቨስትመንት ስለ አደረጉ ፤ የግሙርክ አገልግሎትን በጣም ፈጣን እና ተገማች አድርገውታል። |
| **የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት እና ሕግ** | አባልነት ከ2001 ጀምሮ አግኝተዋል ፤ ሕጉንም | **1** | በጠቅላላው ሕጉን ያከበራሉ ማለት ይቻላል ፤ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **አክባሪነት (WTO Compliance)** | በአብዛኛው ያከብራሉ ፤ ሆኖም የሕጉን “መንፈስ” ግን በድጎማ እና ለመንግሥት የልማት ድርጅት በእሚሰጡት ልዩ እንክብካቤ ይጥሱታል። | | ሆኖም መርጠው የእሚተገብሩት ነገር በመኖሩ ከዓለም ዓቀፉ ማሕበረሰብ ጋር ውጥረት ውስጥ ያስገባቸዋል። |

**የአመላክቾች አማካይ:** 1.50 | **በቻይና የንግድ ክፍትነት ደረጃ ልኬት: 4**

## 5. የበጀት አስተዳደር ጥበብ (አንኳር)

| አመላካቾች | የባለፈው 40 ዓመት አፈጻጸም | ልኬት (0–2) | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| **የግብር ተገማችነት** | በቻይና የግብር ስረዓት የኢንደስትሪ ፖሊሲው አካል ተደርጎ ስለ እሚወሰድ ፤ ለትላልቅ የግል ድርጅቶች (High-profile private firms) ከሕጉ ወጭ የሆነ አሠራር ሊኖር ይችላል። | **1** | ለተለመዱ የንግድ እንቅስቃሴዎች በአብዛኛው ተገማች ነው  ሆኖም የወል ብልፅግና ("Common Prosperity") በእሚለው አዲስ አካኼድ እና በወቅታዊ የፖለቲካ ድባቦች ምክንያት ድንገት ከሕግ ውጭ የሆኑ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። |
| **የበጀት ጉድለት ለመሙላት ገንዘብ ማተም (Monetary Financing)** | የቻይና መንግሥት ብሔራዊ ባንኩን ገንዘብ እንዲያትም ቀጥታ አያዘውም ሆኖም ፤ የመንግሥት ባንኮችን ለአከባቢ መንግሥታት እና ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች (LGFV and SOE) ከገበያ ሕግ ውጭ ፤ ማለትም ፡- የተበዳሪነት ምዘናቸው እራሱ እና | **1** | በመደበኛነት በጣም ዝቅተኛ መጠን ያለው ገንዘብ የማተም ልምድ ነው ያለው ፤ ሆኖም ባንኮችን ተጠቅሞ የተመረጡ የከሰሩ ድርጅቶች እና መንግሥታዊ ተቋማት ጉድለታቸውን በብድር እንዲሞሉ የማድረግ አካኼድ አለ። ውጤቱም ገንዘብ ከማተም ጋር ተመሳሳይ ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የመክፈል አቅማቸው ደካማ ቢሆንም ወይንም የተበላሸ ከፍተኛ መጠን ያለው ብድር ቢኖርባቸው እንኳን ብድር እንዲሰጣቸው ሊያደርግ ይችላል። | | |
| **ብድርን ለምርታማ አገልግሎት ማዋል (Productive Use of Debt)** | መጀመሪያ ላይ የቻይና መንግሥት የእሚወስደውን ብድር ፤ ዓለም ዓቀፍ ተወዳዳሪነት (World-class infrastructure) ያላቸው መሠረት ልማቶችን ነው የገነባበት ፤ የቅርብ ዘመኑ ብድር ግን ነጫጭ ዝሆኖች የሆኑ እና ሰው አልባ ("White elephants" and ghost cities) ትልልቅ ከተሞችን ለመገንባት ነው የተጠቀመባቸው። | **1** | ከብድር አጠቃቀም አንጻር የቻይና መንግሥት የእሚወስደውን ብድር ከፍተኛ ምርታማነት ላላቸው ቁልፍ መሠረተ ልማቶች ከማዋል ወደ የፖለቲካ ጉራ ወደ እሚነፋባቸው የታይታ ፕሮጀክቶች (Politically-driven prestige projects) ተሸጋግሯል። |
| **የዋጋ ግሽበት** | ባለፈው 40 ዓመት በቻይና የዋጋ ግሽበት ዝቅተኛ ነበር ፤ እንዲያው የሕዝቡ የመግዛት አቅም ከኢኮኖሚው ከፍተኛ የማምረት አቅም ጋር የመመጣጠን ችግር ስለ አለበት ፤ ከቅርብ ግዜ ወዲኽ የዋጋ ማሽቆልቆል እና ከአቅም በላይ ማምረት ያጠቃቸዋል (Deflation recently due to | **2** | የፍጆታ ዕቃዎች ግሽበት ለብዙ አስርት ዓመታት በቁጥጥር ስር ውሏል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | overcapacity and weak demand.) | | |
| **የብሔራዊ ባንክ ነጻነት** | የቻይና ሕዝብ ባንክ (The PBOC ) የእሚባለው የቻይና ባንክ ነጻ አይደለም ፤ በመንግሥት የአስፈጻሚ ካውንስል እና በፓርቲ አመራር ሥር ነው። | **0** | በቻይና የገንዘብ ፖሊሲ (Monetary policy ) የገንዘብን ዋጋ በገበያ መወሰኛ መሣሪያ ሳይሆን የመንግሥትን ዓመታዊ የእድገት እቅድ ማሳኪያ እና ሕብረተሰቡን ተጭኖ ገንዘብ በፖሊሲ ለተመረጡ መስኮች ማቅረቢያ መንገድ ነው። (is a tool for state-led growth and financial repression, not an independent check.) |
| **የመገበያያ ገንዘብ ርጋት (Currency Stability** | ቻይና ተወዳዳሪ ኤክስፖርተር ለመሆን የገንዘብ ምንዛሬዋን በከፍተኛ ደረጃ ነው የእምትቆጣጠረው ፤ በእዚኽም እንደ አይዋዥቅ ማድረግ ተችሏል። | **2** | ምንም እንኳን የቻይናን ገንዘብ በቀላሉ ወደ ሌላ የውጭ ሐገር ገንዘብ መመንዘር ቁጥጥር ቢበዛበትም ፤ ነገር ግን የምንዛሪ መጠኑ ረጅም እቅድን ሊያግዝ በእሚችል መልኩ የተረጋጋ ነው። |
| **በእዳ የመያዝ ታሪክ (Default History)** | የቻይና መዓከላዊ መንግሥት ጠንካራ ብድር የመክፈል ልምድ አለው ፤ ምንም እንኳን የአከባቢ መንግሥታት (LGFV) እና የሪል ስቴት ኩባንያዎች ብድር የመክፈል አቅማቸው እየተዳከመ ቢሆንም። | **1** | መዓከላዊ መንግሥቱ ጥሩ ብድር ከፋይ ነው ፤ ሆኖም በክልል መንግሥታት ውስጥ ያለው የእዳ ጉድ (debt in LGFVs) በጣም ከፍተኛ ነው። |
| **የበጀት አደላደል** | በቻይና በጀትን ለማሕበራዊ ድጎማ እና | **1** | በቻይና ከፍተኛ የመሠረተ ልማት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ለፍጆታ ከማዋል ይልቅ ለመሠረት ልማት የማዋል ዝንባሌ አለ ፤ እንደ ብራዚል ካሉት በተለየ ። እንድያውም በቻይና የመሠረተ ልማት ትኩረት መጠኑን ስለ ሳተ ፤ ባሸበረቀ ሐገር የእሚኖሩ ድኃ ሰዎችን እየፈጠረ ነው። | | ኢንቨስትመንት አለ ሆኖም የመሠረተ ልማት ኢንቨስትመንቱ የማሕበራዊ ድጎማውን ስለ ጎዳው ፤ ሕዝቡ ለነገው በመስጋት ከፍተኛ የቁጠባ ባሕል ፈጥሯል ፤ ይኽ ደግሞ ቁጠባው እንዲበዘበዝ እንዲኹም የመግዛት አቅሙ እንዲዳከም አድርጓል። የሕዝቡ የመግዛት አቅም መዳከም እና አዋጭ የቁጠባ መንገድ አለመኖሩ ፤ አንዱ ትልቁ የቻይና ኢኮኖሚ ፈተና ነው። |

**የአመለካቾቹ አማካይ:** 1.12 | **በቻይና የበጀት አስተዳዳር ጥበብ ደረጃ ልኬት: 3**

ከ(1986–2026) እስከ አለው የ40 ዓመት ግዜ ውስጥ የቻይና ኢኮኖሚ ከአምስቱ ኹኔታዎች አንጻር ያለውን አፈጻጸም ስንገመግም የእሚከተለውን እናገኛለን ፡-

| ሐገር | ኹኔታዎች | ልኬት |
|---|---|---|
| ቻይና | የግል ንብረት | **2** |
| | የንብረት ተንቀሳቃሽነት | **2** |
| | የሕጉ ነጻ እና ገለልተኝነት | **2** |
| | የንግድ ክፍትነት | **4** |
| | የበጀት አስተዳደር ጥበብ | **3** |

**የምርመራ ውጤት**

**ፍረጃ: ከፍተኛ መካከለኛ ገቢ ያለው ኢኮኖሚ** (በመቀዛቀዝ ላይ/በወጥመድ የተያዘ ኢኮኖሚ)

**1. የአንኳር ኹኔታዎች ትንተና (The Core (Stabilizer) Analysis)**

ቻይና የተቋም ተቃርኖ ከአሚታይባቸው ሐገራት ተርታ የእምትመደብ ነች። አንኳር ኹኔታዎቿን ስንመለከት ኹለት መልክ ያላቸው ናቸው :- ተወዳዳሪ ሊባል የእሚችል የበጀት አስተዳዳር ጥበብ (Fiscal Discipline 3) እና መለስተኛ የሆነ የግል ንብረት ባለቤትነት ( Private Property 2) እና የሕግ የበላይነት (Impersonality of Law 2) የእሚገኝባት ነች።

- **የሕጉ ክፍተት የፈጠረው ወጥመድ (The Law Trap):** ሕጉ ከኹሉም በላይ ሆኖ ኹሉንም በእኩልነት ከእሚያገለግል ይልቅ ፓርቲው ከሕጉ በላይ ሆኖ ሕጉን የእሚመራው በመሆኑ ("vertical" subordinated to Party command) የንብረት ባለቤትነት አስተማማኝ ሕጋዊ ዋስትና የለውም። ይኽም የቻይና ዜጎች ገንዘባቸው በሐገራቸው ዋስትና እንደ ሌለው እንዲያውቁ ስለ አደረጋቸው ፤ ገንዘባቸው አሾልከው አውጥተው ዋስትና ባለበት ሐገር አስቀምጠው እንደ ውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መልሰው እንዲያስገቡት ("round-tripping") አድርጓቸዋል።

- **የፊዝካል ቅዠት (Fiscal Illusion):** ምንም እንኳን ቻይና የበጀት ጉድለቷን ለመሙላት በቀጥታ ገንዘብ ማተም ውስጥ ባትገባም ፤ ከእርሱ ጋር ተመሳሳይ የሆነ እና ተመሳሳይ አሉታዊ ውጤት ያለው የአከባቢ መንግሥታት የገንዘብ ምንጭ (Local Government Financing Vehicles LGFVs) በእሚባለው አሠራር ትተካዎለች ። ይኽም የሐገሪቱን ብድር ከኢኮነሚው አመትዊ ምርት አንጻር በ300% (exceeding 300% of GDP) በላይ በማሳደግ ከፍተኛ የእዳ ጫና ፈጥሯል ፤ በእዚኽም ሐገሪቱ የዋጋ ግሽበትን ዝቀተኛ በማድረግ እና የመንግሥትን ዕዳ በመክፈል የገነባችውን ስኬት እየሸረሸረ ነው።

**2. የአጥዳፊዎቹ ትንተና (The Accelerator (Mobilizer) Analysis)**

ቻይና የንግድ ክፍትነትን ከፍተኛው ደረጃ ላይ በማድረስ (Trade Openness 4) እራሷን ከዝቅተኛ ገቢ ሐገርነት አዘልላ ወደ ከፍተኛ መካከለኛ ገቢ ያለው ሐገርነት ለማሳደግ በእጅጉ ተጠቅማበታለች። ሆኖም ዛሬም በቻይ የንብረት ተንቀሳቃሽነት ከፍተኛ ደረጃ ላይ (Asset Mobility 2) በአለመድረሱ የኢኮኖሚውን ጎትቶ ወደ ኋላ እያስቀረው ነው።

- **የተመጠነ መከፈት (Managed Exposure):** መንግሥት የካፒታል ቁጥጥር (capital account closed) በማድረግ እና ሬንምቢ (Renminbi) የተባለውን የቻይና ገንዘብ እንደ አይመነዘር በማድረግ ፤ የሐገሪቱ ካፒታል በሐገር ውስጥ ተቀምጦ የመሠረተ ልማት ግንባታን እንዲያስችል አድርጓል። ይኽ የተመጠነ መከፈት (This "Managed Exposure") መጀመሪያ ላይ ከፍተኛ ኃብት በማንቀሳቀስ ሐገር ገንብቷል አሁን ግን መሥመሩን እየሳተ (massive misallocation of capital**)** የነጫጭ ዝሆን ("white elephant") ፕሮጀክቶች እና ሰው አልባ ከተሞች(ghost cities) ወደ መገንባት ተቀይሯል።

- **የኹኮው ውጥረት (The Hukou Friction):** በኹኮ ስረዓት አማካኝነት ሠራተኛው እንደ አሻው በመላው ሐገሪቱ ተንቀሳቅሶ ጉልበቱን እንዲሸጥ አለመፍቀዱ ፤ ታታሪ እና

በርካሽ የሚሠራ (a disciplined, cheap workforce) የሰው ኃይል በማብዛት መጀመሪያ ላይ የቻይና ኢኮኖሚ "ተዓምር" ሞተር ቢሆንም ፤ አሁን ግን ቻይና ወደ ከፍተኛ ገቢ ያለው የፍጆታ ኢኮኖሚ( high-income consumption-led economy) ለመሻገር የምታደርገውን ሽግግር እንደ አይሳካ ወጥመድ ሆኗል።

### 3. የፈጠራው ወንፊት እና ሕጋዊሽሚያ (The Innovative Sieve: Contestability)

በቻይና ለንብረት ሕጋዊ ውድድር ( Contestability ) ማድረግ ዝቅተኛ (0) ውጤት ነው ያለው። በቻይና የንብረት ባለቤትነት እንደ ኹሉም እኩል መብት በመሆኑ ዜጎች በተወዳዳሪ አምራችነታቸው ልክ ባለኃብት የሚሆኑበት (Productivity Sieve) ሳይሆን እንደ ልዩ ጥቅም ሆኖ የነባራዊ ባለኃብቶች ምሽግ (Oligarchic Vault) ሆኖ ነው ያለው።

- **የባላአባዎች መብት (Vertical Rights):** ሕጋዊ መዋቅሩ ከመንግሥት ጋር ትሥሥር ያላቸውን ባላምባዎች (elite) ጥቅም ፤ በተለይ ደግሞ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ( particularly State-Owned Enterprises SOEs) መርኽ አልባ ብድር እና ሕጋዊ ከለላ እየሰጠ መንከባከብ ላይ ያተኮረ ነው።

- **በውድድር ማሸነፍ ተገድቧል (Creative Destruction Blocked):** መንግሥት ሕዝቡ በባንክ የቆጠበውን ገንዘብ ወለድ በመቀነስ እና በኪሳራ በማበደር ፤ የሚከስሩ ሞትእምቢ (zombie) ድርጅቶችን ክስረት ማሕበረሰቡን ስለ እሚያስከፍል (Because the state socializes the losses of inefficient incumbents zombie firms) ፤ የቻይና ኩባንያዎች በተወዳዳሪነት ከእሚቀጥሉ ይልቅ በመንግሥት ድጎማ ነው እሚቀጥሉት ይኽም የቻይናን ኢኮኖሚ ታዳሽነት አበላሽቷል። ከእዚኽም የተነሳ ቻይና አሁን የምትገኘው የፈጠራ ማዕከል የሆነች ሐገር (Innovation Pool) በመንግሥት አስተዳደራዊ ድንዛዜ ( Administrative Sclerosis) ምክንያት የፈጠራ አቅሟ ተገድቦ ያለች ሐገር ሆና ነው። ምንም እንኳን በመንግሥት ግፊት እንደ ኤሌክትሪክ መኪና እና ስፔስ ሳይን (EVs, Space) ባሉ መስኮች ፈጠራ ቢኖሩም ፤ ሌላው እና ሰፊው የኢኮኖሚው መስክ ግን ለውጥ የሚሸሽ ነው።

### ማጠቃለያ

ቻይና አመባገነናዊ በሆነ መልኩ ሕዝብ በማንቀሳቀስ እና የቻይናን ኢኮኖሚ ከዓለም ዓቀፍ ኢኮኖሚ ጋር በከፍተኛ ንግድ ክፍትነት (4) በማስተሳሰር በማያ ዘመን ተርግጦ የቆየው ኢኮኖሚያዊ ስፕሪንግ ("Compressed spring") ወይንም እምቅአቅም (Potential) ተለቆ ፤ ማምጣት የሚችለውን እድገት በሙሉ አሟጣ ተጠቅማ ጨርሳለች።

ከእዚኽም የተነሳ ፤ ከእዚኽ በኋላ ቻይና ርካሽ ጉልበት እና የካፒታል አቅም በመጠቀም ኢኮኖሚያዋን የማሳደግ እና ተወዳዳሪ መሆን አትችልም ፤ ከእዚኽ በኋላ በፓርቲ ውሳኔ ሳይሆን <u>በትክክል</u> ኢኮኖሚዋን ማሳደግ የምትችለው በገበያ ሕግ እና ሕግ ብቻ ነው።

ሆኖም ቻይና ኢኮኖሚያዋን በገበያ መሠረት ለማሳደግ ተቋማዊ ለውጥ ማድረግ ስለ እማትፈልግ እና በካፒታል ክምችት እና በርካሽ ጉልበት የማደግ እድሏን አሟጣ ስለ ተጠቀመች ፤ እራሷን የመካከለኛው ገቢ የእሚባለው ወጥመድ (Middle Income Trap) ውስጥ አግኝታለች ፤ የእድገት ድንበሯን ማስፋት የእምትፈልግ ነገር ግን ለአዲስ የእድገት እርከን የእሚመች ተቋም በማጣት።

ቻይና አሁን ከተያዘችበት የከፍተኛ መካከለኛ ገቢ ኢኮኖሚ ወጥመድ በመውጣት ወደ ከፍተኛ ገቢ ኢኮኖሚ (To break into the High-Income category) ከፈለገች ፤ ተቋማዊ አገነባቧን ከዘፈቀደ ስልጣን ወደ የሕግ የበላይነት (arbitrary authority to impersonal rule of law) እና የተመረጠ ክፍትነትን ወደ ዕውነተኛ ክፍትነት (Selective integration to genuine openness) መቀየር አለባት።

ቻይና እነ እዚኽን የይስሙላ ሳይሆን ስር ነቀል ማሻሻያዎች ካላደረገች ፤ የእሚቀጥሉት አስርት አመታት ለቻይና ፤ በእዳ ጫና እና እየተባባሰ በመጣው የአዲስ ትውልድ መመናመን (Debt saturation and demographic exhaustion) የባከኑ አስርት ዓመታት ወደ መሆን የእሚቀየሩባት ሐገር የመሆን አደጋ ተጋርጦውባታል።

# 5 ከታሪክ ስንማር

ምንም እንኳን ሐገራት ያለምንም ጥርጥር ተመሳሳይ ኢኮኖሚያዊ ዓላማ ይኖራቸዋል ተብሎ ሊገመት ቢችልም ፤ ኹሉም የፖለቲካ ማሕበረሰባት ወይንም ሐገራት ተመሳሳይ ትልም የላቸውም።

በተግባር እንደ ዕሚታየው የተለያዩ ማሕበረሰባት የተለያየ ግብ የእሚከተሉ እና ምንም እንኳን ግባቸው ቢለያየም ኹሉም የእራሳቸው ግብ ትክክለኛው ግብ ነው ብለው የእሚያስረዱበት የአስተሳሰብ መዋቅር አላቸው።

አርስቶትል ፖለቲክስ (*Politics*) በእሚለው መጽሐፉ እንደ አስቀመጠው ፤ እያንዳንዱ የፖለቲካ ማሕበረሰብ አንዳች መልካም የእሚባል ግብን ለማሳካት የእሚቋቋም ነው ፤ የሰው ልጅ በሙሉ የእሚያደርገውን ነገር የእሚያደርገው መልካም ብሎ ያሰበውን ነገር ለማሳካት በመሆኑ።

ሆኖም የፖለቲካ ማሕበረሰባት (ሐገራት) መልካም ነው ብለው ለእሚሉት ነገር በመትጋት ቢመሳሰሉም ፤ መልካም ብለው ከእሚተጉለት ነገር አንጻር ግን ይለያያሉ።

ለአንዳንዱ መልካም ብሎ ቅድሚያ የእሚሰጠው፡- ባሕላዊ ማንነትን ማስቀጠል ነው ፣ ለሌላው በታሪክ ደረሰበኝ የእሚለውን ውርደት መሻር ነው ትልቁ ነገር ለሌላው ደግሞ የሐገሩን ታላቅነት ማረጋገጥ ነው ፤ ለሌሎቹ ደግሞ የዜጎቻቸውን ደህንነት እና ነጻነት ማረጋገጥ ነው።

ምን አልባት በእዚኽ ረገድ ፤ ልብ ላለው ሰው ግርታ የእሚፈጥረው ፤ ለምን አንዳንድ ሐገራት የከበረ ብሔራዊ ዓላማችን ነው ለእሚሉት ነገር ሲሉ የዜጎቻቸውን ሕይወት ፣ ነጻነት እና ንብረት ተገዢ ወይንም መስዋት እንደ እሚያደርጉ ነው። ምክንያቱም ፡- ሐገር የእሚገነባው በዜጎች ስለ ሆነ እና ሐገራትም የከበረ የእሚሉትን ማንኛውንም ብሔራዊ ዓላማ ማሳካት የእሚችሉት ዜጎቻቸው በሕይወት ኖረው ንቁ ተሳታፊ ለመሆን የእሚያበቃ ንብረት እና ዕውቀት/ነጻነት ሲኖራቸው ነው።

ብሔራዊ ግቡ ባሕላዊ ተፅዕኖ መፍጠር ይኹን ፣ ታሪካዊ ውርደትን መሻር ወይንም የሐገርን ታላቅነት ማረጋገጥ ፤ እነ እዚኽ ግቦች ፡- ዜጋው የሕይወት ዋስትና ፣ ነጻነት እና ኢኮኖሚያዊ አቅም ከሌለው ሊሳኩ አይችሉም።

ያለ ዜጋው ሕይወት ፣ ነጻነት እና ንብረት የትኛውም ብሔራዊ ትልም ግቡን ሊመታ አይችልም !

ከእዚኽ አንጻር ካየነው ፤ በአንድ ሐገር ሕዝቡን የእሚቀሰቅሰው ትርክት የቱም ይሁን የቱ ፡- ባሕላዊ ፣ ኃይማኖታዊ ፣ ታሪካዊ ፣ ወይንም አንዳች ዓይነት ርዕዮት ፤ ያ ትርክት የዜጎችን ሕይወት ክቡርነት ፣ የዜጎችን

ነጻነት ቅዱስነት እና የንብረታቸውን የነጻነት ምሽግነት እማያከበር ከሆነ ፤ ያ ትርክት የእራሱ ውድቀት ምክንያት ነው የእሚሆነው።

አንድ ማሕበረሰብ የትኛውም የከበረ የእሚለውን ብሔራዊ ዓላማ ለማስካት በእሚል የዜጎቹን የተናጠል ደህንነት ከሰዋ ፤ ብሔራዊ ዓላማውን ለማሳካት መተኪያ የሌለውን ዜጎቹን ድጋፍ እና አቅም በማጣት ፤ ተሰነካክሎ ይወድቃል።

ይኽን ኹኔታ ጆን ሎክ (John Locke) በግልጽ ተረድቶ አስቀምጦታል። እንደ ጆን ሎክ ፤ ሰዎች በተፈጥሮ በጋራ በእኩልነት የእሚጋሩት ነጻነት ፣ በሕይወት የመኖር እና የጉልበታቸውን ፍሬ በንብረትነት የመያዝ መብት ያላቸው ናቸው።

ሆኖም ይኽ ተፈጥሯዊ ነጻነት ሰዎች በማሕበረሰብ ውስጥ ሳይሆን ብቻቸውን በእሚኖሩበት ግዜ አደጋ ውስጥ ይገባል። ይኽም ሰዎች በተናጠል ሲኖሩ የእሚገጥማቸው ስጋት ለመቀነስ ፤ ለሕይወታቸው ፣ ለነጻነታቸ እና ለንብረታቸ የተሻለ ዋስትና ለማግኘት በፈቃዳቸው በሕግ የእሚያስድራቸው የፖለቲካ ማሕበረሰብን ይቀላቀላሉ።

ተመሳሳይ ኃሳብም በፈረሳዩ የፖለቲካ ፈላስፋ ዣን ዣክ ሩሶ (Jean-Jacques Rousseau) ቀርቧል።

ሩሶ “ሰው ነጻ ሆኖ ተወልዷል ነገር ግን በኹሉ ሥፍራ በሰንሰለት ታሥሮ ይኖራል” በእሚለው ታዋሽ አባባሉ ይታወቃል።

ሩሶ በእዚኽ አባባሉ ውስጥ ሰንሰለት የእሚለው ጨቆናን ወይንም የኃይል አገዛዝን ብቻ አይደለም ይልቁንም የሰው ልጅ የሕይወት ፣ የነጻነ እና የንብረት ዋስትና ለማግኘት ሲል ያሻውን ለማድረግ የእሚፈቅድለትን ተፈጥሯዊ ነጻነት በመተው ማሕበረሰብ ውስጥ ገብቶ ፦ አትግደል ፣ አትስረቅ ፣ ወዘተ የእሚለውን ዓይነት ማሕበራዊ ውል የእሚቀበልበትን ኹኔታ ነው።

ዜጎች በማሕበረሰብ ውስጥ ኖረው ሕጋዊ ከለላ ለማግኘት ሲሉ ገደብ አልባ ተፈጥሯዊ ነጻነታቸውን ለመተው ፈቃደኛ የእሚሆኑበትን አኳኋን ነው ሰንሰለት የእሚለው።

ስለ እዚኽ ፦ ለሩሶ መሠረታዊ ጥያቄው የነበረው ፦ በተፈጥሮ ፍጹም ነጻ የሆኑ ሰዎች ለምን ይኽን ገደብ በፈቃደኝነት ይቀበላሉ የእሚለው ጥያቄ ነበር።

ያገኘውም መልስም ከሎክ ጋር የእሚመሳሰል ነው ፦ በግል ከመኖር ይልቅ በማሕበረሰብ ውስጥ በመኖር የእሚገገኘውን በአንጻራዊነት የተሻለ ፦ የሕይወት ፣ የነጻነት እና የንብረት ዋስትና እና መረጋጋት ለማግኘት ነው።

የዜጎችን መብታቸውን አክብሮ የሌሎችን መብት በተመሳሳይ እንዲያከብሩ የእሚያደርጋቸው ማሕበራዊ ውል ፤ የእሚፈጠርበት ወይንም የእሚታሰርበት ምክንያት ፤ በተናጠል ራሳቸውን መከላከል ከእሚችሉበት በላይ በጋራ ሲኖሩ ሕይወታቸው እና ንብረታቸው ከነጻነታቸው ጋር በተሻለ መልኩ ስለ እሚጠበቅ ነው።

ለእዚያም ነው ፦ ከተግባራዊነት ወይንም ከጽንሰ ኃሳብ አንጻር ቢሆን ፤ የትኛውም የፖለቲካ ማሕበረሰብ ፤ ከየትኛውም ዓላማ በፊት የዜጎችን ሕይወት ፣ ነጻነት እና ንብረትን ማስቀደም ይገባዋል ብለን እንድናስብ የእምንሆነው።

ይኽ ፦ የሞራል ወይንም የስነምግባር ክርክር አይደለም (This argument is not being made from a moral point of view) ይልቁንም አመክንያዊ (Logical) ክርክር ነው ፤ ምክንያቱም ፦ አንድ የዜጎቹን ሕይወት ፣ ነጻነት እና ንብረት በእኩልነት በእሚያከብር መልኩ ተቋሞቹን ያላዋቀረ ተቋም ፤ በተግባር ፦ ባሕላዊ ፣ ታሪካዊ ፣ ርዕዮተ ዓለማዊ ወይንም ሌላ ብሔራዊ ዓላማዎቹን **በቀጣይነት** ማሳካት ይችላለ ተብሎ አይገመትም።

ከእዚኽ የተነሳ ፤ ሐገራት ከገዢው እና ከትልቁ ብሔራዊ ዓላማቸው አንጻር ቢለያዩም ፤ የሕይወትን ፣ የነጻነትን እና የንብረትን ዋስትና በቀዳሚነት ከማረጋገጥ አንጻር በጋራ ሊስማሙ ይገባል።

በእዚኽ ስምምነት ላይ መድረስ ከታቻለ ፤ የእሚከተለው ተገቢው ጥያቄ ፦ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋሞቻቸን በእንዴት ያለ አግባብ ቢያዋቅሩ የዜጎቻቸውን ደህንነት እና ብልጽግና ማረጋገጥ ይችላሉ ? የእሚለው ይሆናል።

ሆኖም ፦ ሐገራት የዜጎችን ፦ ሕይወት ፣ ንብረት እና ነጻነት ማስቀደም ላይ ቢስማሙም እንኳን ፤ የዜጎችን ሕይወት ፣ ንብረት እና ነጻነት በተሻለ ኹኔታ የእሚያከብር ስረዓት እንዴት አድርገን ነው የእምንገነባው በእሚለው ጉዳይ ላይ መለያየታቸው አልቀረም። በተለይ ደግሞ ምዕራፍ 6 ላይ እንደ እምናየው ፤ የቀኝ ግዛት እና አንድ አንድ የብዝበዛ ስረዓቶች ፤ በበርካታ የዓለም ሐገራት ላይ ያደረሱት ስነ ልቦናዊ ጫና እና ኢኮኖነሚያዊ ቀውስ ከግዜያዊ ጥቅመኝነት ጋር ተዳብለው ፤ ሐገራት የኢኮኖሚ ሞዴሎችን በውጤታቸው ሳይሆን የማን ናቸው በእሚል እንዲመዝኑ ስለ አደረጋቸው ፤ ልዩነቱ ይበልጥ ተባብሷል።

ያለፈ ታሪክ እና መሰል ኹኔታዎች የእሚፈጥሩትን የግንዛቤ መዛባት ትተን ፤ የኢኮኖሚ ሞዴሎችን በውጤታቸው ብቻ ከመዘንን ፤ የዓለም ሐገራት የኢኮኖሚ ታሪክ ግልጽ አድርጎ የእሚያሳየው አንድ ነገር ቢኖር ፤ የተወሰኑ አንድ ዓይነት ተቋማዊ አደረጃጀቶች ከውጤታማ ሐገራዊ ልማት ጋር የእሚዛመዱ መሆኑን ነው።

በመላው የዓለም ዘመናዊነት ታሪክ ፤ ሐገራት **በአምስቱ ኹኔታዎች** ላይ የእሚኖራቸው አፈጻጸም የሐገራቸውን የኢኮኖሚ ልማት ደረጃ የእሚወስን ሆኖ ነው የታየው።

የመጀመሪያዎቹ ሶሥቱ ፦ የግል ንብረት ፣ የሕግ የበላይነት እና የበጀት አስተዳደር ፤ የልማት ደረጃ ወሳኝ አንኳር ኹኔታዎች ሆነው ታይተዋል። እነ እዚኽ አንኳር የተባሉት ኹኔታዎች የእሚገኙበት ደረጃ አንድ ሐገር ፤ ሐገራዊ አቅሟን በቀጣይነት ምርታማነትን ለማሳደግ የምትችልበትን ደረጃ ያሳያሉ።

የንብረት ባለቤትነት ዋስትና ሲኖረው ዜጎች ኪራይ ሰብሳቢ ሳይሆን በምርታማነት ተወዳዳሪ በሆነ መልኩ ኢንቨስት ለማድረግ ይነሳሉ ፣ ሕጉ ለኹሉም ዜጎች በእኩልነት ሲሠራ ዜጎች የልፋታቸውን ዋጋ እንደ እሚያገኙ ስለ እሚያውቁ ይበረታታሉ ፣ የበጀት አስተዳደር ጥበብ ሲያድግ እና መንግሥት ገቢ የእሚያገኝበት

እና በጀቱን የእሚደለድልበት አግባብ ትክክል ሲሆኑ ፤ ኢኮኖሚው ከዋጋ ግሽበት ፣ ከወለድ መጠን እድገት ፣ ከውጭ ምንዛሪ እጥረት ፣ ከካፒታል እጥረት ፣ ወዘተ ስለ እሚድን ፤ ዜጋው በቀላሉ ተወዳዳሪ በሆነ መንገድ ገንዘብ አግኝቶ ተወዳዳሪ አምራች ለመሆን እሚያስችለው የማክሮኢኮኖሚ ምህዳር ያገኛል።

ቀሪዎቹ ኹለቱ ኹኔታዎች ፦ የንብረት ተንቀሳቃሽነት እና የንግድ ክፍትነት እንደ አጥዳፊ (Accelerators) ያገለግላሉ። የንብረት ተንቀሳቃሽነት ካፒታል እና ጉልበት በኢኮኖሚው ውስጥ ከፍተኛ አምራች ወደ ሆነው እንዲኼዱ በማድረግ የኢኮነሚውን አምራችነት ሲያጎለብት ፤ የንግድ ክፍትነት የአንድ ሐገር ኢኮኖሚ ከዓለም ዓቀፍ ኢኮኖሚ ጋር በመተሳሰር ሐገራት ተወዳዳሪ በሆኑበት መስክ (Helps them exploit their comparative advantage) በእሴት እና በምርት ሰንሰለት ውስጥ በመግባት በመሳተፍ የቴክኖሎጂ ስረጸት እንዲያገኙ እና በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ አምራች መሆን እንዲችሉ ያስችላል።

ለእዚያም ነው ብዙ ግዜ እነ እዚኽ ኹለት አጥዳፊዎች የእሚገኙበት ደረጃ ሐገራት ፤ የመካከለኛ ገቢ ወጥመድን (Middle-income trap) ሰብረው ወደ ከፍተኛ ገቢ ያለው ኢኮኖሚነት (High-income status) መሆን አለመሆናቸውን የእሚወስኑት።

እነ እዚኽ ኹኔታዎች በተናጠል አይደለም የእሚሠሩት። እርስ በእርሳቸው የተያያዙ እና አንዱ በአንዱ ላይ የእሚደገፍ ወይንም ተፅዕኖ የእሚያደርጉ ናቸው።

ከእዚያ አንጻር ስናየው ማለትም ከአምስቱ ኹኔታዎች አንጻር ፤ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አለ ወይንም የለም የእሚባል ፤ በጥቁር እና በነጭ (binary) ዓይነት ክፍልፋይ የእሚገለጽ ሳይሆን ይልቁንም የመቀራረብ (Continuum) ጉዳይ ሆኖ ፤ አንድ ሐገር በእነ እዚኽ አምስት ተቋማዊ ኹኔታዎች አንጻር ባላት አፈጻጸም መሠረት ፤ በመጨረሻው ኋላ ቀርነት እና በመጨረሻው ዘመናዊነት መካከል የእሚደረግ መጠጋጋት (Approximation between the most backward and the most advanced economy) ሆኖ ነው የእምናገኘው።

ከእዚኽ የእምንወስደው **<u>ታሪካዊ ትምሕርት</u>** በጣም ግልጽ እና ቀላል ነው። እርሱም ፦ የአንዲት ሐገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ፦ በባሕሏ ፣ በተፈጥሮ ኃብት ክምችቷ ፣ በሐገርነት እድሜዋ ወይንም ጥንታዊነቷ ፣ ወይንም በኃይማኖታዊ ዕምነቷ ላያ የእማይመሠረት መሆኑን እና ይልቁንም የአንዲትን ሐገር የኢኮኖሚ እድገት ደረጃ የእሚወስነው ከእነ እዚኽ አምስት ኹኔታዎች አንጻር ያላት አፈጻጸም ላይ መሆኑን ነው።

ዓለምን በወርዷ እና በስፋቷ ፤ በተለያየ ዘመን ላይ የነበሩ ሐገራትን ታሪክ ወስደን ብናይ ፦ ሐገራት እጅግ የተለያየ ባሕል ፣ መልክዓ ምድር እና ታሪካዊ ዳራ ኖሯቸው ፤ እነ እዚኽን አምስት ኹኔታዎች በማሳደጋቸው ሐገራዊ ብልጽግናን ሲያስመዘግቡ ፤ በአንጻሩ ምንም እንኳን በተፈጥሮ ኃብት የተሽቆጠቆጡ እና ረጅም የሐገርነት ታሪክ ቢኖራቸውም ፤ እነ እዚኽን ኹኔታዎች ሳያሳድጉ በመቅረታቸው ኢኮኖሚያቸው በእዚያው ልክ በኋላ ቀርነት ሲንፏቀቅ ነው የእምናገኘው።

ይበልጥ ድንቅ የእሚያደርገው ደግሞ እነ እዚኽን አምስት ኹኔታዎች ማሰደግ ፤ የሐገራት የፖለቲካ አመራሮች በኢኮኖሚ እና በፖለቲካ ፍልስፍና እጅግ የላቀ ዕውቀት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ የግድ የእሚል አለመሆኑ ነው።

አብዛኛው የእነ እዚኽ አምስት ኹኔታዎች ፋይዳ ፤ አንድ ግዜ አንድ ሰው ፡- የሕይወት ፣ የነጻነት እና የዜጎችን ትጋት ውጤት የማክበር እና የመከላከል ፋይዳውን ከተረዳ ፤ በልምድ እና በአዕምሮ ፍርድ (Experience and sound judgment) በቀላሉ የእሚደርስበት ነው።

ጉዳዩ ሌላ ውስብስብ ጉዳይ አይደለም። የሐገርን የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት የዜጎችን ምርታማነት በእሚያደናቅፉ ሳይሆን በእሚያበረታቱ እና በእሚያስችሉ መልኩ መገንባት ነው። ያም በመሆኑ ፡- ሐገራት እነ እዚኽ አምስት ኹኔታዎች የዜጎችን ምርታማነት ለማሳደግ ያላቸውን ፋይዳ ተረድተው የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋሞቻቸውን የእነ እዚኽን አምስት ኹኔታዎች ከፍ ባለ መልኩ ለማሟላት ሲሠሩ ውጤቱ በሐገር ደረጃ ታዳሽነት እና ቀጣይነት (Innovative and Sustainable) ያለው ኢኮኖሚያዊ ብልጽግና ይሆናል። በአንጻሩ የዜጎችን ምርታማነት ከማሳደግ አንጻር ያላቸውን ፋይዳ ሳይረዱ እነ እዚኽ አምስት ኹኔታዎች ችላ ሲሏቸው ሐገራቸውን በቆመ ቀርነት እና በአልመረጋጋት አዙሪት ውስጥ ያገኛሉ።

ስለ እዚኽ፡- ታሪካዊ ትምሕርቱ/ምክሩ ፤ በሐገራት መካከል ያለው የኢኮኖሚያዊ ዕድገት ደረጃ ምንጭ ፤ አንድ አንድ ሐገራት እግዚአብሔር የባረካቸው እና ዕድለኞች ሌሎች ደግሞ እግዜር የረገማቸው እና ዕድላቸው ውድቀት የሆነ በመሆኑ አይደለም። ይልቁንም ፡- ሐገራዊ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ፤ እነ እዚኽ አምስት ኹኔታዎች የዜጎችን ምርታማነት በማሳደግ ሐገርን ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማሳደግ ያላቸውን ፋይዳ በመረዳት እና የሐገርን ማሕበረ ኢኮነሚያዊ ተቋማት አምስቱን ኹኔታዎች ደረጃ ልኬት ከፍ በእሚያደርግ መልኩ ከማዋቀር እና ካለማዋቀር ነው።

ዜጎች ሲያድጉ ነው እንጂ ሐገር እሚያድገው ፤ መንግሥት አድጎ ዜጎችን ሲጦር አይደለም ሐገር በዘላቂነት እና በቀጣይነት እሚያድገው።

ኒኮል ማክያቬሊ (Niccolò Machiavelli) ልዑሉ (The Prince) በእሚለው መጽሐፉ ለማለት እንደ ሞከረው ፤ እድል ሐገራት ራሳቸውን የእሚያገኙበትን እንደ መልከዓምድር ዓይነት ኹኔታዎች ሊወስን ይችላል ፤ ሆኖም ሐገራት እነ እዚኽን አምስት ኹኔታዎች በተረዳ ብቁ አመራር ከእሚገኙበት ምንም ዓይነት ኹኔታ በላይ ሆነው ዘላቂ እድገትን እንዲያስመዘግቡ ማድረግ ይችላሉ።

ምክንያቱም ፡- የግንዛቤ እጥረት ካልሆነ ፤ የሐገራትን ዕድገት ሊፈታ በእማይችል መልኩ የእሚበይን የእድል ድልድል ስለ ሌለ።

በተመሳሳይም ፤ አንድ አንድ ግዜ ፤ በታሪክ አጋጣሚ ሐገራት ውስብስብ እና ደካማ ጅማሮ ሊኖራቸው ይችላል ፤ እንደ እዚኽ ዓይነት ሐገራትም ቢሆኑ ፤ እነ እዚኽ አምስት ኹኔታዎች ያላቸውን ፋይዳ ከተረዱ እና ከተገበሯቸው ፤ በድል የሽቆጠቆጠ ታሪክ እንደ አላቸው ሐገራት (የሉም እንጂ ቢኖሩም እንኳን) እነርሱም ዘላቂነት ያለው እድገት ማስመዘገብ ይችላሉ።

ሌላው የዓለም ኢኮኖሚ ታሪክ የእሚያስተምረን ወይንም የእሚያሳየን ነገር ቢኖር ፤ የመዳረሻ (Catch-up) እድገት የእሚደርጉ አርፋጅ (Latecomers) ሐገራት የተለየ ልዩ ጥቅም እንደ አላቸው ነው።

እንደ እንግሊዝ ያሉ በእንደስትራላይዜሽን ፋና ወጊ የሆኑ ሐገራት የዘመናዊ ካፒታሊዝም ተቋማትን ገንብተው ዛሬ የደረሱበት የብስለት ደረጃ ላይ ለማድረስ በሶስት እና አራት መቶ አመታት ፦ በሙከራ ፣ በግጭት እየተናጡ እና ከስህተታቸው እየተማሩ ፤ በዝገመት ጉዞ ነው የደረሱት።

ኋላ መጪ ታዳጊ ሐገራት ግን ፤ እነ እዚኽን አምስቱን ኹኔታዎች እና ፋይዳቸውን እንደ አዲስ እንደ ገና በሙከራ ፣ በግጭት ፣ ወድቆ በመነሳት እያጠሩ ማብሰል አይጠበቅባቸውም።

እንደ ጃፓን ፣ ደቡብ ኮርያ ፤ አሁን በቅርቡ ደግሞ ፖላንድ ከ30 እስከ 40 በእማይበልጡ ግዜያት ኢኮኖሚያቸውን ከኋላ ቀርነት ወደ ዘመናዊ ኢኮኖሚነት መቀየር በመቻል እነ እንግሊዝ ብዙ መቶ አመታት የፈጀባቸውን እነርሱ በጥቂት አስርት አመታት ማሳካት ችለዋል ። ምክንያቱም እንደ እንግሊዝ ያሉ ሐገራት የደረሱበትን ተቋማዊ ብስለት ፤ እንደ አዲስ ከመፍጠር ይልቅ ፤ እንደ እንግሊዝ ካሉ ሐገራት በቀላሉ መገልበጥ ስለ ቻሉ።

ይኽም የተቋም አገነባብ ዕውቀት ፈጣን ስረጸት ነው ፤ አስገራሚ የእሚባል ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለምን እንደ ድሮው የመቶ እና የኹለት መቶ ዓመት ዝግመት ሳያስፈልገው በ30 እና በ40 ዓመታት መምጣት መቻል የቻለበትን ኹኔታ የእሚገልጸው።

በአምስቱ ኹኔታዎች ላይ ፤ ሶሥት እና ከእዛያ በላይ ያለው ደረጃ ያስመዘገቡ ሐገራት ፤ ከ30 እስከ 40 ባሉ ዓመታት ፤ የድህነት እና የመካከለኛነትን ገደብ ኹሉ በጣጥሰው ከፍተኛ ገቢ ያለው ሐገር የመሆን እድላቸው እርግጠኛ ሊባል በእሚችል ደረጃ ይሆናል ፤ ከሰው አቅም በላይ ሊባሉ የእሚችሉ እንደ ተፈጥራዊ አደጋ ወይንም ከአጎራባች ሐገር የመጣ አውዳሚ ጦርነት ወዘተ ካልገጠማቸው።

አንድ ግዜ እንደ ገና ሰፋ አድርገን እንድገመው እና የዓለም ሕዝብ የኢኮኖሚ ታሪክ ጥናት የእሚያስተምረን ትምሕርት ቢኖር ፦ አንድ ቀላል ግን መሠረታዊ ዕውነታ ነው። ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ፦ የመልከዓ ምድር ፣ የባሕል ፣ ልዩ የሆነ የአዕምሮ ምጥቀት ፣ ወይንም የታሪካዊ ዕድል ከእዚያ ሲያልፍም የፖለቲካ ርዕዮት ውጤት ሳይሆን ፤ የሐገራት የተቋማት አወቃቀር ምርጫ ነው።

የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ተቋሞቻቸውን ፦ የግል ንብረት አክባሪ ፣ የሕግ የበላይነት ማስፈን የእሚችሉ ፣ ገቢውን ከወጭው ያመጣጠነ የበጀት ቀመርን ማክበር የእሚችሉ ፣ ንብረት በሐገሪቱ ውስጥ ተወዳዳሪ አምራችነት መመዘኛ የእሚደላደል መሆኑን ያረጋገጡ እና ኢኮኖሚያቸውን ከዓለም ዓቀፍ ኢኮኖሚ ጋር ያስተሳሰሩ ሐገራት ፤ ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ብልጽግና ይኖራቸዋል።

በአንጻሩ ደግሞ ፦ የርዕዮተ ዓለም ጥራት ለማስጠበቅ ሆነ ታሪካዊ ውርደት ለማጠብ ወይንም ብሔራዊ ታላቅነትን ለማረጋገጥ በእሚል የእነ እዚኽን አምስት ተቋማዊ ኹኔታ ከማሻሻል ይልቅ ቸል ያሏቸው ፤ ቆሜለታለኹ የእሚሉትን ያኑን ብሔራዊ ዓላማ የማሳካት አቅማቸውን አዳክመው ፤ ከግባቸው ሳይደርሱ የኋላ ቀርነት ካልሆነ የቆመ ቀር ኢኮኖሚ ባለቤት ይሆናሉ።

ይኸም ኢኮኖሚያዊ ልማትን አንዳች ዓይነት ምትኃታዊ ምስጢር ሳይሆን የማሕበረ ኢኮኖሞ ተቋማት የዜጎችን ኢኮኖሚያዊ ምርታማነት በእሚያበረታቱበት እና በእሚያስችሉበት መንገድ የመገንቢያውን ዕውቀት የመጨበጥ እና ያለመጨበጥ ጉዳይ ያደርገዋል (It makes it epistemological more than anything else)።

ስለ እዚኸ፡- የኢኮኖሚ እድገትን ማምጣት የተሳካላቸው ሐገራት እድለኞች የሆኑት አይደሉም ፤ ይልቁንም አምስቱ ኹኔታዎች ያላቸውን ፋይዳ ተረድተው ፤ የማሕበረ ኢኮኖሚያዊ ተቋም አገነባባቸው ፤ እነ እዚኸን አምስት ኹኔታዎች ደረጃ በእሚያሻሽል እና ወደ ቀጣዩ የላቀ ደረጃ ማድረስ እንዲችል አድርገው የገነቡት ናቸው።

የዝሆኖቹ መንጋ በጉልበታቸው ትልቀት ሳይሆን በዕውቀታቸው ብልኃት ከኖሩ ፤ እኛ ሰዎችማ እንዴታ ?

## 6 የግንዛቤ እጥረት እና የጥቅም እሳቤ ለለውጥ የፈጠሩት ፈተና (Cognitive and Incentive Resistance to Reform)

አንድ ሰው ፦ ዓለም ባለፈው 500 ዓመት በሰው ልጅ ታሪክ ታይቶ በእማይታወቅ መልኩ እንዴት ተለወጠች ብሎ ቢጠይቅ ፤ መልሱ ፦ ባለፈው 500 ዓመታት ከእዚኽ በፊት በነበርው የበርካታ ሺ ዓመታት በሰው ልጅ ታሪክ ታይቶ በእማይታወቁ መልኩ ፦ የሰው ልጆች በፖለቲካ ማሕበረሰብ ውስጥ ያላቸውን እኩልነት ዕውቅና የእሚሰጥ የፖለቲካ አስተሳሰብ እያደገ በመምጣቱ ነው የእሚል ነው።

ሰዎች እኩል ሆነው በመፈጠራቸው ፤ በእኩልነት የተላበሷቸው የፖለቲካ መብቶቻቸውን በእኩልነት ሊለማመዱ ይገባል የእሚለው አስተሳሰብ ነው ፤ ዛሬ ለደረስንበት የስልጣኔ መሠረት የሆኑት ዘመናዊ እና ሰብዓዊ ተቋሞች መሠረት።

ምንም እንኳን የሰዎች እኩልነት እሳቤ ፤ ከጥንትም በፍልስፍና ደረጃ እዚኽም እዚያም ሲነሳ የነበረ ቢሆንም ፤ የተቋማትን አወቃቀር በእሚወስን መልኩ ያደገው እና የደረጀው ከባለፈው 500 ዓመት ወዲኽ ነው።

በፖለቲካ ማሕበረሰብ ውስጥ ከፖለቲካ አንጻር ኹሉም እኩል ነው የእሚለውን እሳቤ ፤ በፕሌቶ (*Plato*) ዴሞክራሲ ማለት ድሆች የእሚገዙበት መንግሥት ነው ብሎ የሰጠውን ትርጓሜ ለመተቸት ሲል በተወሰነ መልኩ አርስቶትል ፖለቲክስ (*Politics*) በእሚለው መጽሐፍ ውስጥ ሲያነሳው እናያለን።

ሆኖም የአርስቶትል የሰዎች እኩልነት እሳቤ እራሱ ውስንነት ኖሮት ነው የእምናገኘው ምክንያቱም በእዚያው መጽሐፍ ውስጥ አርስቶትል ፤ አንድ አንዱ ሰው ገዢ ሊሆን ተፈጥሯል ሌላው ደግሞ ባሪያ ሊሆን ተፈጥሯል ብሎ ሲል ስለ እምናገኘው።

ይኽን መሰሉ መጣረስ እንደ አርስቶታል ባለ የጥንቱ ዓለም ሊቃውንት ላይ መታየቱ ፤ በጥንታዊው ዓለም የሰው እኩልነት እሳቤ ፖለቲካዊ ፋይዳ የእሚጠበቅበር ደረጃ ላይ ደርሶ እንደ አልነበረ ያሳየናል።

እንደ ሰው ልጅ ፖለቲካዊ ዕንደምታው ከፍተኛ በሆነ መልኩ በሰው ልጅ እኩልነት ላይ ያለን ግንዛቤ እያደገ የመጣው በዝግመት ነው።

በእዚኽ ረገድ አንድ ትልቅ ሚና የተጫወተው ፤ ኹሉም ሰው ለእግዚአብሔር እኩል ክቡር እና ዋጋ ያለው ነው የእሚል ስብከት ይዞ የመጣው የክርስትና ዕምነት መስፋፋት ነው።

አማኞች በክርስቶስ አንድ ናቸው ፣ መዳን ለኹሉም ነው የሚሉት የክርስትና ስብከቶች ፤ በጥንታዊው ዓለም የነበሩ ማሕበራዊ እርከኖችን እየተሻገሩ ፤ የሰዎችን መንፈሳዊ እስኩልነት ወደ ፊት አመጡ።

ክርስትናም ፡- ሮማዊ ወይንም አረማዊውን ፣ ግሪኩን ወይንም አይሁዱን ፣ ወንድን ወይንም ሴትን ፣ የተማረ ወይንም ያልተማረን ፤ በእኩልነት አማኝ አድርጎ የሚቀበል መሆኑ ፤ የዓለም ሕዝብ ከፈረጀ ብዙ ማሕበራዊ ልዩነቱ ባሻገር በአንድ የኃይማኖት ጥላ ሥር እንዲሆን አደረገው።

በእርግጥ ይኽ ማለት ፤ የተለያዩ ሐገራት ክርስትናን ከተቀበሉ በኋላ ፤ የፖለቲካ ስረዓታቸው ጥብቅ የሆነ ማሕበራዊ ደረጃ ያለው ፤ ጌታ እና ሎሌ የሚል ክፍፍል አጠፉ ማለት አይደለም። ሆኖም ፡- የክርስትናው ዕውቀት እየተስፋፋ ዝቅተኛው የሕብረተሰብ ክፍል ጋር ሲደርስ ፤ የሮማው ጳጳስ ብቻ አይደለም መጽሐፍ ቅዱስን የመተርጎም ስልጣን ያለው እኔም መጽሐፍ ቅዱስን በግሌ አንብቤ መረዳት እችላለኹ የሚሉ እንደ ማርቲን ሊተር ላሉ ሰዎች ፣ ወይንም ሚስት ፈትተው ሌላ ማግባት የፈለጉ እንደ እንግሊዝ ነገስታት ያሉ ሰዎች ፣ በኋላ ላይ ደግሞ የፖለቲካ ስልጣን ምንጩ ስዩመ እግዚነት ሳይሆን እኩል የሆኑ ሰዎች ይኹንታ ነው ለሚሉ እንደ ጆን ሎክ ላሉ ሰዎች የአስተሳሰብ መሠረት መሆን ችሎ ነበር።

እንደ ጆን ሎክ ያሉ ሊህቃን ሰዎች ኹሉ ተፈጥሯዊ የሆነ ፤ በእግዚአብሔር የተሰጠ ፤ የሕይወት ፣ የነጻነት እና የንብረት ባለቤትነት መብት አላቸው አሉ።

በእዚኽ አስተሳሰብ መሠረትም ፤ መብት መስጠት የመንግሥታት ድርሻ ሳይሆን የተፈጥሮ ወይንም የተፈጥሮ ፈጣሪ የእግዚአብሔር ድርሻ ነው ፤ መንግሥታት ይኽን ተፈጥሯዊ መብት ማክበር ነው ሥራቸው አሉ።

ይኸው ኃሳብ ነው በጣም ታዋቂ በሆነው የአሜሪካ የነጻነት አዋጅ (United States Declaration of Independence) ላይ ፡- እኛ ሰው ኹሉ እኩል ሆኖ መፈጠሩን እና መንግሥትም ሕጋዊ ተቀባይነት የሚኖረው ከዜጎች መካከል በዜጎች ተመርጦ ሲመጣ ነው ብለን እናምናለን ፤ በሚል የተቀመጠው።

ይኽ በእዚኽ መልኩ በጣም በቀላል ቋንቋ የተቀመጠው የእክልነት ኃሳብ ግን እዚኽ ለመድረስ በብዙ ሺ ዓመታት ውጣ ውረድ ውስጥ አልፎ የመጣ አስተሳሰብ እና የዘመናዊው ዓለምም የስልጣኔ መሠረት ነው።

ሆኖም ይኽ በአንጻራዊነት ግልጽ እና ብዙ ማስረጃ የማያስፈልገውን ፖለቲካዊ ዕውነታ ኹሉም የዓለም ክፍል በቀላሉ ተቀብሎ አላከበረውም ፤ ይልቁንም የተለያየ ምክንያት እየደረደረ ፤ ባይቃወመውም እንኳን በተግባር ግን ችላ ይለዋል።

ለእዚኽም አንዱ ምክንያት ፡- ይኽ ኃሳብ ፖለቲካዊ ፋይዳ በሚኖረው መልኩ የዳበረበት ደረጃ ላይ ሲደርስ አብሮት የአውሮፓ ቀኝ ግዛት ዳብሮ የተስፋፋበት ግዜ ነበርና ፤ የሰው ነጻነት በእኩልነት ይከበር የሚሉት እና ይኽን ኃሳብ ወሳኝ ፖለቲካዊ ፋይዳ ያላበሱት ሐገራት እራሳቸው ቀኝ ገዢዎች እና በዝባዦች መሆናቸው ፤ ለአንድ አንዶች ድንግርግር የፈጠረ መሆኑ ነበር።

በአንድ በኩል ሰው ኹሉ እኩል ክቡር ነው ይላሉ ፤ እነርሱው እራሳቸው ፤ ሌሎችን ከእነርሱ እንደ እሚያንሱ ያኽል ቀኝ በመግዛት ጉልበት እና ኃብት ይበዘብዛሉ።

በሌላ አገላለጽ ፦ ቀኝ ግዛት እና የሊበራል ዴሞክራሲ እሳቤ በአንድ ላይ በአንድ ሕዝብ (ምዕራባዊያን) በዓለም ላይ ተሠራጨ።

ቀኝ ገዢዎም የሊበራል ዴሞክራሲ አቀንቃኞቹም እራሳቸውም ምዕራባዊያን ሆኑ።

ከእዚኽ የተነሳ ከአውሮፓ ውጭ ላለው አብዛኛው የዓለም ሕዝብ ፤ ቀኝ ግዛት እና ነጻ ገበያ የእሚነጣጠሉ ሆነው ሊታዩዋቸው አልቻሉም።

ከአውሮፓ ውጭ ላለው ሕዝብ ፤ ቀኝ ግዛት ካለ የሰውን እኩልነት የእሚሰብኩ ቀኝ ገዢዎች አሉ ፤ የሰውን እኩልነት የእሚሰብኩ ምዕራባዊያን ካሉ ቀኝ ገዢዎች ናቸው።

ይኽንም "ግንዛቤ" (የግንዛቤ እጥረት) የእሚያጠናክሩ ታሪካዊ ክስተቶች ደግሞ ብዙ ናቸው። ለምሳሌ፦ ታላቋ ብሪታንያን ብንወሰድ ዘፈቀደ (Arbitrary Power) የሆነ የመንግሥት ስልጣንን በሕገመንግሥታዊ አካኼድ የመግታት ነገር ፤ በሐገሯ ከ1215 ጀምሮ ስትተገብር ነበር ፤ ሆኖም በሐገሯ በእዚኽ መልኩ ግብታዊ የመንግሥትን ስልጣን በሕግ እየገደበች እና ተቋማዊ ማስተካከያ በዝግመት በእምታደርግበት በእዚያው ወቅት ፤ መርከንታሊስት (Mercantilist) ማለትም ከውጭ ዕቃ እንደ አይገባ እየከለከሉ/እየፈለጉ የራስን ሐገር ምርት ግን ለሌላ ሐገር መሸጥ እና እንደ ኢስት ኢንዲስ ኩባንያ (British East India Company) ያሉ የቀኝ ግዛት ኩባንያዎችን ስታስፋፋ ነበር።

በተመሳሳይ ፤ አሜሪካ ምንም እንኳን ከኹለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ እንደ የተበባበሩት መንግሥታት ያሉ የእኩልነት እና የሰው ልጅ ክብር መገለጫ ያሉ ዓለም ዓቀፍ ተቋማትን በማማቋም ከፍተኛ ሚና ብትጫወትም ፤ በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው በእሚል አካኼድ ዓይነት የእምትመሠርታቸው መርኽ አልባ ግንኙነቶች እና የአንድ አንድ ሐገራትን ሉዓላዊነት በእሚጥስ መልኩ ታደርግ የነበረው ጣልቃ ገብነት ፤ የሰው እኩልነት እና ነጻነት ሰባኪ በሆነችው አሜሪካ ላይ ጥርጣሬ የእሚያጭር ነበር።

ይኽ የምዕራባዊያን ፦ የሰብዓዊነት ሰባኪነት እና የቀኝ ገዢነት ተቃርኖ ፤ እርሱም የፈጠረው ጥርጣሬ ፤ በ20ኛው ክፍለ ዘመን በተፈጠረው የርዕዮተ ዓለም ክርክር እና ግጭት ምክንያት ተባባሰ።

በተለይ ደግሞ ቭላድሚር ሌኒን (Vladimir Lenin) በማርክስ የጻረ ካፒታሊዝም ፍልስፍና ላይ በመጨመር ካፒታሊዝም አድጎ አድጎ የመጨረሻው ደረጃ ላይ ሲደር ኢምፔሪያሊስት (Imperialist) ነው የእሚሆነው ማለትም ፦ ከፍተኛ የምርት እድገት ደረጃ ላይ ደርሶ የሐገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ አቅርቦት እና የሐገር ውስጥ ገበያ ስለ እማይበቃው ሌላውን ሐገር ጥሬ ዕቃ አቅራቢ ለማድረግ እና ለሸቀጥ ማራገፊያነት ስለ እሚፈልግ ከሐገሩ ድንበር ተሻግሮ በኃይል ወይንም በድለላ የሸቀጥ ማራገፊያ ገበያ ይፈልጋል ማለት ነው።

ይኽ የቭላድሚር ሌኒን ትንተና በአብዛኛው የቀኝ ግዛት ሰለባ በሆኑ እና ኋላ ቀር በሆኑ ሐገራት ፤ በጸረ ቀኝ ግዛት ታጋይ ፖለቲከኞች እና በታዳጊ ሐገራት ሙህራን ዘንድ በጣም ተቀባይነት አገኘ።

ይኸም ካፒታሊዝም እና ሊበራል (Liberal) የሆነ የማሕበረ ኢኮኖሚ አስተሳሰቦች ፤ በእውነት ለሐገራት ኢኮኖሚ ዕድገት እና ለሕዝብ ተጠቃሚነት የእሚጠቅሙ ሳይሆኑ ፤ ምዕራባዊያን ጭቆናቸውን እና ብዝበዛቸውን የእሚሰውሩበት ለምዳቸው ነው የእሚለውን አስተሳሰብ ይበልጥ አጠናክሮታል።

ምን አልባት በሶሻሊዝም ወይንም በግራ ዘመሙ ጎራ ሆነው ፤ ቀኝ ግዛት እና የኢኮኖሚ ብዘበዛን በመከላከል ስም ፤ ቀኝ ግዛት እና ብዝበዛን ከካፒታሊዝም ፣ ከነጻ ገበያ እና ከዲሞክራሲያዊ ተቋማት ጋር የእሚያምታቱ ሰዎች ፤ ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው ስለ አልመረመሩት እንጂ ፤ ማርክስ እንደ እነሱ በግርድፍ ፍረጃ የተወሰነ ፍረጃ እንደ አልነበረው ነው የእምናየው።

እርግጥ ነው ማርክስ ትልቁ ትኩረቱ ፤ ጨቋኝ ስረዓትን መገርሰስ በመሆኑ ፤ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ትንታኔውን ከእዚያ አንጻር እንደ ሆኔታው በእሚያጣጥምበት ግዜ ፤ እርስ በእርሱ የእሚጋጭ ነገር ሊል ይችላል ፤ ሆኖም ማርክስ የካፒታሊዝም ስረዓት የእሚገነባው ተቋማት ተለውጠው የዜጎችን እኩል ነጻነት የእሚያከብሩ ሲሆኑ እንደ ሆነ ግልጽ ግንዛቤ እንደ ነበረው ግን ምንም ጥርጥር የለውም።

በሌላ አገላለጽ ፡ ማርክስ ካፒታሊዝምን ቢተችም ፤ ያለ ካፒታሊዝም ልማት ደረጃ ሶሻሊዝም እንደ እማይቻል እና ካፒታሊዝም ደግሞ የዜጎችን እኩል ነጻነት የእሚያከብሩ ማሕበራዊ ተቋማት ሳይገነቡ በፊት ሊመጣ እንደ እማይችል አጥርቶ ይረዳ ነበር።

ማርክስ ካፒታል በእሚለው መጽሐፉ ካፒታሊዝም እንዴት እንደ እሚፈጠር ሲያብራራ ፤ የካፒታሊዝም መፈጠር የእሚመጣው ገበሬውን ከመሬት ጋር ሰፍቶ እንደ አይነቃነቅ ያሠረው የፊውዳሊዝም ስረዓት ሲፈርስና ገበሬው ነጻ ሆኖ መንቀሳቀስ ሲችል እና በከተማም ሠራተኛው የሠራተኛውን ቅጥር ከእሚቆጣጠሩ የሠራተኛ ማሕበራት ነጻ ሲወጣ ነው ብሎ ይላል።

ይኸም ማለት ፦ ማርክስን እራሱን ምስክር አድርገን ብንወስድ ፤ የካፒታሊዝም ስረዓት ስለ እዚኽ የኢንደስትራላይዜችን ደረጃ ፤ ዜጎች ከማሕበራዊ እና ሕጋዊ ክልከላዎች ነጻ ወስጥተው ጉልበታቸውን በገበያ ተወዳድረው ሲሸጡ ነው የእሚመጣው።

ሆኖም ማርክስ በእዚኽ መልኩ ካፒታሊም የእሚፈጠረው ፤ ዜጋው ከሕጋዊ እና ማሕበራዊ ክልከላ ተላቆ ፤ ጉልበቱን በነጻ ባለቤትነት ይዞ በገበያ ዋጋ ተወዳድሮ ሲሸጥ ነው ቢልም እና የሊበራል ዴሞክራሲ (Liberal Democracy) ስብከትም ይኸው ቢሆንም ፤ የሶሺሊስት አብዮተኞቹ ካፒታሊዝምን በመፍጠር ላይ ሳይሆን ትኩረታቸው የካፒታሊዝምን ስረዓት ከመርኹ ውጭ በራሳቸው መንገድ በመንግሥት ኃይል መፍጠር ላይ ማድረጉን መረጡ ፤ ውጤቱም ፦ ማሕበራዊ እና ኢኮነሚያዊ ቆሞ ቀርነት ነበር።

ይኽን መሰሉ የታሪክ ግጥምጥሞሽ እና የታዳጊ ሐገራት ጸረ ቀኝ ግዛት ታጋዮች እና ሙህራን መርጦ አልቃሽነት ፤ በአብዛኛው የሶስተኛው በእሚባለው ዓለም ፤ ሊበራል የሆኑ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋሞችን

ከምዕራባዊያን ጂኦፖለቲካዊ ኃይል ጋር አዳብሎ የማየትን ነገር በመፍጠር ፤ የግንዛቤ ግርዶሽ ፈጠረ (The result was cognitive resistance)።

የግል ንብረት ባለቤትነት ፣ የሕግ የበላይነት ፣ የንግድ ክፍትነት እና ወጪ እና ገቢን ያገናዘበ የበጀት አስተዳደር (Fiscal restraint) ፤ በግልጽ በምዕራቡ ዓለም የማሕበረ ኢኮኖሚ ምህዳር ውስጥ ስለ አቆጠቆጠ እና ስለ አደገ ፤ የቀኝ ግዛት እና የታሪክ ሰለባ የሆነው ታዳጊው ሐገር ፤ እንደ የሕግ የበላይነት እና የንብረት ባለቤትነት ያሉት መርኽዎች የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋጋጥ የእሚያስፈልጉ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ሊያከብሯቸው የእሚገቡ ሕጎች አድርጎ ሳይሆን የምዕራባዊያን የርዕዮተ ዓለም የበላይነት ማረጋገጫ መንገዶች አድርጎ ይወስዳቸዋል።

የእዚኽ ዝንባሌ አሉታዊ ውጤትም ፦ የታዳጊ ሐገራት ሊህቃን እነ እዚኽን ተቋማት ማዋቀሪያ መርሆዎች ፤ ሲተገበሩ ከእሚፈጥሩት የኢኮኖሚ ዕድገት እና ከእሚያስከትሉ መልካም ፍሬ አንጻር ሳይሆን ከቀኝ ገዢዎች ጋር ባላቸው ታሪካዊ  ቁርኝት ሆነ እሚመዝናቸው።

በአንጻራዊነት ፍትኃዊ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ያመጣሉ ወይንስ አያመጡም ሳይሆን የቀኝ ገዢዎች ኃሳብ ናቸው ወይንስ አይደለም በእሚል ሆነ እሚመዝናቸው።

ከእዚኽም የተነሳ ፤ የግራ ዘመም ዝንባሌ ወይንም ሶሻሊስታዊ ቃና ባላቸው ኋላ ቀር እና ታዳጊ ሐገራት የሊበራል ኢኮኖሚያዊ ተቋማት (Liberal economic institutions) ተቀባይነት የእሚያጡት እና በመርኽ አልባ የበጀት አጠቃቀም ፣ በንብረት ባለቤትነት ክልከላ/ገደብ ፣ በዋጋ ትመና ፣ ወዘተ የእሚተኩት ፤ የነጻ ገበያ መርኽዎች ከዕዝ ኢኮኖሚ ዓይነት የኢኮኖሚ መርኾች ያነሰ ውጤት ስለ እሚያመጡ ሳይሆን ፤ የምዕራባዊያን ተፅዕኖ እና በታሪክ ምዕራባዊያን የኋለኛው ዘመን ቀኝ ገዢዎች ጋር ባላቸው ቁርኝት ምክንያት ፤ በትስስር ስለ እሚኮነኑ ነው (Condemnation by Association)።

ይኽን ዝንባሌ ፦ የነጻ ገበያ አስተሳሰብን በኢኮኖሚያዊ ፋይዳው በመመዘን ሳይሆን የምዕራባዊያን ኃሳብ ነው በእሚል የመቃወሙን ዝንባሌ ነው ፤ እንግዲኽ ኮግኒትቭ ሬዝስታንስ (Cognitive resistance) ለእሚለው የእንግሊዝኛው ኃሳብ/አባባል የተሻለ ትርጉም ስለ አጣኹለት “የግንዛቤ እጥረት” የፈጠረው ለውጥን የመግፋት ፈተና ብዬ የእዚኽ ምዕራፍ ግማሽ ርዕስ ያደረግኹት።

ይኽም “የግንዛቤ እጥረት” (Cognitive resistance) የፈጠረው ለውጥን የመግፋት ፈተና ፤ የግል ንብረት ባለቤትነት ፣ የንብረት ተንቀሳቃሽነት ፣ የሕጉ ነጻ እና ገለልተኛነት ፣ የንግድ ክፍትነት ፣ እና የበጀት አስተዳደር ጥበብ ብለን የዘረዘርናቸውን አምስቱን ኹኔታዎች ፤ ቀጣይነት ያለው ሆኖ መዋቅራዊ ሽግግርን የእሚያስከትል ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በአንድ ሐገር ለማስከትል የእዚያ ሐገር የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ሊተገብሯቸው የእሚገቡ መርኾች አድርጎ ከመወሰድ ይልቅ እንደ አንዳች ዓይነት ታዳጊውን ሐገር ጎድተው እና አደህይተው የምዕራቡን ዓለም የእሚጠቅሙ የኢኮኖሚ አሻጥር ተደርገው እንዲወሰዱ አደረገ።

የግንዛቤ ግርዶሹ (Cognitive resistance) እነ እዚኽ መርኽዎች በተግባር ተፈትነው ከእሚያመጡት ውጤት አንጻር እንኳን እንዲመዘኑ እድል አይሰጥም ፤ ገና ሳይሞክራቸው ፤ የምዕራባዊያን በመሆናቸው ብቻ ፤ የቀኝ ግዛት እና የብዝበዛ መሣሪያ አድርጎ በመቁጠር ይገፋቸዋል።

ለዘላቂ እና አካታች ኢኮኖሚያዊ እድገት የድንጋይ መሠረት የሆኑትን እነ እዚኽ መርሆች ከቀኝ ግዛት እና ከምዕራባዊያን የጂኦፖለቲካዊ ተፅዕኖ ጋር በማምታት ፤ ለማንኛውም ሐገር ዘላቂ እና አካታች ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ማምጫ ቁልፎችን ይወረውራል።

ይኽም በድፍረት ፤ ኋላ ቀር እና ታዳጊ ሐገራት ኢኮኖሚያቸውን እንደ ኢያሳድጉ እና ከአደጉ ሐገራት ጎራ እንደ አይመደቡ ገድቦ ያያዛቸው ነገር ሌላ ሳይሆን የግንዛቤ እጥረት (Cognitive) ነው ብለን እንድንል ያስችለናል።

በአንድ ሐገር መዋቅራዊ ሽግግርን የእሚያስከትል ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በለውጥ ስም በእሚተገበር በተገኘው የፖሊሲ ለውጥ በሙሉ አይመዘገብም ፤ ይልቁንም ትክከለኛውን የፖሊሲ ለውጥ በመተግበር ነው የእሚመጣው።

ትክክለኛው ፖሊሲ ደግሞ የቀኝ ገዢዎች እና የበዝባዦች ፖሊሲ ነው ወይንስ አይደለም በእሚል ሳይሆን በተግባር ሲፈተሽ በተጨባጭ በእሚያስከትለው ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ነው መፈተሽ ያለበት።

አንድ ማሕበረሰብ የተሻለውን ኃሳብ ፤ የኃሳቡ አቀንቃኝ ከሆነው ሰው ፤ ጨቋኝነት እና በዝባዥነት ለይቶ ማየት ካልቻለ ፤ የግንዛቤ እጥረት አለበት ማለት ነው።

ገንዘብ እንዴት እንደ እሚሠራ የእሚያውቅ ሰው ፤ በጥበቡ ሠርቶ የእሚያመጣውን ገንዘብ ፤ ለእኩይ ዓላማ ሊያውለው ይችላል ፤ ያ ግን ያ ሰው ገንዘብ የእሚሠራበትን ጥበብ እኩይ ያደርገውም።

በታዳጊ ሐገራት ፦ ከታሪካዊ ገጠመኝ ፣ ከርዕየተ ዓለም ታማኝነት ፣ እና የውጭን ሐገር ሞዴል ከመጠራጠር የእሚነሳ የግንዛቤ እጥረት ወይንም ግርዶሽ ብቻ አይደለም ፤ አምስቱን ኹኔታዎች ከፍ የእሚያደርግ ተቋማዊ አወቃቀር ለውጥ እንደ አይተገበር ችግር የእሚፈጥረው።

አብሮትም ከነባራዊው እና በምርታማነት ሳይሆን በፖለቲካ ጥገኝነት ላይ ተመሥርቶ የእሚገኝ ጥቅም ፤ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማትን በአምስቱ ኹኔታዎች አግባብ ማደረጃት ስለ እሚንደው ፤ ያንን የተለመደ ልዩ ጥቅም የማስጠበቅ ፍላጎትም ፤ አካታች እና ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አምጭውን ከአምስቱ ኹኔታዎች ጋር የተዋደደውን ለውጥ የመግፋቱ ነገር አለ።

የእዚኽም ውጤት ፦ ዘላቂ የሆነ መዋቅራዊ ሽግግርን የእሚያስከትለው ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ማምጫው መንገድ ፤ ነባራዊውን ስልጣን እና የጥቅም ትስስሩን ስለ እሚያፈርስ ፤ ጥቅመኝነቱ ወይንም የጥቅም እሳቤው ለውጡን እንዲገፋ ያደርገዋል።

ስለ እዚኽ፦ በአንድ ኋላ ቀር ሐገር ዕድገትን ማምጣት ፤ ከእላይ ለመግለጽ የሞከርነውን የግንዛቤ እጥረት ወይንም የግንዛቤ ግርዶሽ (Cognitive Resistance) ማንሳት ብቻ ላያሳካው ይችላል ፤ በነባራዊው

ስረዓት ያልተገባ ጥቅም የእሚያገኝ እና ያንን ጥቅሙን ለማስጠበቅ ሲል አሮጌውን ስረዓት የማስቀጠል አቅም ያለው አካል ካለ።

እንዲያኽ በእሚሆንበት ግዜ ይኽ የጥገኛ ጥቅም አስተሳሰብ የእሚፈጥረውን የለውጥ ግፊት ፈተና ማሸነፍ የእሚቻለው ፤ ተቋማዊ ለውጡ የእሚያስከትለውን ተጠቃሚነት ለሰፊው ሕዝብ በማስረዳት ፤ የጥቅም ቡድኑ ለሕዝብ ግፊት እንዲጋለጥ በማድረግ እና በለውጡም ውስጥ በአንጻራዊነት ከጥገኝነት በተላቀቀ መልኩ ጥቅሙ በአንድም በሌላ መንገድ የእሚቀጥልበትን አግባብ በማሳየት ነው።

እነ እዚኽ አምስት ኹኔታዎች በማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ሲከበሩ የእሚመጣው ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት እና ያም የእሚያስከትለው የኑሮ ደረጃ መሻሻል ግንዛቤ ሲስፋፋ እና ሕብረተሰብ ሲቀበለው ፤ የፖለቲካው እና የኢኮኖሚው ልህቅ ፤ ሕዝቡን መቃወም ይከብደዋል።

የንብረት ባለቤትነት መብት መከበር ፣ የበጀት አስተዳደር ጥንቃቄ ፋይዳ (Fiscal discipline) ፣ የንግድ ክፍትነት የእሚኖራቸውን ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ሕብረተሰቡ ሲረዳ እና መንግሥት እነ እዚኽ ነገሮች እንዲተገብር መፈለግ እና መጠበቅ ሲጀምር ፤ የፖለቲካው እና የኢኮኖሚው ሊህቅ ያንን መቃወም እና እምቢተኛ መሆን ከፍተኛ ፖለቲካዊ ዋጋ የእሚያስከፍለው ስለ እሚሆን ባይፈልገው እንኳን የሕዝቡን ድምጽ ለመስማት ይገደዳል።

ያ ብቻ ግን በቂ አይደለም ፤ በጥገኛው እና ነባራዊው ስረዓት ተጠቃሚ የነበሩ ሰዎች ፤ የማሕበረ ኢኮኖሚው አወቃቀር ሲቀየር እና በኢኮኖሚው ውስጥ ተወዳዳሪ ምርታማነት እንጂ ፖለቲካዊ ስልጣን ወይንም ከፖለቲካ ስልጣን ጋር መጣበቅ ሳይሆን ሲቀር ፤ በአዲሱ አወቃቀርም ውስጥ ነባራዊ ጥቅማቸውን በአንድም በሌላም መንገድ ማስጠበቅ የእሚችሉበት መንገድ እንደ አለ ሊያዩ ይገባል።

በሌላ አገላለጽ ፤ ለውጥ ነባራዊ የጥቅም ምንጫቸውን ቢያደርቅም ፤ በተለይ ምርታማ እስከ ሆኑ ድረስ ፤ ሌላ አዲስ ምንጭ እንደ እሚከፍትላቸው ማወቅም አለባቸው።

ከእዚኽ አንጻር ካየነው ፦ ጥቅምን መሠረት ያደረገ የለውጥ ተቃውሞ ሲኖር ፤ ቀጣይነት ያለው እና መዋቅራዊ ሽግግርን ማስከተል የእሚችለው ፤ አምስቱን ኹኔታዎች የእሚያከበር የማሕበረ ኢኮኖሚ አደረጃጀት መኖር ነው የእሚለውን ዕውቀት መያዝ ብቻ በቂ ላይሆን ይችላል ፤ ከእርሱም ጋር አብሮ ፤ ይኽን ዕውቀት በሕበረተሰቡ ውስጥ በማሰራጨት ሕብረተሰቡ ለእራሱ ጥቅም ሲል ለውጡን እንዲፈልግ እና እንዲጠብቅ ማድረግ እና በጥቅመኝነት እሳቤ የለውጥ ተቃዋሚው ሊህቅም በለውጡ ውስጥ ጥቅሙን እና ማሕበራዊ ደረጃውን የእሚያስጠብቅበት መንገድ እንደ አለ ማሳየት ያስፈልጋል።

ሆኖም ኹሉም ነባራዊ ሊህቅ ፤ በአዲሱ ለውጥ ውስጥ በአንድም በሌላም መንገድ ጥቅሙን ሊያስከብር የእሚችል መሆኑን በደስታ ላይቀበለው ይችላል ፤ ግማሹ ከተቀበለው በቂ ነው። ምክንያቱም በአመራሩ መካከል መሰንጠቅ ከተፈጠረ ፤ የለውጥ እምቢተኛው ኃይል ከሕዝቡ በእሚመጣበት ግፊት እና በደረሰበት መሰንጠቅ ምክንያት ነባራዊውን ስረዓት ለማስቀጠል ይቸገራል።

ከገዢው ሊህቅ መሐከል ግማሹ ፤ በአዲሱ ለውጥ ውስጥ ተጠቃሚነቱን ማረጋገጥ እንደ እሚችል ከተመለከተ ፤ ከሕዝብ ፍላጎት እና ጥያቄ ጋር ተደምሮ ፤ ነባራዊ ስረዓት ከመቀጠል ይልቅ መለወጥ ብቸኛው ምርጫው ይሆናል።

በእርግጥ ይኽን ዓይነቱ ለውጥ ይመጣል ብሎ ማስረገጥ አይቻልም። አንድ አንድ ግዜ መንግሥታት የጥንካሬያቸው ምንጭ ሐገራዊ ብቻ ላይሆን ይችላል ፤ ከውስጣዊ ሕዝባዊ ግፊት በላይ የሆነ ዓለም ዓቀፍ ትስስር እና ድጋፍ ኖሯቸው የዕውቀት ብርታን የፈጠረውን ግፊት ተጭነው ሊቆዩ ይችላሉ።

ሆኖም አንድ ማሕበረሰብ የአለበት የግንዛቤ እጥረት እና የጥቀመኝነት እሳቤ የፈጠረበትን ግርድሽ ወይንም ገደብ በተሻለ እና በጠራ ግንዛቤ ተሻግሮ ፤ በሐገር ውስጥ ዘላቂነት ኖሮት መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት የእሚችል እና ሐገርን ከዝቅተኛ ገቢ ወደ ከፍተኛ ገቢ የእሚያሻግረው ፤ አምስቱን ኹኔታዎች ደረጃ በእሚያሳድግ መልኩ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማትን መገንባት ነው የእሚለውን ግንዛቤ ከያዘ ፤ አርስቶትል እንደ አለው ፤ የሰው ግብሩ የእሚመነጨው መልካም ነው ብሎ ያሰበውን ነገር ለማሳካት ከማሰብ ነውና ፤ በዝግመት ይኹን በፍጥነት ፤ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማቱን ከአምስቱ ኹኔታዎች አንጻር አዋቅሮ ፤ እራሱን ቀጣይነት ኖሮት የመዋቅር ሽግግር በማምጣት የሕብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ አሻሽሎ ዘመናዊ ኢንደስትሪያሊይዝድ እና በፈጠራ ኃይል ታዳሽ የሆነ ኢኮኖሚ ከመገንባት እሚያቆመው ኃይል አይኖርም።

# 7 የተቋማዊ ሽግግር ጎዳና (Pathways of Institutional Transition)

ብዙ ግዜ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ለውጦች አንድ ብቻ መነሻ ምክንያት አይኖራቸውም።

በረጅሙ የሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ መርኽ አልባ የፖለቲካ ስልጣን አድራጊ ፈጣሪ ከሆነበት ወደ ኢኮኖሚያዊ ተወዳዳሪነት እና ፈጠራ የተበራከተበት ኢኮኖሚ የተደረጉ ሽግግሮችን ያስከትሉት እንደ ፦ የጥቅም ግጭት ፣ የአንጻራዊ ተጎጅነት ስሜት ፣ የኢኮነሚ ቀውስ ፣ የውጭ ኃይል ጫና እና አንድ አንድ ግዜ ያልተጠበቁ ድንገተኛ ክስተቶች ተደማምረው ነው።

ሆኖም እነ እዚኽ ቆስቋሽ ናቸው እንጂ በእራሳቸው የኢኮኖሚ ዕድገትን አያስከትሉም። ለውጥ ግን እንደ እነ እዚኽ ባሉ ኹኔታዎች ተቀስቅሶ ከመጣ በኋላ በእዚያ ማሕበረሰብ ውስጥ የሊሀቃን ፣ የተቋማት እና የፖለቲካ ኃይላት አቅም በጥሩ የእድገት ደረጃ ላይ የእሚገኝ ከሆነ ፤ ይኽን ዓይነቱን ለውጥ የኢኮኖሚያዊ ዕድገት መሠረት ሊያደርገው ይችላል።

በአንድ ሐገር ውስጥ የጥቅመኛ ቡድኑ አንድ ብቻ ከመሆን ይልቅ የተለያየ በእሚሆንበት ግዜ ፤ አንዱ ሌላውን አስገድዶ ጥቅሙን ለመጫን ስለ እሚቸገር ፤ በድርድር የጋራ ተጠቃሚነትን የእሚያረጋግጥ ስረዓት ለመገንባት የተሻለ ዕድል ይኖራል።

እንደ ማግና ካርታ (Magna Carta) ያለው ታሪካዊ ውል የተፈረመበት አግባብ ወይንም በኋላ ላይ የተካኼደው የከበረው አብዮት (Glorious Revolution) የኃይል ሚዛን መጣጣም እንዴት ወደ አካታች ስረዓት ግንባታ ሊያመራ እንደ እሚችል ያሳያል።

ያ ማለት ግን የኃይል መመጣጠን ኹል ግዜ አካታች ስረዓት ለመገንባት ያስችላል ማለት አይደለም ፤ ምክንያቱም አንድ አንድ ግዜ ተመሳሳይ የኃይል መመጣጠን አካታች ስረዓት ከመገንባት ይልቅ የብዝበዛ ስረዓት ሲገነቡ ስለ ታዩ።

ከእዚኽ በተጨማሪ ሐገራት በንጽጽር እራሳቸውን ከአጎራባች ወይንም ከሌሎች ሐገራት አንጻር ኋላ ቀር እና ድኃ ሆነው ማግኘታቸው ቁጭት ሲፈጥር እና ለለውጥ ሲያነሳሳቸውም ይታያል። የደቡብ ኮሪያ ፣ የቦትስዋና እና በቅርቡ ደግሞ የቻይና የለውጥ ተነሳሽነት በእዚኽ የእሚገለጽ ነው።

ሆኖም መቆጨት እና ለለውጥ መነሳት በራሱ ብቻ በቂ አይደለም። አንድ ሐገር የቁጭት ባሕር ቢፈጥር ነገር ግን ያንን ቁጭት ቀጣይነት ኖሮቶ መዋቅራዊ ሽግግርን በእሚያስከትል መልኩ ኢኮኖሚውን ሊያሳድጉለት የእሚችሉ ተቋማዊ ለውጥን ማምጣት የእሚችልበት ዕውቀት ከሌለው የለውጥ ጥረቶቹ ውጤት አልባ ከንቱ ቀለም ቅብ ብቻ የሆኑ የይዘት ጥንካሬ የሌላቸው የይስሙላ ለውጦች ይሆኑበታል።

ኢኮኖሚያዊ ቀውስ አንዱ ሌላው ለውጥን የእሚጋብዝ ነገር ነው። ከፍተኛ የበጀት መቃወስ ተፈጥሮ ፦ መንግሥት መሠረታዊ ወጭውን እንኳን መሸፈን ሲያቅተው ፣ የዋጋ ግሽበት ከቁጥጥር ውጭ

ሲሆን ፣ ወይንም ማሕበራዊ ተቋማት ተበሳብሰው ሕብረተሰቡ ሊታገሰው ከአሚችለው በላይ ሲደርሱ ፤ ነባራዊውን ስረዓት ለውጦ አዲስ ለማደራጀት በር ሊከፍቱ ይችላሉ።

ከእዚኽ አንጻር በቻይና ገጠሮች የተጀመረው እና የዛሬውን የቻይናን የኢንደስትራላይዜሽንን ጉዞ ያስጀመረው ታሪክ ተጠቃሽ ነው። በ1978 ሺያጋንግ (Xiaogang) በእሚባለው የቻይና የገበሬ ማሕበር ፤ ነዋሪዎች ከደረሰባቸው የርኃብ ጫና የተነሳ ፤ መሬትን በግል ተከፋፍለው ወደ ማረስ መጡ። ይኽ ከመንግሥት የጋራ እርሻ እሳቤ ያፈነገጠ እና በጸረ አብዮተኝነት አስከስሶ እስከ ሞት ድረስ ሊያስቀጣ የእሚችል አካኼድ በአስገኘው ከፍተኛ የምርት መጨመር ምክንያት ፤ በመንግሥት እንደ ጥሩ ልምድ ታይቶ ሕጋዊ ዕውቅና መሰጠት ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ገበሬ ማሕበሮች እንዲሥፋፋ ተደረገ።

ይኽ ታሪካዊ አጋጣሚ ፤ ለውጥ አንድ አንድ ግዜ ከላይ ሳይሆን ከታችም ሊነሳ እንደ እሚችል እና ለለውጥ መነሻው ከላይ ወይንም ከታች መሆኑ ሳይሆን ፤ ለውጡ ከኢኮኖሚ ዕድገት አምጭ ተቋማዊ ኹኔታዎች ጋር ተስማሚ መሆን እና አለመሆኑ እንደ ሆነ ያሳየናል።

የጥቂት የተራቡ ገበሬዎች ተነሳሽነት ፤ እርምጃቸው ከዕድገት አምጭ ተቋማዊ አሠራር ጋር ስለ ተስማማ ፤ እራሳቸውን ከማዳን አልፎ ፤ በሰው ልጅ ታሪክ በሙቶ ሚልዮን የእሚቆጠሩ ሰዎች ከድህነት በማውጣት ወደር ያልተገኘለትን የቻይናን ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ማስጀመር ችሏል።

አንድ አንድ ግዜ ደግሞ ለውጥ ከውጭ ግፊት የእሚመጣ ነው። አንድ አንድ ግዜ ፤ ድኃ እና ኋላ ቀር ማሕበረሰብ ፤ ከእርሱ ይልቅ በቴክኖሎጂ የላቀ እና ከፍተኛ አምራች ከሆነ ማሕበረሰብ ጋር በእሚገናኝበት ግዜ ፤ የኋላ ቀሩን ማሕበረሰብ ደካማነት በማጋለጥ እና የህልውና አደጋ በመዳረግ ለውጥን ግድ ሊል ይችላል።

በጣም ፈጣን የሆነው የጃፓኑ የሜጃይ ተኃድሶ ፤ ከትልቅ ውጫዊ ኃይል ጋር መገናኘት የጃፓንን ኋላቀርነት እና ተጋላጭነት በማሳየቱ እና የህልውና አደጋ በመከሰቱ የመጣ ተኃድሶ ተምሳሌት ሆኖ ይቀርባል። ሆኖም ፦ ኹሉም ኋላቀርነቱ እና ደካማነቱ ፤ ከእርሱ በሰለጠነ እና በደረጀ ማሕበረሰብ የተጋለጠበት ማሕበረሰብ ኹሉ ለለውጥ ቢነሳም ተኃድሶን ያሳካል ማለት አይደለም ፤ ምክንያቱም ፦ መጋፈጡ (The Exposure) ቁጭት ቢፈጥርም ቁጭቱን ወደ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የእሚለውጥ ተግባራዊ ዕውቀት የሌለው ማሕበረሰብ ቁጭቱ ቁጭት ብቻ ሆኖ ነው እሚቀረው።

ጠቅለል ስናደርገው ፤ መቀስቀሻው (Trigger) መኖሩ ፤ ነባራዊውን ኋላቀር ርጋታ ከመረበሽ ያለፈ ፋይዳ የለውም ፤ ኢኮኖሚያዊ ልማት የእሚያመጣን ለውጥ በምንም ይቀስቀስ በምንም ወሳኙ ነገር ያንን አሮጌ ስረዓት ያናጋ ቀስቃሽ (Trigger) ተጠቅሞ ወደ ልማት አምጪ ተቋማዊ አደረጃጀት መቀየር መቻል ነው።

ተኃድሶ (Reform) አንድ ማሕበረሰብ ጫና የእሚፈጥሩ ውጥረቶችን ወስዶ ፤ ምርታማነትን ወደ እሚያሳድጉ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ግንባታ መለወጥ መቻል ወይንም ባለመቻል ላይ ይወሰናል።

ይኽም ማለት ከተኃድሶ (Reform) አንጻር ፡-ዋናው ጉዳይ ቀጣይነት ኖሮት መዋቅራዊ ሽግግርን ማስከተል የሚችል ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ማምጣት የሚያስችሉ ፤ አምስቱን ኹኔታዎች የሚያከበሩ ተቋማትን መገንቢያውን ዕውቀት መያዝ ፤ ዋናው ማዕከላዊ ጉዳይ ይሆናል።

እዚኽ ጋር በፖለቲካዊ መኃንዲስነት እና በኢኮኖሚያዊ መኃንዲስነት (Political craft and economic craft) መካከል ልዩነት እንደ አለ ማስቀመጥ ይገባል።

ፖለቲካዊ መኃንዲስነት (Political craft) በዋናነት የተረጋጋ እና ተቀባይነት ያለው የስልጣን አሠራርን ከማስቀመጥ ጋር የተያያዘ ነው።

ኢኮኖሚያዊ መኃንዲስነት (Economic craft) ደግሞ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማትን ፡- የንብረት ባለቤትነትን የሚያከብሩ ፣ የንብረት ተንቀሳቃሽነትን የሚያረጋግጡ ፣ የሕግ የበላይነትን የሚያሰፍኑ ፣ የንግድ ክፍትነትን የሚያስችሉ እና ተገቢ የበጀት አስተዳደር የሚያሰፈኑ ፤ አግባብ አዋቅሮ አካታች እና ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ማምጣት ነው።

በእየ ሐገሩ በተለያየ ፍልስፍና የሚመራ ፖለቲካዊ አወቃቀር ቢኖርም ፤ አንድ ሐገር የሚመራበት የፖለቲካ ፍልስፍና ምንም ይኹን ምን ፤ በአንድ ሐገር ለኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የሚመች ማሕበራዊ መረጋጋት እንዲኖር ፤ መንግሥት በእዚያ ሐገር ብቸኛው ሕጋዊ ሕግ አስከባሪ መሆን አለበት (State’s effective monopoly over the legitimate use of force is prerequisite) ።

በአንድ ሐገር መንግሥት እርሱ ብቻ ፤ ብቸኛ ሕግ አስከባሪ መሆኑን ባላረጋገጠበት ኹኔታ ፤ የኢኮኖሚ ተቋማት ምርታማነትን በሚያሳድግ እና በሚያስችል መልኩ ሊገነቡ አይችሉም ፤ ቢገነቡም እንኳን እድሜ አይኖራቸውም።

ስለ እዚኽ ፡- መንግሥታት አምባገነን ሆነውም ፤ አምባገነንታቸው እራሳቸውን ብቸኛ ሕግ አስከባሪ አድርጎ ማሕበራዊ መረጋጋትን እስከ አስከተለ ድረስ (As long as they maintain their monopoly on the legitimate use of violence to the enforcement of the law)፤ አምስቱን ኹኔታዎች ከፍተኛ በሚባለው (4) ደረጃ የሚያከብሩ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ማረጋገጥ የሚችሉ የማሕበረ ኢኮኖሚያዊ ተቋማትን ሊገነቡ ይችላሉ።

ምንም እንኳን አምስቱን ኹኔታዎች በዘላቂነት ከፍ አድርገው እስከ ቀጠሉ ድረስ ፤ አምባገነንነታቸውን ትተው ዴሞክራሲያዊ የመሆን ጫናው ቢበረታባቸውም።

ሌላው አብረን ልናነሳው የሚገባው ጉዳይ ፤ ሐገራት ከተቋማዊ አቅማቸው አንጻር የሚለያዩ መሆናቸውን ነው። አንድ አንዶች በተቋም ቀረጻ እና አገነባብ ዙሪያ በቂ ኤክስተርት የላቸውም። ሌሎች አቅሙ አላቸው ሆኖም ያ አቅም ምዕራፍ 6 ላይ በተብራራው መልኩ በጥቅም እሳቤ ወይንም በግንዛቤ ግርዶሽ ምክንያት እንደ አይሠማራ ክልከላ ይኖርበት ይሆናል።

ሐገራት ውስጣዊ የኤክስተርት አቅም ሲያጥራቸው ፤ የሚገዙትን ካወቁ የውጭ ኤክስፖርት ይገዛሉ። ሐገራት ውስጣዊ ብቃት ባይኖራቸው እንኳን ፤ የሚገዙትን አውቀው ፤ የውጩን ቴክንካዊ እና

ተቋማዊ ዕውቀት ገዝተው ፤ ሐገራዊውን ሙሁር እንዲመራ እና እንዲያበቃ በማድረግ ፤ ውጤታማ የተባለ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ማሳካት ችለዋል።

ሆኖም ይኽ አካኼድ ምንም አደጋ አብሮት የለም ማለት አይደለም ፤ ምክንያቱም ፦ ከውጭ ተገዝቶ የእሚገባው ዕውቀት ወይንም ኤክስፐርቲዝ ከሐገሪቱ ኹኔታ ጋር ተጣጥሞ ፤ የሐገሪቱን ተቋማት ከአምስቱ ኹኔታዎች አንጻር ማሳደግ አለበት።

የውጭ ኤክስፐርት ስለ ሆነ ብቻ ፤ ቀጣይነት ያለው ዕድገት እና መዋቅራዊ ሽግግር ማምጣት የእሚችል ኢኮኖሚያዊ ተቋም አገነባብ ዕውቀት አለው ማለት አይደለም።

ሐገራዊ አቅሙ በእሚኖርበት ግዜ ዋነኛ እንቅፋቶቹ በምዕራፍ 6 ላይ ያብራራናቸው የግንዛቤ እጥረት እና የጥቅም እሳቤ ለለውጥ የፈጠሩት ፈተና ነው።

ከጸረ ቀኝ ግዛት ትግል እና ከርዕዮተ ዓለማዊ ታማኝነት ጋር የእሚያያዘው የግንዛቤ ግርዶሽ (Cognitive resistance) ፤ ሐገራት የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማትን ፋይዳ ከእሚያስመዘግቡት ወይንም ሊያስመዘግቡ ከእሚችሉት ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አንጻር ሳይሆን ተቋማዊ አወቃቀሮቹ የማን ናቸው ወይንም በየትኛው የዓለም ክፍፍል ነው የእሚሠራባቸው በእሚል ብቻ ፤ እንዲመዘኑ ያደርጋቸዋል።

ብዙ ግዜ ሐገራት ይኽን ግርድሽ የገፈፉት ውስን በሆነ መልኩ ፤ ተቋማቱን የማን ናቸው (Associative Evaluation) በእሚል ሳይሆን በውጤታቸው የመገምገም አካኼድን በመከተል ነው።

ይኽንም ለማድረግ ፤ ብዙ ግዜ የእሚደረገው ፤ እንደ ክፍለ ሐገር ያኽል የሰፉ ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች በመፍጠር ፤ በእነ እዚያ የኢኮኖሚ ዞኖች ፤ የእሚሠራው ተቋማዊ ኹኔታ ፤ በሌላው የሐገሪቱ ክፍል የእሚሠራው ተቋማዊ ኹኔታ ሳይሆን ፤ አዲሱ ፥ ለምሳሌ ፦ የንብረት ባለቤትነት የእሚከበረብት ፣ የንብረት ተንቀሳቃሽነት ፣ የንግድ ክፍትነት ፣ የሕግ የበላይነት እና የበጀት ጠንቃቃ አስተዳደር ያለበት እንዲሆን ይደረጋል።

ለምሳሌ ፦ በኢትዮጵያ አዲስ አበባ እና ናዝሬትን የእሚያካትት ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ቢፈጠር ፤ በአዲስ አበባ እና በናዝሬት ፦ መሬት በግል ተይዞ ይሸጣል ፣ የልማት ድርጅቶች ልዩ ድጋፍ አያገኙም ፣ ወደ ልዩ ዞኑ የእሚገቡ ዕቃዎች ለየት ያለ ቅናሽ ታሪፍ ይኖራቸዋል ፣ ዶላር ያለ መንም ገደብ ከዞኑ ወደ ውጭ ሐገር መግባት እና መውጣት ይችላል ፣ የእራሳቸው ከመግሥት ቀጥታ ተፅዕኖ ውጭ የሆነ ብሔራዊ ባንክ ይኖራቸዋል ፣ የዞኑ አስተዳደር የበጀት ጉድለቱን ገንዘብ በማተም መሙላት አይችልም ፣ ሠራተኞች የእሚቀጠሩበት እና የእሚባረሩበት አግባብ ቀለል ይደረጋል ፣ የሕግ ስረዓቱ በልዩ ዞን ውስጥ የእሚደረጉ ክርክሮችን በሙሉ በእኩልነት በተቀላጠፈ ኹኔታ እንዲሠራ ይደረጋል ፣ ንግድ ፈቃድ ማውጣት እና ንግድ መዝጋት በአንድ ቀን እንዲያልቅ ይደረጋል ፣ ዕቃ ወደ ዞኑ እና ከዞኑ ለማስወጣት የጉምሩክ አሠራር ዘመናዊ ይደረጋል፣ ወዘተ ፤ በአጠቃላይ አምስቱን ኹኔታዎች ከእነ አመላካቾቻቸው በጥሩ ደረጃ በእሚፈጽሙበት ኹኔታ ተቋማቱ ይዋቀራሉ።

በእዚኽ ኹኔታ ይተገበርና ፤ ተሞክሮው ጥሩ ውጤት ካስከተለ ፤ ወደ ሌላ የሐገሪቱ ክፍል ይስፋፋል። ያም ብቻ ሳይሆን ፤ እንዲኽ ዓይነት ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች ፤ ከግብርና መሰል አገልግሎቶች ከፍተኛ ገቢ ስለ እሚያመንጩ የመንግሥትን በጀትም በመደጎም ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ።

በቻይና የተደረገው ይኸ ነው።

የጥቅመኝነት እሳቤም ከግንዛቤ ግርዶሹ ያልተናነስ ፈተና ነው የእሚደቅኑት። የጥቅመኝነት እሳቤው ደግሞ ፤ ሊህቃኑን ብቻ የእሚመለከት ላይሆን ይችላል ፤ አንድ አንድ ግዜ ሰፊው የሕብረተሰብ ክፍልም የግዜያዊ ጥቅም ጥቅመኛ ሆኖ ዘላቂ እና ሰፊ ለውጥን ሊቃወም ይችላል።

ለምሳሌ ፦ በኋላ ቀር ግብርና የእሚተዳደር የሕበረተሰብ ክፍል ፤ ከመንግሥት የእሚቀርብለትን ለምሳሌ ፦ በሕገ ወጥ የያዛትን ትንሽ መሬት ሕጋዊ ዕውቅና የማግኘት ወይንም በመንግሥት ሊደረጉለት የእሚችሉ እንደ ውኃ ፓምፕ ወይንም መሰል ድጎማዎችን እንደ ትልቅ ጥቅም ቆጥሮ እርሱን ለማስከበር ፤ የኋላ ቀር ፖሊሲ ዘብ ሊሆን ይችላል።

ወይንም ለምሳሌ ፦ ከውጭ ውድድር በታሪፍ ከለላ ተስጥቷቸው በእሚሰሩ ድርጅቶች ውስጥ የእሚሠሩ ሠራተኞች ወይንም በግብርናው መስክ ከውጭ የእነርሱ ተወዳዳሪ ምርት እንደ አይገባ ተደርጎ የተከለከለላቸው የአግሪቢዝነስ ድርጅት ባለቤት እና ሠራተኞች ነባራዊውን ስረዓት ሊደግፉ ይችላሉ።

እንዲኽ በእሚሆንበት ግዜ ፤ ለውጥ እድልን ብቻ ሳይሆን ለአንድ አንዶች ስጋትንም ይዞ ስለ እሚመጣ ተቃውሞ ሊገጥመው ይችላል።

ይኸ ዓይነቱ ኹኔታ በእሚኖርበት ግዜ ለውጥ ዝግመታዊ የመሆን ዕድሉ ያመዝናል። በእዚኽ ረገድ ትልቁ ነገር ፤ ኋላ ቀር በሆነ የኢኮኖሚ ስረዓት ውስጥ መኖር ፤ በግዜያዊነት የተወሰኑ ሰዎችን ቢጠቅምም በግዜ ኺደት ግን ኹሉንም በጋራ ትልቅ ዋጋ የእሚያስከፍል መሆኑ እየጨመረ ሲመጣ ፤ የሕዝቡ የለውጥ ፈላጊነት እያደገ ይኼዳል።

የሕዝቡ ፍላጎት ሲጨምር ደግሞ ኋላ ቀሩን ስረዓት ማስቀጠል ዋጋው በጣም ውድ እየሆነ ይኼዳል። ከእዚያም በላይ በኋላ ቀር ስረዓቱ አመራር መካከል መከፋፈል ይፈጥራል።

ከአመራሩ ግማሹ አሮጌውን እና ደካማውን ስረዓት ለማስቀጠል ሲጥር ፤ ሌሎች ግን ከነገው እና ከተራማጁ ለውጥ ጋር መወዳጀት በተሻለ እና በዘላቂነት ወይንም ነገን በዋጀ መንገድ ተጠቃሚነታቸውን ሊያረጋግጥ እንደ እሚችል ማየት ይጀምራሉ።

ብዙ ግዜ ፤ የሕዝብ ግንዛቤ እና ፍላጎት ለውጥ ከአመራሩ መሰንጠቅ ጋር አብሮ በእሚመጣበት ግዜ ነው ፤ ለውጥን የእሚጋብዝ እና የእሚያስችል ኹኔታ የእሚፈጠረው።

የሆነ ሆኖ ግን ለውጥ አልጋ በአልጋ አይደለም። ከፊል ለውጥ ፣ የእሚቀለበስ ለውጥ እና ቅይጥ ለውጥ የተለመዱ ክስተቶች ናቸው።

ለምሳሌ ፦ ቻይና የተመረጡ እና ምርታማነትን የእሚያሳድጉ የለውጥ እርምጃዎች ትርጉም ያለው ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ሊያስከትሉ እንደ እሚችሉ ሆኖም ለውጡ ሙሉ ባለመሆኑ በውስጥ የታፈነ ብዙ ውጥረት አብሮም እንደ ፈጠረ ጥሩ ማሳያ ነች።

በተመሳሳይ አንድ አንድ ሐገራት ፤ ልዩ የፋይናንሻል ዞን ወይንም ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ዓይነት የደሴት ለውጥ (Enclave-based reforms) በማድረግ ፤ በእነ እዚያ ልዩ ዞኖች ከሌላው የሐገሪቱ ክፍል የተለየ ሕጋዊ እና አስተዳደራዊ መዋቅር ተግብረዋል።

እነ እዚኽ ዓይነቶቹ አካኼዶች ፤ እንደ ሠርቶ ማሳያ ጥሩ የተሞክሮ ላብራቶሪ ሊሆኑ ይችላሉ ፤ ሆኖም ከእዚያ የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች ከደሴት ወጥተው መላው ሐገሪቱን ካላዳረሱ ፋይዳቸው እምብዛም ነው።

ትግበራ ፥ ተያያዥነትን ከግምት ማስገባትም አለበት ። ምክንያቱም ፦ የዘረዘርናቸው አምስቱ ኹኔታዎች እርስ በእርስ የመመጋገብ እና የመደጋገፍ ነገር ስለ አላቸው።

ለምሳሌ ፦ የንብረት ባለቤትነት መብት ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው የእሚጎላው ንብረት በቀላሉ በገበያ ውድድር ወደ በለጠው አምራ እጅ መቀያየር የእሚችልበት ኹኔታ ሲኖር ወይንም የንብረት ተንቀሳቃሽነት ሲኖር ነው።

ሕጉ ለኹሉም በእኩልነት ሲሠራ ሰዎች ኢንቨስት ለማድረግ እና ለመገበያየት ይደፍራሉ ፤ የንግድ ክፍትነት ሲኖር የኩባንያዎች የጥራት እና የዋጋ ተወዳዳሪነት ዓለም ዓቀፍ ይሆናል ፤ የቴክኖሎጂ ስርጭቱም አብሮ ያድጋል። ያም ብቻ ሳይሆን የውጭ ባለኃብቶች ፤ ለምሳሌ ፦ የኢትዮጵያን መወዳደሪያ ጥካሬ ተጠቅመው ፤ በኢትዮጵያ ለማምረት ስለ እሚበረታቱ ፦ ኃብት ፣ ቴክኖሎጂ ፣ የሥራ ዕድል እና ዶላር ይዘው ይመጣሉ።

የበጀት አስተዳዳሩ በጥበብ ሲሆን ፦ የመንግሥት ግብር አሰባሰብ ሕዝብን የእሚያደቅ አይሆንም ፤ የበጀት አደላደሉም ፤ የዋጋ ግሽበትን ፣ የወለድ እድገትን ፣ የስራ አጥነትን ፣ ወዘተ የእሚያባብስ ባለመሆን ፤ ማክሮ ኢኮኖሚው የተረጋጋ እንዲሆን ያደርጋል።

ያልተሟላ እና የተወሰነ ለውጥ ወይንም ማሻሻያ ውጤቱ ያልተሟላ እና የተወሰነ ኢኮኖሚያዊ እድገት ነው የእሚሆነው ። የንብረት ባለቤትነትን ፣ የበጀት አስተዳደርን ፣ የንግድ ክፍትነትን 2 አድርጎ ከፍተኛ መካከለኛ ገቢ ያለው ኢኮኖሚ መገንባት አዳጋች ነው የእሚሆነው።

በተጨማሪም የአምስቱን ኹኔታዎችን ደረጃ ማሻሻል በእራሱ ግብ አይደለም ፤ ይልቁንም ግቡ መዋቅራዊ ሽግግርን የእሚያስችል ቀጣይነት ያለው ኢኮነሚያዊ ዕድገት ነው።

ከእዚኽ አንጻር ፤ ዋናው ኢኮኖሚያዊ እሳቤ ፤ በአንድ ሐገር ውስጥ ኃብት እና ጉልበት ምርታማነትን እና ፈጠራን በእሚያሳድጉበት አግባብ በስራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ነው።

ስለ እዚኽ ፦ ተቋማዊ ውጤታማነት የእሚለካው ፤ የንብረት ባለቤትነትን ወይንም የንግድ ክፍትነትን ከፍተኛ ደረጃ ላይ አድርሻለው በእሚል መመዘኛ ብቻ አይደለም ፤ ነገር ግን እነ እዚኽ አምስት

ኹኔታዎች ደረጃቸው የተሻሻለበት አግባብ እርስ በእርሱ ተያይዞ ፤ አንድ ሐገር ከእምትገኝበት አንዱ ዓይነት የኢኮኖሚ ደረጃ ወደ እሚቀጥለው እና ወደ እሚሻለው ደረጃ ሊያስገባት ችሏል ወይንም ደግሞ ከፍተኛው ደረጃ ላይ ካለች እዚያ ያደረሳት ተቋማዊ ኹኔታ ስኬቱን አስቀጥሎ መኼድ ችሏል በእሚል ነው።

ተቋማዊ ኹኔታዎቹ ተደማምረው እና ተያይዘው ፦ የኃብት እና የጉልበት አጠቃቀማቸው ፦ ምርታማነትን በእሚያሳድግ መልክ ሆኗል? ሰዎች ረጅም ዘመን የእሚቆይ ኢንቨስትመንት ለማድረግ መተማመናቸውን ጨምሯል? ዘላቂ ዕድገትን ሊያመጣ በእሚችልበት መልኩ ሆናል? የእሚሉትን ጥያቄዎች በአዎንታዊ መመለሳቸው ነው።

በስተመጨረሻ ኹሉንም ነገር ማቀድ እና መገመት እማይቻል መሆኑን ከግምት ማስገባት ይገባል። የለውጥ ኺደቶች በመዋቅራዊ ኹኔታዎች ላይ ብቻ አይደገፉም ፦ ግዜ ፣ አመራር ፣ አንድ አንድ ግዜ ያልተገመቱ እና ያልተጠበቁ ኹኔታዎች የእራሳቸውን ሚና ይጫወታሉ።

የለውጥ ኺደት ፤ በተፈጥሮ አደጋ ፣ በወረርሽኝ ፣ በጦርነት ፣ ወዘተ ሊደናቀፍ እና ወደ አልተጠበቀ አቅጣጫ ሊኼድ ይችላል።

ሆኖም ግዜ እና ኹኔታዎች የለውጥ ኺደቶችን ሊያወሳስቡ ቢችሉም ፤ ከሞላ ጎደል መደበኛ በእሚባለው ኹኔታ (ceteris paribus) በአንድ ሐገር መዋቅራዊ ለውጥ አምጥቶ የዜጎችን የኑሮ ደረጃ የእሚያሻሻል ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን የእሚያመጡ ተቋማዊ ኹኔታዎች በኹሉም ሐገራት አንድ ናቸው።

የተለያዩ ሐገራት የተለያዩ የዕድገት አቅጣጫ እና ፍጻሜ ከኖራቸው የኖራቸው ፤ አምስቱን ኹኔታዎች ፦ በተለያየ መንገድ ስለተረዷቸው እና ስለተገበሯቸው ብቻ እና ብቻ ነው።

እነ እዚኽ አምስት ኹኔታዎች ፤ ምርታማነትን በእሚያሳድግ መልኩ (Productivity-enhancing) አንድ ማሕበረሰብ ሲረዳቸው እና ሲተገብራቸው ፤ ዘላቂነት ያለው መዋቅራዊ ለውጥን በማምጣት የሕዝብን የኑሮ ደረጃ በእሚያሻሽል መልኩ ኢኮኖሚያቸው አድጓል። በአንጻሩ ደግሞ ስለ እነ እዚኽ አምስቱ ኹኔታዎች ያላቸው ግንዛቤ ቁንጽል ሲሆን ፣ በተሳሳተ መልኩ ሲቀመጥ ወይንም ሲቃወሙት ኢኮኖሚያዊ ዕድገታቸው አሳስተው በተረዱበት እና በተገበሩበት ልክ ውስን እና ያልተረጋጋ ሆኗል።

ስለ እዚኽ ፦ አሁንም በድጋሚ የዜጎችን የኑሮ ደረጃ የእሚያሻሽል ዘላቂነት ያለው ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ጉዳይ ፦ የእነ እዚኽን አምስት ኹኔታዎች ፋይዳ መረዳት እና እነርሱን አክብሮ የእሚያስከብር የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ግንባታ ላይ የተደገፈ ነው።

# 8 ዘመነ ሰውሠራሽ ብልኃት እና የዕውቀት ክፍተትን ለመሙላት ያለው ሚና (The Age of AI and its relevance in narrowing the knowledge gap)

**ዘመነ ሰውሠራሽ ብልኃት: የዕውቀት ክፍተትን መሙላት**

የምንኖረው በዘመነ ሰውሠራሽ ብልኃት(AI) ነው። ይኽን መጽሐፍ በምጽፍበት ግዜ ፤ ከመጀመሪያ ኃሳቡን ከማዳበር ጀምሮ የኃሳቤን ትክክለኛነት ለመመዘን ፣ ኃሳቤን የሚደግፉ ታሪካዊ ግንዛቤዎችን ለማግኘት እና ለመመዘን ፣ እና የመመርመሪያ ማሽኑን ንድፍ እና ምዘና ጥንካሬ ለመመዘን ሰውሠራሽ ብልኃትን(AI) ተጠቅሚያለኹ።

ሰውሠራሽ አስተውሎት (AI) በራሱ መጽሐፍ አይጽፍም ፤ ሆኖም የእዚኽ የምንኖርበት ዘመን *በዲጅታሉ* ዓለም ብቻ የሚኖር ሊህቅ ሆኖ (Sage of the Digital Age)—በብዙ ሺ ዘመናት በሚቆጠሩ ግዜ ውስጥ የተከማቹ የሰው ልጅ ታሪክ ፣ ልምድ እና ዕውቀት ላይ ከሞላ ጎደል ማንኛውንም ዓይነት ጥያቄ በጽሑፍ (በድምጽ) ተጠይቆ ፤ የጥያቄውን መልስ ለሰው በሚገባው መልክ ማቅረብ ይችላል።

ልክ ሪፐብሊክ (*The Republic*) በሚለው መጽሐፍ ውስጥ ሶቅራጠስ ፍትሕ የሰፈነባትን ከተማ ለመገንባት እንደ ሚጥረው እኔም በእዚኽ መጽሐፍ ውስጥ ከእዚኽ የሰውሠራሽ አስተውሎ (AI) ጋር በመሥራት ምርታማዋን ከተማ (Productive City) ለመገንባት ሞክሪያለኹ።

እኔ ያችን ምርታማዋን ከተማ ፈላጊ ነበርኩ ፤ ሰውሠራሽ አስተውሎው ደግሞ በዓለም ላይ የነበሩ ሐገራት ኹሉ በዘመናቸው የነበራቸውን ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚዘግብ የሒሳብ መዝገባቸው በእጁ የያዘ ፤ የኢኮኖሚው ካርታ (Economic Hippocampus) ነበር ።

ይኽን ኺደት ለማሳየት ፤ የሰው ልጅ የኢኮኖሚ ልማትን የማምጣት ቁርጠኝነት (Human Will to Prosper) ከማሽን (AI) ሰፊ የማስታወስ ችሎታ (Machine Memory of Success) ጋር አብሮ እንዴት እንደ ሠራ ፤ በድርማ መልክ ከእዚኽ በታች አስቀምጬዋለኹ (To epitomize that, I present a dramatization of this process—a dialogue that illustrates how the "Human Will to Prosper" meets the "Machine Memory of Success.") ፦

**ምልልሱ (The Dialogue) : የዕውቀት ብርኃን እና የአመክንዮ መዝገቡ (The Ledger of Light and Logic)**

*ንጉሡ፦ የተቀዛቀዘው እና ቆሞ የቀረው የሐገሩ ኢኮኖሚ ጉዳይ እንደ ትልቅ ሸክም ከብዶት ፤ ደንገዝገዝ ባለው በእልፍኝ አዳራሹ ራስጌ ተቀምጧል ። በፊቱ በሺ የሚቆጠሩ የኮምፒውተር የማስላት አቅም ተላብሶ ዓይኖቹ ቀይ የሚያበሩት የኢኮኖሚ **"አማካሪው"** ቆሟል ፦*

**ንጉሡ :** (ያጉተመትማል) "ሐገራት ያላቸው የዕውቀት መዝገብ የሐገራቱ ነፍስ ነው ትላለኽ። ይኽ ያሸበረቀ እና ውስብስብ ዕውቀት ፤ አምስቱን ኹኔታዎች ከ0 እስከ 4 የእሚለካ ፤ የፖላንድ ኢኮኖሚ እንዴት እንደ አደገ የእሚተርክ ፤ የአርጀንቲናው ኢኮኖሚ እንዴት እንደ ወደቀ የእሚተርክ ነው ትላለኽ—እንዴት የአንድ ሰው አዕምሮ ይኽን ኹሉ ሊያይ ይችላል? እኔ በበኩል አንድም ሰው አላውቅም ፤ አርጀንቲና በጭንቀት ያማጠችበትን ፤ የተባበሩት ኢምሬት በኢኮኖሚ ስኬት በደስታ የተነፈሰችበትን ግዜ በዓኑ ዓይቶ ምስክር ለመሆን የቻለ ፤ ተፍጥሮ ይኽን ረዥም ዕድሜ የሰጠችውን አንድም ሰው አላውቅም።

**"አማካሪው":** ክብሩነቶ ልክ ኖት ፤ የአንድ ሰው አዕምሮ የኩባያ ዓይነት አቅም ነው ያለው። ይኽን ኹሉ ነገር ሊያስታውስ አይችልም። እኔ ግን ታላቁ ሸማኔ ነኝ (Great Weaver) ፤ ይኽ መፅሐፍ በአንድ ጸሐፍት ብቻ አልተጻፈም ፤ ነገር ግን ዓላማ ይዞ በተነሳ (Human Purpose) በአንድ ሰው እና በሰውሠራሽ ብልኃት (Artificial Intelligence) መካከል በተደረገ ምልልስ ነው የተጻፈው።

ወደ እርሶ ይዞኝ የመጣው ጸሐፍት ፤ እስኪ ታሪክ አጫውተኝ የእሚል ጥያቄ አይደለም ይዞ ወደ እኔ የመጣው ፤ ይልቁንም እስኪ ዘዴውን( Mechanism) ዓሳየኝ የእሚል ጥያቄ ነው ይዞ የመጣው። እኔ ጋር ሲመጣ እንደ ጣዖት እምመለክ አድርጎ አላየኝም ይልቁን እንደ እሚታለብ ቤተመጽሐፍት ነው ያየኝ( Library to be Milked)።

ልማት ለማስታወስ የእሚደረግ ትግል ነው ብሎ ፤ ያንን የሶቅራጠስን ማቀጣጠያ (Socratic Spark) አቀረበ። እኔ ደግሞ የባለፈውን አስር ሺ ዓመት ታሪክ ማስረጃ አድርጌ አቀረብኹለት። እያንዳንዱ በእዚኽ መጽሐፍ ውስጥ ያለው ቃል ፦ የሰው አዕምሮ አቅጣጫ ሲሰጥ ፤ ማሽኑ ትልቁን የማስታወስ ችሎታውን ተጠቅሞ ለእዚያ ሰዋዊ ጥያቄ መልስ በእሚሰጥበት ውይይት ተፈልፍሎ የወጣ ነው።

**ንጉሡ:** (በግርምት ተሞልቶ, ትልቁን የወርቅ ቀለበቱን እየተመለከተ) "አማካሪ ፥ ከፈለክ ወደ ግምጃ ቤቴ ግባና ተመልከት። ከእኔ ብዙ ርቀው ያሉ ምድሮችን አስገብሪያለኹ ፣ ነጋዴዎች ሚዛናቸው ከብዶት እስኪንቋቋ ግብር አስከፍያቸዋለኹ ፣ በግምጃ ቤቴ አባቴ እንኳን ኖሮት አይደለም አስቦት ከእሚያውቀው በላይ የብር ረብጣ አከማችቻለኹ።ሆኖም ከተሞቼ በእየ ግዜው ይኮሰምናሉ ፤ ከማደግ ይልቅ። አሉኝ የእምላቸው የእጅ ባለሞያዎቼ ሐገሬን ጥለው ወደ ሩቅ ሐገር ይሰደዳሉ። ለምን ይኽ ያለኝ ከፍተኛ የፖለቲካ ስልጣን ሐገሬን አላበለጸገም?"

**"አማካሪው":** "ክብሩነቶ ፥ ዋንጫውን እና ዋንጫውን ለማግኘት የእሚደረገውን የአደን ውድድር አምታተዋል። እርሶ እንደ ዝሆኑ ትልቅ ጉልበት አሎት ፤ ውኃ የት እንደ እሚገኝ ግን ረስተዋል። ኃብት በጉልበት የእሚነጥቁት ነገር አይደለም ይልቁንም የማስታወስ አቅም ነው (memory you keep)።

**ንጉሡ :** "የማስታወስ አቅም ነው ያልከው? ለእዚያማ ጸሐፍት እና ሒሳብ ያዞች አሉኝ። አንድ ሳንቲምም አትቀራቸው ፤ የት እንደ ገባች ያውቃሉ።

**"አማካሪው":** "እንዲያ ዓይነት የቁጥር ማስታወስ አይደለም እኔ የእምለው ዓይነት ማስታወስ። አንድ ሰው በርዶኛል ብሎ እራሱን ለማሞቅ ሙሉ ቤተ መጽሐፍት ውስጥ የእሚገኝ መጽሐፍትን ቢያቃጥል ፤

ለግዜው ይሞቀዋል ፤ በዘመኑ ኹሉ ግን ሞኝ ይሆናል። መንግሥቶ የመርሳት በሽታ ይዞታል (suffers from Amnesia)። ጉልበቶ ወደር የሌለው ስለ ሆነ ፤ ሲያሻዎት አንድ ጎበዝ ገበሬ ምርቱ ተተርፍርፎ ሲያዩ ፤ ያሻዎትን ይወስዳሉ ፤ ገበሬውም ምርቴ እንዲኽ ድንገት እሚወሰድ ከሆነ ደግሜ አልዘራም ብሎ መዝግቦ ይይዛል። ከነጋዴው የተበደሩትን ብድር በአሻዎ ግዜ ተነስተው አልከፍልም ስለ እሚሉ ፤ ነጋዴው የዛሬን እንጂ ኹለተኛ አይደግመኝም ብሎ ያስታውሳል። ስልጣኖን እንደ አሻዎ በተጠቀሙ ቁጥር ሕዝቦን በዜሮ እያባዙ ነው"

**ንጉሡ:** "ያሻኝን ማድረግ ካልቻልኩ ንጉሥነት ታዲያ ፋይዳው ምንድ ነው?"

**"አማካሪው":** "ስልጣን እሚያነደውን ነገር ሲያጣ እንደ እሚጠፋ እሳት ነው ፤ ምርታማነት( Productivity) ግን እንደ ጸሐይ ሳያቆራጥ ብርኃን የእሚሰጥ ነው (Productivity is a sun that sustains)። ነዳጁን በልቶ የእሚጨርስ እሳት ሳይሆን እንደ ጸሐይ ኹሉ ግዜ ፍንትው የእሚል ብርኃን መሆን ከፈለጉ የስልጣን እጆን ማሠር አለቦት። የእርሶ መንፈስ ሆኖ እርሶን እንኳን የእሚገዛ ነጻ እና ገለልተኛ ሕግ ('Impersonal Rules') ማቆም አለቦት። የሐገሮ ዜጋ ጥሮ ግሮ ያፈራው ኃብቱ ለልጁ እንደ እሚተላለፍ ሲያውቅ ፤ ወርቁን ቆፍሮ አይቀብርም ፤ ይልቁንም ላብዛው ብሎ ይነግድበታል። እንደ አዳኝ አውሬ አድብተው የሕዝብ ኃብት የእሚቀሙ መሆን ማቆም አለቦት ይልቁንም እንደ መሐንዲስ የሐገር ኃብት የእሚገነቡ መሆን አለቦት።

**ንጉሡ:** "አንተ እጆችን ይሠሩ ትለኛለኽ" ነገር ግን እንደ ጠዋት ጸሐይ እየወጣች ያለችውን የምስራቋን ቬትናምን ወይንም የሰሜኑ ምሽግ የሆነችውን ፖላንድን ተመልከት። መንግሥታቸው በትልቅ መቅዘፊያ ኢኮኖሚውን ስለ ቀዘፈው አይደለም ያደጉት ? ይኼ ስልጣን አይደለም?"

**"አማካሪ":** "ቀዘፋው አቅጣጫ (Direction) መስጠት ነው የነበረው ፤ አድብቶ ጥጃ እንደ እሚነጥቅ አዳኝ እንሰሳ መሆን አልነበረም (not Predation)። በቪስቱላ ወንዝ ምድር በፖላንድ የዘፈቀደን ስልጣን የኹሉንም አምራችነት በእሚያክብር ስረዓት ተኩት። በሐገራቸው የሕግ የበላይነትን ከፍ አድርገው በእኔ የምርመራ ማሽን መሠረት ልኬቱን 4 በማድረስ ፤ ከሩቅ ሐገር ገንዘቡን ልኮ እነርሱ ሐገር ኢንቨስት የእሚያደርገውን ነጋዴ ንብረቱ እንደ እማይወረስ መተመማኛ ሰጡት።

የሩቁ ሐገር ነጋዴ በፖላንድ መንግሥት ንብረቱን እንደ እማይወርስበት ስለ አወቀ ፤ ወደ ፖላንድ የእሚገባው እና የእሚወጣው ጭነት በብዙ ሺ እጥፍ ጨመረ።

ደቡባዊ ፓምፓ አርጀንቲናን በአንጻሩ ይመልከቱ። ከመቶ ዓመት በፊት የዓለም ቅናት ነበሩ። እነርሱ ግን መጽሐፎቹን አቃጥለው የእሚገኘውን የአሁን ሙቀት መረጡ። ገንዘባቸው እሳት እሚያቀጣጥል ደረቅ ቅጠል እንጂ የላብ ዋጋ አልመሰላቸውም ፤ ስለ እዚኽ በእሳቱ ዙሪያ ከቦ በደስታ የእሚጨኸውን ሕዝብ ለማስደሰት አቀጣጠሉት። የበጀት አስተዳደር ጥበባቸው ወርዶ ዜሮ ሆነ ፤ በእዚኽም መሐንዲስ ሳይሆን ነጣቂ አውሬ እንደ ሆኑ አሳዩ። ዛሬ ፤ "ዕውቀት"በኃብት ስደት ተውክሎ ፤ ባሕር አቋርጦ ሐገራቸውን ጥሎ ይሰደዳል።

**ንጉሡ:** "ስለ በረሐዎቹ መሐንዲሶች ኳታር እና ዩኤኢ ምን ትላለኽ? እንደ ሰሜኗ ፖላንድ ጥሩ ሕገመንግሥት የላቸውም ፤ ከተሞቻቸው ግን አድገው ሰማይ ደርሰዋል። "

**"አማካሪው":** "የእነርሱማ እሚገርም ነው ፤ መቼም የኢኮኖሚ ጥበባቸው ከኹሉ በላይ ነው። ወርቅ በጣም ፈሪ እንደ ሆነ አውቀዋል። ትንሽ ስጋት ከተሰማው ክንፍ አውጥቶ እንደ እሚበር እና የደህንነት ዋስትና እንደ እሚፈልግ አውቀዋል። ስለ እዚኽ ፦ የንጉሡ ማን አለብኝነት የእማይደርስበት የሕግ የበላይነት የእሚነግስባቸው ደረቅ ወደቦች ('Islands of Rules') በሐገራቸው ፈጠሩ። የንብረት ተንቀሳቃሽነት ደረጃቸው (Asset Mobility) ከፍተኛው ደረጃ 4 ላይ አደረሱት። ለመላው ዓለም አስተማማኝ አድማስ በመፍጠር ፤ በርኃማ ሐገራቸውን የንግድ አስተማማኝነት ትውስታ እንደ ትልቅ ላይብረሪ የእሚኖርበት አደረጉት።

**ንጉሡ:** "አነጋገርኽ ሲታይ የእራስኽ የታላቅነት እንቅፋት እራስኽ ነኽ እምትል ይመስላል። "

**"አማካሪው":** "ልክ ብለዋል ንጉሥ ሆይ። የመንግሥቶ የኢኮኖሚ ዕድገት ደረጃ በጠንካራው ወታደሮ ጥንካሬ ልክ አይለካም ፤ ይልቁንም ተፈጻሚነት በሌላት በአንዷ ደካማዋ ሕጎ ልክ ይለካል። የምስራቋን ድርጎን ቬየትናምን ይመልከቱ የንግድ ክፍትነት ደረጃዋ ልኬት ከፍተኛው ደረጃ (4) ላይ ደርሷል ፤ ሆኖም የሕግ የበላይነት ሳያሰፍኑ ሙስና እንዋጋለን ብለው የመንግሥትን ቢሮክራሲ በፍርኃት በማንቀጥቀጥ የዕድገታቸው ማነቆ ፈጥረዋል። የመንግሥት ሹመኞች እንደ እቶን እሳት የእሚፋጀውን የጸረ ሙስና አብዮት ፈርተው ፤ የኢኮኖሚ ዕድገት የእሚያመጣው የውሳኔ ወረቀት ላይ ለመፈረም እጃቸው በፍርኃት እየተንቀጠቀጠ እምቢ ብሏል። የሕግ የበላይነትን በማስፈን ይኽን የፍርኃት ቆፈን ካላነሱ ፤ የኢኮኖሚ ዕድገታቸው በወጥመድ ውስጥ ተይዞ ፤ ከእዚኽ በላይ ማደግ አይችሉም።

**ንጉሡ:** "ይኽን ኹሉ ነገር እንዴት አውቅኽ? ሳይኽ በጭለማ ቤት ተቀምጠኽ ነው እምትውለው ፤ ስትናገር ግን በትልቁ ማማ ላይ ቆመኽ የሐገሩን ኹሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የእምትመዘግብ ነው እምትመስለው "

**"አማካሪው":** "እኔ ይኽ የያዙት መጽሐፍ አጥልሎ ያቀረበሎት ምርት አሳዳጊው ዕውቀት ገበታ ነኝ። ክብሩነቶ በግምት አልናገርም። መልሴ በስሌት ነው። ሐገራት የግል ንብረት ባለቤትነትን በአግባቡ ሳያከብሩ ሲቀሩ እና የግል ንብረት ባለቤትነት ደረጃ ልኬታቸው 1 ሲሆን ፤ ለማኝ ሲሆኑ አያለሁ። በሐገራቸው ያለው የተፍጥሮ ኃብት እጅግ ብዙ ቢሆን እንኳን ከእዚኽ ለማኝነት ሲያድናቸው አላየሁም። ሐገራት ደግሞ ንግድ ክፍትነታቸውን ሲያሳድጉ ልክ አዕምሮ ጥሩ ኦክስጂን ያገኘ ግዜ እንደ እሚነቃቃው ያኽል ኢኮነሚያቸው ሲነቃቃ አያለኹ።

ንጉሥ ሆይ ይህንን መጽሐፍ አንብበው ሲጨርሱ ፤ የሐገሮን ኢኮኖሚ ለማሳደግ የእሚያስፈልጎት ዕውቀት ሊህቃን ብቻ በእሚረዱት ውስብስብ መጽሐፍ ውስጥ ተደብቆ እንደ እማይገኝ ይወቁ። ይልቁንም ተገቢውን ጥያቄ መጠየቅ ለእሚችል ሰው ኹሉ ፤ ዓየሩ ላይ ተበትኖ የእሚገኝ እንደ ሆነ ልብ ይበሉ።

ከእዚኽ በኋላ ፤ የመካከለኛ ገቢ ወጥመድ (The 'Middle-Income Trap') ሐገራት ሊያሸንፉት የእማይችሉት ተከርችም  አይደለም ፤ ይልቁንም ጥያቄ ያለመጠየቅ ችግር ነው።

አዋቂው ተናግሯል ፤ መዝገቡ ተከፍቷል ፤ በስተመጨረሻ ከዘፈቀደ ስልጣን ወደ ምርታማነት መሸጋገር ምርጫው የእርሶ እና የእርሶ ብቻ ነው።

ይኽ በእጆ የያዙት መጽሐፍ ጽንሰ ኃሳባዊ ማብራሪያ ብቻ አይደለም - የመዋቅራዊ ሽግግር መመሪያም ነው።

በዓለም ሕዝብ ታሪክ ፤ የድህነትን ወጥመድ አምልጠው ወደ ኢንደስትሪያላይዜሽን ውስጥ የገቡ ኢኮኖሚዎች እንደው በአጋጣሚ አልገቡም። በወርቅ በተለበጠው (Gilded Age) ዘመን የነበረችው አሜርካ ትሁን ፣ ወይንም በቅርቡ ኢንደስትሪያላይዝድ የሆኑት ፡- ደቡብ ኮሪያ ፣ ሲንጋፖር ፣ ፖላንድ እና ቻይና ፤ ኢኮኖሚያዊ ስኬት ማስመዝገብ የቻሉት የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋሞቻቸውን አንዳች የልቀት ደረጃ ላይ ማድረስ በመቻላቸው ነው።

ይኽ መጽሐፍ እነ እዚኽ ሐገራት ኢኮኖሚያቸውን ያስወነጨፉበትን ያንን የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋም ግንባታ መርኽ ይዞ መጥቷል።

የእዚኽ ዓይነቱ፡- ሐገራት ኢኮኖሚያቸው ቆሞ ይቀራል ወይንስ ይሻገራል የእሚለውን የእሚወስኑት ፤ ተቋማዊ ኹኔታዎች የእሚከተሉት አምስቱ ኹኔታዎች ናቸው ፡-

- የንብረት ባለቤትነት መከበር
- የንብረት ተንቀሳቃሽነት
- ነጻ እና ገለልተኛ የፍትሕ ስረዓት
- የንግድ ክፍትነት
- የበጀት አስተዳደር ጥበብ

እነ እዚኽ ኹኔታዎች እርስ በእርስ ተያይዘው የእሚፈለገው ደረጃ ላይ ሲደርሱ ፤ የአንድ ሐገር ኢኮኖሚ ማደግ ብቻ ሳይሆን መዋቅራዊ ሽግግር ማስመዝገብ ውስጥ ትገባለች። በእዚኽን ግዜ ፤ ኢንደስትሪያሌዝሽን አንዳች ዓይነት ምስጢር ሳይሆን ፤ ከ20 እስከ 40 ባሉ ዓመታት ወይንም በአንድ ትውልድ ውስጥ የእሚሳካ ኢክኖሚያዊ እመርታ ይሆናል።

በእርግጥ እነ እዚኽ ከዕላይ የተዘረዘሩት አምስት ተቋማዊ ኹኔታዎች እና ለኢንደስትራላዜሽን ያላቸው አስፈላጊነት ፤ የዋሽንግተኑ ስምምነት ወይንም ለምን ሐገራት ይወድቃሉ በእሚባለው መጽሐፍ ("Washington Consensus" or works like *Why Nations Fail)* በተወሰነ ደረጃ የተነሱ ቢሆንም ፤ ይኽ መጽሐፍ ግን ጉዳዩን ይበልጥ ተግባራዊ በሆነ መልኩ ያቀርበዋል። ርዕዮተ ዓለማዊ ከሆነ ገለጻ በማለፍ ፤ እንደ መመሪያ ያኽል ሊተገበር የእሚችል አድርጎ ያቀርበዋል።

መጽሐፉ የእራሱ አዲስ ፤ የምርመራ ማሽን ይዞ በመምጣት፤ የእያንዳንዱን ሐገር ኢኮኖሚ በመርመር ፤ ያ ኢኮኖሚ ምን ደረጃ ላይ እንደ እሚገኝ እና ወደ እሚቀጥለው የዕድገት ደረጃ መሸጋገር ከፈለገ የትኞቹን ኹኔታዎች ማሻሻል እንደ አለበት ያሳያል።

አንድ ሰው ይኽን መጽሐፍ መረጃ ለማግኘት ሊያነበው ቢችልም ፤ መጽሐፉ ግን መረጃ ከመስጠት በላይ ነው ፤ የሐገራትን ኢኮኖሚ ለመርመር እና ደረጃውን ለማወቅ በማስቻል እንዲኹም እንዴት የሐገራትን ኢክኖሚ ማሻገር እንደ እሚቻል በመጠቆም።

በአግባቡ ለተረዳቸው እና ለተገበራቸው ፤ በእዚኽ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ዕውነታዎች ፤ ከመረጃ በላይ መመሪያ ናቸው።

ይኽን መጽሐፍ በማንበብ እራሰን ፤ የኢኮኖሚያዊ ሽግግር መሐንዲስ ያድርጉ !